“Religions are corona Virus of the Mind in Human history” Fact 1

The fool says in his heart, "There is God" fact 2



ይድረስ



ለእግዚአብሔር ልጆች



Created in Master PDF Editor

የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው::

የሽፋን ስዕል መግለጫ

ከግራ ወደ ቀኝ ጋሊሊዮ ጋሊሌ፣ ማሪ ኮሪ፣ ሮበርት ኦፔፐንሃመር፣ አይዛክ ኒውተን፣ ሉዊ ፓስተር፣ ስቲቨን ሃውኪንግ፣ አልበርት አንስታይን፣ ካርል ሳጋን፣ ቶማስ ኤዲሰን፣ አርስቶትል፣ ኒል ዲግሪስታይሰን፣ ሪቻርድ ዶውኪንስ እና ቻርለስ ዳርዊን::

ይህ ስዕል በክርስትና ዘንድ እጅግ የሚወደደውን ፀሎት ሀሙስ (the last supper)ን መሰረት ተደርጎ የተሳለ ነው:: በስዕሉ 12ቱ ቅዱሳን የሳይንስ ሀዋርያት በመሲሁ አልበርት አንስታይን ግብዣ ሲደረግላቸው ያሳያል:: (ስዕሉን ኢንተርኔት ላይ በአጋጣሚ ያገኘሁት ስለሆነ ማን እንደሳለው ለማወቅ አልቻልኩም)

በደራሲው ለህትመት በዝግጅት ላይ ያሉ መጽሃፍት

1) የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ገድላት፣ ድርሳናት እና ታምራት በአርዮስ እይታ
2) የፕሮቴስታንት ፈውስ፣ ትንቢትና አምልኮ በአርዮስ እይታ
3) ጉባኤ አንድ፣ ጉባኤ ሁለት - - -
4) ታላላቆቹ ቅዱሳን መፅሃፍት (The three Impostors)
5) ማህበራዊ ተቋማት 'የሰው አእምሮ ልጆች' (Social Institutions as the childrens of Human mind)
6) ዝግመተ ለውጥ ከታላቁ ፍንዳታ እስከ ታላቁ መኮማተር (Evolution: from the big bang to the big crunch)
7) ኢየሱስ ክርስቶስ ታሪክ ወይስ አፈታሪክ (Jesus Christ, History or Myth)

Created in Master PDF Editor

ማስታወሻነቱ

ይህ መጽሐፍ ለሐቀኝነት እና መልካምነት አስተሳሰብ ለታገሉ ብሎም ራሳቸውን ለእውነት እና ምክንያታዊነት ላስገዙ ማስታወሻ ይሁን። በተለይም በእንግሊዝ ዊይስት ሚኒስተር አብይ ከጀግኖቹ ኒውተን እና ዳርዊን መካከል ለዘላለም ለተኛው ሊቀ ሊቃውንት ስቴፈን ሀውኪንግ ትሁንልኝ።

መልዕክት

ይህቺን መጽሐፌን የምታነብ ወንድሜ ሆይ!! አንተም ጥበብ ካለህ እግዚአብሔር የገለፀልህን ፃፍ። በምድራችን ላይ ጥበብ እንዲበዛ፣ እውነት በመስራት ድንቁርናና ኃጢያት እንዲጠፉ፣ ለሀገራችንም ልጆች ዕውቀትና ተግሳፅ እንዲሆናቸው የጥበብህን ብርሃን አውጣው እንጂ ከእንቅብ በታች እንደሚያኖሩት መብራት አትሁን። __ ፈላስፋው ወልደ ህይወት



Created in Master PDF Editor

ማውጫ

ምስጋና 7
ማሳሰቢያ 8
መግቢያ 10
ይህ መጽሐፍ ለማን ተፃፈ? 14
ክፍል አንድ 27
ሰው ለምን ተጠራጣሪ እና ኢ-አመኝ ይሆናል? 27

1. ሀይማኖት ለመንፈሳዊት እንቅፋት ነው፡፡ 37
2. አሁን ካሉት ብዙ ሐይማኖቶች መካከል እውነተኛው የቱ ነው? 66
3. የእግዚአብሔር ዝምታ (God's Silece) 86
4. አማልዕክት ምናባዊ (Imaginary) ናቸው 88
5. የተዛባ ማስረጃ (Wrong Evidence) 94
6. Science (the magic of reality) explains almost everything 100
7. በአጽናፈ ዓለም ውስጥ የእኛ ኢምንት ቦታ 113
8. የዝግመተ ለውጥ እውነታ 115
9. የሀይማኖት አብዮተኞች ታሪክና ትምህርቶቻቸው 130
10. የክፍተት አምላክ (God of the gap) ውድቀት 135
11. አጉል ምኞትና የሀብት ብክነት 136
12. የጸሎት ዋጋ 144
13. አታላይ እና አስመሳይ የሃይማኖት መስራቾች፣ መሪዎችና ሰባኪዎች 147
14. ሀማኖቶች የሚፍጥሩት ችግር 150
15. God Is Not Great, but Christopher Hitchens 160
16. ብዛኞቹ ሳይንቲስቶች አምላክ የለሾች መሆናቸው 164
17. በቅዱሳን መፅሃፍት የተተረከው እግዚአብሔር ኢ-ሰብአዊ ነው 165
18. ሀይማኖትዊ አስተሳሰቦች አርጅተዋል 169
19. God is Dead, Now Zen is the Only Living Truth 170
20. እግዚአብሔር ቅዠት ነው (God is Delusion) 177
21. Bierf Answers to the Big Questions 180

Created in Master PDF Editor

22. The stars died so that you could be here today...183
23. የሰውን ልጅ ተፈጥሮ ያላገናዘቡ፣ ሀይል የተቀላቀለባቸውና ፍትህ የጎደላቸው ትዕዛዛትና ስብከቶች 184
24. ኢ-አማኞች ያዳበሩት ሰላማዊ የአኗኗር ዘይቤ 190
ክፍል ሁለት 197
አማኞች በእግዚአብሔር ለማመን ለሚያቀርቧቸው ምክንያቶች መልስ 197
1. የእግዚአብሔር መኖር በተለያየ መልኩ ተግልጧል 200
2. የእግዚአብሔርን መኖር ታሪክ ይመሰክራል 207
3. የሕይወትን ውስብስብነት በሳይንስ ሊገልጽ አይችልም............................210
4. የእግዚአብሔር መኖር በቅዱሳን መፅሀፍት ተገልጧል 233
5. ሰዎች የሚሰጡት ምስክርነት የእግዚአብሔር መኖር ያረጋግጣል 265
6. ያልተጠበቁ ክስተቶች እና ተአምራት የእግዚአብሔር መኖር ያረጋግጣሉ 269
7. ግብረ-ገብነት የሚመነጨው ከእግዚአብሔር ነው እናም ግብረግብነት ስላለ እግዚአብሔር አለ 272
8. አምላክ ባይኖር ኖሮ በአምላክ ማመን ባልተስፋፋ ነበር 289
9. እግዚአብሔር በመኖሩ ለጸሎት መልስ ይሰጣል 293
10. ከአምላክ ጋር ግልአዊ ግንኙነት እንዳለኝ ይሰማኛል 301
11. በእግዚአብሔር ማመን የተሻለ ነው፤የእኔ ማመንም ማንንም አይጎዳም305
12. የእግዚአብሔርን ባህሪ መተንተን አንችልም 310
13. አምላክ ላለመኖሩ ማስረጃ የለም 312
14. እግዚአብሔር ከለለ ሁሉም ነገር ከየት መጣ?.......................................313
15. እግዚአብሔር ረድቶኛል፣ ፈውሶኛል፣ አድኖኛል፣ ጠብቆኛል፣ ጸሎቴን ሰምቶኛል ወ.ዘ.ተ 317
16. እግዚአብሔር ፍቅር ነው..328
17. ሳይንስና ፍልስፍና አምላክ መኖሩን ያረጋግጣሉ....................................342
18. በአምላክ ማመን ለህይወት ትርጉም ያስገኛል ካለሱ ሕይወት ትርጉም የለሽ ይሆናል 351

Created in Master PDF Editor

19. በጣም ብዙ ቅዱሳን ሰዎች ለእግዚአብሔር እና ለሀይመኖታቸው ሞተዋል 355
20. እምነት የለሽነት ከሃይማኖት በላይ ብዙ ሰዎችን አስገድሏል፣ መጥፎና ሰይጣን አምላኪነት ነው 357
21. የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ 362
22. የእግዚአብሔር እርዳታ በሚፈልጉበት ጊዜ አማኝ ትሆናላችሁ 364
23. ብዙ ታዋቂ ሳይንቲስቶች፣ አክተሮች፣ እስፖርተኞ፣ ዶክተሮች ወ.ዘ.ተ በእግዚአብሔር ያምናሉ 367
24. ሀገር የምትመሰረተው፣ የምትጠበቀው በፈጣሪ ነው ኢትዮጵያ እንደማሳያ 369
ክፍል ሦስት፦....380
ሐዋርያው ቅዱስ አርዮስ ማን ነው? 380
የመውጫ መልዕክት 393
ምንጮች....394
አማርኛ ዋቢ መፅሐፍት....394
Bibliography and Recommended Reading....396
INTERNET REFERENCES....400

Created in Master PDF Editor

ምስጋና

በመጀመርያ ማመስገን የምፈልገው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ነው፡፡ የልጅነት ጊዜየን ከእረኝነት እና ከት/ቤት ውጭ ያሳለፍኩት በተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ነው፡፡ ዛሬም አለሽ በልቤ እንዳለ ዘማሪው በኔም ልብምአትጠፋም፡፡ ዛሬን አያድርገውና ትንሽ ሲከፋኝ እንኳ የምፅናናው ከአውደ ምህረቱ ስደርስ ነበር፡፡ በእርግጥ አላማየ አርዮስ መሆን አልነበርም በተቃራኒው ሆኖ አገኘሁት እንጅ፡፡ እናቴ! ከአንቺ ፊደል ቆጠሬአለሁ፤ ውዳሴ ማርያም አጥንቻአለሁ፤ የታምራትን፣ የድርሳናትን እና የገድላት መፅሀፍት ሲነበቡ ሰምቻአለሁ፤ቁሜ አስቀድሻአለሁ፤ በፆም በፀሎት ለመኖር ወስኘ ነበር ሁሉም እንደጤዛ በጥዋቱ ቀረ፡፡ ይህ ሁሉ ሆኖ ዛሬም ደጅሽን እንደአማኝ ሳይሆን እንደ ቱሪስት እጎበኛለሁ፡፡

አንችን ሳስብ ሁለት የተቀላቀለ ስሜት ይሰማኛል፡፡ አንድም የ1600 አመታት የኮፕቲክን ቅኝ አገዛዝ፣ የንግስት ዮዲት የጥፋት ዘመቻን፣ የግራኝ አህመድንጦርነት፣ ድርቡሾች የፈፀሙትን ቃጠሎ፣ የአልፎንሱ ሜንዴዝን አዋጅና ለዘመናት በቤተ ክርስቲያናት፣ በገዳማትና በአማኞች የደረሰውን ግፍ ሳስብ አይኔ በእንባ ይሞላል፡፡ ሁለትም በሌላኛው የታሪክ ገፅ በሲሶ መንግስትነት (ባይሆን እንኳ በጣልቃ ገብነት) የተሰሩ ስህተቶችን፣ በተደጋጋሚ የከሸፋው ሁለንተናዊ አብዮት፣ ከነባራዊ አለም ጋር ቁርኝት የሌላቸውን መፅሃፍት፣ ዛሬም ድረስ የገነነውን የማንአለብኝነት ስሜት ሳስብ በቁጭትና በብስጭት ስሜት እዋጣለሁ፡፡ ያም ሆነ ይህ ቤተ ክርስቲያን በአንቺ እንዳምን እራሴን አላስገድድም ስለአሳደግሽኝ ግን አመሰግናለሁ፡፡ በቃ ተለያየን!

በመቀጠልም መፅሀፉን በማሳታም፣ በማከፋፈል እና በማንበብ ለምትተባበሩኝ ሁሉ የከበረ ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡ ጓደኞቼ በተለይም ስጦታው እና አብርሃም የጠፋውን አርዮስ ወደ ቤቱ ለመመለስ ብዙ ደከማችሁ አመሰግናለሁ፡፡ ይልቁንም እነደማልመለስ ስታውቁት የሰጣችሁኝ ነፃነት ይደንቀኛል የምታወራዉን በመፅሀፍ ፃፈው እስከማለት ድርስ፡፡

ድጋፋችሁ ላልተለየኝ መምህራኖቼ፣ ተማሪዎቼ፣ አለቆቼ እና ሊቃውንት ለህይወት ስንቅ ምክር ስለምትለግሱኝ እና በስራየ ሁሉ ከጎኔ ስለሆናችሁ አመሰግናለሁ፡፡ በመጨረሻም በታለቁ ሰላማዊ የሳይንስ እና የምክንያታዊነት አብዮት የላቀ አስተዋፅኦ ላበረከታችሁና ለእኔም በጨለማ ውስጥ ሻማ ላበራችሁልኝ ሁሉ የዚህ መፅሀፍ ባለውለታዎች ናችሁና አመሰግናለሁ፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ አርዮስ (STAR DUST)

2012 ዓ.ም

Created in Master PDF Editor

ማሳሰቢያ

መፅሃፉ በውስጡ

መስማት የማይፈልጓቸው ድምፆች፣

ማየት የማይፈልጓቸው ምስሎች፣

መጥራት የማይፈልጓቸው ስሞች፣

መቅመስ የማይፈልጓቸው መራራ እውነቶች፣

ማሽተት የማይፈልጓቸው የናርዶስ ማዕዛዎች፣

ማስታወስ የማይፈልጓቸው ክስተቶች፣

መተንፈስ የማይፈልጓቸው ምስጢሮች፣

መተንተን የማይፈልጓቸው ታሪኮች፣

መመለስ የማይፈልጓቸው ጥያቄዎች፣

ማወቅ የማይፈልጓቸው እውቀቶች፣

መወያየት የማይፈልጓቸው አጀንዳዎች፣

እንዲሰራጭ የማይፈልጓቸው ዜናዎች፣

እና የተለያዩ ድንቅና አወዛጋቢ እይታዎችን በውስጡ ስለያዘና ምን አላባት ገለፃዎቹ ስሜት ሊጎዱ ስለሚችሉ በልበ ሙልነትን እና በትዕግስትን እንዲያነቡት እመክራለሁ:: እንጀመር!

እስኪ በሙዚቃ አዋዝተን እንጀምር:: ናቲ ማን ምን ነበር ያለው? <<እመነኝ>>:: ናቲ ማን ለፖለቲካው ስርዓት እኔ ለእምነቱ ስርዓት የምናንጎራጉረውን ዘፈን ልጋብዛችሁ:: ‘እመነኝ’ ይሰኛል::

እመነኝ……

እስኪ ና ቁጭ በል “እህ” በል አድምጠኝ የሆዴን፤

አረፍ በል ከጥላው ከዋርካው፤

ላንተ የኔ ኑሮ …. ሚዛኑ… መጠኑ… ምን ይሆን መለኪያው?

እስኪ ና ዝቅ በል <u>ውረድ ወደ መሬት</u> አይተኽ ብትረዳው

Created in Master PDF Editor

ዐይንህ ቢመለከት የኛን ኑሮ የኛን ሕይወት እ…

የናንተ ቁም ነገር የናንተ ክርክር ጥማድ ለኔ አይገዛ አያድስም ሞፈር፤

ሚታይ ሚናፈሰው በየሞገዱ ላይ ቅንጣት ደስታን እንጂ የኛን ችግር አያይ

እመነኝ …..

እስኪ ና ዝቅ በል ግልጽ እንነጋገር የእውነት፣

በል እንወቃቀስ ስለፍቅር

ስንት አለ በሆዴ "እህ" ብዬ ፍርዱን ለርሱ ትቼ ያለፍኩት… ሳልናገር…

(ምንጭ፦ እመነኝ ከናቲ ማን የመጀመሪያዬ አልበም፣2010ዓ.ም)

Created in Master PDF Editor

መግቢያ

ሶሾሎጅስቶች በተለይም የሶሾሎጅ አባት የሚባለው ኮሜት (Auguste Comte) ታሪክን ከሶስት ይከፍለዋል:: የመጀመርያውን ክፍል የስነ መለኮት ጊዜ (theological stage) ሲሆን ትኩረቱ ሁሉንም ክስተት በአማልዕክት እንደሚፈፀም የሚታመንበት ዘመን ነው፣ ሁለተኛው የሜታፍዚክስ (metaphysical stage) ዘመን ሲሆን ከመለኮታዊ አስተሳሰብ ወደ ተፈጥሮአዊ አስተሳሰብ የተደረገ ሽግግር ነው:: ይህን ዘመን የተሃድሶ ዘመን (Age of Enlightenment) ይሉታል:: ሶስተኛው ዘመን የሳይንስ ዘመን (scientific stage) ሲሆን ተፈጥሮን ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ ክስተቶችን (ሀይማኖትን ጨምሮ) በሳይንሳዊ መንገድ መተንተን ይችላል የሚል አስተሳሰብ የነገሰበት ወቅት ነው:: የኔም ትኩረት ይህ ነው ሀይማኖት እንደማንኛውም **ማህበራዊ ተቋም** (Social Institution) መቆጠር እንዳለበት ማሳወቅ:: የሶሾሎጅ ተማሪ እንደመሆኔም በሃይማኖት ጉዳይ ምልከታየን ማካፈል ግዴታየ እንጅ መብቴ ብቻ አይደለም:: ይልቅም ከሌሎቹ ማህበራዊ ተቋማት በበለጠ የስነ-መለኮት ተማሪነቴ በጉዳዩ ዙርያ ትኩረት እንዳደርግ ያስገድደኛል:: ከልምድ አንጻርም በዚህች ምድር ከማቱሳላ እድሜ በላይ በመኖሬ በሀይማኖቶች አመሰራረት፣ ለውጥና ወቅታዊ ኩነቶች ማስረጃዎች አሉኝ::

እምነት ከሰው ልጅ ስልጣኔ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ በመሆኑ ብዙ ሀሳቦች ሲሰነዘርና ሲሰነዘርበት፣ ብዙ ክርክሮችና ምርምሮች ሲደርጉበት የኖረና ያለ ነው:: ሀይማኖት እንዴት ተፈጠረ፣ በማን ተፈጠረ፣ ለምን ተፈጠረ፣ መቸ ተፈጠረ፣ እንዴት ለዚህ በቃ እና በሰዎች ላይ ስለሚያሳድረው በጎና መጥፎ ተጽዕኖ ብዙ ነገር ተብሏል:: ሀይማኖትን በዘርፉ ልምድ ካላቸው ሰባኪዎችና የስነ-መለኮት ተመራማሪዎች በተጨማሪ ፈልስፋው፣ ሳይንቲስቱ፣ የስነ-ልቦና ባለሙያው፣ የማህበረሰብ አጥኚው፣ ጋዜጠኛው፣ የተማረውና ያልተማረው በገባው መጠን ይተነትነዋል:: ሀይማኖት መስራቹ፣ አማኙና ታማኙ ሰው ስለሆነ ከሰው ውጭ ትርጉም የለውም:: ሀይማኖት በሰዎች ስለሰዎች የተዘጋጀ የህይወትን መቋጫ የሌለው ጥያቄ ለመመለስ የሚታትር አንድ የፍልስፍና ዘርፍ ነው::

ሀይማኖት በሰው ልጆች ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ እኮኖሚያዊ እና ስነ ልቦናው ህይወት ውስጥ ትልቅ ተፅዕኖ አለው:: ተፅዕኖ መልካምም መጥፎም ነው:: ወርቁ ፈቀደ “Religion and Its Impact upon the Realization of Human Actual and Potential Capacities” ሲል ባጠናው ጥናት የሚከተለውን ግሩም መደምደሚያ አስቀምጧል:: “Ever since the rise of men, religion has contributed to the development of morality, social organizations, laws and ethical principles. However, such contribution of religion was made by suppressing human

freedom and rationality." ብዙ ፅሀፍት እና ሚድያዎች የሚያተኩሩት መልካም አስተዋፅኦው ላይ ብቻና ብቻ ነው። በእርግጥ ያለፈን ጠባሳ መቁጠር ሌላ ጠባሳ መፍጠር ስለሆነ ልክ ናቸው። እምነት የሁሉ መፍትሔ ነው፤ **ኢ-አማኝነት የጥፋት ድምፅ ነው፤**በሀይማኖት ስም አንዳች ችግር አልተፈጠረም ሌላም ሌላም የለለ ሙገሳና ውዳሴለአማክክቶቻቸው የሚያቀርቡ ግን ከስህተቶቻቸንን እንዳንማር እየከለከሉን እንደሆነ ይሰማኛል። በተለይ የአለም አብያተ ክርስቲያናት ከበዝባዥ ነገስታት ጋር እጅና ጓንት በመሆን በጭቁኑ ገባር ህዝብ ያደረሱትን ታሪክ አይረሳውም። ይህ ሁኖ እያለበየሞገዱ ላይ በኢ-አማኝነት ዙርያ በምሰማው አሉባልታ ወሬ ሰዎች ማንነታቸውን እንዳይፈትሹና እንዳይመራመሩ ስለሚከለክል ይህን አይቶ ዝም ማለፍ ስላልቻልና በተለይም ሀይማኖትን አንግሶ ሳይንስና ፍልስፍናን ጥላሸት ለመቀባት የሚደረገው ጥረት የሚያስተዛዝብ በመሆኑ ልሞግት ተነስቻለሁ።(በዘመነ እይታ የሚሞግተኝም ካለ ዝግጁ ነኝ። እንዲከፈለኝ የምፈልገው መናፍቅ የሚለውን ስም ብቻ ነው። እኔ አርዮስ የሰኞ ምንፍቅና ለማክሰኞ ጥርጣሬ ለረብዕ እውነት መሆኑን አውቃለሁ)።

ሀይማኖቶች አንድ የሚሆኑበት ብቸኛ አቋም ቢኖር ኢ-አማኞችን ማጥላላት ነው። በስብከቶቻችን ሳይቀር እገሌ የተባለው ቅዱስ በዚህና በዚያ የነበሩትን አረመኔዎች አጥምቆ ክርስቲያን አደረጋቸው ነው የሚባለው። what? በዚህ መፅሃፍ ግን ኢ-አማኝ ማለት ምን ማለት እንደሆነና አረመኔው ማን እንደሆን እንፈትሻለን። እውነቱን ተናግረን የሚቀረው ቢቀርስ።የጠላቴ ጠላት ወዳጅ የሚሉት ነገር የሆነባቸው የሀይማኖት አባቶች በእየ አትሮንሳቸው የሚሰብኩትን ትምህርት በኋላ ኪሳቸው አስቀምጠው በአንድነት ኢ-አማኝነትን ያወግዛሉ፣ የማያውቁትን ይተነትናሉ፣ ያልተጻፈ ያነባሉ። በእርግጥ ሀይማኖቶች እርስ በእርሳቸው ያለውን ከማመንና ካለማመን የማይተናነስ ልዩነት ሆድ ይፍጀው ብለው እጃቸውን በኢ-አማኞች ላይ የሚቀስሩት በሀይማኖቶች መካከል መቻቻል እና መከባበር እንዲኖር ፈልገው ይመስለኛል። እኔም በዚህ መፅሀፍ የማተኩረው ሀይመኖቶች በድብብቆሽ ከመቻቻል እና ከመከባበር አልፈው በእውነት እንዲዋሀዱ ነው።ሳንደማመጥና ሳንስማማ መዋሃድ ስለማንችል የውህደቱ መጀመርያ ከመሰርቱ እግዚአብሄር አለን ከሚለው ይጀምራል። ስለ ነገረ ድህነትና ስለ ስርዓተ አምልኮ ከመተንተናችን በፊት ይህን ጥያቄ መመለስ አለብን። አለ ካልን ለአንድ ለሁሉም በቂ እና አሳማኝ ለሆነ ፈጣሪ እንገዛለን።የለም ከሆነ በሀሳብ ልዕልና የሚመራ እና የራሱን እድል በራሱ የሚወስን ማህበረሰብ እንፈጠራለን። እኔ አርዮስ የሁለተኛው ሃሳብ ደጋፊ ነኝ እናንተ የመጀመርያው አቀንቃኝ ከሆናችሁ ኑ እንወያይ እና ያሸነፈው ሀሳብ ይገዛን ለማለት ይህን ደብዳቤ ጻፍኩላችሁ።

Created in Master PDF Editor

ወዳጆች እኔ እንደነመ/ር ዘበነ፣ መ/ር ሮዳስ፣ መ/ር ግርማ ወንድሙ፣ ዲ/ን ዳንኤል ክብረት፣ እህተ ማርያም፣ ሐዋርያ ዘላለም ጌታቸው፣ ሐዋርያ ይዲድያ ጳውሎስ፣ ነብይ መስፍን፣ ነብይት ብርቱካን ጣሰው፣ ነብይ ታምራት፣ ሐዋርያ እስራኤል ዴንሳ፣ የቴሌቪዥን ስርጭትና የሚድያ ቁጥጥር የለኝም። የተነባቢ መጽሄቶች፣ ጋዜጦችና ድህረ ገጾች አምደኛም አይደለሁም። (ምን አልባት ወደ ፊት)? መደበኛ ስራየም ከስብክት ጋር የተያያዘ አይደለም፣ ነገር ግን ያለኝን ቅሬታና ሙግት በደብዳቤ እላካለሁ። ይድረስ ለእግዚአብሔር ልጆች! <u>ሙግቱ ቅንጭላት በሚያዞር የማይክራፎን ድምፅ የታጀበ ሳይሆን አጃይብ በሚያሰኙ ታሪኮችና ፍልስፍናዎች የተቀመመ ነው።</u>

በዚህ የጦፈና የጦዘ ክርክር በሚደረግበት ርዕስ ብዙ በልበ ሙሉነት የሚታለፉ ንግግሮች እንደሚኖሩ እሙን ነው። ኢ-አማኙ ደረጀ ፀጋዬ ምን ነበር ያለው *"ምንም እንኳን የክርክሩ ዙር ቢከርም እኛም የእለት ጉርሳችንን ለማሸነፍ ከምንባዝንበት ውሎ ስንመለስ ከቤተሰብ የጨዋታ ሰዓት ላይ በምንቀነጫጭባት ጥቂት ጊዜ የሞነጫጨርናትን ጀባ እንላለን።"* (የኢ-አማኒው ኑዛዜ)

በቃላት አጠቃቀሜ ስሜታዊነት ሊሰማቸው ለሚችሉ አንባቢዎች አስቀድሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ። (ትንሽ የደፈርኳችሁ ስለመሰለኝ ነው)። ለነገሩ "ድፍረት የሌላት ብዕር ወረቀት ባታበላሽ ይመረጣል፣ ከአድር ባይ ብዕር ባዶ ወረቀት ብዙ ይናገራል" ነበር ያለው በዓሉ ግርማ። የእኔ የሀሳብ ልዩነት ሀይማኖትን እንደ ማህበራዊ ክስተት ስለምመለከተው መወቀስ ባለበት መወቀስ መመስገን ባለበት መመስገን ይገባዋል ባይ በመሆኔ ነው። የምናውቀው ሰባኪወቻችን መርጠው ያሰተመሩንን መልካም ጥቅሶች እና ስኬቶች ስለሆነ ከእውነታው ብዙ የራቅን ይመስለኛል።

ነገር ግን መልካሙን ብቻ እያነሱ ጥፋቱን መደበቅ አይዞህ አጠፋ እንደማለት ነው። አራቱ ሀያላን ሀይማኖት፣ ፖለቲካ፣ ሳይንስ እና ፍልስፍና የሰው ልጅ ጥበብ ውጤቶች ስለሆኑ መታረም ፣ መተቸት እና መሻሻል አለባቸው። በተለይ በሃይማኖት ላይ <u>ተሃድሶ</u> መደረግ አለበት። ደስ የሚለው አንዳንዶቹ ሀይማኖቶች ዘመኑን ዋጅተውታል። ነገር ግን ብዙዎቹ ቤተ እምነቶች በሲወርድ ሲዋረድ አስተሳሰብ ላይ ናቸው። ተሃድሶ ለሌሎች ተቋማት በተለይም ለፖለቲካ ፓርቲዎች እንጅ ተሃድሶ በሀይማኖት የሚደረግ አይደለም ምክንያቱም መንፈሳዊው አለም መመሪያው የእግዚአብሄር ቃል መሪው መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ነው ማለታቸውን ቀጥለዋል። ግን ግን የእግዚአብሄር ቃልስ ቢሆን መመርመር የለበትም?

ውድ አንባቢያን በአብዛኛው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምዕራፎች ገለልተኛ ናቸው። ብትችሉ ከመጀመርያ ጀምራችሁ አንቡት ከፈለጋችሁም ከመጨረሻው ጀምሩ ወይም ደስ ካላችሁ ምዕራፍ ጀምሩ። እምለምናችሁ ቢኖር እነደጀመራችሁ ጨርሱት እና ገለልተኛ ሁናችሁ አስቡት። የስነ ጹህፍና የሰዋሰው አጠቃቀሜን በሚቀጥሉት

Created in Master PDF Editor

እትሞች አስተካክላለሁ፣ እንደምታግዙኝም ተስፋ አለኝ። ያነሳሁት ርዕስ አስፈላጊና ለውይይት የሚጋብዝ ነው ብየ አስባለሁ። ከሃሳቡ ስፋት አንጻር በአንድ ጥራዝ መፅሃፉ ማዘጋጀት ተገቢ መስሎ ስላልታየኝ በተለያየ ቅፅ ለማሳተም ተገድጃለሁ። ከዚህ መፅሃፍ ቀጥሎ 1ኛ. የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ገድላት፣ ድርሳናት እና ታምራት በአርዮስ እይታ 2ኛ. የፕሮቴስታንት ፈውስ፣ ትንቢትና አምልኮ በአርዮስ እይታ፣ 3ኛ. ታላላቆቹ ቅዱሳን መፅሃፍት 4ኛ. ማህበራዊ ተቋማት 'የሰው አእምሮ ልጆች' እንዲሁም 5ኛ. ዝግመተ ለውጥ ከታላቁ ፍንዳታ እስከ ታላቁ መጨፍለቅ የሚሉትን መፅሃፍት ለማሳተም በዝግጅት ላይ ነኝ። በሁሉም መፅሃፍቶቸ <u>የሚነሱት ሃሳቦች ከኔ ይልቅ ከሌሎች የተመነዘሩ ስለሆነ ጹህፎቹ ወደ ጥናታዊ ጹህፍነት ያጋደሉ ይመስለኛል። መጽሀፎቹን ለማዘጋጀት በርካታ መፅሀፍትን፣ የጥናት ውጤቶችን፣ መፅሄትና ጋዜጦችን፣ ድረ ገጾች፣ ጦማሮችን፣ የቴሌቭዥንና የሬድዮ ፕሮግራሞችን፣ ፊልሞችና ዶክመንተሪዎችን፣ ግጥሞችን፣ ቀልዶችን፣ መዝሙሮችን፣ ዘፈኖችን፣ የማህበራዊ ሚድያ መጣጥፎችን ተጠቅሜያለሁ።</u> ውድ አንባቢያን በዚህ የሃሳቦች ውድድር ውስጥ ስለተቀላቀላችሁ አመሰግናለሁ። ልክ እንደ ስፖርት ውድድሮች ጭዋ እስፖርተኞች እርስ በርስ በመከባበር እንደሚወዳደሩ እኔ እና እናንተ እስከ ፍጻሜው በመወያየት ውድድሩን እንደምንጨርስ ተስፋ አደርጋለሁ።

መልካም ንባብ

Created in Master PDF Editor

ይህ መጽሐፍ ለማን ተፃፈ?

I am against religion because it teaches us to be satisfied with not understanding the world. –Richard Dawkins

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በዋናነት ለአማኞች ነው። በተጨማሪም ኢ-አማኞች፣ ያልወሰኑ ሰዎች፣ ተማሪዎች እና ተመራማሪዎችም ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

1ኛ. አማኞች፡-መጽሃፉ ለሁሉም አማኞች የተዘጋጀ ቢሆንም በተለይ ግን ቀጥሎ ለተዘረዘሩት እንዲደርስ እፈልጋለሁ።

- ፩ ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ፣ ለካቶሊክ፣ ለፕሮቴስታንትና ለሙስሊም ሊቃውንት
- ፪ ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ አጥማቂዎች እና ለፕሮቴስታንት ነብያት፣ ሀዋርያትና ቴሌቫንጋሊስቶች
- ፫ ለዲ/ን ዳንኤል ክብረት፣ መ/ር ዘበነ ለማ፣ ለመ/ር ሮዳስና ለመጋቤ ሃዲስ እሸቱ አለማየሁ
- ፬ ለንቡረ ዕድ ኤርሚያስ ከበደና ለተክለ ኪዳን
- ፭ ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ን ሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምርያ ማህበረ ቅዱሳን
- ፮ ታሪክን በተለይ የኢትዮጵያን ታሪክ <u>በመስኮት</u> ተምረው ለሚሰብኩን ሙህራን

አማኞች ሆይ እንደ አማኝ ከመፅሀፉ ሀሳቦች ከአብዛኛዎቹ ጋር አትስማሙም ይሆናል ሲጀምር ስለኢ-አማኛን አመለካከቶች እንድታውቁ እንጅ እንድትስማሙ አልጠብቅም። ይህንን መጽሐፍ ማንበቡ ኢ-አማኞች ምን እንደሚያምኑ፣እንዴት እንደሚኖሩ እና ስለ ተፈጥሮ ያላቸውን ግንዛቤ ምን እንደሚመስል እንድትመለከቱ ያስችላችኋል። እነዚህ ሰዎች የእናንተን እምነቶች እንዴት እንደሚጠራጠሩ ትረዳላችሁ። ስለእምነታችሁ ለመሟገት እቅድ ካላችሁ ይህ መጽሐፍ የተቃዋሚዎች ያለማመን ምክንያቱን በመረዳት ምክንያታዊ ክርክር እንድታደርጉ ሊረዳችሁ ይችላል። ስለ አምላክ እና ስለ ሃይማኖት በጠንካራ ማስረጃዎች ላይ የተመሰረተ ፍሬያማ ውይይት ማድረግ ትችላላችሁ።

የሂስ መፅሀፍ እንደመሆኑ እምነታችሁን እስከቻልኩት ድረስ ለመተቸት ሞክሬአለሁ ከጥቂት ሙገሳ ጋር። ለምን ወደ ትችቱ አደላህ ብትሉ ሀይማኖታችሁ በእየ ቀኑ ሳይወደስ አይዉልም የጎደለው ሊያስተካክል የሚችል ትችት ነው። መፅሀፉን አንባችሁ ልማርበት የሚችል የማስተባበያ ፅሁፍ እንደምትልኩልኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ወገኖቸ ብትችሉ ውደዱኝ ፍቅር ነው የራበኝ፣ ባትችሉ ግንሽህ ጊዜ ጻፉብኝ፣ አምራችሁ እርገሙኝ፣ አስደግሙብኝ፣ እንደሰይጣን ጥሉኝ፣ ስደቡኝ፣ መሳለቂያ አድርጉኝ ይህ ሁሉ ለኔ ፀጋ ነው። ነገር ግን ድንጋይ ለመወርወር፣ ቡጢ ለመሰንዘር፣ ለማሰር እና ለማሳደድ ለምታስቡበምታምኑት አምላክ፣ በምትወዷት ሀገር

Created in Master PDF Editor

በተለይም በወላጅ እናታችሁ ልለምናችሁ ተውኝ:: ይህን የምላችሁ ስለምፈራ ብቻ አይደለም የተለየ ሃሳብ ያላቸው ሰዎች በህዝብ ፊት ሲደበደቡ፣ ሲሰቀሉ፣ ሲዘረፉ፣ ሲታሰሩ እና ሲሳደዱ ስላየሁ ነው:: እኔም ብዙ ጊዜ <ሰው የሚያስብ ፍጡር ነው> የሚለውን እስክጠራጠር ድረስ በአሳዳጆቸ ቀለበት ውስጥ ገብቸ አውቃለሁ:: እንዳንዴ ስንተኛው ክፍለ ዘመን እንዳለን ግራ ይገባኛል:: በኦሪት ዘመን ይሆን እላለሁ:: **ስንተኛው ክፍለ ዘመን ላይ ነን እባካችሁ???**

ብዙ እቅድ አለብኝ ብዙ መመራመር፣ ብዙ መፈላሰፍ፣ ብዙ መጎብኘት፣ ብዙ ማንበብ እና መጻፍ፣ ብዙ መማር እና ማስተማር አለብኝ:: እንዴ! የአፍሪካን መዲና አዲስ አበባን፣ ውቧ ባህር ዳርን፣ ንግስቷ ጎንደርን፣ ጥንታዊቷ አክሱምን፣ ባለድሏ አድዋን፣ ድንቋ ላሊበላን፣ ሞቃቷ አፋርን፣ ጠበብቷ ሀረርን፣ ስብጥር ደቡብን፣ አርባምንጭ ሀዋሳን፣ የገዳ ስርአትን ሌሎች ሌሎችንም የማየት ህልም አለኝ:: ኢትዮጵያ እኮ የሚስጢር መፅሃፍ (መጽሃፈ ሚስጢር) ናት:: እንዴ! በማይክሮስኮፕ ህዋሳትን ሳላይ፣ በቴሌስኮፕ ህዋውን ሳላየው፣ በጥንት ግሪኮች የተተከለውን የእውቀት ዛፍ ፍሬን ሳልበላው ማለፍ አልፈልግም:: ብዙ ያላነበብኩት መፅሃፍ፣ ያላሳትምኩት ረቂቅ ጹህፍ፣ ያላጣጣምኩት ሙዚቃ፣ ያልጎበኘሁት ቦታ፣ ማየት የሚገባይ ያላየሁት አለም አለ:: ይህን ሁሉ ከምትለማማጥ ለምን አርፈህ አትቀመጥም ልትሉኝ ትችላላችሁ እኔ ግን ከአባቶቼ አልበልጥም እላችኋለሁ፣ ድግሜም ህልም ፈርቸ ሳልተኛ አላድርም እላችኋለሁ:: ለማንኛውም የሰለጠነ ሰው ይግጠምህ፣ የተማረ ይግደልህ በሉኝ::

እንደ ተወዳጁ ዲ/ን ዳንኤል ክብረት የሰለጠኑት አማኞች የእኔን መሰሎችን ሃሳብ እንደ መልካም ተግዳሮት እና ግብዐት ይጠቀሙባታል:: ያም ብቻ ሳይሆን አማኞች ልበ ሙሉ እንዲሆኑ ያስተምራሉ፣ ምሳሌ ይሆናሉ:: ዲ/ን ዳንኤል ክብረት በዕውቀቱ ስዩም 'እግር አልባ ባለ ክንፍ' ብሎ ለጻፈው 'እግር ያለው ባለ ክንፍ' ሲል የመልስ ምት በሰጠበት የዳንኤል ክብረት ዕይታዎች ከተሰኘው ድረ ገጹ እንዲህ ያስደምመናል፦*"ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍቷን በቀኖና እንድትወስን፣ ሥርዓቷን እንድትወስን፣ የሃይማኖት መግለጫዋን ወስና እንድታወጣ፣ ሕግ እና ደንብ እንድትሠራ፣ መጻሕፍትን እንድትጽፍ፣ ያደረጓት ተግዳሮቶች በየዘመናቱ መኖራቸው ነው:: ሄሊቪዲየስ ተነሥቶ በቅድስት ድንግል ማርያም ላይ የተለየ ትምህርት ባያመጣ ኖሮ አባ ጀሮም እና አባ ኤጲፋንዮስ የጻፏቸውን መጻሕፍት ባላገኘን ነበር::"*ይላል ምሳሌውን ይቀጥልና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ትልቅ ክብር የሚሰጣቸው አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ስላደረጉት ነገር ይነግረናል:: *"ቴዎድሮስ የተባለ የጦር አዛዥ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫን ስለ ሃይማኖት ባይገዳደረው ኖሮ አስደናቂውን ርቱዐ ሃይማኖት የተሰኘ መጽሐፍ ባላገኘን ነበር:: የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል እንደሚነግረንም በንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን በሃይማኖት ምክንያት ክርክር ሆነ:: አባ ጊዮርጊስም ከአንድ ፈረንጅ ጋር ተከራክሮ ረታው:: መጽሐፈ ምሥጢርንም ደረሰ::"*

Created in Master PDF Editor

ዲ/ን ዳንኤል ክብረት የምናምነውን የማያምኑ መኖራቸው እምነታችንን እንደሚያጠነክሩልን ሲግልፅ እንዲህ ይላል፦ *“መልአከ ብርሃናት አድማሱ ጀንበሬ (የሞተ ልጃቸውን በጸሎት ያስነሱ ብርቱ አማኝም ነበሩ ይባላል) ያንን የመሰለ ኮኩሐ ሃይማኖት የተሰኘ መጽሐፍ እንዲጽፉ ምክንያት የሆናቸው አባ አየለ ተክለ ሃይማኖት የሚባል ካቶሊካዊ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጻፈው ጽሑፍ ነው። እነ አስረስ የኔሰው ያንን የመሰለ ትቤ አኩስም መኑ አንተ የተሰኘ የታሪክ፣ የእምነት፣ የቅርስ እና የሥነ ልሳን መጽሐፍ የጻፉት በወቅቱ ለተነሡት የታሪክ፣ የቋንቋ እና የእምነት ተግዳሮቶች መልስ ለመስጠት ነው።”*(በቅንፉ የተጨመረውን ያገኘሁት ከካሳሁን አለሙ ተጠየቅ ድህረ ገጽ ነው)

ዲያቆን ዳንኤል ክብረት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ‘እግር አልባ ባለ ክንፍ’ ሳይሆኑ ‘ክንፍ ያለው ባለ እግር’ መሆናቸውን ለማስረዳት ታሪክን እና እምነትን መሰረት አድርጎ አብራርቶ መልሶታል፣ በአንድ ወር ደሞወዝ የሚገዛ ዳጎስ ያለ መፅሃፍም ለአቡኑ ጽፎላቸዋል። *(በነገራችን ላይ እኒህ አወዛጋቢ ቅዱስ ሰይጣንን ወንጌል ሰብከው ገርዘው ስሙን ክርስቶስ ሀረዮ በማለት ሰይመውና አመንኩሰው በዘመኑ ሁሉ መነኮሳቱን በቅንነት አገልግሎ ሲሞት መንግስተ ሰማይያት እንዳስገቡት በገድላቸው ይተርካል። ይገርማል!)* ዳንኤል ወቅታው እይታወቹን በሚዳስስበት ድህረ ገጹም የበዕውቀቱን ጥርጣሬ እንደጠቀሳቸው አባቶቹ በግብዐትነት ተጠቅሞበታል።ከዳንኤል ክብረት ጋር የማያግባቡን ብዙ ልዩነቶች ቢኖሩኝም እንደሱ የማደንቀው አማኝ ፈልጌ አጥቻለሁ። እንደ ብዞዎቹ ተቆርቋሪ ነን ባዮች ማጥላላት አይታይበትም፣ ጠላቴ ከማለት ይልቅ ወንድሜ ማለትን አስቀድሟል። ብዙዎች ግን አይነኬ ሀይማኖታቸውን በዕውቀቱ ስዩም ስለነካባቸው አይናቸው ቀልቷል፣ እስከ መደባደብም የደረሱ አሉ።እነዚህ የሂትለር ርዝራዦች ለቡጣ ቡጢ እንጅ ለውይይት ስላልታደሉ ያስፈራሉ፣ ያሳፍራሉም።

የተማሩት የተመራመሩት እነዲ/ን ዳንኤል ክብረት ግን የሰጡን የመጻፍ ነጻነት ብቻ ሳይሆን በመሃይሞች ለሚደርስብን ጥቃት ጥብቅና እስከመቆም ነው። በምንም መንገድ ይላል ዲ/ን ዳንኤል ክብረት *“በምንም መንገድ ይሁን በምንም እንደ በዕውቀቱ ያሉ ጸሐፍት የመጻፍ ነጻነታቸው መከበር አለበት። ጥያቄ ያለው ወይንም በሃሳባቸው የማይስማማ ሰው እስከ ሕግ አግባብ ድረስ በመሄድ ጤናማውን እና የሠለጠነውን መንገድ ተከትሎ መሞገት ይቻላል። አንድ ጸሐፊ በመጻፉ ምክንያት ብቻ አካላዊም፣ ሃሳባዊም ጥቃት እንዳይደርስበት የምንከላከለው በሚጽፈው ሃሳብ ስለምንስማማ ብቻ መሆን የለበትም። ለማንስማማበትም ሃሳብ ነጻነት መሟገት አለብን። ሃሳቡን እየተከራከርነውም፤ መብታችን ተደፍሯል ብለን በፍርድ ቤት እየከሰስነውም ቢሆን ለሃሳብ ነጻነቱ ግን መሟገት ግድ ይለናል።እናም በዕወቀቱ ይጻፍ፣ የማልስማማበትንም ነገር ይጻፍ፣ እኔም የምስማማበትን እይዛለሁ፣ የማልስማማበትን*

Created in Master PDF Editor

እምግታለሁ። ለበዕውቀቱ የመጻፍ ነጻነት ግን ጥብቅና እቆማሁ።” (የዳንኤል ክብረት ዕይታዎች ድህረ ገጽ)

ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ይህን ተስፋ ሰጭ ፅሁፍ በመጻፉ እኔን ጨምሮ ብዙ አድናቂዎቹ ቢደሰቱም አንዳንዶቹ የዘራፍ ዘመን አስተሳሰብ አራማጆች ግን ከበዉቀቱ ይልቅ ዳንኤል ያናደዳቸው ይመስላል። እነዚህን ሰዎች ለማስደሰት ሲል ዳንኤል በዕውቀቱን መሳደብ ነበረበት፣ መናፍቅ ምናምን ማለት ነበረበት ግን አላደረገውም ይልቅስ በዕውቀቱ ሥዩም ነገሮችን በአዲስ መልክ ከሚያዩ ጥቂት የሀገራችን ጸሐፍት አንዱ ነው ሲል አወደሰው። ገና ብዙ ሥራ የሚጠበቅበት ወጣት ጸሐፊም እና ሕይወቱን ለጽሑፍ የቀየደ ሰውም ነው በማለት የቤት ስራ ሲሰጠው ይታያል። መታደል ካመኑም ከተማሩም እንዲህ ነው። ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በርታ ተበራታ እላለሁ፣ ምን አለ ያለ ስጋት በነጻነት የምንኖርበት ዘመን በሆነልን ወይም ቢያንስ ሲናገሩ እንጅ ሲናገሯቸው የማይወዱ ባይኖሩ።

በስጋቴ ዙርያ አንድ ኤቲስት የማህበራዊ ሚድያ ጓደኛየ በሚድያው ገጽ ያሰፈረውን ላካፍላችሁ እኔም እጅግ በጣም እስማማበታለሁ።

“የምፅፈዉ እኔ የተሰማኝን እንጅ እናንተ የተሰማችሁን አይደለም። የተሰማችሁን ፅፌዉ ካገኛችሁ መልካም ነዉ። ካልፃፍኩትም አትበሳጩ። ምክንያቱም እኔ እናንተ አይደለሁም። ሰወች ይጠሉኛል ብየ የማምንበትን ነገር ከመፃፍ ወደ ኋላ አልልም። ሰወች እንዲወዱኝ ብየም የማላምንበትን ነገር አልፅፍም። ስለዚ እኔ እንድትወዱኝም ሆነ እንድትጠሉኝ ሆን ብየ የምፅፈዉ ነገር አይኖርም። እኔ የምፅፈዉ የራሴን ሀሳቦች ነዉ። ሀሳቦቸ ሁሌም ትክክል ሊሆኑ አይችሉም፣ የተሳሳተ ሀሳብ ልፅፍም እችላለሁ። እኔ ለእናንተ አስቤ አልፅፍም እናንተም ለኔ ብላችሁ አታነቡም። ስለዚ እኔም የተመቸኝን የመፃፍ እናንተም የተመቻችሁን አብባችሁ ያልተመቻችሁን የማለፍ መብት አላችሁ። የናንተና የኔ ግንኙነት የሻጭና የገዥ ግንኙነት ነዉ። ሻጩም እቃዉን የሚሸጠዉ ለገዡ አስቦ አይደለም። ገዡም እቃዉን የሚገዛዉ ለሻጩ አስቦ አይደለም። በመሀል ግን ሁለቱም ተጠቃሚ ይሆናሉ።”<ከማመን መጠራጠር ይሻላል>

በጣም የሚገርመኝ አይቶ ማለፍ፣ ማስተባበል፣ አለማንበብ፣ አለመግዛት፣ ዲሌት፣ አንፍሬንድ፣ ብሎክ እና የማሳሰሉት የማንፈልጋቸውን የመከልከያ መንገዶች እያሉን ይህ ሚድያ ይዘጋ፣ ያ መጽሀፍ ይቃጠል ወዘተ እያልን መንግስትን የምንወተውት አለን። ወገኖች እናንተ ስለ ሌላ ሰው እያወራችሁ ስለእናንተ የሚያወራውን አትከልክሉት። ከኢ-አማኒ ወደአማኒ የሚሰነዘር ማንኛውም ሃይማኖት ነክ ጉንተላ ምክንያታዊ አይደለም የምትሉ እናንተ ስለ ኢ-አማኝ በህዝብ ሚድያ ሳይቀር ስትደነፉ ቅር አይላችሁም? ተስፋ አደርጋለሁ እናንተ የሰው ስጋ ካልበላችሁ የእናንተን ስጋ የሚበላ የለም። መውገር ያለበት ንጹህ የሆነ ብቻ ነው። ማን ነው ንጽህና እውነተኛ

Created in Master PDF Editor

ማንም የለም፡፡ ቤተ ክርስቲያን በአዋጅ ደረጃ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ረቂቅ ሕገ ቤተክርስቲያን፣ አንቀጽ 3 ቁጥር 7-8 *“ቤተክርስቲያን ያሏትን ጥንታውያት መጻሕፍት እየተረጎመችና እያሳተመች ለምእመናን አገልግሎት የማዋልና የማሰራጨት እንዲሁም የጥናትና የምርምር ተቋማትን የማቋቋም መብት አላት፡፡ ቤተክርስቲያን ማሠልጠኛዎችንና መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶችን የማቋቋም፤ ለተቋቋሙትም እስከ ኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ዕውቅና የመስጠት፤ በትምህርት ቤቶቿም አማካይነት ሃይማኖቷንና ቀኖናዋን የማስተማርና የማስፋፋት፤ በየገዳማቱና በየአድባራቱ የሚገኙትን ጥንታውያን የአብነት ትምህርት ቤቶች የማጠናከርና ከየትምህርት ቤቱ ለሚመረቁ መምህራንና ደቀመዛሙርት የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት መብት አላት. . .”* እያለች ከኄ ውጭ ወደ ውጭ የምትል ከሆነና ልጆቿን አብሮ መኖርን እንዲላመዱና ልበ ሙሉ የማታደርግ ከሆነ እኛስ የት ሂደን ሀሳባችንን እናሰማ፡፡

ቀና አስተሳሰብ ያላችሁ ውድ አማኞች ክህደቴን በማሰብ እኔ ስለምቃጠልበት ሲኦል አንዳች እንዳታስቡ በወላጆቸ በኩል ከ10 ትወልድ በላይ ዋስትና ተሰጥቶኛል፡፡ ከፈለጋችሁ ከእልፍ ቅዱሳን ውስጥ ለአንዱ ቅዱስ አገልጋይ ክርስቶስ የገባለትን ቃል ኪዳን አንቡ፡፡ ለነገሩ በወላጆቸም በኩል ብቻም ሳይሆን እኔ እራሴ ከበላየ ሰብ የተሻለ በብዙ ቅዱሳን ስም እመፀውታለሁ በተለይ በድንግል ማርያም ስም፣ ገዳማት እጎበኛለሁ፣ በክበረ ብአላት ቤተ ክርስቲያን እሳለማለሁ ወዘተ፡፡ይህም እንኳ ባይሆን ቅዱሳን ሲኦልን ሲበረብሩ በክንፋቸው ተጥልየ ገነት እገባለሁ፡፡ ስለዚህ ጌታ እኔን በተመለከተ ልዩ የህግ ማስተካከያ እስካላደረገ ድረስ ከእናንተ ጋር መንግስቱን እወርሳለሁ አትጠራጠሩ፡፡ ለማንኛውም የሚያደርገውን አያውቅምና ሀዋርያው ቅዱስ አርዮስን ማረው እያላችሁ አንቡት፡፡

2ኛ. ኢ-አማኞች፡-ይህ መጽሐፍ አምላክ የለሾቹ እራሳችሁን በደንብ እንድትገልጹ ይረዳችኃል፡፡ በእርግጥ ማስረጃን ማቅረብ ያለበት ፈጣሪ አለ የሚሉት ናቸው፡፡ እግዚአብሄርን በተመለከተ አማኞች መኖሩን ማረጋገጥ ካልቻሉ ለእናንተ በቂ ነው፡፡ ግን ከዚህም አልፎ አለመኖሩን ማስረዳት ባይጠበቀባችሁም ለውይይት ሲባል ከመፅሀፋቸው እና ከተፈጠሮ እያመሳከራችሁ ላመናችሁበት እውነት ተጨማሪ ዘዴዎችን ማወቅ ይኖርባችኃል፡፡ የዚህን መፅሀፍ ክርክሮች በመረዳት እና ሌሎች እንዴት እንደሚረዱ በመመልከት ሎጂካዊ በሆነ መንገድ ውይይቶች እንድታደርጉ ሊያግዛችሁ ይችላል፡፡ከአማኞች ወይም ከሀሊናችሁ ጋር ለመከራከር በመጀመርያ እግዚአብሄር ሊኖር ይችላል ብላችሁ ተነሱ፡፡ ቀጥሎ መመራመር ይቻላል፡፡ ሲጀመር አለ ወይም የለም ብላችሁ ከዘጋችሁት ግን መመራመር፣ መፈላሰፍ አያስፈልግም፡፡

Created in Master PDF Editor

እኔ አርዮስ በዚህ መጽሐፍ የእኔና የሌሎች ኤቲስቶችን ተፈጥሮአዊ አረዳድ ለሃይማኖታዊ ክርክር በሚያስኬድ እና የሀሳብ ለውውጥን በሚያመጣ መልኩ ለመማዘጋጀት ሞክሬየለሁ፡፡ የእኔን አስተሳሰብ ወደ ለየለት ሂሰኛ ያደረሱኝይህን መሰል መፅሀፍት እና የኢንተርኔት መጣጥፎችናቸው፡፡ “The Internet is the modern-day World Book Encyclopedia. Everyone should have access to the Internet in their home, school, or public library” የሚለውን የአክቲቪስት Margaret Downey ምክር የተገበርኩት ይመስለኛል፡፡ ብዙ ደፋር ኤቲስቶች ህይወታቸውን አደጋ ላይ በመጣል ለምክንያታዊነት እየታገሉ ይገኛል፡፡ ተግሉም ህንፃ በማፈራረስ፣ በማሸበር፣ እና ነፃ አስተሳሰብን በመንፈግ አይደለም፡፡ ይልቁንስ አማኞች አይተው የሚፈሩት የእውነትን ማጅክ የሚያስረዱ መፅሀፊትን በመፃፍ እና ጹሁፎችን በእንተርኔት በማሰራጨት አንጅ፡፡ በግሌ የግሪክ ፍላስፎች፣ የአበው ሊቃውንት፣ የማርክስ፣ የፍሬድሪክ ኒቸ፣ (የአርዮስ?፣ የንስጥሮስ?፣ የሉተር?፣)የዘረዐ ያዕቆብ፣ የወልድ ህይወት፣ የዙምራ፣ (የበውቀቱ ስዩም፣ የዋለልኝ እምሩ፣ የብሩህ አለምነህ፣ የሃይለ ጊዮርጊስ ማሞ፣ የወርቁ ፈቀደ፣ የደረጀ ፀጋዬ) የኦሾ፣ የክሪስቶፈር ሂችን፣ የሳም ሃሪስ፣ የሪቻርድ ዶውኪንስ፣ የካርል ሳጋን፣ የማርሻል ብሬን፣የአያና አርሲ አሊ፣ የማይክል ሸርመር፣ የዳርዊን፣ የፍሮይድ፣ የጋሊሊዮ፣ የአንስታየን፣ የሀውክንግ ኧረ ስንቱን ሙህር ልጥራብቃ የነዚህ እና የሌሎች የሳይንስ እና የምክንያታዊነት አቀንቃኞችአደናቂ ነኝ፡፡ሞት ይርሳይ በፍቃዱ ሃይሉን ረሳሁት ምን ነበር ያለው፦ “የዓለም ሕዝቦች የቀለም እውቀት እና ከተሜነት እየተስፋፋ እና እየተመነደገ እየመጣ እንደመሆኑ መጠን፣ ከጥቂት መቶ ዓመታት በኋላ፣ አሁን ኢ-አማኒነት እብድነት እንደሆነው ሁሉ አማኒነት እብድነት መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡”

አንተ ኢ-አማኝ ከሆንክ በቻልከው መጠን የቱንም መፅሀፍ ማንም ይፃፈው መቸም ይፃፍ ያለፍርሃት አንብብ እውነትን ካገኘህበት ተቀበል ካልመሰለህ ተወዉ፡፡ ብዙ ሰወች ከራሳቸው እምነት ውጭ ማንበብ ይፈራሉ፡፡ የሚገርመው እነዚ ሰወች የራሳቸውን ቀኖና እንኳ ቁሶቹ እንዲያውቁት እንጅ እነሱ እንዲገባቸው አይፈልጉም፡፡ ከተኙበት የሰመመን እቅልፍ ለመንቃት አያስቡም፣ ቀስቃሽም አይሹም፡፡ በአጭሩ ይህን መፅሀፍ በጃቸው ከነኩት ሰይጣን የሚያዛቸው የሚመስላቸው፣በመንጋ አስተሳሰብ የሚነዱ፣ ከእዉቀት ዛፍ እንዳይበሉ የተከለከሉ፣ ለራሳቸው ሀላፊነት የማይወስዱና ከጦር ይልቅ አስተሳሰብ የሚያስፈራቸው ናቸው፡፡ ስለ እምነታቸው እንዲሁም ስለ ፍልስፍን እና ሳይንስን ላለማወቅ ራሳቸውን ከጥበብ ያወሩ ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን ህይወታቸውን በአደራ ያስቀመጡ አስከሬኖች ናቸው፡፡ አስከሬን የት እንደተነሳ፣ በዙርያው ምን እየተፈፀመ እነደሆነ እና የት እነደሚሄድ አያውቅም፡፡ ሰው የትላንት ማንነቱን፣ የዛሬ ውሎ እና አዳሩን፣ እና የነገ ተስፋውን

Created in Master PDF Editor

ከራሱ አሳልፎ ለ3ኛ ወገን ከሰጠ የቀረው ስጋ ብቻ ስለሆነ አስከሬን ማለቱ ቢከፋም አማራጭ የለኝም፡፡ ወይስ እንደ ደረጀ ፀጋየ “የስሜት የሹፌርነታቸውን ቦታ ለቀውለሽክም የተመቻቹ ጋሪዎች” ልበል፡፡ ለነገሩ እነዚህ ወቀሳዎች ደንበር ጥሰው ኢ-አማኝነትን ‘ሰነፎች’ ‘የገሃነብ ድጆች’ ‘የሰይጣን ልጆች’ ‘አረምውኔ ከሃዲዎች’ ‘አርዮሳዊያን’ ‘ለሶኦል የተጠበቁ’ ‘እራሳቸውን አምላኪዎች’ ‘666ቶች’ ‘እሪያዎች’ ‘አህዛብ’ እያሉ ለሚሳደቡ ሰባኪዎች ሲያንስ እንጅ አይበዛም፡፡

ኢ-አማኞችን በተመለከተም ፍርሀት አለኝ፡፡ አንዳንድ የፀረ ሀይማኖት አስተሳሰብ አራማጆች በአንድ ጀንበር አማልዕክት ሙተው፣ ሀይመኖት ተወግዶ፤ቤተ-እምነቶች ሙዝየም ሁነው፤እና ዝግመታዊ ለውጥ ብቸኛው የተፈጥሮ አተረጓጎም ሁኖ ማየት የሚፈልጉ ጠባብ አተያይ ያላቸውን አሉ፡፡ ለምሳሌ ኮሚኒስት መንግስታት ሀይማኖት ካልጠፋ እድገት አይመጣምብለው በማሰባቸው በእምነቶች ላይ ዘመቻ ከፍተው ነበር፡፡ለእኔ ይህ አለማመንን ማምለክ ነው፡፡ ከማምለክ ስላልወጡ መሬት ገነት ሳትሆን ቀረች፡፡ ህልመቸውም ከሸፈ፡፡ መፍትሄዉ ይላል <ከማመን መጠራጠር ይሻላል>

“መፍትሄዉ በተለያየ አጋጣሚ የሀይማኖቶችን አላስፈላጊነት የተረዱና ሐይማኖቶችም ለሀገር እድገት ፀር መሆናቸዉን የተገነዘቡ ምክንያታዊ አሳቢወችን አደራጅቶ ህዝቡን የማስተማር ስራ እንዲሰሩ እድል መስጠት ነዉ፡፡ ታድያ እነኝህ ምክኒያታዊ አሳቢያን ማህበራዊ ሚድያ ላይ የምንፅፈዉን አይነት ሐይማኖትን የማዉገዝና የማንቋሸሽ ስራ እየሰሩ ህዝቡን የሚያስቆጡ መሆን የለባቸዉም፡፡ምክንያቱም ህዝቡ ሐይማኖቱን ከጥንት ጀምሮ ጠብቆ ያቆየዉና ከህልዉናዉም ለይቶ ስለማያየዉ በህዝቡ ሊፈረድበት አይገባም፡፡ ሌላዉ ቢቀር የኛ ህዝብ አለም ላይ ከእስልምናና ከክርስትና ዉጭ ሌላ ሐይማኖቶች መኖራቸዉን እንኳ የማያዉቅ አሳዛኝ ህዝብ ነዉ፡፡ ታድያ ይሄ ህዝብ ሳይንስንና ፍልስፍናን ቢፀየፍ ምን ይፈረድበታል? የሌላዉ አለም ህዝቦች እኮ ለሐይማኖታቸዉ ብዙም ቦታ የማይሰጡት በሐይማኖት ፋንታ ሳይንሳዊ እዉቀቶችን በደንብ በመማራቸዉና በማወቃቸዉ ነዉ፡፡ ስለዚህ የኛንም ህዝብ በባዶዉ ሀይማኖትህን ተዉ ማለት ሳይሆን ሳይንሳዊ እዉቀቶችን እያስጨበጡ በሐይማኖቱ ላይ ጥርጣሬን መፍጠርና ሀይማኖቱንም የሚተዉበትን መንገድ ማመቻቸት ነዉ የሚያዋጣዉ፡፡”

ይህ የ<ከማመን መጠራጠር ይሻላል> ሀሳብ በ21ኛው ክ/ዘመን ላለን የድሀ ሀገራት ቦርን አጌን (Born Again) ኤቲስቶች ጠቃሚ ምክር ይመስለኛል፡፡ እንደ ኢ-አማኝ ልናስበው የሚገባን ነገር ቢኖር የእውቀትን ዛፍ ፍሬ ወደ አለም መዝራት ነው፡፡ ከዚ ሌላ ሀይል መጠቀም ጅልነት ነው፡፡ በአራቱም የምድር ማዕዘኖች ከመቼውም ጊዜ

Created in Master PDF Editor

በበለጠ መልኩ መረጃን መስጠትና መቀበል እንችላለን፡፡ ቀደም ሲል ኤቲስት ብትሆኑ ኖሮ የራችሁን ድምጽ ከመስማት በቀር አማራጭ አልነበርም፡፡ አሁን ግን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ በነፃነት በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ በድብቅ የሰውን ልጅ ጠፍንጎ ካሰረው አሉባልታ ነፃ መውጣታቸውን ልታውቁ ይገባል፡፡ ሳይንቲስት፣ፈላስፋ ወይም የስነ መለኮት ተመራማሪ መሆን ሳይጠበቅብን የሙህራኑን ምርምር በመረዳት ለዚህ ሰላማዊ ትግል የሚጠበቅብንን ማድረግ እንችላለን፡፡ በዚህ አብዮት የሚሳተፍ ከሰውነት የዘለለ ማዕረግ አይሰጠውም፡፡ ታምራት፣ ገድላት እና ድርሳናት አይፃፉለትም፡፡ ሽልማቱ በአደባባይ የሚሰጥ የኖበል ሽልማት አይደለም በጨለማ ለሚኖሩ ብርሃን በማካፈል የሚገኝ ደስታ እንጅ፡፡

ለብዙ አማኞች ኢ-አማኝ የሆናችሁት ባለማወቅ፣ በማይረባ ሳይንስ እና ፍልስፍና በመሸወድ፣ በሰይጣን በመታለል፣ አሊያም በድፍረት ይመስላቸዋል፡፡ አማኝ አለመሆናችሁ ሲታውቅ ከሀድ አርዮስ እና ጭራቅ ትባላላችሁ፡፡ ይልቁንም መፅሐፋቸዉም የማያምኑ ወዮላቸዉ የገሃነብ ደጆች የሰይጣን ልጆች ናቸውና ይላሉ፡፡ የሚያሳዝነው አማኞች እንደሰው እንኳላይቆጥሯችሁ ይችላሉ፡፡ ራሳቸዉን ቅዱስ የፈጣሪ ልጆች ለማለት እናንተን ርኩስ የሰይጣን መልዕክተኛ ያደረጋሉ፡፡ እናንት ግን ነፃ ሰው እንደመሆናችሁ መጠን በትርፍ ጊዛአችሁ ማነሰላሰል፣ መፈላሰፍ እና መመራመር ትችላላችሁ፡፡ ስለራሳችሁ ብቻ ሳይሆን ስለ አማኞች መሰረታዊ ዶግማዎች እውቀት ይኑራችሁ፡፡እኔ ስለ ሀይማኖት ለማንበብ እና ለመፃፍየምጠቀመው የእርፍት ጊዜየንነው፡፡ በማንኛው መደበኛ ስራየ ውስጥ ስለ ጉዳዩ አላስብም፤ ሀይማኖትን የማስካድ የስብክት አጀንዳም የለኝም፤ ማንም እኔን እንዲመስል አልጠይቅም፡፡ እንዲያውም ለቅርብ ጓደኞቼ ሳይቀር ክርስቲያን እመስላቸዋልሁ፡፡ ይህን የተማርኩት ከመምህሬ ከፈላስፋው ዘረ-ያዕቆብ ነው <ለሰዎች አማኝ (ክርስቲያን) እመስላቸው ነበር፡፡> ነው ያልው፡፡ አላማየ በህይወት ዘመኔ ይህ ማህበረሰብ ማንነቱን መልሶ እንዲፈትሽ ማሳሰብ ነው በተለይም ስለ ኢ-አማኝነት የተዛባ እሳቤ ላላቸው ሰባኪዎች አፀፋ ከመመለስ ወደኋላ አልልም፡፡ ይህ ለእኔ በቂ ነው ፈረስ ያደርሳል እንጅ አይዋጋም፡፡

3ኛ. ለወላዋዮች፡-መወላወል መጠራጠር አይደለም ግራ መጋባት ነው፡፡ ‘ፅድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም፡፡’ በዚህ አባባል ህዝባችን ያለውን ጥርጥሬ በግልጽ ነግሮናልይህን የነገረን ማህበረሰብ አብዛኛው ፍፁም አማኝ ነው ወላዋይ አይደለም፡፡ ብዙ ሰወች ፈጣሪ ቢኖር ይኑር ባይኖርም አይመለከተኝም ብለው ተከናንበው ተኝተዋል፡፡ መላዋዮች የሃልወተ እግዚአብሔር ጥያቄ የማይሞቃቸውና የማይበርዳቸው ለዘብተኞች ናቸው፡፡ ህሊናቸውን እንዳያስብ አስረውት ካልሆነ ደስ ይለኛል፡፡ ነገር ግን የፈጣሪን መኖር ወይም አለመኖር ማወቅ

Created in Master PDF Editor

አይቻልም ብለው ደምድመው ከሆነ ከሞት ባልተናነሰ ስንፍና ውስጥ ናቸው። ሳያስቡ ከመኖር እያሰቡ መሞት እጅግ ይሻላል። እናም በእግዚአብሔር ህልውና ጉዳይ ገና ያልወሰናችሁ ሰዎች እውነት ከሁለቱም ጫፍ በአንዱ አንጅ በማዕከል አትገኝም። እኔ ለ6 ወር ያህል ወላዋይ ነበርኩ ያ የሽግግር ጊዜ ወሳኝ እና ከባድ ነበር። ከጭንቀቴ ብዛት የተማንፀንኳቸው አዳኞች፣ የተሳልኩት ስለት እና የጸለይኩት ጸሎት ዛሬ ድረስ ይገርመኛል። ሁሉም ከእንባየ ጋር ደረቀ። ከአንዱም ሳትሆኑ ራሳችሁን ከነፃ አስተሳሰብ በማራቅ የምትኖሩ እየተሸወዳችሁ መሆኑን አውቃችሁ ጥጋችሁን ለመያዝ ሞክሩ እላለሁ። እናም ይህን መፅሀፍ እና ሌሎች የሀይማኖት ነክ መፅሀፍትን በማንበብ ከሁለቱ የተሻለውን ምረጡ። በእርግጥ በዚህ መፃሀፉ እግዚአብሔር እንደለለ ለማስረዳት እሞክራለሁ ቢሆንም እኔ ፍንጭ እንጅ እግዚአብሔርን ካመናችሁ ሲኦል ትገባላችሁ፣እግዚአብሄርን ከካዳችሁ ግን ገነትን ትወርሳላችሁ አልልም።

4ኛ. ለተማሪዎች እና ተመራማሪዎች፦ወድ ተማሪዎች እና ተመራማሪዎች ታሪክን፣ ባህልን፣ ሀይማኖትን፣ ፍልስፍናን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጅን ስታስተውሉ ትደነቃላችሁ፣ ሁሉንም ግን ታሪክ ይጠቀልላቸዋል። ታሪክን ሙት ወቃሽ ነው የሚሉ አሉ፣ እነዚህ ሰዎች ራሳቸው የሞቱ ናቸው እንጅ ታሪክ አይሞትም። በታሪክ ውስጥ ስነ ፍጥረትን፣ ባህልን፣ ሀይማኖትን፣ ተቃርኖን፣ ለውጥን፣ ፍቅርን፣ ጥላቻን፣ ፍልስፍናን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጅን ታገኛላችሁ። ብንችል የሁለንታን ታሪክ፣ ካልሆነም የስርዓተ ፀሀይን ታሪክ፣ ቢያንስ ቢያንስ ግን የመሬትን ታሪክ እስከቻልነው ርቀት ማውቅ አለብን። ለነገሩ የኢትዮጵያን ታሪክስ ስንት ኢትዮጵያዊ ያውቀዋል፣ በተለይ የተማረው ለብዙ ጥንታው ክስተቶች እንግዳ ነው። ታሪክ ለታሪክ ተመራማሪወች የተተወ ሳይሆን የሁሉም ዜጋ የቤት ስራ ነው። አለማወቅ ሀጢአት አይደለም የሚባለው ትረት እዚ ላይ አይሰራም። የሀገሩን ታሪክ አለማወቅ ከሴቶች መሃል እናትን እንዳለማወቅ ይቆጠራል የሚባለው ግን እውነት ነው። ማንም ተነስቶ (እኔን ጨምሮ) ኢትዮጵያን ያለስሟ ስም ሰጥቶ፣ ያለግብሯ ግብር ሰቶ፣ ያልሆነውን ሆነ የሆነውን ሀቅ አልሆነም ብሎ ሲቀባጥር መሞገት የምንችለው ስንማርና ስንመራመር ብቻ ነው። እውነትን በመደባበቅ የትም አይደረስም፣ የሚሻለው እውነቱን ተናግሮ ከመሸበት ማደር እንጅ ለፖለቲካ አበል ሲባል መዋሸት ያስተዛዝባል።የሆነስ ቢሆን ከሩዋንዳ እልቂት የባሰ ተፈፅሟልን? ሩዋንዳዊያን በግሃድ የተፈፀመውን ያውቃሉ፣ አላስተባበሉም፣ ይቅር ለመባባልም ልባቸው አልደነደነም። እውነት ለመናገር የኢትዮጵያን ታሪክ እንፈራዋለን እንጅ የሚፈራውን ያህል የሚጎዳን አይመስለኝም። በማንምና የትም የተፈፀመ መጥፎ ታሪካችንን በአመድ በመሸፈን የትም አንደርስም። የሞተ ሙቷል የገደለ ግድሏል አበቃ። ታሪኩን ማስታወስ መብት ነው መድገም ግን ወንጀል ነው። አሜሪካ በጃፓን፣ በጀርመንና በቬትናም ምድር ያደረገችውን አለም

ያውቃል፣ እኛም ተምረናል። አሁን ግን ሮማንቲክ በሚመስል ፍቅር ውስጥ ናቸው፣ ደም የማይመልስ ትውልድ አፍርተዋልና። እኛስ?

ችግራችን አባቶቻችን ፍጹም፣ ሀይማኖታችን ፍጹም፣ ብሔራችን ፍጹም፣ ነገስታቶቻችንና ጳጳሳቶቻችን ፍጹም ነበሩ ብለን ስለምናምን ከታሪክ ጋር ሆድና ጀርባ ሆንን። እንደ ፍጹምነት ነቀርሳ የሆነ በሽታ በአለም የለም። በዚህ በተዳፈነው ታሪካችን ጉዳይ የበዛ ቅሬታ አለኝ ቢሆንም ብዙ ሰው ለታሪኩ ባዳ በመሆኑ ሊረዳኝ ስለማይችል ዝም ብል ደስ ይለኝ ነበር፣ ቢሆንም ይህንም አልችልምና በጹህፌ ውስጥ ሊንጸባረቅ ይችላል። ብዙ ሰው ለታሪኩ ባዳ ነው ስል የማንንም ጥናት መሰረት አድርጌ ሳይሆን የራሴን ምልከታና ለታሪካችን ያለንን አናሳ ግንዛቤ መሰረት አድርጌ ነው፣ (እርግጠኛ ነኝ ለዚህ አባባሌ መቸም አይቆጨኝም)። በነገራችን ላይ የተፈጠረውን ክፍተት ለሞሙላት ጥረት የሚያደርጉትን የታሪክ ጽሃፍትን፣ የሬድዮና ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች (በተለይ የebsን አርአያ ሰብ ዝግጅት) ሳላመሰግን አላልፍም።

ዜጎች ላብራቶሪ ውስጥ ገብተው ኬሚስት መሆን አይጠበቅባቸውም፣ መፅሀፍትን አንበው መሰረታዊ ታሪካቸውንና አመጣጣቸውን ማወቅ ግን የሰብአዊነት ግዴታቸው ነው። የሩቁን ተውትና በኢትዮጵያ ምድር ለ5000 አመታት በቤተ መንግስቱ፣ በቤተ ህዝቡና በቤተ እምነቱ የተከናወነውን ሲያውቅ በመደነቅ አፉን በእጁ የማይጨብጥ፣ ራሱን የማያወዛውዝ አለ ብየ አላስብም። ምን አለ በሉኝ ትገረማላችሁ። ታሪክን ማንበብ የተዋጣለት ፊልም እንደማየት ቅርብ ነው። ልዩነቱ ፊሊም የሚተወነው በተምሳሌት ሲሆን ታሪክ ግን መቸቱና ተዋናዮቹ አማናዊ ናቸው።**ምስጋና ለተክለ ፃዲቅ መኩርያ፣ ለፍስሐ ያዜ፣ ለመራሪስ አማን በላይ፣ ለካሳሁን ደምሴ በላይ፣ ለፕ/ር ባህሩ ዘውዴ፣ ለፕ/ር ላጲሶ ድሌቦ፣ ለአለቃ ታየና የብራና መፅሀፍትን ከትበው ላቆዩን አባቶቻችን በሙሉ ይሁንና ታሪካችንን አብስለው እንድንበላው ሰተውናል። ከትውልዱ የሚጠበቀው ማንበብ ነው፣ አንብቦም ማወቅ፣ አውቆም ማስተዋል፣ አስተውሎም በጎውን መውሰድ መጥፎውን መተው፣በስማ በለው መነዳት ግን የከብት እንጅ የሰው ባህሪ አይመስለኝም።**ተወዳጁ ዲ/ን ዳንኤል ክብረት *"የታሪክ ሂደት ያመጣቸውን የትናንት ነገሮች ዛሬ አንቀይራቸውም። ሆነዋልና። ነገር ግን እንማርባቸዋለን፤ ከትናንት ወስደንም ለዛሬ እንጠቀምባቸዋለን። የዛሬ ማንነታችን መገንቢያም እናደርጋቸዋለን። በታሪክ መስክ ላይ የተሠማራ ትውልድም ጊዜውን ማጥፋት፣ ጉልበቱን መሠዋት፣ ጥበቡን ማፍሰስ፣ ዕውቀቱን መከስከስ፣ ያለበት ለአረሙ አይደለም ለእህሉ እንጅ። ጥላቻው፣ ቂም በቀሉ፣ መቆራቆሱ፣ መናከሱ፣ መለያየቱ፣ መጠፋፋቱ፣ ይኼ የትውልድ አረም ነው። በስንፍና ብቻ ሊበቅል የሚችል ነውና። ትኩረታችንን እህሉ ላይ ካደረግነው አረሙን እንቋቋመዋለን፣ እናጠፋዋለንም። አረሙን ማጥፋት ያለብን አረም ስላልነበረ አይደለም፣ አረምን ለመሸፋፈን ሲባልም*

Created in Master PDF Editor

አይደለም:: አረም ስለማይጠቅመን ነው::” ነበር ያለው (ዳንኤል ክብረት፣ የቀለም
ቀንድ ቅፅ 3 ቁጥር 11):: የጥቅጥቅ ደኖች፣ የብርቅየ ዱር እንስሳት፣ የአፅዋፍት፣
የታላላቅ ወንዞችና ሃይቆች፣ የትናንሽ ደሴቶች፣ የአስደማሚ ስምጥ ሸለቆዎች፣
ጋራዎችና ሸንተረሮች እንዲሁም ረዥም ታሪክ ያላቸው ቅርሶች ባለቤት የሆነችውን
ኢትዮጵያን እንድታውቋት የምመክራችሁ በፍቅር እየለመንኩ እንጅ እንደ ንቡረ እድ
ኤርሚይስ ከበደ እያስፈራራሁ አይደለም::

ንቡረ እድ ኤርሚይስ ከበደ ኢትዮጵያ የአለሙ መፍረጃ በሚለው ሀይማኖታዊ
መጻፋቸው ሦስተኛ እትም ገፅ 32 እና 40 እንዲህ ይላሉ፦“(መጽሃፌ) ስለ ኢትዮጵያና
ስለኢትዮጵያዊነታችሁ የእግዚአብሔር እውነት የሰጠችውን የምስክርነት ቃል የያዘ
ስለሆነ እርሱን አንስታችሁና ገላልጣችሁ ለማንበብ አትፍሩ! ካልወደዳችኋት
አትፈልጓትም! ካልፈለጋችኋት የእሷን ልጆች አይደላችሁም እርሷ በእግዚአብሔር
እውነትነቷ ኢየሱስ መሲህና ድንግል ማርያም ኾና ስለተገለጸች የእርሷ ወገን፣ የእርሷ
አገልጋይ አይደላችሁም ማለት ነው! እንዲህ ካልኾናችሁ ደግሞ ይህ አቋማችሁ
የሀሰት ያውም የዲያብሎስ ወገኖችና አገልጋዮች ያደርጋችኋል::ይህን መጽሀፍ
(የአለሙ መፍረጃን) ከዳር እስከ ዳር በንባብ ለመውጣት ቀርቶ ወደውስጥ ገላልጦ
ለመመልከት እንኳ አንባቢዎች መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው፣ የእግዚአብሔር ወገኖች
ብቻ መኾናቸውን የምታረጋግጠው እውነት ናት::” እኔ ግን እላችኋለሁ የቱንም
መፅሀፍ፣ ማንም ይጻፈው ተጠራጠሩ፣ አለመቀበልም ትችላላችሁ፣ ከቻላችሁም
መተቸት ትችላላችሁ ከዜግነታችሁ ቅንጣት አይቀንስባችሁም:: እኔ ካልኩት ውጭ
ሙቸ እገኛለሁ፣ እኔ ከሞትክ ሰርዶ አይብቀል የሚሉት ኤርሚይስ ከበደና ተክለ
ኪዳን ወጣቱን ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ በሚሸት ርዕስ ግን ለምርምር በር በማይከፍት
አሳሪ ትንታኔ እያጃጃሉት ይመስለኛል:: ተክለ ኪዳን የጨለማው ገዥ ተግባርና
ንግግር የሚለውን ሀይማኖታዊ መጽሃፍ ገፅ 1 ላይ መጽሃፉን ሲያስተዋውቁን
እንዲህ ነበር ያሉት “ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በስጋና ደም ስሜት መነሻነት ሳሆን፣
ያልኖረበት ጊዜ የሌለ፣ የማይኖርበት ጊዜ የማይኖር፣ ረቂቁንና ግዙፉን ፍጥረት
በመለኮታዊ ሀይሉ የፈጠረ፣ ሁሉ በእርሱ የእርሱ የሆነ፣ ከእርሱ ዕይታና ቁጥጥር
ውጭ የሆነ አንዳች ነገር የሌለ፣ ከለእርሱ ፈቃድ አንዳች ሊሆን ሆነ ሊኮን የማይቻል፣
ፊተኛውና መጨረሻው፣ አልፋና ኦሜጋ የሆነው ፈጣሪ አምላክ ከመስከረም አጋማሽ
እስከ ታኅሣሥ መጀመሪያ (2004 ዓ.ም) ድረስ በተለያዩ ቀናትና ሰዓት ወደ ኅሊናዬ
በሚያሳስበኝና በሚናገረኝ ድምፅ ብቻ ተመርቼ ነው የጻፍኩት::'ከቃ መጠራጠር
አይቻልም፣ የመፅሀፉን እውነታ በተለይም ሰይጣንና እግዚአብሔር ጋዜጠኛ ሁኖ
ለቀረበው ተክለ ኪዳን የሰጡትን ቃለ ምልልስ አሜን ብሎ አለመቀበል እንደ ትልቅ
ክህደት ተቆጥሯል:: ቅን ልብና አስተዋይ አዕምሮ ላላቸው ተመራማሪዎች ግን

Created in Master PDF Editor

መፅሃፍቱ ከምፈተሽ አይድኑም፣ በምንም አጥር ይታጠሩ:: የሁለቱም ግለሰቦች መፅሃፍቶቻቸው ብዙ መልካም ነገር ቢኖራቸውም ውስጥ ውስጡን ግን በአድሎ የታጨቁና ኢ-ፍትሀዊነት የሰፈነባቸው ናቸው::

ተማሪና ተመራማሪ የተጻፈን በመረጃ በማመሳከር እንጅ እንደወረደ መቀበልን የምርምር ስነ-ምግባር አይፈቅድለትም::በሀገራችን ወግ ውስጥ የልቡን የነገሩት የኮለኮሉት ያህል ይስቃል ይባላል፡፡ የተማሪዎች እና የተመራማሪዎች ስራ ግን የልብን ከመናገር የበለጠ ነው፡፡ ተመራማሪ ማለት ከማህበረሰባዊና ከግል ፍላጎት ነፃ በሆነ መልኩ የማህበረሰቡን መልካምና መጥፎ ልምዶች፣ አኗኗሮች እና ስርዓቶች ማንኛውም ሰው ሊረዳው ከሚችለው በላይ ወደ ውስጥ ጠልቆ ወይም ወደ ላይ ተመስጦ የሚያሳስ የእውነት አፍቃሪ ማለት ነው፡፡ ለመማር እና ለመመራመር ከውጫዊ ተፅዕኖ እና ከውስጣዊ ተፅዕኖ ነፃ መሆን አለብን፡፡ ተፅዕኖ ወደ እውነት የሚደረገውን ጉዞ የሚያደናቅፍ ታላቅ መሰናክል ነው፡፡ በሀይማኖት፣ በፍልስፍና እና በሳይንስ ላይ ተፅዕኖ ከባድ አሉታዊ ጫና አለው፡፡ አንድ ሰው በእግዚአብሔር ካመነ በኂላ ስለእግዚአብሔር መኖር መመራመር አይጠቅመውም፣ ከጥያቄው መልሱ ስለቀደመ፡፡ የማያምንም እግዚአብሔር የለም ብሎ ከተነሳ ድካም ነው፡፡

ለአንድ ተመራማሪ ሊኖረው የሚገባ ትልቅ ሀብት "መጠራጠር" ነው፡፡ እራሳችሁን እኔ ግን በህይወት አለሁ፣ እስከ ሚለው ድረስ መጠራጠር፡፡ ፈላስፎቹ እኮ ከመጠራጠራቸው ብዛት የምናየው ነገር ሁሉ illusion ነው ይላሉ፡፡ በመጠራጠር ዉሰጥ ድምደሜ የሚባል የለም፡፡ በመጠራጠር ፈልስፍና ማር ጥፈጭ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፡፡ ማርን የሚመገቡት ሰዉእና ጥቂት እንሰሳት ናቸዉ፡፡ ማር ፈጽም ጣፈጭ ቢሆን ሁሉም በወደዱት ነበር፡፡ ከሌሎች እንሰሳት ጋር መወዳደሩ ይቅርና <u>የእባብ ጥብስ እና የአይጥቋንጣ ፍርፍር</u> ምንምን እንደሚል ታዉቃላችሁ? ካወቃችሁ ምሰክር ትሆናላችሁ ካልሆነ ግን እኛ የማንበላዉ ሰለማይጣፈጥ ሳይሆን ሰላልለመድነው እና ሰለማናዉቀዉ ነዉ ሰለዚህ እባብ አይበላም፣ ይባላል (አሳ በጾም ወቅት ይበላል አይበላም እንደማለት ነው) ብላችሁ ከመከራከር በፊት መመራመር ያስፈልጋል፡፡ ምርምሩ በላብራቶሪ ወይም በተግባር በመቅመስ ወይም የቀመሱትን እና ያልቀመሱትን ስለጉዳዩ ያላቸዉ ግንዛቤ በመጠየቅ ሊሆን ይችላል፡፡ የምርምሩ ዉጤት እንዳይበላሽ የምርምሩ መንገድ ከአድሎ ነፃ መሆን አለበት፡፡ ስለእግዚአብሄር መኖር ቤተ-ክርስትያን ሂደህቃለ መጠይቅ ከምታደርግ ምንሊሉ እደሚችሉ አዉቀህ ፈጣሪ አለ ብለህ ብትደመድም ይሻላል፡፡

ምርምር ፍርድነዉ፡፡ ከሳሻ እና ተከሳሽ ሀሳቦች መነሳት አለባቸዉ፡፡ የሁለቱም ወገን ምስክሮችም መጠራት አለባቸዉ፡፡ ያካልሆነ ግን ፈርዱ ይዛባል፡፡ሠዎች ያለጥፋታቸዉ

Created in Master PDF Editor

በእሰር ይማቅቃሉ፣ እዉነትስ በዉሸት ተወንጅላ በእሰር እተሰቃየች እንደሆነ በምን እናዉቃለን?እንደ ተመራማሪ ይህ የቅንብር መጽሀፍ በአለማዊ እና መንፈሳዊ ኮሌጆች ለሚማሩ እና ለሚመራመሩ እንደማጣቀሻ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። በነገራችን ላይ እኔ በዚህ መጽሀፍ የቀረብኩት ተመራማሪ ሁኜ ሳይሆን እንደ ሰባኪ ሀዋርያ ነዉ። በይበልጥ እናንተ ገምግሙት። የመጽሀፉ አለማ ከማመራመር ይልቅ ከመንገድ ዳር ሰባኪዎች እስከጳጳሳት ድረስ በአለማመን አስተሳሰብ ላይ ለሚሰነዝሩት ወቀሳ የመልስ ምት መስጠት ነው።

በድጋሜ መልካም ንባብ

Created in Master PDF Editor

ክፍል አንድ

ሰው ለምን ተጠራጣሪ እና ኢ-አመኝ ይሆናል?

ጥርጣሬ ምንድን ነው? “ጥርጣሬ አብዮት አይደለም፤ አዲስ ህይወት፣ አዲስ ጅማሮ፣ ስር ነቀል ለውጥ አይፈልግም። አብዮት ክህደት ነው የቀደመውን በጅምላ መጠየፍ፣ ከሰሩ ቆርጦ የመጣል መንገድ። ጥርጣሬ ግን የምርመራ መንገድ ነው፤ ድሪቶውን እያራገፈ የቀደመውን እውነት ለትውልዱ ውሉ የማሳየት ጉዞ ነው፤ ድሪቶውን የመግለፅ ጅማሮ ነው መጠራጠር።” (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 52) መጠራጠር ትምህርት ቤት ነው፣ መጠራጠር ከሌለ ትምህርት ትርጉሙ መስማት ይሆናል። መስማት እውቀት ሊሆን ይችላል እንጅ ለውጥ ሊፈጥር አይችልም። ተማሪ ከመምህሩ ሊበልጥ የሚችለው የመምህሩን ትምህርት መጠራጠር ሲችል ነው። በትምህርት ስርዐታችን የተፈተነው እና የምንፈትነው እውነት ሀሰት፣ ምርጫ፣ ቢበዛ የተጻፈውን ጻፍ ነው። ለዚህም ይመስለኛል ብዙ አዋቂ ሁነን ሳለ ብዙ መፍጠር ግን አልቻልነም። ከመሸምደድ ይልቅ በመጠራጠርና በመመራመር ብንቀረፅ ኑሮ የፈጠራ ውጤቶች ሀገራችንን ባጥለቀለቋት ነበር። መሸምደድና በአንድ ዘርፍ ብቻ ችክ ማለት ለምርምር ሁኔታዎችን አያመቻችም። ለዚህ ነው አለቃ ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ በተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን እንደ ትልቅ ጥበብና ፍልስፍና የሚቆጠረውን የቅኔ ትምህርት የሚተቹት። እንዲህ ሲሉ “የያሬድ ዜማ ከተጀመረ ወዲህ በኢትዮጵያ ትምህርት ጠፋ። የኢትዮጵያ ሊቃውንት ህፃናቱም ኑሯቸውን በዜማና በቅኔ ላይ ብቻ አድርገውት ይኖራሉ። ሌላ ትምህርት አላገኙም። በዚህም ምክንያት ሚስጥረ ስጋዌን የሚያውቅ ሰው ታጣ። የያሬድ ጥበብ ብዙ ሰው አቦዘነ። የቅኔ ብልሃት ኢትዮጵያን አደኸየ። አንድ ሰው ቅኔ ሲማር 10 ዓመታት ያሳልፋል፣ ቁራሽ እየለመነ እድሜውን በከንቱ ይጨርሳል።” (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 221) ብሩህ አለምነህም እንዲህ ነበር ያለው “*እውነት ለመናገር፣ ለ1700 ዓመታት የቆው ሥርዓት ትምህርት ከፈጠራቸው ሊቃውንት ይልቅ፣ የአንድ ክፍለ ዘመን ክስተት ሆኑት ዘርዓያዕቆብና ወልደ ህወት የማህበረሰቡን ህይወት ለመለወጥ ትልቅ አቅም ነበራቸው። ከ1700 ዓመታት የድንዛዜ ዘመናት በኋላም ቢሆን ግን አሁን የቆሎ ተማሪዎች ይሄንን እውነታ እየተረዱ መጥተዋል። ያለ አንዳች ፋይዳ ዕድሜንና ዘመንን የሚበላው ትምህርት ትርጉም የለሽ መሆኑን ተማሪዎች እያወቁ ነው። ገነት ከበደ እንዳጠናችው <ወደ አብነት ትምህርት ቤት የገቡበትን ቀን የሚያማርሩና በወላጆቻቸውም የሚያዝኑ ሆነዋል>።*” (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ ምዕራፍ፣ 16) አሁን አሁን ግን ነገሩ ተስፋ ሰጭ ይመስላል የቆሎ ተማሪዎች የሳይንስ ተማሪዎች እየሆኑ ነው፣ በእውነት ትልቅ ለውጥ ነው። መታደስ ማለት ይህ ነው፣ ሳይንስን የሰይጣን ስራ ነው

Created in Master PDF Editor

ከማለት ሳይንስ የሰው ልጆች የድካም ውጤት ነው ወደ ማለት መለወጥ በእርግጥ ትሃድሶ ነው::

እንዳለመታደል ሁኖ በአጭሩ ተቀጨ እንጅ የፈላስፋው ዘርዓያዕቆብን ተማሪ ተኮርና መጠየቃዊ የትምህርት ዘዴ ተግባር ላይ ብናውል የት በደረስን? ብሩህ አለምነህ ለፈላስፋው ዘርዓያዕቆብ ትምህርት አርሰበርስ የተያዙ ሦስት ዓላማዎች አሉት ይላል፦ እነሱም

1) ትምህርት ከተፈጥሮ ህግና ሥርዓት ጋር ተስማምቶ የሚኖር ማህበረሰቡን መፍጠሪያ መሳሪያ ነው፤
2) የአጉል ልማድ፣ የአፈ ታሪክና የእምነት እዳና ሸክም የሌለበት፣ በራሱ ነፃ ሆኖ የሚያስብ፣ የሚመራመርና በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ማህበረሰብን መፍጠሪያ ነው፤
3) መንፈሳዊና ዓለማዊ ህይወትን በማስታረቅ፣ በምልዓትና በብልፅግና የሚኖር ማህበረሰብን መፍጠር:: (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 55)

የፈላስፋው ዘርዓያዕቆብ ተማሪ የነበረው ፈላስፋው ወልደ ህይወት ስለ ትምህርት ትንታኔ በሰጠበት በምዕራፍ 17 ሐተታው ግርም በሚል ሁኔታ ስለ ሁለገብ የትምህርት ዘዴ ያስተምረናል:: እንዲህ ነበር ያለው፦ “ትምህርትን ለመማር አትድከም:: በህይወት ዘመንህም ሁሉ አትተዋት:: የሚበቃኝ ብዙ ትምህርት ተምሬያለሁ ከቶ አትበል:: የሰዎችን ትምህርት ሁሉ ብትማር እንኳ እንደገና የምታወቀው ይበዛል:: በአንድ ትምህርት መኖርም ትዕቢተኛ ስለሚያደርግ ብዙ ስራዎች እንድታገኝበት ትምህርት የተባለውን ሁሉ ተማር:: እስቲ ንቦች የበርሃ አበቦችን እንዴት አድርገው እንደሚቀስሙ ተመልከት:: ንቦች ከሁሉም አበባዎች እየዞሩ ምግባቸውን ይሰበስባሉ እንጂ በአንድ እርሻና በአንድ አበባ ብቻ አይኖሩም::” (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 303)

ብሩህ አለምነህ ‘ዘርዓያዕቆብ እና ወልደ ሕይወት’ ስለ ትምህርት የነበራቸውን አስደናቂ እይታ እንዲህ ያስታውሰናል፦

> በማስተማር ስራ ውስጥ የአንድን ወገን አስተሳሰብ ብቻ ማስተማር የተማሪዎችን የተመራማሪነት ችሎታቸውን ከማኮላሸቱም ባሻገር፣ የላቀ እውነትና ዕውቀት ለመፈለግ ያላቸውን ተነሳሽነትም ያመክንባቸዋል:: ዘርዓያዕቆብ ሐተታውን ሲዘጋ፣ ይሄንና ከዚህም የተሻለ የሚያስተውል ከተገኘ፣ ካስተማረና ከፃፈውም እግዚአብሔር የልቡን ይስጠው:: ያለው ተማሪዎች ወይም አዲሱ ትውልድ ሁሌጊዜ በእውቀት እየበለጠና እየተሻለ ሊሄድ የሚችለው ደግሞ ትውልዱ በአንድ ወገን አስተሳሰብ ሲቀረፅ ሳይሆን በተለያዩ አመለካከቶችና ትምህርቶች ሲታነፁ ነው:: በዚህ ነገር ላይ ወልደ ሕይወትም ጠንከር አድርጎ ፅፏል፣ እንዲህ ይላል፣ትምህርትን በመማር ደካማ

Created in Master PDF Editor

> አትሁን፤ በመላ የህይወት ዘመንህም አትተዋት። ደግሞም በአንድ ትምህርት አትኑር፤ ይህ ስንፍና ነውና። ልክ ንቦች የተለያዩ ማዕዛ ያላቸውን አበቦች እየቀሰሙ ጣፋጭ ማር እንደሚሰሩ ሁሉ፣ አንተም በተለያዩ ትምህርቶች ሁሉ ጥበብን ሰብስብ። (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 60)

ስለፈላስፋው ዘርዓያዕቆብ ማንነት ብዙ ክርክሮች ቢኖሩም በሐተታው ስለተላለፉት ድንቅ ፍልስፍናዎች ከመናገርና ከመጻፍ የሚያግዱ አይደለም። ዘርዓያዕቆብ ማንም ይሁን ማን ፍልስፍናው ጠቃሚ እስከሆነ ድረስ አጀንዳ መሆኑ አይቀርም። ዛሬም ድረስ ፈላስፋው ቀኖናቸውን ያናጋባቸው (ለምሳሌ እነዲ/ን ዳንኤል ክብረት) ስም አጠራሩ ከምድር እንዲጠፋ ይጥራሉ። ፈላስፋው ዘርዓያዕቆብ ከጥንት እስከዛሬ ከሰባኪዎች ጥርስ ውስጥ የገባው በሚያስተምርበት የማስተማር ስነ-ዘዴ ነው። የፈላስፋውን የማስተማር ዘዴ የስነ-ትምህርት ሊህቃን ተማሪ ተኮር (student centered) ይሉታል። የፈላስፍው ትምህርት እንደ ብሩህ አለምነህ አባባል በመንፈሳዊነትና በዓለማዊነት፣ በሂብራይዝምና በሄለኒዝም፣ በሀይማኖትና በፍልስፍና፣ በስሜትና በአመክንዮ፤ በመንፈስና በስጋ መካከል ሚዛኑን የጠበቀ ነው። ተማሪዎቹን እነዚያ እንዲህ ይላሉ እናንተስ ምን ትላላችህ? ይላቸው ነበር። ይህን የኢትዮጵያዋ አቴንስ 'አክሱም' መቋቋም ያቃታትን የማስተማር ዘዴ ብሩህ አለምነህ በሚገባ ግልጾታል።

> ይህ የማስተማር ዘዴ የመጀመሪያው ተግባሩ ባህልን፣ ልማድን፣ እምነትንና አፈ ታሪክን መፈተሽ ነው። እናም አመክንዩ (Reason) ወደ አደባባይ መውጣቷን ተከትሎ አክሱም በአደባባይ ልትጠይቅ፣ በአደባባይ ልትመረምር፣ በአደባባይ ልትፈትሽ ሆነ። በዚህም በአክሱም አውራጃዎች ሁሉ ታላቅ ሽብርና መናወጥ ሆነ። አክሱም ወልደ ዩሐንስን ደጋግማ ወደ ንጉሱ ጋ ለክስ የላከችው ለዚህ ነው። አክሱም ዘርዓያዕቆብ ባታሳድደው ኖሮ በዚህ የማስተማር ዘዴ ብዙ ተማሪዎችን ያፈራ ነበር። ቀስ እያለም ይህ ባህል ስር እየሰደደ በንግግርና በውይይት የሚያምን ማህበረሰብ ለመፍጠር አዲስ አይነት ማህበረሰባዊ ንቅናቄ ይፈጠር ነበር። በዚህም አክሱም በላሊበላዊነት ብሕትውና የተነጠቀችውን የስልጣኔ ማዕከልነት በዘርዓያዕቆብ ለማስመለስ ዕድሉ ነበራት። ዘርዓያዕቆብን ስታሳድደው ግን ይህ ዕድሏ መክነባት። አክሱም ዘርዓያዕቆብን ብትታገሰው ኖሮ ግን፣ የፍልስፍና፣ የስነ ፅሁፍ፣ የኪነጥበብና የሳይንስ ማዕከል ሆና ዳግም ትንሳኤዋን ታገኝ ነበር። ዘርዓያዕቆብን በማሳደዷ ግን የዳግም ትንሳኤዋን ተስፋ አጨናገፈችው። (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 65)

Created in Master PDF Editor

ትምህርትን ብንወድ፣ NO የማለትን ጥበብን ብናከብር፣ WHY የማለት መብት ቢሰጠን ብዙ የሚያስኬድ እድል ነበረን።የChurch of Reality መስራችMarc Perkel NO የማለትን ጥበብን እንድህ ያብራራዋል፦

<<What do we mean by saying NO? NO is an easy word. It's just one syllable and two letters. One letter less than saying ***YES****, but two letters more than saying nothing at all. To some people if you don't say NO fast enough or hard enough they interpret it as saying yes.* ***But the word NO is a very powerful word.*** *It is probably the most important word in our language. NO tells people that you are someone and you refuse to go along. NO means that you will not allow yourself to be taken advantage of. NO means that you are not going to allow yourself to be passively controlled by others.* ***NO means that you think for yourself. NO means that you own yourself.*** *And owning yourself is an important concept in the Church of Reality.*

NO is the word that starts revolutions. NO is the word that allows the oppressed to rise up. NO is the word that is the point where change occurs. When the Martin Luther King started a revolution for the equality of people, the revolution started by saying NO. When Rosa Parks was told that she had to sit in the back of the bus she said NO and ***NO changed the world.*** *Ghandi in India said NO and drove out British control. Nelson Mandela said NO and ended apartheid in South Africa. Susan B. Anthony said NO, that women will not be denied the right to vote, and she prevailed. No is the word of empowerment. NO is the word of leadership. NO allows us to look at who we are and what we are doing and decide who we are and what we will become. NO allows you to stand up for yourself, to defend your rights, and to assert who you are in the world. You can not own yourself until you own the word NO.*

NO often has a price. If you say NO, then they won't be your friend anymore. If you say NO, then you are un cool. If you say NO, then the person won't date you anymore. Sometimes they will threaten violence against you if you say NO. And NO gives you the inner strength to control your life and make your own decisions for yourself. When you say NO then you reclaim who you are. You are telling the world that you own yourself. That you are a strong person. That you control your own destiny. That you care about your future. That you know that choices have consequences. That you will not worship fictional deities. That you are not going to smoke cigarettes to fit in. It's your life. You own it. But you have to say NO to claim it.>> (Source, From church of reality website)

Created in Master PDF Editor

No የማለት ጥበብ በርካታ ማህበራዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ለውጦች አስገኝቷል፡፡ በኢትዮጵያ ባለፉት ሃምሳ አመታት ብቻ ወጣቶች የፊውዳል ስርዓትን፣ የደርግን ስርዓትና የህወአት መረሹ ኢህአዴግን ስርዓት No በማለታቸው ለውጦች ተከስተዋል፡፡ እነዚህ በአንፃራዊነት ተገቢ ለውጦችን ስናስብ የከሸፉት No የማለት ትግሎች ተግባራዊ ቢሆኑ ኑሮ አሁን ካለንበት የተሻለ ቦታ በተገኘን ነበር እንድንል ያደርገናል፡፡

እምቢ ማለት ቆራጥነትን ይጠይቃል፡፡ እሽ ይሁን እንደ ማለት ቀላል አይደለም፡፡ እምቢ ማለት ከራስ ህሊና ውጭ ከሁሉም ሰዎች ጋር ሊያራርቅ ይችላል፡፡ እምቢ ያሉ የከፈሉትን ዋጋ ከታሪክ መዛግብት መረዳት እንችላለን፡፡ ደስ የሚለው ነገር እንቢ ማለት ከሚያስከፍለው ዋጋ በላይ ትርፍ አለው፡፡ የአለምን የለውጥ መዘውር የመሩት እንቢ የሚሉ ሰዎች ናቸው፡፡

ጨለማን እንቢ ያሉ ኤሌክትሪክን ፈጠሩ፡፡ ፊውዳሊዝምን እንቢ ያለ ዲሞክራሲን ፈጠሩ፡፡ በሽታን እንቢ ያሉ መድኃኒቱን ፈጠሩ፡፡ ባርነትን እምቢ ያሉ እኩልነትን ፈጠሩ፡፡ ቅኝ ግዛትን እምቢ ያሉ ነጻነትን ፈጠሩ፡፡ መሀይመነትን እንቢ ያሉ ትምህርት ፈጠሩ፡፡

ማንኛውም አዲስ አመለካከት ሲጀመር መናፍቅነት ነው፣ እንቢ የማለት ደግሞ መግለጫው ነው፡፡ NO ማለት የመለወጥ፣ የመታደስና የማደግ ተንሳኤ ነው፡፡ የማህበራዊ ሳይንስ የጥናት ዘርፎች በተለይ ፖለቲካዊ፣ ሀይማኖትና ማህበራዊ እሴቶች እንደየጊዜው፣ እንደሁኔታውና እንደቦታው እየታደሱ መሄድ አለባቸው፡፡ ለውጡን ለማስቀጠል ደግሞ እንቢ የሚሉ የሚከፈለውን ዋጋ ለመክፈል የተዘጋጁና ብቻቸውን እንኳ እስከ መቅረት የሚታገሉ ፅኑአን ያስፈልጋሉ፡፡ በግሌ የመንጋ አስተሳሰብ ለውጥ የማምጣት እድሉ የመነመነ ነው እላለሁ፡፡ የስነ ልቦና እና የስራ አመራር ሊህቃን እንደሚሉት ሰዎች ለውጥ ይፈራሉ፡፡ በነባሩ አስተሳሰብና መንገድ ብቻ የሙጥኝ የማለት ሱስ አለባቸው፡፡ ሰዎች ሁሉ ለውጥን በጸጋ የሚቀበሉ ቢሆን ኑሮ ሶቅራጦስን መርዝ ባላጠጡት ነበር፡፡ ኢየሱስን ባልሰቀሉት ነበር፡፡ ሙሀመድን ባለሳደዱት ነበር፡፡ ሀይፓትያን ባልገደሏት ነበር፡፡ ማይክል ሴርቪተስን፣ ኤቴኔ ይሌን፣ ፓምፒኒዮ አልጀርዮን እና ጆርዳኖ ቡሩኖን በእሳት ባላቋጠሏቸው ነበር፡፡

የሚያሳዝነው እንቢ ማለትን እንቢ ማለት ሲቻል በሞት መቅጣት ምን የሚሉት ጀብድ ነው፡፡ ለሳይንስና ፍልስፍና ክርስትና በዘመነ ሰቆቃ ከፈለኩት ከምትለው የማይተናነስ ሰማዕትነት ተከፍሏል፡፡ ላለፉት 3,000 አመታት የለውጥ አራማጆች እና እንቢ የማለት ፍልስፍና አራማጆች አልፍ ታምራትን እና ገድላትን ፈጽመዋል፡፡ አጥፊወቻቸው ሲጠፉ እነሱን ግን ታሪክ ዛሬም ያስተውሳቸዋል፡፡ ሶቅራጠስን መርዝ ያስጋቱትን ሰዎች ስም ዝርዝር ታስታውሳለችሁ? በጭራሽ ስም አጠራራቸው ከመድረ

Created in Master PDF Editor

ገጽ ጠፍቷል:: ሙሀመድን ያሳደዱት ሰዎች ስም ዝርዝር ይታወቃልን? አይመስለኝም:: በሀይፓትያ ሞት ጊዜ የአስከሬኗን ጭስ የታጠኑት የአስከንድርያ ሰዎች ስማቸው ይታወቃልን? ታላቁን የፍልስና፣ የሳይንስና የስነ መለኮት ሊቅ ጆርዳኖ ቡርኖን እርቃኑን ሰቅለው በእሳት የለበለቡት፣ እሳቱን የሞቁት፣ እና በመፈራረጃው በሮም ካምፖ ዲ ፊዮሪ አደባባይ የታደሙት የድንቁርና ሀይሎች ስማቸውን መዘርዘር ይቻላልን? ያበረከቱትን አመለካከትስ መጥቀስ ይቻላልን? በጭራሽ:: አወ እንቢ ማት ዋጋ ያስከፍላል:: ከሞትም ለከፋ ለክፍ አሟሟት አሳልፎ ይሰጣል::

እንቢ ማለት ሁሉ መልካም ነገር ባይሆንም አለምን እንዲህ ከትላንት የተሻሻለች ያደርጋት ፍልስፋና ግን "እንቢ" ማለት ነው:: እንቢ ማለት የለውጦች ሁሉ መሪ አስተሳሰብ ነው:: please let us say no.

No የማለት ጥበብ ማህበረሰባዊ ብቻ ሳይሆን ግለሰባዊ ጭምር ነው:: ግለሰቦች ከራሳቸው ህሊና ጋር ሙግት ይገጥማሉ:: አንዳንዶቹ የህሊና ሙግቶች ወደ ጭንቀትና እብደት የሚያመሩ ቢሆንም የህሊናችን ጥያቄዎች በአግባቡ የምናስተናግድ ከሆነ ልዩ ወደ ሆነ የሚጣፍጥ አለም ይወስደናል:: በተለይ መመሰጥ ከራሳችን እና ከውጭው አለም ጋር ለመታረቅ የምንጠቀመው መንገድ ነው:: መመሰጥ መቻል መታደል ነው:: በተፈጥሮ እንደመመሰጥ፣ በህይወት እንመሰጥ፣ በልዩ ልዩ አስተሳሰቦች፣ በእምነቶች እና በባህሎች እንመሰጥ:: መመሰጥ ጥልቅ የመመራመር ቁልፍ ነው:: መመሰጥ የማይገልጠው ሚስጢር የለም:: ኑሮአችን ግልብ ሆኖ ነው እንጅ ነገሮችን ወደ ውስጥ ብናስገባቸው ሁሉም ነገር ፍቅር ነው፣ ደስታ ነው፣ እውቀት ነው፣ ህይወት ነው:: ብዙ ሰዎች መመሰጥ፣ መራቀቅ እና መመራመር ይፈራሉ:: ለኔ ግን መመሰጥ፣ መራቀቅ መመራመር እና መፈላሰፍ የሌለበት ህይወት ባዶ ናት እላለሁ:: ሰው በነፃ ፍቃዱ ይህን ማድረግ ካልቻለ ሰውን ከእንስሳት የሚለየውን ደንበር አፈርሰው ማለት ነው:: ሰው በግ አይደለም:: ማንም ሰው ተነስቶ እኔ ጌታህ ነኝ ሊለው አይገባም:: ሰው ያለመነዳት፣ ያለመሸጥ፣ ያለመገዛት፣ ያለማሰለብ ሙሉ ሰብዓዊ መብት አለው:: ግንዛቤያቸውን በጎች እረኛቸውን እስከ ሚያውቁበት የማሰብ ደረጃ መሆን የለበትም:: ብዙ ርቀን ማንሰላሰል እና መመራመር ይጠበቅብናል:: ደስ የሚለው ብቃቱ አለን ጭዋታው ፍላጎቱ ለይ ነው:: በተፈጥሮ እንመሰጥ ተራራውን፣ ጋራውን፣ ሸለቆውን፣ አሸዋውንና ውሃውን ጨረቃቆን ከዋክብትን፣ በውሃ ውስጥ ያለውን፣ በምድር ያለውን፣ በሰማይ ባለው ሁሉ እንመሰጥበት:: እውቀትም ህይወትም ነው:: በራሳችንም ላይ እንመሰጥ መስታውት ፊት ቁመን ራሳችንን እንመልከት:: ተፈጥሮ ወይም እግዚአብሔር እንዴት ድንቅ አድርጎ እንደሰራን እንይ:: እስኪ አይናችንን በአይናችን አፍጠን እንየው:: እስኪ ፈገግ እንበል የሰውነታችን ስሪቱን እናስተውለው እጅግ ድንቅ ነገር እኮ ነው::

Created in Master PDF Editor

ራሳችንን ብቻም ሳይሆን ሰዎችን እንያቸው። የፍቅር ድንኳን ከሚጣልበት አልጋ ጀምሮ ሚሊየኖች እስከ ሚታደሙበት ሰልፎች እና ክብረ-በዓላት ድረስ እንገኝ። በተጣሉትም በሚዋደዱትም አደባባዮች እንውጣ። ወደ ጠንቋይ ቤት እንሂድ። ቡናው ሲፈላ ፈንድሻው ሲፈነድቅ፣ ጢሱ ሲጫጫስ፣ መልካምና መጥፎ መነፍሳት ሲጠሩ፣ ሰዎች ከመነፍሳት ጋር ሲያወሩ፣ ስለ ትላንት ስለዛሬ እና ስለነገ ሲተርኩ፣ የሰው ልጅ እጣ ፈንታው ሲነገረው እንስማ። ጠንቋይ ቤት ትልቅ ሚስጢር እንዳለ እና እንደሌለ በምን እናውቃለን። ካልሆነ ግን ስለጠንቋይ፣ ስለአስጠንቋይ፣ ስለ ሚርት፣ ስለምትሀት፣ ስለአስማት፣ ስለዛር፣ ስለ ውቃቤ ስለመዳፍ ማንበብ፣ ስለቆሌ፣ ስለአውሊያ፣ ስለድግምት፣ ስለመስተፋቅር፣ ስለመተት እና ስለ ሌሎች የጠንቋይ ቤት ሚስጢሮች መተንተን አንችልም። ከመናገር ማወቅ ይቀድማልና። ትልቁ በእዕውቀት ምንጭ ደግሞ ማየት ነው። ኑ እና እዩ ብለውናል ሂደን እንያቸው።

ወደ ከበሩት ቤተክርስቲያናት፣ መስጊዶች እና ሌሎች የማምለኪያ ቦታዎች እንገስግስ። በእነዚህ ቦታዎች ልዩ፣ ድንቅ እና ብርቅ ሚስጥራቶች አሉ። እስኪ በጥዋት ተነስተን የአመት በዓል ወደ ሚከበርበት ቤተክርስቲያን እንሂድ። የለማኞችን እንጉርጉሮ እናዳምጥ። አለች አለች የሚሉትን ነጋዴዎች እንግዛቸው። ከቅጥሩ ውጭና ውስጥ የሚያነበንቡትን ምዕመናን እንመልከት። አትሮኑንስ አቁሞ በአንድ እጁ ማይክ በሌላ እጁ መጽሀፍ ይዞ የሚሰብከውን መምህር እንስማው። በመቅደሱ ውስጥ በማይገባን እና በሚገባን ቋንቋ የሚቀድሱትን አገልጋዮች እንስማቸው። ታቦታት ከመንበራቸው ሲወጡ እንይ። የህዝቡን እልልታ፣ ጭፈራ እና መዝሙር እንይ። በዚህም ትልቅ ሀሴት እናገኛለን። የፀበል ቦታዎችን እንጎብኛቸው። የአጥማቂዎችን ስብከት እንስማ። የመዳን ፕሮግራሞችን እንታደም፣ የፓስተሮችን አገልግሎት እንይ። መንፍስት ሲወጡ እና ሲጋቡ ሲናገሩም እንስማ። የክርስቲያኖችን መዝሙር፣ የሙስሊሞችን መንዙማ እናዳምጥ። በእየ ቤቱ እምነቱ የተሰደሩትን ታሪኮች፣ ዶግማዎች፣ ቀናወች፣ ትንቢቶች፣ ስንክሳሮች፣ ገድሎች፣ ታምራቶች እና ፍልስፍናዎች ብናውቅስ ምን ይቀርብናል።

እስኪ ሰልፈኞችን እንስማቸው። እስኪ የአርሶ አደሮችን፣ አርብቶ አደሮችን፣ የነጋዴዎችን፣ የፖለቲከኞችን፣ የተማሪዎችን፣ የአስተማሪዎችን፣ የቅጥረኞችን፣ የቀጣሪዎችን፣ የቆጣሪዎችን እና ያቋጣሪዎችን እንዲሁም የአቃጣሪዎችን ህይወት፣ ልምድ፣ አስተያየት እና አኗኗር እንገምግም። ብዙ ጊዜ አይፈጅም ጥቂት ብቻ ቢቻል በአካል ካልሆነም በመንፈስ ከዋሉበት ውለን ካደሩበት አድረን፣ የበሉትን በልተን፣ የጠጡትን ጠተን፣ የሰሩትን ሰርተን፣ ያመኑትን አምነን፣ መከራ ደስታችን ሀዘን ሰርጋቸውን እናድምቅ። ማን ይናገር የነበረ ማን ያረዳ የቀበረ ነውና ነገሩ የሰርቶ አደሮችን፣ ቀምቶ አደሮችን፣ የተኝቶ አደሮችን፣ የበልቶ እና ጠጥቶ አደሮችን፣ የሸጦ እና ገዝቶ አደሮችን፣ የዘፍኖ እና ዘምሮ አደሮችን፣ የዋሽቶ አደሮችን፣ የገሎ እና

Created in Master PDF Editor

ታድጎ አደሮችን፣ የአመሰግኖ እና አማሮ አደሮችን፣ የጠግቦ እና ተርቦ አደሮችን፣ የታሞ እና ድኖ አደሮችን፣ የኑሮ እና የሙቶ አደሮችን አስተዳደር እንመሰጥበት፡፡ እንመራመረው፡፡ አይን፣ ልቦና እና አዕምሮ ሲተባበሩ ምርመሮችን በአጭር ጊዜ መረዳት ይቻላል፡፡ እኔም የማህበራዊና የተፈጥሮ ሳይንስ ተመሳጭ ተማሪ እንደመሆኑ ይህን ሁሉ አደርጋለሁ፡፡ እድለኛ ነኝ አዕምሮየ፣ ልቤ እና አይኔ የመናበብ ችግር የለባቸውም፡፡ ህይወቴ በሙሉ የመመሰጥ ነው፡፡ የምጠላውን ሁሉ የምወደው ስመሰጥበት ነው፡፡ በመመሰጥ ፍቅር እንጅ ጥላቻ የለም፡፡ በእውነት ሰዎችን የሚገዛቸውን መንፈስ እንደማወቅ የሚያስደስት የሚያስደምም የለም፡፡

ወደ ቀደመ ነገሬ ልመለስ የመጠራጠር መሰረቱ ምንድን ነው? መኖርና መማር ይመስላኛል፡፡ በመጠራጠር የተመሰረተ ትምህርትና የኑሮ ትዝብት እኮ የእውቀት ገብያ ብቻ ሳይሆን መዝናኛም ጭምር ነው፡፡ *Lemuel Washburn 'Is the Bible Worth Reading and Other Essays' በሚል መጽሃፉ "We learn everything by living. The truth is not revealed to us: we must discover it. It is seen when we climb high enough to see it, or live wise enough to feel it, or act true enough to utter it. Let us not fear to speak it."* ነበር ያለው፡፡ Question Everything የሚለውን የአንስታየንን አባባል ብንተገብረው መልካም ነው እያልኩ ስለትምህርት የጻፍኳትን ስንኝ ከማስታወሻየ ልጋብዛችሁ፡፡

ፍቅሬ አንች እኮ

ለተመራመረ መላምቱ

ለተጠራጠረ ምልክቱ

ለተፈላሰፈ ጥበቡ

ወዳጀ አንች እኮ

ለተገለለ ቤቱ

ለታመመ መድሀኒቱ

ለታረዘ ሀብቱ

ለተገፋ ርስቱ

ውስጤ አንች እኮ

ለደከመ መዝናኛው

ለተከፋ መፅናኛው ነሽ

እናም ውዴ <u>በቀለበትሽ እንዳሰርሽኝ</u> በቀለበቴ አስሬሻለሁ፡፡

Created in Master PDF Editor

(በ22/05/2008 ዓ.ም፥ ጎንዳር ዩኒቨርስቲ፣ አፄ ቴወድሮስ ካምፓስ ቤተ-መጽሃፍት ፊት ለፊት ተጻፈ::)

በዚህ መፅሃፍ የምጠራጠረው የእግዚአብሔርን መኖር ነው:: በእውን እግዚአብሔር አለን? በሀገራችን ኢትዮጵያ የሚኖሩ ህዝቦች በአይሁድ፣ በክርስትና እና በእስልምና ፀንተው የኖሩ እንደሆነ ይተረካል:: ታሪኩ እውነት ቢሆንም እጅግ አማኝ የሚባሉት አባቶቻችን በግጥማቸው፣ በእንጉርጉሮአቸውና በሙዚቃቸው የእግዚአብሔርን ህልውና ተፈታትነዋል:: መጠራጠር ዛሬ የመጣ አይደለም ከየትኛውም ማህበረሰብ ጋ የኖረና የሚኖር ነው:: ለምሳሌ፦

- የለህም እንዳልል ይመሻል ይነጋል፣ አለህም እንዳልል እንዲህ ይደረጋል::
- ወይ ፍረድ ወይ ውረድ---
- በእውነት ከመንበርህ አለህን? (በእውነት ከመንበርህ የለህማ)
- ያላዛር እህቶች እንደኛው ሰው ናቸው፣ ከቶ ምን ቢሰሩ ዳነ ወንድማቸው
- በሰማይ ላይ ሆነህ፣ ስታላግጥ በሰው--እናትህ ነደደች፣ሐዘኑን ቅመሰው
- ከገበታ በታች ነኝ ከገበታ፣ እንጨት ሲበልጠኝ የት ሂዷል ጌታ ወዘተ.

ተጠራጣሪነትን የአዕምሮ ልህቀት መለኪያ ነው:: ነገሮችን በግልቡ ከማመን ይሰውራል:: መጠራጠር ወደ እውነት ያደርሳል:: ተጠራጣሪ ሰው ደፋር ጠያቂ ነው:: ለጥያቄ ቀይ መስመር የለውም:: ሁሉንም ይጠይቃል፣ ይመረምራል፣ ይመልሳል:: በግፍ፣ በቡድን፣ በይሉኝታና በማስመሰል አይኖርም:: ተጠራጣሪ ሰው፦

- እስልምና በስሙ <ሰላም> ከሚለው ቃል ጋር ስለሚመሳሰል ብቻ ቁርዓንን ሳይበረብርና የእስልምናን ሚስጢርና ታሪክ ሳይረዳ ለማመን አይከጅልም::
- ክርስትና <የመገለጥ> ሃይማኖት እንደሆነ ስለተሰበከለት ብቻ ለራሱ ያልተገለጠለትን እውነት ሳያይ የሚያምን ብጹህ አይደለም::
- ሳይንስ ኑሮን ስላቀለለለት ብቻ ሳይንስ ሁሉ እውነት ነው ብሎ አይቀበልም::
- ፈላስፎች ስማቸው የገነነና እውነትን አፍቃሪ ስለሆኑ ብቻ ፍልስፍና የሚለውን ሁሉ ለመቀበል የሚጓጓ አይደለም::
- መጽሃፍት በቅዱስ መንፍስ ተጽፏል ወይም ከአምላክ ዘንዳ ወርዷል ስለተባለ ብቻ ወይም በጻድቅና በሙህር ስለጻፈው ብቻ ሳይመረመር አይቀበልም::
- ሳይገባው አይጠላም፣ ሳይመስለው አይወድም፣ አይቀላመድምወዘተ::

በበርካታ የሀይማኖት መፅሃፍት መጠራጥርና ተጠራጣሪዎች የተጠሉ ቢሆንም በሁሉም ሰው አስተሳሰብ ውስጥ መጠራጠር አለ:: አንቱ የተባሉ ሰባኪዎችን፣ ዘማሪዎችንና አገልጋዮችን ቀርባችሁ ብትጠይቋቸው ይብዛም ይነስም በእምነታቸው ላይ ጥርጣሬ አላቸው:: ችግሩ ጥርጣሬያቸውን ይደፍቁታል ወይም ያስታምሙታል::

Created in Master PDF Editor

አንዳንዴም በተለይ አማኞች በሚያደርጓቸው ውይይቶች ግልጽ ሁኖ ይወጣል። በተለይም አማኞች አዋቂ ለተባሉ ሰባኪዎች ከሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች ብዙዎች እምነትን ከመጠራጠር የመጡ ናቸው፣ ይህን በጉባዔያት ተገኝቸ ታዝቤያለሁ። ከሰማኋቸው ጥያቄዎች ምሳሌ ይሆነኝ ዘንድ አንድ የተዋህዶ አማኝ <የሚሰበከው ሁሉ ውሸት ቢሆንስ?>ሲል ለስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ የላከው ማንሳት ወደደሁ። ተጠራጣሪው የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪ እንድሆነና ያንዣበበበትን ጥርጣሬ ይፈታ ዘንድ አምላኩን በእንባ ቢማጸንም ሊመልስለት እንዳልቻለ ማህበረ ቅድሳን ባዘጋጀው ‘ምስጢሬል ላካፍላችሁ’ መጽሃፍ ተዘግቧል። እኔን የገረመኝ የልጁ መጠራጠር አይደለም የማህበረ ቅዱሳን ሊህቃን የመለሱበት መንገድ ነው። ሊህቃኑ የጥርጣሬው ምንጭ ሄዋንን ያሳታት ሰይጣን መሆኑን ይገልጹና ልጁ በሆነ ባልሆነው መጠራጠር የሚያበዛ ከሆነ መጨረሻው እብደት ሊሆን እንደሚችል ያስጠነቅቁታል። በጣም የሚገርማው ደግሞ ከሰይጣን በተጨማሪ ሃይማኖትን በስጋዊ ጥበብ ለመረዳት መሞከር፣ ከሀድያንና መናፍቃን የሚሉትን መስማትና ማንበብ እና መንፈሳዊ ምግባራትን መቀነስ ለችግሩ እንደምክንያትነት ተጥቅሰዋል። (ምስጢሬል ላካፍላችሁ ስምዐ ጽድቅ፣271-276)

የፈረደበት ሰይጣን አሳሳች ነው እንበል ነገር ግን ሃይማኖትን በስጋዊ ጥበብ ለመረዳት ካልቻልን በየትኛው ጥበብ አውቀን እንረዳው። በመንፈሳዊ ጥበብ እንዳንል ልጁ መንፈሳዊ ጥበብ ከሚባሉት ዋና የሆነውን ፀሎት በእንባ አጅቦ አቅርቦታል። መልስ የለም ተስፋ ቆርጧል። የቀረው ነገር ቢኖር እኔ አርዮስ እንዳደረኩት ኢ-አማኞችና መናፍቃን የሚሉትን መስማትና ማንበብ ነበር። ልጁ ይህን ያደርግ ዘንድ የሃይማኖት ሊህቃኑ አልፈቀዱም፣ አማራጭ ፈልግ፣ መርምር አላሉትም። አብዝተህ ጹም፣ ስገድ፣ ጸልይ ነበር ያሉት። ያም ሆነ ይህ ሰው መጠራጠር አለበት። ማንኛውንም ጉዳይ በተለይም አስፈሪ ተደርጎ የተቀረጸውን የእግዚአብሔርን ህልውና እንዲሁም አይነኬ የሃይማኖት ዶግማዎችን መጠራጠርን በመጨነቅ ሳይሆን በመደሰት መጠራጠር አለብን። እምነትና ሀይማኖት የሰው ልጅ የጥበብ ውጤቶች፣ የስልጣኔ መገለጫዎች መሆናቸውን ታሪክ ምስክር ስለሆነ ከሰማይ እንደወረዱ በማሰብ ከመመርመር ነጻ ልናደርጋቸው አይገባም።voices of disbelief የተባለ መጽሃፍ የሀይማኖትን ስር መሰረትና እድገት እንዲህ ነበር የገለጸው፦ *“In ancient times, the earth was a less crowded place. People lived in small communities isolated from each other. Each group had its own leader. Each leader dictated his own codes to his followers. Religions were born. Each religious community had its own identity and felt no need to look beyond its own ethnic group. But with increasing population and a rising crisis of resources, different human communities had to cross territories. Clashes were inevitable as rituals had gradually grown rigid and complex, and the basic unifying purpose of each religion was forgotten. Moreover, “God” as a*

Created in Master PDF Editor

superpower was created by Man out of fear and uncertainty. As human society became complex, religion was institutionalized to become a tool for exploitation and a ground for clashes and bloodshed. In the original, simple form of religion there was no need of God in society. Now we have unnecessarily complicated lives; we are imprisoned within our own creation." (50 voices of disbelief, page 261)

አማልዕክትንና ስራዎቻቸውን የምንጠራጠረውና የምንመረምረው ስለምናውቅ ሳይሆን ስለማናውቅ ነው፡፡ ማንም ስለምንም ጉዳይ እርግጠኛ እውቀት አይኖረውም፡፡ በእርግጠኝነት የምንመሰክረው ነገር የለም በሃሳባችን የምንደግፈውና የምንቃወመው እንጅ፡፡ እኛ ሰዎች ስለ ሁለንታ ያለን እውቀት ፅንስ በማህጸን ውስጥ ሁኖ ስለ መሬት ከሚያውቀው ጋር የሚነጻጸር ነው፡፡ እውቀታችን ምንም ሊባል የሚችል ቢሆንም ተስፋ በመቁረጥ <God did it> ማለት ግን ሌላኛው የእውቀት ዝቅጠትና ሞኝነት ነው፡፡

አሉ በሚባሉት አማልዕክት ላይ ተጠራጣሪነትን ለማስጠበቅ የሚከተሉተን ምክንያቶችን እንመርምር፡፡ ሁሉም ምክንያቶች ከሳይንሳዊ ግኝቶች፣ ከፍልስፍና እይታዎች፣ ከነባራዊ ልምምዶችና ከታሪክ ማስረጃዎች እንጅ ከእኔ ከአርዮስ ምኞት ብቻ የመነጩ አይደሉም፡፡ለማንኛዉም እስኪ የተወሰኑ ሀልወተ እግዚአብሔርን እና በሃይማኖቶች የሚሰበከው ሁሉ ውሸት ሊሆን እንደሚችል የሚያስረዱ የተጠራጣሪነትን ክፍታ የሚገልጹ ምክንያቶችን እንይ፦

1. **ሀይማኖት ለመንፈሳዊት እንቅፋት ነው፡፡**

ብዙዎች መንፈሳዊነት እና ሀይማኖታዊነት የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ይመሰክራሉ፡፡ በተቃራኒው ያለሀይማኖት መንፈሳዊ መሆን ይችላል የሚሉም አሉ፡፡ መንፈሳዊነት ከበጎ ምግባር ጋር የምናያይዘው ከሆነ በእርግጥም ያለ ሀይማኖት መንፈሳዊ መሆን ይቻላል፡፡ ነገር ግን መንፈሳዊነት ከሰማያዊ ቅጣትና ተስፋ፣ ፈጣሪን ከመፍራት እና የአንድን ሀይማኖት ትዕዛዛት ከመጠበቅ ጋር የተያያዘ ከሆነ የማያምን ሰው መንፈሳዊ ሊባል አይችልም፡፡ መንፈሳዊነት ከሀይማኖት ጋር የምናያይዘው ከሆነ በሀይማኖቶች ቁጥር ልክ መንፈሳዊነት አለ ማለታችን ነው፡፡ ይህ ደግሞ የመንፈሳዊነትን እውነተኛነት ጥያቄ ውስጥ ይጥለዋል፡፡

በእንደኔ አረዳድ መንፈሳዊነት ሰው ከእንሳሳነቱ የወረሰውን በደመነብስ የመኖር ህይወት ትቶ ለራሱ እውነተኛ የህይወት ትርጉም ሰጥቶ በመልካም ስነ ምግባር መኖር ሲችል ነው፡፡ የአንድ ሰው የቅድስና ማዕረግ መወሰን ያለበት ለህይወቱ በሰጠው ዋጋ እና በስነ መግባሩ ነው፡፡ ስለዚህ ሰው ቅዱስ ሁኖ ለመኖር በአጥር መታጠር አይጠበቅበትም በየትኛውም ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ሆኖ ቅዱስነትን መቀዳጃት

Created in Master PDF Editor

ይችላል። ጥያቄው አማኝ መሆን ለቅዱሳነት ድጋፍ ነው ወይስ መሰናክል? ለመንፈሳዊነት ቅርብ የሆነው አማኝ ነው ወይስ ኢ-አማኝ?

> *The whole past and its religions have been pseudo, false. To me religion has a totally different meaning. There is no God. There is no heaven and hell. All those past religions have exploited man with fear of hell and greed for heaven, and all those religions have kept man retarded, dependent on God, a big daddy somewhere above who is taking care of you. This made man irresponsible. This made man unintelligent. (The Last Testament, Vol 1)*

> *We have to change our consciousness, create more meditative energy in the world, create more lovingness. We have to destroy the old man and his ugliness, his rotten ideologies, his stupid discriminations, idiotic superstitions, and create a new man, with fresh eyes, with new values. (The Rebel, page 3)*

ሀይማኖት ምንድን ነው? ሊቀ ካህናት ኃይለሥላሴ ዓለማየሁ *“ሃይማኖት ወይም እምነት ማለት ማመን፤ መታመን፤ የፈጣሪን ሕልውና ማወቅ፤ ከሃሊነቱን፣ መግቦቱንና ቸርነቱን መረዳት፤ መለኮታዊ እውነታዎችን በትክክል መቀበል፤ በእግዚአብሔር መለኮታዊ ሥራ ፈጽሞ አለመጠራጠር፤ ጥርጥርን ከኅሊና ማስወገድ፤ ስለ ሰማያዊ ሕይወት ጽኑ ተስፋ ማድረግ በሚሉ አገላለጾች ይተረጐማል።”* ይላሉ። (ሐመረ ኖኅ፣ ፳ኛ ዓመት ቁጥር ፪) በተጨማሪም ሊቀ ካህናት ኃይለሥላሴ ዓለማየሁ *“ሃይማኖት በረቂቅ ሐሳብ፣ በልብ ሰሌዳነት፣ የሚጻፍ የአእምሮ መጽሔት ነው። ሃይማኖት የኅሊና መሰላል በመሆኑ የዓለምን አስቸጋሪ ዳገት ይወጡበታል። ሃይማኖት የሕይወት መርከብ በመሆኑ ገፊውን ማዕበል ተቋቁመው ባሕሩን ይሻገሩበታል።እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙበታል። ልክና መጠን፣ ወሰንና ዳርቻ የሌለው መለኮታዊ ባሕርይ የሚታየው፣ ሕልውናው ከሃሊነቱና መግቦቱ የሚታወቀው በሃይማኖት ነው።”* ብለዋል። ስለሀይማኖት ትርጓሜ ከሚሰጡ በርካታ ሊቃውንት የሊቀ ካህናት ኃይለሥላሴ ዓለማየሁ ትርጓሜ የወሰድኩት አጠቃላይ (Comprehensive) በመሆኑ እና ግልጸኝነት የተሞላበት በመሆኑ ነው። ሊቀ ካህናት ኃይለሥላሴ የሀይማኖትን ትርጉም ብቻ ሳይሆን ሀያልነት እና አስፈላጊነትንም አብራርተዋል። የሃይማኖት ኃይል ልዩና ዕፁብ ድንቅ የሚያሰኘው ይላሉ፦ *“የሃይማኖት ኃይል ልዩና ዕፁብ ድንቅ የሚያሰኘው፣ ምድራዊ ባለሥልጣን የማይገዛውን የሚገዛ፣ በዓይነ ሥጋ የማይታየውን የሚያሳይ፣ በእጅ የማይዳሰሰውን የሚዳስስ፣ በሥጋዊ ጥበብ የማይመረመረውን የሚመረምር ምሥጢር መሆኑ ነው። --- እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ሁሉ መገኘት ምክንያት ሳይሻለት በከሃሊነቱ ከምንም ፈጥሮታል። ይህን ማወቅ የሚያስችል ከሃይማኖት ውጪ ሌላ ጥበብ ፈጽሞ የለም።*

Created in Master PDF Editor

የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወራሽ የመሆን ዕድል የሚያገኘው በሃይማኖት ብቻ ነው።” (ሐመረ ኖኅ፣ ፳ኛ ዓመት፣ ቁጥር ፪)

እንዲህ የሀይማኖት ሊቃውንት የሚያወዱሱትን እና እንጀራቸውን የሚያበስሉበትን ሀይማኖት ኦሾ እና <ከማመን መጠራጠር ይሻላል> ክፉኛ ይነቅፉታል። <ከማመን መጠራጠር ይሻላል> ሐይማኖት ምንድነዉ? ብሎ ይጠይቅና ሲመልስ፦ “ሀይማኖት ማለት አንድ ሰዉ ይህችን አለም ከተቀላቀለ በኋላ እያደገ ሲመጣ ከቤተሰቦቹ የሚወርሰዉ በማይረቡ ሀሳቦች የተሞላ፣ ጭንቅላትን የሚያደድብ፣ ጊዜን፣ ገንዘብንና ጤናን የሚያቃዉስ፣ ተፈጥሮአዊ ነገሮችን የሚፃረርና ያለተፈጥሮአችን እንድንኖር የሚያደርግ አስቀያሚ ነገር ነዉ።” ኦሾ ደግሞ ሀይማኖት የሚጠቅም አለመሆኑን ብቻ ሳይሆን የማይጠቅም የመደብ ስርዓት መሆኑና ሀይማኖት መንፋሳዊነት አለመሆኑን ያስረዳል። እንዲህ ነው የሚለው የምስራቁ ፈርጥ አወዛጋቢው ፈላስፋ፦

> A religion is a marketplace thing. It is a kind of bureaucracy you should go through the right channel. You are not even allowed to confess to God directly; you have to confess to the priest and the priest will pray for you. The priest has to always be there as a mediator. Religion is the business of the priest; it has nothing to do with religiousness. It is a profession, pure and simple, of exploiting the ignorance and the helplessness of mankind. It is exploiting the fear of death, the fear of the unknown, the fear of the responsibilities of life. The priest takes care you have to simply believe in his church, his religion, his god, his holy scripture. To belong to a religion is to belong to all kinds of lies and superstitions. To belong to a religion is to belong to the past which is dead.” (The Rebel, page 92)

እኔ የአለም ህዝብ ያለምንም ደንበር፣ ያለምንም ሀይማኖት፣ ያለምንም ብሔር፣ ያለምንም ዜግነት፣ ከምድር ጫፍ እስከ ጫፍ የመኖር ሰብአዊ መብቱ ተከብሮለት ባይ ደስታየ ነበር። ይህ ጎጥ፣ ብሔር፣ ሀይማኖት፣ ሀገር፣ አህጉር የሚባል የከፋፍለህ ግዛው በዝባዥ ስርዓት ተወግዶ እንደማየት የምስራች የለም። አንድ ገዥ ፍቅር፣ አንድ ጌታ ጥበብ፣ አንድ ሀገር መሬት፣ አንድ የአለም መንግስት፣ አንድ ፖለቲካ ሰብአዊነት ኑሮን ማየት እንዴት ያስደስታል። ያኔ ቪዛ የለም፣ ምንዛሬ የለም፣ ወታደር የለም፣ ኒውክለር የለም፣ አሸባሪ የለም፣ ደንዛዥ እና አደንዛዥ የለም፣ ሰይጣን የለም፣ እግዚአብሔር የለም።

መከፋፈላችን ጎዳን እንጅ አለም ለብዙ ቢሊዮን ህዝብ የሚበቃ ሀብት አላት። ምድር ከምናባዊዋ ገነት ታምራለች። አስቡት የአለም ሀገራት የጦር መሳሪያቸውን አውርደው ወታደራቸውን ትጥቅ አስፈትተው ወደ ሲቪልነት ቢቀይሩት፣ የመካላከያ በጀታቸውን ወደ ዜሮ ቢያወርዱት፣ ታንኮቻቸውን አቅልጠው ለኢንዱስትሪ ግብዓት ቢያደርጉት፣

Created in Master PDF Editor

ደህንነት ስለላ እና ሌሎች ጠብ ጫሪ መስርያ ቤቶች ቢዘጉ እንዴት መልካም ነበር። ደስ ሲል ስላሰብኩት ብቻ የኖርኩት ያህል ደስ አልኝ። እንዴ ቃየል ወንድሙ አቤልን ገደለ አበቃ። እስኪ ግለሰቦችን ሊያገዳድል፣ ሀገራትን ሊያዋጋ የሚችል አንዳች ምክንያት ይኖር ይሆን? ምንም አይነት ልዩነት እስከመጋደል ማድርስ የለበትም። ልዩነት ውበት ነው መባል ያለበት መቸ ነው የአንድም የአለም ዜጋ ደም የማያስፈስስ ከሆነ ብቻ እና ብቻ ነው ካልሆነ ግን ኤጭ በአፍንጫየ ይውጥ የምን ውበት ድቀት እንጅ። ለእኔ አንድ ሰው ከሚሞት አንድ ብሄር ወይም ጎሳ ወይም ቋንቋ ወይም ሀይማኖት ስሙ ከመዝገብ ቢጠፋ ይሻላል እላለሁ። እነዚህ ማህበራዊ መስተጋብሮችና ቡድኖች ሰው ፈጠራቸው እንጅ ሰውን አልፈጠሩትም። ብዙ ሰው ያለብሔር፣ ያለሀይማኖት፣ ያለዜግነት የሚኖር አይመስለውም። እውነቱ ግን ይላያል ይደንቃል ይገርማልም ይቻላልና።

እስኪ የኢትዮጵያን እና የሱዳንን ደንበር ያሰመረው ማን ነው? የኢትዮጵያን እና የኤርትራን ደንበር የኮለኮለው ማን ነው? ፖለቲከኞች አይደሉምን? **እውነት ልንገራችሁ ኢትዮጵያ የምትባል ተፍጥሮአዊ ሀገር የለችም።**ሀገራት የፖለቲከኞች ሴራ ናቸው። ሀይማኖቶች የአስማተኞች ሴራ ናቸው። ደማችን ቢመረመር ብሔራችንን፣ ሀይማኖታችንን እና ዜግነችንን የሚያሳይ ይመስላችኋልን? በፍጹም የሚነግረን ሰው መሆናችንን ነው። እስኪ ወደ ማንነታችን እንመልስ ወደ ሰውነታችን እንመለስ እንዋሃድ። መንፈሳዊነት ማለት ይህ ነው። ከውህደቶች ዋናዎቹ ውህደቶች ደግሞ ባህላዊ፣ ሀይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ ውህደቶች ናቸው።

ተስፋ አለኝ እንቅፋቶቹ ከተጠራረጉ ሰው በተፈጥሮው ያን ያህል መጥፎ አይደለም። በዚህ ጹሁፍ የሀይማኖት ውህደትን ከሚያዘገዩት ውስጥ ዋናዋና ያልኳቸውን ለመዳሰስ እሞክራለሁ። እነሱም፦ያልተረጋገጠው ህልወተ አግዚአብሔር፣ በእየ ቦታው የሚለያየው የአግዚአብሔር ባህሪ፣ ቅዱሳን መልዕክተኞችና ቅዱሳን መፅሀፍት፣ ምንፍቅና እና ውግዘት፣ አወዛጋቢው የድህነት መንገድ፣ የቅዱሳን አማላጅነት እና የክብር ደረጃ፣ የምንኩስና አስፈላጊነትና የስርዓት አምልኮ ልዩነት ናቸው።

፩ ያልተረጋገጠው ህልወተ አግዚአብሔር

ሰባኪዎች፣ ማጅካኖች፣ ነብያቶች፣ ፈላስፎችና ሳይንቲስቶች ፈጣሪን በመፈለግ ሽህ አመታትን አሳልፈዋል። አንዳቸውም ግን ግልፅ በሆነ መልኩ ሊሳዩን አልቻሉም። ሁሉም ለእኔ ያሉትን አማልዕክት እየፈጠሩ የአማልዕክትን ብዛት ከ100,000 በላይ እንዲሆን አደረጉት። በተለይ ሰባኪዎችና የሃይማኖት መስራቾች የተለያዩና ተጻጻራሪ አማልዕክትን በመፍጠር የሰውን ልጅ ሲያወዛግቡት ኑረዋል። በሳይንቶስቶችና በፈላስፎችም ፈጣሪ ሊኖር ይችላል የሚል ግንዛቤ ቢኖራቸውም የቅዱስና መፅሀፍቱ እንደማይሆን ግን እርግጠኛ ናቸው።

Created in Master PDF Editor

በመላው አለም ቅዱስን መፅሀፍታቸውን በድንጋይ፣ በስዕል፣ በህንፃ፣ በሀውልት እና ቅርሶች በተለይ ደግሞ በመፅሀፍት ያፃፉት ሁሉ በአንድ እውነት ናቸው ብሎ መቀበል የማይተሰብ ነው፡፡ ከአዲስ አበባ ሀዋሳ በሚኒባስ የተሳፈረ ተጓዥ ወደ መቀሌ እየሄድኩ ነው ይላልን? የሚል ከሆነ ወይ አብዷል ወይ መቀሌ እና ሀዋሳ ተምታተውበታል፡፡ ስለዚህ ሁሉም መንገዶች ወደ አንድ ያደርሳሉ የሚበላው ተረት ብቻ ነው፡፡ እብደት ነው፣ በማይጻረር ህግ (Law of Non-contradiction) የፍልስፍና ህግ መሰረት ተቃራኒ እውነት የለም፡፡

በዚህ ዘመን ያሉ ከ50,000 የማያንሱ የእምነት ድርጅቶች እግዚአብሔር መኖሩን ይሰብካሉ፣ እንዳንዶቹ በተለይ የምስራቆቹ ሀይማኖቶች ሁሉም ነገር እግዚአብሔር ነው አሊያ እግዚአብሔር የለም የሚል አቋም አላቸው ውስጣዊ ልየነቶች እንዳሉ ሆኖ፡፡ ያም ሆነ ይህ የአለም አብዛኛው ህዝብ እግዚአብሔር አለ ብሎ ያምናል፡፡ የእግዚአብሔር መኖር ለማስረዳት የሚጥሩትም አንዳንዶቹ በእምነት ብቻ ሌሎች ፍልስፍናዊ እና ሳይንሳዊ ትንታኔ በመስጠት እና ሌሎች ደግሞ ግላዊ አስተያየታቸውን በመሰንዘር ነው፡፡ በሁሉም እይታ ብንሄድ እግዚአብሔር በእምነትም በፍስልስናም በሳይንስም በግላዊ ቁርኝትም እግዚአብሔርን ገልጦ ማሳየት የሚችል እንድስ እንኳ የለም፡፡ በመሰረቱ በክርስትና “እግዚአብሔርን ያየው ማንም የለም” ተብሏልና፡፡ እግዚአብሔር የያው ማንም የለም፤ ድምፁን የሰማ ማንም የለም፤ ትዕዛዙን የተቀበለ ማንም የለም፤ መፅሀፍት የፃፈለት ማንም የለም፤ መፅሀፍትን ተቀብሎ ያመጣ ማንም የለም፣ የመረጠው ነብይ ወይም ሀዋሪያ የለም፤ የላከው አዳኝ መሲህ የለም፤ የገለጠው መንፈስ የለም፤ ማረጋገጫ ታአምርም የለም- የለም- የለም- የለም- ሁሉንም እንዲሆንና እንዲመስል ያደረጉት ሰዎች ናቸው፡፡ በሌለ ነገር ላይ የተመሰረተ ደግሞ መሰረተ ቢስ ይባላል፡፡ የሌለውን ፍለጋ ማለት ይሄ ነው፡፡ ለዲ/ን ዳንኤል ክብረት ማን በነገረልኝ?

፪ በእየ ቦታው የሚለያየው የእግዚአብሔር ባህሪ

ሀይማኖቶችች ስለ አማልዕክቶቻቸው ባህርያት ይዘረዝራሉ፡፡ ሁሉም የሚሰጧቸው ባህሪ ከጊዜ ከቦታ እና ከሁኔታ አንፃር የተለያየ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ሰባኪዎችና እና በርካታ አማኞች ደግሞ ዝምታን መርጠዋል፡፡ ምክንያታቸው ስለ ፈጣሪ አብዝቶ መመራመር ምንፍቅና ወይም ክህደት ነው ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡ ለእኔ ግን በሩቅ የሚያስፈሩ፣ ሲቀርቧቸው የሰውን ባህሪ የተላበሱ፣ ብዙ ሲቀርቧቸውና ሲመረምሯቸው ግን ስዕሎች ናቸው፡፡

ለሃይማኖቶች መበራከት የአማልዕክት ባህርያት ተለዋዋጭነትና የግልጸኝነት ችግር ሁኖ እያለ <የአማኞች ጋሻ> መፅሀፍ በቅዱስ ቁርዓን ስለተገለፀው አላህ ባህሪ ሲተነትን እንዲህ ይላል፡-

Created in Master PDF Editor

“በቁርኣንና በትክክለኛ ሐዲሦች በግልፅ ሂደት የፀደቁትን የአላህ ስሞችና ባህሪያት ለርሱ ልቅና በሚገባ መልኩ እንዳሉ ማረጋገጥ አማራጭ የሌለው ግዴታ ነው። ይሁንና አብዛኞዎቹን የአላህ መገለጫዎች ለፈጣሪ የማይገባ ጉድለትን እንደሚያንፀባርቁ በማመን ሳይታክቱ አንድ በአንድ የሚያፋርሱና ትርጓሜያቸውንም የሚጠመዝዙ ጎራዎች እንዳሉ አውቀናል። የአንድ ተናጋሪ ንግግር በተወሰኑ ርዕሶች ላይ ሁል ጊዜ አሻሚና የተድበሰበሰ የሚሆነው፦ ወይ ስለ ጉዳዩ ካለው እውቀት ማነስ ነው፤ወይ ደግሞ ከአገላለፅ ችሎታው ማነስ ነው፤አሊያም እውነታውን የመግለፅ ፍላጎት (ቅንነት) ካለመኖር ነው! ከእነኚህ ሶስት እንከኖች አንዱም በአላህና በመልዕክተኛ ንግግር ውስጥ ፍፁም ሊኖር እንደማይችል ደግሞ የማይታበል እውነታ ነው።” (የአማኞች ጋሻ፣ ገፅ 264-265)

በአለም ታሪክ እጅግ አወዛጋቢው ኢየሱስ ክርስቶስ በተለያዩ ሰዎች፣ ሙህራን እና ሀይማኖታዊ ድርጅቶች የተለያየ ባህሪ ተሰቶት ይገኛል። አምላክ ነው የሚሉ አሉ፤ የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ነው የሚሉ አሉ፤ አንደኛ ተራ ሰው ነው የሚሉ አሉ፤ ፈላስፋ ነው የሚሉ አሉ፤ የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ነው የሚሉ አሉ፤ ምድራዊ ንጉስ ነው የሚሉ አሉ፤ የስነ ባህሪ መምህር ነው የሚሉ አሉ፤ ሌላም ሌላም የሚሉ አሉ።

የኢየሱስ ክርስቶስ አወዛጋቢነት የጀመረው ገና ከመሰረቱ ነው። እኔን ማን ይሉኛል ብሎ ሀዋርያቱን በጠየቀ ጊዜ የተለያየ መልስ እንደሰጡት ተጽፏልና። ዛሬም ክርስቲያኖች ሳይቀር ኢየሱስን ከተራ ሰው እስከ ፍጹም አምላክነት የሚፈርጁት አሉ። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ምሥጢረ ሥጋዌ በሚባለው ትምህርቷ እንዲህ ትላለች፦ “ምስጢረ ሥጋዌ ከሦስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ ከሰማያት ወርዶ ከቅድስት ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍስ ነፍስ ነሥቶ በሥጋ የመገለጹ፣ አምለክ ሰው፣ የመሆኑ ምሥጢር ነው። ቃል ሥጋ ሆነ። መለኮት ከሥጋ፣ ሥጋ ከመለኮት ጋር ያለመለወጥ፣ ያለመቀላቀል፣ ያለ መለያየትና ያለ መከፋፈል በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ። ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ ሰውም ከሆነ በኋላ አንድ ወልድ አንድ ክርስቶስ ነው።” ትላለች። ሌሎች የክርስቲያን ዘርፎች ግን ምስጢረ ሥጋዌን በከፊል ወይም በሙሉ የማይቀበሉ ናቸው። በተለይ ለካቶሊኮች እና ኦርቶዶክሶች መከፋፈል ዋነኛ ምክንያት ይህ የምስጢረ ሥጋዌ አስተምህሮ ነው።

በእየመድረኩ በእየቦታው እና በእየጊዜው የሚቀያየረውን ማንነት እንተወውና አብዛኛዎቹ ክርስቲያኖች ሀያል አምላክ እግዚአብሔር ወልድ ይባላል የሚሉትን እና እንደማንኛውም ነብይ የተላከ ሰው ነው የሚለውን የእስልምና አቋም ከመፅሀፍ ቅዱስ አንፃር እንይ። ኢየሱስ ክርስቶስን በተመለከተ ከሁሉም የሚልቀው ልዩነት ክርስቶስ

Created in Master PDF Editor

ከነብያት አንዱ ነው ወይስ አምላክ ነው የሚለው ይመስለኛል። ኢየሱስ ክርስቶስ ነቢይና መልዕክተኛ ስለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች በደርዘን የሚቆጠሩ ጥቅሶችን መጥቀስ ይቻላል። የሚከተሉትን ጥቅሶች ደራሲው ካልተገለፀ ‘ታላቅ ምክር ለአዲሱ ትውልድ’ ከሚል መፅሃፍ አግኝቸ እያመሳከርኩ እንደሚከተለው አቀናበርኩት። በመጽሃፉ ከተዘረዘሩት የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎች የምንገነዘበው መሠረታዊ ጉዳይ በማያሻማ መልኩ ያለንዳች መቃረን ላኪው አላህ ተላኪውም ደግሞ ኢሳ ወይንም ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ በግልፅ ተቀምጧል። <<ጆሮ ያለው ይስማ፤ አይን ያለውም ይመልከት፤ ልብ ያለውም ይገንዘብ>> ሲል አሳስቧል።

፩ “ከእግዚእብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኋችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ?” (ዮሐ. 8÷40)

፪ “እግዚአብሔርስ አባታችሁ ከሆነ በወደዳችሁኝ ነበር፤ እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፤ እርሱ ላከኝ እንጂ ከራሴ አልመጣሁምና።” (ዮሐ. 8÷42)

፫ “እኔ ከራሴ አልተናገርሁምና፤ ነገር ግን የላከኝ አብ እርሱ የምለውን የምናገረውንም ትእዛዝ ሰጠኝ።” (ዮሐ. 12÷49)

፬ “የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም፤ የምትሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም።” (ዮሐ. 14÷24)

፭ “የምትወዱኝስ ብትሆኑ ከእኔ አብ ይበልጣልና ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር።” (ዮሐ. 14÷28)

፮ “እኔ ቃልህን ሰጥቻቸዋለሁ፤ እኔም ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉምና ዓለም ጠላቸው። ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም። እኔ ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉም። በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው። ወደ ዓለም እንደ ላክኸኝ እንዲሁ እኔ ወደ ዓለም ላክኋቸው፤” (ዮሐ.17÷14-18)

፯ “ኢየሱስም። ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፤ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ። እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዓርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው አላት።” (ዮሐ. 20÷17)

፰ “ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤ አንተ እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፥ አንተ፥ አባት ሆይ፥ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ።” (ዮሐ. 17÷21)

፱ “እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም፤ ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋልና። አብ ወልድን ይወዳልና፥ የሚያደርገውንም ሁሉ ያሳየዋል፤ እናንተም ትደነቁ ዘንድ ከዚህ የሚበልጥ ሥራ ያሳየዋል።” (ዮሐ. 5÷19-20)

፩፲ “እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው፥ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና። እኔ ስለ እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር ምስክሬ እውነት አይደለም” (ዮሐ. 5÷30-31)

Created in Master PDF Editor

፩፩ “እኔ ግን ከዮሐንስ ምስክር የሚበልጥ ምስክር አለኝ፤ አብ ልፈጽመው የሰጠኝ ሥራ፥ ይህ የማደርገው ሥራ፥ አብ እንደ ላከኝ ስለ እኔ ይመሰክራልና:: የላከኝ አብም እርሱ ስለ እኔ መስክሮአል::” (ዮሐ. 5÷36-37)

፩፪ “የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው” (ዮሐ. 6÷29)

፩፫ “እንግዲህ ኢየሱስ በመቅደስ ሲያስተምር:: እኔንም ታውቁኛላችሁ ከወዴትም እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ፤ እኔም በራሴ አልመጣሁም ነገር ግን እናንተ የማታውቁት የላከኝ እውነተኛ ነው፤ እኔ ግን ከእርሱ ዘንድ ነኝ እርሱም ልኮኛልና አውቀዋለሁ ብሎ ጮኸ::” (ዮሐ. 7÷28-29)

፩፬ “የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤ እነርሱም ተቀበሉት፥ ከአንተም ዘንድ እንደ ወጣሁ በእውነት አወቁ፥ አንተም እንደላክኸኝ አመኑ:: እኔ ስለ እነዚህ እለምናለሁ፤ ስለ ዓለም አልለምንም ስለ ሰጠኸኝ እንጂ፤ የአንተ ናቸውና፤” (ዮሐ. 17÷8-9)

፩፭ “በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም::” (ማቴ. 7÷21)

፩፮ “መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል እግርህንም በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሡሃል ተብሎ ተጽፎአልና የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ፥ ወደ ታች ራስህን ወርውር አለው:: ኢየሱስም፣ ጌታን አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ደግሞ ተጽፎአል አለው:: ደግሞ ዲያቢሎስ እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ ወሰደው፥ የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ:: ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው:: ያን ጊዜ ኢየሱስ:: ሂድ፥ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው:: ያን ጊዜ ዲያቢሎስ ተወው፥ እነሆም፥ መላእክት ቀርበው ያገለግሉት ነበር::” (ማቴ. 4÷6-11)

፩፯ “ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አለ:: አባት ሆይ፥ የሰማይና የምድር ጌታ፥ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ፤” (ማቴ. 11÷25)

፩፰ “ሕዝቡንም አሰናብቶ ይጸልይ ዘንድ ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ:: በመሸም ጊዜ ብቻውን በዚያ ነበረ::” (ማቴ. 14÷23)

፩፱ “ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም::” (ማቴ. 24÷36)

፪፲ “ኢየሱስም ዓይኖቹን ወደ ላይ አንሥቶ:: አባት ሆይ፥ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ::” (ዮሐ. 11÷41)

፪፩ “አንቺ ቤተ ልሔም፥ የይሁዳ ምድር፥ ከይሁዳ ገዢዎች ከቶ አታንስም፤ ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወጣልና ተብሎ በነቢይ እንዲህ ተጽፎአልና በይሁዳ ቤተ ልሔም ነው አሉት::” (ማቴ. 2÷5)

፪፪ “ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም አለ::” (ማቴ. 15÷24)

፪፫ “ከዚህም ሰው ዘር እግዚአብሔር እንደ ተስፋው ቃል ለእስራኤል መድኃኒትን እርሱም ኢየሱስን አመጣ::” (ሐዋ. ስራ 13÷23)

የሙስሊም ሙህራን እኒህን ጥቅሶች ይጠቃቅሱና እንዲህ ይደመድማሉ፦

ቤተክርስቲያን የኢየሱስን ብሩሕ ትምሕርቶች በጭፍኑ ትፃረራለች:: ሌሎች የክርስትና መሰረታዊ እምነቶችም የቤተክርስቲያን የፈጠራ ውጤቶች ናቸው::

Created in Master PDF Editor

ስለዚህም የዛሬው ክርስትና መለኮታዊ ሃይማኖት አይደለም። የነብይ ኢየሱስን ስም ብቻ እንደ መሣሪያ እየተጠቀመ በቀጥታ ኢየሱስ ያስተማሩትን የሚቃረን አቋም ያራምዳል።

በነገራችን ላይ ሙስሊሞች የእየሱስን አምላክነት ላለመቀበል ከወንጌሉ በጥቂቱ ሁለት ደርዘን ምክንያት ቢያቀርቡም አምላክነቱን የሚገልፁ ሁለት ካርቶን ጥቅሶች መጥቀስ ይቻላል። እየሱስ አምላክ ነው ወይስ የአዳም ብጤ የሆነ ከማርያም የተወለደና ሰው ብቻ የሆነ ነብይ? ክርስቲያንኖች የእየሱስን አማላክነት ለማረጋገጥ መጽሃፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ አላቸው። ለምሳሌ፦

፩ "ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፥ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ" (ራእ 1፡17-18)
፪ "እኔና አብ አንድ ነን" (ዮሐ 10፡30)
፫ "በመጀመሪያው ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ…ቃልም ሥጋ ሆነ" (ዮሐ 1፡14)
፬ "አሁንም አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ" (ዮሐ 17፡5)
፭ "እናንተ ከታች ናችሁ፣ እኔ ከላይ ነኝ፤ እናንተ ከዚህ ዓለም ናችሁ፣ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም" ዮሐ (8፡23)
፮ "ሰብአ ሰገል ወደቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት ወድቀውም ሰገዱለት" (ማቴ 1፡11) "በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ" (ፊልጵ 2፡10)
፯ "ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ" (ዮሐ 14፡14) ‹‹የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፣ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፣ በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም" (ዮሐ 6፡35)
፰ "አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ አየም ደስም አለው…እውነት እውነት እላችኋለሁ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ" (ዮሐ 8፡56-57)
፱ "ቶማስም። ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት" (ዮሐ 20፡28)
፲ "የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ መጣ፥ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በርሱ አለን፥ ርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው" (1ኛ ዮሐ 5፡20)
፲፩ "ጌታችንና አምላካችን ሆይ! አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል።" (ራእይ 4፡10)
፲፪ "የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው፤ ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሯል። (ቆላይ 1፡15-16) ‹‹በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን›› ብሏል።" (ኤፌ 2፡10)
፲፫ "ደግሞም ኢየሱስ ‹እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም› ብሎ ተናገራቸው" (ዮሐ 8፡12)

Created in Master PDF Editor

፩፬ “ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም (ዮሐ 5፡22) “የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል” (ማቴ 25፡31)

፩፭ “አባቶችም ለእነርሱ ናቸውና፤ ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው” (ሮሜ 9፡5)

፩፮ “የታላቁን የአምላካችንንና የመድኀኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን” (ቲቶ 2፡13)

፩፯ “ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ ‹አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ› ይላል” (ራእ 1፡8)

፩፰ “በልብሱና በጭኑም የተጻፈበት የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ የሚል ስም አለው” (ራእ 19፡11-16)

፩፱ “እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ” (ራእ 22፡12)

፪፲ “እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣ እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው” (1ኛ ዮሐ 5፡20)

፪፩ “ኢየሱስም መልሶ ፊልጶስ ሳይጠራህ፥ ከበለስ በታች ሳለህ፥ አየሁህ አለው” (ዮሐ 1፡48) ስለ ሁሉን አዋቂነቱ፦ “አዎን ጌታ ሆይ! እንድምወድህ አንተ ታውቃለህ አለው” (ዮሐ 21፡15)

፪፪ “ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፣ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤ ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም” (ዮሐ 11፡25)

፪፫ “አይሁድም ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ ስለ ስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት።” (ዮሐ 10፡33)

፪፬ “ይህንም ሲነግራቸው፥ አንድ መኰንን መጥቶ፦ ልጄ አሁን ሞተች፤ ነገር ግን መጥተህ እጅህን ጫንባት፥ በሕይወትም ትኖራለች እያለ ሰገደለት።” (ማቴ 9፡18)

፪፭ “ቶማስም፦ ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት። ኢየሱስም፦ ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው።” (ዮሐ 20፡28-29)

፪፮ “በታንኳይቱም የነበሩት፦ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው ሰገዱለት።” (ማቴ 14፡33)

ከእነዚህ ጥቅሶች በመነሳት ባለራዕዩ ተክለ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አምላክ የማይቆጥሩትን በተገለጠለት መሰረት ይገስፃቸዋል። መልዕክቱን የላከው እርሱ እራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እንዲህ ይላል፡-*“እናንተ ኢየሱስ በነቢይነት፣ በአማላጅነትና በፍጡር ደረጃ የምትቀበሉ! በውኑ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተዋል በእናንተ ዘንድ አለ? አንዳች የለም። ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስተካክል ማን ደፋር ነው? ‹‹እኔና እግዚአብሔር አንድ ነን›› የሚል ማን ነው?”* (የመጨረሻው ፍርድ አፈጻጸም ውሳኔ፣ 2ኛ ዕትም፣ 46)። በግልጽ ስም ጠርቶ ሲወቅስ ከፈለጋችሁ እንዲህ በላቸው ይለዋል ክርስቶስ ለተክለ ኪዳን *“እናንተ በተለያየ መልክ እንዲህ የወቀስኳችሁ፤ እነማን እንደሆናችሁ አላወቃችሁምን? እናንተ ‹‹ነቢይ ነው››*

Created in Master PDF Editor

ብላችሁ በስሜ የምትነግዱ የካዳችሁኝና በእስልምና ‹‹እምነት›› ውስጥ ያላችሁ፤ ‹‹አማላጅ ነው›› ብላችሁ በስሜ የምትነግዱ የካዳችሁኝና ዕለት ዕለት የምትሰድቡኝ እጅግ ያስቆጣችሁኝ የፕሮቴስታንት የተለያየ ክፍልፍይ ‹‹እምነት›› ውስጥ ያላችሁ በእውነተኛዋ ሃይማኖት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ስም የምትነግዱ ተሐድሶዎችና በመናፍቃን መንፈስ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምትመላለሱ ተጠራጣሪዎች ናችሁ:: እናንተ ሁላችሁ ከማያምኑብኝ የበለጠ የባሰ ፍርድ ይጠብቃችኋል::”
(የመጨረሻው ፍርድ አፈጻጸም ውሳኔ፣ 2ኛ ዕትም፣ 50)

እየሱስ ክርስቶስ በቅዱሳን መፅሃፍት አንዴ ሀያል ፈጣሪ ሌላ ጊዜ ምስኪን ነብይ ተደርጎ ተስሏል:: በምንም አይነት መንገድ ሁለቱም አካሄድ እውነት ሊሆን አይችልም ምን አልባት ፈጣሪም ነብይም ላይሆን ይችላል:: በዘመናት እንደተነሱት ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎች ሊሆን ይችላል:: ይህ ሰፊ ምርምር ይጠይቃል::

፫ ቅዱሳን መልዕክተኞችና ቅዱሳን መፅሀፍት

ሀ) ቅዱሳን መልዕክተኞች በተመለከተ

The Islamic Bulletin የተባለ ድህረ ገፅ የሙስሊሞችን እምነት በጥቅል ባስቀመጠበት ምላሹ እንዲህ ይላል፦

> “ሙስሊሞች በአንድ፣ ልዩ በሆነ፣ በማይነጻጸር አምላክ፣ በእርሱ በተፈጠሩት መላዕክቶች፣ <u>የእርሱን ራዕይ ወደ ሰው ልጅ ባመጡት ነብያት፣</u> በመጨረሻዋ የፍርድ ቀንና ለድርጊቶቻቸው ባለው ግላዊ ተጠያቂነት፤ በሰው ልጅ ዕጣፈንታ እና ከሞት በኋላ ባለው ህይወት ላይ በአምላክ ፍጹም ስልጣን ሁሉ ያምናሉ፤ **ሙስሊሞች በነብያት የሚያምኑ ሲሆን** በተዋረድም በአዳም፣ በኖህ፣ በአብርሀም፣ በእስማኤል፣ በይስሀቅ፣ በያዕቆብ፣ በእዮብ፣ በሙሴ፣ በአሮን፣ በዳዊት፣ በሰሎሞን፣ በኤልያስ፣ በዮናስ፣ በመጥምቁ ዩሀንስ እንዲሁም በእየሱስ ያምናሉ:: <u>ግን</u> ለሰው ልጆች በአምላክ የመጨረሻዋ መልዕክት፣ የዘላለማዊ መልዕክት ማረጋገጫ እና ከዛ በፊት የሆነው ሁሉ ማጠቃለያ የሆነው በገብርኤል በኩል **ለነብዩ መሀመድ** በተገለጸው ነው::”

ይህ የእምነት ድንጋጌ ክርስትና እና እስልምና የአብርሃም ሀይማኖቶች እንዲባሉ አድርጓቸዋል:: በብዙዎቹ መልዕክተኞች ይመሳሰላሉ ግን የሚመሳሰሉት በስምና በአንዳንድ ታሪኮች ካልሆነ በአብዛኛው ልዩነታቸው ይልቃል:: ቢሆንም ከአዳም ጀምሮ እስከ ኢየሱስ ድረስ የተዘረዘሩት የሃይማኖቶቹ አምዶች የሚመስሉት ክርስትና ነው ወይስ እስልምናን? የመልዕክተኞችና ነብያት የእውነተኝነት መስፈርትስ ምንድን ነው?

ፈላፋው ዘርአ ያዕቆብ ይላል ብሩህ አለምነህ፦ “ዘርዓያዕቆብ ከክርስትና የሚገነጠልበት አንዱ ዲባ አካላዊ አቋም፤ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ እንዴት ነው የተገለጠው

Created in Master PDF Editor

በሚለው ሐሳብ ላይ ነው። ኦሪትም ሆነ ሐዲሱ እግዚአብሔር በየዘመኑ በካህናቱና በነቢያቱ በኩል ለሰው ልጅ እየተገለጠ መልዕክት እንደሚያስተላልፍ ይናገራል። ዘርዓያዕቆብ በዚህ ሐሳብ አይስማማም። ለዘርዓያዕቆብ እግዚአብሔር የተገለጠው በተፈጥሮ ብቻ ነው።" (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣27)

ፈላፋው ዘርአ ያዕቆብ ይህን ይበል እንጅ ፈጣሪ በእየ ቀኑ የሚያነጋግራቸው እነተክለ ኪዳን ግን የእውነተኛ ነብይነትን መስርቶች ይደነግጋሉ። እግዚአብሔር ለተክለ ኪዳን እንደነገረው ሰዎች ከአምላክ ዘንድ የሚላኩ ልዩ መልእክተኞችን የሚለዩበት 10 መንገዶች የሚከተሉት ናቸዉ።

1) የራሱን ክብር የማይፈልግና እግዚአብሔር ከፍ ከፍ የሚያደርግ
2) ራሱን በፊቴ የሚያዋርድና ዝቅ ዝቅ ሚያደርግ
3) ስለ እዉነት የሚመሰክር፣ በእዉነት የሚኖር፣ ስለ እዉነት ራሱን የካደ
4) ‹‹እንዲሁ ይሆናል›› ብሎ ከተናገረ ያለዉ የሚሆንለት፤ የሚፈጸምለት
5) በእግዚአብሔር ዘንድ ምህረትን ሆነ መዓትን ቢጠይቅ እንደ ነብዩ ኤልያስ የሚከናወንለት
6) በሰማያዉያን ሠራዊት ስለሚጠበቅ ማንም ፍጡር በራሱ ሥልጣንና ኃይል ሊጎዳዉ ሆነ ሊያጠቃዉ የማይችል
7) እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሄርነቱ ምንም ጥርጣሬ በዉስጡ የሌለዉ
8) በእግዚአብሔር ስም፣ በሥላሴ ስም ፣ድንግል ማርያም ስም፣ በቅዱሳን መላእክት ስም፤ በጻድቃን በሰማእታት፤ በነቢያት፣ በሐዋርያት ስም፣ እንደ ተሰጠዉ ጸጋ የመፈወስና ተአምራትን የማድረግ ስልጣን ያለዉ
9) ለድንግል ማርያም ልዩ ፍቅር ያለዉ
10) ለምርጥ ባለሚሎቹና ወዳጆቹ ለቅዱሳን ሰዎች ልዩ አክብሮት ያለዉ (የመጨረሻው ፍርድ አፈጻጸም ውሳኔ፣ 2ኛ ዕትም፣ 54)

ባለራዕዩ ተክለ ኪዳን በዘረዘራቸው መስፍርቶች መሰረት መልዕክተኞች ትክክለኛ ለመሆን የኢትዮጵያዋ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ መሆን አለባቸው መስፈርቶች የሚያሳዩት የቤተ-ክርስቲያኗን ስርዓቶች ነውና። በተጨማሪም ባለራዕዩ ተክለ ኪዳን ከቤተ ክርስቲያኗ ስርዓት ውጭ የሆኑትን ያስጠነቅቃል። እንዲህ በማለት

"እንኳን እናንተ በግፋና በዓመጻ ውስጥ ያላችሁት ቀርቶ፣ በእውነተኛ ሃይማኖት ውስጥ ሆነው በቅንነት የማይመላለሱ፣ ዓመጽና ትዕቢት የሞላባቸው ሰዎች፤ እንዲሁ በዘልማድ የሚመላለሱ፣ መንፈሳዊ እውቀታቸውን እንድ ስራ መስክ ቆጥረው የሚያገለግሉ፣ እግዚያብሔርን ያገለገሉ እየመሳላቸው በክህደት ሕይወት ውስጥ የሚመላለሱ፣ እግዚያብሔርን በግልጽ አያዉቁትም፤ ቢያውቁትም በውስጣቸው እግዚያብሔር መፍራት የሌለባቸውና የድፍረትን

Created in Master PDF Editor

በደልና ኃጢአት ስለሚሰሩ ለሰማያዊ መንግስትና ክብር አይበቁም፡፡ (የመጨረሻው ፍርድ አፈጻጸም ውሳኔ፣ 2ኛ ዕትም፣ 34)

ለ) ቅዱሳን መፅሀፍትን በተመለከተ

ሀይማኖቶች ተወዳጅ ቅዱስን መፅሀፍት አሏቸው፡፡ ሁሉም በመፅሀፎቻቸው እውነተኝነት አይደራደሩም፡፡ መፅሀፎቹ የክብር ክብር ተሰቷቸው የህይወት ዘመን መመሪያ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ፈጹምና ቅዱስ እንደሆኑና ከፈጣሪ ዘንድ እንደመጡ ይታመናል፡፡ የመፅሀፍቱ አመጣጥ እንደየሃይማኖቶቹ ይለያያል፡፡

ሙስሊሞች እንደሚሉት አላህ በመልእክተኞቹ ላይ ቅን መመሪያ ፀጋና ተሀድሶን ያዘሉ መፅሐፍትን አውርዷል:: ከነዚህም ውሥጥ የሚከተሉትን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

- ተውራት (ኦሪት)፦ አላህ በነቢዩ ሙሳ ላይ ያወረደው ነው
- ኢንጂል (ወንጌል)፦ አላህ በነቢዩ ኢሣ ላያ ያወረደው መፅሐፍ ነው::
- ዘቡር (መዝሙር)፦ አላህ ለነቢዩ ዳውድ የሰጠው ነው::
- ቅዱስ ቁርኣን፦ ነብዩ ሙሐመድ ላይ ያወረደው ነው::

ብዙ (ሁሉም ካልሆኑ) ሙስሊሞች እንደሚያምኑት ቅዱስ ቁርኣን አላህ በመጨረሻ ነብዩ ሙሐመድ ላይ ያወረደው ሲሆን አላህ ከቁርኣን በፊት የነበሩ መጽሐፍትን በሙሉ ሽሯል:: ቁርዓን ግን ተውራት፣ ኢንጅልና ዘቡር ተሽረዋል አላለም የመፅሃፍት ሰዎች የሚባሉትን አይሁዶችና ክርስቲያኖችን ይነቅፋል እንጅ:: ሌሎቹ ሙስሊሞች ደግሞ ተውራት፣ ኢንጅልና ዘቡር የተባሉትን መፅሀፍት ባይሻሩ እንኳ ተበርዘዋል፣ ተደልዘዋል ስለዚህ አናምንባቸውም ይላሉ:: ክርስቲያኖች ከዚ ላይ ጠንከር ያለ ጥያቄ ያነሳሉ እንዲህ በማለት፦

> *“ቁርኣን በተጻፈበት ዘመን መጽሐፍ ቅዱስ የተበከለ አለመሆኑን በግልጽ በራሱ በቁርኣኑ ተጽፎ እናያለን:: ቁርኣኑ የመጽሐፉ ሰዎች፥ የመጽሐፉ ባለቤቶች ወይም መጽሐፉ የተሰጣቸው ሰዎች የሚላቸው የአይሁድና የክርስቲያኖቹ መጻሕፍት ተውራት፥ ዛቡር እና ኢንጂል ትክክለኛ መሆናቸውን እንጂ የተሳሳቱ መሆናቸውን ከቶም አይናገርም:: ከውስጣቸው በከፊልም በጥቂትም ሲያመላክት መሳሳታቸውን ሳይሆን ትክክለኛነታቸውን በማመን ነው:: ከተሳሳተ ምንጭ ማን ይቀዳል? ከዚያ ወዲህ ተበክሉ ከተባለ ደግሞ በዚያ ቁርኣን በተነገረበት ወይም በተጻፈበት ዘመን የነበረውና አሁን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ልዩነት የሌላቸው መሆኑን ማንም በአእምሮ መርምሮ ሊደርስበት፥ ሊጨብጠውና ሊገነዘበው ይችላል:: በ7ኛውና በ8ኛው መቶ ምዕት ዓመት የነበረው መጽሐፍ ቅዱስ ዛሬ በእጃችን ካለው ምንም ልዩነት የሌለው መሆኑን እውነትን የሚፈልግ ያገኘዋል::”* (ዘላለም መንግሥቱ፣ እስላም እና ክርስትና ንጽጽራዊ አቀራረብ ለዶ/ር ሙሀመድ ዓሊ የተሰጠ ምላሽ)

Created in Master PDF Editor

ለዚህ ጥያቄ ሙስሊሞች በቂ መልስ የላቸውም፣ ምን አልባት አንዳንድ የተለመዱ ስተቶችን ሊዘረዝሩ ካልሆነ። እንደ አማኝ በተውራት፣ በዛቡር እና በኢንጂል ያሉ ስህተቶችን አርመው ማመን በተገባቸው ነበር ችግሩ <u>በምንም አይነት መንገድ</u> እነዚህ መፅሃፍት ከቁርዓን ጋር ሊጣጣሙ አይችሉም። ስለዚህ ሙስሊሞች ያላቸው አማራጭ ቁርኣን እስከ ዕለተ-ትንሳኤ በፍጡራን ላይ ሁሉ ማስረጃ ሆኖ ስለሚኖር የጥበቃውን ዋስትና አላህ ወስዷል ማለት ነው። ቅዱስ ቁርኣን አይከስምም፣ ከሙስሊሞች ልቦናም አይጠፋም፣ አይረሳምም ማለት ነው። መቃወምም አይቻልም። ቁርዓኑም የሚለው "ይህ መጽሐፍ (ከአላህ ለመኾኑ) ጥርጥር የለበትም" ነው።

ተውራትና ኢንጂል ተበርዘዋል የሚሉት የሙስሊም ሙህራን የሚያቀርቧቸው ቁራዓናዊ ማስረጃዎቻቸው ግልፅ ያልሆኑ ቢሆኑም እንደምሳሌ የሚጠቀሱት የሚከተሉት ናቸው።

1. ‹‹(አይሁዶች) ከነሱ የኾኑ ጭፍሮች የአላህን ቃል የሚሰሙና ከዚያም ከተረዱት በኋላ እነርሱ እያወቁ የሚለውጡት ሲኾኑ ለናንተ ማመናቸውን ትከጅላላችሁን?›› አል በቀራህ 75
2. ‹‹ከነዚያ አይሁዳውያን ከኾኑት ሰዎች ንግግሮችን ከስፍራዎቹ የሚያጣምሙ አልሉ።›› ኒሳእ 46
3. ‹‹ከእነዚያም እኛ ክርስቲያኖች ነን ካሉት የጠበቀ ቃል ኪዳናቸውን ያዝን። በእርሱም ከታዘዙበት ነገር ፈንታን ተውት። ስለዚህ እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ በመካከላቸው ጠብንና ጥላቻን ጣልንባቸው። አላህም ይሠሩት የነበሩትን ሁሉ በእርግጥ ይነግራቸዋል። የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! ከመጽሐፉ ትሸሽጉት ከነበራችሁት ነገር ብዙውን ለእናንተ የሚገልጽ ከብዙውም የሚተው ሲኾን መልክተኛችን (ሙሐመድ) በእርግጥ መጣላችሁ።›› ማኢዳህ 14-15
4. ‹‹ለነዚያም መጽሐፉን በእጆቻቸው ለሚጽፉና ከዚያም በርሱ ጥቂትን ዋጋ ሊገዙበት «ይህ ከአላህ ዘንድ ነው» ለሚሉ ወዮላቸው። ለነርሱም ከዚያ እጆቻቸው ከጻፉት ወዮላቸው። ለነሱም ከዚያ ከሚያፈሩት (ኃጢኣት) ወዮላቸው።›› አል በቀራህ 79
5. ‹‹(እንዲህ) በላቸው፦ «ያንን ብርሃንና ለሰዎች መሪ ኾኖ ሙሳ ያመጣውን መጽሐፍ ክፍልፍሎች የምታደርጉት ስትኾኑ ማን አወረደው (የወደዳችኋትን) ትገልጿታላችሁ ብዙውንም ትደብቃላችሁ።›› አል አንዓም 91

ቁርኣንን አስቀድመው ስለወረዱት መጽሃፍት ግልጽ ተቃውሞ ወይም ድጋፍ የለውም። ይህ በሁለቱም ወገን ውዝግብ እንዲፈጠር አድርጓል፣ አንዳንዶች ባይዋጥላቸውም። የአማኞች ጋሻ ቁርኣንን በተመለከተ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ያነሳል፣ ይመልሳል።

"አላህ ስለ ቁርኣን ወደ እውነት የሚመራ ብርሃን፣ የተብራሩ አንቀፆችን ያዘለ፤ ለግንዛቤ የቀለለ፤ በግልጽ ዐረብኛ ቋንቋ የወረደ እና የመሳሰሉት መገለጫዎችን የተላበሰ እንደሆነ የሚነግረን ሁሉ እውነት አይደለም ማለት ነው(ን)?! መቼም 'እውነት ነው እንጂ!' ማለታችሁ አይቀርም! ታዲያ፦ የጌታን ህልውና

በሚመለከተው በዚህ ታላቅ መሠረት ላይ ቁርኣን የሚያንፀባርቀው ጉልህ መልዕክት ክህደትን የሚያስገነዝብ ሊሆን ይችላል(ን)?!፣ ወይስ አላህ በተዟዟረ ዘይቤ ራሱን ለማወደስ በቀጥታ ጉድለትን የሚያስተላልፉ ገለፃዎችን ደጋግሞ ያሰፍራል(ን)?፣ እንዴትስ የቁርኣን አንቀፆች እርስ በርስ የሚቃረኑ ግልፅና ድብቅ መልዕክቶችን አጣምረው ያስተላልፋሉ? እንዲያ ከሆነ ቁርኣን ሰምና ወርቁ ከሚያደናግር የቅኔ ፈተና የባሰ እንቆቅልሽ ነው ማለት አይደል?!" (የአማኞች ጋሻ፣ ገፅ 266)

ክርክሩ በቁርዓን እና በመጽሃፍ ቅዱስ ምርጫ ላይ ብቻ አይደለም። ከመጽሃፍ ቅዱስ የቱ መጽሃፍ ይግባ የቱ ይውጣ የሚለውም አካራካሪ ነው። አንዱ 81 ሲያክትት፣ ሌላው 76ቱን ሲመርጥ፣ ቀሪው 66ቱ በቂ ናቸው ይላል። ሁሉም አጀንዳ ተይዞ <u>በይሁን ይሁን</u> እንጅ የቱ መካተት እንዳለበትና እንደሌለበት ባለቤቱ ያለው ነገር የለም፣ በቅርቡ ግን ለተክለ ኪዳን ሳይነግረው አልቀረም። ኢየሱስ ክርስቶስ ለባለራዕዩ ተክለ ኪዳን እንደነገረው ክርስቲያኖች መፅሀፍ ቅዱስን ብቻ ሳይሆን አዋልድ መፅሀፍትን እንደ መመሪያ እንዲጠቀሙባቸው አሳስቧል። እንዲህ በማለት፦

"የቀደሙት አባቶቻችሁ ቅዱሳት መጻህፍትን ከጥፋት በተጋድሎ ጠብቁ፤ አዋልድ መጻህፍትን እንድትጠቀሙበት÷ ቅዱስ ጻጋዉ የበዛላቸዉ በምድራዊ ህይዎት ዘመናቸዉ ታላቅ ተጋድሎ የፈጸሙትን ታሪክ፣ ተጋድሏቸዉን፣ በስሜና በቃሌ የተለያየ ተአምራትና ፈዉስ ያደረጉበትን፣ ለታላቅ ክብር የበቁበትን የሚገልጽና እንድትዘክሯቸዉ፣ መታሰቢያቸዉን እንድታደርጉ፣ የምርጦቼ አገልጋዮች ክብርና ፍቅር እንዲኖራችሁ ገድላትን፣ ሰንክሳር፣ እንዲሁም የእናቴ የአደራ እናታችሁ የእመቤታችሁ ድንግል ማርያም ፍቅርና ክብር እንዲኖራችሁ ተአምሯን፣ ኑሩዋቸዉ ከዚህች ዓለም ዉጭ የሆኑት ቅዱሳን ባሟሎቼን መላእክትን እንድታዉቁና ክብርና ፍቅር እንዲኖራችሁ ድርሳናትን፤ በረከት፣ ጸጋን፣ እዉቀት የምታገኙበትን የተለያዩ መንፈሳዊ የፀሎት፣ የምስጋና፣ እንዲሁ የእዉቀት መጻሕፍትን አዘጋጁላችሁ። የዓመጻ ልጆች ደግሞ በተቃራኒዉ የእኔን እግዚአብሄርነትን እንድትጠራጠሩ፣ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት እንድትክዱ፣ የእመቤታችሁን ድንግል ማርያም ፍቅርና ክብር እንዳይኖራችሁ የሚያደርግ፣ ከነዚህ በተጨማሪ ደግሞ ለነፍሳችሁም ለሥጋችሁም አንዳች የማይጠቅማችሁን በአጠቃላይ ከእዉነተኛዉ የህይዎት መንግድ ለይቷችሁ ወደ ሞትና መቀመቅ የሚወስዳችሁን የክህደት፣ የጥርጥር፣ የርኩሰት፣ የጥላቻ፣ የጊዜ ማባከኛና ማጥፊያ የተለያዩ ዓይነት ጽሁፎችን አዘጋጁላችሁ።" (የመጨረሻው ፍርድ አፈጻጸም ውሳኔ፣ 2ኛ ዕትም፣ 65)

ስለ መፅሀፍ ቅዱስና ቁርኣን የህይወት ዘመን መመሪያነት ብዙ ተፅፏል። ብዙ ተነግሯል፤ ብዙ ተሰብኳልም። ስለ አዋልድ መፅሀፍት ከክርስቶስ ጋር ቃል ምልልስ

Created in Master PDF Editor

ያደረገው ተክለ ኪዳን አዲስ ነገር ያስተዋወቀ ይመስላል ተረት ተረት የሚመስል ቢሆንም፡፡ (በግሌ ተረት ተረት እንደሆነ አምናለሁ፡፡)

የአለምን ህዝብ የቸገረው ነገር የመፅሀፍቱ መኖር ሳይሆን ሁሉም የተለያዩ ግን እውነተኛ ነን የሚሉ መሆናቸው ነው፡፡ የትኛውን ጥለን የትኛውን ማንሳት እንዳለብን የሚነግሩን ሰዎች ቢሆኑ እንጅ የመፅሀፍቱ ባለቤት በቀጥታ አልነገረንም፣ አይነግረንምም፡፡ ታዲያ የ100,000 ቅዱስን መፅሀፍትን እስከ አዋልድ መፅሀፍቶቻቸው በማመን መንፈሳዊ መሆን ይቻላልን? ወይስ አንዱን ብቻ በአጋጣሚ መርጦ በማመን መንፈሳዊ መሆን ይቻላልን? ወይስ በሃአዎችና ዩኒታሪ ዩኒቨርስታሊስቶች እንደሚሉት ሁሉንም ባማመን መንፈሳዊ መሆን ይቻላልን? ጭራሽ አይቻልም፡፡ በእርግጥ በሃአዎች፣ ዩኒታሪ ዩኒቨርስታሊስቶችና የምስራቁ (ህንድ፣ ቻይና፣ ጃፓን) ሃይማኖቶች ከአብርሃም ሀይማኖቶች በተሻለ ለመንፈሳዊነት ይቀርባሉ፡፡ ይብዛም ይነስም ከተፈጥሮ እና ከሰብአዊነት ጋር ለመታረቅ ይጥራሉ፡፡ ከአብርሃም ሀይማኖቶች በተሻለ ሁኔታ ሃሳቦች በነጻነት ይንሸራሸራሉ፡፡

፩ ምንፍቅና እና ውግዘት

ምንፍቅና እና ውግዘት የሃይማኖቶች የመሰረተ ድንጋይ ናቸው፡፡ በአለም ታሪክ ሀይማኖት አንድ ሆኖ ባያውቅም ከአንዱ እየተገነጠሉ እና እንደ አሜባ እየተፈረካከሱ መለያት ግን የዕለት ተዕለት ዜና ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ምንፍቅና፣ ውግዘትና መለያየት በክርስትና ሀይማኖት ጎልቶ ይታያል፡፡

በአሁኑ ወቅት ክርስትና በጀምላ በ3 ይከፈላል፡፡ እርስ በእራሳቸው የተወጋገዙ ናቸው፡፡ ይብዛም ይነስም በካቶሊክና በኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያናት ያለውን ልዩነት ማጥናት ይቻላል፡፡ ፕሮቴስታንት ቤተ-ክርስቲያናትን ከሌሎች ጋር ማነጻጸር ግን አይሞከርም፣ እንዲያውም ይህን ከማጥናት ይልቅ በእያንዳንዳችን አእምሮ ያለውን የአስተሳሰብ ልዩነት ማጥናት ሳይቀል አይቀርም፡፡ ፕሮቴስታንት ቤተ-ክርስቲያናትን ከካቶሊክና ከኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያናት በነገረ ድህነት፣ በጥምቀት፣ በቁርባን፣ በእምነትና በስራ ስለሚገኝ ጽድቅ፣ ስለክህነት፣ ስለንስሃ፣ ስለቅዱሳን ክበርና አማላጅነት፣ ስለምንኩስና፣ እና በሌሎች በርካታ አስተምህሮዎች የማይታረቁ የዶግማ ልዩነቶች አሏቸው፡፡ ያ ብቻም ሳይሆን ፕሮቴስታንት ቤተ-ክርስቲያናት እርስ በራሳቸው የትየሌሌ የዶግማ ልዩነቶች አሏቸው፡፡ ለዚህ ነው ፕሮቴስታንት ቤተ-ክርስቲያናትን ማጥናት አስልቺ ነው የምለው፡፡ ቢሆንም ሁሉንም ባይገልጻቸውም አንዳንድ መገለጫወችን መዘርዘር ግን የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ስለዚህ ከተለያዩ ምንጮች እንዳገኘሁ በሦስቱ ቤተ-ክርስቲያናት የሚያወጋግዙት የሚከተሉት ጥቂት የዶግማ ልዩነቶች እንይ፡፡

Created in Master PDF Editor

የካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን ከኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያናት

- ✓ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድም ነው የሠረጸው ትላለች፣
- ✓ ብዙ ሰዎች ስለሠሩት ኃጢአት በመፀፀት ንስሐ ገብተው ሳይፈጽሙት ቢሞቱ በመንግስተ-ሰማያትና በገሃነመ-እሳት መካከል ልዩ የሆነ ቦታ 'መካነ-ንስሐ' ስላለ ነፍሶቻቸው ወደዚያ ሄደው ከኃጢአታቸው እስኪነጹ ድረስ መከራ እየተቀበሉ ቆይተው ኋላ ወደ መንግስተ-ሰማያት ይገባሉ ትላለች፣
- ✓ የሮም ፖፕ የክርስቶስ እንደራሴና የአብያተ-ክርስቲያናት ሁሉ በላይ ስለሆነ በመንበሩ ተቀምጦ በሚወስነው ሁሉ አይሳሳትም ትላለች፣
- ✓ የምንቀበለው የክርስቶስ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነፍስ ያለው መለኮት የተዋሃደው ነው ትላለች፣
- ✓ በካህናት የሚኖር ማንኛውም ሰው ሚስት አያገባም ትላለች፣
- ✓ ከሥዕል በተጨማሪ ለቅዱሳን መታሰቢያ የድንጋይ ሐውልት ይቀረጽላቸው ትላላች፣
- ✓ ሕጻናት እንደተጠመቁ ወዲያው ሳይሆን ነፍስ ዐውቀው ሜሮን ከተቀቡ በኋላ ይቁረቡ ትላለች፣
- ✓ ወዘተ

ኦርቶዶክስ (ተዋህዶ) አብያተ-ክርስቲያናት ከካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን

- ✓ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ሠረጸ ይላሉ፣
- ✓ 'መካነ-ንስሐ' (Purgatory) የሚባል ነገር የለም ይላሉ፣
- ✓ ለፓፑ ፍጹምነትን ይልቅ የቤተ-ክርስቲያን መሪዎች በጉባኤ ተሰብስበው በተገኙበት የሚወሰን ውሳኔ አይሳሳትም ይላሉ፣
- ✓ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሃደው ነው ይላሉ፣
- ✓ ከጳጳሳት በስተቀር ቀሳውስትና ዲያቆናት ከፈለጉ ሚስት ማግባትን ይፈቅዳሉ፣
- ✓ ለጌታ ለእመቤታችን ለጻድቃንና ለሰማዕታት መታሰቢያ ስዕል እንጅ የድንጋይ ሐውልት ሊቀረጽላቸው አይገባም ይላሉ፣
- ✓ ሕጻናት ከተጠመቁና ሜሮን ከተቀቡ በኋላ ወዲያው ይቁረቡ ይላሉ፣
- ✓ ወዘተ

ፕሮቴስታንት አብያተ-ክርስቲያናት፦

- ✓ ብዙዎች በስላሴ አስተምህሮ ያምናሉ፣ አንዳንዶቹ አያምኑም
- ✓ ኢየሱስ ክርስቶስን ይለምናል፣ ያማልዳል፣ ያስታርቃል ብለው ያምናሉ
- ✓ ኢየሱስ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት በኩር ነው የሚሉ አሉ (ለምሳሌ፦ ጄሆባ ዊትነስ)
- ✓ ኢየሱስ ክርስቶስን መካከለኛ አምላክ ነው የሚሉም አሉ

Created in Master PDF Editor

- ✓ ኢየሱስ ክርስቶስ የሉስፌር ወንድም ነው የሚሉም አሉ (ለምሳሌ፡- ሞርመኖች)
- ✓ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመቃብር የተነሳው በመንፍስ ነው እንጅ በአካል አይደለም የሚሉ አሉ
- ✓ ኢየሱስ ክርስቶስ አብ ነው የሚያምኑም አሉ (ለምሳሌ፡- The Only Jesus)
- ✓ ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋዊ አካል አልነበረውም የሚሉም አሉ (ለምሳሌ፡- The new age movement)
- ✓ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጅ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ አያስፈልግም የሚሉም አሉ
- ✓ መንፈስ ቅዱስ ከአብም ከወልድም ይወጣል ብለው ያምናሉ
- ✓ መንፈስ ቅዱስ ራሱን የቻለ አካል ሳይሆን የእግዚአብሔር ሀይል ነው የሚሉም አሉ
- ✓ ድህነት በእምነት የሚፈጸም እንጂ በስራ የሚገኝ አይደልም የሚሉት ይበዛሉ
- ✓ ስጋውና ደሙ የጌታ ስጋና ደም ሳይሆን መታሰቢያ ነው ብለው ያምናሉ
- ✓ ሲኦል መቃብር ነው የዘላለም ቅጣት ብሎ ነገር የለም የሚሉም አሉ (ለምሳሌ፡- ሞርመኖች፣ ኢየሱስ ብቻዎች ሌሎችም)
- ✓ እግዚአብሔር ድሮ እንደኛ ሰው ነበር፣ እኛም ወደ እግዚአብሔርነት እንለወጣለን የሚሉም አሉ (ለምሳሌ፡- ሞርመኖች)
- ✓ እግዚአብሔር ሰው ነው፣ ሰውም እግዚአብሔር ነው ብለው የሚያምኑ አሉ (ለምሳሌ፡- ዩኒፊኬሽን ቤተ-ክርስቲያንና የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ)
- ✓ የይሁዳና የኢየሱስ ክርስቶስ የግጭት መንስኤ ማርያም መግደላዊት ይሁዳን ትታ ኢየሱስ ክርስቶስን በማፍቀሯ ነው የሚሉ አሉ (ለምሳሌ፡- ዩኒፊኬሽን ቤተ-ክርስቲያን)
- ✓ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ነው፣ ሚስቶች አግብቶ ልጆች ወልዶ ኑሯል የሚሉም አሉ (ለምሳሌ፡- ሞርመኖች)
- ✓ ቃየል የተወለደው ሄዋን ከሰይጣን በግብረ ስጋ ተገናኝተው ነው የሚሉም አሉ፣ ይቅር ይበላቸው እንጅ ኢየሱስ የተወለደው ማርያም ከእግዚአብሔር አብ ጋር ተገናኝተው ነው የሚሉም አሉ፣ (ሎቱ ስብሀት ያስብላል)(ለምሳሌ፡- ዩኒፊኬሽን ቤተ-ክርስቲያን)
- ✓ ሰባኪወች በሚያዩት ራዕይ ትልቅ እምነት ያላቸው አሉ(ሁሉም በሚባል ሁኔታ)
- ✓ ከመናፍስትና ከሙታን ጋር መነጋገር ይቻላል የሚሉም አሉ (ለምሳሌ፡- The new age movement)
- ✓ ሀይማኖትን እና ሳይንስን አቀላቅለው የሚያምኑ አሉ (ለምሳሌ፡- የክርስቲያን ሳይንስ አራማጆች)

- ✓ ጥምቀት ለመዳን የግድ አይደለም ለክርስትናችን ማረጋገጫ እንጅ የሚሉም አሉ
- ✓ የአዋጅ ጾምን፣ ስግደትን፣ መሳለምን፣ ክበረ ብዓላትን፣ ጸለትን ጭምር የሚቃወሙ አሉ
- ✓ የቅዱሳንን መታሰቢያ ማድረግንና ቅዱሳንን ማመስገን ባእድ አምልኮ ነው ይላሉ
- ✓ ቅዱሳንን ከሞቱ በኋላ መማጸንናለሞተ ሰው የፍትሀት ጸሎት ማድረግ አስፈላጊ አይደለም ይላሉ
- ✓ ስእል፣ ታቦት፣ ቅዱሳን መካናትና ቅዱሳን ንዋያተ ቤተ ክርስቲያን አያስፈልግም እንዲያውም ጣኦት ነው ይላሉ
- ✓ ገድላትና ድርሳናት የሰዎችን ታሪክ ስለሚተርኩና የተሰጣቸውም ቃል ኪዳን የሰዎች ፈጠራ ስለሆነ አስፈላጊ አይደሉም ይላሉ፡፡
- ✓ ስለጸበል፣ ስለቅዱስ መስቀል፣ ስለገዳማትና ስለምንኩስና ኦርቶዶክስና ካቶሊክ ያላቸው አቋም ስህተት ነው ብለው ያምናሉ፡፡

ግን ለምን? ይህን መከፋፈል አስመልክቶ ኢየሱስ ክርስቶስ ነገረኝ ብሎ ለ2000 ዓመታት የዘለቀውን የክፍፍል ሂደት ተክለ ኪዳን እንዲህ ይተርከዋል፡፡

<<የሃየማኖት አባቶች ስለ እዉነት በአንድነት ቆመዉ ክርስትናን በአራቱም ማእዘን ሊያስፋፉና ሰወችን ከሞት ወደ ህይዎት መመለስ፤ ከክህደት ወደ እምነት ማምጣት ሲገባቸዉ እርስ በእርስ እየተከፋፈሉና እየተዎጋገዙ ክርስታን አዳከሟአት፤ አቀጨጯት፡፡

በዚህ ምክንያት በስድስተኛ መቶ ክፍለ ዘመን ማለቂያ ላይ በራሱ ምኞትና ሐሳብ ተነሳስቶ ለፈጣሪ የቀና መስሎት ሕሊናዉን ለዲያብሎስ ማደሪያ ያደረገ ሐሰተኛ ነቢይ፤ ክህደትን አስፋፉ፤ ክርስትናን ለማጥፋት ዘመቻ አደረገ፡፡ እኔ አልፋና ዖሜጋ እግዚአብሄር የሁሉ ፈጣሪ የሆኝኩትን ‹‹ኢየሱስ ነቢይ ነዉ፤ እኔም ከፈጣሪ የተላኩ ነቢይ ነኝ›› አለ በድፍረት፡፡ በዚህ ክህደት ምክያት ትዉልዱ ለአንድ ሺህ አራት መቶ ዘመን በላይ በሞት ህይዎት ዉስጥ እንዲመላለሱ አደረገ፡፡

በ14ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ሁለት ባህሪይ ብለዉ ከከፈሉኝ ወገኖች (ኦርቶዶክስ) ከተባሉት ‹‹መንፈስ ቅዱስ ከአብም ከወልድም ነው የሰረጸው›› በማለት ተከፋፍለው ከኦርቶዶክስ ካቶሊክ ተፈጠር፡፡ወደ መጀመሪያዋ ሃይማኖት ‹‹አንድአካል፤ አንድ ባሕርይ›› ከምትለው፤ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ብቻ ነው የሚሰርጸው ብላ ከምታምነው ወደ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ መመለስ ሲገባቸው ሌላ ፍልስፍና ፈጠሩ፡፡

Created in Master PDF Editor

ታዲያ ይህ መከፋፈል በእዉነት ስለ እኔ በመቅናትና እዉነትን ለህዝብ ለማሳወቅ ሳይሆን ለስልጣን፣ ለክብር፣ ለጥቅም ለዝና ነበር። ይህም ክፍፍል ክርስትናን አዳከማት፤ አቀጨጫት እንጂ የሰዉ ዘሮች ወደ እዉነት እንዲመጡ አላደረገም።

የዚህች ክርስትና ፈተናዋ አልበቃ ብሎ በ16ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ላይ የካቶሊክ ተከታይ የነበረዉ መነኩሴ ሐሰተኛ ወንጌላዊ፤የስጋ ፍቃዱና ምኞቱ አሸንፎት ዉስጡ ዐመጻ የሞላበት ነበርና ለፕሮቴስታንት የክህደት እምነት መሰረት ጣለ። እኔ የሁሉ ፈራጅ ዳኛ የሆንኩትን፣ ከእኔ በላይ ማንም የሌለዉን፣ ፈጣሪ አምላክ የሆንኩትን ‹‹አማላጅ›› ነዉ በማለት አስካደኝ፤ አሰደበኝ። ከዚያም አልፎ የእናቴን የእመቤታችሁን የድንግል ማርያምን ክብር አዋረደ፤ አቀለለ። የቅዱሳንን ምላጅና ክብር አዋረደ፤ አቀለለ፤። በዚህ ክህደትና መናፍቅነት ምክንያት ትዉልዱ ለአምስት መቶ ዘመን በላይ በሞት ሕይዎት ዉስጥ እንዲመላለሱ አደረገ።>> (የመጨረሻው ፍርድ አፈጻጸም ውሳኔ፣ 2ኛ ዕትም፣ 59)

ለተክለ ኪዳን የተገለፀለት ኢየሱስ ክርስቶስ ውግዘቱን ይቀጥልና እንዲህ ይላል፡-

“እንግዲህ ስብከቶቻችሁ መናፍቅ መናፍቅ የሸተተ፣ መዝሙራችሁ ዘፈን ዘፈን ያለ፣ ምስጋናችሁ ደዘንኪራና ጭፈራ የመሰለ፤ እንክርዳዳችሁን ከእዉነተኛዉ አገልግሎት አዉጡ። እናንተ ባለማወቅ ከዓመጻ ልጆች ጋር የተሰለፋችሁ፤ የዓመጻ ልጆች ዓላማቸዉ የሃይማኖታችሁንና የቤተ ክርስቲያናችሁን ፍቅር ሊሸረሽሩ፤ እንደቀደሙት በቤተ ክርስቲያኒቱ እንክርዳድ እንደዘሩት ቅባት፣ ጸጋ፣ ተሐድሶ ፣ ምዕመናን ወደ ክህደትና ጥርጥር ለመዉሰድ ነዉ። ስለ እምነት ሆነ ስለ ምግባር ደንታ ቢስ እንድትሆኑ ለማድረግ፣ በመጨረሻም ወደ ሞት መንገድ ሊወስዳችሁ ነዉ ዲያቢሎስ በበላይ ሆኖ እነዚህ የዓመጻ ልጆችን ያሰማራዉ። እናንተ በዓላማ ለጥፋት የተሰማራችሁ እንክርዳድ ናችሁና ቦታ የላችሁም። ትበጠራላችሁ፤ ከስንዴዉ ትለያላችሁ።” (የመጨረሻው ፍርድ አፈጻጸም ውሳኔ፣ 2ኛ ዕትም፣ 61)

ታዲያ አንዱ ሌላኛውን በሚያወግዝበት የሃይማኖት ስርዓት ውስጥ የትኛውን ተከትለን እንዳን። ሁሉንም መከተል አንዱንም መምረጥ መንፈሳዊነት አይደለም። መንፈሳዊነት ጥላቻ መቃቃርና መወጋገዝ ሳይሆን ፍቅር ነው። ፍቅር ምንም ሀያል ቢሆንም በሬ እና እጭድን፣ በግና ቀበሮን፣ አይጥና ድመትን፣ ቆሻሻና ዝንብን፣ እሳትና ውሃን አዋህዶ መኖር አይቻልም። ፍቅር የኖህ መርከብ አይደለም። ሁሉንም በእየቦታው እንጅ በአንድ ማጨቅ አይቻልም።

፯ አወዛጋቢው የድህነት መንገድ

ሀ) መዳን በኢየሱስ በማመን

በኢየሱስ እናምናለን በሚል ተከታታይ የስልጠና መጽሀፍ (ማኑዋል) ውስጥ ስለክርስቶስ በሚያትተው ትምህርት ሁለት ላይ በእምነት ስለመዳን እንዲህ የሚል ትምህርት አለ፦

<<በሚያሳዝን መንገድ፣ ብዙ ክርስቲያኖች ኀጢአትን ሲሠሩ በሚሰማቸው የተሳሳተ ግንዛቤ ምክንያት፣ ምንም ተስፋ የሌላቸው፣ በራሳቸውም ጥረት ለውድቀታቸው መልስን ለማግኘት የሚፍጨረጨሩ ሆነው በእግዚአብሔር ፊት ይቆማሉ። አስደናቂው እውነታ ግን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለ ኀጢአታችን ዋጋ እንደከፈለ ሁሉ፣ አሁንም እርሱ ስለ እኛ በሰማያት በአብ ፊት ይማልድልናል፣ አብም ይቅር ማለቱን እንደሚቀጥልና እንደሚባርከን ያረጋግጥልናል። በእግዚአብሔር ሰማያዊ የፍርድ ዙፋን ፊት መቼም ቢሆን ብቻችንን አይደለንም፣ ኢየሱስ ያለማቋረጥ በእኛ ምትክ ይጸልያል።ኢየሱስ አሁንም በእኛ ሕይወት ውስጥ እንደጠበቃችን፣ እንደ አማላጃችን፣ እንደ ወኪላችን ሆኖ፣ የማይቋረጥ፣ እንደ ቅርብ ወዳጃችን ሆኖ ሃላፊነቱን እየተወጣ ነው። በታላቁም ፈራጅ ፊት በየዕለቱ፣ ያለማቋረጥ በመቆም ስለ እኛ የሚለምንልን ጠበቃችን ነው። አስደናቂው የምሥራች ደግሞ ከሠራው የስርየት ሥራ የተነሳ አንድም ጉዳያችን የማያመልጠው መሆኑ ነው። እርሱ በእኛ ምትክ ሆኖ በሊቀ ካህንነት በሠራው ፍጹምና የተጠናቀቀ ሥራ፣ ዘወትር ውጤታማና ሁልጊዜም ስኬታማ ሆኖ ስለ እኛ ይግባኝ እያለ ይኖራል። (ዶ/ር ኬ. ኤሪክ ቶኔስ)

እርግጥ ነው፣ ሰዎች መልካም ሥራን መሥራት የሚችሉት መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው በኀይል ሲያድር መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። እንግዲህ ይህ መልካም ሥራ ለክርስቲያኖች በክርስቶስ የመጽደቃቸው እውነታ ካልሆነ በስተቀር በራሳቸው ፋይዳ ቢስ ናቸው። አማኞችን ካላመኑት በላጭ የሚያደርጋቸው ሌላ ምንም ነገር የለም። ጳውሎስ በኤፌሶን ምዕራፍ 2 ከቁጥር 8 እስከ 10 እንደጠቀሰው “ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን። (ኤፌ 2፥8-10)

በማንነታችን፣ ፍጥረት ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት በደለኛ ነው። በመጨረሻው የፍርድ ቀን ግን፣ በክርስቶስ ያመነን እኛ፣ ስለ እኛ የሞተልን ሥላለ፣ በክርስቶስ ሞት፣ ከፍርድ እናመልጣለን፣ እርሱም በእኛ በኩል ስለሠራው መልካም

Created in Master PDF Editor

የእግዚአብሔር ሥራ ሽልማትን እንቀበላለን፡፡>> (ምንጭ፦ በኢየሱስ እናምናለን፣ ትምህርት ሁለት፣ ክርስቶስ)

ለ) መዳን በስራ

=ማቴዎስ ምህራፍ 25 ቁጥር 34-46 "ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል:: እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ:: ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፥ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና::" ለማይድኑት ደግሞ "እናንተ ርጉማን፥ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ:: ተርቤ አላበላችሁኝምና፥ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና፥ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፥ ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፥ ታምሜ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና::"

= ያእቆብ ምህራፍ 2 ቁጥር 14-26 "እምነት አለኝ የሚል ስራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱንስ ሊያድነው ይችላልን?.... ስራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው"

=1ኛቆሮንጦስ ምህራፍ 6 ቁጥር 9-11 "ወይስ አመጸኞች የእግዚአብሄር መንግስት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ:: ሴሰኞች ቢሆኑ ወይም ጣኦትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሰሩ ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሄርን መንግስት አይወርሱም"

=ሮሜምህራፍ 2 ቁጥር 6-12-16 "እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ስራው ያስረክበዋል:: በበጎ ስራ በመጽናት ምስጋናና ክብርን የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘለአለም ሕይወትን ይሰጣቸዋል:: ለአመጻም በሚታዘዙ እንጂ ለእውነት በማይታዘዙና በአድመኞች ላይ ግን ቁጣና መቅሰፍት ይሆንባቸዋል:: ክፉን በሚያደርግ ሰው ነፍስ ሁሉ መከራና ጭንቀት ይሆንበታል::"

=ማቴዎስ ምህራፍ 3 ቁጥር 10 "መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል::"

=ሮሜ ምህራፍ 2 ቁጥር 12-16 "በእግዚአብሄር ዘንድ ሕግን የሚያደርጉ ይጽድቃሉ እንጂ : ህግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉም"

=ገላትያ ምህራፍ 5 ቁጥር 19-21 "የስጋ ስራም የተገለጠ ነው:: እርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣መዳራት፣ ጣኦትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንአት፣ ቁጣ፣ አድመኝነት፣ መለያየት መናፍቅነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ ይህንንም የሚመስል ነው:: አስቀድሜ እንዳልሁ፣ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሄርን መንግስት አይወርሱም::"

ባለራዕዩ ተክለ ኪዳን ስለሚያድኑ ሰዎች ከአምላክ የተቀበለው መግለጫ የሚከለው ነው፡-

Created in Master PDF Editor

ዉስጣችሁ ስለ እዉነት የሚቃጠሉ፤ስለ በጎቹ መቅበዝበዝ እረኛ ማጣት የሚያዝኑ ለወንጌል መስፋፋት የሚተጉ፤ የቅድስት ቤተክርስቲያን እምነቷን፣ ሥርዓቷን፣ ትዉፊቷን ጠብቀዉ ለቀጣይ ትዉልድ ለማስተላለፍ ገንዘባቸዉን÷ እዉቀታቸዉን ÷ ጊዝያቸዉን በመሰዋት ልት ተቀን የሚተጉ፤ ቤተ ክርስቲያንን ለእናትነቷ እንጂ የሚፈልጓት በስሟ የማይነግዱባት፤ እኔ ያከበርኳቸዉን ሐዋርያትን፣ ነቢያትን፣ ታድቃንን፣ ሰማእታትን፣ ባጠቃላይ የቅዱሳንን ገድል፣ ትሩፋትና አማላጂነት የሚዘክሩ፤ እናቴንና እናታችሁን እመቤታችሁን ድንግል ማርያምን ከፋ ከፍ የሚያደርጉና ቅድስናዋን የሚመሰክሩ፤ በዚህ መንፈሳዊ ሆነ ስጋዊ ወንበር ላይ ተቀምጠዉ ለጊዜዊ ስልጣን÷ ክብር፣ ዝና፣ ጥቅም፣ ሰዎች ሁሉ ሕሊናቸዉ ሸጠዉ እዉነቱን ሐሰት፣ ሐሰቱን እዉነት፣ እምነቱን ክህደት፣ ክህደቱን እምነት፣ ጠማማዉን ቀና፣ ቀናዉን ጠማማ፣ መልካሙን መጥፎ፣ መጥፎዉን መልካም፣ ብርሃኑን ጨለማዉን ብርሃን፣ ቅዱሱን ርኩስ፣ ርኩሱን ቅዱስ፣ትእቢቱን ትሁት፣ እዉነተኛዉን አስመሳይ፣ አስመሳዩን እዉነተኛ፣ ከሃዲዉንና መናፍቁን አማኝ፣ እዉነተኛ አማኙን ከሃዲ፣ ማህበረ ሰይጣንን ማህበረ ቅዱሳን፣ ማህበረ ቅዱሳንን ማህበረ ሰይጣን በሚባለበት ዘመን፤ ከነፈሰዉ ጋር ያልነፈሱ፤ ሕሊናቸዉን ያልሸጡ፤ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ እምነቷን፣ ሥርአቷን፤ ዜማዋን ለመለወጥና ለማሻሻል በተነሱት የዓመጻ ልጆች ላይ በጽናት የጥፋት ተግባራቸዉን የገቱ ፤ አሁንም የዓመጻ ልጆች በዋንኛ የሃይማኖት መሪዎች ተደግፈዉ በተለያየ መንገድ በቅድስት ቤተክርስቲያን የሚያደርሱትን ጥፋት በጽናት ተግባራቸዉን የሚቃዎሙና ለማስቆም የሚታገሉ፤ በአጠቃላይ የእኔን ፈቃድ የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ፤ መሪያቸዉ መንፈስ ቅዱስ የሆነ የሚቆጣጠራቸዉም እርሱ የሆነ፤ ባላቸዉ አቅም ሁሉ ቤተክርስቲያንን ገዳማትን፣ የአብነት ትምህርት ቤቶችን የሚረዱና እገዛ የሚያደርጉ፤ ዓለም ግን ያላዎቃቸዉ፤ ለዚህ ትዉልድ ያስነሳዋቸዉ የእኔ ባሎሚሎች÷ የድንግል ማርያም ምርጥ ልጆች አሉና፡፡ (የመጨረሻው ፍርድ አፈጻጸም ውሳኔ፣ 2ኛ ዕትም፣ 62)

ሐ) መዳን ሙስሊም በመሆን

“የክርስትና መሰረታዊ እምነቶች የኢየሱስን ስም ብቻ እንደ መሣሪያ እየተጠቀመ በቀጥታ ኢየሱስ ያስተማሩትን የሚቃረን አቋም ያራምዳል፡፡ እስላም ግን ሙሉ በሙሉ ግልጽና ከራሱ ጋር የተጣጣመ ወጥ ሀይማኖት ነው፡፡ አንድ ሰው መዳን የሚችለው በእግዚአብሔር በማመንና ትእዛዞቹን በመፈጸም ብቻ ነው፡፡ ሌሎች ስለኛ በኛ ፈንታ በሚሠሩት ነገር መዳን አይቻልም” (islamictruethamharic.html)

መ) መዳን በኢትዮጵያዊነት

“Everybody has his own idea. Hindus think they are the chosen people of God, and that God gave to the Hindus the first holy books in the world. Hindus were the first

Created in Master PDF Editor

to become a civilized nation, and they have one of the most perfect languages, Sanskrit, which they claim is the only language that God understands. So if you are praying in any other language you are simply wasting your time."

በተጨማሪም

"The Germans think that they are the purest race, and this was the conflict, this was why they wanted to destroy the Jews, because two peoples cannot be the chosen people of God; one has to be completely erased. When Adolf Hitler succeeded in killing six million Jews it became more and more certain to the Germans that he was right, because God was not protecting the Jews and he was not punishing Adolf Hitler either." (The Rebel, pege 157)

ስለ ኢትዮጵያ ደግሞ እንዲህ ተብሏል፦

ኢትዮጵያውያ"የእግዚአብሔር ገነት" የተተከላባት አዳምና ሔዋን የተፈጠሩባት አገራቸው የምትገነው በምድር ማዕከል ወይም መቀነት ክልል ውስጥ ስለኾነ የጊዜ አቈጣተራቸው ስርዓተ መዓልቷና ሌሊቷ ዓመቱን ሙሉ በ12 በ12 ሰዓታት እኩል በተከፈለበት የአሰፋፈር ስልት ላይ ተመስርቶ የባህረ ሓሳቡ ቅመራ ስርዓን ጠብቆ ያለችግር ይካሔዳል። (ኢትዮጵያ የአለሙ መፍረጃ፣ 2010 ዓ.ም፣ 150)

ላለፉት ኹለት ሺህ አመታት እኔ በእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ ከእውነት የኾነ ኹሉ ድምፄን ይሰማል ብሎ የተናገረ የመለኮትነት ባህርይ ያለው ሰው የኾነ አምላክ ከይሁዳ ነገድ የተገኘና ድል አድራጊ የኾነ አንበሳ፣ የዳዊትና የቤትሳባ፣የሰሎሞንና የማክዳ ዘር ኾኖ በመጨረሻ ከድንግል ማርያም የተወለደ ስሙም ኢየሱስ ተብሎ የተጠራ የጽዮን ንጉስ፣ ኢትዮጵያና እንዲሁም በሰማይና በምድር የፍጥረቱ ኹሉ ንጉሰነገስት የኾነ፣ በዚህ ማንነቱም በመላው ዓለም ሰው ዘር ዘንድ በአብዛኛው ተቀባይነትን ያገኘ እንዲህ ያለ ኢትዮጵያዊ መሲህ በፊታችን በሕያውነት ቆሞ የሚገኝ ሲኾን ታዲያ እናንተ ለምንድር ነው ሌላ አምላክ ለማድረግ የምትፈልጉት? (ኢትዮጵያ የአለሙ መፍረጃ፣ 2010 ዓ.ም፣ 204)

፮ የቅዱሳን አማላጅነት እና የክብር ደረጃ

<<እንደ ሃጢአቴ ብዛት እንደ በደሌማ

የጥልቁ ሰንሰለት ሲያንሰኝ ነው ጨለማ

ግን ያንቺ ሆንኩና ሁሉንም አለፍኩት

ያንን የሞት ባህር በምልጃሽ ቀዘፍኩት . . .

እጅግ ብዙ ነገር አድርገሽልኛል

Created in Master PDF Editor

ይቅር ባይም ልጅሽ በፍቅር አይቶኛል

እኔስ እኖራለሁ ድንግል ባንቺ ጥላ

ጨለማን አላይም ከእንግዲህ በኃላ . . . >>

(ምንጭ፦ ዛሬም አለሽ በልቤ ከተሰኝ መዝሙር የተወሰደ)

የምልጃን አስፈላጊነት በተመለከተ ዲ/ን ያረጋል መናፍቃን የሚከተለውን ክስ ያቀርባሉ ይላል። ክሱ በእውነት ተገቢነት ያለው ቢሆንም ዲ/ን ያረጋል መድሎተ ጽድቅ ሲል በሰየመው መጽሃፉ በሰፊው ሞግቷል። ክሱ ምን ነበር?

> “…ሙስናን በእግዚአብሔር መንግስት የሚሰራበት ህግ አስመሰለው በሀይማኖታቸው እስተምሮ ውስጥ ሰፊ የትምህርት ምዕራፍ የሰጡ ቡድኖች እንዳሉ አሰተውላችሁ ታውቃላችሁን? በመላዕክት፣ በጻድቃን፣ በሰማዕታት ስሞች የተደረሱ ገድላት፣ ታምራት፣ ድርሳናት ወዘተ በመላ የሚታወቁት መንፈሳዊ መሰል መጻሕፍት ሁሉ ሙስና በእግዚአብሔር መንግስት የተፈቀደ ህጋዊ ስርዓት እንደ ሆነ አስመስለው ይናገራሉ። መጽሀፍ ቅዱስ እድል ፈንታ የላቸውም የሚላቸው ነፍስ ጉዳዮች፣ አመንዝራዎች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ ሌቦች፣ ቀማኞች በጠቅላላው ህገ እግዚአብሔርን የሚያፈርሱ ወንጀለኞች በእግዚአብሔር ባለሟሎች በኩል ከቅጣት ሊያመልጡ እንደሚችሉ ድርሳናትና ገድላት ይሰብካሉ። እንዲህ የሚያደርግ ሰው ህገ እግዚአብሔርን ማፍረስ ብቻም አይደለም፣ ስላሴን ቢክድ እንኳ በተከፈተው የሙስና መንገድና የስርቆሽ በር አልፎ ገነት መንግስተ ሰማያት ይገባል ይሉናል። 78 ሰዎችን የገደለ ስጋቸውን የበላና ስላሴን የካደ በላዔ ሰብእ በማርያም አማላጅነት ከእግዚያብሔር የቅጣት ፍርድ ማምለጡን ተአምረ ማርያም ይተርክልናል። መጠቆም የምንፈላገውም ሙስናን ከአገራችን መጥፋት የሚቻለው በእግዚአብሔር መንግስት ሙስና የተፈቀደና የሚሠራበት ህግ አስመስለው የሚሰብኩት መጸሀፍት በቅድሚያ ሲወገዙ ነው።” (ጮራ ቁ.30፣ ገጽ1-2 መድሎተ ጽድቅ ገጽ 341 እንደተጠቀሰው)

ሀይማኖቶች በተለይም የክርስትና ሀይማኖት ቅዱሳን አማላጅነት እና የክብር ደረጃ ላይ ከፍ ያለ ልዩነት አለው። ሲጀምር በህይወት ስጋ የሌሉ ሰዎች የማልዳሉ የሚለው ጥያቄ ያከራክራል። ሲቀጥል የሚያማልዱት በአካል ስጋ ሳሉ በፀለዩት ፀሎት ነው ወይስ አሁንም ስለ ሰዎች ይፀልያሉ የሚል ጥያቄ ይነሳል። በተጨማሪም ምልጃ በመሰረቱ አስፈላጊ ነውን? ፈጣሪ በምልጃ ይታረቃልን? መሰል ጥያቄዎች ይነሳሉ። ሌላው ደግሞ ይህን ምልጃ አስፈላጊ እንኳ ቢሆንና እግዚአብሔር ስለቅዱሳኑ ሲል የሚምር ቢሆን እንኳ ቅዱሳትን አማልዱን የመንለው እንዴት ነው? ማለቴ ቅዱሳን በሁሉ የሞሉ (ምሉዕ) ናቸው ወይ?

Created in Master PDF Editor

ቅዱስ ገብርኤል ሀዋሳ ላይ ሁኖ መቀሌ በስሙ የሚፀልይን ይሰማል ወይ? ቅዱስ ጊዮርጊስ አዲስ አበባ ሁኖ ጎንደር ላይ በስሙ የሚፀልይን ሽክሙ የከበደበት ፀሎተኛን ይሰማል ወይ? ይህ ጥያቄ ንቀት የሚመስላቸው የዋህዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን ያልተመለሰ መሰረታዊ ጥያቄ ነው። ሰዎች ስለ ቅዱሳን የሚነቅፉ ፅሁፎችን ሲያነቡና ስብከቶችን ሲሰሙ የሚበሳጩት ህሊናቸው ለትችቱ በቂ መልስ ስሌለው <የመሸነፍ መንፈስ> ስለሚወራቸው ነው። በእውቀት ላይ ተመስርተው ማርያም ታማልዳለች የሚሉ ሰዎች ማርያም አታማልድም የሚሉ ሰዎችን አይጣሉም። ሀ ሁ A B C D እንደሚያጣና ተማሪ በእምነት ብቻ የተባለውን የሚሉ ግን አማራጭ ስሌለላቸው ያስበረግጋሉ ወይም ይበረግጋሉ።

የቅዱሳንን ክብር አንዳንዶቹ ያበዙታል (በተለይ ኦርቶዶክሶች)፣ አንዳንዶቹ ግን በተቃራኒው ነገረ ቅዱሳንን ያቃልሉታል። እኔን ግርም የሚለኝ ቅዱሳንን አማልዱኝ ማለትና ከፍ ያለ ክብር መስጠት አይደለም፣ ይህን እኔም አደርገው ነበር፣ አሁንም በመጠኑ። ዛሬም ስምል እንኳ <<ማርያምን>> ካልኩ አበቃ የመጨረሻየ ነው። ማንነትን እስከማስረከብ ክብርን እስከመጣል የሚያደርስ አንዳች ነገር አለ ብየ አላምንም። ይህን ያልኩትየተክለኪዳን የ18 ዓመት ጸሎት ካነበብኩ ባኋላ ነው። እስኪ በጌታ እንዲህ ይጸለያል።

> <<እናንተ ቅዱሳን መላእክት፣ ጻድቃን፣ ሰማዕታት፣ ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ (የሥላሴ) ባለሟሎች ወዳጆች ሁሉ፤ እናንተም ክበሩልኝ ተመስገኑልኝ። እኔ ውዳቂ ባሪያችሁን እገሌን (ተክለ ኪዳን) ባርኩኝ፤ የምስራውን ስራ የማላውቅ ነኝና ቀኝ እጅ ሆናችሁ የምታስሩኝ እናንተ ሁኑ፤ የምናገረውን አላውቅምና አንደበት ሆናችሁ የምትናገሩኝ እናንተ ሁኑ፤ የማስበውን አለውቅምና አእምሮ ሆናችሁ የምታሳስቡኝ እናንተ ሁኑ እንጂ፤ እንደዚህች እንደምትፈሰው ዓይኔ፣ እንደሚፈረካከሰው ሥጋዬ፤ አሩን፣ ቅዘኑን፣ ጥምቡን ማቆሪያ እንደሆነው ሆዴ ፈቀድ ተመርቼ አንዳች የመስራት፣ የመናገር፣ የማሰብ ሥልጣን አይኑረኝ። እናንተ መርታችሁኝ የምታስሩኝ፣ የምታናግሩኝ፣ የምታሳስቡኝ ከሆነ ፍፁም የእግዚአብሔር የሆነውን ማከናወን እችላለውና። ምክንያቱም ፍፁም የምትሰሩለት እግዚአብሔር የሚያስራችሁን ነውና፤ የምትናገሩት እርሱ እግዚአብሔር የሚያናግራችሁን ነውና፣ የምታሰቡት እርሱ የሚያሳስባችሁን ነውና። ዓለሙንም የሰላም፣ የፍቅር፣ የበረከት፣ የእምነት አድርጉ። አቡነ ዘበሰማያት። ምስጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ ምስጋና ይሁን ለእመቤትዬ ቅዱሳን ድንግል ማርያም፤ ምስጋና ይሁን ለቅዱሳን መላእክት ጻድቃን፣ ሰማዕታት፣ ነቢያት፣ ሐዋርያት ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ለሥላሴ ባለሟሎችና ወዳጆች።>> (የመጨረሻው ፍርድ አፈጻጸም ውሳኔ፣ 2ኛ ዕትም፣ 76-77)

Created in Master PDF Editor

፯ የምንኩስና አስፈላጊነት

ምንኩስና ይላል ብሩህ አለምነህ

> “ምንኩስና የሰውን ልጅ ወደ ባህርያ መላዕክት ከፍ ያደርጋል ከሚል እምነት በመነሳት ነው ከፍተኛው ክርስትና ምንኩስና ነው የሚል አዲስ የክርስትና ትምህርት 3ኛውና 4ኛው ክ/ዘ ላይ በግብፅ መነኮሳት የተጀመረው፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትና ውስጥም ከፍተኛውን የስልጣን አካል የሚይዙት ፓትሪያርክ፣ የሲኖዶስ አባላት፣ የየሀገሩ ስብከት ጳጳሳት የገዳማት አስተዳዳሪዎችና አብዛኛዎቹ አብያተ ክርስቲያናት ኃላፊዎች መነኩሴ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቤተክርስቲያኗ በስርዓት ትምህርቷ ውስጥ መምህር ሾማ፣ ጉባኤ አስፍታ፣ ወንበር ዘርግታ በከፍተኛው የትምህርት ደረጃ ላይ መፃህፈ መነኮሳትን ማስተማሯ ለምንኩስና ህይወት ያላትን ታላቅ ቦታ የሚያሳይ ነው፡፡” (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 37)

በተለይዩ የሀይማኖት አይነቶች ብቻም ሳይሆን በክርስትና ውስጥ ባሉ በርካት የእምነት ተቋማትም ምንኩስና ላይ ትችት ይሰነዝራሉ፣ ከመሰረቱም አስፈላጊ እንዳልሆነ ይሰብካሉ፡፡ ምንኩስናን የሚተቹ ክርስትና ምንኩስናን አይደግፍም ብለው ቢከራከሩም የመፅሐፍ ቅዱስ ለምሳሌ በማቴወስ ወንጌል 19፣21 እንዲህ ይላል፦ “ፍጹም ልትሆን ብትወድ፥ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፥ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፥ መጥተህም ተከተለኝ፡፡”

ከማንም ምንኩስና አያስፈልግም ከሚል ተንታኝ በለይ ፈላስፋው ዘርዓያዕቆብ በምሬት ተቃውሞታል፣ ተማሪው ወልደ ህይወትም እንደመምህሩ ነበር፡፡ ብሩህ አለምነህ ስለፈላስፋው ሲነግረን እንዲህ ይላል፦ *“ፈላስፋው የሰው ልጅ በእግዚአብሔር የተፈጠረ የነፍስና የስጋ ውህደት ውጤት ነው በሚለው ነገር ይስማማና፤ ሆኖም ግን፤ መንፈሳዊ ከፍታን የምንመጣው የስጋን ፍላጎትና ስሜታችንን ስንጨቁን ነው በሚለው ሀሳብ ግን አይስማማም፡፡ ዘርዓያዕቆብ ከክርስትና ዲቦ አካላዊ ልዩነት የሚፈጥረው እዚህ ላይ ነው፡፡ ኦሪትንና ወንጌልን እንዲተች ያደረገውም እዚህጋ የፈጠረው ልዩነት ነው፡፡”* ይለናል፡፡ (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 27)

በመሆኑ ዘርዓያዕቆብና የወልደ ህይወት ምንኩስናን የሚቃወሙት ለምንድን ነው? ብሩህ አለምነህ ምንኩስና ስላደረሰው መዘዝና የፈላስፎቹን ጥሪ እንዲህ ይተነትነዋል፡፡

> “ምንኩስና የዓለም ተቃዋሚ ስለሚያደርገን የምንኩስና ህይወት አንድ ማህበረሰብ ውስጥ ማህበራዊ ተቀባይነት አግኝቶ ከተስፋፋ ያ ማህበረሰብ ሰርቶ ኑሮውን ለማሻሻልና ህይወቱንም ለማበልፀግ ያለው ውስጣዊ ተነሳሽነት ይሰለባል፡፡ በዚህም ኑሮው ይቆረቁዛል፤ ሀገርም ትደኸያለች፡፡ ኋላ ቀርናትና ድንቁርንም ይሰለጥንባታል፡፡ የዘርዓያዕቆብና የወልደ ህይወትም ተቃውሞ ይኸው ነው፡፡ ስርዓት ምንኩስና በ9ኙ ቅዱሳን አማካኝነት ገና ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቱ በተከታታይ የነገሱ አራት ነገስታትን ከነቤተሰቦቻቸው ሀገራዊ ሃላፊነታቸውን ትተው እንዲመነኩሱ አድርጓል፡፡ የመሪዎቹን መመንኮስ የተመለከተው የሀገሬው ህዝብም ስራውን ትቶ፣ ሀብትና ንብረቱን ጥሎ፣ ቤተሰቡንም የትም በትኖ ወደ ባህርየ መላእክት ከፍ በማለት

Created in Master PDF Editor

በየገዳሙና በየዋሻው መመነን ተያያዘው፡፡ በዚህም ከ9ኙ ቅዱሳን አንዱ የሆኑት አባ ጰንጠሌዎን ብቻ አፄ ካሌብን ጨምሮ 1500 ሰዎችን አመንኩሰዋል፡፡ ምንኩስና በእኛ ሀገር የተመረጡ የጥቂት ሰዎች የህይወት ምርጫ አልነበረም፤ የመለው ሀገሬው ህዝብ እንጂ፡፡ ምንኩስና ሰውን ወደ መላእክትነት ከፍ የሚያደርግ ከሆነ መላእክት መሆንን ማን ይጠላል? ይሄ ነበር በወቅቱ የነበረው የህዝቡ ስነ ልቦና፡፡ 9ኙ ቅዱሳን ሀገር ነው ያመነኮሱት፤ ኢትዮጵያን ነው ያመነኮሷት፡፡ ይሄ ነው የዘርዓያዕቆብ የወልደ ህይወትም ተቃውሞ፣ እንደ ሀገር የተያያዝነው የብሕትውና ጉዞ ይብቃን፤ ከመንፈሳዊ ህይወታችን ጎን ለጎን ለአለማዊ ህይወታችንም ትኩረት በመስጠት ወደ ቀድሞው ገናናታችን እንመለስ፤ የሚል ነበር የፈላስፎቹ ጥሪ፡፡ (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 41)

ምንኩስናን አምሮ ስለሚቃወመው ስለፈላስፋው ዘርዓያዕቆብ ሰፊ ትንታኔ የሰጠውብሩህ አለምነህ በኢትዮጵያ የምንኩስናን ባህል መወለድና ማስፋፋት እንዲሁም ላሊበላዊነትንአስመልክቶም እንዲህ ተርኮታል፡-

6ኛው ክ/ዘ ሁለተኛው አጋማሽ ግን የነገስታቱም ሆነ የማህበረሰቡ አመለካከት ከቁሳዊ ኃይል ወደ መንፈሳዊ ጭምትነት መቀየር የጀመረበት ዘመን ሆነ፡፡ በዚህም የደቡብ አረቢያው የንግድ ማዕከልና የቀይ ባህሩ የንግድ መስመር በፐርሺኖች ተነጠቀ፤ እንዲሁም የእጅ ሙያዎችና ለአለማዊ ህይወት ብልፅግና መጣር የተንቋሸሸበት በአንፃሩ ደግሞ መንኩስናዊ የአለም አመለካከት ገዥ ሐሳብ ሆኖ የወጣበት ዘመን ሆነ፡፡. . . ነገስታቱ ፊታቸውን ሙሉ በሙሉ ከቁሳዊ ስልጣኔ ወደ መንፈሳዊ ህይወት ያዞሩበት ዘመን ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ከሀገራዊ ስልጣንና ዝና ይልቅ የግል ነፍሳቸውን ወደ ማዳን የዞሩበት እንዲሁም ከነ ቤተሰባቸው አለምን እየናቁ መመንኮስ የጀመሩበት ዘመን ነው - 6ኛው ክ/ዘመን፡፡ ስልጣን በህግ ሳይሆን በምንኩስና የተገራበት፤ በዚህም በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ በርካታ ነገስታት ስልጣናቸውን በገዛ ፈቃዳቸው በመልቀቅ የመነኮሱበት ዘመን ነው ለምሳሌ ዳግማዊ አፄ አለ አሚዳ፤ አፄ ካሌብ፤ አፄ ገ/መስቀልና አፄ አለ ገበዝ፡፡ በዚህም ከአለም አቀፍ ንግድ ተነጥሎ ገዳማትን ወደ ደቡብ ማስፋፋት የተጀመረበት ዘመን ነው፡፡ በወቅቱም ምንኩስና በፈጠረው የስልጣን ክፍተት የተነሳ የርስበርስ ጦርነት ሆነ፡፡ . . .

ይህ ዘመን በመንፈሳዊና በአለማዊ ህይወት መካከል ቅራኔ መፈጠር የጀመረበትና ይሄም ቅራኔ እያደገ የሄደበት ዘመን ነው፡፡ ይህ ቅራኔ ነው እንግዲህ የሀገሪቱንና የህዝቧን ቀጣይ ዕጣ ፋንታ የወሰነው፡፡ በዚህም ምንኩስናዊ በሆነው አዲስ ባህል የተነሳ አጠቃላይ ህዝቡ በመንፈሳዊ ህይወት እያደገ ሆኖም ግን በቁሳዊ ሀብቱ እየደኸየ የሄደበት፣ በሃይማኖታዊ ዕውቀት እየተራቀቀ ሆኖም ግን ለአለማዊ ዕውቀት እየደነቆረ የሄደበት፣ በፆምና በፀሎት እየበረታ ሆኖም ግን በእጅ ሙያዎች እየዘቀጠ የሄደበት የተቃርኖ ዘመን ነው፡፡ ይሄንን ነው ላሊበላዊነት የምንለው፡፡" (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 30-33)

እና ምን ተሻለን? ፈላስፋው ዘርዓያዕቆ መፍትሔ ሲጠቁም በሐተው ምዕራፍ 7 እንዲህ ይፈላሰፋል፣ እጅግ ማራኪ አተያይ ነው።

<<ከጋብቻ ይልቅ ምንኩስናን ይበልጣል ብለው የሚያምኑ እነርሱ በፈጣሪ ስራ ፅናት ወደ ጋብቻ ይሳባሉ። ፆም ነፍስ እንደሚያፀድቅ የሚያምኑ እነርሱ ደግሞ እረሃብ በበዛባቸው ጊዜ ይበላሉ። ገንዘቡን የተወ ፍፁም እንዲሆን የሚያምኑ በገንዘብ ለሚያገኙት ጥቅም ወደ ገንዘብ መፈለግ ይሳባሉ። ብዙዎች የሀገራችን መነኩሴዎችም እንደሚደርጉት ከተውት በኋላ እንደገና ይፈልጉታል። እንደዚሁ ዋሾዎች ሁላቸው የተፈጥሮን ሥራ ሊያፈርሱ ይፈልጋሉ።ነገር ግን ደካማነታቸውን ያሳያሉ እንጂ አይችሉም። ፈጣሪም ይስቅባቸዋል። . . . ስለዚህም የጋብቻን ሥርዓት የሚያስነውር መነኩሴ በክፉ በሽታና ፍጥረቱ ባልሆነ በሌላ የሴት አበሳ በዝሙት ተፅኖ ይጠመዳል። ገንዘባቸውን የሚንቁ ገንዘብ እንዲያገኙ በሀብታሞችና በነገስታት ዘንድ ግብዞች ይሆናሉ። ለእግዚያብሔር ብለው ዘመዶቻቸውንም በሽምግልናቸው በችግራቸው እረዳት ባጡ ጊዜ የተው በነሱ ሽምግልና ጊዜ ሰውና እግዚያብሔርን ወደ ማማት መሳደብይደርሳሉ። እንደዚሁም የፈጣሪን ሥርዓት የሚያፈርሱ ሁሉ በእጃቸው በሰሩት ወጥመድ ይወድቃሉ።>>

፰ የስርዓት አምልኮ ልዩነት

ሀይማኖት የሰው ልጆች ውብ ባህል በመሆኑ በጊዜ በቦታና በሁኔታ የሚለዋወጥ ነው። ምን አልባትም ሁሉንም ሀይማኖቶች የሚያመሳስላቸው ስርዓተ አምልእኮ አላቸው። ነገር ግን ከጥንቶቹ ስማቸው ብቻ ከቀሩት አማልእክት እስከ የዚህ ዘመን ታላላቅ ሀይማኖቶች ድረስ ሊታረቅ የማይችል የስርዓተ አምልእኮ ክንውን አላቸው። በተለይም በፀሎት፣ በፆም፣ በምፅዋት፣ በፍትሀት፣ በመሳለም፣ በማማተብ፣ በስግደት፣ በማተብ ማሰር፣ በብዓላት አከባበር፣ በቅዱሳን ቅርፅና ስዕል፣ በቁርባን፣ በታቦት አስፈላጊነት፣ በስርዓተ ጥምቀት፣ በሙዝሙር እና ምስጋና አቀራረብ፣ በንዋየ ቅድሳት አጠቃቀም እና በሌሎች የአምልእኮ ስርዓቶች አፈፃፀም ከፍተኛ መራራቅ ብቻ ሳይሆን መቃረንም ጨምሮ ይታይባቸዋል። የሚያሳዝነው በፖለቲካ አቋም የተለያዩ ሀይሎችን በድርድር ወደ አንድ ወደ ተሻለ አቋም መምጣት ይችላል። በሀይማኖት ረገድ ግን እንዲህ አይነት ድርድር ማሰብ አይታሰብም። ለዚህ ነው የሚበተን እንጅ የሚዋሀድ ሀይማኖት የሌለው። የተለያየ ሀይማኖት በዚያው ልክ የተለያየ የዓምልእኮ ስርዓት መኖር ከባህልና ከማህበራዊ ሳይንስ አንጻር መልካም ነው። ከእውነት አንፃር ግን በምንም አይነት አተያይ የተለያየ የአምልእኮ ስርዓት ያላቸው አካላት የሚያመልኩት አንድ አምለክን ነው ማለት አይችልም። እውነት የፖለቲካ ትርፍ ለማትረፍ ሁሉንም አትደልልም፣ የሆነችውን ብቻ ነው የምትሆነው። የዋሆች አላህም፣ እግዚአብሔርም፣ ዋቄፍናም፣ ሌሎችም የአንድ ፈጣሪ የተለያዩ ስሞች ናቸው ቢሉም እውነት ግን በየዋህነት የሚያለባብሷት ተደላይ አትመስለኝም።

Created in Master PDF Editor

2. **አሁን ካሉት ብዙ ሐይማኖቶች መካከል እውነተኛው የቱ ነው?**

<<ቤተ ክርስቲያን ሆይ ምነው ተረበሽ

አንድነትሽ ጠፍቶ ሰላምን አጣሽ

አንደኛው ሲጠቅምሽ ሌላኛው ሲጎዳሽ

ብዙ ልጆች ወልደሽ የወላድ መካን ሆንሽ::

በዘርና ጎሳ ስንከፋፈል

ቅጥራችን ፈረሰ በጠላታችን

መሳለቂያ ሆነን በየአደባባዩ

ልዩነትን አይተው ብዙዎች ተለዩ::

ላያችን የሚያምር ልስን መቃብሮች

አስመስለን ያለን የሀሰት አማኞች

በመካከላችን ፍቅርን አስወጥተን

እንደ ርብቃ ልጆች እንገፋፋለን::

ለፅምነት ያልቆመው በውሸት ሲከሰን

አንድነት ሳይኖረን ዘመንን አስቆጠርን

ያ ጥቅም ፈላጊው ሰምን እያጠፋ

ለስጋው የሚሆን ርስቱን አሰፋ::>> (ምንጭ፦ አንድ አድርገን መዝሙር)

ማን ይጠየቅ?

<<በ1054 ዓ.ም ግሪኮች ከካቶሊካውያን ተፅእኖ ነፃ ከወጡ በኋላ የሮም ካቶሊካዊት የእምነት ተቋም ውስጣዊ ብልሽት ገጠማት:: ከእነዚህ ብልሽቶች መካከል የካቶሊካውያንን የእምነት አስተዳደር ከሚመሩት ጳጳስ ጀምሮ እስከ ታችኛው ተራው ሰባኪ ድረስ በትንሹም በትልቁም መማለጃ የሚቀበሉ፤ በእውቀታቸው እና በስነ ምግባራቸውም ቢሆን ስልጣን ክህነት ከሌላቸው ምዕመናን የማይሻሉ፤ ፈፅሞ ለመነኩሴ የተከለከለውን ጋብቻ በስውር የሚያገቡ፣ በድብቅ ልጅ የሚወልዱ፣ ጳጳሳቱ ምንም ዕውቀት የሌላቸውን ዘመዶቻቸውን እና የሚቀርቧቸውን አላዋቂዎች ጵጵስና የሚሾሙ፣ ሌላው በእውቀቱ ለመሾም የሚመጣውን ከፍተኛ ገንዘብ ጉዞ የሚጠይቁ፣ በቤተክርስቲያኗ ስም ከምእምናን የሚሰበሰበውን ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው የሚያውሉ በአጠቃላይ ከክርስቲያናዊ ስነ-ምግባር ውጭ የሚንቀሳቀሱ ነበሩ:: በአስተዳደርም ቢሆን መልካም አስተዳደር ያልሰፈነበት፣ የእምነት ተቋሚ ባለተማሩ ሰዎች የምትመራበት፣

Created in Master PDF Editor

ፈላጭ ቆራጭነት የበዛበት፣ በዚህ እና በመሳሰሉት ምክንያቶች ቀስ በቀስ ምዕመናኑ እና በእምነት ተቋሟ ውስጥ የሚያገለግለው አመራር ሆድና ጀርባ የሆኑበትና የተለያዩበት ሁኔታ እየተከሰተ መጣ።

የቤተ መንግስቱን ፊውዳል ነገስታቶች ከጎናቸው ያደረጉት የካቶሊክ እምነት መሪዎች በማን አለብኝነት የእምነት ተቋሟን እንደፈለጋቸው ይቀልዱባትን ያዙ። ይህንን ያልተገባ ድርጊት የተመለከቱት የእምነቷ ተከታዮች በተለይ የተማረው ክፍል ተቃውሞውን በተለያዩ መልኩ መገልፅ ጀመረ። ይህንን የእርስ በእርስ አለመግባባት የእምነቱ መሪዎች በብስለት ተረጋግተው ከመመለስ ይልቅ እጅግ አሰቃቂ እና ዘግናኝ እርምጃዎችን በእምነቱ ተከታይ ምእመናን ላይ ወሰዱ። ለምሳሌ ጆን ውክሊፍ (1320-1384) የተባለው እንግሊዛዊ የካቶሊክ ሰባኪ የእምነት ተቋም የነበረባትን ችግር በማጋለጡ በህይወት ቢያመልጣቸው ሬሣውን ከመቃብሩ አውጥተው እንዲቃጠል አደረጉ። ጆን ሁስ (1370-1415) የተባለውም በእሳት አቃጥለው በአደባባይ ገደሉት። ጌርላሞ ሳባናሮላ (1452-1498) የተባለውን ሰው በአደባባይ በስቅላት ከገደሉት በኋላ ሬሣውንም በእሳት አቃጥሉ። በጣም ብዙ የእምነት ተቋምን መሪዎች እና አገልጋዮች ስህተት የተረዱ ፀረ-ካቶሊክ አካሄዳቸውን በመቃወማቸው ምክንያት በጳጳሱ ውሳኔ በአደባባይ ተገደሉ፣ ተሰቀሉ እንዲሁም ተቃጠሉ።

እነዚህ የእምነት መሪዎች ስህተታቸውን ከማስተካከል ይልቅ በዚህ መልኩ ቀስ በቀስ ወደ ባሰ ስህተት ውስጥ ጭልጥ ብለው ገቡ። ዓለማዊ ድሎት እና ምቾት እንዲሁም የገንዘብ ፍቅር አይናቸውን ያሳወራቸው የእመነቷ መሪዎች ሌላ ዘዴ ዘየዱ። ይኸውም፣ የገነት መግቢያ ትኬት እንዲሸጡ በየአገሪቱ ያሉ የእምነት ተቋማት ሰባኪዎች ከጳጳሱ ጥብቅ መመሪያ ተላለፈላቸው። ቀሳውስቶቹም የገነት መግቢያ ትኬቱን ለህዝብ መሸጥ ጀመሩ። እንደ እምነቱ መሪዎች አባባል ትኬቱን የገዛ ሰው በቀላሉ ወደ ገነት መግባት ይችላል። ለሞቱትም ዘመዶቻቸው ከገዙ ከመካነ ንስሃ ወደ ገነት ይገባሉ በማለት የእምነቱን ተከታዮች ማጭበርበር ሰፊ የስራ ድርሻቸው ሆነ። በመሪዎቹ ገደብ የለሽ ብዝበዛ እና ጭቆና የተማረረው የእምነቱ ተከታይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየባሰ የመጣውን ዘረፋ ፍፁም መታገስ ስላቃተው ውስጥ ውስጡን ማማረር እና እርስ በእርስ በለሆሳስ መነጋገር እና መወያየት ጀመረ። በዚህ ወቅት ደፋሩ ጀርመናዊው መነኩሴ ማርቲን ሉተር (1483-1546 እ.ኤ.አ) የእምነት ተቋሟን ድክመት በይፋ በማጋለጡ ለዘመናት ሆድ የባሰው ተከታይ ‹ሆ› ብሎ ደገፈው፣ በዚህ ሁኔታ እንግሊዝ፣ ፈረንሣይ፣ ጀርመን ከጨቋኝ እና ከዘረኛው የሮማው ጳጳስ አመራር ራሳቸውን አገለሉ። ከ1517 ዓ.ም /እ.ኤ.አ/ በኋላ <u>በካቶሊክ የእምነት መሪዎች ስህተት ምክንያት በክርስትና ስም ብዙ እምነቶች በፈጣሪዎቻቸው ተፈጠሩ።</u>>>

(ምንጭ፦ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ን አበይት ፈተናዎች ገጽ 166-169፣ በካሳሁን ደምሴ)

Created in Master PDF Editor

“In fact, Islam is the Truth that all the original inspired Books teach. It meets with humanity demands, scientific conclusions and faithful happiness, away from tales, fairy-tales and fallacies.” (Islâm and Science, page 407)

“ሰዎች እውነቱን ከሐሰቱ ለመለየት አልመረመሩምና አላወቁም። ያለ ምርመራ ከፊተኞቻቸው የሰሙትን አምነው ተቀበሉ። ስለዚህም የአይሁድ ልጆች አይሁዶች፣ የክርስቲያን ልጆች ክርስቲያን፣ የእስላም ልጆችም እስላም ሆኑ። እነርሱ የአባቶቻቸው ልጆች ናቸውና። ይህ ካልሆነ በስተቀር ለሃይማኖታቸው ሌላ ምክንያት የላቸውም በትንሽነታቸው ጊዜ የአባቶቻቸው ሃይማኖት እውነት እንደሆነ ሰምተዋል። ሳያውቁትና ሳይመረምሩትም በአባቶቻቸው ሃይማኖት አመኑ። ሁላቸውም እውነት ነው እያሉ ስለሃይማኖታቸው እርስ በእርሳቸው ይከራከራሉና እውነተኞች ሊሆኑ አይችሉም። ሐሰት ብዙ ሲሆን እውነት ግን ብቻዋን አንዲት ናትና፤ ሁላቸው ግን ሐሰተኞች ሊሆኑ ይህ ይቻላል።” ፈላስፋው ወ/ህይወት- (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 285)

“If we are living in the Age of Science, then why do so many pseudoscientific and nonscientific beliefs abound? Religions, myths, superstitions, mysticisms, cults, New Age ideas, and nonsense of all sorts have penetrated every corner of both popular and high culture.”- Michael Shermer, Why people believe weird things

የሙስሊም ሙህራን እንዲህ ይላሉ *“እንደሚታወቀው ዱናችን (ሀይማኖታችን) ኢስሊም ምለዕ ነው። ስለሆነምለሁለም የአምልኮ ዘርፎች እንዱሁም የህይወት መስኮች ደንቦችንደንግጓል ስርዓቶችንም አስቀምጧል። ሕግጋቶቹ ፍትሀዊ እና ሚዛናዊ ስርዓቶቹምለሁለም ቦታ እና ዘመን የሚበጁ ናቸው።”* መጨመርንም ይሁን መቀነስን አይቀበልም እንዱሁም ከሌሎች መኮረጅንም ሆነ መመሳሰልን ይከለክላል ይላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ በቅርብ አመታት ፈጣሪ ለተክለ ኪዳን እንደነገረው ትክክላኛዋ ሀይማኖት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ብቻ ናት። ስሙት የሚለውን፦*“ስለዚህ ሁላችሁም ከዚህ የሞተ ሕይወት ራሳችሁን ለይታችሁ በእኔ በአንዱ እግዚአብሔር ብቻ አምልኩ። ሃይማኖታችሁም በነበረቸው፣ አሁንም ባለቸው፣ እሰከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በምትኖረው፣ እኔ በደሜ በመሰረትኳት፣ ሐዋርይት ደቀመዛሙርቴ በሰበኳት፣ አበው ሐዋርያት ባስፋፏት፣ ሰማዕታት በተጋደሉላት፣ ጻድቃን ባጸኗት፣ ሊቃውንት መምህራን ባስተማሯት ብቸኛዋ የሕይወት መንገድበኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ስር ሆኖችሁ፤ እንደ እምነቱ ሥርዓት በመመላለስ እንደ ቃሌ ኑሩ። ያኔ በሥጋችሁ በረከትን፣ በነፍሳችሁ ድኅነት ታገኛላችሁ። ከዚያ ውጭ በሥጋም በረከት፣ በነፍስም ድኅነትን አታገኙም። እውነተኛውን ሰላም፣ ፍቅር፣ ደስታና እርካታ የምታገኙት*

Created in Master PDF Editor

በዚህችው ቀጥተኛዋ ተዋሕዶ ሃይማኖት ብቻ ነው፡፡(የመጨረሻው ፍርድ አፈጻጸም ውሳኔ፣ 2ኛ ዕትም፣ 33)

ከተለያዩ ምንጮች እንዳገኘሁ በአሁኑ ወቅትክርስትና 2.2 ቢልዮን ተከታዮች፣ እስላምና 1.6 ቢሊዮን፣ (ሀይማኖት የለሽ 1.1 ቢሊዮን)፣ ሂንዱይዝም 1.1 ቢሊዮን በተጨማሪም ከ15 የማያንሱ ሌሎች ሀይማኖቶች ከ400 ሚሊዮን እስከ 500 ሽ የሚደርሱ ተከታዮች አሏቸው፡፡ በእነዚህ ሃይማኖቶች መካከል ያለው ልዩነት ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ አንዳንዶቹም ከዚ ሕይወት በኂላ እንደገና በሌላ አይነት ተፈጥሮ እንመለሳለን ይላሉ፤ ሌሎች አይደለም እኛ እራሳችን እንደገና እንነሳለን ይለሉ፡፡ በሌላ ጎራም ፈጣሪ አንድ ነው፣ ሁለት ናቸው፣ ሦስት ናቸው እና ብዙ ናቸው የሚል አለመተማማን አለ፡፡ እንኳን በእነዚህ ፍፁም በተለያዩ እምነቶች ቀርቶ በአንድ ፕሮቴስታንት እና በሌላኛው ፅንፍ ፕሮቴስታነት መካከል ለድርድር የማይቀርቡ ልዩነቶች አሉ፡፡ ሁሉም የገነት ቁልፍ በእጃቸው እንዳለ በሙሉ መተማመን ይሰብካሉ፣ ከአጥሩ ውጭ ያሉትን የግሃነብ ደጆች ይሏቸውል፡፡ በዚህ ሂሳብ ወደ ሲኦል የሚተመውን የሰው ብዛት አቆጣጠሩ*"ስንት ነፍስ ደግሞ ወደገሃነም እንደሚገባ ለማወቅ በመጀመሪያ ስንት ሀይማኖቶች ዛሬ በምድር ላይ እንዳሉ ማስላት ይገባል፡፡ ብዙዎቹ ሀይማኖቶች ደግሞ የእነሱ አባል ካልሆነክ ወደገሃነም እንደምትገባ ይነግሩሃል፡፡ ከዚህ ተነስተን ስናስብ አንድ ሰው አባል መሆን የሚችለው ደግሞ ለአንድ ሀይማኖት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም የሌላ ሀይማኖት አባል ስለሆነ ገሃነም እንዲገባ ተፈርዶበታልና ሁሉም ነፍስ ገሃነም ይገባል ማለት ነው፡፡ በምድር ላይ ያለውን የውልደትና የሞት ፍጥነት ተመልክተን ገሃነም የሚገባውን ነፍሳት ብዛት ደግሞ መገመት እንችላለን፡፡"* (ጥበብ ቅጽ አንድ፣ 2009፣ 136) ይህን ሰቆቃ የሚያመጣውን ሀይማኖት ነው ማርክስ *"religion equated with projection and fantasy wish-fulfillment. It distracted man from creating a world free of oppression. Religion is the sigh of the oppressed creature, the heart of a heartless world, just as it is the spirit of a spiritless situation. It is the opium of the people. The abolition of religion as the illusory happiness of the people is required for the real happiness."* ያለው፡፡

ሃይማኖት ለምን ተለያየ?

> *"religion as any set of beliefs that contains rituals, deities, and an afterlife that includes the concept of a soul; **ritual** to be a prescribed set of ceremonial behaviors; a **deity** to be a being who is worshipped and has authority over certain aspects of life; **souls** to be the animating essence of a person that distinguishes them from others; and an **afterlife** in which the soul separates from the physical body*

Created in Master PDF Editor

and survives the death of the body." (The Invention of Religion, by Alexander Drake)

በፍልስፍና የማስተርስ ድግሪ መመርቂያ የምርምር ጽሁፍ አቅራቢው ወርቁ ፈቀደ B.A. Robinson የተባለ ጽሃፊን ጠቅሶ "Religion and Its Impact upon the Realization of Human Actual and Potential Capacities" ሲል በሰየመው ጥናቱ ስለሃይማኖት አመጣጥ የሚከተለውን ብሏል።

> *"In the history of human society, no one knows with accuracy about how the first religious system was started. However, there were some assumptions which claim that religion was started in reaction to human fear and anxiety. It was projected by humans to insure the feeling of security and control over nature. This was because, nature was challenging and too tough for men and there was little control over it. Humans were extremely suffering from the strong power of nature. People had lost their life due to Earth quake; volcano, and thunder. Fierce animals like lion, hyena and Tiger snatched their life. At a time, human's life was shrouded in haze from different corners. Hence, the question of people's need of survival and security demands them to conceive imaginary superman (God) which assumed to be almighty and powerful in avoiding insecurity and preserving human life. (Worku Fekade፣2015፣page 1).*

የሸገር ብሎጉ ጦማሪ አገኘሁ አሰግድ እንዳለው የሰው ልጅ ሃይማኖት የመፍጠር ሱስ ያለው ይመስላኛል።ለዚህም ነው ኢ-አማኞች እንኳ ሳይቀር አምላክ ከሌለ ዛሬውኑ መፈጠር አለበት ያለሱ መኖር የማይቻላቸው አሉና የሚሉት። ግን ለምን የሌለን ነገር እንዲኖር ሱስ ይሆነናል። ኒቼ ምን ነበር ያለው "የሰው ልጅ ብዙ ውሸት የሚዋሸው ለራሱ ነው፣ ለሌላ ሰው የሚናገረው ውሸት በአንጻሩ ኢምንት ነው!"

በቤተ እምነቶች ምን ያህል ልዩነት እንዳለ አንድ የጎልጉል ድህረ ገጽ ሃሳብ ሰጭ ያለውን ላስታውስ "አንተም በመጋዘንህ እኛም በቤተ መቅደሳችን ቃለ እግዚአብሄርን ሰምተን በልቦናችን ጽላት እንዲጽፍልን እንጸልይ" (ጎልጉል የድህረ-ገፅ ጋዜጣ)

ጽሃፊው ካሳሁን አለሙ በተጠየቅ ድህረ ገጹ በሃይማኖት አምዱ "የሰው ልጅ በዓለም ላይ ሲኖር በባህል፣ በልምድ፣ በግንዛቤ መለያየትና በቀደምት ትውልዶች አስተሳሰብ ተፅዕኖ እንደሚደረግበት ይታወቃል፡፡፡ ይህ ደግሞ የአምልኮ ሥርዓትና የዶግማ መለያየትን እንደሚፈጥር ይነግረናል። በዓለም ላይም የተለያየ ሃይማኖት መኖሩ እርግጥ ነው። ይህንን መለያየት በማየት የሚመለከው እግዚአብሔር አንድ ኾኖ እያለ ለምን ሃይማኖት እንደዚህ ሊለያይ ቻለ?" በማለትም ይጠይቅና ልዩነቱን የወለዱትን የሚከተሉት ምክንያቶች እንደሆኑ ይዘረዝራል።

Created in Master PDF Editor

በሰው ልጆች ፍላጎት መለያየት፡- ሃይማኖት ከሰዎች አመለካከት ጋር የተያያዘ በፍላጎት የሚቀበሉት ነገር ነው፡፡ በመኾኑም ሰዎች አመለካከታቸው በመለያየቱ የሚከተሉት ሃይማኖትም በፍላጎታቸው ላይ ተመሥርቶ መለያየቱ የግድ ይኾናል፡፡

መልስ፦ በእኔ እይታ ግን አምላክ ሁለንታናዊ ስለሆነ ሀይማኖትም ሁለንተናዊ መሆን አለበት፡፡ ቢያንስ በመሰረታዊ ዶግማዎች መለያየት አልነበረበትም፡፡ ነገር ግን ሀይማኖት የሰው ልጆች የፈጠራ ውጤት ነው ብለን የምናስብ ከሆነ በሰው ልጆች ፍላጎትም መለያየቱ አይቀሬ ይሆናል፡፡

የሰው ልጅ በነፃ አዕምሮው በመምረጥ የሚያምን መኾኑ፡- ሰዎች በፈቃዳቸውና በነፃ ምርጫው ተመሥርተው ነው ዕምነታቸውን የሚወስኑት፡፡ በነፃ ምርጫቸው በመጠቀምም የሚፈልጉትን፣ ቅርብ የኾኑለትንና ተፅዕኖ ያደረገባቸውን ሃይማኖት መርጠው ያምናሉ፡፡ ነፃ ምርጫም የኹኔታዎች ተገዥ ስለኾነ ሰዎች ተገዥ በኾኑበት ነገር ላይ ተመሥርተው እምነታቸውን እንዲመርጡ ያደርጋቸዋል፡፡ በዚህ የተነሳም ሃይማኖት እንደ ኅብረተሰቡና ሰዎች ልዩነት ሊለያይ ችሏል፡፡

መልስ፦ የአለም ህዝብ በአብዛኛው ሀይማኖቱን የወረሰው ከወላጆቹ ወይም ከአሳዳጊው ነው፡፡ ከሙስሊም የተወሰደ ሙስሊም ይሆናል፡፡ ከአይሁድ የተወለደ አይሁድ ይሆናል፡፡ ከክርስቶያኖች የተወለደ ክርስቲያን ይሆናል፡፡ ከዚህ በመነሳት አብዛኛው ህዝብ የሚያምነው የቤተሰቦቹን ሀይማኖት መሆኑ በህፃንነቱ ያለምንም ነፃ ምርጫ ሀይማኖታቸውን መቀበሉን መረዳት ይቻላል፡፡ ቅዱሳን መፅሀፍትም በነፃ ምርጫ አያምኑም፡፡ ሁሉም ያልተቀበሏቸውን ያስፈራራሉና፡፡ ስለዚህ ሀይማኖቶች የበዙት፣ የተባዙት ነፃ ምርጫ ስላለ ሳይሆን የጋራ አንድ ገዥ አስተሳሰብ ስሌለለ ነው፡፡

የሰው ልጅ ስህተት ፈፅሞ የሚኖር መኾኑ፡- በክርስትና ሃይማኖት ዕይታ የሰው ልጅ በምድር ላይ መኖር የጀመረው ስህተትን ከፈፀመ በኋላ ነው፡፡ በዚህ ዓለም ላይ ሲኖርም ብዙ የዕለታዊ ሥራዎችና የታሪክ ውርሶች ተፅዕኖ ያደርጉበታል፡፡ በዚህ የተነሳም አዕምሮው እየዛገ በመሔዱ የፅሑፍ ሕግ በዕየለቱ እየተመለከተ እንዲያስታውስ ተደርጓል፡፡ በመኾኑም የሰው ልጅ ስህተትን ከፈፀመ በኋላ ያለው ሕይወቱ በስህተት የተሞላ ሊኾን ችሏል፡፡ ይህም የተለያየ ሃይማኖትንም እንዲፈጥር አድርጎታል፡፡

መልስ፦ በትክክል የሰው ልጅ ምሉዕ ባለመሆኑ ይሣሣታል፡፡ የተሣሣተውንም ያርማል፡፡ አዕምሮው እየዛገ ሳይሆን እያደገ በሄደ ቁጥር የቀደሙትን ስህተቶች ለማረም ይነሣሣል፡፡ በዚህ መሀል በነባሩና በአዲሱ አስተሳሰብ መካከል አለመግባባት ይፈጠርና ከሁለት ይከፈላል ከዚያም በማያቋርጥ ክፍፍል ውስጥ ይገባል፡፡

Created in Master PDF Editor

የሰው ልጅ አኗኗር በሕግና በልምድ እየተለያየ መሔድ፡- ሰዎች በመኖሪያ አካባቢያቸውና በአኗኗር ስልታቸው ይለያያሉ። በመኾኑም በዓለም ላይ አንድ ተመሳሳይ የኾነ ነገርን በተለያየ መንገድ ሊገልፁትና ሊተገብሩት ይችላሉ። ይህም ከታሪካዊ ቆይታ ጋር ተያይዞ ልምድ ይኾናል። ሃይማኖትም በዚህ ልምድና አኗኗር ሥርዓት ተገኘ ነው። ይህ በመኾኑም በዓለማችን ላይ የሃይማኖት መለያየት ሊፈጠር ችሏል።

መልስ፡ በትክክል የሰው ልጅ ለማዳ እንሰሳ ነው። አምርሮ የሚጠላቸውን የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ሀይማኖታዊ ጉዳዮች ቀስ በቀስ ይለመደቸውና የራሱ ያደርጋቸዋል። በአለም ታሪክ ውስጥ ከምንረዳው መሰረታዊ ነገሮች አንዱ የስልጣኔና የባህል መወራረስ ነው። ለዚህም ነው በጥንታዊ ስልጣኔ ሳይቀር በዝርዝር ጉዳዮች ልዩነት ቢኖርም የስነ-ህንፃ፣ የስነጥበብ፣ የባህልና የእምነት ተመሳሳይነቶች ጎልቶ የሚታየው ሀይማኖቶችም ከአንድ ቦታ ተነስተው ወደ ሌሎች አካባቢ ሲሰራጩ መልካቸውን በተወሰነ መልኩ ይቀየራሉ ከዚያም ከረዥም ጊዜ በኋላ የተለያዩ ሀይማኖቶች ይሆናሉ።

በሰይጣን መኖር፡- በዓለማችን ላይ ሰዎች በስህተት ጎዳና እንዲጓዙ የሚያደርግ ሰይጣን የሚባል እርኩስ መንፈስ አለ። የእሱም ዓላማ ሰዎች ከመልካምነት ርቀው ከአምላካቸው እንዲለዩ ማድረግ ነው። በዚህ ተግባሩም የሰዎች እምነት የተለያየ እንዲኾን በማድረግ ያሳስታል። በመኾኑም በዓለም ላይ የተለያዩ ሃይማኖቶች እንዲፈጠሩ አድርጓል። ለዚህም በአንድ መጽሐፍ ቅዱስ የሚመሩ ክርስቲያኖች የተለያየ እምነት መከተላቸው ጥሩ ማሳያ ነው። ስለዚህ ሰይጣን በዓለም ላይ መኖሩ ለሃይማኖት መዛባትና መብዛት ምክንያት ነው።

መልስ፡ ሰይጣንን የማይወቅ አማኝ አላጋጠመኝም። ለሁሉም ጥፋት ሰይጣን ይወቀሳል። እውነት ሰይጣን የለም እንጅ ቢኖር የተሻለ ነበር ለምን ቢባል ወደ ተሻለ እውቀትና ብልጽግና የሚመራ መንፈስ ስለሆነ። የእውቀትን ዛፍ ፍሬ የሚመግብ ስለሆነ። የመጀመርያው አብዮተኛ ስለሆነ። ሀይማኖቶች እንደ <ዋልካ> መሬት የተሰነጣጠቁት በሳይጣን ስም ሳይሆን በእግዚአብሔር ስም ነው። አለ ብለን ካሰብን ሰይጣን ተወቃሽ ሳይሆን የሰው ልጅ ባውለታ ነው። እግዚአብሔር እውር አድርጎ ፈጠረን ሰይጣን ግን የእውቀትን ብርሃን አበራልን፣ የዘለአለም ህይወት የሚሰጠውን ፍሬ ሊጋብዘን ሲል ቀናተኛው አምላክ ተቆጥቶ አባረረን። “The Devil was the first rebellion against a dictatorial God.” የሚባለው ለዚህ ነው።

ሀይማኖቶችን እንዲህ ያባዛቸው ሰይጣን ነው ከማለታችን በፊት ሰይጣን አለ ወይ ማለት አለብን። ሰይጣን ከመሰረቱ አለን? በሰይጣን የሚያምኑ ይመልሳሉ <ሰይጣንማ ያለጥርጥር አለ ምክንያቱም ክፉ ክስተቶች በሀይማኖት መከፋፈልን ጨምሮ በዓለም

Created in Master PDF Editor

ላይ ስላሉ። ፍቅርም ጥፍቷል፣ ወዘተ።> ብሩህ አለምነህ ስለዚህ አመክንዮ አስተያየት ሲሰጥ እንዲህ ነበር ያለው፦

> እንደነዚህ ዓይነት አመክንዮ በጣም ደካማ ነው። ምክንያቱም የሰይጣንን ህልውና መጀመሪያ ሳታረጋግጡ፣ እነዚህ ክስተቶች የሰይጣን ናቸው ልትሉ አትችሉም። ከባህሪ በፊት የሚቀድመው ህልውና ነው። ባህሪ የህልውና መገለጫ ነው እንጂ ህልውና የባህሪ መገለጫ አይደለም። ህልውና የሌለው ነገር ባህሪ ሊኖረው አይችልም። ስለዚህ ሰይጣን እንዲህ፣ እንዲህ ያደርጋል፣ ባህሪውም እንደዚህ ነው ከማለታችሁ በፊት መጀመሪያ ስለህልውናው እርግጠኛ ሁኑ። የህልውናውን ተጠያቂነት ትታችሁ ስለባህሪው የምትዘረዝሩት ነገር ሁሉ እርባና ቢስ ነው። ስለሆነም በክስተቶች በኩል ስለሰይጣን ህልውና አፋችሁን ሞልታችሁ ልትናገሩ አትችሉም። ደግሞም ለክስተቶች ዲበ አካላዊ (መለኮታዊ) ትርጉም መስጠት እየቀረ የመጣ ነገር ነው። ይሄንንም ተከትሎ ሰዎች ለክስተቶች የሚሰጡት ሃይማኖታዊ ትርጉም እየቀረ በሳይንሳዊ ትርጉም እየተተካ ነው። (ፍልስፍና 2፣ 3ኛ ዕትም፣ 107)

በነገራችን ላይ እግዚአብሔር አለ ማለት የሀይማኖቶች መሰረት ቢሆንም ከእግዚአብሔር ህልውና ጋር ይጋጫል። ለዚህም ነው አንዳንድ የክርስትና ዲኖሚነሽኖች ሰይጣን የለም የሚል ስብከት የጀመሩት። ልክ ብለዋል በሁለንታ በመላው ደግ አምላክ ጎን ለጎን መጥፎ መንፈስ ሊኖር አይችልምና። እግዚአብሔር ሰይጣን እንዲኖር የሚፈቅድ ቢሆን እንኳ መሰረታዊ የሆነው በሁሉ ቦታ የመገኘት ጽንሰ ሃሳብ ይደረመሳል። ብሩህ አለምነህ እንንዲህ ያብራራዋል፦

> መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው እማኞችም ከልባቸው እንደሚያምኑት እግዚአብሔር መንፈስ በመሆኑ የቦታና የጊዜ ገደብ የለበትም፤ በእኛ ውስጥም ሆነ ከእኛ ውጭ ባለው ቦታና ጊዜ ውስጥ ሁሉ በምልዓት ይኖራል። በመሆኑም እግዚአብሔር የሌለበት ቦታና ጊዜ ዩኒቨርስ ውስጥ የለም። እንግዲህ እግዚአብሔር በሁሉም ቦታና ጊዜ ውስጥ ነዋሪ ከሆነ ሰይጣን በየትኛው ቦታና ጊዜ ውስጥ ሆኖ ነው ከእግዚአብሔር ጋር የሚያዋራው ለዚህ ጥያቄ ክርስትያኖች መልስ የላቸውም። በሁሉም ቦታና ጊዜ ውስጥ ሰፍኖ የመገኘት የእግዚአብሔር ባህሪ ሰይጣንን የሚኖርበት የቦታና የጊዜ አውታር ያሳጣዋል። ምክንያቱም እነዚሁ እማኞች እንደሚሉት እግዚአብሔርና ሰይጣን በቦታና በጊዜ አንድ ላይ እንዲኖሩ የሚያስችል ተፈጥሮዊ ባህሪ ስለሌላቸው እግዚአብሔር ባለበት ቦታና ጊዜ ውስጥ ሰይጣን ሊኖር አይችልም፤ እንዲሁም ሰይጣን ባለበት ቦታና ጊዜ ውስጥ እግዚአብሔር አይኖርም። (ፍልስፍና 2፣ 3ኛ ዕትም፣ 87)

Created in Master PDF Editor

ይህ የክርስትናን መሰረት የሚንድ ፍልስፍና ነው:: ሰይጣን አለም-የለም ማለት ክርስትናን ነጻ አያወጣውም:: ሉጅኩ ይህ ሁኖ እያለ የክርስትና ሀይማኖት መስራቾች ግን ስለመከፋፈላቸው ሰይጣንን ይወቅሳሉ:: ካቶሊኮች ኦርቶክሳችን ሰይጣን አሳሳታቸው ይላሉ:: ኦርቶዶክሶችም በተቃራኒው ይላሉ:: ፕሮቴስታንቶችም እንዲሁ፤ ሙስሊሞችም እንዲሁ ሁሉንም ሰይጣን አሳሳታቸው ይላሉ:: እውነቱ ግን እንዲህ ይገለፃል:: *"Luther saw the Pope as the anti-Christ and Catholicism as the Devil's Church. Each side believed, or purported to believe, that Satan, the father of lies, had deluded the other one. The devil, they claimed, pretending to be an angel of light, was luring people from righteousness with false doctrines. People believed in the devil as they believed in god. If there was no devil, there would also be no god.if there is no proof of the devil, there is no proof of god. They are both dead. Rest in peace" (atheist scholar.org)*

እግዚአብሔር በግደታ አምልኩኝ አለማለቱ፡- ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ሃይማኖት መለያየት የቻለው እግዚአብሔር በግደታ አምልኩኝ ባለማለቱ የተነሳ ነው:: እግዚአብሔርን የማምለክ ሥርዓት በግደታ ላይ የተመሠረተ ቢኾን ኖሮ ሃይማኖት የፍርሃት ውጤት ስለሚኾን በየትም አካባቢ ተመሳሳይ ይኾን ነበር:: እግዚአብሔር ግን የነፃነት አምላክ ስለኾነ በዚህ እመኑ በማለት አያስገድድም:: በመኾኑም ሰዎች እንደ አካባቢያቸው ተጨባጭ ኹኔታና ልምዳቸው የተለያየ እምነት ሊኖራቸው ችሏል:: በመኾኑም ሃይማኖት ሊለያይ ችሏል::

መልስ፦ ይገርማል በየትኛውም ቅዱስ መፅሀፍ እግዚአብሔር አላስገድዳችሁም አላለም:: ይልቅስ ከእኔ ብትወጡ ወዮላችሁ ነበር የሚሉት:: በቅዱስ መፅሀፍት ከፈለጋችሁ እመኑኝ ካልመሰላችሁ ትውኝ ችግር የለው የሚል ፅሁፍ የለም:: በእርግጥ እግዚአብሔር እጃችን ይዞ ወደ ቤተክርስቲያን አይወስደንም አላህም ይህን አያደርግም የትኛውም አማልዕክት ይሄን አላደረጉትም:: ይህ ደግሞ ነፃ ምርጫ ሳይሆን ማወዛገብ ነው:: እግዚአብሔር ልጆቹን በእጁ ይዞ ወደ ቤቱ ቢወስድ ችግሩ ምንድን ነው? የትኛውን ነፃነትስ ይገፋል? ወላጅ በልጅ ላይ መብት አለው ቢያንስ እራሱን እስኪያውቅ ድረስ::

ሁሉም ሀይማኖቶችና መሪዎቻቸው ፍጹም የተለያዩ ናቸው:: በምንም ማተሳሰርና አንድ ማድረግ ወይም ማስታርቅ አይቻልም:: እኔ ነኝ እውነት እኔ ነኝ እውነት፣ እኔ ነኝ ልዩ እኔ ነኝ ልዩ ለሚሉት 3ቱ የአብርሃም ሀይማኖቶች Abrahamic monotheism grew organically out of the "primitive" by a process more evolutionary than revolutionary የሚለውRobert Wright 'The Evolution of God' **መጽሃፍ ላይ የትኛው ነው ልዩ ቅዱስ ሲል ይጠይቃል::** "Among the things Muslims, Christians, and Jews have had in common over the years is a tendency to exaggerate their past specialness."

ይላል:: ጽሃፊው የሶስቱም ሀይማኖቶች አመሰራርትና እንቆቅልሾች ተንትኖ የተለየ ነግር ባለማግነቱ እንዲህ ይላል:: "if neither Moses nor Jesus nor Muhammad arrived on the scene with breathtaking news, and if indeed the origin of all three Abrahamic faiths can be viewed as a kind of cultural synthesis, an organic recombination of preexisting elements, what becomes of the claim that they are religions of revelation?"

ምን አልባት የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖር የጭካኔ ልካቸው፣ ለሰው ልጅ የሰጡት ትኩረትና የቡርጃ ስርዓታቸው ነው:: አገኘሁ አሰግድ በተለያየ ሃይማኖት ውስጥ ያየኋቸው ፈጣሪዎች የሚከተሉት ነገሮች ያመሳስሏቸዋል ይላል::

1) ፍፁም ጭካኔ እና ፍፁም ምህረት፦ ስህተት ሰርተህ ሲያጠፉህ፣ በቁምህ በእሳት ቢያነዱህ ቅር አይላቸውም:: ዘላለም እሳት ውስጥ ሊያቃጥሉህ ፍቃደኛ ናቸው:: ካንተ የሚጠበቀው ሰፍረው ካስቀመጧት ትእዛዝ ብቻ ሸውረር ማለት ነው:: በዛው ልክ ፍፁም መሃሪ ናቸው ትባላለህ:: ሁለቱን ባህሪ እንዴት አጣጥመው በፍቅር እንደሚያስገዙ እንጃ!

2) የሙሉ ጊዜ ትኩረታቸው ሰው ነው፦ ከሰው ውጪ ትኩረት ያላቸው፣ የራሳቸው ህይወት ያላቸው አይመስሉም:: ቢቆጡ በሰው ወይ ለሰው ነው:: ሚናቸው፣ ለሚገባው ህይወትን ማቅለል፣ ለጠገበው ደግሞ ከመርግ ድንጋይ ማክበድ ነው:: ከክርስቶስ ልደት ብዙ ዓመታት በፊት ኢፒኩረስ የተባለ ሰው፣ «አማላክት የራሳቸው ህይወትና ፍላጎት አላቸው:: በሰው ተራ ፍላጎት ዙሪያ ሲጨነቁ አይኖሩም» ብሎ ነበር::

3) አምጡ ባይ ናቸው፦ ለድርጊታቸው ምላሽ ይሻሉ:: ፈጠሩ ይባልና፣ ለመፍጠራቸው ውለታ የእድሜ ዘመን ተንበርካኪ፣ ለቁጣ ምላሻቸው ተብረክራኪ ይሻሉ:: ምስጋና፣ አምልኮ፣ እድሜህን፣ አገልግሎትህን ብትሰጣቸው ይወዳሉ:: ይህን ካልሰጠህ አትወደድም:: ምንም አታገኝም:: የእነሱ ልጅ አይደለህም:: መስዋእት ይፈልጋሉ:: ገንዘብ ይፈልጋሉ:: እንደ ደላላ ላሳለጡት አገልግሎት፣ የሚጠብቁት አለ:: (ለምሳሌ ስዕለት ለምንድን ነው የሚከፈለው?)

4) የትኞቹም ላለህ የአዕምሮ ንቃት አይሸልሙህም፦ ለመታዘዝህ እና ለመንበርከክህ እንጂ ዊዝደም ምናምን ብትል ውደም ብለው ነው የሚያባሩህ:: ከሰው ልጅ ጥበብ፣የፈጣሪ ሞኝነት ይበልጣል ይሉሃል ሲሻቸው:: (ምንጭ፦ አገኘሁ አሰግድ፣ http://www.shegerblogs.com/author/agegnehu/)

እውነት የቱ ጋ ነው? Lemuel K. Washburn ይመልሳል "Man has searched for truth in books, but has not found it there. He has invented words to conceal his disappointment, such as God, heaven, providence, etc. Nature contains all the truth. Men in all ages have tried to read the secret of the universe. We have been told that God directs it, that

Created in Master PDF Editor

a divine mind planned it and keeps it in motion. Why not let the universe explain itself? Why not read it by its own light? Why not admit our ignorance? God is a figure of speech, but Nature is a reality." (Lemuel K. Washburn, page 49)

ብሩህ በፈላስፋው ዘርዓያዕቆብ አመለካከት እውነት ማለት ይላል፦

"በዘርዓያዕቆብ አመለካከት እውነት ከሰው ልጅ ፍላጎት ውጭ ነው በስምምነት አይፈጠርም። እውነት ከሰው ልጅ ፖለቲካዊ ስልጣንና ሀይል ጋርም ግንኙነት የለውም፤ የኃይል ብዛት እውነትን ማጥፋትም ሆነ መፍጠር አይችልም። በርግጥ እውነትን የኃይለኞች ፍላጎት አድርገው የሚተረጉሙ አሉ። የራሳቸውን ፍላጎት ህዝቡ ሁሉ የሚገዛበት እውነት አድርገው ለማቅረብ ቄሱ መፅሐፍ ቅዱስን፣ ሸሁ ቁርዓንን፣ ሀብታም ገንዘቡን፣ ባለስልጣን ደግሞ ህግንና ሚዲያን ይጠቀማሉ። በዚህም የተነሳ ሀይማኖት፣ ገንዘብ፣ ስልጣንና ሚዲያ እውነትን የመፈብረኪያ ማሽኖች እየሆኑ በዘመናት ሁሉ ታይተዋል።" (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 52)

ሰዎች የራሳቸውን ቅዱሳን መልዕክተኞች እና ነብያት የመጨረሻው የእውነት መንገድ፣ ብርሃንና ህይወት አድርገው ይቀርጿቸውል። እየሱስ ክርስቶስም በባከኑት አይሁድ መሃል ተነስቶ ካህናቱን ነቀፋቸው፣ ሰደባቸው፣ ረገማቸው፣ መታገስ ያልቻሉት አይሁድ በደሙ ተማምለው ሰቀሉት ተከታዮቹ ግን አልጠፉም ነበርና ክርስትናን መሰረቱ። ሙስሊሞች ስለ ሙሃመድ ሲናገሩ የመጨረሻው መልዕክተኛ የቀድሞዎቹን ነብያት ተልዕኮ የሚያረጋግጡና የሚያሟሉ መለኮታዊ መመሪያዎችን ይዘው በመምጣት በምድር ሰፍኖ የነበረው የመሃይምነት ፅልመት ገረሰሱት። ነብዩ ይኋቸዋል ከብዙ ሙገሳ ጋር በጥራዝ ነጠቅ ፍልስፍና አእምሯቸው አልተበረዘም፤ በአጉል ፈሊጥም እይታቸው አልተሟሸም። በእርግጥ ነብዩ የተነሱበት ዘመንና ቦታ ኋላቀርነት የነገሰበትና ለመቁጠር የሚያታክቱ አማልዕክት የሚመለኩበት ነበር። ነብዩ በቅዱስ ገብርኤል ተበስረው የሰበኩት ስብከት ትክክል ነው ባልልም ለጊዜው ተገቢ ነበር። ነብዩ በአረብያ ምድር ተንሰራፍቶ የነበረውን የሞራል ዝቅጠት አስተውለው፣ የዝቅጠቱ ምንጮች የሆኑትን የወቅቱን ጣኦታት ሃሰትነት ለማረጋገጥ ዘመቱ፣ ተሳካላቸውም። እንዲህ እንዲያ እያለ ሀይማኖቶች በእየዘመኑ ይፈጠራሉ።

እናንተ ምን ያህል እርግጠኛ ናችሁ? የተወለዳችሁበትወይም በንፅፅር የተቀበላችሁት ሀይማኖት እውነተኛው አምላክ የሚመለክበትመሆኑን? ወይም ደግሞ ከጠፋትሃይማኖቶች፣ በስም ከማታውቋቸች እና ሌሎች እናንተ ከማተቀበሏቸው ሀየማኖቶችአንዱ እውነተኛ ቢሆንስ።ጅሎች አትሁኑ ይላል ብሩህ አለምነህ "ጅሎች አትሁኑ! ጅልነታችሁ እየተገለጠ ነው! አምላክ የየትኛው ሃይመኖት ፈጣሪ ነው? አምላክ ኦርቶዶክስ ነውን? ሙስሊም ነውን? ወይስ ጴንጤ? አንደ አስተሳሰባችሁ ውስንነት አምላክንም በአስተሳሰባችሁ ከረጢት ውስጥ ከተታችሁት፤ ሁለንተናዊ

Created in Master PDF Editor

የሆነውን አምላክ ጴንጤ፣ ሙስሊም፣ ኦርቶዶክስ አደረጋችሁት፤ እንዴት ዓይነት ጎበዝ ናችሁ!" (ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣ 33) በተጨማሪም ወደ ኋላ ይመልሰንና "ከዛሬ 2400 ዓመት በፊት ዲሞክሪተዝ የተባለው የጥንታዊት ግሪክ ፈላስፋ ስለ እውነት ሲናገር ጣፋጭም ሆነ መራራ፣ ቀዝቃካም ሆነ የሞቀ፣ ቀለማት ሳይቀሩ የሚያንፀባርቁት የኛን አስተያየት እንጂ ነባራዊ እውነትነት የላቸውም:: በዓለም ላይ ያለው ነባራዊ እውነት፣ ተለዋዋጭ ያልሆኑት አተሞችና በባዶ ቦታ ውስጥ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ብቻ ነው ብሎ ነበር" ይለናል:: በመቀጠልም፦

> አብዛኛዎቹ ፊዚስስቶችና ፈላስፎች ስለዚህ ዓለም የመጨረሻው እወኑትን በተመለከተ ያላቸው ግንዛቤ ተመሳሳይ ነው:: የስሜት ሕዋሶቻችን የሚሰጡንን መረጃ ማጣቀሻ አድርገን አንድን ቁስ በቀለም፣ በድምጽ፣ በእንቅስቃሴ፣ በልስላሴ፣ በጣዕምና በሽታ በመግለፅ የቁሱን የመጨረሻ ምንነት መገንዘብ አንችልም፤ መገኛ ቦታውንም በጊዜና በቦታ መጥቀስ አንችልም:: ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ የቁስ መገለጫ ባህሪያት ያሉት ቁሱ ላይ ሳይሆን የእኛ አእምሮ ውስጥ በመሆናቸው ነው:: ቀይ፣ ቢጫ፡ ሰማያዊ... ወዘተ የሚባሉ ቀለሞች በዓለም ላይ የሉም:: ሙቀትና ድምጽ የሚባሉ ነገሮችም በዓለም ላይ የሉም:: በተለያየ ርዝመት የሚረጩ የኤሌክትሮ ማግኔቲክ ሞገዶችን አእምሯችን አንዱን ቀይ ሌላውን ሐምራዊ፣ አንዱን ሙቀት፣ ሌላውን ደግሞ የማይታወቅ ያደርገዋል:: ለምሳሌ በ0.00007 ሳ.ሜ ርዝመት የሚረጭን የኤሌክትሮ ማግኔቲክ ሞገድ አእምሮ ቀይ አድርጎ ሲተርጉመው፣ በ0.00008 ሳ.ሜ የሚረጨውን ሞገድ ደግሞ አእምሯችን ሙቀት አድርጎ ይተረጉመዋል:: በመሆኑም ቀለማትና ሙቀት የሚባል ነገር አይደለም:: ለእኛ ጣፋጭ የሆነው ስኳር ለውሾችና ለድመቶች እጅግ መራራ ነው:: እንቅስቃሴም ምትሀታዊ (Illusion) እንጂ ነባራዊ ሕልውና የለውም:: ቦታ፣ ጊዜ፣ መንስዔ ውጤት ... ወዘተ የሚባሉ ክስተቶች ሁሉ አእምሯዊ እንጂ ነባራዊ እውነትነት የላቸውም:: በመሆኑም በዓለም ላይ የስሜት ሕዋሶቻችንን መሠረት አድርገን በእርግጠኝነት የምናቀው ነገር የለም:: (ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣ 108-109)

በአለም ላይ ካሉት ምናባዊ እይታዎች ውስጥም ዋነኛው ሀይማኖት ነው:: ስለዚህ ከታሪክ እና ከስነ ልቦና አንፃር ሀይማኖት ምናባዊ መሆኑን እንረዳለን:: የሃርቫርድ የሥነ ሕይወት ተመራማሪ ኤድሮው ዊልሰን እንዳለው ሰዎች ከ100,000 በላይ ሃይማኖቶችን ፈጥረዋል:: አብዛኛዎቹ ጠፍተዋል::ይህን በቀላሉ ለመረዳት በምዕራቡ ዓለም ውስጥ የታወቁ የግሪክ አፈታሪኮች በጊዜአቸው ሀይመኖት ነበሩ::በዚያን ዘመን የግሪክ ዜጎች አዋቂ፣ የተማሩ እና የተራቀቁ ነበሩ:: እነሱ አፖሎ እና ሌሎች አማልክትን ያመልኩ ነበር:: እናም እነአፖሎ እውነት እንደነበሩ ዛሬ ግን እዳለሆኑ እናወቃለን:: ከእውነታ አንፃር የዘመናዊ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች እምነቶችምከግሪክ አፈታሪኮች የተለየነገር የላቸውም:: ምን አልባት ረቀቅ ማለቱ ካልሆነ::

Created in Master PDF Editor

> *“ይህ ረቂቅ ሰዋዊ አምላክ (እግዚአብሔር) የሰው ልጅ ለሚያነሳቸው አደገኛ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ይዞ መጥቷል። እግዚአብሔር የሚኖረው የት ነው እንዳትሉ እግዚአብሔር የትም የሚገኝ መንፈስነውና፣ ፍጥረት እንዴት ተጀመረ ብትሉ ረቂቁ አምላክ ተረት የሚመስል ቢሆንም መልስ አለው። እግዚአብሔርን ማን ፈጠረው? ዕድሜውስ ስንት ነው እንዳትሉ፣ እግዚአብሔር ቀደሞም የነበረ፣ አሁንም ያለና ወደፊትም ለዘላለም የሚኖር ነውትባላላችሁ። እግዚአብሔር ይሄንን ዓለም ከመፍጡ በፊት ምን ሲያደርግ ነበር? እንዳትሉ፣ ይሄ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት <ጊዜ> የሚባል ነገር እንዳልነበረ ሳይንሱም ደርሶበታል ትባላለችሁ። አዲሱ አምላክ ሁሉን ቻይ፣ በቦታና በጊዜ የማይገደብ፣ እሴቶችን ሁሉ በፍፁማዊነት ደረጃ ባህሪው ያደረገ ስለሆነ የሰው ልጅ ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች ሁሉ መልስ አለው።”* (ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣ 90)

አማኞች ከጥንት እስከዛሬ ለአማልዕክቶቻቸው በቡድን እና በጋራ ጥያቄዎችን፣ ልመናዎችን እና ምስጋናዎችን ሲያደርሱ ኑረዋል። በዚህ የጥያቄና መልስ ሰንሰለት ውስጥ የአማልዕክት ወኪሎችካህናት እና ቤተ አምልዕኮዎችና ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።

ካህናት ከጥንቶቹ ሀይማኖቶች ጀምሮ የእግዚአብሔር ወኪሎች ተደረገው በመሳላቸው የማይነጥፍ እንጀራ አብስለዋል።ፈላስፋው ኢማኒኤል ካንት እንዳለው “ለዘመናት የሰው ልጅ ህይወት ለካህናቱና ለሀገር ሽማግሌዎች የተሰጠ ነበር። ለእያንዳንዱ የግል ችግራችን ሁሉ መፍትሄ ስናፈላልግ የነበረው ከሌሎች ሰዎች ነበር። ስለምንበላው፣ ስለምንጠጣው፣ ስለአለባበሳችን፣ ስለጤናችን፣ ስለምግባራችን፣ ስለመንፈሳዊ ህይወታችን፣ ስለማህበራዊ ግንኙነታችን፣ ስለፍቅራችን፣ ስለጋብቻችን፣ ስለልጅ አያያዛችን... ሁሉ የሚነግሩን ሌሎች ሰዎች ናቸው። ይሄንንም ስናደርግ የነበረው በስንፍናችን ነው፤ ለራሳችን ህይወት ራሳችን ኃላፊነት ላለመውሰድ።” (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 172)

ማምለኪያ ቦታዎች አማኞች ከልባቸው ጋር ያልተዋሀዳቸውን ነገር እግዚአብሔር የሚያስቀምጡባቸው ሳጥኖች ናቸው። የእምነት ተቋማትን የሚገነቡ ሠዎች ይገርሙኛል። እግዚአብሔርን ከኤቲስቶች ይልቅ የከዱት እነሱ ናቸው። የሚኖርበትን ቤተ- መቅደስ ሠሩለትና ወደ ቤታቸው ተመለሱ። ቀን ቆጥረው፣ ኘሮግራም ቀርፀው እየሄዱ ይጠይቁታል። በድንገት ሲልፋም ያስታውሱታል። ቤተ-እምነቶች የሚገነቧቸው ድንቅ ቤተ-መቅደሶች የዘመኑን የስልጣኔ ሁኔታ እና የሰዎችን የአኗኗር ዘይቤ ከመግለፃቸው በላይ እግዚአብሔር መኖሩን ተሎ ለሚረሱ አማኞች የማስታወሻ ምልክቶች ናቸው። የማምለኪያ ግንባታዎችን እንደ የማህበራዊ ግንኙነት ማዳበሪያ እና የጥበብ ማዕከል አድርገን የምንቆጥራቸው ከሆነ ከቤተ-መፅሐፍቶችና ከስብሰባ ማዕከሎች ከሚገኘው እውቀት ያልተናነሰ ትምህርት ይገኝባቸዋል። ቦታዎቹ

Created in Master PDF Editor

ለአማልዕክት ማደሪያ የተገነቡ ኮሮጆዎች ከሆነ ግን ከጥቅማቸው ጉዳታቸው ያመዝናል። ለአምላክ ቤት መስራት የአምላክን በሁሉ ቦታ የመገኘት ባህሪን መካድ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ሀገር ነው፤ ይህ የእግዚአብሔር መቅደስ ነው፤ ይህ እግዚአብሔር የቀደሰው ተራራ ነው፤ ይህ የእግዚአብሔር ማረፊያ ነው ወዘተ የሚባሉት ንግግሮች እግዚአብሔር ውስን ነው ከማለት አይተናነሱም። እግዚአብሔር መቸምና የትም መገኘት አለበት። ካልሆነ ግን እንደአባቶቹ ሙቷል ማለት ነው።

የግሪክ ሃይማኖቶችንበደካማ ወይም ያለምንም ምክንያት የምድር ነዋሪዎች ለሽ ዓመታት አመኑባቸው።የዛሬዎቹን ሃይማኖቶች ከግሪኮች እና ከግብፃውያን የተለየ ስለ አማልክት ምንም ተጨማሪ ማስረጃ አላቀረቡም። አፖሎ የሚባል አምለክ የለም አልነበረምም። የክርስትያኖች አምላክ የሚባል አምለክ የለም አልነበረምም። የክርስትያኖች አምላክ ካለ ከግሪኮች አማልክት ቢያንስ አነዱ ሊኖር ይችላል። ለሁለቱም የመኖር እና ያለመኖር ማስረጃ እኩል ነው። በየትኛውም ሚዛን በንመዝነው እግዚአብሔርና የተጣለው አፖሎ ክብደታቸው እኩል ነው። እውነቱ ሃይማኖት ከስህተቱ ሃይማኖት ለመለየት የሃይማኖት ትክክለኛነትመመዘኛ መስፈርቶች ያስፈልጉናል። ካሳሁን አለሙ በተጠየቅ ድህረ ገጹ በጥቅል መልክ አንድን ሃይማኖት በሚከተሉት ሚዛኖች መገምገም ይቻላል ይለናል።

1ኛ) አንድ ሃይማኖት ትክክለኛ ነው ለመባል በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ህልውነት ላይ ሙሉ እምነት ያለው መሆን ይኖርበታል። ያለበለዚያ አሳማኝ የሆነ የእምነት መሠረት አይኖረውምና። ምክንያቱም ሃይማኖት የሁለት አካላትን ቃል ኪዳን (አማኝና ታማኝ) መጠበቅና መተማመን የሚፈልግ ፅንሰ-ሐሣብ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔርን መሠረቱ ያላደረገ ሃይማኖት ትክክል አይደለም።

መልስ፡ የስነ-መለኮትና የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪዎች ግን ሀይማኖትን ከአንድ በሰማይ ካለ እግዚአብሔር ጋር ብቻ አያገናኙትም። ሀይማኖት ማለት በአንድ እግዚአብሔር መኖር ማመን ከሆነ በብዙ አማልዕክት የሚምኑትና እግዚአብሔር ላይ ትኩረት የሚያደርጉት የምስራቁ አለም ሀይማኖቶች ከጭዋታው ውጭ ሊሆኑ ነው ይልቅም እግዚአብሔር የትኛውም ሀይማኖት አልመሰረተም።

2ኛ) የእግዚአብሔርን መታወቂያ ጠባያትም ሳያምታታና ሳይሻራርፍ በሙሉነት መቀበል መቻል አለበት። አግዚአብሔርን ልናውቀው የቻልነው በጠባያቱ ምንባብነት ነውና። የእግዚአብሔርን ጠባያት ሙሉ ለሙሉ ሳያካትት እና እያምታታ የሚገልጽ ሃይማኖት አስተማማኝነት አይኖረውም፤ ችግር አለበት።

መልስ፡በአለም ከነበሩትና ካሉት ሀይማኖቶች አንዱም እንኳ የእግዚአብሔር ማንነት የሚውቅ የለም። ብዙዎቹ በደግነት፣ በግለጸልን ልክ እናመልከዋለን ይላሉ። እናም

Created in Master PDF Editor

እግዚአብሔር ጠባያቱን ሙሉ በሙሉ የገለፀለት እስከሌለ ድረስ መምታቱና ማምታታቱ ይቀጥላል።

3ኛ) ከእግዚአብሔር ተነገረ የተባለው ነገር በተግባር ተገልጾ መታየት (መተግበር) መቻል አለበት። ለምሳሌ በትንቢት መልክ የተገለጹ በተግባር ተፈጽመው፣ በምሳሌ የተገለፁም በአማዊነት እውን ሆነው መታየት አለባቸው።

መልስ፦ የከሸፉትን ሳይሆን የተሳኩትን ትንቢቶች ስለሞንቆጥር ነው እንጅ በቅዱሳን መፅሀፍት ብዙ ትንቢቶች ከሽፈዋል። ለምሳሌ፡- ማቴ 16:28 "እውነት እላችኋለሁ፥ የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ እዚህ ከሚቆሙት ሞትን የማይቀምሱ አንዳንድ አሉ።" በሚገርም ሁኔታ 2ኛ ነገስት 20:1 "በዚያም ወራት ሕዝቅያስ እስከ ሞት ድረስ ታመመ። ነቢዩም የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ ወደ እርሱ መጥቶ። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ትሞታለህ እንጂ በሕይወት አትኖርምና ቤትህን አስተካክል አለው።" ይልና 2ኛ ነገስት 20:6 "በዕድሜህም ላይ አሥራ አምስት ዓመት እጨምራለሁ፤ አንተንና ይህችን ከተማ ከአሦር ንጉሥ እጅ እታደጋለሁ፤ ስለ እኔም ስለ ባሪያዬም ስለ ዳዊት ይህችን ከተማ እጋርዳታለሁ።" ይላል። ይህ ለምህረት ተብሎ ይሆን የከሸፈው። ሌላ ምስሌዎች ልጨምር ትንቢት ኤርሚያስ 36:30 "ስለ ይሁዳ ንጉሥ ስለ ኢዮአቄም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። <u>በዳዊት ዙፋን ላይ ተቀማጭ አይኖርለትም፥</u> ሬሳውም በቀን ለትኩሳት በሌሊትም ለውርጭ ይጣላል።" ሲል ይህን ትንቢት ያልሰማው 2ኛ ነገስት 24:6 ደግሞ "ኢዮአቄምም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ፤ ልጁም ዮአኪን፤ በእርሱ ፋንታ ነገሠ።" ይላል። ኢሳያስ ደግሞ በ17:1-2 "ስለ ደማስቆ የተነገረ ሸክም። እነሆ፥ ደማስቆ ከተማ ከመሆን ተቋርጣለች፤ ባድማና የፍርስራሽ ክምር ትሆናለች። ከተሞችዋ ለዘላለም የተፈቱ ይሆናሉ፤ ለመንጋ ማሰማሪያ ሆናሉ፤ መንጎች በዚያ ያርፋሉ የሚያስፈራቸውም የለም።" ብሎ ነበር ደማስቆ ግን ዛሬም አለች።

ሕዝእቂልም በበኩሉ በ26:4-6 "የጢሮስንም ቅጥሮች ያጠፋሉ ግንቦችዋንም ያፈርሳሉ፤ ትቢያዋንም ከእርስዋ እፍቃለሁ፥ የተራቈተ ድንጋይም አደርጋታለሁ። በባሕር ውስጥ የመረብ ማስጫ ትሆናለች፤ እኔ ተናግሬአለሁና፥ ይላል እግዚአብሔር፤ ለአሕዛብም ብዝበዛ ትሆናለች። በሜዳ ያሉትም ሴቶች ልጆችዋ በሰይፍ ይገደላሉ፤ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ያውቃሉ።" ብሎ ነብርዛሬም ግን አለች በሕዝእቂል በምዕራፍ 26 ያወረደባት ናዳ ከሸፈ።

ክርስቶስ ተሎ እመጣለሁ ብሎ አልመጣም፤ ደመስቆ ትጠፋለች ተብሎ አልጠፋችም ስለ ግብፅ ምድረ በዳነት ተተንብዮ ነበር ግን አልሆነም ሌላም ሌላም መዘርዘር ይቻላል። ትንቢቶች ለክራክር አይመቹም ለምን አልተሳኩም ተብሎ ሲጠየቅ ጊዜው ስላልደረሰ ይባላል ይህን ትንቢቶች ይሆናሉ የተባሉበትን ዘመንና ሁኔታ በልብ

ሙሉነት የተረዳ ካልሆነ በስተቀር መግባባት አይቻልም:: ብዙ ጊዜ የሚያሳዝነው ደግሞ ትንቢቶችን ወደ ተፈፀሙ ነገሮች ወይም የተፈፀመ ነገሮችን ወደ ትንቢት የመነተት ነገር ነው:: ስለዚህ ያለምንም ማሻማት የተፈፀመ እንዳች ትንቢት ባለመኖሩ እውነተኛ ሀይማኖት የለም::

4ኛ) ሃይማኖቱ ከእግዚአብሔር ለሰዎች በሰዎች አማካይነት የተገለጸ መሆን ይኖርበታል:: ምክንያቱም ሃይማኖት ከሰዎች አዕምሮ አስተሳሰብ በላይ የሆኑ ነገሮችን የያዘና የእግዚአብሔርን ሥራዎች የሚገልፅ ነው፤ እነዚህን መገለጦች በአግባቡ አውቆ ለሰዎች መግለጽ የሚችለው ደግሞ ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው::

መልስ፡ ዋው! ትክክለኛው ሀይማኖት በዚህ አለም የለም እንጅ በመገለጥ ላይ የተመሰረተ ነው:: ገላጩ ደግሞ መልዕክተኛ ነብይ ወይም ሀዋርያ አይደለም ራሱ ባለቤቱ ነው:: የሚገልጠው ደግሞ ለተመረጡ ጎሳዎች ሳይሆን ለሁሉም ፍጥረታት ነው:: በዚህ አለም ያሉትን ግን በሰዎች ለሰዎች የተቋቋሙ ናቸው የክርስትና ሀይማኖትን መገለጥ የመሰረታቸው መሆኑን አብክረው ይሰብካሉ:: እግዚአብሔር ቢኖር በጣም ይታዘባቸው ነበር::

5ኛ) ከሰዎች ተፈጥሯዊ ሥነ ልቦና፣ የአዕምሯ ሚዛንና የተፈጥሮ ሁኔታዎች ጋር መስማማት አለበት:: ምክንያቱም በሃይማኖት አምኖ አምልኮ የሚፈጽመው ሰው ነውና:: ሰው ደግሞ የአዕምሮና የስሜት ሥሪት መሆኑ ይታወቃል፤ አምልኮም የሚፈጽመው በአዕምሮው አስቦና በሰሜቱ አንብቦ ነው እንጂ እነዚህን የተፈጥሮ ሀብቶቹን አውልቆ አይደለም:: እነዚህም የተፈጥሮው ሀብቶች ከውጭው ዓለም (ነገሮች) ጋር ግኑኝነት ያላቸው ናቸው:: ስለዚህ ሃይማኖቱ የእነዚህን የተፈጥሮ መስተጋብሮች በማስማማት መግለጽ መቻል አለበት::

መልስ፡ ደስ የሚል ሚዛን ነበር ነገር ግን የሀይማኖቶች የአምልዕኮ ስርዓት ከነባራዊ አለም ፈፅሞ የወጣ ነው:: በቅዱሳን መፅሀፍት የተተረኩት መሰረታዊ ታሪኮች ከተፈጥሮ ያፈነገጡ ምናባዊ ናቸው:: ስለዚህ ሀይማኖቶች በምድረ ያሉ ምናባዊ የፈጠራ አለማት ናቸው:: ከሀይማኖቶች ይልቅስ የፈላስፋው ወልደ ህይወት ሀተታ እጅግ ለተፈጥሮ ትቀርባለች::

> *"ልንፆም ይገባናል፣ ባሉህ ጊዜም እነርሱን መምሰል ይሻልሃልና "አዎን" በላቸው እንጂ ነገራቸውን አትከራከራቸው:: ነገር ግን ከመብላትና ከመጠጣት ፍላጎት ጋር የፈጠረህ የእግዚአብሔር የፈጣሪህ ፈቃድ ይህ ነውና <u>ሲርብህ ብትበላና ሲጠማህም ብትጠጣ መልካም ታደርጋለህ</u>:: ህይወታችንን የሚያጠፋ እስካልሆነ ድረስ እሱ (ፈጣሪ) ከፈጠረው ፍጥረት እንዳንበለው የተከለከልነው ነገር የለም:: ያስፈለገንን ለመብላት በሁሉ ቀንና በእድሜያችንም ሁሉ ትክክል ነው እንጂ የሚከለከል*

Created in Master PDF Editor

የለውም። የፆምን ህግ የሰሩ ሰዎች ግን አልመረመሩምና የፈጣሪንም ጥበብ አላወቁም።” (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 307)

“ሴትና ወንድን ከፈቃደ አውስቦ ጋር የፈጠረ የፈጣሪ ትዕዛዝ ነውና ሴት ከሌለችህ አግባ፣ ባል ከሌለሽም አግቢ። በልጅነታቸው የሚመነኩሱ መነኩሴዎችን አታመስግናቸው። አውስቦን እንደሚያስነውሩ ዕብዶች አትሁን። ይህም ምንኩስና የሰው ተፈጥሯዊ ባህሪን የሚቃወምና የፈጣሪንም ስርዓት የሚያፈርስ ነው። አውስቦ ከፈጣሪ የእጅ ስራዎች ሁሉ ይልቅ ትልቅና የተቀደሰ ጥበብ ነው።” (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 309)

ታድያ ከተፈጥሮም፣ ከሰብአዊነትም፣ ከፍትህና ከፈጣሪም ያፈነገጡ ሀይማኖቶች እንዴት ተፈጠሩ? አፈጣጠራቸው Alexander Drake *እንዳለው፦ “certain psychological phenomena can produce a set of beliefs that contains rituals, deities, and an afterlife that includes the concept of a soul. And when these beliefs evolve and are combined with etiological stories, they form a religion. Therefore, in the absence of knowledge, humans will invent a religion.”*

6ኛ) *ምክንያታዊ የሆነና ዓላማ ያለው መሆን አለበት። እግዚአብሔር ግብታዊ አምላክ አይደለም፤ ስለሆነም አንዲትም ነገር በዘፈቀደ አይሠራም። በዚህ የተነሣም በሃይማኖት መኖርና መመራት ያስፈለገበት ምክንያት ያለው መሆን ይኖርበታል። ይህም ሊሆን የቻለበት ግብና ግቡ ጋር መድረሻም ሥርዓትና ዓላማ ሊኖረው ይገባል።*

መልስ፦ *እማኞች እንደሚመሰክሩት የሃይማኖቶች የመጨረሻ ግብ መንግስተ ሰማያት እና መንግስተ ግሃነም ናቸው። ወደ ሁለቱ መንግስታት የሚያስገቡ መንገዶችንም ቆጥረው ለክተው በስርዓተ አምልኳቸው አካተዋቸዋል። አላማ መኖሩ መልካም ቢሆንም መንግስተ ሰማያት መግባትም አስደሳች ቢሆንም በስርዓተ አምልከውና በመንገዱ ፍትሃዊነት ዙሪያ ትችት የማይቀርብበት አንድም ሀይማኖት እስከአሁን አልተገኘም።*

7ኛ) *እንደዘመኑና እንደሁኔታው የሚለዋወጥ መሆን የለበትም። ያለበለዚያ ከትውልድ ሁኔታ መለዋወጥ ጋር አብሮ የሚቀያየር ከሆነ ዋስትና አይኖረውም።*

መልስ፦ *በዝግመተ ለውጥ ታሪክ ውስጥ እንደ ሀይማኖት ፈጥኖ ተለዋጭ ያለ አይመስለኝም። በቁሳቁስ አካላት ከማመን በሰማያዊ አካላት ማመን ከዚያም አልፎ ከሰማያዊ አካላት በላይ የሆነን የማይታይ አካል ወደ ማምለክ ፈጣን ለውጥ ተደርጓል። አብርሃም ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። ጣኦታቱን ሰብሮ ወደ ሰማይ አንጋጠጠ። አሀዳዊ ሀይማኖትንም መሰረተ። በኋለኛው ዘመንም ክርስቶስ መጥቶ ክርስትናን መሰረተ። ተከታዮችም ግልፅ ያልሆነውን ለራሳቸው እንደሚስማማ*

Created in Master PDF Editor

እያደረጉ ያልሆነውን እየጨመሩ 40,000 ንዑስ ሀይማኖቶችን መሰረቱ። ሀይማኖት ዘመኑንና ሁኔታውን እያየ ዛሬም በፈጣን ተሀድሶ ላይ ነው። በተለይ ከሳይንስ ጋር ለመወዳጀት የሚያደርገው ጥረት የሀይማኖትን ምንነት እስከ መርሳት ይደርሳል።

8ኛ) በሃይማኖቱ ዙሪያ ለሚነሱ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ መስጠት አለበት። ምክንያቱም ሃይማኖት በእግዚአብሔር የተገለጠና በሰዎች እሳቤ የታገዘ ስለሆነ ነው።

መልስ፦ ሀይማኖቶች ለጥያቄዎቻችሁ ሁሉ መልስ አለን ማለት የተለመደ አባባላቸው ነው። ለጥያቄዎች ሁሉ መልስ ቢኖር ኑሮ ሀይማኖታችን እና ማንነታችን በጥያቄ ብዛት ባልተወሳሰበ ነበር። ሀይማኖቶች ከሚመልሱት ጥያቄ ይልቅ በሰው አዕምሮ ውስጥ የሚፈጥሩት ተጨማሪ ጥያቄ ይበዛል። መልሶች እንኳ ቢኖሩ ግምታዊ እና ግላዊ ናቸው። መልስ ደግሞ ነበራዊ ሐቅ ነው። ተብሏልና ይሆናል መልስ አይደለም ግምት ነው ለዚህ ደግሞ ሳይንስና ፍልስፍና የተሻሉ ናቸው።

9ኛ) የሰው ዘሮችን ሁሉ በእኩል ዕይታ የሚያይ መሆን አለበት። ማለትም አንዱን ዘር የተመረጠ ሌላውን ደግሞ የተለየ ማድረግ የለበትም።

መልስ፦ ነበር ባይሰበር! ምን አልባት የምስራቁ ንፍቀ ክበብ ሀይማኖቶች ይሻሉ እንደሆን እንጅ የመካከለኛው ምስራቅና የምእራቡ አለም ሀይማኖቶች እጅግ ሲበዛ ብሔርተኛ፣ ጎጠኛና ኢ-ፍትሃዊ ናቸው። መፅሀፍ ቅዱሳን ያነበበ ሰው ይህን ሃሳብ ይጋራኛል። ብሔርተኛነቱ በብሉይ ኪዳን ብቻ ሳይሆን በወንጌልም ተደግሟል። ኢየሱስ እንኳ ሲያስተምር ለውሾች አልተላኩም ለህዝቦች እንጅ ያለበት አጋጣሚ ነበር። ህዝብና አህዛብ የሚባለው ክፍፍልም ተጠናክሮ የቀጠለበት ሁኔታ ነበር የተከሰተው፣ በኋላ ሀይማኖቱን አለም አቀፍዊ ለማደድረግ እነ ቅዱስ ጳውሎስ ቢጥሩም። አንድ ጥያቄ ላንሳ ኢየሱስ ለምን አፍሪካ ወይም አውሮፓ ውስጥ አልተወለደም?

10ኛ) በተፈጥሮ ሥርዓት ውስጥ የሰውን ልጅ የመመራመር ተፈጥሮ የሚያግድ መሆን የለበትም። የሰው ልጅ የመመራመር ተፈጥሮ ያለው ፍጡር ነውና፤ እስከቻለው ማሰብ፣ መጠየቅና የጠየቀውን መልስ ለመስጠት መሞከር አለበት።

መልስ፦ የሰው ልጅ ቢከለከልም ባይከለከልም በተፈጥሮ ላይ መመራመሩን አይተውም። የሚያሳዝነው ግን ሀይማኖቶች አስቀድመው "አዲስ ነገር አታገኝም" በማለት ሊያስሩት ይጥራሉ። ሊጠየቁ ለሚችሉ ጥያቄዎችም ቅድሚያ መልስ በመስጠት በእምነት ብቻ እንድንቀበላቸው ያዛሉ። መመራመርና መጠራጠር የተወገዘ ነው። ሳያይ የተባለውን የሚያምን ግን ቅዱስ ነው ተብሏል። <ጅል ነው> ነበር በመባል የነበረበት። እኔ እስከማውቀው ድረስ በሀይማኖቶች በተለይ በምዕራቡ

Created in Master PDF Editor

የአብርሃም ሀይማኖቶች ማሰብ፣ መጠየቅና መጠራጠር የምንፍቅና ልጆች ተደርገው ተስለዋል። እስኪ የመጠራጠር መብትን የሚያጎናፅፍ ሀይማኖት ስም ጥሩልኝ?

ያኔ በ17ኛው ክ/ዘመን ሀይማኖት እንዲህ እንደ አሸን ሳይፈላ ወልደ ሕይወት በሃተታው ምዕራፍ 5 ላይ እንዲህ ይላል።*"አንዱ በእስክንድርያ ሃይማኖት እመኑ ይለናል። 2ኛው በሮም ሃይማኖት እመኑ ይለናል። 3ኛ በእስልምና በመሐመድ ሃይማኖት እመኑ ይለናል። 4ኛው በሙሴ ሃይማኖት እመኑ ይለናል። የህንድ ሰዎችም እንዲሁ ልዩ ሀይማኖት አላቸው። የሳባ ሰዎች እና ሌሎችም እንዲሁ ሁላቸው ሃይማኖታችን ከእግዚአብሔር ነው ይላሉ።እንገዲያውስ በስራው ሁሉ ፃድቅ የሆነ እግዚአብሔር ለአንደኛው አንድ ሃይማኖት ለሁለተኛውም ሌላ ሃይማኖት ሊገልጽለት ይችላል?"* (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 289) የሃይማኖቶች ልዩነት እንዲህ አንድ፣ ሁለት የሚባል አይደለም 30ሽ፣ 40ሽ የሚባል ነው። ለነገሩ አይገርምም ክርስትናን በአቀኑት ሀዋርያት ሳይቀር መከፋፍል እና መቃቃር ነበር። የሐዋርያት ስራ 15÷35-39 እንዲህ ይላል።*"ጳውሎስና በርናባስም ከሌሎች ከብዙ ሰዎች ጋር ደግሞ የጌታን ቃል እያስተማሩና ወንጌልን እየሰበኩ በአንጾኪያ ይቀመጡ ነበር። ከጥቂት ቀንም በኋላ ጳውሎስ በርናባስን ተመልሰን የጌታን ቃል በተናገርንበት በየከተማው ሁሉ ወንድሞችን እንጎብኛቸው፥ እንዴት እንዳሉም እንወቅ አለው።* ***በርናባስምማርቆስ*** *የተባለውን ዮሐንስን ደግሞ ከእነርሱ ጋር ይወስድ ዘንድ አሰበ፤ ጳውሎስ ግን ይህን ከእነርሱ ጋር ሊወስድ* ***አልፈቀደም፥*** *ከእነርሱ ዘንድ ከጵንፍልያ ተለይቶ ነበርና፥ ወደ ሥራም ከእነርሱ ጋር አልመጣም ነበርና። ስለዚህም እርስ በርሳቸው እስኪለያዩ ድረስ መከፋፋትሆነ፥ በርናባስም ማርቆስን ይዞ በመርከብ ወደ ቆጵሮስ ሄደ።"*

በእርግጥ በጳውሎስና በማርቆስ መካከል የተፈጠረው ልዩነት የዶክትሪን አይደለም ቢሆንም ዛሬ እንደ አሜባ እራሳቸውን ለሚከፋፍሉት የክርስትና ሃዋርያት ግን ትንቢት ነው። የፈላስፋው ዘረዓ ያዕቆብ ተማሪ ወልደ ሕይወት በሃተታው ምዕራፍ 5 ላይ የእምነት ድርጅቶችን መብዛት የፈጠረበትን ጭንቀት እንዲህ ያካፍለናል።*"እንዴትስ ይህ ሁሉ ሃይማኖት ከእግዚአብሔር ተለያይቶ ሊሰጥ ይችላል? ከእነዚህ ሁሉ ሃይማኖቶች ውስጥስ እውነትን የያዘውና ልናምንበት የሚገባን ሃይማኖት የትኛው ነው? ካወቃችሁ እስቲ ንገሩኝ? እኔ ግን አላውቅም፤ በሃይማኖቴ እንዳልስትም እግዚአብሔር በብርሃነ ልቦናዬ ያሳየኝ ካልሆነ በስተቀር በምንም አላምንም። <እንግዲያውስ አማኝ ካልሆንክ ከእግዚአብሔር ዘንድ ኩነኔ ያገኝሃል> የሚሉኝ ሰዎች ቢኖሩ፣ እግዚአብሔር በሐሰት እንዳምን ሊያዘኝ አይችልም። እርሱ መልካሙንና ክፉውን፣ እውነቱንና ሐሰቱን የምለይበት ብርሃነ ልቦና ሰጥቶኛልና እውነት ያልመሰለኝን ሃይማኖት ስለተውኩ ሊኮንነኝ አይችልም።"* (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 289)

Created in Master PDF Editor

ሁሉም ሰው ኢ-አማኝ (ኤቲስት) ነው፡፡ ክርስቲያኖች በዜኡስ አያምኑም፡፡ ሙስሊሞች በቱር (Thor) አያምኑም፡፡ ሂንዱዎች በክርስትና አምላክ አያምኑም፡፡ማንም አማኝ ተክክለኛውን እንደሚያምን ያውቃል እናነተም አነዲሁ፡፡ ትክክለኛው አምላክ የቱ ነው? ይብዛም ይነስም በዓለም ውስጥ ያሉት አማኞች እንደ እናንተ እርግጠኛ ናቸው፡፡ ግን ብዙ የተለያዩአማልክት በአንዴ እውነት ለሆኑ ይችላሉን? ደራሲው ስቲቨን ሮበርትስ እንዲህ በማለት ያብራራዋል‹‹እኛ ሁላችንም ለብዙዎቹ አማልዕክትኢ-አማኞች ነን ልዩነቱ እናንተበአንድ ተጨማሪ አምላክ ታምናላችሁ››፡፡በተመሳሳይ አገላለጽ ፕ/ር ሪቻርድ ዳውኪንስን ኤቲስት ነህን በለው ለሚጠይቁት አማኞች እንዲህ ይመልስላቸዋል፡፡ “I have found it an amusing strategy, when asked whether I am an atheist, to point out that the questioner is also an atheist when considering Zeus, Apollo, Amon Ra, Mithras, Baal, Thor, Wotan, the Golden Calf and the Flying Spaghetti Monster. I just go one god further.” (The God Delusion, page 53)

ደረጀ ፀጋዬ ደግሞ እንዲህ ይላል “እያንዳንዱ አማኝ የራሱን እምነት የአምላክ ቃል አድርጎ ይመለከታል፡፡ ከእርሱ እምነት ውጪ ያሉትን እምነቶች በሙሉ የሰው ልጅ ስራ እንደሆኑ አድርጎ ያስባል፡፡ አልያም ያው የፈረደበት ሰይጣን በምክንያትነት ይቀርባል፡፡ በአማኝና ኢ-አማኒ መካከል ያለው ልዩነት ከየትኛውም አማኒ አቅጣጫ ሲታይ ኢ-አማኒው አንድ ተጨማሪ አምላክ መካዱ ነው፡፡ አማኒው የኔ አምላክ እኩል ይሆናል እውነት ይላል፡፡ ኢ-አማኒው ያንተ አምላክ ሲደመር የሌላው አምላክ እኩል ይሆናል አልቦ..(ዜሮ) ይላል፡፡” (ደረጀ ፀጋዬ፣ የኢ-አማኒው ኑዛዜ) ‘Life driven purpose: how an atheist finds meaning’ የሚል መጽሃፍ የጻፈው Dan Barker ደግሞ እንዲህ ያዜማል፦

“None of the Above”

Everybody tries to tell me
I need to choose a god to love,
But after looking them all over,
I'll take none of the above.
I am happy in the natural world,
Like a hand fits in a glove.
Only sinners need a savior.
I'll take none of the above.
Why talk to me of heaven?

Created in Master PDF Editor

What makes you think I wanna go,
When it's right here in the real world
Where the milk and honey flow?
You preachers and messiahs,
What were you thinking of?
Don't need to fix what isn't broken.
I'll take none of the above.

3. የእግዚአብሔር ዝምታ (God's Silece)

አለው ነገር እግዚአብሔር እንድህ አብዝቶ ዝም ካለ

ከሳሽ ሆይ ደስ አይበልህ ቢመሽም ለኔ ጊዜ አለ::

ዘማሪዋ የእግዚአብሔር አብዝቶ ዝም ማለት ስለታያት ይመስላል <አለው ነገር> ያለችው:: ብዙዎች እግዚአብሔር ዝም ብሏል በሚለው አይስማሙም ለምን ቢባል እግዚአብሔር በእየለቱ ጸሎታችንን እየሰማን፣ መግቦቱና ጥበቃው ሳይለየን እየኖርን ነው ይላሉ:: እውነት እግዚአብሔር በእየ ቤታችንና በእየቤተ-እምነታቸን የምንጸልየውን ጸሎት እየሰማን ነው? መልሱ አወ ከሆነ ዝምታው ተሰበረ ማለት ነው:: አይደለም ከሆነ ግን ለምን እንደክማለን:: የምንጸልየው እኮ የጎደለንን እንዲሞላልን እና በህይወታችን የሚያጋጥመንን ማዕበል ጸጥ እንዲያደርግን ነው::

ማርሻል ብሬን Why Won't God Heal Amputees በሚል ድህረ ገጹ ላይ እንዲህ ይላል፦ *How do we know, for sure, that God does not answer prayers? We simply pray and watch what happens. What we find is that nothing happens. <u>No matter how many people pray, no matter how often they pray, no matter how sincerely they pray, no matter how worthy the prayer, nothing ever happens.</u> If we pray for anything that is impossible for example, regenerating an amputated limb or moving Mt. Everest it never happens. We all know that. If we pray for anything that is possible, the results of the prayer will unfold in exact accord with the normal laws of probability.*

እንደማርሻል ብሬን ገለጻ እግዚአብሔር በጸሎት በኩል ከአማኞች ጋር የሚያደርገው ቃለ-ምልልስ የለም:: ብቻችንንም፣ ተሰባስበንም፣ በምንም ያህል ቅንነትና እምነት ብንጸልይ የማይሰማን ከሆነ ለዝምታው ማስረጃ ተገኘ ማለት ነው:: ግን ግን እግዚአብሔር በዝምታስ ቢሆን ይኖራልን?

Created in Master PDF Editor

ቴወድሮስ ተ/አረጋይ መጋቢ ሃዲስ እሸቱ አለማየሁን ስለ እግዚአብሔር ያለንን መረጃ ከየት ያገኘነው ነው ሲል ጠየቃቸው፡፡ መ/ር እሸቱም መለሱ እንዲህ በማለት፡- "ከራሱ ከእግዚአብሔር፡፡ ስለ እግዚአብሔር እንድናውቅ ያደረገን ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ ከመፈጠራችን በፊት አጠገቡ ሌላ ማንም አልነበረም፡፡ እግዚአብሔር ፍጥረትን እሁድ ጀምሮ አርብ መጨረሱን ኑሮ ከተጀመረ ከሶስት ሺህ ዓመት በኂላ ሙሴ ኦሪትን ሲጽፍ ነው የነገረው፡፡ ስለ ስነ ፍጥረት መጽሐፍ የፃፈልን በ6ኛው ቀን የተፈጠረው የመጀመሪያው የሰው ፍጡር አዳም አይደለም፡፡ ዓለም ከተፈጠረ ከ3,800 ዓመት በኂላ ሙሴ ነው፡፡ ለሙሴ ይህን መረጃ የሰጠው ራሱ እግዚአብሔር ነው፡፡ ስለዚህ ነው ስለ እግዚአብሔር የመረጃ ምንጮችን ራሱ እግዚአብሔር ነው ብለን የምናምነው፡፡" (ፍልስምና፣ ቁጥር 2፣ 2004 ዓ.ም፣ 23)መጋቢ ሃዲስ እሸቱ አለማየሁ ማወቅ ያለባቸው አንድ ነገር አለ ማንም ስለራሱ ምስክር መሆን አይችልም፣ ከመሰከረም ምስክርነቱ ለሙሴ እንጅ ለእኛ አይደለም ሙሴን የማመን ግዴታ የለብንም፡፡ ሙሴ እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ አለን እንጅ ለሙሴ እንዲህ ብየዋለሁ ብሎ በቀጥታ የነገረን የለም፡፡ እግዚአብሔር ለሁሉ የሚበቃ የትም ያለ በመሆኑ ለሙሴ ብቻ ሳይሆን ለሁላችንንም መገለጥ ይችላል፡፡ ዝምታውንም መስብር ይችላል፡፡ የእግዚአብሔር መገለጥ ነጻነታችንን አይጋፋም፣ ይልቅ ፍቅሩን ይገልጥበታል እንጅ፡፡(እናዳለመታደል ሁኖ?) ሰዎች የቶማስነት (ካላየን አናምንም) የማለት ብሃሪ አለብን፡፡ ማየት ማመን ነው፣ ካላየን እናምን ዘንድ አንገደድም፡፡ ቢሆንም በምንችለው አቅም ሳይንስና ፍልስፍናን ተጠቅመን እናገኘው እንደሆን መፈለጉ አይከፋም፡፡

ካሳሁን አለሙ ፈላስፎች እግዚአብሔርን በተመለከተ ስለሚያራምዱት ውዝግብ እንዲህ ይል፡-"*እግዚአብሔር አለ ግን ሥራው ግን ትክክል አይደለም፡- ፍጥረቱን ሲመለከቱት ፈጣሪና ተቆጣጣሪ እንዳለው ይገልጻል፡፡ ይሁንና የፍጠረቱ አኗኗርና በችግር የሚገኝ መሆኑ ከእርሱ ጠባያት ጋር ይጋጫል፡፡ ስለሆነም እኩይነት በዓላማችን መንሠራፋቱ ትክክል አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ቅዱስና ከሁሉም በላይ ስለሆነ በእርኩሰትና በክፋት ከተሞላው የፍጥረቱ ሁኔታ ጋር ግኑኝነት የለውም፡፡ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር ግኑኝነት ያደርጋል ማለት ከፍጹማዊ ጠባያቱ ጋር ይጋጫል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ካለ የፍጥረቱ አካል ያልሆነ ነው፡፡ ለምሳሌ የአርስቶትሉ የማይንቀሳቀስ አንቀሳቃሽ፡፡"* (ካሳሁን አለሙ፣ ተጠየቅ ድህረ ገጽ)ፍልስፍና ሊኖርም ላይኖርም ይችላል በሚለው አቋሙ እንደቀጠለ ሲሆን ሳይንስ ግን በተቻለ መጠን ተፈጥሮን ከተፈጥሮ ህግ አንጻር መተንተን ስለሚቻል እግዚአብሔር አስፈላጊ አይደለም ወደሚል አዝማሚያ ላይ ደርሷል፡፡ ምን አልባት የተፈጥሮን ህግ እንደ እግዚአብሔር ከወሰድነው የአልበርታን አንስታየንን ሰዋዊ ያልሆነ (Impersonal god) አቋም ያዝን ማለት ነው፡፡

Created in Master PDF Editor

4. አማልዕክት ምናባዊ (Imaginary) ናቸው

It is easy to prove to yourself that God is imaginary የሚለን ማርሻል ብሬን God is imaginary በሚል ድህረ ገጹ 50 የሚሆኑ ማስረጃዎችን ከምርቃን (Bonus) ጋር ተንትኖታል:: ወደ ኤቲዝምነት ከገፋፉኝ ድህረ ገጾች ዋነኛው ይህ ድህረ ገጽ ነበር:: አንብቦ ለመረዳት ቀላል መሆኑ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ (Comprehensive) ነው:: በነገራችን ላይ ማርሻል ብሬን (Marshall Brain) ረቂቅ ትንታኔ የሚያስፈልጋቸውን ሃሳቦች በአጭሩና በቀላሉ የሚያስረዳ የበርካታ መጽሃፍት ደራሲና ብሎገር ነው::በዚህ God is imaginary ሲል በሰየመው ድህረ ገጹ ላይ የሚከተሉትን ማስረጃዎች ተንትኗል፣ ቀጥሎ የዘረዘርኳቸው እንድታነቧቸው ለመጋበዝ ነው::

Try praying, Statistically analyze prayer, Look at all historical gods, Think about science, Read the Bible, Ponder (contemplate) God's plan, Understand religious delusion, Think about Near Death Experiences, Understand ambiguity, Watch the offering plate, Notice that there is no scientific evidence, See the magic, Take a look at slavery, Examine Jesus' miracles, Examine Jesus' resurrection, Contemplate the contradictions, Think about Leprechauns, Imagine heaven, Notice that you ignore Jesus, Notice your church, Understand Jesus' core message, Count all the people God wants to murder, Listen to the Doxology, Ask why religion causes so many problems, Understand evolution and abiogenesis, Notice that the Bible's author is not "all-knowing", Think about life after death, Notice how many gods you reject, Think about communion, Examine God's sexism, Understand that religion is superstition, Talk to a theologian, Contemplate the crucifixion, Examine your health insurance policy, Notice Jesus' myopia, Realize that God is impossible, Think about DNA, Contemplate the divorce rate among Christians, Realize that Jesus was a jerk, Understand Christian motivations, Flip a coin, Listen when "God talks", Realize that a "hidden God" is impossible, Think about a Christian housewife, Consider Noah's Ark, Ponder Pascal's Wager, Contemplate Creation, Compare prayer to a lucky horseshoe, Look at who speaks for God, Ask Jesus to appear.

Bonus!

Compare God and Baal, Watch your Minister, Pastor or Priest, Think about Marriage in the Bible, Understand the Power of Doublethink, Understand God's Monstrosity (Atrocity), Comprehend God's Many Contradictions, Consider Eliminating Religion, Note all of the excuses, Contemplate the Watchmaker and Intelligent Design, Think about Noah's Ark as an Intelligent Person, Contemplate other imaginary things, Think about Santa, Consider Evolution, Understand the Bible's ambiguity, Examine all the Evidence, Ask a simple question and Acknowledge the Bible's Insanity.

Created in Master PDF Editor

አማልዕክት ምናባዊ ድርሰቶች ከሆኑ ለምን ይታመንባቸዋል? አማኞች በሚያመልኩባቸውና እምነታቸውን በሚገልፁባቸው ቤተ እምነቶች ከሚከውኑት፣ ከሚፅፏቸው ፅህፎችና ከሚያራምዷቸው አቋሞች በመነሳት ለምን እንደሚያምኑ ማወቅ ይችላል:: በአንድ አምላክም ይመኑ በብዙ የሶሾሎጅና የሳይኮሎጅ ሙህራን ከሚያስቀምጧቸው ምክንያቶች የሚወጣ አይመስለኝም:: እምነት ነክ ምክንያቶቹ ሀይማኖትን ለማስቀጠል ሚናቸው እጅግ ከፍተኛ ቢሆንም እውነተኝነታቸው ግን ጥያቄ ውስጥ ነው:: አማኞች እግዚአብሔር አለ ካሉ ማስረዳት አለባቸው:: መናፍቃንና ካሂዲዎች ለሚሉን ለእኛ ለማሳየትና ማሳመን ይጠበቅባቸዋል:: ኢ-አማኞች አስቸጋሪ ባህሪያችን አማልዕክትን በተመለከተ ካላየን አናምንም:: እኔን ጨምሮ እግዚአብሔር በቢ.ቢ.ሲ፣ በሲ.ኤን.ኤን፣ በኢ.ቢ.ሲ፣ በፋና፣ በኢሳት፣ በአልጀዚራ፣ በኒዮርክ ታይምስ፣ ወይም በማንኛውም መገናኛ ብዙሃን መግለጫ እንዲሰጥ እንፈልጋለን:: ለብዙ አማኞች ይህ ፍላጎት ሞኝነት ይመስላቸዋል:: በፅሁፎቻቸውና በሰብከቶቻቸው የሚወርፉን ከምንም አንቆጥራቸውም የምንፈልገው የሰማዩን አለቃ ንጉሱን ብቻ ነው:: ጋሻ ጃግሬዎቹሰልችተውናል:: ጉዳያችን ከንጉሱ ጋር እንጅ ከኮልኮሌዎቹ ጋር አይደለም:: ጉዳያችን ከሁሉ ጌታ ጋር እንጅ ከእስራኤል አምላክ፣ ከግሪክ አማልዕክት፣ ከግብፅ ጣኦታት፣ ከአረቢያው መልዕክተኛና ከየዘመናቱ መናፍስት ጋር አይደለም::

እኛ የምንፈልገውን እንከን የለሽ ፈጣሪ ፈልገን አጣነው:: ያጣነው ስለተሰወረ አይደለም ስለሌለ እንጅ:: አምላክ ከሚያምኑት ይልቅ ለማያምኑት ቅርብ ነው ይፈልጉታልና:: ችግሩ የሚያምኑት የአመኑትን ሲፈጥሩት ያለመኑት ግን ገና ይፈልጉታል:: የሰው ስልጣኔ ከተጀመረ ጀምሮ ፈለግነው አልተገኘም ለምን አሁንም መልሱ ስሌለለ እንጂ ድብብቆሽ የሚጫወት ህፃን ሆኖ አይደለም:: ማርሻል ብሬን Why Won't God Heal Amputees በሚል ድህረ ገጹ ላይ እንዲህ ይላል፦

<<It is plainly obvious to any intelligent human being that all human gods are imaginary. The belief in God and prayer is pure superstition, nothing more. It has come time for rational, intelligent people to openly discuss this fact because superstition and fraud are harmful to society. There is not a single piece of empirical evidence showing that God is real. There is a mountain of evidence showing that God is imaginary. God is a completely imaginary, mythological being that springs from human imagination.>>

ኢ-አማኞች እግዚአብሔር የለም ብንልም አማኞች ግን ዛሬም አለ ይሉናል:: ችግሩ አለ የሚሉት የፈጠራቸውን ፈጣሪ አምላክ ወይም አማልዕክት ሳይሆን ፈጠሩትን ምናባዊ አምላክ ነው:: ከድሮ እስከ ዘንድሮ ስለእነዚህ መናባዊ ሀይሎች አማኞች ተከራክረውላቸዋል:: አብዛኛዋቹ ክርክሮች ከቅዱሳን መፅሀፍት፣ ከፈልስፍና፣ ከሳይንስ እና ከማህበራዊ እሳቤዎች የመነጩ ስለሆነ ተቀባይነታቸው ከፍተኛ ነው:: ከእውነትና

Created in Master PDF Editor

ከፍትህ አንፃር ግን መፈተሹ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ሰዎች ብዙ በተማሩና በተመራመሩ ቁጥር የአማልዕክት ነገር እንደተረተ ይሆንባቸዋል፡፡ አማኞቹ ስለዚህ ሲጠየቁ ሰይጣን አሳስቷቸው ነው ይላሉ፡፡ ከዚህ የተነሳ ትምህርት በተለይም የሳይንስና ፍልስፍና ትምህርት የተጣለ ሁኗል፡፡ ብዙዎች የሚማሩት እንጀራ ለማብሰል እንጅ ለማብሰልሰል ያልሆነው ለትምህርቱ ጥላቻ ስለላቸው ነው፡፡ ደስ የሚለው ነገር አክራሪ አማኞች ሳይቀር ሰለሳይንሳዊ ምርምር ሂደቶችና ውጤቶች ሲነገራቸው ይደነግጣሉ፡፡ እምነታቸው እንዳይሸረሸር ስለሚፈሩ እራሳቸውን ይደብቃሉ፣ ሰይጣንን ይከሳሉ፡፡

ፍራታቸው እውነት ነው ልቦናቸው ለምርምር ከፍት የሆኑት የሲውድን፣ የዴንማርክ፣ የኖርዌ፣ የጃፓን፣ የካናዳ፣ የፈረንሳይ፣ የእንግሊዝና የሌሎች የበለፀጉ ሀገራት ህዝቦች አያምኑም ቢያምኑም እንደተባለውና እንደወረደ ሳይሆን እንደገባቸው ተርጉመው ነው፡፡ በቅዱሳን መፅሐፍት የተገለጡትን አማልዕክት እንደወረደ የሚያምኑ በድሃ ሀገራት ያሉት ያልተማሩ የዋህ ዜጎች ናቸው፡፡ ይህን የምለው እኔ አይደለሁም ምርምሮች እንጅ፡፡ ስለዚህ ከአለም የጋረደንን ሀይማኖት የሚሉት ህይወትን የመሰጠት ኑዛዜ ለመሻር ዋናው ቁልፍ መማር ነው፡፡ የተማረ፣ ያነበበ፣ የተመራመረ ሰው የሚያወራው ከሚሰማው ወንድሙ ጋር ሲሆን የሚኖረው በቅዠት ሳይሆን በእውነት ነው፡፡ ከቅዠትና ከእውነት የቱ ይከብዳል?

"Life is very hard, and facing death is difficult to endure. Belief in god places people into a form of regression, a return to the "safety" of childhood. People receive a sense of security believing that they have a god, the father." የሳይኮአናላይስቱ ሲግመንድ ፍሮይድ ፍልስፍና ነበር፡፡ በሳይኮአናላይስቱ ሲግመንድ ፍሮይድ እና በበርካታ የስነ-ጽሁፍና ፍልስፍና ባለሙያዎች ትልቅ መነሳሳት የፈጠረው የእግዚአብሔር ምናባዊነት ያወጀው ፍሬድሪክ ኒቼ ነበር፡፡ በፍሬድሪክ ኒቼ ዘመን በሀልወተ እግዚአብሔር ዙርያ መቅበዝበዞች ጨምረው ነበር፡፡

በዚህ ሁሉ መቅበዝበዝ መሀል አንድ አማራጭ ዜና ከወደ ጀርመን ተሰማ፡፡ ነውጠኛው ፍሬድሪክ ኒቼ ታላቁን የምስራች ነገረን እግዚአብሔር ሙቷል፣ሰው ነጻ ውጥቷል፡፡ ኒቼ እግዚአብሔርን ሬሳ የቀበሩ የመቃብር ቆፋሪዎችን ድምጽ አልሰማችሁምን ይለናል፡፡ እግዚአብሔርን ማን ገደለው ብንለው እናንተም እኔም ገድለነዋል አለን ድሮም ምናባዊ እንደነበር ለማስረዳት፡፡

ታድያ ምን እንሁን ብንለው ደስ ይበላችሁ የሰው ልጅ ነጻ ነው አለን፡፡ ኤቲስቶች አሜን ብለን ተቀበልነው ነጻነት ከሁሉ እንድሚበልጥ ስለምናውቅ፡፡ ብዙዎች ግን የምስራቹ መርዶ ስለሆነባቸው አጉረመረሙ፣ ዘመኑ 19ኛው ክ/ዘመን ስለነበርና

Created in Master PDF Editor

በአደባባይ ይሰቅሉት ዘንድ ስልጣን ስላልነበራቸው ዝም አሉ። ዘመኑ የመካከለኛው የጨለማ ዘመን ቢሆን ኑሮ ህይወቱና ስራዎች የእሳት እራት ይሆኑ ነበር።

ጀርመናዊ ጻህፊና ፈላስፋ ፍሬደሪክ ዊልሄልም ኒቼ (1844-1900) አለምን ይቀይራሉ ብሎ ያመነባቸውን ብዙ መጻህፍት በመድረስ ይታወቃል። ኒቸ በዘመኑ ብዙ ተቃዋሚወችና አድናቂዎች አፍርቷል። የሚያደንቁት ብዙ ሰወች ስራወቹን እንደ ታላቅ የፍልስፍና እና ስነ ጽሁፍ ስራ ይወስዷቸዋል። ኒቼ አብዛኛው ጽሁፉ የሚያተኩረው ሰወች እንዴት ሊኖሩ ይገባቸዋል? በሚለው ጥያቄ ነው። በዚህ ምክንያት በሥነ ምግባር ዙርያ ብዙ እንደተመራመረና እንደጻፈ ይነገርለታል። በዘመኑ ክፍተኛ ቦታ የሚሰጣቸውን አማልዕክት ከጥንቶቹ አማልዕክት ያልተሻሉ መሆናቸውን ለማስረዳት ጥሯል።

ጥንታዊ የአማልዕክት መጻሕፍትን በከፍተኛ ፌዝ እናነባለን። በአፈ ታሪክ የተሞሉ ትርክቶች እንደሆኑ ሁላችንም እንስማማለን። እነዚህ ታሪኮች ዛሬን አያርገውና የዘመኑን ፍልስፍና፣ አኗኗርና ለዘለዓለማዊ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የተደረሱና የተተረኩ ነበር። ዛሬ ግን በእየ ቤተ መዘክሩ እንዲሁም በእየቅርስ ጥናት ቦታዎች እንደዋዛ ይጎበኛሉ። ሽፋን ሲሰጧቸው የነበሩት ካህናትና ነገስታትም ለዘለአለም አሽልበዋል።

ታድያ ለምን የት ሄዱ? መንፈሳቸውን ማን ቀማቸው ብሎ መጠየቁ ተገቢ አይደለምን?Lemuel K. Washburn በመገረም ይጠይቃል። “Where Are They? Where are the sons of gods that loved the daughters of men? Where are the nymphs, the goddesses of the winds and waters? Where are the gnomes that lived inside the earth? Where are the goblins that used to play tricks on mortals? Where are the fairies that could blight or bless the human heart? Where are the ghosts that haunted this globe? Where are the witches that flew in and out of the homes of men? Where is the devil that once roamed over the earth? Where are they? Gone with the ignorance that believed in them.” (Lemuel K. Washburn, page, 65)

እርግጥ ነው በድሮ ገዜ ሰው ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ አማልክትን ከማምለክ ውጭ አማራጫ አልነበረውም። ከሞት በኋላ ሕይወት አለ የሚባለው ግምት በአብዛኛው ከጥንታዊ ባሕል፣ ከህይማኖት ባለስልጣናት ትምህርት እና ከሳይንስ ማበብ በፊት ከተጻፉ መለኮታዊ መጽሐፍት የተወሰደ ነው።

ቀናተኛ አማኞችም የአምላካቸው መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ መፅሀፍትን ይልቁንም ራሳቸውን መጠየቅ አይደፍሩም የተነገራቸውን በደመ ነፍስ የሚያምኑ ናቸው። በተቃራኒው በጣም አሳቢ እና ክፍት-አእምሮ ያላቸው አማኞች ሀይማኖታቸው ክፍተት አንዳለበት ይረዳሉ ጨክነው እንደይቃወሙ ግን ይፈራሉ።

Created in Master PDF Editor

ለራሳቸው አማኝ እንደሆኑ ይገነዘባሉ አጉል ባህሎችን ለመተው እና አዳዲስ አስተሳሰቦችን ለመቀበል ዝግጁ ናቸው በተለይም በግርድፉ ከሚያምኑት እምነት ጋር አዳዲስ አስተሳሰቦችን ለማዋሀድ ይሞክራሉ።

ተጠራጣሪ መሆን ያስፈልጋል። በእኔ ምልከታ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ እና ምክንያታዊነት ብቻ ነው። በግለሰብ ደረጃ የተደረጉ ልዩ መገለጦች ለሌሎች ከተረት የዘለለ ትርጎም የላቸውም። ሀያሉ አምላካችን በድብቅ ለአንድ በግ እረኛ ብቻ የሚገለጥበት ምክንያት የለውም። እስከገባይ ድረስ የአሁኖቹ ታላላቅ ሀይማኖቶች ከድሮዎቹ የተሻለ እውነት የላቸውም።

I know bible is a book of mythology and god is imaginary. አስተዋይ የሆነ ሰው እንዴት አወክ ሊለኝ ይችላል። God is imaginary እንድል ያበረታታኝ በዋናነት ራሱ መጽሃፍ ቅዱስ ነው። እንዴት መጽሀፍ ቅዱስ የተረት መፅሀፍ ሊሆን ይችላል? እንዴትስ የአምላክን ምናባዊነት ያስረዳል? ጥሩ ጥያቄ ነው አንድ ምሳሌ ልጥቀስ? ምሳሌው የኖህ መርከብ ትርክት ነው።

የዛሬ 4,000 አመት ገዳማ ነው አሉ። እግዚአብሔር በሰው ልጆች ተቆጣና ስነ ፍጥረትን ሊቀጣ ፈለገ። አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ ቢሆንም ቅሉ የተወሰኑ ዝርያዎችን ታሪካዊቷ መርከብ የምትችለውን ያህል ባልና ሚስት እንየሆኑ እንዲገቡ አዘዘና የእልቂቱን ዝናብ አወረደው። ሰማይ ተከፈተ ዶፍም ወረደ ተራሮች ተሸፈኑ፣ ከመርከቧ ውጭ የነበሩ ፍጥረታት በሙሉ ሞቱ። በሚገርም ሁኔታ በጥቂት ጊዜአት ውስጥ ውሃው ጎደሎ ህይወት እንደገና ጀመረና ዛሬ ላይ ደረሰን። ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ። ይህን ትርክት እንደ እውነት ለሚወስዱ ሰዎች መመለስ የማይችሉት ጥቂት ጥያቄዎች ላቅርብ።

1ኛ. ለእልቂት የሚያበቃ ሃጥያት ተፈፅሟል ወይ? ምን አልባት አወ ካላችሁ ጥፋቱን የፈፀመው ማን ነው? ምን አልባት ሰው ትሉኝ ይሆናል። የት አካባቢ የነበሩ ሰዎች? ምን አልባት ፍረዱ አለም አቀፋዊ ስለነበረ ሁሉም ልትሉኝ ይሆናል። ይሁን ግድ የለም ግን እንስሳት እና እፅዋት ምን አደረጉ? ምን አልባት እነሱም በድለው ይሆን? ኢ-ፍትሀዊነት አይታያችሁም?

2ኛ. እሽ ዝናቡ ዘንቧል እንበል መሬት ሙሉ በሙሉ ውቂያኖስ ሆና ነበር ማለት ነው። አንድ ውቂያኖስ ለመትነን ስንት አመት እንደሚፈጅበት ገምቱ እስኪ። ውሀው የትም ሊሄድ አይችልም ሁሉ ውሃ ነውና። ታዲያ እባካችሁ ውሃውን ምን በላው? በአስማት ተኖ ከሆነ ለምን አልተነገረንም?

3ኛ. እሽ ዝናቡም ውሃውም ጎደለ እንበል። የፍጥረታት ቅሬተ አካል የት ሄደ?

Created in Master PDF Editor

4ኛ. በተፈጥሮ ጥንድ የሌላቸው ፍጥረታትስ ወደ መርከቧ ያልገቡት ለምንድን ነው? አሁንስ ለምሳሌ ባክተሪያ ለምን ይኖራሉ። እፅዋትስ ዘራቸው ከሞተ በኋላ ከየት መጡ? በመፅሀፍ ቅዱስ ስነ ፍጥረት ምዕራፍ 1 እና 2 ሁለት ጊዜ የፍጥረት ስራ ሰርቷል ከኖህ ንፍረ ውሃ በኋላም 3ኛ ስነ-ፍጥረት ሳይኖር አይቀርም።

5ኛ. መርከቧ የት ገባች? በተለያዩ ሀገራት ዛሬም የኖህ መርከብ በሀገራቸው መገኘቷን የሚተረኩ ፅሀፍት አሉ። የቱን ማመን እንዳለባችሁ እናንተ እውቁበት እንጅ መርከቧ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለመሆኗ መጽሀፍት ተፅፈዋል። ስብከቶች ተሰብከዋል።

6ኛ. ማስረጃ የለም። እውነት ለመናገር ድንጋይ ዳቦ ነበርን?እና ውሃም ወተት ነበርን የሚለውን ለማረጋገጥ ምርምር መሰራት አልነበረበትም። ቢሆንም የኖህ መርከብ ትርክት በብዙሀኑ የታመነ በመሆኑ የምርምር አጀንዳ መሆኑ አልቀረም።

ቢሆንም በጆኦሎጅ እና በተያያዘ ሳይንሶች ውስጥ በቅንነት የሚገለግሉ ሙህራን ጉዳዩ ተረት መሆኑን አረጋግጠዋል። እንዴት ባለፉት 8,000 ዓመታት ውስጥ እንዲህ አይነት ክስተት አልተከሰተም በተጨማሪም አለም አቀፋዊ እልቂቱን የሚስረዳ ቅሬተ አካል አልተገኘም። የዛሬ ሚሊየን አመታት የተከሰቱ እልቂቶች ሲደረስባቸው የዛሬ 4,000 ዓመት የተከሰተ እልቂት እንዴት ማስረጃ ይታጣበታል?

7ኛ. የኖህ መርከብ ትርክት የተኮረጀ መሆኑ ተረጋግጧል። የኖህ ትርክት በመካከለኛው ምስራቅ ሲነገሩ ከነበሩት ያልተኮረጀ ስለመሆኑ ምን ማስረጃ አላችሁ? በነገራችን ላይ የመፅሀፍ ቅዱስ ታሪክ ሙህራን እንደሚመሰክሩት መጽሀፍ በአብዛኛው የተኮረጀ ነው።

8ኛ. ሁሉም ነገር እውነት ይሁንና ከኖህ መርከብ የወጡት ፍጥረታት በምን ፍጥነት ቢባዙና ቢለወጡ ነው ዛሬ ለዚህ ውብ ብዙሃዊነት የበቁት? እባካችሁ መርከቧ ጣና ሀይቅ አካባቢ ከሆነ ጭነቷን ያራገፈችው ፍጥረታት ወደ ምዕራብ እስከ አሜሪካ ወደ ምስራቅ እስከ ቻይና፣ ጃፓን፣ አውስትራሊያ ድረስ የተሰራጩት በነፈስ ነው እንዴ? ፍጥረታት ይህን ያህል እርቀት እንዲሰደዱስ ምን አስገደዳቸው? አንዳንዶች ሲቀሩ ሌሎች ዝርያዎች ደግሞ አንድም ሳይቀሩ የተሰደዱት ለምንድን ነው? ያኔም ከክልሌ ውጣልኝ የሚለው አስተሳሰብ ነበር እንዴ?

9ኛ. ይህን መሰል የሚያስተዘዝቡ ትረክቶችን የያዘ መፅሀፍ The Book of Mythology ቢባል ችግሩ ምንድን ነው? ዋና ተዋነኙን God is Imaginary ብንለውስ? አይመስላችሁም?

Created in Master PDF Editor

5. የተዛባ ማስረጃ (Wrong Evidence)

➢ **የያዝኩት በቂ ነው።**

በበለፀጉትና ትምህርት በተስፋፋባቸው ሀገራት ጭምር የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በሚያሳዝን የአንዱ እምነት አማኞች ስለ ሌሎች ሀይማኖቶች እውቅና የላቸውም። የሚያስደነግጠው ደግሞ የራሳቸውን የሚያውቁት ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው። ያ ማለት የሚያምኑት የማያውቁት ነው ማለት ነው። እኔም በገሌ ይህን ምርምር በመንፈሳዊ ኮሌጅ ውስጥ በመገኘት አረጋግጫለሁ። በእየለቱ የሚሰበኩትን ስብከት የት እንደሚያተኑት ግራ ይገባኛል። ይህ ችግር በተራው አማኞች ብቻ ሳይሆን ብዙ ያውቃሉ የምንላቸው ሰባኪዎች እንኳ መሰረታዊ የሆነ የእምነት እውቀት ችግር አለባቸው። እውነት ለመናገር ስነ መለኮት ሳጠና ፈተና ያስኮረዥኳቸውም አሉ። (ኩረዡን እያበረታታሁ ሳይሆን ላለመጠቆር ያደረኩት ነው) በነገራችን ላይ መቅደም ያለበት መሰረታዊ ነገር ማወቅ ነው ወይስ ማመን? ለብዙዎቹ ግን ብቸኛው ማስረጃ እምነት ብቻ ነው። እምነት ደግሞ የተዛባ ማስረጃ ነው።

➢ **ህይወቴ ተቀይሯል።**

እምነት እጅግ ግላዊ ከመሆኑ የተነሳ ከሰው ሰው ይለያያል። ሁሉም ያመኑትን ብቸኛ የህይወት ቀያሪና ዘዋሪ መርህ አድርገው ይወስዱታል። ግላዊ ጉዳይ በአደባባይ ሲመሰከር የሀይማኖት ስብከት ይሆናል።ኦርቶዶክሶች፣ ካፒቲኮች፣ ፕሮቴስታንቶች፣ ሙሉሊሞች፣ ሳይንቶሎጅስቶች፣ አኒሚስቶች፣ ሌሎችም ሌሎችም አምላኮቻቸው ህይወታችን እንደቀየሩት ይሰብካሉ። በተለይ ሀይማኖታቸውን ከሚቀይሩ ሰዎች ይህን መሰል ንግግር መስማት የተለመደ ነው። የሚያሳዝነው ደግሞ የመጀመሪያ ሀይማኖታቸውን እንደ ባርነት ዘመን መቁጠራቸው ነው። ይህን ለማረጋገጥ ከዘማሪት ዘርፌ ከበደ ጀምሮ መስማት ነው። ህይወት ቀያሪው ጌታ የት ነው?ተገልጦ ያናግረን ይሆን?

ክርስቶስ ከሞተ በኃላ ለብዙ ሰዎች እንደተገለጠላቸው በወንጌል ተገልጿል። ዛሬም እነ ተክለ ኪዳን፣ ንቡረ ዕድ ኤሪሚያስ ከበደ እና ሌሎች እንደተገለፀላቸው ፅፈዋል፤ ሠብከዋል። እኛም በማቴ ምዕ 28፣ በማርቆስ ምዕ 15፣ በሉቃስ መዕ24፣ በዮሐንስ ምዕ 20 እና 21 እንዲሁም በሐዋሪያት ስራና በቅዱስ ጳውሎስ መልዕክቶች መሠረት አድርገን ጌታ እንዲገለፅልን ብንጠይቅ መደፋፈር ሊሆን ይችላል? ከቅዱስ ጳውሎስ የባስስ አሳደነዋል? ደግሞስ ምንም ያህል ሀጢአተኛ ብንሆን ከተመለሰን ሊሰማን ፍጹማን ሊያደርገን ቃል ገብቶልን ነበር አይደል። ሰባኪዎች ግን ይህን የመገለጥ ሙከራ ጥያቄ እንዳናቀርብ የሚከለክሉን የተለያዩ ምክንያቶች ይደረድራሉ። ለምሳሌ፡- ፍቃዱ ባይሆንስ፤ ከጊዜ በኃላ ቢሆንስ በተለይ በምዕአት፤ ይህን ታምር ለማየት

Created in Master PDF Editor

እምነት የለንም፤ በቂ አይደለንም፤ በትክክለኛው መንገድ ባንፀልያስ፤ አትፈታተኑኝ ማለቱን መርሳት የለብነም፤ ለቅዱስን የተገለጠላቸው በቂ ነው፤ ጌታ ስላረገ አይታይም፤ ጌታ መንፈስ ስለሆነ አሁንም ከኛ ጋር አብሮ አለ፤ ጌታ በአካል ከመገለጥ ይልቅ በልባችን ከተገለጠ በቂ ነው፤ ወዘ.ተ ይህን ሁሉ መላምልት የሚደረድሩት ሰባኪዎች ጌታ ለማንም ግልፅ በሆነ ሁኔታ እንደማይገለጥ ስለሚያውቁ ነው። ታድያ መሠረታዊ ስለሆነው መገለጥ ካልፀለይን ስለምን እንድንፀልይ ይጠበቃል? ስለ የእለት እንጀራ ከመጸለይ ይህ አይሻልም? ችግሩ መገለጥ በህልም እንጅ በእውናዊ አለም የለም።

➢ **እግዚአብሔር ባይኖር ማመን እንዴት ተስፋፋ።**

እኔ አርዮስ የፕሮፖጋንዳ ፀሀፊ አይደለሁም ከጀምላው ጋር አልጀምልም። ይህን ያልኩት ብዙ ሰዎች እውነቱን እያወቁ ስለሚዋሹ ነው። ምን አልባት አንዳንዴ ለውሽታቸው ምክንያት አላቸው ብዙ ጊዜ ግን ከመንጋው ክብር ለማግኘትና ለውሎ አበል ብለው ነው። በኢትዮጵያ ሚድያዎች ስንት ውሸት እንደሚዋሽ ያልደረሰበት የለም። የእኔ አቋም ህዝብ እንደ ህዝብ ባለመረዳት ሊሳሳት ይችላል ባይ ነኝ። ሀይማኖቶችም ምንም ያህል ተከታይ ይኑራቸው ሊሳሳቱ ይችላሉ። እውነት ከብዛት ጋር ምንም ቁርኝት ኑሯት አያውቅም። ይሄን የዘነጉት ሰባኪዎች ብዙ በማሰመን፣ ብዙ አማኝ በማፍራት የእምነታቸውን እውነተኛነት ለማረጋገጥ እየደከሙ ይገኛል።

➢ **ደርሶ መልስ።**

በዘመናችን የሰባኪዎች ችገር የሆነው እግዚአብሔር ሳያዩት ለምን ይሰብኩታል ቢሆንም ሂደን አይተነዋል የሚሉ ከዛም ከዚህም አልጠፋም። አንዳንዶቹ የሚያስጎመዥ ታሪክ ተረክውልናል። እነዚህ በአካል ያለምንም መሳሪያ መንበር ፀበኦትን ጎብኝተው የሚመጡ የአይን እማኞች የሚቀርቡትን ትንታኔ የማመን ግዴታ ቢኖርብን እንኳ ሂደው ስለመምጣታቸው ነገሩን እንጅ ሲነጠቁና ሲመለሱ በአደባባይ ያየ የለም ይህም ይቀር እንደማስረጃ ያመጡት አንዳች ነገር የለም። በማራኪ ታሪክ ልባችንን ቀጥ አደረዱት እንጅ ምንም አልፈየዱልንም።

➢ **ኢንተሊጀንት ዲዛይን (ID)።**

አሁን አሁን የድሮዎቹ መረጃዎች የከሸፉባቸው ሰባኪዎች ሽር ጉድ የሚሉበት የቆየ ግን እንደ አዲስ የተሞሸረ ማስረጃ አለ። ይህም ኢንተሊጀንት ዲዛይን (ID) ይባላል።

ታሪኩ እንዲህ ነው። የእምነት ድርጅቶች የሚፈለፈሉባት የአማኞች ደሴት የሆነችው አሜሪካ ዝግመተ ለውጥ በትምህርት ቤቶች ማስተማር ከልክላ ነበር። በኋላ በኋላ ከመፅሀፍ ቅዱስ ጋር ጎን ለጎን ለማስኬድ ስለፈለገችና ጊዜውም ስላስገደዳት ዝግመተ

Created in Master PDF Editor

ለውጥ በትምህርት ቤቶች ማስተማር ጀመረች። የፈራችው አልቀረም ተማሪዎችን ከዘፈጥረት ትንታኔ ይልቅ በዝግመተ ለውጥ ተማረኩ። ጥናትና ምርምሮችንም ሰሩ። አሁንም ዝግመት ለውጥን በአሜሪካ ማስተማር ብዙ ቢቀረውም የሙሴውን ዘፍጥረት ግን ከጭዋታ ውጭ አድርጎታል። ይህ ያበሳጫቸው ክርሽናሊስቶች(Crentionalists)የተሻሻለ ፈጣሪ ፈጥሯል ID(Intelligent Design) ይሉታል። ሀሳቡ በፍልስፍናው አለም የቆየ ቢሆንም አሁን አሁን እንደ አዲስ አገርሽቶ ዝግመተ ለውጥ ልክ ነው ነገር ግን ሂደቱን በጥንቃቄ የመራው ID ነው ይላሉ።

IDን አስመልክቶ ፈላስፋው ዘርዓያዕቆብን እንዲህ ሲጠይቅና ሲመልስ ነበር ነበር፦ "በአርያም የሚያውቅ አለን? አዋቂስ አድርጎ የፈጠረኝ ማነው? በዚህስ አለም እኔ እንደምን መጣሁ? እኔ በገዛ እጄ ተፈጠርኩን?" ይልና መልስ ሲሰጥ *"እኔ በተፈጠርኩ ጊዜ አልኖርኩም። አባት እናቴ ፈጠሩኝ ብልም እንደገና ወላጆችና የወላጆችን ወላጅ፣ ወላጅ የሌላቸው በሌላ መንገድ ወደዚህ ዓለም የመጡትን እንደኛ ያልተወለዱትን የፊተኞቹ ድረስ ፈጣሪያቸውን እፈልጋለሁ። እነርሱም ቢወለዱ የፈጠራቸው አንድ ህላዌ አለ ከማለት በቀር የጥንት መወለዳቸውን አላውቅም። ያለና በሁሉም የሚኖር የሁሉ ጌታ ሁሉን የያዘ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዓመቱ እማይቆጠር እማይለወጥ ያልተፈጠረ ፈጣሪ አለ አልኩ።ፈጣሪስ በውኑ አለ አልኩ፤ ምክንያቱም ፈጣሪ ከሌለ ፍጥረት ባልተገኘም ነበረ።"* ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብ፣ ምዕራፍ፦3

ችግሩ ይህ ID የተባለ ፈጣሪ ወንጌል አላፃፈም፣ መልዕክተኛም አላከም፣ ቀኖናውን እና ዶግማዎቹን የሚመስኑለት ቄሶች አልመረጠም። የዚህ አስቸጋሪ አመክንዮ መሰረታዊ ችግሩ ሳይንስና እግዚአብሔር እየቀለቀለ መሆኑ ነው። እንደኔ አመለካከት ሁለቱ ዘርፎቹ የሚጋሯቸው ጉዳዩች ቢኖሩም ባልሆነ መልኩ ለማዋኸድ መሞከር ግን ውሃና ዘይትን እንደመቀላቀል፣ ቀበሮና በጎችን በአንድ እንደማስፈር ነው። ID ሌላው ችግሩ ሳይንስን እግር በእግር እየተከተለ እኔ ነኝ ማለቱ ነው። ሳይንቲስቶች ስንት ደክመው የሚያስደምም ጥናታዊ ውጤት ሲያገኙ የID አማኞች ይህን ያደርገው የኛው ID ነው ይሏቸዋል። የID አማኞች ከመልሱ ወደ ጥያቄው ሲሄዱ ሳይንቲስቶች ደግሞ ከጥያቄው ወደ መልስ እየገሰገሱ ይገኛሉ።

በአብዛኛው ሳይንቲስቶች ጥናት መሰረት ግን "ተፈጥሮ አሁን ላይ ከደረሰበት ዲዛይንና ስርዓት ከመድረሱ በፊት ለሚሊዮን (ቢሊዮን) አመታት በጣም አዝጋሚ በሆነ የለውጥ ሂደት ውስጥ አልፏል። በመሆኑም ፍፁም የሆነው ዲዛይነር እግዚአብሔር ሳይሆን ዝግመተ ለውጥ ነው።" (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 22)

የኢትዮጵያ ሙህራን ግን ከየትም ወደ የትም እየሄዱ አይደለም ወይም ገና በልጅነት ከተማሩት ድንጋይ ዳቦ ነበር ትረት ላይ ናቸው ከጥቂቶቹ በስተቀር። እንዲያውም

Created in Master PDF Editor

ለሙህራን ማህበረሰባዊ ባህሎችን እንደ አጀንዳ አድርጎ መነጋገር እርማቸው ነው። እባካችሁ ስለ ዝግመተ ለውጥ እንኳ ቢቀር ስለ ID መነጋገር እንጀምር። <ሳንታ ኮሎስ> ላይ እስከ መቸ ሙጥኝ እንበል። ሳንታ ኮሎስ ለህጻናት የትም አይሄድም አለ።

- ***ታምራት ያረጋግጣሉ።***

የቴሌቨንጋሊስቶችን ቻናሎች እያቀያየርኩ ምርመራ አደረኩ። ምንም የሚያሳምን ታምር ሲሰራ አላየሁም። አንዳንዴ በሚሆነው ነገር እገረማለሁ። አማኞችም ተፈዋሾችም ሲያለቅሱ አለቅሳለሁ። በየቻናሎቹ ያየሁት ግን ከፊልምነት የዘለለ የሚሳምን ነገር አላየሁም። በእርግጥ ጉዳዩን ቀርቤ እስካልመረመርኩ ድረስ ሙሉ በሙሉ መከድ አልችልም። ቢሆንም ቴሌቪንጋሊስቶቹ የሚተነብዩትን ትንቢት ሳስብ ግን ሆዴ እስኪቆስል እስቃለሁ። እንዲህ የሚስብ ሰው በዚህ ምድር መኖሩን ሳስብ እገረማለሁ። ከእህት ማርያም፣ ከመምህር ግርማ ወንድሙና ከፕሮቴስታንቶቹ ቴሌቪጋሊስቶቹ ጀርባ ያለውን ታሪክ ማጥናት የቤት ስራየ ነው።

ምን አልባት የተወገዙትም ያልተወገዙትም፣ የሚደነቁትም የሚተቹቱም ማጀካኖች የሚሰሩት ድብብቆሽ እንዳለ ይሰማኛል። ታይተው የጠፋ ብዙ ታምር አድራጊዎች በሀገራችን እንኳ ሰምተን ተደንቀን ዛሬ እረስተናቸዋል። ታስታውሳላችሁ ከሰማያት ደርሰው ስለመጡት ልጆች፣ ቅድስት ድንግል ማርያም ነኝ ብላ የመጣቸውንስእረሳችኋት፣ነብዩ ኤሊያስ ነኝ እያሉ የመጡትንስ እረሳችኋቸው? እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ የመጡትንስ እረሳችኋቸው? እኔ የምንጊዜም የስነ መለኮት እና የሶሽሎጅ ተማሪ ስለሆንኩ ችላ አልላቸውም።

ያም ይሁን ይህ የሚፈፀመው ትንግርት እውነት እንኳ ቢሆን የእግዚአብሔርን መኖር ለማረጋገጥ ብቁ አይደለም። ታምራት በእየ ቤተ እምነቱ ይፈፀማሉና። አሁን አሁንስ ማጀክ መስራት እንደፋሽን ሆኖ እምነት በሌላቸው ሰዎች ጭምር ለአይዶል ውድድር እያዋሉት ይገኛሉ በተለይ በእንግሊዝ እና በአሜሪካ። ስለዚህ God did it ከማለታችን በፊት ከጀርባው ያለውን ሚስጢር ማጥናት ይገባል።

- ***ሀይማኖቶች የጥበብ ምንጭ ናቸው።***

ያለምንም ጥርጥር ሀይማኖቶች ውስጥ ድንቅ ስነ ህንፃ፣ ድንቅ ስነ ፅሁፍ፣ ድንቅ ቅርስ እና የሚገርሙ ፍልስፍናዎች አሉ። ይህን የሚክድ ቅዱስ ላሊበላን ይጎብኝ፣ የግብፅን ፒራሚዶች ይጎብኝ፣ የድማስቆን መስጊዶች ይጎብኝ፣ የህንዱንታጅ መሀል ይጎብኝ፣ ቫቲከንን ይጎብኝ፣ ከሂማሊያ ተራራ እስከ ጣና ድረስ ያሉትን ገደማት ይጎብኝ የማይጠገብ የማይሰለች ጥበብ እንዳለ ይረዳል።

Created in Master PDF Editor

ልዩነቱ አማኞቹ እና ኤቲስቶቹ የሚያዩበት መነፀር ግን ይለያያል፡፡ ማድነቅ ሌላ ነው ማመን ሌላ ነው፡፡ ኤቲስቶች በሀይማኖት ቦታዎች ያለው ስነ-ጥበብ የሰው ልጅ የድካም ውጤትና ታሪካዊ አሻራ አድረገን እንወሰደዋለን፡፡ አማኞች ጣታቸውን ወደ አማልዕክቶች ይቀስራሉ፡፡

➢ **ታዋቂዎች ያምናሉ፡፡**

ታላቁ ሳይንቲስት አንስታየን እና የቅርብ ጊዜ ትዝታችን አስቴፈን ሀውኪንግ ሳይቀሩ ለዚህ አይነት ክርክሮች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የሚገርመው ሀውኪንግ የእግዚአብሔር ስም በተደጋጋሚ ቢጠቀስም የለየለት ኤቲስት ነበር፡፡ አንስታየንም በግልፅ ኤቲስት ነኝ አይበል እንጅ በእግዚአብሔር እንደማያምን በተደጋጋሚ ተናግሯል ጽፏልም፡፡ ያም ይሁን ይህ የሳይንቲስቶችና የታዋቂ ሰዎች ስም እየተጠቀሰ አካሌ ስለሚያምን እግዚአብሔር አለ ማለት ነው ማለት ሲበዛ ሞኝነት ነው፡፡

➢ **ትንቢቶች ያረጋግጣሉ፡፡**

ትንቢቶች የእግዚአብሔርህልወት ያረጋግጣሉ ማለት የተለመደ መከራከሪያ ነው፡፡ በእርግጥ የሚመስሉ ትንቢቶች አሉ፡፡ ጦርነት እንደሚነሳ መተንበይ አያስፈልግም ነበር፤ ድርቅ፣ ሱናሚና ሌሎች አደጋዎች ይከሰታሉ ብሎ መናገር ትንቢት አይደለም ግምት ነው፡፡ትንቢቶች ያረጋግጣሉ ለማለት ምንም ግልፅ የሆነ ትንቢት ከመፅሀፍት አላየነም፡፡ አይታችኋል እንዴ?

➢ **አለመኖሩ አልተረጋገጠም፡፡**

ማንም ሊያውቀው የሚገባ አንድ ሀቅ አለ መንፈስን የለም ማለት አይቻልም፡፡ አለ ማለት ደግሞ የባሰ ስንፍና ነው፡፡ ጥያቄው የመጽሃፍቱ እግዚአብሔር ስላለመኖሩ ማስረጃ አለወይ ከሆነ አወ በመጠኑ፡፡ የክርስቲያኖች፣ የሙስሊሞች፣ የአኒሚስቶች እና የጥንታዊ ሰዎች አማልዕክት አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ እራሳቸው ምስክር ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ላለመኖሩ ከክርስትና ህይወትና ከመፅሀፍ ቅዱስ ውጭ ማስረጃ መፈለግ አያስፈልግም፡፡ የክርስትናን ታሪክና የመፅሀፍ ቅዱሳን ሁለንተና የተረዳ የክርስትና አምላክ አለመኖሩን ማረጋገጥ ይቻላል የሌሎችንም እንዲሁ፡፡ ችግሩ መናፍስት አሉ ወይ ከሆነ አላውቅም ካሉ አሳየኝ ነው መልሱ፡፡ በፍልስፍና "The burden of proof" የሚባል ነገር አለ የማስረዳት ሸክሙ ያለውአማልዕክት፣ መናፍስትና፣ መላዕክትና UFOs አሉ ለሚለው ነው፡፡

➢ **የማህበራዊነትና የፍቅር ምንጭ፡፡**

ሀይማኖቶች ማህበራዊ ህይወትን እና በጋራ መኖርን ያጠናክራሉ፡፡ አው ምን ጥርጥር አለው ግን ሀይማኖቶች ስላፈረሱት ትዳር ስለከፋፈሉት ሀገርና ስለ አጨፋጨፍት

Created in Master PDF Editor

ህዝብ ታሪክን ማስታወስ የለብንም ትላላችሁ? ሀይማኖቶች አንድ ካደረጉት የከፋፈሉትና ያጨካከኑት የሚልቅ ይመስለኛል፡፡

➢ **ቅዱሳንን አስነስቷል፣ ልኳል፣ እራሱም መቷል፡፡**

በሁሉም ሀይማኖቶች ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆነና ቅንነት የተሞላባቸው ቅዱሳንን እናውቃለን፡፡ በቋንቋ፣ በስነ-ጥበብ፣ በስነ-ህንፃ፣ በስነ-ፈለክ፣ በሙዚቃ፣ በፍልስፍና፣ በስነ-ምግባር እና አመራር አለማችንን ወደፊት የሚያራምዱ ቅዱሳን ተነስተዋል፡፡ ግን የእነሱ ቅዱሳነት የእግዚአብሔር መኖር አያረጋግጥም፡፡ የእጆቻው አሻራም የሰውን ልጅ ብሩህነት እንጅ የአማልዕክትን መኖር አያስረዳም፡፡

➢ **ሳይንስ አይችልም፡፡**

ሁለንታ እንዴት ተገነባ? እንዴትስ ተጀመረ? ህይወት ምንድን ነው? ህይወት እንዴት ጀመረ? ስንሞት የት ነው የምንሄደው? እውነት ምንድን ነው?... የመሳሰሉ ጥያቄዎች መጠየቅ የጀመሩት ከሽህ አመታት በፊት ነው፡፡ አሁንም እንደ ሰበር ጥያቄ ይጠየቃሉ፡፡ ጥያቄዎቹ ህፃናት የሚጠይቁት ጥያቄ ቢሆንም መልሱ ግን ከጎልማሶች አቅም በላይ ነው፡፡ የሳይንስ ጥረቱ ለዘመናት ሲጠየቁ የኖሩትን ጥያቄዎች መመለስ ነው ቢያንስ በከፊል፡፡ መልሱ ሊያረካም ላያረካም ይችላል፡፡ ሳይንስ እንደ ሃይማኖት በእምነት የተመሰረተ ባለመሆኑ ሁሉንም የሰውን ልጅ ጥያቄዎች አልመለሰም፣ ወደ ፊትም ይመልሳል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ “ሳይንስ የተመሠረተ በአመክንዮ (Reasoning)፣ ማስረጃ (Evidence) እና አስተውሎ (Empiricism) ሲሆን፤ የሐይማኖት መሠረቱ ግን እምነት፣ በኃያል አካል መመራት፣ ተአምር፣ መገለጥ፣ መጽደቅ ነው፡፡ ባጭሩ የሃይማኖት መሠረቱ እምነት ነው፡፡ ምክንያት አይጠይቅም፤ በተቃራኒው ሳይንስ ምክንያት/ማስረጃ ይሻል፡፡ በሳይንስ እና በሃይማኖት መካከል ያለው ልዩነት መሠረታዊ ስለሆነ፣ የሁለቱ መስማሚያ (አንድ ዓይነት ዕይታ እንዲኖራቸው ለማድረግ) መንገድ/ስልት ያለ አይመስልም፡፡” (ሽብሩ ተድላ፣ የህያው ፈለግ፣11)

➢ **ማመን ይሻላል፡፡**

ለአማኞች አለማመን ሞት ነው፡፡ ሁለንተናቸው የተገነባው ከእምነት ነው፤ በእርግጥ ከአተም (Atom) ነው፡፡ ቀላሉ ምክንያታቸው አለማመንን ይፈሩታል፤ እንኳን አለማመን ጥቂት መጠራጠር የሚያስቀስፋቸው ይመስላቸዋል፡፡ ብሩህ አዕምሮአቸውን በሌላው ቁልፍ ይቆለፍበታል፡፡ ያን እምነት ብለው ይጠሩታል፡፡

Created in Master PDF Editor

➢ **የሀይማኖቱ እድሜ ረዥም ነው።**

የሃይማኖቶት እድሜ ትልቁ የእርስ በእርስ ንትርክ መንስኤ ነው። የኔው ከአንተው በእድሜ ስለሚባልጥ ትክክል ነው ይባባላሉ። በቅርብ ጊዜ የተመሰረቱት እምነቶች እንኳ ጭዋታውን ለማሸነፍ ከቀደምቶቹ ጋር እራሳቸውን ያስተሳስራሉ። የሞርመኑን ጆሴፍ እስሚዝ ታሪኩን ወደ ኋላ ጎትቶ ነው ሀይማኖቱን የመሰረተው መፅሀፍቱንም የፃፈው። እድሜ የእምነት እውነተኛነት ማረጋገጫ እንኳ ቢሆን የትክክለኝነት ቅደም ተከተሉ አኒሚዛም፣ ሂንዱይዝም፣ አይሁድ፣ ቢዲዝም፣ ክርስትና እና እስልምና ነው። በስም የማላውቃቸውና የስም ዝርዝራቸው ብቻ ዳጎስ ያለ መፅሀፍ የሚወጣው አመልዕክት ሲመለኩ ኑረዋል። በእድሜ ቢሆን ኑሮ እነዚያ እውነት ይሆኑ ነበር። ሊሆኑም ይችላሉ? ቢያንስ አንዱ። የሀይማኖታችንን ታሪክ ምንም ያህል ርቀት ወደኋላ ብንዘረጋው እና ታሪኩ እውነት እንኳ ቢሆን በጥንታዊ መንገድ እየሄድን መሆናችንን እንጅ ትክክለኝነታችንን አያሳይም። በተለይ ኦርቶይክሶች ፕሮቴስንቶችን ለመተቸት የሚጠቀሙት የእድሜ ጉዳይ ከእውነት ጋር ምንም ትስስር እንደሌለው ባወቁ።

እውነት ነው በመፅሀፍ የቀደመችውን መንገድ ተከተሉ ተብሏል። የቀደመችው መንገድ የት ናት? እንደኔ አኒሚዝምና ፓጋኒዝም ይመስለኛል። ከዚያም ካለፈ ኤቲዚም ይሆናል። በእውነት የሆሞ (Homo) ዝርያዎች የክርስቶስን ልደት ተስፋ ሲያደርጉ ነበርን? የአፋሯ ሉሲስ በአክሱሞቹ አማልዕክት ታምን ነበርን? መረጃ የለም፤ እንደ አንትሮፖሎጂስቶች ግምት ግን እምነት የተጀመረው ከ30,000 ዓመት ወዲህ ነው። ከዚያ በፊት ይህን ለማሰብ ብቁ የሆነ ማህበረሰብ አልነበረም።

6. Science (the magic of reality) explains almost everything

አንደብዙ ምሁራን ዕይታ የሳይንስ አስተሳሰብ በሶስት ወጋግራዎች ላይ የተደገፈ ነው። እነሱም ተሞክሮ/ማስተዋል (Observation/Empiricism)፣ ራሽናሊዝም/ሎጂካዊ አመክንዮ (Logical Reasoning) እና ነባር ዕውቀትን ሁሉ እንደወረደ አለመቀበል/ መጠራጠር (Skepticism) ናቸው። (ሽብሩ ተድላ፣ የህያው ፈለግ፣ 2010 ዓ.ም)

ጸጥ ያለ አብዮት እየተካሄደ ነው። የሃሳብ ልዕልና የሚያሸንፍበት። ምንም ጠመንጃ የለም። ምንም ወታደሮች በጦርነት አልተሳተፉም። ይህ ሰላማዊ ዝግመተ ለውጥ ለማንሳት፣ ለማሻሻል፣ ለዓለም አቀፋዊነት ስርአት መታገል ነው። ሰው ሁሉ ፈጣሪን በእያደባባዩ ይፈልጋል፣ የዘላለም ህይወቱን በእየስርቻው ይቆፍራል፣ በእስትንፋሱ ውስጥ ነብሱን ይዳስሳል ሌላም ሌላም ያደርጋል።

Created in Master PDF Editor

ሳይንስ በምርምር ላይ የተመሠረተ ዕውቀትን ያመነጫል። ሳይንስና ተክኖሎጅ ባለፉት 400 ዓመታት ውስጥ በፍጥነት ተፅዕኖ እየፈጠሩ ይገኛል። በተለይም በቅርብ አሥርት ዓመታት ሳይንስ ከላበራቶሪ ወጥቶ ለተራው ህዝብ እየተሰበከ ይገኛል። የማያምኑት በአስተማማኝ ሁኔታ እንደሚናገሩት የትረት ትምህርቶችን (ይህም ማለት አማልክት አሉ፣ ከሞት በኋላ ሕይወት አለ ወ.ዘ.ተ) ብሎ ለመደገፍ የሚያስችል አሳማኝ ማስረጃ የለም።

ሳይንስ ከተጨባጩ ዓለም በሥርዓት መረጃ የሚሰበስብ፤ ከተሰበሰበው መረጃ ተነስቶ ዕውቀት የሚገነባ እና ተፈትነው ጸንተው ሊቆሙ የሚችሉ ትንቢቶችንና ማብራሪያዎችን የሚያስገኝ የዕውቀት ዓይነት ነው። ሳይንስ በተጨባጩ አለም ውስጥ በመሞከር፣ ከተሞክሮውም ዕውነትና ውሸቱ እየጠራና እየተመዘገበ በሂደት እየተሻሻለ የሚሄድ የዕውቀት አይነት ነው። “Science has no creed, no dogmas. Her search is for facts, and on these she stands. If what is discovered by lovers of truth is contrary to the tenets of religion, such tenets must be abandoned, for what is scientifically false cannot be religiously true. Men may have lied, and lies are not holy. Christianity has been afraid of the divine name. What it has found in the name of God it has blindly worshiped as the word of God. Science has not found the name of God in the earth or in the heavens.”(Lemuel K. Washburn, page, 70)

“ሳይንስ እንደ አንድ የእውቀት አካል (Body of knowledge) በለውጥ ላይ ያለ (Dynamic) ነው። በመሆኑም የተፈጥሮ ምስጢሮችንና ህጐችን በመግለጽ በኩል ምሉዕ ባይሆንም በሂደት ግን በነባራዊው አለምና ሳይንስ በሚያጠናቅራቸው ምስለ ዓለም መካከል ያለው ልዩነት እየጠበበ ይሄዳል። እያንዳንዱ ሳይንሳዊ እውነታ በየዘመኑ ከሚኖሩ አማራጭ እውነታዎች የተሻለ ነው። በመሆኑም በየዘመኑ ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት በኩል አገልግሎት ላይ ይውላል። ሳይንስ በእውነታዎቹ (Scientific truths) አይታበይም። ለተግባራዊ ጠቀሜታ (For practical Purposes) እንደ እውነት ይቆጥራቸዋል። እንደ ፍልስፍናዊ አመለካከት ደግሞ በማንኛውም ጊዜ ሊለወጡ የሚችሉ (tentative) አድርጐ ይቆጥራቸዋል። ማንኛውም እውነተኛ የሳይንስ የምርምር ውጤት በተመሳሳይ የምርምር ዘርፍ ውስጥ ባሉ ባለሞያዎች መገምገምና በተለያዩ ማዕቀፎች (Parameters) ውስጥ ተደጋጋሚ ሙከራዎችን ማለፍ አለበት።” (ደረጀ ፀጋዬ፣ የኢ-አማኒው ኑዛዜ)። ከሳይንስ ሁሉ ድንቅ የሆነው ሳይንስ ደግሞ የዝግመተ ለውጥ ሳይንስ ነው።

የዝግመተ ለውጥ ሳይንስ ህይወት ያለፈጣሪ መፈጠሩንና መኖሩን በማብራራት ለአምላክ የለሾች መሠረት ሰጥቶናል። ይህ ጽንሰ ሐሳብ አምላክ በዩኒቨርስ ውስጥ የፈጣሪነትምና የአስተዳዳሪነትም ሚና እንደሌለው ያስረዳል። ይህ ከ1859 በኋላ ተቀባይነት ያገኘው አመለካከት ስለ ሰው ዘር ብቻ ሳይሆን ስለተፈጥሮ አመጣጥ በቂ

Created in Master PDF Editor

ሊባል የሚችል መልስ ሰቷል:: ይህም ለብዙ መለኮታዊ ጣልቃ ገብነትን ለሚያራግቡ አፈ ታሪኮች የግብዓተ መሬት መርዶ ነው::

የዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሐሳብ ሰዎችምንም ነፍስ እና ዘላለማዊ ሕይወት የሚባል አለመኖሩን ከተፈጥሮ ዕድሜያችን ባሻገር ሽልማት ወይም ቅጣት አለመኖራቸውንና ከከንቱ ጭንቀትና ጉጉት እንድንላቀቅ አድርጓል::

ይልቅምለሕይወታችንእራሳችን ትርጉም፣ ዓላማ እና ክብር በመፍጠርእና በራሳቸው ጥረት መዳረሻችንን እንድንወስን አድርጓል:: ይህ የዘመናችን ታላቅ የምርምር ሳይንስ በሕክምና፣በግብርና እና ሌሎች በርካታ መስኮች ላይ አስገራሚ አስተዋፅኦ አበርክቷል:: ማንኛውም የሳይንስ ዘርፍ የተፈጥሮም ይሁን ማህበራዊ ሳይንስ የዝግመተ-ለውጥ አሻራ አለበት:: ደረጀ ፀጋዬ እንዲህ ነበር ያለው "የዝግመተ-ለውጥ መላምት በህክምና፣ በእርሻ በስነልቦና ጥናት ዘርፎች አስተዋጽኦ ያበረክታል:: ከከንቱ አምልኮም ያላቅቃል::"(ደረጀ ፀጋዬ፣ የኢ-አማኒው ኑዛዜ)

በእርግጥ የዝግመተ ለውጥ ጥናት ሀይማኖት ስላልሆነ አንድ የመጨረሻ እና ፍጹም ብቸኛ የእውነት እኔ ነኝ አይልም::ይህ ለለውጥ ተገዥ አስተሳሰብ በሳይንሳዊ ዘዴ ያለፉትን አዳዲስ እውነታዎች እየተቀበለ በምናልባት ያስቀመጣቸውን እሳቤዎች እያሻሻለ ጉዞን ቀጥሏል:: ዝግመተ ለውጥ አዳዲስ ግኝቶች እንደበረከት እንጅ እንደ እርግማን አይቆጥርም:: እንደ እድል ሆኖ በየትኛውም ዘርፍ የሚደረጉ ምርምሮች ዝግመተ ለውጥን የሚያጸኑ እንጅ የሚንዱ አይደለም:: ቢሆንም አሁንም ቢሆን ዘርፉ ገና 200 አመት ያልሞላው ስለሆነ ብዙ ክፍተቶች ሊኖሩ ይችላሉ:: ይህን ጥቃቅን እንቆቅልሾች በመጠቀም የትችት ናዳ የሚያወርዱት ያሉትን ቢሉም የማጅኩ መፍቻ ቁልፍ የት እንዳለ ማወቅ አይከብድም:: የዝግመተ ለውጥ ስይንስ ቴሌቫንጋሊስቶች የሚሉትን ያህል እምነት ወይም ተራ ተረት ተረት አይደለም:: ሳይንስ የሰው ጥበብ በመሆኑ አንዳንድ ስህተቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ የታመነ ነው::

የሳይንስና የሳይንቲስቶች ስህተት መስራት የመፅሐፍ ቅዱስን እውነትነት አያረጋግጥም የሚለው ደረጀ ፀጋዬ አማኞች ይላል፦ "አማኞች ሳይንስ ስለ ፍጥረት አመጣጥ ለመናገር ብቃት የላትም፤ መብትም የላትም:: ለዚህ በብቸኝነት መልስ መስጠት ያለባት እምነታቸው ብቻ እንደሆነች አድርገው ያምናሉ:: ሳይንስ አለት ከሰክሶ ቤተ-ሙከራ ቀይሶ የስነፍጥረትን ሚስጢርና አመጣጥ ደረጃ በደረጃ እየፈታ ባለበት በአሁኑ ወቅት ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት የተፃፉ መጽሐፍት ላይ የሙጥኝ ማለት አሳዛኝ ነው::" (ደረጀ ፀጋዬ፣ የኢ-አማኒው ኑዛዜ)

ሳይንስ ከሚሰራው ታምር(ሚራክል) በላይ በተፈጥሮ ውስጥ ለመገመት የሚከብድ፣ ለመተንተን የሚያስቸግር እና እፀብ ድንቅ የሆነ ምስጢር እንዳለ ይነግረናል::

Created in Master PDF Editor

ከሁሉም የሚደንቀው ደግሞ ሁለንታ ከሲንጉላሪቲ እስከ ሌለኛው ሲንጉለሪቲ ያለው በድርብርብ ታምራቶች (Chains of miracles) የተሞላው እይታ ነው፡፡ ብዙ የስነ-መለኮት ሙህራን ይህን የተቀናበረ የታምራቶች ክምችት ሲመለከቱ ይህን ያቀናበረው ምንኛ ድንቅ ፈጣሪ ነው ይላሉ፡፡ ቅንብሩን ያገኘው ሳይንስ ግን አቀናባሪው እውሩ ሰዓት ሰሪ (Blind Watchmaker) መሆኑን ደርሶበታል፡፡

የስነ መለኮት ተመራማሪዎች ግን ሁለንታን ዲዛይን ያደረገው እግዚአብሔር ነው ወይም ID(Intelligent Designer)ነው ይላሉ፡፡ ኢንተሊጀንት ዲዛይን መልካም ፍልስፍና ቢሆንም ይህ ታላቅ ዲዛይነር እንዴ ፈጥሮ ሁለንተን በአለበት እንዲቀጥል አድርጎታል ወይስ ሁሉም ያለማቋረጥ ይፈጥራል? ሁሉም ነገር እንዴ የተፈጠረና በአለበት የሚቀጥል ነው ካልን በምድርም በሰማይም አዳዲስ ፈጥረታት ለሚሊየን እና ለቢሊዩን አመታት እንደተፈጠሩ የስነ ህያወትና የስሀ-ህዋ ጠበብቶች ይመሰክራል፡፡ ሁለንታም እየሰፋ እንደሚሄድ የኮስሞሎጅ ሙህራን አረጋግጠዋል፡፡ የሁለንተን የኋላ ታሪክ በማጥናትና በህዋ አካላት የሚፈጠረውን መራራቅ በመማገናዘብ፡፡

አይ ዛሬም እየፈጠረ ነው እንዳንል ይህን የሚል አንድም ሀይማኖት የለም ቢኖርም እንኳ የታላቁን ዲዛይነር ሁሉን አዋቂነት ጥያቄ ውስጥ ይጥለዋል፡፡ ሁሉን ማድረግና ሁሉን የሚያውቅ ሀያል ፈጣሪ የመፍጠር እቅድ አያስፈልገውም፡፡ ሁለንታን እና በሁለንታ ያለውን ለመፈጠር ሰኮንድ እንኳ ይበዛበታል፡፡ ስለዚህ ዛሬም እየፈጠረ ነው ማለት በፈጠረው ፍጥረት መሰለቸቱን ወይም አዲስ ፍጥረት ፈጥሮ ለማየት መጓጓቱን ወይም ባለፈው የፍጥረት አለም አለመርካቱን ወይም አዳዲስ ሀሳብ እያሰበ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ ከሰው እንጅ ከሰማያዊ ዲዛይነር አይጠበቅም፡፡ ፈጣሪ የህንፃ ወይም የፋሽን ዲዛይነር አይደለም፡፡ ሲጀመር እግዚአብሔር ፍጥረትን ለመፍጠር ዲዛይን አያስፈልገውም ይህን የምለው አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ለተፈጥሮ ዲዛይን ወይም ቀመር ሰጥቷል ስለሚሉ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለተፈጥሮ የሂሳብ፣ የፊዚክስ፣ የኬሚስትሪና የስነ-ህይወት ቀመር ዲዛይንአድርጎ ከሆነ በእርግጥ ታላቅ ዲዛይነር ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ከተረዳነው እግዚአብሔር የዲዛይኑ ባለቤት እንጅ የፍጥረቱ ባለቤት አይደለም፡፡

አንድ የህንፃ ፕሮጀክት መጀመሪያ ዲዛይን ይደረጋል ከዚያ ተቋራጩ ህንፃውን ይሰራል፡፡ በህንፃው ሁለንተና ዲዛይነሩ የማይነቅ አስተዋፅኦ ቢኖረውም ህንፃውን የገነባው ግን ዲዛይነሩ ሳይሆን ተቋራጩ ነው፡፡ ይህን ትንታኔ በእግዚአብሔር እና በተፈጥሮ ባለው ቁርኝት ውስጥ እንድናስገባውና ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር እንዳንሰጠው የሚከለክለን እግዚአብሔር ዲዛይን ማድረግ ከባህሪው ጋር የማይሄድ መሆኑ ነው፡፡ እግዚአብሔር “ይሁን” ይላል እንጅ ለተፈጥሮ እንዲህ አድርጊ፣በዚህ ሰዓት ዳይኖሰር ይፈጠር፣ በዚያ ሰዓት የበረዶ ዘመን ይሁን፤ በዚያ ሰዓት የሳይንስ

Created in Master PDF Editor

አብዩት ይሁን፤ በዚያ ሰዓት አንስታየን የተባለ ሰው ይወለድ፣ በዚያ ሰዓት ዳውኪንስ “The God Delusion” የሚባል መፅሀፍ ይፃፍ፤ በዚያ ዘመን ጉረፍ፣ ችጋር፣ርሃብ፣ ጦርነት እና በሽታ ይሁን ብሎ ተፈጥሮን አያዛትም፡፡ ይህ ውስንነት ላለበት እያሰበ እና እየሞከረ ለሚፈጥር እንጅ ወሰን የለሽ ለሆነው አምላክ የሚስማማ ባህሪ አይደለም፡፡

ታድያ በሁለንታ ግንባታ ላይ ዲዛይነሩ እና ተቋራጩ ማን ነው ቃሉ ለብዙዎች ባይዋጥላቸውም የሁለንታ የምንጊዜም ዲዛይነር እና ተቋራጭ አይነ ስውሩ ዝግመተ ለውጥ ነው፡፡ መሬትም በዚህ አይነ ስውር አንዴ ውሃ ሲውጣት፤ አንዴ በረዶ ሲሸፍናት፣ አንዴ ማዕበል ሲያናውጣት ላለፉት 4.6 ቢሊዩን አመታት ቁም ስቅሏን እያየች ኑራለች፡፡ የመሬት አብዛኛው ታሪኳ ለህይወት የማትመች ነበረች አሁን በአመሻሽ ከሌሎች ተለይታ እጣ ወጣለትና ግሩም የሆነ ፍሬ አፈራች፡፡ ነገር ግን ይህን 10 ሚሊዮን የማይሞላውን የጫጉላዋን ዘመን ከ4 ቢሊዮን አመት ጋር ስናነጻረው የታሪኳን 0.2% ቢሆን ነው፡፡ 1% እንኳ ለመሙላት መሬት መከራዋን ችላ የቻሉትንም ፈጥረታት ይዛ ለሚቀጥሉት 45 ሚሊዮን አመታት መቆየት አለበት፡፡ ይህ ጉዞ ምን አለበት በምስረታዋ ሲዘንብባት እንደነበረው የህዋ አካላት ድንጋይ እና እሳት መወርወር ከጀመሩ ፍጥረታት ብቻ ሳይሆን የራሷም ህልውና ይጠፋል፡፡

በእውነት ይህን ትንታኔ የደረሰበት ሳይንስ ምንኛ ድንቅ ነው፡፡ ይህን ገድል ያነበብንስ ምንኛ እድለኞች ነን፡፡ፕ/ር ሪቻርድ ደውኪንስ The magic of Reality, how we know what is really true? ሲል ባሳተመው ድንቅ መጽሃፍ ሳይንስ ምን ያህል ከአፈ ታሪክ እንደሚሻል አሳይቶናል፡፡ ፕ/ር ሪቻርድ ደውኪንስዱኮሬሽን በበዛበት በ “The magic of Reality” መፅሐፍ 12 መሰረታዊ ጥያቄዎችን ያነሳነ ጥንታዊ ምላሾችን ያስታውስል፣ ከዚያም በአሁኑ ወቅት በሳይንሱ አለም የተሰጡትን ምላሾች ለአቅመ ማንበብ ለደረሱ ወጣቶች በሚመጥንአቀራረብ ያብራራዋል፡፡

ጥያቄ አንድ፡- What is reality? What is magic?

ስለ እውነት የተነሳው ጥያቄ ቀላል አይደለም፡፡ እንደ ዳውኪንስ አባባል ብዙ እውነቶችን በአምስቱ የስሜት ህዋስት ለመረዳት ካበድ ናቸው፡፡ የሁለንታን እውነታ ለመረዳት 5ቱ የስሜት ህዋሳት በቂ አይደሉም፡፡ ከመቶ አመት በፊት፣ ከ10 ሽህ አመት በፊት፣ ከ10 ሚሊዮን አመት በፊት፣ ከ10 ቢሊዩን አመት በፊት ስለነበረው እውነታ ለመረዳት ማሻተት፣ መቅመስ፣ ማየት፣ መዳሰስና መስማት አንችልም፣ አይጠበቅብንም፡፡ ስለ ፕላኔቶች ስለ ልዩ ልዩ ከዋከብት፣ ስለ ጋላክሲዎች ለመረዳት ወይም ስለጥቃቅን በአይን ስለማይታዩ አካላት ለማወቅ የስሜት ህዋሶቻችን ብቁ አይደሉም፡፡ ቢሆንም እንደ ዳውኪንስ እምነት የራቁትን ለማቅረብ ቴሌስኮፕ

Created in Master PDF Editor

መፈጠሩ፣ የረቀቁትን ለማጉላት ማይክሮስኮፕ መፈጠሩ ታላቅ እምርታ ነው፡፡ ሳይንስን The magic of reality የሚያስብለው ይህ ይመስለኛል፡፡

ዳውኪንስ ማጅክን ከ3 ከፍሎ ተንትኖታል፡፡ 1ኛው Super natural magic ሲሆን ይህን የማጅክ አይነት Myths and fairy tales ይለዋል፡፡ እንደ ምሳሌ በተለያዩ ማህበረሰቦችና ሀይማኖቶች የሚነገሩትን ታሪኮች መጥቀስ ይቻላል፡፡ 2ኛው የማጅክ አይነት Stage magic የሚባለው ነው፡፡ በበርካታ የተሊቪዥን ስርጭቶች እንደመዝናኛ የሚቆጠር ማጅክ ነው፡፡ ይህን ድራማዊ እና የኮሜዲ ማጅክ የሚሰሩት በተሰጥኦና በስልጠና የተካኑ ባለሙያዎች ናቸው፡፡ 3ኛው የማጀግ አይነት Poetic magic ነው፡፡ እንደ ዳውኪንስ አባባል ይህ ማጅክ ስሜት ነው፡፡ የምንወዳቸውን ሙዚቃዎች ስናዳምጥ የሚሰማን ስሜት፣ የምንደግፈው ክለብ ዋንጫ ሲባለ የሚሰማን ስሜት፣ የራቀውን በቴሌስኮፕ የረቀቀውን በማይክሮስኮፕ ስንመለከት የሚሰማን ስሜት፣ የናሽናል ጅኦግራፊን ይክመንታሪዎችን ስናይ የሚሰማን ስሜት፣ እራሳችንን ስንሰበሰብ የሚሰማን ስሜት ይህን መሰል ረቂቅ ሰሜት ሲሰማን ነው ዳውኪንስ The magic of reality የሚለው በእርግጥም ነው፡፡

ዳውኪንስ ከሶስት የከፈለውን magic ያወዳድርና magic of reality ከ supernatural እና ከ stage magic የተሻለ ድንቅ ነገር እንደሆን ይናገራል፡፡ እንዲህም ይላል፦ “The magic of reality is neither super natural nor a trick but simply wonderful and real.” ለዚህም እንደ ምሳሌ የሚያነሳው የዘግመተ ለውጥን እውነታ ነው፡፡ እንደ ዳውኪንስ አተያይ ዝግመተ ለውጥ በእድል ላይ የተመሰረተ የሚመስላቸው ሰዎች እጅግ ተሳስተዋል፡፡ ተፈጥሮ በምንም አይነት መንገድ አፈረ ቆንጥራ የሰውን ልጅ አትፈጥርም፡፡ ይህ በእድል በሚባለው ነገር በቆሻሻ መጠራቀሚያ የሚገኙ የብረት ቁርጥራጮች ተሰባስበው ያለምንም ሰሪ መኪና መስርተው ሲገኙ እንደማለት ነው፡፡ እንኳን ግዙፍ ፍጥረት ነውና በአይን የማይታዩ ጥቃቅን አካላትን እንኳ በእድል ለማግኘት የማይታሰብ ነው፡፡ ትንሽ ነው በምንለው ውስጥ ታላቅ ውስብስብነት አለ፡፡ ተፈጥሮ ፍጥረታትን የማስገኘቷ ጉዳይ ጌም እንደመጫወት አይደለም እጅግ ረቂቅ ነው፡፡ ታድያ ይህን ረቂቅ ሚስጠር የሚፈተነውን Evolution by natural selection ነው ዳውኪንስ The magic of reality የሚለው፡፡

የዝግመተ ለውጥን አምጭ ከሆነቱ ምክንያቶች ዋነኛው የተፈጥሮ ምርጦሽ ነው፡፡ በተፈጥሮ ምርጫሽ ተፈጥሮ ትክክለኛውን እየመረጠችና እያበለጸገች ትቀጥላለች፡፡ የተፈጥሮ ምርጦሽ ህይወት እንዴት ተጀምረ የሚለውን አይፈተም፡፡ ህይወት እንዴት ጀመረ የሚለውን የቤት ስራ ዳውኪንስ ለኬሚስትሪ እና ለፊዚክስ ሊህቃን ትቶታል፡፡ የስነ-ህይወት ሙህር እንደ መሆኑ ግን ህይወት እንዴትም ከየትም ይጀመር ከተጀመረበት ጀምሮ ያለውን የትርምስ ታሪክ በሚገባ ይተረከዋል፡፡ ዳውኪንስ የእድሜ

Created in Master PDF Editor

ዘመን ምርምሩን ያደርገውና ተደናቂ መፅሐፍትን የፃፈው ስለ ህይወት አጀማመር ሳይሆን ስለ ህይወት ከቀለል(simple single cell) ተነስቶ እንዴት ማሰብ የሚችል ሰውን እንደፈጠረ ነው፡፡ ዳውኪንስ የሚከራከርለት የተፈጥሮ ምርጦሽ የማይዋጥላቸው በርካቶች ቢኖሩም ከጠቅላላ የህይወት ዝርያዎች ውስጥ አሁን ያሉት ኢምንት መሆናቸው ተፈጥሮ ምን እየሰራች እንደሆነ ለማወቅ አያዳግትም፡፡ በ100 ዓመት በማያሞላ እድሜያችን ስንት ለውጥ እያየን በቢሊዩን አመታት ለውጥ አይኖርም ማለት ጅልነት ነው፡፡

ጥያቄ ሁለት፡- Who was the 1st person?

የመጀመሪያው ሰው ማን ነው ለሚለው ጥያቄ በመላው አለም የተመሰረቱ ስልጣኔዎች የተለያየ መልስ አላቸው፡፡ አንዳንዶቹ ያስቃሉ (በእርግጥ ሁሉም ያስቃሉ)፡፡ የፕ/ር ዳውኪንስ መልስ ግን የተለየ ነው፡፡ የመጀመሪያ የሚባል ሰው የለም፡፡ ለዚህም አንድ ምናባዊ ምርምር እንድናደርግ ይጋብዘናል፡፡ ምርምሩን በእኔ ላይ ልሞክረው እኔ ፎቶ ተነሳሁ ወላጆቸ ፎቶ ተነሱ፣ የወላጆች ወላጆች እንዲሁ፣ የእነሱም ወላጆች ተነሱ እንበል፡፡ ወደ ኋላ 185 ሚሊዮን ፎቶዎችን ተነሳን 185,000,000 ትውልድ መሆኑ ነው፡፡ እኔ እና ወላጆቼ ሰዎች ነን፡፡ እኔ እና 10ኛው ትውልድ ሰዎች ነን፡፡ እኔ እና 100ኛው ትውልድ ሰዎችን ነን፡፡ እኔ እና 1000ኛው ትውልድ ሰዎችን ነን ልዩነቶች ግን ይኖራሉ፡፡ እኔ እና 10,000ኛው ትውልድ ሰዎችን ነን ልዩነቱ ግን እየሰፋ ነው፡፡ እኔ እና 50,000ኛው ትውልድ ዘመናዊ ሰው ለመባል ይቸግረናል፡፡ እኔ Homo Sapiens እነሱ Homo erectus፡፡ ይህ 50,000 ትውልድ ያባከነው ዝግመተ ለውጥ በዚህኛው ትውልድ Homo erectus ባለትዳሮች Homo Sapiens ልጅ ወለዱ አይባልም፡፡ ለውጡ እንደ ውሃ ደራሽ አልነበረምና፡፡ ጉዞው አያበቃም 100,000ኛ፣500,000ኛ 1ሚሊዮነኛ፣ 10 ሚሊዮነኛ፣ 100 ሚሊዮነኛ፣ 185 ሚሊዮነኛ፡፡ 185 ሚሊዮነኛ ላይ ስደርስ አሳ ሁኘ እገኛለሁ፡፡ እስከ መጨረሻው ኮሞከርኩም በአይን የማይታይ ህዋስ ብቻ የሆነ ቅደመ አያቴን አገኛለሁ፡፡እየቀለድኩ አይደለም አንድ ቀላል ምሳሌና አንድ ቀለል ማስረጃ ላቅርብ፡፡

ቀለላ ምሳሌ፡- አንድ በ100 አመቱ የሞተ ሰውን አሰቡ፡፡ ከተወለደበት ቀን ጀምሮ ፎቶ ቢነሳ ከ36,500 በላይ ፎቶዎች ይወጣዋል፡፡ ፎቶዎቹ በመቶ ጥራዝ መፅሀፍት ታትመው ቀረቡ እንበል፡፡ የዚህን ሰው ፎቶ በማየት በተወለደበት የመጀመሪያው ቀን እና በ2ኛው ቀን መከከለ ልዩነት የለም፡፡ 100 መፅሐፍት በትዕግስት ብትመረምሯቸው ልዩነቱን የፈጠረውን ፎቶ አታገኙትም፡፡ እየዘለለችሁ ካያችሁት ግን በ1ኛው ቀን ያለው ፎቶ ከ1ኛ አመቱ ፎቶ ጋር ይለያያል፡፡ 1ኛው ቀን እና 10ኛ አመቱ እጅግ ይለያያል፡፡ 1ኛው ቀን እና 50ኛ አመቱ አይገናኝም፡፡ 1ኛው ቀን እና 100ኛው አመት የአንድ ሰው ፎቶ ነው ለማለት ይከብዳል፡፡ የሰው ልጅ አመጣጥም

Created in Master PDF Editor

እንዲሁ ነው፡፡ ዘበት የሚመስለውን አዝጋሚ ለውጥ ለማስረዳት ይህ ምሳሌ በቂ ባይሆንም ከመምህሬ የተማርኩትን እንዲህ ተረኩት፡፡

ቀላል ማስረጃ፡- የስነ ፍጥረት መነሻው አንድ ነው ስንል የሚሳለቁ ብዙዎች ናቸው፡፡ እኔ ግን ደውኪንስ እንደነገረኝ አንድ ምሳሌ ልጥቀስ፡፡ (DNA) ዲ.ኤን.ኤ፡፡ ገራሚው DNA የሚደንቅ መረጃ የመያዙ ብቻ ሳይሆን የሚያስደምም ማስረጃም ነው፡፡ የፍጥረታት DNA መመሳሰል የቅርብ ዝምድናን ያመላክታል፡፡ሰውና የተለያዩ የጦጣ ዝርያዎች ተቀራራቢ DNA ሲኖራቸው ሰውና ሌሎች ፍጥረታት በእየርቀታቸው ተመሳሳያነታቸው እየራቀ ይሄዳል፡፡ DNA የአባትነትን ሚስጢር ብቻ ሳይሆን የፍጥረትን ዝምድና ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡፡ በጣም የሚያስደስተው ደግሞ ዘመድ የሌለው አለመኖሩ ነው፡፡ እጅግ የሚደንቀው ደግሞ በምንም ታምር 100% ተመሳሳይ አለመኖሩ ነው፡፡ በወላጅና በልጅ ሳይቀር በመንትዮች ሳይቀር መጠነኛ ልዩነቶች አሉ፡፡ አስገራሚው የመረጃ ማዕከል፣ ታላቁ ቤተ መፅሀፍትና ታላቅ የማዘዥያ ጣቢያ የሆነው DNA የሚገኘው በ Cell ውስጥ በሚገኝ Nucleus በ Nucleus ውስጥ በሚገኝ Chromosome ላይ ነው፡፡

ጥያቄ ሶስት፡- Why are there so many different kinds of animals?

ስለ እንስሳት ዝርያ መብዛት ብዙ ትርክቶች በየ ባህሉ ይኖራሉ፡፡ ዳውኪንስ ኦሪት ዘፍጥረትን ያስታውሳል፡፡ አምላክ ሁሉንም ፈጠረና አዳም ስም እንዲያወጣላቸው አደረገ፡፡ የመፍጠሩን ነገር ተውትና ወደ ምስኪኑ ሰው ወደ አዳም ልውሰዳችሁ ያሉትና የጠፉት የእንስሳት ዘርያዎች ብዙ ሚሊየን ይሆናሉ፡፡ እና አዳም 2,000,000 ዝርያዎች ስም ያውጣ ቢባል ስንት ዘመን ይፈጅበታል፡፡ ስም አውጣጡ የግብር ይውጣ ካልሆነ አመታትን ይፈጅበታል፡፡ አስቡት እንስሳት ስም እንዲወጣላቸው በሰልፍ ሲጠባበቁ እኔ እና ዳውኪንስ ግን እንዲህ እናስባለን በተፈጥሮ ሂደት፣ በቦታ መራራቅ፣ በአየር ንብረት ለውጥ፣ በምግብ መቀየር እና በሌሎች ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች እንስሳት ዝርያዎች ሊበዙ ቻሉ፡፡ አንዳቸውም ስማቸውን አያውቁም ከሰዎች በስተቀር ሳይንስ ግን ለሚሊየን የእንስሳት ዝርያዎች ስም በማውጣት ላይ ይገኛል፡፡

ጥያቄ አራት፡- What are things made of?

እያንዳንዱ ቁስ አካል ከምን ተገነባ የሚለው ጥያቄ ሽህ ዘመናትን ያስቆጠረ ነው፡፡ ዳውኪንስ እንዳለው የግሪክ፣ የቻይና እና የህንድ ስልጣኔዎች ጥያቄውን አስተው ለጊዜው የሚመጥን ቁስ አካል የተሰራው ከአየር፣ ከውሃ፣ ከእሳትና ከመሬት ውህድ ነው ብለዋል፡፡ እንደ ዳውንኪስ እይታ ከእነዚህ በተሻለ የግሪኩ ዲሞክራተስ የተሻለ ወደ እውነታው ተጠግቷል፡፡ አንድ ቁስ እስከመጨረሻው ድረስ ቢቆረጥና መቆረጥ

Created in Master PDF Editor

ከማይችልበት ጥግ ሲደርስ አተም ይባላል የሚል ፅንስ ሀሳብ ያመጣው ዲሞክራተስ ነው። ስለዚህ ሁሉም ነገር የተገነባው ከአተም ነው። አተም በአይን የማይታይ ነገር ቢሆንም ሳይንቲስቶች አጋዥ ቴክኖሎጅዎችን ተጠቅመው ውስጡን መበርበራቸው አልቀረም። እናም በተሰካው ብርበራ የሁሉ ነገር ገንቢ የሆነው አተም የተገነባው በፕሮቶን፣ ኒውትሮን እና ኤሌክትሮን መሆኑ ተደርሶበታል። ዳውኪንስ እንዳለው አቅማችን ማወቅ አለብን እንጅ በፕሮቶን እና ኒውትሮን ውስጥም የሚካሄደውን መመርመር ይቻላል። አተም፣ ንጥረ ነገርና ውህድ የኬሚስትሪው አለም መናኛ አጀንዳዎች እንዲሆኑ ይቀጥላሉ ዋናው ነገር ግን ሁለታችንም የተገነባው ከአተሞ መሆኑን ማወቁ ላይ ነው።

ጥያቄ አምስት፡- Why do we have night and day, winter and summer?

የመሬት ዙሪት እና እሽክርክሪት ቀን እና ሌሊት በጋ እና ክረምት የሚባል ነገር እንዲኖር አድርጓል። የመሬት ዙሪት እና እሽክርክሪት በሳይንሱ አለም ብቻ ሳይሆን በሀይማኖትም ተቀባይነት ያገኘ ሀቅ ሆኗልብዙ ዝግመታዊ ለውጥ በኋላ ቢሆንም። ነገር ግን አሁንም ቢሆን የመሬት እንቅስቃሴ ፈገግ የሚያስብላቸው ሰዎች አይጠፋም። ዳውኪንስ ለዚህ ቀላል አማክንዮአዊ ማስረጃ ይሰጣል። በባቡር ላይ የሚጓዝ ሰው የተሳፈረበት ባቡር እየሄደ ሳይሆን ሌሎች ከባቡሩ ውጭ ያሉ ነገሮች እየሄዱ እንደሆነ ቢሰማው አይገርምም ይለናል። እኛ የተሳፈርነባት መሬት የተባለች ባቡር በፅሐይ ዙሪያ ስትከንፍ ፀሐይ ልባ እስኪወልቅ መሬትን እየዞረች ይመስለናል። አንዳንድ ሰዎች መሬት የምትንቀሳቀስ ከሆነ ለምን የእንቅስቃሴዎ ድምጽና ንዝረት አይሰማንም ሊሉ ይችላሉ። እኔ ግን ከዳውኪንስ እንደተማርኩት ምሳሌ ልመስል። ከአዲስ አበባ ለንደን በሚከንፍ አውሮፕላን ብትጓዙ አውሮፕላኑ ሲነሳና ሲያርፍ ከሚያስማው ለየት ያለ ድምፅና ንዝረት በስተቀር ቤታችሁ ሶፋ ላይ የተቀመጣችሁ ያህል ይመቻችኋል። ይህ እንዲህ ከሆነ መስመሯን ጠብቃ ያለመታከት ከምትንቀሳቀሰው መሬት ድምፅና ንዝረት መጠበቅ አግባብ አይደለም። የምትንቀሳቀሰው እንኮ በማዕበል ውስጥ አይደለም በሀሳብ መስመር እንጅ።

ጥያቄ ስድስት፦ what is the sun?

በአምልኮ ታሪክ ውስጥ እንደ ፀሀይ ለረዥም ጊዜ የተመለከ ስለመኖሩ እጠራጠራለሁ። የጥንት ስልጣኔዎች ከስልጣኔዎች መነሳት በፊት የነበሩት የዋሻና የአደን ሰዎች ፀሐይን ያመልኩ እንደ ነበር ይገመታል። በተለይ በመካከለኛው ምስራቅ፣ በአውሮፓ፣ በአፍሪካና በደቡባዊ አሜሪካ ተጠቃሽ በሆኑት ስልጣኔዎች ፀሐይ ስትመለክ እንደነበር መረጃዎች ተገኝተዋል። አንድ ማህበረሰብ አምላኩን ለመፈለግ ወደ ሰማይ ቢያንጋጥጥ በጉልህ የሚያየው ፀሐይና ጨረቃ ስለሆነ ለማምለክ ቅድሚያ ለእነዚህ

Created in Master PDF Editor

ጉሉዛን መስጠቱ አያሳውቅሰውም፣ አላዋቂም አያስብልም። የምናምነው የገባንን ስለሆነ።

አሁን በደረስንበት የስልጣኔ ደረጃ ግን ፀሐይ ማለት በስርዓተ ፀሀይ ውስጥ 99% ግዝፈት የምትሸፈን በዙሪያዋ ለሚዞረት ጥቃቅን ፕላኔቶች ብርሃን የምትለግስ ኮከብ ናት። ፕላኔቶን ጥቃቅን ያልኳቸው ከፀሐይ ግዝፈት አንፃር ፕላኔቶች ኢምንት በመሆናቸው ነው። ዳውኪንስ እንዲህ ይላል። “The sun is a star. It’s no different from lots of other stars, except that we happen to be near it so it looks much bigger and brighter than the others”

ጥያቄ ሰባት፡- What is rainbow?

ቀስተ ደመና ምንድን ነው? እንደ ዳውኪንስ ፍለጋ ለዚህ ጥያቄ ቀደምት መልስ የሰጡት የጥንቶቹ ሱመርያኖች ናቸው። ዳውኪንስ The Epic of Gilgamesh የተባለውን ታሪካዊ ፅሁፍ ያስታውሳል። ይህ ጥንታዊ ጽሁፍ ከግሪክ እና አይሁድ አፈ-ታሪክ የቀደመ ነው።

ቀስተ ደመናን እንዲህ ይተርከዋል።ታላቁ ንጉስ ጊልጋሚሽ (Gilgamesh) ታላቅ ጉብኝት እያደረገ በነበረበት ወቅት ብዙ መቶ አመታት ምን አልባትም ብዙ ሽህ አመታት የኖሩ ሽማግሌ አገኘ። ሽማግሌው Utnapashtim ናቸው። ይህ ሽማግሌ ለንጉሱ እንዲህ አሉ። በድሮ ጊዜ ሰዎች እየጮሁ አማልዕክትን አላስተኙ አሉ። በዚህ የተበሳጨው ዋናው አምላክ Enlil በንፍረ ውሃ ፍጥረትን ሊያጠፋ ወሰነ። ይህን ያወቀው የውሃ አምላክ Ea ለሽማግሌው ጀልባ እንዲሰራ ነገረው። ታሪክ ነጋሪው ሽማግሌ ታላቅ ጀልባ ሰራ። ዝናቡ 6 ቀን እና 6 ሌሊት ያለማባራት ዘነበ። ዝናቡ እንደበራ ሽማግሌው እርግብን ላካት ደርቅ መሬት ይኖር እንዲሆን ለማወቅ። እርግቧ ደረቅ መሬት ባለማግኘቷ ተመለሰች እንደገናም ትንሽየ ወፍ ላከ እሷም ተመለሰች በሶስተኛው ቁራን ላከ፣ ቁራዋ ግን አልተመለሰችም። ባለጀልባውም የሆነ ቦታ ላይ የብስ እንዳለ ተረዳና ፈልጎ አገኘ። በዚህ የጥፋት ዘመን ከአማልዕክት አንዱ Ishtar የመጀመሪያውን ቀስተ ደመና ፈጠረ። ቀስተ ደመናውም አማልዕክት በድጋሜ በንፈረ ውሃ አለምን ላያጠፏት ቃል ኪዳን የገቡበት ነበር።

ሁለተኛውን የቀስተ ደመና አመጣጥ ታሪክ የምናገኘው ደግሞ በኖህ ታሪክ ውስጥ ነው። የሰዎችና የአማልዕክት ስም ከመቀየሩ ሌላ ታሪኩ እንደወረደ (copy paste) ስለሆነ መድገም አያስፈልግም። ዳውኪንስ በመጽሀፉ ሌሎች አስቂኝ ተያያዥ ትርከቶችን ያስታውሳል። አንዱን ልጥቀስ የቹማሽ (Chumash) ደሴት ሰዎች ትርክት ነው። ሁታሽ (hutash) የተባለችው የደሴቷ አምላክ የሰማዩን እባብ (milk way)ን አገባችው። እንዲህ እየኖረች እያለ የሰው ልጆች ቁጥር በመጨመሩ አረበሿት። ይህች

Created in Master PDF Editor

ደግ አምላክ የሰውን ልጅ በንፍረ ውሃ ከማጠፋ በማለት ከሰው ልጅ ጫጫታ የሚያረቅ ድልድይ ሰራች። ሰዎች በጫጫታ ከሚኖሩበት ደሴት ወጥተው ወደ ምድር (mainland) እንዲሄዱላት ስትል የፈጠረችው ድልድይ ነበር የቀስተ ደመና መጀመሪያ። የሚገርመው ይህ አይደለም። ሰዎች ከደሴት ተነስተው ወደ ዋናው ምድረ በሚሄዱበት ወቅት ቀስተ ደመናው አደልጧቸው የወደቁት ሰዎች ወደ ዶልፊንነት ተቀየሩ የሚለው ግን የሚገርም ይመስለኛል። ይህ ታሪክ የቀስተ ደመናን አመጣጥ ብቻ ሳይሆን የተወዳጆቹን ዶልፊኖች አፈጣጠርም ይተርካል።

በነገራችን ላይ ቀስተ ደመና ምንድን ነው? የታላቁን ኒውተን ተላቅነት ካናሩት የዚህ ጥያቄ መልስ ይገኝበታል። ኒውተን ጥያቄውን ለመመለሱ እንዲህ አደረገ በጨለማ ቤት ውስጥ ትንሽየ ብርሃን እንድትገባ አደረገ። ብርሀኑ በሚያርፍበት ላይ አንፀባራቂ ሶስት ማዕዘን ያለው ብርጭቆ (መስታውት) አስቀመጠ። ብርሀኑ ፕሪዝሙ (prism) ላይ ሲያርፍ ቀስተ ደመና ሲፈጠር አየ። ከአማልዕክት ቀጥሎ ቀስተ ደመናን የፈጠረ ሰው ለመሆን በቃ። (እስከማውቀው ድረስ)። ታዲያ በዝናብ ወቅት ወይም በፏፏቴዎች አካባቢ ቀስተ ደመና እንዴት ይፈጠራል? ትልቁን ትንታኔ ለፊዚክስ ሙህራን ልተውና የዝናብ ጠብታዎችን (raindrops) እንደ ፕሪዝሙ በመውሰዱ ይፈጠራል።

ጥያቄ ስምንት፡- When and how everything begin?

ሁሉ ነገር እንዴት ተጀመረ ማለትም ሁለንታ እንዴት ተፈጠረ? የሚለውን ጥያቄ መጠየቅ ቀላል ነው ችግሩ መመለሱ ነው። መልስ ተብለው ተሰጥተዋል ከተባሉበት ጥንታዊና ዘመናዊ መልሶች ጥቂቶችን ዳውኪንስ ጠቅሷቸዋል። እኔም በጨረፈታ ልተረክላችሁ።

እንደ ባንቱ ጎሳ (Bantu tribe) በመጀመሪያ ከጨለማ ውጭ ምንም አልነበረም። በጨለማው ውስጥ ግን አምላክ ነበር። (Bumba ይሉታል)። ቡንባን የሆድ ቁርጠት አመመውና ለመጀመሪያ ጊዜ ሽቀብ ሲለው ፀሀይ ተፈጠረች። ብርሃን ሆነ። በተደጋጋሚ ሲያስታውከው ጨረቃ፣ ከዋከብት፣ እንስሳትና ሰዎች ተፈጠሩ። ደስ የሚል የስነ ፍጥረት ታሪክ ነው።

ዳውኪንስ እንዳተተው የጥንት ቻይናዎች ደግሞ ሌላ ደስ የሚል የስነ ፍጥረት ታሪክ አላቸው። በመጀመሪያ ሰማይና ምድር የገጠሙ ነበሩ። በዚህ ወቅት በጥቁር እንቁላል ውስጥ ፓን-ጉ (Pan-Gu) ተኝቶ ይኖር ነበር። ፓንጉ ሲነቃከእንቁላል ማምለጥ ፈለገ። ፓንጉ እንቁላሉን ሰበረውና ወጣ። ሰብረባሪውም ሁለንታን ፈጠረ። ፓንጉ ሁለንታን በፈጠረበት ሰዓት ሰማይ ሩቅ አልነበረም። ስለዚህ ሰማይን መግፋት ነበረባት እስኪሞት ድረስ ሲገፋ ኖረ።ፓን ጉ በከንቱ አልደከመም ትንፋሹ አየር ሆነ። ድምጹ መብረቅ ሆነ። አይኖቹ ፀሀይና ጨረቃ ሆኑ። ጡንቻዎቹ የእርሻ መሬት፣ የደም ስሮቹ

Created in Master PDF Editor

መንገድ ሆኑ። ላቡ ዝናብ ሆነ። ጸጉሮቹ ከዋከብት ሆኑ። በሰውነቱ ከነበሩት ጥቃቅን ነፍስት ሰዎች ተፈጠሩ። ትርክቶች ይቀጥላሉ ዳውኪንስ ግን ይጠይቃል ይመልሳልም። How did everything begin realiy?

ለዚህ ጥያቄ ሳይንቲስቶቹና የሀይማኖት ሊህቃን በከፊል የሚስማሙበት ፅንሰ ሀሳብ አለ ታላቁ ፈንዳታ (Big Bang ይሉታል።) የኮስሞሎጅ ታሪኩን እና ማረጋገጫ ማስረጃዎችን ልተውና ታላቁን ፈንዳታ በአንድ አረፍት ነገር ልግለፀው። ታላቁ ፈንዳታ ማለት ሁለንታ የተፈጠረበት የዛሬ 14 ቢሊዮን አመት አካባቢ የተፈፀመ ታላቅ ክስተት ሲሆን በዝግመታዊ ለውጥ የያኔው ሲንጉላሪቲ ሰውን እና በሁለንታ የመለውን ስነ ፍጥረት አስገኝቷል።

ጥያቄ ዘጠኝ፡- Are we alone?

ለዚህ ጥያቄ ከጥንቶቹ ይልቅ ሳይንሳዊ ልቦለድ ፊልሞችን የሚኮመኩሙት የዛሪዎች ወጣቶች በእርግጠኝነት አወ ብቻችንና አይደለንም አሊያንስ (Aliens)፣ ዩኤፍኦ (UFO) ወዘተረፈ አሉ ይላሉ። በእርግጥ Aliens እና UFO የሉም ለማለት አይቻልም፣ አሉ ማለትም አይቻልም። መጠራጠሩ መልካም ሳይሆን አይቀርም። ዳውኪንስ አለመጠራጠር ያስከፈለውን ዋጋ ለማሳየት የገነት በር እማኞች (Heavens Gate Cult)ን ያጋጠማቸውን ይጠቅሳል። የገነት በር እማኞች UFO የሚባሉ አካላት የሰዎችን ነፍስ ወደ ሌላ አለም ሊወስዱ ይመጣሉ ብለው በማመናቸው እድሉ እንደያመልጣቸው ወሳጆቹ ከመምጣታቸው በፊት እራሳቸውን በመርዝ አጥፍተዋል። እርግጠኛ መሆን እስከዚህ ይጎዳል። የሚገርመው ደግሞ መሪያቸው እራሱ እራሱን ማጥፋቱ ሰው ለሌላ ሰው ከሚዋሸው በላይ እራሱን ይዋሻል የሚባለው አባባል ልክ መሆኑን አሳይቷል።

ጥያቄ አስር፡- What is an earthquake?

የመሬት መንቀጥቀጥ የአማልዕክት ቁጣ አድርገው የሚያስቡት ብዙዎች ናቸው። ሌሎች ሰዎች ደግሞ የተለያየ ትንታኔ ሊሰጡ ይችላሉ። ጉዳዩን የምድረ ሳይንስ ሙህራን ሲያወሩት ደግሞ ተፈጥሮ ውስጥ ፍትህ እንደሌለ ለመረዳት እንችላለን። መሬት ዛሬ እንዲህ ከመረጋጋቷ በፊት ተራራዎችን የምትተፋ አመፀኛ ነበረች። ከመሬት ውስጣዊ እንቅስቃሴ አንፃር መሬት አሁን ትኝታለች ማለት ይቻላል።

ይህ ባይሆን ኑሮ እኔም ይህን አልፈፅም፣ እናንተም አተነቡም። ደስ የሚለው መሬት አልፎ አልፎ በማኩረፏ ሚሊዮኖችን ብታሰጋም፣ በመቶ ሽህ የሚቆጠሩትን ብትቀጥፋም አንደድሮው አይደለችም ሰከን ብላለች ይህ እድለኛ ያስብለናል።

Created in Master PDF Editor

ጥያቄ አስራ አንድ፡- Why do bad things happen?

በበርካታ የዓለም ስልጣኔዎች መጥፎና ደግ አማልዕክት አሉ፡፡ ደጎቹ አማልዕክት ለሰው ልጅ መልካም ነገር ሲያመጡ መጥፎዎቹ ለሰው ልጅ ክፋትን ሲያመጡ ይኖራሉ፡፡ ሞት፣ ህመም፣ ድርቅ፣ ወረርሽኝ፣ ጦርነት፣ የተፈጥሮ አደጋዎች እና ሌሎችም መከራዎች የሚመጡብን ከመጥፎ አማልዕክት ዘንድ ነው ይባላል፡፡ በክርስትና በእስልምና በአይሁድ ሀይማኖቶችም የሰው ልጅ ውድቀት የመጣው ከሰይጣን ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ ዳውኪንስ Why do bad things happen? ለሚለው ጥያቄ መልስ ከመስጠቱ በፊት ጥያቄውን አሻሽሎ ይጠይቃል "Why does anthing happen?" ሲመልስም እንዲህ ይላል Luck, Chance and Cause.

እንደ ዳውኪንስ እይታ ለእያንዳንዱ ነገር ምክንያት ሊኖረው ይችላል ካልኖረው እድል ነው፡፡ ሱናሚ ለምን ኖረ የመሬት መንቀጥቀጥ ስላለ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ ለምን ኖረ የመሬት ውስጣዊ እንቅስቃሴ ስላለ፡፡ እራስ ወዳዶች እኔ ልሳፈርበት እጅን ብዘረጋ ትቶኝ የሄደው መኪና ተገለበጠ ይላሉ ይህን መሰል የባለ እድለኞች ታሪክ መስማት የተለመደ ነው፡፡ ነገሩን ከአደጋ ያመለጡ ዕድለኛ ያላመለጡት ደግሞ ዕድለ ቢስናቸው ብለን ፋይሉን ከዘጋነው መልካም ነው፡፡ ነገር ግን እኔ የተረፍኩት ዕድለኛ ስለሆንኩ ሳይሆን አምላኬ ስለሚወደኝ ለክፉ አሳልፎ ስላልሰጠኝ ነው ወዘተ አይነት ምስክርነቶች ግን ያሳተዛዝባሉ፡፡ እኔ ግን በእንዲህ አይነት ምስክርነቶች እጅግ አዝናለሁ፡፡

ጥያቄ አስራ ሁለት፡-What is miracle?

ተአምር ምንድን ነው? በእርግጥ ሁሉም ነገር ተአምር ነው፡፡ በተለምዶአዊ እይታው ግን ተአምር ከተፈጥሮአዊ ስርዓት ውጭ የሆነ ድርጊት ማለት ነው፡፡ በ2 እንጀራ እና በ3 አሣ ሜዳ ሙሉ ህዝብ መመገብ በእርግጥ ተአምር ነው፡፡ በውሃ ላይ መራመድ ተአምር ነው፡፡ የአሣ መመላለሻ እስከመሆን መፀለይም ተአምር ነው፡፡ በእሳት ውስጥ ዘማሬ ማቅረብም እጅግ ተአምር ነው፡፡ ተገድሎ፣ ተፈጭቶና በተራራ ተዘርቶ ተመልሶ መምጣትም ልዩ ተአምር ነው፡፡ እንዲህ አይነት ተአምር ለሽህ ዘመናት ሲነገሩና ሲዘከሩ ይኖራሉ፡፡ ብዙዎቹም ተአምር በአይናቸው ለማየት የታደሉ አሉ፡፡ ተአምር ሰምተናል ለሚሉት ከሰሚዎች የሰሙት የሰሚ ሰሚ በመሆኑ አይደንቀኝም፤ ተአምር አይተናል ለሚሉት ግን የስነ-ልቦና ባለሙያዎች በቂ መልስ አላቸው፡፡ የሰው ልጅ ቅንጭላት ታላቅ የውሸት ፋብሪካ መሆኑንም መዘንጋት የለብንም፡፡ ይህ ማለት ግን የምናስበው ሁሉ ውሸት ነው ማለት አይደለም፡፡ ሁሉን መርምሩ መልካሙን ያዙ የተባለውን ድንቅ ምክር መተግበር ግን ብልህነት ነው፡፡

Created in Master PDF Editor

7. በአጽናፈ ዓለም ውስጥ የእኛ ኢምንት ቦታ

ፀሐይ የኛ ኮከብ፣ በኛ የገነነች፤

ላለኝታችን ሁሉ መንስኤ የሆነች፤

ጠፈር ስትሰለፍ፣ ተራ ወታደር ነች።

ግዙፎች ሞልተዋል፣ ነበልበል፣ ውሽንፍር፤

"ጠፈር" በሚባለው፣ በከዋክብት መንደር፤

ጠፈር ተሞልታለች፣ በቋያ ነበልባለ፤ መጠነ ትላልቅ፤

ወይ ፀለምት- መሰል ዋሻ፣ ከሳበ የማይለቅ።

ወይ ነበልባል መሆን፣ ነፀብራቅ ቃጠሎ፤

ወይ ጊዜው ያለፈ፣ የከሰለ አለሎ።

ከዋከብት፣ ጋላክሱ፣ ቢሊዮን! ቢሊዮን!

በማናውቀው ቋንቋ፣ እንደነጋበት ጅብ፣ ሁሌ ፈጠን፣ ፈጠን፣

ጉዞ ወተት፣ ወተት፣

መነሻውስ ከየት፣ መድረሻወስ ወዴት?

ጠፈር ወለ-ፈንዲ፣ ፍጥነት ነፀብራቅሽ፤

እምቅ ኃይል ግለትሽ፤

ስፋትና ጉዞሽ፣ መነሻ መድረሻሽ፤

የጊዜ ስሌትሽ፣ ብርቅ ነሽ ድንቅ ነሽ፣ አምሳያ የሌለሽ።

(ምንጭ፦ ሽብሩ ተድላ፣ የህያው ፈለግ፣ 2010 ዓ.ም፣ 37)

ፀሐያችን በሚልኪ ዌይ ጋላክሲካሉ 400 ቢሊዮንከዋክብት ውስጥ አንዷ ኮከብ ናት።ሚልኪዌይጋላክሲ ከ 100 ቢሊዮን ከሚበልጡ ጋላክሲዎች አንዱ ነው። የሥነ ፈለክ ተመራማሪዎች በቅርብ ጊዜ ውስጥ አንድ ትሪሊዮን ፕላኔቶች በሚልኪዌይጋላክሲእንዳሉ ገምተዋል ከእነዚህ ውስጥ 30 ቢሊዮን የሚሆኑት ከመሬት ጋር ተመሳሳይነትአላቸው (በተለይ ፈሳሽ ውሃ ይኖራቸዋል)። አንዳንድ ፕላኔቶች ላይ ህይወት ሊኖር ይችላል።እስኪ እንሰበውበአማካኝ 30 ቢሊየን መሬት መሰል ፕላኔቶች በእያንዳንዱ 100 ቢሊዮን ጋላክሲወች ቢኖሩ ስንት መሬት መሰል ፕላኔቶች ይኖራሉ? (30 በሊየን ሲባዛ 100 ቢሊዮን) በስም አላውቀውም በቁጥር ግን 3,000,000,000,000,000,000,000 ይሆናል። ብዙ ምድርን የሚመስሉ ፕላኔቶች ይኖራሉ። በተመሳሳይ መልኩ መሬት ላይ እንደሆነው በዚያም ዝግመታዊ ለውጥ

Created in Master PDF Editor

ይኖራል፡፡ ምንም እንኳን ሕይወት አለ ብሎ ለማመን ምንም ማስረጃ የለለ ቢሆንም፡፡ እስቡት ከእነዚህ ፕለኔቶች ውስጥ ሰው እንኳን ባሆን የሆነ ፍጥረት አለ ብሎ መገመት ጥፋቱ ምንድን ነው?

በዚህ ሰፊና ግዙፍ ጠፈር ውስጥ ይላሉ መ. ኃ. ዶ/ር መስቀል 'ከምድራዊነታችን ባሻገር፣ ሦስተኛ መጽሐፍ'<ብቸኝነት የለም>ሲሉ ባሰፈሩት መጣጥፍ፡፡

> "በዚህ ሰፊና ግዙፍ ጠፈር ውስጥ ፍጥረት የተጀመረው እኛ ከምናውቀው ምድር ብቻ መሆን አለመሆኑን አናውቅም፡፡ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ፈጠረ ስንል እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በዚህ ምድር ላይ ብቻ መፍጠሩን አናወቅም፡፡ ከዚህ ምድር በስተቀር ስንት የሰው ልጅ (ወይንም የሰው ልጅን የመሰለ ፍጡር) ሊኖርበት የሚችልበት ምድር መኖር አለመኖሩን አናውቅም፡፡ በቁጥር አንድ ሚሊዮን ወይም ከዛም በላይ የሚሆኑ አለማት ውስጥ፥ የሰው ልጅ (ወይንም የሰው ልጅን የመሰለ ፍጡር) የሚኖርበት አለም ቢኖር፣ እኛ ምንም የምናውቀው ነገር የለም፡፡ እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው ብለን ካመንን የጠፈርን ግዙፍነት እየተመለከትን፥ እግዚአብሔር ኃያልነቱን በዚህች በኛ ታናሽ ምድር ላይ ብቻ ወስኗል ብሎ ከማመን ይልቅ አያሌ አካላዊ ሕያዋንን በጠፈር ሁሉ ፈጥሯል ብሎ ማመን ይቀላል፡፡"

እንዲያዉም ከኛ በላይ የሰለጠኑ ሊያጠፉን ወይም ሊተባበሩን የሚችሉ ፍጥረታት አሉ በሚል መላምት በሬዲዮ መገድ መልዕክት ተልኮ መልስ እየተጠበቀ ነው፡፡ በተለይ ታለቁ የስነ ከዋክብት ተመራመሪ ስቴፈን ሀውኪንግ ከአሊያኖች ጋር መተዋወቅ አዳጋ ሊኖረው እንደሚችል አስጠንቅቋል፡፡ይሁን እንጅ ፍለጋው ተጠናክሯል፡፡

ጊዜን አስመልክቶ የኛው ሁለንታ የተከሰተው ከ 13.8 ቢሊዮን ዓመታት በፊት ነው፡፡ የሰው ልጆች እና የቅርብየሆኑት ዝርያዎች (ማለትም ቺምፓንዚዎች) ከአንድ የጋራ ቅድመ አያት የተለያዩት ከዛሬ አምስት ሚሊዮን ዓመታት በፊት ነው፡፡የሁለንታን እድሜ ወደ አንድ ሽህ አመት ዝቅ አድርገን ብናስበው የሰው ልጅ አመጣጡ የዛሬ 132 ቀን ነበር፡፡ የኛዋ መመኪያ ሉሲ ከተመለደች 85 ቀን ሁኗል፡፡ ሰወች ግብርና ከጀመሩ 6 ሰዐት አልፏል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰበከ 1 ሰዐት ከ25 ደቂቃ ሁኗል፡፡ ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ አለም ከተፈጠረች 10ሽ አመት አልሞላትም የሚሉት የዋህወች ምን ይሉ ይሆን?

> "የሳይንስ ፈተና ላይ፣ <የሰው ልጅ አመጣጥ፣ የኢቮሉሽን (የዝግመተ ለውጥ) ውጤት ለመሆኑ የ3.5 ሚሊዩን አመት እድሜ ያላት ሉሲ ምሳሌ ናት> ብለህ መልስ መልሰህ፣ እሁድ ሲነጋ ቤተስኪያን ለጸሎት ከሄድክ፣ ወይም አርብ ዕለት ለሶላት መስጊድ ከተሰለፍክ ለራስህ ታማኝ ያልሆንክ/አስመሳይ ነህ፡፡

Created in Master PDF Editor

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ምሁር “አስመሳይ” ነው:: ስለ እውነት እና ውሸት፣ ጥሩ እና መጥፎ፣ ትክክል እና ስህተት.. ወዘተ ስለመሳሰሉት መሰረታዊ የሆኑ የሞራል ጉዳዩች ላይ የምዕራባዊያኑን “Renaissance” ያህል አብዮት ማካሄድ ሳያስፈልገን አይቀርም::” (ጎልጉል የድረገጽ ጋዜጣ፣ የኔ ሃሳብ አምድ)

የሥነ ፈለክ ተመራማሪዎች ፀሐይ በሚቀጥሉት 5 ቢሊዮን አመታት ወደ ሪድ ጊያንት ኮከብነት ትቀየራለች ይላሉ::ከዚያ በፊት ግን መሬት ምቹ መሆኗ ያበቃል:: መሬት ከታላቁ ሁለንታ አንፃር በአንድ ሄክትር ማሳ ውስጥ ከተሸፈነ ሰብል እንደ አንዷ ፍሬ ናት:: ወይም ካርል ሳጋን እንዳለው ጊጋንቲክ በሆነው ዩንቨርስ እንደ አንዲት ነጥብ ናት:: ይህ ማለት ምንም አትጠቅምም ማለት ሳይሆን መሬትን የሁሉ መዕከል አድርገው ለሚቆጠሩት ራስ ወዳዶች ትምህርት ይሆን ዘንድ ነው::

8. የዝግመተ ለውጥ እውነታ

ቻርልስ ዳርዊን (Charles Darwin-1809-1882) ቻርልስ ዳርዊን የሚታወቀው ለዝግመተ ለውጥ (evolution) ባደረገው ሳይንሳዊ አስተዋፅዖ ነው:: ዘመናት በፈጀ ጥናት ላይ ተመስርቶ በ1859 ስለብቸኛ ዝርያዎች መንስዔ (On the Origin of Species) የሚለውን ፈር ቀዳጅ መጽሐፍ አሳትሞ፣ ከእርሱ በፊት የነበረን የሕያው አመጣጥ እምነት ለመለወጥ አስቻለ:: ብቸኛ ዝርያዎች በዝግመተ-ለውጥ (evolution) ከቀደምት ዝርያዎች የተገኙ/የተወለዱ እንጅ፣ በአንድ ጊዜ በመለኮት ኃይል እንዳልተፈጠሩ በቂ እና ታማኚ ማስረጃዎች አበረከተ:: (ሽብሩ ተድላ፣ የህያው ፈለግ፣22)

"Nothing in biology makes sense except in the light of evolution." -- Theodosius Dobzhansky

"In the broadest sense, evolution is merely change, and so is all-pervasive; galaxies, languages, and political systems all evolve.” Douglas J. Futuyma

“This century will be called Darwin’s century. He was one of the greatest men who ever touched this globe. He has explained more of the phenomena of life than all of the religious teachers.” …–Robert G. Ingersoll

አሌክስ አብርሃም ስነፍጥረትን እንዲህ ያስጎበኘናል፦

<<ምድርም ሰማይም ባዶ ነበሩ! …እና ባዶው ምድር ላይ …እግዚአብሔር ሳር ነሸ፣ ቅጠል ነሸ፣ ውሃ ነሸ፣ ፀሃይ ነሸ እንደጉድ ፈጠረው …. በግ ነሸ፣ ዶሮ ነሸ፣ በሬ ነሸ፣ ዳይኖሰር

Created in Master PDF Editor

ነሽ …..ፈጠረ ፈጠረና ከዳር እስከዳር አየት አድርጎ ሲያበቃ ‹‹ፓ መልካም ነው›› አለ! ከዙፋኑ በታላቅ ግርማ ሞገስ ተነስቶ ወደፈጠረው ምድር እጁን ዘረጋ …..እናም ትኩሱን አፈር ቆንጠር አድርጎ ትንፋሹን እፍ ቢልበት ሰው ሁኖ እርፍ! ያውም አዳምን የመሰለ ጎምላላ ትካሻ ከባድ ሰው!‹‹ ያውልህ በተዘጋጀ ምድር ላይ ዘና ብለህ ኑር ….›› አለው አዳምን:: ምን ዋጋ አለው አዳም ነጭናጫ ነበር ….እግዜር ብቅ ብሎ ‹‹ እንዴት ነው ኑሮ›› ሲለውአዳም ይነጫነጫል ‹‹ ምን ኑሮ ሳር፣ ቅጠል፣ ውሃ፣ተራራ፣ ሸንተረር፣ ጫካ፣ ዝሆን፣ ዳይኖሰር፣ ወፍ፣ ወንዝ፣ ኹረት ይሄ ሁሉ ኮተት ገና በፈጠርከኝ በሳምንቱ ደበረኝ›› አለ::‹‹ ጥሩ! ምን ልፍጠርልህ ታዲያ ›› አለ እግዚአብሔር የሆዱን በሆዱ ይዞ ‹‹ እኔ ምን አውቄ ብትችል እንደገና ወደአፈር ብትመልሰኝ ›› ሲል አዳም ተነጫነጨ:: እግዚአብሔርም ሂዋንን አሰበ …አሰበ ማለት ያው ፈጠረ ነው:: ሰነባብቶ እግዜር አዳምን ጠራና ‹‹እህ እንዴት ነው ሂወት? ›› ሲለው‹‹ ኧረ ተወኝ ! አሁን ገና ገነትን ሙሉ አደረካት ›› ብሎ እግዜርን በሳቅ ሊገለው:: እንግዲህ ሂዋን ከአዳም ጋር ወዲያ ወዲህ እያለች ስለወደፊቱ ብቻ እያወሩ በደስታ ፍንክንክ ብላ ስትኖር አንድ ቀን እንዲሁ ብቻዋን ወደጫካው ጎራ አለች … እባብ እያፏጨ ቁሞ ነበር …ሂዋንን ሲያያት እንዲህ አላት::

‹‹ ሃይ ቆንጅት እዚህ ሰፈር ነሽ እንዴ? ››

‹‹ አዎ አንተስ?››

‹‹ እኔም እዚሁ ነኝ …አንችን የመሰልሽ ቆንጆ ግን እንዴት እዚህ ጫካ ውስጥ ያስቀምጥሻል? እኔ እንዳንች አማላይና ውብ እግሮች ቢኖረኝ ኖሮ የት በደረስኩ››ሂዋን ለመጀመሪያ ጊዜ አካባቢዋን ቃኘችው የተሸለ ሰፈር ይኖር ይሆን እንዴ ብላ ነፍሷን አባነነችው:: --- ቀጥሎም

‹‹ እስኪ ሳር ቅጠል እንበል የኔ ቆንጆ ›› አላት እባብ …ያኔ ሳር ቅጠል እንበል ማለት በአሁኑ ቋንቋ ‹‹ሻይ ቡና እንበል›› እንደማለት ነው…እናም ሴት ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ ግብዣ የተጋበዘችው የዛን ጊዜ ነው እንግዲህ ሂዋን በእባብ ተጋብዛ ግብዣው መዘዝ መዘዘና አዳምንም ይዞት ዘጭ አለ::

አዳም ፍሬውን ሲበላ መብላትን መሰረት ያደረጉ ሁለት ርግማኖችን ተረገመ::

አንደኛ ‹‹አዳም›› አለው እግዜር‹‹ አቤት ›› አለ እየፈራ‹‹ግረህ ጥረህ ብላ››

ሁለተኛ ‹‹አዳም ቅድም ግረህ ጥረህ ብላ ብየሃለሁ አይደል?›› አለው እግዜር

‹‹አዎ›› አለ ምን ሊለኝ ነው ብሎ በጉጉት‹‹ አሁን ደግሞ እለሃለሁ… አፈር ብላ ››>>

(ምንጭ፣ አሌክስ አብርሃም፣ http://www.shegerblogs.com/author/alex/)

የዝግመተ ለውጥ ጽንሰ-ሃሳብ በጥድፊያ፣ በችኮላና በይሁን ይሁን የተቀናበረ አይደለም:: ለመረዳት ቀላል ነው በተፈጥሮ ውስጥ ጥቃቶች በብዙ አቅጣጫዎች ይመጣሉ:: የምግብ እጥረት፣ ድርቅ፣ግጭት፣ በሽታ፣ አዲስ አዳኝና አዲስ የአየር

Created in Master PDF Editor

ሁኔታ እኒህ ክስተቶች ለውጥ እንዲኖር ያስገድዳሉ።ድርቅን፣ ግጭትን፣ በሽታዎችን፣ አዲስ ጠንካራ አዳኞችንና ተለዋዋጩን የአየር ንብረት ለመልመድና ለማሸነፍ ፍጥረት ይታገላል። ተፈጥሮ ስነ-መግባርና ይሉኝታ የላትም አሸናፊውን ብቻ ይዛ ተጓዛለች። አሸናፊዎች ለአሸአናፊነት ያበቃቸን ባህርያት ለልጆቻቸው ያወርሳሉ።ልጆችም አባቶቻቸው የጀመሩትን ሩጫ ያስቀጥላሉ። መቆም፣ መስልቸትና መድከም የትውልድ ሞት ዋዜማዎች መሆናቸውን ሁሉም ይረዳሉ፣ በስነ-ፍጥረት ሁሉም ፍጥረታት ሞት እንዳለ የሚያውቁ ይመስለኛል። ለምሳሌ ቀበሮ ያዩ በጎች ለምን ይሮጣሉ? እባብና ጭልፊት ያዩ አይጦች ለምን ይደበቃሉ? ሞትን በመፍራት አይመስላችሁም? ሰውስ ሞት እንዴት ይቀበለው ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም እንዳሉት“ልደት የሞት ዋዜማ ነው፤ ሕይወት የሞት ጥሪ ነው፣ ኑሮ የሕይወት ጻዕር ነው። ሰው መሆን ይህንን እውነት ማወቅ ነው።” ይህንን እውነት ያወቀ ደግሞ እስከመጨረሻዋ እስትንፋስ ይታገላል፣ ይሮጣል። በመጨረሻው ሰዓትም ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ‘ሩጫዬኝ ጨርሻለሁ’ በማለት ለትውልድ የዱላ ቅብብሎሽ የሚመስል አኗኗርን ያስረክባል።

በተፍጥሮ ውስጥ ትልቁ ጥበብ ራስን ማዳን ነው። ፍጥረታት ራሳቸውን ለማዳን የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። ይህ ራስን ላማዳን የሚደረገው ጥረት ነው የብዛህነት ምንጭ፣ የስነ ምህዳር ውበት። ይህን ድንቅ ጥበብ የሚያጠናውን ዘርፍ የዝግመተ ለውጥ ሳይንስ የምንለው። የዝግመተ ለውጥ ሳይንስን ለመረዳት ደግሞ የሁለንታን እድሜና በዚህ ረዥም እድሜ ምን ሊለማና ሊጠፋ እንደሚችል ማንሰላሰል ያስፈልጋል። ቀጭኔ የረጃጅም ዛፎችን ቅጠል የመብላት፣ ሰውም በኮምፒተር የመጻፍ ደረጃ ላይ ለመድረስ አሰልቺ ፍትጊያ ለሚሊዮን አመታት ተካሂዷል። ለዚህ ነው ተመራማሪዎቹ “The short-necked ancestors of giraffes did not evolve long necks overnight or even over the course of a few generations. It has taken dozens, hundreds, thousands, and in some cases millions of generations for the process of selection to gradually shape the organic mechanisms we see today. Of course, some changes occur extremely slowly, others more rapidly. And there can be long periods of no change, followed by a relatively sudden change” የሚሉት። (David Buss፣ Evolutionary Psychology፣ page 8)

ከእዉነት ሚዛን አንፃር የዝግመተ ለውጥ ጽንሰ-ሃሳብ ከስበት ህግ ንድፈ ሃሳብ ጋር ተመሳሳይ ነው። ልዩነቱ ዝግመተ ለውጥ ከሀይማኖት ጋር ይጋጫል።በመሰረቱ ከ5ኛ ፎቅ ድንጋይ ቢወረወር መሬት ይወድቃል እና የዛሬ 5 ሚሊዮን አመት በፊት ጦጣ መሰል ፍጥረት ዛሬ ሰው ሆነ ማለት እኩል ነው። ነገር ግን ስሙ እደሚነግረን ዝግመተ ለውጥ ጊዜ አባካኝ ነው። በህይወት ዘመናችን ልናየው አንችልም ወደ ኃላ

Created in Master PDF Editor

ተመልሰን ካልመረመርን በስተቀር። ይህን ክፍተት ተጠቅመው ዝግመተ ለውጥ የሰይጣን ምክር ነው የሚሉ አሉ። ለምሳሌ ተክለ ኪዳን ሰይጣን ለሳይንቲስቶቹ የነገራቸውን የአደራ ቃል ነግሮናል።

> *"እናንተ አምላካችሁን በራሳችሁ እውቀት ለመገደብና በራሳችሁ ስጋዊ እውቀትና ጥበብ ለማገልገልና ለመገልገል የምትፈልጉ ሊቅ ሊቃውንት፣ ሊቅ ምሁራን፣ ስለ ድፍረታችሁና በራሳችሁ ስለመተማመናችሁ ያለኝን አድናቆት እየገለጽኩላችሁ፤ ለወደፊት ከእናንተ እውቀትና አስተሳሰብ በላይ የሆነውን እንዳች እንዳትቀበሉ። እንኳን ፍጡር ሰው አይደለም እርሱ እግዚአብሔር ተገልጾ ቢናገራችሁ፣ ቢያዛችሁ፤ ቢገላጽላችሁ፣ እንዳትሰሙ እንዳትቀበሉ።ነገር ግን እውቀታችሁ እንዲጎለብትና እንደዲበለጽግ ከእኔ ከጨለማው ገዥ የሆኑትን ለየት ያሉ ትምህርቶችን ተቀበብሉ። ለምሳሌ 'ሰዎች የተገኙት ከተፈጥሮ ነው። ከጦጣ መሰል አንስሳ ቀስ በቀስ ዕድገትና ለውጥ (በኢቮሊሽን) ደረጃ አልፈው ነው። እግዚያብሔር የሚባል ነገር የፈጠሩት የገዥ መደቦች ሕዝቡን ሊጨቁኑበት ለመጠቀሚነት ነው። ወዘተ' የሚሉትን እናንተም ተቀብላችሁ ሌሎቹንም ብታስተምሩ ዋጋችሁ ከእኔ ዘንድ ታላቅና የተለያየ የክብር ማዕድ የሚያስጣችሁ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ አሳውቃችኋለሁ።"*(የጨለማው ገዥ ተግባርና ንግግር፣ 2009 ዓ.ም፣14)

ፀረ ዝግመተ ለውጥ ያሉትን ቢሉም በተለያየ ሀገር፣ በተለያየ ቋንቋ፣ በተለያየ ዘርፍ ጥናት የሚያደርጉ ሳይንቲስቶች ግን ዝግመተ ለውጥን እንደ ነባራዊ ሀቅ ይቆጥሩታል። የSkeptics Society ጸሃፊዎች no one has ever seen evolution happen ለሚለው ትችት መልስ ሲሰጡ የሚከተለውን ብለዋል። "Evolution is a historical science confirmed by the fact that so many independent lines of evidence converge to this single conclusion. Independent sets of data from geology, paleontology, botany, zoology, biogeography, comparative anatomy and physiology, genetics, molecular biology, developmental biology, embryology, population genetics, genome sequencing, and many other sciences each point to the conclusion that life evolved." (skeptic.com) ዝግመተ ለውጥን ሳይንቲስቶች ብቻ ሳይሆኑ አብዛኛው ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ተቀብለውታል። አንዳንዶች የሀይማኖት ተቋማትም በይፋ የድጋፍ መግለጫ አውጥተዋል። ለምሳሌ፦

"There is no contradiction between an evolutionary theory of human origins and the doctrine of God as Creator." — General Assembly of the Presbyterian Church
"Students' ignorance about evolution will seriously undermine their understanding of the world and the natural laws governing it.— Central Conference of American Rabbis

Created in Master PDF Editor

"... there is no conflict between evolution and the doctrine of the faith. … Today, more than a half-century after the appearance of that encyclical, some new findings lead us toward the recognition of evolution as more than an hypothesis. In fact it is remarkable that this theory has had progressively greater influence on the spirit of researchers, following a series of discoveries in different scholarly disciplines."— Pope John Paul II

ከሁሉ የሚደንቀው ደግሞ በተለያየ የክርስትና ሀይማኖት ክፍፍሎች ውስጥ የሚገኙ ከ10,000 በላይ የሚሆኑ ቀሳውስት በጋራ ያወጡት ያቋም መግለጫ ደብዳቤ ነው:: እንዲህ ይነበባል፦

"<u>We the undersigned</u>, Christian clergy from many different traditions, believe that the timeless truths of the Bible and the discoveries of modern science may comfortably coexist. We believe that the theory of <u>evolution is a foundational scientific truth,</u> one that has stood up to rigorous scrutiny and upon which much of human knowledge and achievement rests. … We believe that among God's good gifts are human minds capable of critical thought and that the failure to fully employ this gift is a rejection of the will of our Creator. . . . We urge school boardmembers to preserve the integrity of the science curriculumby affirming the teaching of the theory of evolution as acore component of human knowledge. We ask that scienceremain science and that religion remain religion, two verydifferent, but complementary, forms of truth."—The Clergy Letter Project signed by more than 10,000Christian clergy members. (Science, Evolution, and Creationism, page 13)

ስለዚህ ይህ ሁሉ ህዝብ የሰይጣን መልዕክተኛ ነውን? አማኞቹ ምርምሩን የተቀበሉት እንደግለሰብ ሳይሆን እንደ ተቋም ነው፣ በተለይ የሮሟ ካቶሊክ እና እስልምና (ተቃውሞ ቢኖርም):: የኦርቶዶክስ አባቶች ግን ቃሉን ስለሚፈሩት የሰይጣን ትምህርት ነው ከማለት ውጭ ወደ ውስጥ በቅን ልቦና ገብተው መመርመር አይፈልጉም:: ኦርቶዶክስ ሊህቃን እንደ ተሃድሶና ዝግመተ ለውጥ የሚፈሩት ቃል ያለ አይመስለኝም::በተለይ ዝግመተ ለውጥን የሚፈሩት አምላክ ከ5500 ዘመን በኋላ ከልጅ ልጅህ ተወልጅ አድንሃለሁ ካለበት አቆጣጠር ጋር ስለሚጋጭ ነው:: በኦርቶዶክሶቹ ሂሳብ ሁለንታ ከተፈጠረ 7511 አመት ነው:: ይህን ለተክለ ኪዳን የነገረው ዲያቢሎስ ሲያብራራው እንዲህ ይላል::

> *"5500 ዘመን ሲያልቅ ያቺ የሰው ዘሮች መዳኛ ምክንያት የሆነቻውና ትጠበቅ የኘበረችው ነፍስ ኢያቄምና ሃና ከሚባሉ እግዚያብሔርን በመፍራት ከሚኖሩ ቤተሰቦች ተወልዳ ለአቅመ ሔዋን ስትደርስ ያ ለአዳም <u>‹‹ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለው::››</u> ብሎ ቃል የገባለት አልፋና ዖሜጋ፤ በሕያውነት ዘመን ውስጥ ከዛሬ 7503 ዓመት (በ2003) በፊት ስማያትንና እልፍ አእላፋት ወትእልፊት መናፍስና*

Created in Master PDF Editor

ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ፤ በኋላም ዓለምንና በውስጧ የሚታዩትንና የማይታዩትን ፍጥረቶች ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ፤ ከፈለገም በዓይን ቅጽበት ውስጥ አሁን ካለው ፍጥረት በእልፍ አእላፍት እጥፍ ካለመኖር ወደ መኖር ማምጣት የሚችል፤ ከፈለገም የሚታየውንም የማይታየውን ዓለም በዓይንቅጽበት ውስጥ ከመኖር ወደ አለመኖር ማሳለፍየሚችል፤ ካለእርሱ ፍቃድ አንዳች ሊሆን ሆነ ሊኮን የማይቻል፤ ሁሉን የሚመለከትና የሚቆጣጠር፤ ያልኖረበትና የማይኖርበት ጊዜ የሌለ፤ ለእያንዳንዱ እንደ ስራውና እምነቱ የሚፈረድለትና የሚፈርድበት እውነተኛ ፈጣሪ አምላክ እግዚአብሔር፤ ከአማናዊ ሕዋ ውስጥ ሳይጎል፣ ከሰማያት ሳይጎል፣ ከዓለም መግቦቱ ሳይጎል፣ ባጠቃላይ በሁሉ ቦታ ምሉዕ እንደሆነ ባሕርይውን ብቻ ዝቅ አድርጎ ከእመቤታችሁ ከመዳኛችሁ ምክንያት፣ ከአደራ እናታችሁ ከእኔ ደግሞ ከዘመናት ደመኛዬና ጠላቴ ከሆነችው ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ፣ ከነፍስ ነሰቶ ከሁለት አካል አንድ፤ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በመሆን በዋተሕዶ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ሆኖ ተወለደ።” (የጨለማው ገዥ ተግባርና ንግግር፣ 2009 ዓ.ም፣ 58)

ማንም የማይክደው ዝግመተ ለውጥ ምንም ያህል ቅሬት ቢሰበሰብ ክፍተቱ ይቀንሳል እንጅ ፍጹም አይሆንም፣ ለምን ቢባል የሚልዮኖችን አመጣጥ የሚያጠና ሳይንስ በመሆኑ ነው። ቢሆንም ግን ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለው ከሚለው የልጆች ትረት ግን በእጅጉ ይልቃል። የዝግመተ ለውጥን እውነታነት ሊከራከሩ የሚችሉት የክርስቲያን ሳይንስ አራማጆች እንጅ ክርስቲያኖች አይደሉም። የክርስቲያን ሳይንስ አራማጆች ሳይንስን እየተከተሉ ‘አወ ልክ ነው’ ግን ይህ እውነት ከየት መጣ ይላሉ። ለምሳሌ የዝግመተ ለውጥ ፍልስፍና ብዙ እውነቶችን ያዘለ መሆኑ አያጠራጥርም የሚሉት መ. ኃ. ዶ/ር መስቀል ‘ከምድራዊነታችን ባሻገር’ 3ኛ መጽሃፋቸው ላይ የክርስቲያን ሳይንስ ዝግመተ ለውጥን የሚሞግትበትን ጠንካራ ጥያቄወች ዘርዝረዋል። ልክ እንደማንኛውም የክርስቲያን ሳይንስ አራማጅ የራሳቸው ግልጽ አቋም የላቸውም። ከፈለጉ “እግዚአብሔር ሰውን ጭቃ ጠፍጥፎ ነው የሠራው ማለት ወይንም እግዚአብሔር ሰውን እንዴት እንደፈጠረው እኔ አውቃለሁ ብሎ አላስፈላጊ ትንተና ውስጥ መግባትም የድፍረት ሞኝነት ነው። እግዚአብሔር ፍጥረቱን በፈለገው አይነት መንገድ ይፈጥራል። እግዚአብሔር በቅድሚያ ቺምፓንዚን ፈጥሮ ከዚያ በኋላ የራሱን መንፈስ ቺምፓንዚ ውስጥ ሲያስገባ ከሆነ እኛ ሰው የሆነው ይሁና። ምናለበት?” ይላሉ። (ገጽ፣ 116)

ሙህሩ ሕይወት ከመጨረሻውና ከዝቅተኛው ህዋስ (ሴል) በመልክም “በጥራትም” ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ስለመጣ የምድር ሕያዋን ሁሉ መነሻቸው የመጀመሪያውና ዝቅተኛው ህዋስ መሆን አለበት የሚለውን የዝግመተ ለውጥ መነሻ ሀሳብ ሲሞግቱ “የመጀመሪያው ባለ አንድ ህዋስ (ሴል) በራሱ ተገኘ ስንል ግን የሚከተሉትን

Created in Master PDF Editor

ጥያቄዎች ያስከትላል" ይላሉ:: "1. እንዴት ነጠላ የሕይወት መስራች ሞሌኩሎች (ካርቦን፥ ኦክሲጂን፥ ሃይድሮጂን፥ ናይትሮጂን፥ ሰልፈርና ፎስፎረስ) ባንድ ላይ ተከማችተው ተገኙ? 2. እነኚህ ሞሌኩሎች እንዴት ነው ባንድነት ተቀናጅተው (ማንም ሳይነካቸው በራሳቸው) ለህዋሱ ሰውነት የሚሆኑትን ኬሚካሎች (starch, cellulose) የመሠረቱት? 3. እንዴት ነው ህዋሱ እነኚህን ኬሚካሎች (starch, cellulose) በአንድ አካሉ የታቀፋቸውና የራሱ ያደረጋቸው? እንዴት ነው ኬሚካሉቹ እንዳይረግፉ ዙሪያውን መታቀፊያ ቆዳ (membrane) ለራሱና በራሱ ያበጀ? 4. ህዋሱ ለመንቀሳቀስ ኃይል ያስፈልገዋል፤ የመጀመሪያው ኃይል እንዴት ከኬሚካሎቹ ሊመነጭ ቻለ? ወይንም እንዴት ነው ኬሚካሉን የሚቀሰቅስ ውጫዊ ኃይል (የጸሐይ ብርሃንና ሙቀት) ነፍስ ዘሪ የሆነ? 5. የአካላዊ ሕያዋን ሁሉ የተፈጥሮ ሕግ የሆነው እራስን የማባዛት ጠባይ እንዴት ነው በመጀመሪያው ህዋስ ውስጥ የተከሰተው?" ይቀጥሉና "ከተጠቀሱት አምስት ጥያቄዎች ውስጥ የመጀመሪያዎቹ አራቱ ጥያቄዎች በሚከተለው አንድ ጥያቄ ይጠቃለላሉ፡- እንዴት ነው ሕይወት ከግዑዛን የሚመነጭ?" ይላሉ:: (ገጽ፣ 94)

ሕይወት ከግዑዛን እንዴት ነው የሚመነጭው ወይም ህይወት ለመጀመርያ ጊዜ እንዴት ያለ ፈጣሪ ተፈጠረ የሚለው መሰረታዊ ጥያቄ የዶ/ር መስቀል ጥያቄ ብቻ አይደለም:: የእኔም፣ የሳይንቲስቶችና የፈላስፎችም ጥያቄ ነው:: ጥያቄውን ለመመለስ በርካታ ጥናቶች ቢደረጉም አጥጋቢ ውጤት ግን አልተገኘም የተለያዩ አማራጭ መላምልቶችን ከማስቀመጥ ውጭ:: ይህን ክፍተት ለሞሙላት የክፍተት አምላክ (God of the Gap) መፍጠር ግን የዶ/ር መስቀል ጥያቄ አይመልሰውም:: በነገራችን ላይ ኢንተሊጀንት ዲዛይን የሚለው ቲወሪ መነሻው ይህ ጥያቄ ነው:: እንደሌሎቹ ጥያቄዎች ይህ ጥያቄ የተመለሰ ጊዜ የክሬሽን ሳይንስ እና የልጁ ኢንተሊጀንት ዲዛይን ግብዓተ መሬት ይፈጸማል::

ዶ/ር መስቀል የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ቃላል አይደሉም የፍጥረታትን ዝምድና በተለይም ሰውን በተመለከተ በተደጋጋሚ የጠየቁት ሌላ መሰረታዊ ጥያቄ አለ:: "በሰው ዘርና በዝንጀሮዎች መካከል እንደ ማስረጃ የሚቀርብ <u>መሃል ሠፋሪ</u>(የዝንጀሮ ዘር ወይም የሰው ዘር የማይባል) የት አለ? መሀል ሰፋሪን አስመልክቶ "Evolution does not teach that humans descended from monkeys; it states that both have a common ancestor" የሚለውን የዝግመተ ለውጥ ትምህርት ያልሰሙ የምዕራቡ አለም ቴሌቫንጋሊስቶችም ዛሬም "If humans descended from monkeys, why are there still monkeys?" በተጨማሪም "If evolution is gradual, there should be no gaps between species." ይላሉ::

ሳይንቲስቶች ሲመልሱ እንዲህ ይላሉ “Evolution is not always gradual. It is often quite sporadic. And evolutionists never said there should not be gaps. Butgaps do not prove creation.. . . The existence of living fossils (organisms that have not changed for millions of years) simply means that they evolved a structure adequate for their relatively static and unchanging environment, so they stopped once they could maintain their ecological place. Sharks and many other sea creatures are relatively unchanged over millions of years, while other sea creatures, such as marine mammals, have obviously changed rapidly and dramatically. Evolutionary change or lack of change, as the case may be, all depends on how and when a species' immediate environment changes.” (Why people believe weird things, page 152)

የማስረጃ እጥረት አለ ለሚሉትም “Hundreds of studies verify the facts of evolution, at both the microevolutionary and macroevolutionary scale—from the origin of new traits and new species to the underpinnings of the complexity we see in life and the statistical probability of such complexity arising. …These days even most creationists acknowledge that microevolution has been upheld by tests in the laboratory (as in studies of cells, plants and fruit flies) and in the field (as Galpagos finches). Natural selection and other mechanisms—such as chromosomal changes, symbiosis and hybridization—can drive profound changes in populations over time. The historical nature of macroevolutionary study involves inference from fossils and DNA rather than direct observation. (15 Answers to Creationist Nonsense by John Rennie)

“በዘገምተኛ ለውጥ ሂደት አዳዲስ ሁኔታዎች እየተከሰቱ፣ አዲስ ሁኔታዎችን ለመቋቋም የሚችሉ ወራሾች እየተገኙ፣ አዳዲስ ሁኔታዎችን መቋቋም የተሳናቸው እየወደሙ፣ እየከሰሙ፣ በቢሊዮን ዘመናት መሬት አሁን የምናያቸው የብዙ ዓይነት የሕይወት ባለፀጋዎች መኖሪያ ሆነች፡፡” (ሽብሩ ተድላ፣ የህያው ፈለግ፣ 2010 ዓ.ም)፡፡ በዝግመተ ለውጥ ውስጥ ጊዜና የተፈጥሮ መለዋወጥ ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ ስነ ፍጥረት ከቀላል ስሪት ተነስቶ ውስብስብ ለመሆን በቂ ጊዜና ሁኔታዎች አሉት፡፡ በ7500 አመት ውሰጥ ግን የተወሰነ ለውጥ ሊኖር ቢችልም በርካታ የተለያዩ ዝርያዎችን የማስገኘት አቅም የለውም፡፡ ዝግመተ ለውጥን ከ7500 አመት የአለም ታሪክ ጋር አቆራኝተው የሚያምኑ ሰዎች ቢኖሩም በ10,000 አመት ውስጥ ይህን ያህል የተጋነነ ለውጥ ሊኖር አይችልም የሚሉት ደግሞ መጽሃፋቸውን አስቀድመው ሳይንሱን የሰይጣን ምክር ነው ብለው አጣጥለውታል፡፡

የስነ-ፍጥረት ታሪክ 7500 አመት ነው ማለት ከአዲስ አበባ ዋሽንግተን ያለው ርቀት 7500 ሜትር ነው እንደማለት ነው፡፡ ይህን አይን ያወጣ ውሸት ሙጥኝ ማለት ያስተዛዝባል፡፡ከአዲስ አበባ ዋሽንግተን ያለው ርቀት 7500 ሜትር አለመሆኑን ለማረጋገጥ በሜትር መለካት አይጠበቅብኝም፣ የሁለንታን እድሜም እንዲሁ፡፡ ከአዲስ

Created in Master PDF Editor

አበባ ዋሽንግተን ምን ያህል ኪሎ ሜትር መሆኑን ለክተው እንደነገሩን ሁሉ ከቢግ ባንግ እስከዛሬ ያለው የዘመን ርቀትምአስልተው ነግረውናል። እግዚአብሔር ደግሞ ለተክለ ኪዳን በዝግመተ ለውጥና የሁለንታ እድሜ በቢልዮን የሚቆጠር ነው ብለው ለሚያምኑት እንድህ ብለህ ጻፍ አለው፦

> እናንተ አፈጣጠራችሁ ታላቅ የሆነ፣ ነገር ግን ክብራችን ያዋረዳችሁ፣ ማንነታችሁን የዘነጋችሁ፣ ሕያው የሆነች ነፍስ፣ የማትሞት የማታልፍ ሕይወት እያላችሁ የቀስ በቀስ እድገትና ለውጥ (በኢቮሊሽን) ጦጣ መስል እንስሳ ወደ ሰው ተለውጥን እያላችሁ የምታምኑ፣ ሌላውንም የምታሳምኑ የዓመጻ ልጆች፣ ምን አይነት ሕሊና ነው ያላችሁ? አስራ ሺህ ዕደሜ እንኳን የሌላትን አለም፤ እናንተ ለሰው ዘሮች በሚሊዩን የሚቆጠር ዕድሜ እየሰጣችሁ ለክህደታቹሁ ማሳመኛ የምታቀርቡ፤ ለመሆኑ ሰዎች በሚሊዩን የሚቆጠር ዕድሜ ታሪክ ቢኖራቸው እንኳን ይህች መሬት አይደለም አስር እጥፍ ሌላ መሬት ለመኖሪያነት ይበቃችሁ ነበርን? እስቲ በእናነተ ዘመን እንኳን የሰው ልጆች ቁጥር ከዓመት ዓመት እየጨመረ ምን ያህል እንደሆነ በዚህች በትንሿ ጠባብ አእምሯችሁ ገምቱ? ታድያ የሚሊዮን ዓመት የሚቆጠር ከሆነ የሰው ዘሮች ታሪክ፣ አሁን ያለው የሰው ልጆች ቀጥር ብዛት በትርሊዮንና በካትርሊዮን አይደለም ከሰው አእምሮ በላይ የሆነ ቀጥር ሊኖራችሁ ይገባ ነበር። እናንተም ስታችሁ ሌላውንም ታስታላችሁ፣ ይህ ሁሉ ጥረታችሁና ሐሳባችሁ እንደ መሪያችሁ ዲያብሎስ የእኔን ህልውና ለማጠራጠርና ተፈጥሮን ያስገኘውን ኃይል ተለይታችሁ ስትመጡ ወዴት ይሆን መግቢያችሁ? (የመጨረሻው ፍርድ አፈጻጸም ውሳኔ፣ 2ኛ ዕትም፣ 28-29)

የተክለ ኪዳኑ አምላክ ስማኝማ ዝንጀሮም ጦጣምአይደለሁም፣ ከዝንጀሮም አልመጣሁም በዝግመተ ለውጥ ጥናት ያደረገማንም ሳይንቲስት ሰው የመጣው ከጦጣ ወይም ከዝንጀሮ ነው አላለም። ሰባኪያን ሳይንሱን ለማወናበድ የተጠቀሙት ነው። እውነቱን ግን ዶ/ር ሽብሩ ተድላ እንደሚከተለው ያብራሩታል።

> የሰው ልጅ፣ ከችምፓንዚዎች ጋር (96-99%) የሚሆነውን በራሂውን (ዘረ-መሎችን-DNA) ይጋራል። በራሂን የመጋራት ልኬት መጠን፣ የዝምድና ቅርበት ማረጋገጫ ነው። የሰው ልጅ አሁን በዓለም ላይ ግንኙነት አለው እንጂ፣ ሰው እና ጭላዳ የአንድ ዘመን እንስሳት በመሆናቸው የወላጅ እና የልጅ ዝምድና የላቸውም። የዘር ግንዳቸው በተለያዩ የዘር ቅርንጫፎች መጓዝ የጀመረው ከ25 ሚሊዮን ዓመታት ገደማ በፊት ነው። ከረጅም ጊዜ በፊት ወንድማማቾች/ እህትማማቾች ያፈሯቸው የልጅ፣ ልጅ፣ ልጅ፣ ልጅ … ናቸው። በሰው ልጅ ዝግመተ-ለውጥ ወሳኝ የነበረው በሁለት እግር ብቻ ቆሞ መሄድ መቻሉ ነበር። ይህንንም ቀስ በቀስ ለማድረግ የቻለው ከስደስት ሚሊዮን ዓመታት ጀመሮ ሲሆን፤ ለውጡ የተካሄደው በአፍሪቃ "ስምጥ ሸለቆ" ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነበር። አፋር ውስጥ አፅሟ የተገኘው ድንቅነሽ (ሉሲ-lucy) ከሶስት ተኩል

Created in Master PDF Editor

ሚሊዮን ዓመታት በፊት በሁለት እግሮቿ ቆማ ለመሄድ ትችል እንደነበር ሳይንስ ይዘግባል። (ሽብሩ ተድላ፣ የህያው ፈለግ፣ 2010 ዓ.ም፣ 125-126)

ሳይንሱ ሰውና የተለያዩ የጦጣና ዝንጀሮ ዝርያዎች ከአንድ የጋራ ቅደመ አያት የመጡ ናቸው ነው የሚለው። ይህን ለማረጋገጥ የቅሬተ አካል፣ የአናቶሚ፣ የጀነቲክስ፣ የስነ ፍጥረት የኬሚካል ግንባታ ተመሳሳይነትና የጂኦግራፊካል ስርጭትና እና ሌሎችም ማስረጃዎችአሉ።

የተክለ ኪዳኑ አምላክ ስለአለም ታሪክ፣ ስለታላላቅ እልቂቶች፣ ስለጠፉት ዝርያዎች፣ ስለወረርሽኞች፣ ስለበረዶው ዘመን፣ ይልቁንም የሰው ልጅ አመጣጥ ታሪክ ሰለማያውቅ አሁን ህክምና የሞትን አንገት በአነቀበት ሂሳብ የአለም ህዝብ በካትርሊዮን ይቆጠር ነበር ማለቱ አይደንቅም። Why God earn PhD in Biology? History? Chemistry? Physics? And Astronomy?

በዝግመተ ለውጥ ፍጥረት እንዴት ተፈጠረ? ሁሉም የዕፅዋት እና የእንስሳት ዝርያዎች እኛን ጨምሮ በተፈጥሯዊ ምርጦሽ (Natural Selection) ሂደት ለዚ በቅቷል።ተፈጥሯዊ ምርጦሽ እጅግ በጣም ብዙ የተለያዩ ህይወት ያላቸው ፍጥረታት እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል።የዘረመል ተመራማሪዎች ዘመናዊው የሰው ዘር ከሌላው ህይወት ጋር የጋራ ዝርያ እንዳለው ያስረዳሉ።መጠኑ ይለያያል እንጅ ከቺምፓንዚዎች ጋር ብቻ ሳይሆን ከሁሉንም አጥቢ እንስሳት፣ ከወፎች፣ ከተሳቢ እንስሳት፣ ከነፍሳት፣ ከተክሎች እና ከፈንገሶች ጋር ሳይቀር የዘረመል ዝምድና አለን። አይገርምም እኛ በእየ ብሔራችን ዘር እንቆጥራለን ሳይንሱ ግን ከሚያገለግሉን እንሰሳት እና ከምንመገባቸው እፅዋት ጋር አዛመደን። ታድያ የሰው ልጅ ከስነ ፍጥረት ተለይቶ ዘላለማዊ እና ልዩ የሚሆንበት ሂሳብ ምንድን ነው? “የሰው ልጅ ዘላለማዊነትን የሚመኘው ህይወትን ስለሚያፈቅር ሳይሆን ሞተን ስለሚፈራ ነው። እንስሳት ሞትን አይፈሩም፤ ስለሞት አያስቡም፤ ቀድሞውንም ሞትን አያውቁም። ስለዚህም ስለገነት አያስቡም፤ ሰለዘላለማዊ ሕይወት አይጨነቁም። የሰው ልጅ ማሰብ ሲጀምር መጀመሪያ ያወቀው መሞቱን ነበር። ሞትን ለማሸነፍ ደግሞ አምላኩን ፈጠረ። በፈጠረው አምላክ የተፈጠረ ገነትና ገሃነምንም መመኘትና መፍራት ጀመረ።” (ጥበብ ቅጽ አንድ፣ 2009፣ 138-139) ይህ ከሆነ ጀምሮ የሰው ልጅ ለፈጠረው ፈጣሪ ሲሰግድ ይኖራል። ይህን መሰል ኳልኩለስ የማይሰሩት ሌሎች ፍጥረታት ግን ዛሬም ከሆዳቸው የዘለለ የሚያስጨንቃቸው እንደለለ ተረጋግጧል። በዚህ ረገድ ውስብስብ ነገሮችን አላማሰባቸው ሳይጠቅማቸው አልቀረም።

በአሁኑ ወቅት በሳይንሱ ማህበረሰብ ያለው ግንዛቤ ሕያው የሆነ ሁሉ መሠረቱ ከአንድ ከዝቅተኛ የሕያው ህዋስ ካለ ፈጣሪ ጣልቃ ገብነት በገዛ ራሱ ሕይወትን መሥርቶ በገዛ ራሱ በረዥም ጊዜ ቀስ በቀስ እየተለዋወጠ ዛሬ የሚታየውን

Created in Master PDF Editor

የእንስሳትና የእጽዋት ብዛትና አይነት አስገኝቷል የሚል ነው። የመጨረሻው ዓለም አቀፍ የጋራ ቅድመ አያት (LUCA በሳይንሳዊ አጠራር) ከ 3.7 ቢሊዮን ዓመታት በፊት ነበር።ዝግመተ ለውጥ ጊዜ ይወስድበታል በቀላሉ ለማሰብ ይከብዳል። ዝግመተ ለውጥን የሚኮንኑ ሰወች እነደሚሉት ሰው ከጦጣ መሰል ባለትደሮች የተወለደ አይደለም። “We didn’t evolve from chimps, but chimps and humans do share a common ancestor.” በቅድመ-ሰው እና በሰዎች መካከል ያለው ወሰን ብዙሚሊዮን አመታትን ፈጅቷል።ስለዚህ መጀመሪያ የተወለደ የሚባል ሰው የለም። የምዕራቡ አለም አመኞች በዝግመተ ለውጥ በማመን ዝግመተ ለውጥን ያስኬደው እግዚአብሔር ነው በማለት ከሳይነሱም ከሀይማኖቱም ሳይሆኑ እግራቸውን ከሁለት ዛፍ ሰቅለዋል። ጥያቄውፈጣሪ ሰወችን መርጦ ነፍስ እፍ ያለበቸው በየትኛ የለውጥ ደረጃ ሲደርሱነው? ወይስ ትንኞች፣ እንቁራሪቶች እና እንጉዳዮች እንደ ሰው ልጆች ዘላለማዊ ነፍስ ይኖራቸዋልን? “የሰው ልጆች ነፍስ ወደ ላይ እንደምትወጣ የእንስሳም ነፍስ ወደ ታች ወደ ምድር እንደምትወርድ የሚያውቅ ማነው?” መክብብ 3፡21።

በሰውና በሌሎች እንስሳት ያለውን ዝምድና ግልጽ ከሚያደርጉት ውስጥ አንዱ የፅንስ እድገት ነው። ፅንስ ወይም ሽል ለዝግመተ ለውጥ እንደማስረጃ ሊቀርብ ይችላል። ስለ ዝግመተ ለውጥ እውነተኛነት ቀላል ማስረጃ ስፈልግ አንድ ፊልም አየሁ። ዶከመንተሪው የወንዱ የዘር ፍሬና የሴት እንቁላል ከተዋሀዱበት እስኪወለድ ያለውን በእየሳምንቱ ከፍሎ ይተነትናል። በእየ ጊዜው የሚመጡትን ለውጦች ይቃኛል። እኔን የገረመኝ ህፃኑ አብዛኛውን የፅንሰ ዘመኑ ሰው ስለመሆኑ በግልፅ አይታወቅም። በደንብ ማስተዋል ይጠይቃል። መጀመሪያ ትል (worm) ይመስላል፣ ከዚያ አሳ ይመስላል፣ ከዚያ የሆነ ባለ አራት እግር ይመስላል፣ ከዚያ ሰው ይመስላል በመጨረሻም ሰው ይሆናል። ስለዚህ ዝግመተ ለውጥን አይተነው አናውቅም ለሚሉት ይህን ፊልም መጋበዝ ነበር። ለነገሩ ሁላችንም በዚህ መስመር አልፈናል የብዙ ሚሊዮን አመታት ለውጥ በ9 ወር አልፈነዋል ማለት ይሆን? በዘመነ ፅንስ ያለውን ታሪኮችን ተውት ሰዎችን ከሌሎች እንሰሳት የሚለየን ምንድን ነው? ከእነሱ ያለው ከእኛ አለ፣ ከእኛ ያለው በአብዛኛው ከእነሱ አለ። ጦጣ መሰል ብቻ አይደለንም ጦጣዎች ነን እንጅ።

ሃይማኖት ከሳይንሳዊ ግኝቶች ጋር እንዴት እንደሚታረቅ የስነ መለኮት ተመራማሪወች እና አንዳንድ አማኝ ሳይንቲስቶች ብዙ የእርቅ ንድፈ ሐሳቦችን አስተዋውቀዋል። ቢሆንም ሀይማኖትን ከሳይንስ ማስታረቅ በአሮጌ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ እንደመጨመር ነው።ይህን አስቀድሞ የተረዳው Lemuel K. Washburn ‘Is the Bible Worth Reading and Other Essays’ በሚል መጽሃፉ እንዲህ ብሎ ነበር፦ “Churches are all hurrying to catch up with the world. There is a desire to square ideas with facts, and shape beliefs with knowledge. Religion must suffer in this process. Something will be lost, but only what is bad, false and wrong. Creeds are out

Created in Master PDF Editor

of date. They are behind the times. They are the dead leaves from the tree of knowledge, the dead branches on the tree of life. The world's faith is in the living; in the bud, the blossom, the promise of things—not in the husk, the shell, in dead and useless things."

ለዝግመታዊ ለውጥ እውነተኝነት ማስርውጃዎች (Evidences of Evolution)

The Talk.Origins Archive ድህረ ገጽ ላይ እንዳገየሁ Helena Curtis እና Sue Barnes, Biology 5thed ገጽ 972 ላይ እንዲህ ይላሉ፦ "Since Darwin's time, massive additional evidence has accumulated supporting the fact of evolution--that all living organisms present on earth today have arisen from earlier forms in the course of earth's long history. Indeed, all of modern biology is an affirmation of this relatedness of the many species of living things and of their gradual divergence from one another over the course of time."

1ኛ. The Fossil Record: (ቅሬታ አካል)፡- traces the history of life; የእንሰሳትሃ የዕፅዋት ቅሬታ አካለ በደለሌ አለቶች (Sedimentary rocks) ውስጥ በብዛት ይገኛል፡፡ በደለሌ አለቶች በሚገኙ ቅሬታ አካሎች የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በርካታ የተለያዩ ያሉ እና የጠፉ የእንስሳትና የእፅዋት ዝርያዎች መኖራቸውን ነው፡፡ ይህ ስነ-ፍጥረት አንዴ የተተከለ ቋሚና የማይለወጥ አለመሆኑን የሚያስረደ ነው፡፡ በዝቅተኛው ደለሌ አለት እስከ ቅርቡ የመሬት ገጽ ድረስ የተደረደሩት ቅሬቶች የሚያስረዱት ዝግመታዊ ለውጥን ነው፡፡ በእርግጥ ሁሉም ቅሬቶች ተሞልተው ተገኝተዋል ማለት አይቻልም፡፡ በቅሬታ አካል አሰባሰብና የሚገኙት ቅሬታ አካሎችም ያለመሟላት ችግር ይስተዋላል፡፡ የመሸጋገሪያ ቅሬቶች መጥፋት በዝግመተ ለውጥ ፅንስ ሐሳብ ጥያቄ የሚያስነሳ ሳይሆን መገኘታቸው በቲወሪው አንድ ጠጠር እንደመጣል ስለሆነ ነው፡፡ በአለፋት 150 ዓመታት የተገኙ ቅሬታ አካሎች ዝግመተ ለውጥን ይብዛም ይነስም የሚደገፍ ናቸው፡፡

2ኛ. Anatomy & Biochemistry (የኬሚካላዊ እና የአናቶሚ መመሳሰል)፡- ሕይወት ያለው ነገር የተገነባበትን የኬሚካል ይዘት እና የአካል ስሪት በማየት ምን ያህል መመሳሳል እንዳለ መረዳት ይቻላል፡፡ ከነጠላ ህዋስ ፍጥረታት እስከ ግዙፍ እንስሳት ድረስ ሁሉም በጋራ የሚጋሯቸው ባህሪያት አሏቸው፡፡ መወለድ፣ ማደግ፣ ዘር መተካት እና መሞት፡፡ ከዚህ ሁሉ የሚደንቀው ግን በስነ ፍጥረት መካከል ልዩነት እንደ ሌላ ያረጋገጠው የDNA ኮድ ነው፡፡

የሁሉም ስነ ፍጥረት DNA የተገነባው ከተመሳሳይ ስሪት ነው፡፡ በሰዋቂ ቋንቋ ማንለማን የቅርብ ዘመድ እንደሆነ ለማወቅ ዝምድና እንደምንቆጥረው ሁሉ DNA የዝምድና ሰንሰለቱን ሊያስረዳን ይችላል፡፡ ስለዚህ ሰው ከጦጣ መሰል እንሰሳ መጣ

ሲባል DNA ባበረከተው የቅርብ ዝምድና ቆጠራ መሠረት እንጅ ተራ አሉባልታ አይደለም።

የእንስሳትን አካላ ስሪት በጥንቃቄ ካጠናነው እጅግ የሚገረም መመሳሰል እናስተውላለን። የሰውን እጅ ከእንስሳት የፊት እግር (በተለይ ከጦጣ፣ ከዝንጀሮ፣ ከውሻ፣ ከድመት) ጋር ቢነፃፀር የተቀራረበ ስሪት አለው። በተጨማሪም እንስሳትን በእየምድባቸው ከፋፍለን ውስጣዊ እና ውጫዊ የአካል ስሪታቸውን ብናይ የሆነ ጊዜ ከተመሳሳይ ምንጭ እንደተቀዱ ይመሰክራሉ።

3ኛ. Biogeography: (የስነ- ፍጥረት መልዕካ-ምድራዊ ስርጭት)፡- ፍጥረታት ተጓዦች ነን። በተመሳሳይ አካባቢ ተረጋግተው እንዲኖሩ የተገደዱ ካልሆነ በስተቀር የስነ-ፍጥረት ታሪክ የሚነግረን ስደትን ነው። በአየር ንብረት መለወጥ እና በምግብ እጥረት የሚችል በክንፉ የማይችል በእግሩ አለምን ሲያከልል ኑሯዋል። በተቃራኒው አንዳንድ የተገለሉ ደሴቶች ግን ፍጥረታትን ሳይሰጡና ሳይቀበሉ በብቸኝነት አኑርዋል። በተለይ አውስትራሊያ፣ በኒውዝላድ እና በሐዊ (Hawaii) አጥቢ እንስሳት በብዛት አልተገኙም። ቅሬታቸው የተገኙትም የአካባቢው ብቸኛ ዝርያዎች ናቸው። ለምሳሌ በአውስትራሊያ የካንጋሮ እና የኮላ ዝርያዎች።

4ኛ. የሽል (Embryo) ተመሳሳይነት፡- ስነ ፍጥረታ ከቅፅበት ፅንሰቱ ጀምሮ ወላጆቹን እስኪመስል ድረስ የተለያዩ የእድገት ደረጃዎችን ያልፋል። በሽል ውስጥ የሚከናውነው የዕድገት ሁኔታ ለዝግመተ ለውጥ አንድ ማስረጃ ነው። ያም ፍጥረታት ይብዛም ይነስም ተመሳሳይ የአስተዳደግ መስፈርት ተከትለው የሚያድጉ መሆናቸው ለይቶላቸው ወላጆቻቸውን እስኪመስሉ ድረስ የቅርፅም መመሳሰል አላቸው። አንዱን ከአንድ ለመለየት እስኪያስቸግር ድረስ።

ከስነ ህይወት (Biology) መፅሀፎቻችን ከማስታውሰው፣ ሊህቃኑም ከሚያቀነቅኑት፣ ተፍጥሮም ካስረዳኝ እንዲሁም በፍቃዱ ኃይሉ የሚባል ኢትዮጵያን ኤቲስት በጻፈው መጣጥፍ መሰረት ዝግመተ ለውጥ ከመላ ምት በላይ የሆነ እውነታ እንደሆነ የሚያረጋግጡ በርካታ ዓይነት ሳንሳዊ መንገዶች አሉ። እነዚህም agents of evolutionary changes የሚባሉት የተፈጥሮ ምርጫ (natural selection) ፣ የዘረመል ለውጥ (genetic drift)፣ ሙቴሽን (mutation) እና የዘረመል ፍሰት (gene flow) ናቸው።

- **የተፈጥሮ ምርጫ (natural selection)** <<differential reproduction of organisms as a function of heritable traits that influence adaptation to the environment.>> በወቅታዊው አካባቢያዊ ሁኔታ፣ ለመራባት እና ዘርን ለመቀጠል የሚያስችል ብቃት ያላቸው ዝርያዎች ሲራቡ

Created in Master PDF Editor

እና ሲባዙ ይህንን ያልቻሉት ግን እየተመናመኑና እየጠፉ ይሄዳሉ። በዚህም የተፈጥሮ ምርጫ ዳይኖሶርን ጨምሮ በርካታ እንስሳትና እፅዋት ጠፍተዋል። ዳርዊን የተፈጥሮ ምርጫ ጽንሰ ሃሳብ ሕይወት ያላቸው ማህበረሰቦች ዝግመተ ለውጥ የሚያካሂዱት ምንም እንኳ በዘፈቀደ ስህተት እየፈጸሙ ቢሆንም፣ ተፈጥሮ እራሷ በምትፈጥረው መሰናክሎች እኒህን መሰናክሎች አልፈው የሚሄዱትን በመምረጧ ነው። ስለሆነም የአንድ ማህበረሰብ አባላት ሲሞቱ፣ ጠንክረው የሚቋቋሙት ግለሰቦች ብቻ በሕይወት ቆይተው ወደፊት መራባች ይችላሉ። ስለሆነም ቀስ በቀስ እነዚህ በህይወት ያሉ፣ በህይወት የሌሉትን አይነቶች እየተኩ ይሄዳሉ።ዝግመታዊ ለውጥ ምርጥ ዘርን እያራባ ኮስማና ዝርያዎችን ወደ መቃብር የሚልክ አስቀያሚ ክስተት ነው። ይህም ቢሆን ከተወቃሽ ነጻ ነው ምክንያቱም “evolution by natural selection is not forward-looking and is not intentional rather it is blind king of king”። የተፈጥሮ ምርጦሽ የለውጥ መሳርያው ዝግመት ነው። በዝግመት ተፈጥሮ ማን እንደሚሆናትና ማን እንደማይመጥናት ትረዳለች።

- **የዘረመል ለውጥ (genetic drift):** ሁለት (ወንዴ እና ሴቴ) የዘረመል ቅንጣቶች ተዋህደው በመጠኑ የተለየ የዘረመል ቅንጣት መፍጠር ሲችሉ ነው። ሳይንቲስቶቹ genetic driftየሚመጣን ለውጥ “random changes in the genetic makeup of a population.” እያሉ ይገልጹታል።
- **ሙቴሽን** (mutation ወይም a random hereditary change in the DNA፣ A change in the sequence of nucleotides in DNA) የሚባለው በተፈጥሮአዊ፣ ወይም አካባቢያዊ ተፅዕኖ ሳቢያ ዘረመሎች ድንገታዊ ለውጥ ሲያመጡ ነው። ሙቴሽን መስሎ መኖርና እራስን በራስ ለመለወጥ የሚያስችል ከአካባቢው ሁኔታ ጋር ስምም የመሆን ጥበብ ነው።
- **የዘረመል ፍሰት (gene flow);** (Gene flow is the exchange of alleles between populations. Also called migration.) የዘረ መል ባሕርያት ከአንድ ዝርያ ወደሌላው በሆነ መንገድ ሲገቡ የሚፈጠረው ለውጥ ነው።

እነዚህ አራቱ መንስኤዎች በተለያዩ ጊዜያት የሚያስመዘግቧቸው ለውጦች በሚሊዮን ዓመታት ውስጥ በርካታ የተለያዩ ዝርያዎችን ለማፍራት ያስችላሉ።

ዝግመተ ለወጥ መላመድ ነው። ሁላችን በዚህ የመላመድ ለውጥ ለይ ነን። መስከረም አበራ ነፍስ ያለው ፍጡር ቀርቶ “ነፍስ ያለው ፍጡር ቀርቶ ግዑዝነገርም ሁሌ በለውጥ ሂደት ውስጥእንዲሆን የተፈጥሮ ሕግ ነው። ይህንንትዳይ ታዋቂው ጸሐፊና መምህርፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም‹‹አዳፍኔ›› የሚል ርእስ በሰጡትድንቅ መጽሐፋቸው ‹‹ተፈጥሮ ቆሞ-ቀርነትንአታውቅም፤ ወደ ተሻለ ወይ ወደባሰ መለወጥ

ግድነው::›› ይላሉ:: እውነት ነው:: የሰው ልጅ ቀርቶድንጋይ እንኳን ፀሐይና ዝናብ፣ ሐሩርና ቁርበሚፈራረቅበት ረዥም ሂደትሲያልፍ ወደ አፈርነት ይቀየራል::” ነጻ አስተያየቷን የቀለም ቀንድ መፅሄት ላይ ያሰፈረችው መስከረም አበራ ይህን ተፈጥሮዓዊ ለውጥ ወደ ማህበራዊ ህይወታችን እንደሚደገም ትነግረናለች:: “ይህን ለውጥ ወደማኅበራዊ ሳይንስ አውድ ስናመጣው የሰው ልጅበኢኮኖሚ ሆነ በፖለቲካ ከትናንት ዛሬ መቀየሩግድ ነው:: አዳኝና ለቃሚ የነበረው የጥንታዊውሰው የዘር ሐረግ ዛሬ ባለ ኒውክለር የሆነው፤ ከመሀከሉ በተነሳ ታጣቂ ጉልበተኛ ከመመራት ወደ ራስን በራስ የማስተዳደር ዴሞክራሲያዊ የአስተዳደር ዘውግ የተራመደው በዚህ የለውጥ ሂደት በማለፉ ነው::” (የቀለም ቀንድ ቅፅ 3 ቁጥር 11)

ሰውነታችን አካባቢውን ይለምዳል፣ ይመሳሰላልም:: ጦርነት ባለበት ወታደር እንዳለ በሽታ ባለበት የበለጠ በሽታ ተከላካይ ይኖራል:: እኔን እንደ ቤተ ሙከራ ልውሰድ እረኛ ሳለሁ የወንዝ ውሃ በሸንበቆ ቀለም ስጠጣ ነበር:: የተጣራ ውሃ ለመጠጣት ሳሆን ትልልቅ ተዋህሲያን በተለይ አለቅት ወደ ጉሮሮየ እንዳይገባ ነበር:: በወቅቱ በውሃ ወለድ በሽታ የታመምኩበትን ጊዜ አላስታውስም:: ዛሬ በብዛት የምጠቀመው በተለይ ከቤቴ ውጭ የታሸገ ውሃ ነው:: በተጨማሪም ቡሌ ለተወሰነ ጊዜ ቁርስ፣ እራት፣ ምሳየ ነበር:: ዛሬ ያ ቡሌ ቢሸተኝ ሊያመኝ ይችላል:: ይህን ለውጥ እኔ አልፈጠርኩትም በማላውቀውም ዝግመተ ለውጥ ውስጥ እያለፍኩ ይሰማኛል:: ሌላ አንድ ሙከራ እስኪ የተወሰኑ ጦጣዎችና ዝንጀሮዎችን ከዱር አውጥተን ቤት ውስጥ እናስገባቸው እንዲረቡም እናድርግ:: በእርግጥ ዛፍ ላይ መንጠልጠልን ታጋቾቹ አይረሱትም:: ልጆቻቸው እና የልጅ ልጆቻቸው ግን አያውቁትም በውስጣቸው ግን የመንጠልጠል ፍላጎቱ ይኖራል:: የልጅ ልጆቻቸው የመንጠልጠል ፍላጎታቸው እየቀነሰ ይሄድና ከብዙ ትውልድ በኋላ ዛፍ ለመውጣት የሚፈራ ጦጣ እና ዝንጀሮ ልናገናኝ እንችላለን:: ያኔ ጦጣ ከሁለት ይከፈላል የዛፍ እና የሜዳ ተብሎ:: እኔ እንዲህ በምሳሌ የማብራራውን የመላመድ ጥበብ የማይዋጥላቸው በሌላ ምሳሌ እንዲህ ይላሉ

> *“ሁላችንም የአይጥ ወጥመድ እናቃለን:: ወጥመዱ የተፈበረከበትን ተግባር ሳያስተጓጉል፣ ከተሰራበት አካል አንድ አጉድሉ ብትባሉ የቱን ትፈቱ ይሆን? ምላሾቹ:- <ሁሉም አካላት ወጥመዱ የተሰራበትን አላማ ለማሳካት አስፈላጊዎች ናቸው> እንደሚሆን አልጠራጠርም:: የወጥመዱን ውስብስብነት ከዚ በተሻለ መቀነስ አትችሉም:: ይሄ የመጨረሻ ደረጃ ውስብስብ አካል ነው:: እንዲሁ፣ አንዳንድ ሕይወት ያላቸው አካላት ካሉበት የዉስብስብነት ደረጃ ዝቅ እንዲሉ ለማድረግ መሞከር፣ የወጥመዱን አንድ አካል አጉድሎ አይጥ በአግባቡ እንዲያጠምድ ለማድረግ እንደመሞከር የማይቻል ተግባር ነው:: አንዱን አካላቸውን አጎደልን ማለት አጠቃላይ የአሰራራቸውን መዋቅር አናጋነው ማለት*

Created in Master PDF Editor

ይሆናል። በአጭሩ በሕይወት ያሉበት ደረጃ፣ የመጨረሻው የውስብስብነት ደረጃ ነው ማለት ነው። ይህ የመጨረሻ ደረጃ ውስብስብ መዋቅር በሂደት የሚገኝ (የሚፈጠር) አይሆንም። ከነሱ በታች ዝቅ ያለ የውስብስብነት ደረጃ ስለሌላ ኢቮልቭ (evolve) ሊያደርጉ አይችሉም። በሕይወት ለመኖር አንዳች ነገራቸው ሳይጎድል ባሉበት ሁኔታ መገኘት (መኖር) አለባቸው። ምክንያት ቢሉ የሕልውናቸው መዋቅር ይህና ይህ ብቻ ነውና። ከዚ አንዱ ቢጎድል፣ እነሱ የሉም።" (ወንጌል በድረ-ገፅ አገልግሎት፣ https://ethiopiansite.com/)

የሁሉም እንስሳት እና እፅዋት ትግል ከአካባቢያቸው ጋር መለመድ ነው። መልመድ ፍላጎት አይደለም አስገዳጅ ነው፣ መልመድ ያልቻሉ ይሞታሉ። ቀጭኔ አንገቱ እረጅም ያሆነው ፈልጎ አይደለም። ሰውም ሁለት እግር የሆነው ፈልጎ አይደለም። ስለ ተፈጥሮ ስደመም የቀዝቃዛው ጦርነት ይታወሰኛል። በዚህ ተፈጥሮ በምንለው ታላቁ የቀዛቃዛ ጦርነት እየተካሄደ ነው። አዳኝ ታዳኙን ለመያዝ ሁሌ ይሻሻላል፣ ታዳኝ ከአዳኙ ለማምለጥ እና ለመከላከል ሁሌ ይሻሻላል። እንስሳት ከተፈጥሮ ጋር ብቻ ሳይሆን እርስ በእርሳቸው ፍጥጫ ውስጥ ናቸው። ጦርነት ከጥንት እስከዛሬ ለወደፊትም እስከ አለም ፍፃሜ ይቀጥላል። በዚህ ጦርነት በቢሎዮን የሚቆጠሩ ዝርያዎች ከምድር ገፅ ጠፍተዋል ተብሎ ይገመታል። ተፈጥሮን የለመዱ፣ አዳኞቻቸውን ያመለጡ እና ልጆቻቸውን የተኩ ዝርያዎች ብቻ ይኖራሉ።

በዚህ ጦርነት ሁሌ ማሸነፍ አይችልም። ሁሉም እንስሳት የማይለምዱት ተፈጥሮ ወይም የማያመልጡት አዳኝ ያገኛቸዋል። ዛሬ የውሃ ሽታ የሆነው ታለቁ የምድር ንጉስ ዳይኖሰር ለዚህ ምሳሌ ነው። አሁን አሉ ከሚባሉት ዝርያዎች በብዙ እጥፍ የሚሆንኑት ጠፍተዋል። አሁን ያሉትም ቀስ በቀስ ይጠፋሉ እኛን ጨምሮ። ጥያቄ አለኝ እንበልና ኢየሱስ ክርስቶስ መምጫ ዘመኑን በ1 ቢሊዮን አመት ቢያራዝመው ሰው በምድር ከተፈጥሮ ጋር ተግባብቶ ለስንት አመት መኖር ይችላል? (የሙቀት መጨመርን፣ የህዝብ ቁጥርን፣ የበርሀማነት መስፋፋትን፣ የተፈጥሮ አደጋን፣ ሊውክለርን ታሳቢ አድረጉ)።

9. የሀይማኖት አብዮተኞች ታሪክና ትምህርቶቻቸው

ኢየሱስ፣ መሐመድ፣ አብርሃም፣ ሙሴ፣ ቡድሃ እና ሌሎች የሃይማኖት መሥራቾች በእየጊዜው የተነሱ የለውጥ አራማጅ አብዮተኞች ናቸው። እንደማንኛውም እውነት ናፋቂ ኢየሱስን፣ መሐመድን፣ አብርሃምን፣ ሙሴን፣ እና ቡድሃን ላመጡት ታላቅ ለውጥ አክብሮት አለኝ። ችግሩ የእነዚህ አብዮተኞች እና የመሰረቷቸው ሀይመኖቶች እድሜ ከ 5,000 አመት አይበልጥም። የሰው ልጅ ስዕል መሳል፣የዘመኑ ማደኛ ቁሳቁሶችን መጠቀም፣ጎሳ መፍጠር፣ጨረቃን ፀሀይን እና ሌሎች ጉኡዛንን ማምለክ ከጀመረከ25,000 አመት በላይ እንደሆነው ጥናቶች ያሳያሉ። የሚያሳዝነው አንዳንድ

Created in Master PDF Editor

አማኞች የሁለንታ እድሜ (5500 + 2011= 7,511) አመት ገደማ ነው ብለው ያምናሉ። ይህን አቆጣጠር ብዙዎች ትክክል እንዳልሆነ ቢናገሩም እግዚአብሔር አናግሮኛል የሚለው ተክለ ኪዳን ግን ዛሬ ያምንበታል። አንዳንዶች ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን 5500 ዓመት ሲያመስጥሩት አምስት ቀን ተኩል ይሉታል።

እስከ ቅርብ ጊዜ ማመን አስፈላጊ ነበር ብየ ስለማምን የሚያስጨንቀኝ እነዚ ሰዎች ባይወለዱ ኖሮ ሰው ዛሬ ምን ያመልክ ነበር የሚለው ነው። የዛሬዎቹን ሃይማኖቶች የመሰረቱትነቢያት እና መሲሆች ባይኖሩ ክርስትና፣ እስልምና፣ ይሁዲነት፣ ቡድሂዝም እና ሌሎችምባህላዊ እምነቶች ሊኖሩ አይችልም ነበር። ግን ለራሴ እነዚ ባይኖሩ ሌሎች ይኖሩ ነበር ብየ እመልሳለሁ። በዚያከማመን በስተቀር የሰው ፍላጎቶች እና ማንነታዊ ጥየቄወች መመለስ በማይቻልበት ዘመንከፍርሀት እና ከሽብር አስታግሰውታል ይልቁንም ከሞት በኃላ የተሻለ ህይወት አለ ብለው ጮቤ አስረግጠውታል።በተለይ እራሳችን እያደሱ የተለወጡበት መንገድ እድሜያችን አስረዝሞታል። የንፍስን ነገርም አብዝተው ሰብከዋል። ጥያቂው ግን ነፍስ የት ነው ያለችው? የጥበብ ስብስቦች ፅሃፊ ሀይለ ጊዮርጊስ ማሞ "ታዋቂዋ ፓራሳይክሎጂስት ሱሳን ብላክ ሞር ይሽንኑ የመንፈስ ነገር አስመልክቶ ያደረገችውን ምርምር "Elusive" በተባለ መጽሐፏ ስትገልፀው፡- ከስጋ ሞት በኂላ ወደሌላ አለም ጥሎን የሚሄድ አንዳች ነገር መኖሩን በማስረጃ መቅረብ የቻለ የለም፤ ማንኛውም ሰው ከሞተ በኂላ እሱን በመወከል በሌላ አለም የሚገለፅ ነገር ይኖራል ብሎ ማሰብም ከንቱ ድካም ነው ብላለች ይለናል" (ጥበብ ቅጽ አንድ፣ 2009፣ 130)ደረጀ ፀጋዬ ግን እንዲህ ይላል "ከየትም ይምጣ ወዴትም ይሂድ የሰው ልጅ ለአፍታም ቢሆን በዚህች ዓለም ህያው ሆኖ ያልፋል። ሁሉም ትውልድ የየዘመኑን ጥያቄ ይጠይቃል። ከዘመኑ ቀድሞ የጠየቀ ደግሞ እብድ ይባላል። ጥሩነቱን ጤነኞቹ ሁሉ ሲያልፉና ሲረሱ እርሱ በታሪክ ስሙ ይወሳል። እያንዳንዱ ትውልድ ከቀደመው ትውልድ በወረሰው መሰረት የራሱንም ጥበብ ጨምሮ ለማንነት ጥያቄው መልስ ይሰጣል። (ደረጀ ፀጋዬ፣ የኢ-አማኒው ኑዛዜ)

ከሞት በኂላ ህይወት አለ ማለት መፍትሔ አይደለም ከእውነት መደበቂያ ነው።እስኪ ተንሳኤ ሙታን ይኑር እንዴት ነው ከሞት የምንነሳው? ምንስ መስለን ነው የምንነሳው? "አበው ሊቃውንት ከትንሣኤ በኂላ የሚኖረን አካል ከመሞታችን በፊት ከነበረን አካል ጋር አንድ እንደሆነ ተናግረዋል። ልዩነቱ የማይሞትና የማይበሰብስ ወደመሆን መለወጡ ብቻ ነው። ይህ መለወጥ የማይሆን ከሆነ ትንሣኤ ረብ የሌለው ይሆናል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የሞተው አካልና የሚነሣው አካል ተመሣሣይ ዘር ያላቸው መሆኑን ተናግሯል። ‹‹ይህን ቤተመቅደስ (ሰውነቱን) አፍርሱት በሦስት ቀንም አነሳዋለሁ›› ዮሐ 2÷19 የሚለው የኢየሱስ ክርስቶስ ቃልም የሚያመለክተው ነገር ቢኖር ሁለቱም የሞተውም ሆነ የተነሳ አካል ተመሣሣይ ዘር እንዳላቸው ነው።"

Created in Master PDF Editor

(ፍኖተ ብርሃን፣ 10ኛ ዕትም 2009 ዓ.ም) በዚህ ይሳብ ካየነው ሙታን ከመሞታቸው በፊት በነበራቸው ስብዕና፣ ቁመና እና አስተሳሰብ ይመለሳሉ። ለምን ቢባል ይህ አስተሳሰብ ሞትን እንደ እንቅልፍ ስለሚቆጥረው። ‹‹እነሆ አንድ ምስጢር እነግራችኋለሁ ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበት ዓይን እንለወጣለን። መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሳሉ፤ እኛም እንለወጣለን።›› 1ቆሮ 15÷51-52። እንቅልፍ በሰው ተፈጥሮአዊ ባህሪ ለውጥ አይፈጥርም ማለት አንድ ሰው ከእንቅልፍ የሚነቃው ከእንቅልፍ በፊት ከነበረው ማንነቱ ጋር ነው። ይህን መሰል ተንሳኤ ባይኖር የሚወዱ አማኞች አይጠፉም ራሳቸውን በተለይም ቁመናቸውን የማይወዱ አሉና። ይህ መሆነ ግድ ከሆነ የውበት መጠበቂያ ቁሳቁስ ጉዳይ ሊታሰብበት ይገባል።

የእምነት አብዮተኞችና መሲሆች የጨመሩልን ቢኖር በየትም በኩል ይሆን በደስታ የሚኖርበት የማያልቅ ዘመን ከፊታችን እንዳለ ነው። “ዘላለማዊ ሕይወት፣ በቀላሉ ከችግርና ከደስታ ጋር ቀጣይ አይደለም። አሁን ያለው ሕይወት አስከፊ ፍፃሜ፣ ገሀነም ከመሆኑ ጋር ሲነፃፀር፣ ዘላለማዊ ሕይወት ከሁሉ የተሻለ ነው፤ ኃጢአትና ሀዘን ሁሉ የማይኖሩበት፣ ከሁሉ የላቀና ሁሌ የሚጨምር ደስታ ያለበት። በዚህ በወደቀ ተፈጥሮ ውስጥ ያሉ ክፉና ጎጂ ነገሮች ሁሉ ይወገዳሉ።” (ጆን ፓይፐር፣ ስለ ኢየሱስ የሚጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው)።አብዮተኞቹ በተለያየ መንገድ የሰበኩትን ተንሳኤ ሙታን ሳይንቲስቶቹ እና ፈላስፎቹ ውድቅ አደረጉት። እንዴት ብለው፦

> “ስጋ ከሞት በኋላ የእሱ አምሳያ የሆነ መንፈስ ይኖራል ብንል፣ ስጋ የሞተ ቀን አምሳያውም ሊሞት ይገባል። እንበልና ልቡን በጥይት ተመትቶ የሞተ ሰው የእሱ ስጋ አምሳያ በሆነውም መንፈሱ ውስጥ ልቡ ሊኖር አይገባምን አለበለዚያማ ምኑን ተመሳስሎት። አንድ ሰው ሞቶ፣ ሥጋው በስብሶና በትል ተበልቶ ካበቃ በኋላ እየተገጣጠመ ትንሣኤው የሚሆነው ስጋው ከየት መጥቶ ነው ይላሉ። ጆን ፍሊው ሲናገር ‹‹አንድ ሰው ሞቶ፣ በስብሶ፣ ማንነቱ ከፈራረሰና ከጠፋ በኋላ በትንሣኤ ይነሣል ብንል እንኳን ተመልሶ ሲገጣጠም እንደመጀመሪያው ኦሪጅናሊቲውን ጠብቆ አይመለስም፤ ትንሳኤ እውነት እንኳን ቢሆን ተመሣሣዩን (replica) እንጂ እራሱን አይፈጥርም›› በማለት አንድ ምሳሌ ያስቀምጥልናል፡- ‹‹አንድ ሰው በአንበሳ ተበልቶ ሞተ። የዚህ ሰው ስጋና አጥንት በአንበሳ ጥርስ ከደቀቀ በኋላ ሆዱ ውስጥ ገብቶ ወደ አንበሳው ስጋና ደም ወይም ወደ ሰገራው ተቀየረ። ይኸ ሰው በትንሣኤ ስጋውም ሆነ ደሙ አይገኝምና ሊነሣ አይችልም ማለት ነው፤ ካልሆነ ደግሞ ተመሳሳዩ ይፈጠራል፤ ለትንሣኤ ብለህ አዲስ ሰው ከፈጠረክ ደግሞ ተመሳሳዩ የጥንቱን ሰውነቱን አልሰጠኸውምና በትንሣኤ በራሱ የጥንቱን ሰውነቱን አጠፋኸውም ማለት አይደል?›› በማለት ተንሳኤ ሙታንን ይሳለቅበታል።” (ጥበብ ቅጽ አንድ፣ 2009፣ 127)

Created in Master PDF Editor

የፈላስፎቹን ጥያቄ እናንተን ልጠይቃችሁ ነብያት እናዳስተማሯችሁ፣ ሃዋርያት እንደሰበኳችሁ በትንሳኤ ሙታን ታምናላችሁ ለመሆኑ አንድ ሽማግሌ ሲሞት በዘላለማዊነት የሚኖረው እንደሕፃን ዘመኑ፣ እንደወጣትነቱ፣ ወይንስ እንደሽማግሌነቱ ሆኖ ይህን? ይህ ጥንታዊ የፍልስፍና ጥያቄ እንደሆነ ሀይለ ጊዮርጊስ ማሞ ነግሮናል፣ በተጨማሪም ስታንሌ የተባለ ፈላስፋ የተናገረውን ያስታውሰናል ‹‹ከነፍሴ ይልቅ ስጋዬ ዘላለማዊ ቢሆን እመርጣለሁ›› ስታንሌ ትክክል አይመስላችሁም? ሀይለ ጊዮርጊስ ማሞ ለየት ያለ ተንሳኤ እናዳላቸው በሚታመነው ወደ ህንድ ይወስደንና በህንድ ስለ ነፍስ ዙርያ የተደረገውን ምርምር ይተርክላናል ጥናቱ የኢያን ስቴቨንሰን ነው፡፡

> *ፓራሳይኮሎጂስቶቹ ዳግም ሌላ ሰው ወይም ፍጡር ሆኖ መፈጠርን (reincarnation) በሚያምኑት በሕንዶች ዘንድ ደግሞ ሰፊ ጥናትና ምርምር እስከዛሬ ማድረጋቸውን ይናገራሉ፡፡ ለአመታት በህንድ ኑሮውን መስርቶ ይህንኑ ምርምር በስፋትና በጥልቀት ሲያደረግ የኖረው ኢያን ስቴቨንሰን በሺዎች በሚቆጠሩና ዕድሜያቸው ከ2-4 ዓመት በሚደርሱ ህፃናት ላይ የቀድሞ ህይወታቸው ወይም ሞታቸው ምን ይመስል እንደነበር ለማወቅ ባደረገው ምርምር ድካሙ ሁሉ ከንቱ መቅረቱን ይናገራል፡፡ የአንዱ ነፍስ ከሞት በኋላ በሌላው ስጋ ውስጥ ከገባች ስለቀድሞ ሕይወቷ በሚገባ ልታውቅ እንደሚገባት የሚያሰምረው ስቴቨንሰን የነፍስ ዳግሚያ የመምጣቷ ‹‹ጨዋታ›› እንደ ጊዜ ማሳለፊያ የሚታይ እንጅ በአግባቡ ሲመረመር ቁም ነገር እንደማይገኝበት የዓመታት ምርምሩን ዋቢ አድርጎ ይነግረናል፡፡*(ጥበብ ቅጽ አንድ፣ 2009፣ 132)
>
> ፈላስፎቹም ሆኑ ሳይኮሎጅስቶቹ ማሰብን ከአእምሮ ለይተን ማየት እንደማንችል ይነግሩናል፡፡ ማሰብ የሚሞተው ማሰቢያው ሲጠፋ ነው፤ ማሰቢያው የጠፋ ዕለት የምናስበው ነገር ሁሉ (ዘላለማዊነትን ጨምሮ) የዚያን ቀን የበቃል ማለት ነው፡፡ ከሞት በኋላ ዘላለማዊነት የሚለው እሳቤም ቢሆን አእምሮ ስራውን ያቆመ ቀን የመጨረሻው ይሆናል፡፡እኛ የአስተሳሰባችን ውጤት ስንሆን አስተሳሰባችን ደግሞ የአእምሮአችን ውጤት ነው፤ ስለዚህም በተዘዋዋሪ እኛ የአእምሮአችን ውጤት ነን ማለት ይሆናል፡፡ ለዚህ ቀላሉ ማሳያ ደግሞ በአእምሮህ ማሰብ ስታቆም የምትሆነውን መመልከት ትችላለህ፡፡ እንግዲህ ከብዙው ሀሳብህ ውስጥ አንዱ ደግሞ ዘላለማዊነት ነው፡፡ በተዘዋዋሪ ዘላለማዊነት የአእምሮህ ውጤትና አእምሮህ ሞቶ ሲበሰብስ አብሮ የሚበሰብስ አስተሳሰብ ይሆናል ማለት ነው፡፡ (ጥበብ ቅጽ አንድ፣ 2009፣ 132-133)

Created in Master PDF Editor

የክርስቶስ እና የሌሎች እምነቶች ነብያት እና ሀዋርያት የሰጡን ተስፋ ከልባቻው የሚያስቡትን እንጅ ከፈጣሪ የተቀበሉትን አይደለም፣ፈጣሪ አይዋሽምና። ሲጀምር እነሱን ማን የምስራች ነጋሪ አደረጋቸው። ብሩህ አለምነህ የታላቁን ፈላስፋ የዘርዓያዕቆብን ፍልስፍና መሰረታዊ ሃሳቦች በተነተነበት መጽሃፉ መልዕክተኞችን አስመልክቶ እንዲህ ብሏል። “ማንም ሰው ከመሬት ተነስቶ የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ሊሆን አይችልም፤ እግዚአብሔር በግል የሚመርጠው፣ በግል የሚያናግረው፣ በግል ራሱን የሚገልጥለት ሰው የለም። እግዚአብሔር ለአንዱ፣ የሚገልጥ ለሌላው ደግሞ የሚሰውር አይደለም። እግዚአብሔር ማስተዋልና መመርመር ለሚፈልግ ሰው ሁሉ እኩል ተደራሽ ነው። አንዱ ከሌላው ተለይቶ የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ሊሆን አይችልም።” (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 70)

እናም ስለዘለአለማዊ ህይወት የሰበኩን እንደኛው ሰው ናቸው። ከሞት ተመልሶ መቃብር ከፍቶ የሰበከን የለምና ያለማመን መብት አለን። መብት የማይገባቸው አማልዕክት ግን የራሳቸው ጉዳይ። ያየነውን የማመን የሰማነውን የመጠራጠር ልቦና አለን፣ ቢያንስ ቢያንስ እንመረምራለን። ስለዚህ በዘለአለማዊ ህይወት ዙርያ እና ይህን ተከትሎ የሚመጡ ድንቅ የምስራቾች ቅዠቶች ሳይሆኑ አይቀሩም፣ ነውም።

በነገራችን ላይ እንዳትገረሙ በዘለአለማዊ ህይወት የሚያምኑ ኤቲስቶች አሉ እኔን ጨምሮ። ግን እምነቱ በገነት ወይም በሲኦል እንደሚሆነው አይደለም። የእኔን አመለካከት ላጋራችሁ። ሞት ግድ ነው እሞታለሁ። ደስ የሚለው እኔ ስሞት ስጋየን የሚመገቡ እፅዋት፣ እንስሳትና ነፍሳት አሉ። እነሱ ሲሞቱ ሌሎች እፅዋት፣ እንስሳትና ነፍሳት እየበሏቸው ስንሰለቱ ይቀጥላል። በኋላኛው ዘመን ነገሮች ወደ ጥፋት ሲቀየሩ የእኛም ቅሬት በህዋው ውስጥ ይዋኛል። ጨረቃዎች በጨረቃዎች ላይ፣ ፀሐዮች በፀሐዮች ላይ፣ ፕላኔቶች በፕላኔቶች፣ ስርዓተ ፀሐዮች በስርዓተ ፀሐዮች ላይ፣ ጋላክሲዋች በጋላክሲዎች ላይ ይደረመሳሉ። ያኔ የእኛም ቅሬታ በዚያ አለ። በመጨረሻው የመደርመስ ጊዜ ብርሃናት ጠፍተው ጨለማ ሲነገስ እኛ በዚያ አለን። ከዚያም አልፎ ቁስ አካል ወደ ሀይል ሲቀየር በሀይሉ ውስጥ አለን። ከዚያም ሌላኛው ቢግ ባንግ ሲፈነዳ በዚያም አለን። ዘለአለማዊነት ይሉታል ይሄ ነው። በእርግጥ ደስ አይልም ግን ሊሆን ይችላል። የወቅቱ ምርምር የሚያሳየው ይህን ነው።

የእማኞች ዘለአለማዊነት ግን ከዚህ ይለያል፣ እጅግ ደስ የሚል ስፍራ ነው። እንደየሰውና እንደየእምነቱ ይለያያል እንጂ የሚደንቅ የአትክልት ቦታና ሪዞርት ነው። በዚህ ሪዞርት የተመረጡት ከተመረጠው ጋር ለዘለአለም ይኖራሉ።

Created in Master PDF Editor

ይህ የአማኞች ዘለአለማዊነት በመሬት ለኩንትራትና ለዝግጅት በኖሩበት ዘመን ላሳለፉት መከራ፣ ለአምላካቸውና ለእምነታቸው ለከፈሉት ዋጋ የሚስማማ የእረፍት ቦታ ነው፡፡ ዝም ብሎ ማረፍ ነው፡፡ የማያልቅ እረፍት፡፡ አንድ ሰባኪ በዚያ ቢሮ የለም፣ ታክሲ ተራ የለም፣ ዳቦ ተራ የለም፣ ዘይትና ስኳር ተራ የለም፣ ፍ/ቤት ቀጠሮ የለም ወ.ዘ.ተ ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡ ግን ያለ ተራ መኖር አይሰለችም ይሆን?

የዘለአለማዊ ህይወትን በተመለከተ በአማኞችና በማያምኑት ዘንድ በጉጉት የሚጠበቅ ዜና አለ፡፡ የሚጠበቀው ዜና በBBC "ከዛሬ ጀምሮ ሞት ሙቷል" የሚለው ዜና ነው፡፡ ይህ ዜና የሚያነበው ጋዜጠኛ ሊሆን ይችላል ስራው የሚሰሩት ግን በላብራቶሪ ውስጥ ሞትን ለመግደል የሚታትሩት ሳይንቲስቶች ናቸው፡፡ ባይሳካላቸው ደስ ይለኛል መሬት ላይ በተፈጥሮአዊ መንገድ ኑረን ብንሞት እመርጣለሁ፡፡ ሞትን በተለይም ሲኦል እገባይሆን ለሚሉትና የንስሃ ጊዜ ለሚያስፈልጋቸው ግን ዜናው ተጠባቂ ነው፡፡ ሰዎች አይሳካም ብለው ሊያስቡ ይችላሉ ግን በሳይንስ ብዙ ተችሏል ምን ችግር አለው በሽታና እርጅና አምጭ መንስኤዎችን መግደል ነው፡፡ ዋጋው ውድ የሚሆን ይመስለኛል ወይም ደግሞ በክትባት መልክ ህፃናት እንደተወለዱ ሊሰጥ ይችላል ወይ ደግሞ መሞት እስከምንፈልግ የምንወስደው ሊሆን ይችላል፡፡ ያም ይሁን ይህ የዘረፉ ሙህራን ግን 'Singularity iscoming, the time is now' እያሉ ነው፡፡

10. **የክፍተት አምላክ (God of the gap) ውድቀት**

ቀዳሚዋ አምላክ በአሁኑ አጠራር ጣዖት ፀሐይ ነበረች ይባላል፡፡ ከዚያ ጨረቃ በኋላም የተለያዩ ወቅቶችን የሚያፈራርቁ አማልክት፤ ልደትን፣ ሞትን፣ ተፈጥሮዊ አደጋወችን እና ሌሎች ነገሮችን የሚቆጣጠሩ ተጨማሪ አማልክት ተፈጠሩ፡፡ ከዚናም ሰዎች የአማልክቶቻቸውን ቁጥር ወደ አንድ በመቀነስ ወይም የድሮውን ላለመተው አንድም ሦስትም በማለት ተጨማሪ አማልዕክትን ፈጠሩ፡፡ ከአዝማናት በኃላ ሚስጥራዊ ክስተቶች በሳይንሳዊ መንገድ መተንተን ተጀመረ፡፡ አሁን ፀሐይ አምላክእንዳልሆነች ታውቋል፡፡ ወቅቶች የሚፈራረቁት መሬት ከጨረቃ እና ከፀሀይጋር ባላት እንቅስቃሴመሆኑ ተደረሰበት፡፡መራባትንበ ተመለከተ ሥነ-ሕይወት ያብራራል ወ.ዘ.ተ፡፡ሌሎችተፈጠሮአዊ ሚስጥሮች ያለ ሃይማኖት ጣልቃ ገብነት መረዳት ይቻላል፡፡ በቅረቡም ሃይማኖታዊባለሥልጣናት ሳይንሳዊ ምርምሮችን መቀበል ጀምረዋል፡፡ ለምሳሌ ፖፕጆን ፓውል ዳግማዊበ 1996 'እውነት ከእውነት'ጋር አይቃረንም በማለት ሳይንቲስቶችን ስታድን የኖረችው ካቶሊክ ሳይንሳዊ ምርምሮችን መቀበሏን ይፋአድርጋለች፡፡እንደ ብሩህ አባባል "ሀይማኖት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አስፈላጊ ሆኖ የመጣው ተጨባጭ በሆነው ሰውና ረቂቅ በሆነው እግዚአብሔር መካከል ያለውን ገደል ለመሙላት ነው፡፡ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው የታዋቂነት ክፍተት ለመድፈን፡፡" (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 70) ብሩህ

Created in Master PDF Editor

አንተ እንዳልከው ሀይማኖት አንድ ገደል ለመሙላት ሲጥር ብዙ ገደል ይፈጥራል (ገድል አይደለም)፡፡ ምክንያቱም ሀይማኖት እግዚአብሔርን ለሰው የመግለጥ የሚሞክርበት አካሄድ አሳማኝ አይደለም፡፡ ቃል ቃል ነው ስጋ አድርጎ ማሳየት የሚችል የለም፡፡ መለኮት መንፈስ ነው የሚዳሰስ አካል አድርጎ ማሳየት የሚችል የለም፡፡ ኢየሱስን ተቀበሉት የሚሉ ሀይማኖቶች እንጅ ኢየሱስ ወደ ማንም ቤት ሂዶ ተቀበሉኝ አላለም፡፡ ቢልም እንኳ ሁሉንም እንጅ ቅዱስ ጳውሎስን ብቻ አይደለም፡፡ በመገለጥ ጉዳይ የቁራንምህራን እንቅጩን ይነግሩናል፡፡ አላህ በዚህኛው አለም ለማንም አይታይም፣ በወዲያኛው ዓለም አማኞች ሲያዩትም በእይታ አያካልሉትም፤ አምሳያም፥ ልጅም የለውም፤ ስለዚህ ስለርሱ ማወቅ የምንችልበት ብቸኛ መንገድ የቁዕራን ገለጻ ነው፡፡

ይልቅስ ይህን የክፍተት አምላክ (God of the gap) የሚለውን ፅንሰ ሃሰብ በእምነት ሳይሆን በምርምር መሙላት አለብን፡፡ አሁን በሳይንሳዊ እውቀት እና በቀሪዎቹ ያልተደረሰባቸው ምሥጢሮች መካከል ያለው ክፍተት ጠባብ ሆኗል፡፡ ድንቅ በሆነ ሁኔታ ባለፈው መቶ ዓመታት ብቻ ሳይንስ አስገራሚ ቴክኖሎጅወችን አስገኝቷል፡፡ዘመናዊው ሳይንስ፣ ሰፊ ዕውቀትን በመሰብሰብ ብቻ ሳይሆን ይህን ዕውቀት በሥራ ላይ በማዋል ያለተወዳዳሪ የሰውን ልጅ ህይወት በማሻሻል ላይ ይገኛል፡፡ በሽተኞች መታከማቸው፣ የእርሻ ምርት በሄክታር እምርታ ማስገኘት፣ የመገናኛ ብዙሃን መፈጠርና ማደግ፣ ወዘተ…እነዚህ ሁሉ የዚህን ዕውቅት ሥኬት የሚያሳዩ ናቸው፡፡ አዎን አሁንም ያልተፈቱ ምስጢሮችአሉ፡፡ ያም ቢሆን አምላክን እስከ ማምለክ የሚደርሱ አይደሉም ምክንያቱም ጥያቄዎቹ መሰረታዊ ሳይሆኑ የቅንጦት ጥያቄዎች ናቸው፡፡

ıı. አጉል ምኞትና የሀብት ብክነት

ማጅላን እንዲህ ብሎ ነበር፦ “The church says the earth is flat, but I know that it is round, for I have seen the shadow on the moon, and I have more faith in a shadow than in the church.”ሀይማኖቶች የተመሰረቱት በአጉል፣ በማይጨበጥና በቅዠት ፍልስፍና ነው፡፡ ሀይማኖቶች የሚሰብኩት ሳያዩ የሚያምኑ ቅዱሳን ናቸው ብለው ነው፡፡ ሳያዩ ማመን ቅዠት ነው፣ ሳያዩ ማመን እብደት ነው፣ ሳያዩ ማመን ሞኝነት ነው፣ ሳያዩ ማመን አጉል ምኞት ነው፡፡ አጉል ምኞት ተስፋ አይደለም ይልቅስ ቅዠት ነው፡፡ ይቅርታ ይደረግልኝና ብዙ ጊዜ እንዲህ እላለሁ **ሀይማኖት በጀምላ የማበድ ስርዓት ነው፡፡** አይንን ጨፍኖ ማመን፣ በቅጽበት መፈወስ፣ በስሜት መገንደስ፣ በመንፈስ መደነስ፣ አሜን፣ አሜን፣ አሜን፣ አሜን፣ አሜን፣ ማለት፡፡አትበሳጩብኝ በደርዘን ከሚቆጠሩት የዚህ ዘመን ነብያት የቴሌቭዥን ስርጭቶችና በማህበራዊ ሚድያ የሚለቀቁትን የፈውስ ፕሮግራሞች ተመልከቱ፣

Created in Master PDF Editor

በተለይ የእዩ ጩፋን እና የግርማ ወንድሙን:: በእውነት እየሱስ ክርስቶስ የመጣ ይመስላችኋል፣ በ100 ሜትር እርቀት ጌታን ታዩታላችሁ፣ ለነብያቱ የዘነበው መንፈስ ቅዱስ ለናንተም ሊያካፋ ይችላል ዋናው ነገር ያለ ጥርጥር በመጮህ አሜን፣ አሜን፣ አሜን፣ አሜን፣ አሜን ማለት ነው:: ነገሩን በጥርጣሬ ካያችሁት ንግግሮቻቸው፣ ትንቢቶቻቸው፣ ፈውሶቻቸው ከንቱ ምኞቶች ናቸው:: በእነዚህ ፕሮግራሞች እድሜ ልክህን ድነሀል፣ ተፈውሰሃል፣ ሀዘንህ ተሸሯል የተባለ ሰው ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ህክምና ሲከታተል ብታገኙት እንዳትገረሙ የዳነ የመሰለው በምኞት ነው፣ ያዳኑትም በቅዠት መንፈስ ነው:: ጎበዝ ከመጋረጃው ጀርባ ምን እየተሰራ እንደሆነ ብንጠረጥርስ:: የሃይማኖቶች ትልቁ ፈተና መጠራጠር ነው፣ ለዚህም ነው መጠራጠርን ታላቅ ሀጥያት የሚሉት:: Lemuel K. Washburn ምን ነበር ያለው "When a man is required to believe certain doctrines, he is not free to think. A creed is to keep the mind from inquiry. Questions lead to doubt, and doubt is the death of faith."

የሥነ ልቦና ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሰዎች የሚወዱት ምኞት እውነት እነዲሆን ይፈልጋሉ::የሰው ልጅ ደህንነቱ የተጠበቀ ዘላለምአዊ መሆን ይፈልጋል:: ከዚህም ሲያልፍ በሞት ከተለዩት ቤተሰቦቹጋር እንደገና መቀለቀል ይመኛል:: ከጠፉ ወዳጆቻቸው ጋር ዳግመኛ ለመገናኘት ይጓጓሉ:: ለዚህም ነው የአብርሀም አምላክ ኃያል፣ አዳኝ፣ ጥበበኛ፣ አፍቃሪ እና አባት ሆኖ የመጣው::

እንዲህ ያሉት እምነቶች ሌላ ምድር ሌላ ሰማይ አለ ማለታቸው የሰውን ልጅ ካለበት ጭንቀት፣ ፍርሃት፣ ብቸኛነት፣ ተስፋ መቁረጥ እና በአጠቃላይ ከህይወት ዋጋ ማጣት እፎይ እንዲል አድርገውታል::የተለያየ እምነት አራማጆች ከዚህ አለም ሥቃይእፎይታለማግኘትመንግስት ሰማያትን ተስፋያደርጋሉ:: ግን ምን ያደርጋል ህልም እንደፈቺ ነው:: ሀይለ ጊዮርጊስ ማሞ እንደነገረን ፈላስፋው ኮርሊስ ላሞንት ‹‹እንወለድ ዘንድ አልጠየቅንም፤ ለመሞትም እንዲሁ አንጠይቅም:: ወደ መኖር ሳንጠይቅ እንደመጣን እንዲሁ ደግሞ ወደሞት እንሄዳለን:: ከዚያ በኋላ የሚጠበቅብንም አንዳች ነገር አይኖርም::" ብሏል:: (ጥበብ ቅጽ አንድ፣ 2009፣ 133) ብሩህ አለምነህም እምንቶች ስለፈጠሩት ባዶ ተስፋ እንዲህ ይላል "እኔ የምድር ቆሻሻ (ትቢያ) ነኝ የሚል ምድራዊ ህይወትን የኮንትራት አለም እያለ የሚጥላላ ነፍሳችን እንድትድን፣ ስጋችን እንጣላት ብሎ የሚያምን የሰው ልጅ እንዲፈጠር አድርጓል::"በመቀጠልም ከፍሬድሪክ ኒቸ ሃሳብ ይዋስና"በዚህም ምክንያት ደስታና ጸሎትን የምትጠየፍ ፕላኔት፣ ከስሜቱ የተገነጠለና ከተፈጥሮ ስርዓቱም ያፈነገጠ፣ ከማህበራዊ ህይወትም ተገልሎ በብቸኝነት የሚያሰቃይ፣ ምድራዊ ህይወትን አምርሮ የሚጠላ፣ ከስቃይ ውስጥም ደስታንና ተስፋን የሚፈልግ ከንቱ የሆነ ማህበረሰብንና አለምን ፈጥረናል ይላል::"ይላል:: (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 45) ሰው

Created in Master PDF Editor

በአለም ስልረካ ከአለም ርቆ መሄድን መረጠ ይህም ከአለም የመራቅ ህይወት ምንኩስና ይባላል። ከግብፅ ከወረስነው መጥፎ ባህል እንደ ምንኩስና የሚሆን የለም። ለኛ ኢትዮጵያዊያን ምንኩስና የእድሜ ጉዳይ ካልሆነ የቻሉት በረሃ ገብተው (ሸፍተው) ያልቻሉት በቤታቸው የሚፈፅሙት ባህል ነው። ሰው ስለምንኩስና ሲያስብ ድግ ደጉን ነው። እውነቱን ስንመረምር ግን አሳዛኝ ድምዳሜ እንደርሳለን። እስኪ የምንኩስናን ህይወት የሆድ ዕቃ ከመረመሩት አንዱ ብሩህ ያልውን ላካፍላችሁ። ብሩህ ገናናዋ አክሱም በአጉል ምኞት እንዴት እንደሞተች ሲያስረዳ፦

> "አክሱም የሞተችው በውጭ ወረራ ሳይሆን ከውስጥ 'ታንቃ' ነው በጠባቡ የብህትውና ህይወት በምንኩስና ባህል። በምንኩስና ባህል የተነሳ የህብረተሰቡ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ህይወት የተመሰቃቀለ ሆነ። እናትና አባቱን አየተወ የሚመነኩሰው ወጣት ጨመረ፣አባወራ ልጆቹንና ሚስቱን እየተወ፣ እናት ልጆቿንና ባሏን እየበተነች መመንኮስ በጣም የተለመደ ሆነ። አፄ አለ ገበዝ(የአፄ ገ/መስቀል ልጅ) ያደረገውም ይሄንኑ ነው፤ ስልጣኑን ለማንም ሳያወርስ፣ሀገሪቷንና ህዝቡን የትም በትኖ ከሚስቱ በስተቀር ለማንም ሳይናገር መነነ። ወዲያውም የአርስበርስ ጦርነትም ተነሳ። ምንኩስና ለግብረሰዶማዊነት መነሻ ምክንያት መሆኑንም እንዳንረሳ።" (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 193-196)

ይህን ሁሉ ተንኮል የምያስተምሩት ግብፃዊናን ነበሩ። ከግብፅ የመጡ ጳጳሳት ለሃገራቸው የዋሉት ውለታ የኢትዮጵያዊያን ህዝብ እስከ ነገስታት ድርስበማምንኮስ በአባይ ለይ መንገስ ነው ተሳክቶላቸዋል።ህዝቡን እንዳይወልድ አመንኩሰው እራሳቸው ግን መሸት ሲል ቆባቸውን አውልቀው ወደ እቁባቶቻቸው ይሄዳሉ። ህዝቡን እስከነገስታቱ የአለምን ጣዕም አስረስተውና አጉል ስርዓት ዘርግተው ራሳቸው ግን የሉበትም። ሀገሪቱ እርስ በእርስ እንድትጋጭ፣ ንጉስ በንጉስ ላይ እንዲነሳ ሲጥሩ ነበር፣ ህዝብና መንግስት የሚሉትን የማይሰሚቸው ከሆነ እንደሚያወግዟቸው ያስፈራራሉ። እስከ ዛሬ ድረስ ጭምተኛ፣ NO ማለትን የምንፈራ፣ ምድራዊ ህይወትን የምንጠየፍ ያደረጉን ከግብፅ የመጡ ጳጳሳትና 9ኙ ቅዱሳን ናቸው። ብሩህ ይቀጥላል፦

> ነገስታቱ ከስልጣን ገናናነት ይልቅ ግላዊ ነፍሳቸውን ለማዳን ያደረጉት ሩጫ፣ ለህዘቡ ትልቅ መልዕክት ነበረው። የምንኩስና ህይወት ከእምነት አልፎ ለህብረተሰቡ ዓለምን መመልከቻ መነፅር ለመሆን የበቃው ነገስታቱ ከዓለማዊ ድሎት ይልቅ የምንኩስና ህይወትን ሲመርጡ መታየታቸው ነው። በዚህም ምክንያት ምንኩስና ከእምነት ወደ ባህልነት ሰፋ። ምንኩስና የተመረጡ ጥቂቶች የሚኖሩበት እምነት ከመሆን አልፎ ህዘቡ ገዳም መግባት ሳያስፈልገው በየዕለቱ የሚኖረው ህይወት ሆነ።በዚህም ዓለምን የሚጠየፍ፣ ስጋዊ ህይወትን

Created in Master PDF Editor

> የሚያንቋሽሽ ህብረተሰብ ሁነ፡፡ እንኳን የስራ መሳሪያዎችን ሊያሻሽል ይቅርና በአክሱማዊነት ዘመን እንኳ የነበሩትን ጥበቦችን የእጅ ሙያዎች ማስቀጠል የማይችል ማህበረሰብ ተፈጠረ፡፡ ጭራሽ ከዚህ በተቃራኒ ለዓለማዊ ብልፅግና መጣር እንደ ከንቱ ድካም ተቆጠረ፡፡ ግንበኝነት፣ አናጢነት፣ቀጥቃጭነትና ሌሎችም እጅ ሙያዎች ከመከበሪያነት ወደ መሰደቢያነት ተቀየሩ፡፡ (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 193)

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ለእኔ፣ ለብሩህ እና ለአለም የሚያጠግብ ፍልስፍናን ያስተማሩት ዘረ-ያዕቆብ እና ወ/ህይወት ደመና ስለሚያስጨብጠው ምንኩስና የሚሉትን እንስማ ብሩህ አለምነህ እንደተነተነው፦

> ምንኩስናን ዘርዓያዕቆብ የሰውን ፍጥረትና የፈጣሪን ጥበብ የሚያጠፋ ሲለው ወልደ ህይወት ደግሞ ምንኩስናን ከጠወለገና ከደረቀ እንጨት ከማይለመልምና ከማያፈራ እንጨት ጋር በማመሳሰል ምዑት ይለዋል፡፡ መነኩሴዎችን ደግሞ ዘርዓያዕቆብ ዋሾዎች (እግዜር ለፈጠረው የተፈጥሮ ህግ የማይታመኑ)፣ በክፉ በሽታና ተፈጥሯቸው ባልሆነ በሌላም የፍትወት አበሳ (በግብረሰዶማዊነት) ዝሙት ወጥመድ የሚጠምዱ ሲላቸው ወልደ ህይወት ደግሞ የሞቱ ከንቱዎች፣ ዋሾዎች፣ በሚዛን የቀለሉ፣ የፈጣሪ ካህዲዎች፣ በስጋዊ ፍትዎታቸው፣ ሁልጊዜ የሚቃጠሉ፣ ሽፍቶች የፈጣሪን ስርዓት አፍራሾች፣ እንስሳትን የመሰሉ፣ አረ እንዲያውም ከነሱም የባሱ፡፡ ይላቸዋል፡፡ ወልደ ህይወት ምንኩስናን የሚያስበልጠውን የሰው አመለካከት ወስላታ የሰው (አባይ፣ አሳሳች) ሚዛን ይለዋል፡፡ በጣም የሚገርመው ነገር ዘርዓያዕቆብ ወልደ ህይወት በእንደዚህ አይነት ጠንካራ ቃለትና ስድብ የተቹትን የምንኩስና ህይወት ክርስትያናዊት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ወደ መላዕክታን ከፍ የሚያደረግ ህይወት በማለት ከፍተኛ ከበሬታን መስጠቷ ነው፡፡ (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 36-37፣ ሐተታ ዘረያቆብ ምዕ 5-7፣ ሐተታ ወልደ ህይወት ምዕ 13 እና 24)

ታድያ በእግዚአብሔር በማመኔ የማጣው ነገር የለም ይሚባለው ለምንድን ነው? በአለም ውድ የሚባሉት ሀብቶች ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ ናቸው፡፡ ሰባኪዎች እንደሚሉት እግዚአብሔር ባይኖር እንኳ በማመናችን የሚቀርብን ነገር የለም ነው፡፡ አማኞችም ይህን አመክንዮ ደጋግመው ይናገሩታል፡፡ ነገሩን ከመረመርነው ግን ውድ ጊዜአችንን፣ ጉልታችንን እና ገንዘባችንን ለአጉል ህልም አባክነን ነው፡፡ የእግዚአብሔር ባይሆኖር ምንም አይቀረብንም ማለት ሞኝነት ነው፡፡ በአለም ከፍተኛ የሚባል ገንዘብ በእምነት ተቋማት ይንቀሳቀሳል፡፡ ገንዘቡ የመጣው ገነትን መውረስ ከሚፈልጉት ሰማያዊ ቤት ለመስራት ከሚጣደፉት ምዕመናን ነው፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ያላቸውን ሁሉ ሽጠው የሚከተሉም አሉ ምንኩስና እንደምሳሌ፡፡ እውነት ለመናገር

Created in Master PDF Editor

የሀይማኖት ተቋማት ከመንግስታት ያልተናነሰ ገንዘብና ሀይል አላቸው፡፡ ይህ ገንዘብ የተሰበሰበው በአብዛኛው ከድሀው ነው፡፡ በእርግጥ የሀይማኖት ተቋማት የሚሰበሰቡትን ረብጣ ገንዘብ ለበጎ ነገር ያውሉታል ተብሎ ይገመታል ሙስናው፣ ስርቆቱና ማጭበርበሩ እንዳለ ሆኖ፡፡ ስለዚህ ገንዘቡ ሙሉ በሙሉ ባክኗል ለማለት ይከብዳል ለምን ቢባል አንደኛ ምርጥ ህንፃዎች ተሰርቶበታል፣ ሁለተኛ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ የስራ እድል ተፈጥሮበታል፣ ሶስተኛ በቅንነትም ይሁን ለታይታ ለድሆች እገዛ ይደረጋል፡፡ እኔ የሚያሳዝነኝ ውብ ህንፃ መሰራቱ፣ የስራ እድል መፈጠሩና ለድሆች ድጋፍ መዋሉ አይደለም በመሀል የሚባክነው ነው፡፡ ጭራሽ ገንዘብ ሰብሳቢዎችና አሰባሳቢዎች መላዕእክት የሆኑ ይመስል ኦዲት አይደርጉም፡፡ ይህ የሚያሳፍር ልምድ ነው፡፡ ቅንነት የሚያረጋግጠው በኦዲት ነው እንጅ በለበስነው ግን ባልተዋሀደን መንፈሳዊ ህልም አይደለም፡፡ ኦዲት ባይደረጉም በሹክሹክታ እንኳ እንደምንሰማው የሌብነት ደረጃ ቢወጣ የቤተ እምነት አገልጋዮችን የሚቀድማቸው እንደሌለ ይገመታል፡፡ በሀገራችን እንኳ የሚያገለግሉትን ታቦት ሰርቀው የሚሸጡ ካህናት አይጠፉም፡፡ የቅርሱ ሽያጭና ምዝበራማ እንደለ ነው፡፡

በአለም ታሪክ ካህናት በተለይ በነገስታት ሀይል እየተገዙ ብዙ ምዝበራ አድርሰዋል፡፡ በፈቃደኝነት የማይለግሳቸውን እንኳ በሃይል በመዝረፍና በአዋጅ በማስገደድ የግላቸውን ሀብት ሲያካብቱ ኑረዋል፡፡ ለዚህም የመንግስተ ሰማይን መግቢያ ካርድ ቸብቻቢዋ ካቶሊክ ተጠቃሽ ናት፡፡ ሳሁን ደምሴ 'የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ዐበይት ፈተናዎች ከቅድመ ንጉስ ኢዛና እስከ ዘመነ ኢህአዴግ' መጽሀፍ ላይ ገጽ 221 እንዲህ ዘግቦታል፡-

> የሮም ካቶሊካዊ የእምነት ተቋም መሪዎች የቅዱስ ጴጥሮስን ካቴድራልን እናሰራለን በሚል ሰበብ በድህነት ከሚማቅቀው የእምነቱ ተከታይ ህዝብ ያለምንም ሃፍረት እና ይሉኝታ ገንዘብ እና ቁሳቁስ በማታለል እና በማጭበርበር ይወስዱበት ነበር፡፡ የእምነቱ ተከታይም ሳይጠረጥር እና ሳያገናዝብ መሪዎቹ ያሉትን ብቻ በመስማት ከራሱ እና ከቤተሰቡ ጉሮሮ ላይ እየነጠቀ ያለውን ጥሪት ለእነሱ በማስረከብ በችግር አረንቋ ውስጥ ተዘፍቆ ለእለት ጉርስ ለአመት ልብስ እለት እለት ይማስን ነበር፡፡ እናውቅልሃለን የሚሉት የእምነት መሪዎቹ ደግሞ በእምነት ተቋሚ ስም ከተከታዮች እጅ በመፈልቀቅ ያለአግባብ የሰበሰቡትን ገንዘብ ለግል ኪሳቸው ማዳበሪያ እና ለቤተሰቦቻቸው የቅንጦት ኑሮ መንደላቀቂያ ለማድረግ ችለው ነበር፡፡

ለነገሩ ማስገደድ የካቶሊክ መገለጫ ብቻ አይደለም፣ የኛው ተወዳጁ እና እጅግ አማኝ እንደሆነ የሚነገርለት አጼ ምኒሊክም ከአድዋ ድል መልስ የሚትአለውን አዋጅ አውጀው እንደነበር ካሳሁን ደምሴ ተርኮታል፡፡ አዋጁ "---- ለገንዘብህ ሳስተህ

Created in Master PDF Editor

ቤተክርስቲያንን አልሰራም ብለህ የወሰለትህ ሰው በሰማይ ይፈርድብሃል፡፡ በምደርም ሹመትህን፣ ገንዘብህን ታጣለህ፡፡" የሚል ነበር፡፡

በእየ ቤተ እምነቱ ይህና ያልተጠቀሱት ዘግናኝ አዋጆች፣ ዘረፋዎችና ማታለሎችና አላማቸው ቤተ እምነቶችን ቱጃር፣ ነጋዴና ተጽዕኖ ፈጣሪ ለማድረግ ነው፡፡ በዚህ ዘመን ቤተ እምነቶች የንግዱን አለም ለመምራት እየተሽቀዳደሙ ይገኛል፡፡ በተለይ በህንፃ ኪራይ፣ በትምህርትና በሌሎች የአክስዮን ድርሻ በመግዛት በገንዘብ ሀይል አለምን ለመቆጣጠር እቅድ የነደፉ ይመስላል፡፡ የሚየሳዝነው ደግሞ ግብር ከፋይ ባለመሆናቸው ተወዳዳሪ ነጋዴዎች ላይ ጫና መፍጠራቸው ነው፡፡ የቤተ እምነቶች ማደግ በጎ ተፅዕ ሊኖረው የሚችለው በህግና በስርዓት እየተመሩ እንደ ነጋዴ ግብር እየከፈሉ ቢነግዱ ነው፡፡ ሀይማኖቶች የካፒታሊዝም አቀንቃኝ መሆናቸውና ካፒታሊስት መሆናቸው እንደ ችግር የሚቆጠረው የመንግስትን አቋም መጠምዘዝ የሚችል ክንድ ስለሚያዳብሩ ነው፡፡ ክንዳቸው ደግሞ ገንዘብ ብቻ አይደለም የሚከተላቸውን ህዝብም በተቃወማቸው ላይ ሊያሳምፁ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የቤተ እምነቶች ካፒታሊስት መሆን በስጋት የተሞላ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ቤተ እምነቶች ካፒታሊስት ቱጃር የሚሆኑት የድሀውን ኪስ በመበርበር መሆኑ ነው፡፡ እውነት ስራቸው መንፈሳዊነት ከሆነ በካዝናቸው የሚንቀሳቀሰውን እረብጣ ገንዘብ በከፊል በድህነት ለሚሞቱት ወገኖቻችን ቢያውሉት ምን ነበር፡፡ ቅንነት ይጎላቸዋል አስተማሪያቸው እንዲህ ነበር፡፡ ቅዱስ ይሁዳ ብዙ ገንዘብ የሚያውጣ ሽቶ በክርስቶስ ላይ ሲፈስ ባየ ጊዜ ለድሆች ቢሰጥ ብሎ ተመኘ ክርስቶስ ግን ተቆጣ፡፡ ለዚህ ነው ዛሬም ሽህዎች የሚለብሱት ቁራጭ ጨርቅ አጥተው ቤተ እምነቶች ግን በወርቅ ተንቆጥቁጠዋል፡፡

የቤተ-እምነቶች ገንዘብ ለበጎ አድራጎት ቢውል መልካም ነገር ነበር ምንጩም እንደማይደርቅ ይታወቃልና፡፡ እንደኔ ሂሳብ ቤተ-እምነቶች ገንዘብ ለማግኘት ግብር የማይከፍለበት ንግድ ከሚያሯሩጡና በነጋዴዎች ላይ ጫና ከሚፈጥሩ በእየጊዜው የሚሰበስቡትን ለራሳቸው ፈጆታና ለበጎ አድራጎት ስራ ቢያውሉት መልካም ነው፡፡ ግን እውነቱ በንግድም በምእመናንም በማንኛውም ገንዘብ ማግኛ መንገድ ቱጃር መሆን ነው፡፡ ሀብታም ከሚፀድቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል የተባለው ከቤተ-ክርሰቲያን ውጭ ላሉት ነበር እንዴ?

ግርም ያደረጋል ሰባኪዎች ልባቸው እስኪወልቅ፣ ምድር እስክትንቀጠቀጥ ስለ ገንዘብ መጥፎነት ይሰብኩና መዝጊያው ላይ ቤተ-ክርስቲያናችን ለሆቴል፣ ለንግድና ለኪራይ የሚሆኑ ህንፃዎችን እያስገነባች ስለሆነ ያለችሁን አስተዋጽኦ አድርጉ ይላሉ፡፡ ስለ ገንዘብ አጥፊነት ሲሰብከው የኖረ ድሃም ሀብታምም ያለውን ይሰጣል፡፡ የሚያናደው የባለቤቶቻቸውን የወርቅ ቀለበት ሳይቀር የሚሰጡ

Created in Master PDF Editor

አይጠፉም፡፡ አስቡት የቃል ኪዳን ቀለበት ለስጦታ ይሰጣል እና ይህ ኪሳራ አይደለም ትላላችሁ ኪሳራ ብቻ አይደለም እብደት ጭምር ነው፡፡

ጊዜን በተመለከተም በአለም ላይ በገንዘብ የማይተመን ኪሳራ ደርሷል፡፡ በተለይ በሰርዓተ አምልኮ የሚባክነው ጊዜ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ በዚህ በሚባክነው ጊዜ ችግኝ ቢተከል፣ የድሆች ቤት ቢታደስ፣ የአስቆሮቱው ይሁዳ እንዳለው ገንዘቡም ድሆችን ለመታደግ ቢውል፣ በፀሎት የሚባክነውን ጊዜ ለአካባቢ ውበትና ፅዳት ቢውል ገነትን በመሬት የመፈጠር እድሉ ነበረን፡፡ ግን 30 ደቂቃ እስከ 12 ሰዓት በፀሎት የሚያሳልፍ ሰው አካባቢውን የማየት እድሉ የመነመነ ነው፡፡ ለዚህ ይመስለኛል ትላልቅ የቆሻሻ ክምሮች የሚገኙት ከቤተ-እምነቶች በቅርብ እረቀት የሆነው፡፡ በተለይ የቤተ-ክርስቲያናት አካባቢ የህዝብ ሽንት ቤትነት ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ ይህን ሳይ ስለ አማኞች እኔ አፍራለሁ፡፡ ምን አለ የአንድ ቀን ቅዳሴ ታጥፎ የፅዳት ዘመቻ ቢካሄድ፡፡

አማኞች እንዲህ አይነት ትቶችን መስማት እርማቸው እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ግን እውነቱን ማንም ማየት ይቻላል፡፡ ከሁሉም በላይ ጊዜን በተመለከተ የሚያሳዝነኝ እድሜ ዘመናቸውን ከእምነት ውጭ አንዳች ማሰብ ሳይፈልጉ የሚኖሩ ሰዎች በተለይም መነኮሳት መኖራቸው ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ታላቅ የሳይንስና ቴክኖሎጅ ሰዎች ሊሆኑ ይችሉ ነበር፡፡ ግን ህይወታቸው በሙሉ ስለአንድ ነገር ብቻ እያሰቡ አባከኑት፡፡እነዚህ ሰዎች ስለአንድ ብቸኛ መንገድ ማሰብ ከጀመሩበት ጀምሮ የሞቱ ናቸው ምን አልባት የሚቀበሩት ቆይተው ይሆናል፡፡ አንዳንዴ ሰዎች በ25 አመታቸው ይሞታሉ በ75 አመታቸው ይቀበራሉ የሚባለው አባባል እውነታ አለው፡፡

ሌላው የባከነ ሀብት ጉልበት ነው፡፡ ወገ አጥባቂ አማኞች አብዛኛውን ጉልበታቸውን የሚያፈሱት በስርዓተ አምልኮ ነው፡፡ ይህ ጉልበት ወጭ መሆኑ ሳይሆን የሚያስቆጨው ምን አልባት ያወጡት ጉልበት መና ቢሆን ነው፡፡ ደግሞም ነው ምን አልባት የአንዱ ሀይማኖት ተከታዮች ጉልበት ትርፍ ሊያስገኝ ይችል ይሆናል፡፡ የሌሎቹ ጉልበት ግን የአህያ ልፋት ሆኖ ይቀራል፡፡ እና ይህ አያስቆጭም፡፡

እኔ እንደሚገባኝ አማልዕክት የሰውን ልጅ ከቂሶች ጋር በተዋዋሉት የባርነት ውል እየገዘገዙት ነው፡፡ ጉልበቱን፣ ገንዘቡን እና ውድ ጊዜውን አባክነውታል፡፡ አንድ ትንሽየ ተስፋ መሰል ህልም ግን አለ የአንዱ እምነት ተከታዮች አይከስሩም ይልቅስ እጅግ ብዙ ሊያተርፉ ይችላሉ፡፡ ግን ያ እምነት የቱ ነው? ያ እምነት እስልምና ከሆነ ክርስቲያኖች ከስራችኋል፡፡ ያ እምነት ክርስትና ከሆነ ሙስሊሞች ከስራችኋል፡፡ ያ እምነት ከምሰራቆቹ አንዱ ከሆነ ክርስቲያኖችም ሙስሊሞችም

Created in Master PDF Editor

ከስራችኋል፡፡ ያ እምነት ከጥንቶቹ ከሆነ ሁሉም አማኞች ከስራችኋል፡፡ ያ እምነት ጭራሹኑ ባይኖር በሰው ልጅ ታሪክ የአመኑ በሙሉ ከስራዋል ማለት ነው፡፡ አቤቱ ከዚህ የህይወት ኪሳራ አድነን በሉት፡፡

ገነት፣ መንግስተ ሰማያት፣ ዘላለማዊነት ወዘተ የሚባሉ ምኞቶች አሳማኝ እውነታ ስለሌላቸው እንጅ ማንም ወደ ሲኦል መሄድ የሚፈልግ የለም፡፡ ማንም! ወደ መቃብር መሄድ ማን ይፈልጋል፡፡ ወደ ማይቆጠር ዘመን ቅጣት ማን መሄድ ይፈልጋል፡፡ ነገር ግን ገነት ማታለያ ሲኦል ማስፈራርያ ድርሰቶች ናቸው፡፡ ችግሩ ገነትና ሲኦል መግባት መፈለግ አለመፈለጉ ላይ አይደለም ገነት ምንድን ነው? ሲኦል ምንድን ነው? ለምንስ አስፈለጉ? በእውነት አሉን? የሚሉ ጥያቄዎች መመለስ አለባቸው፡፡ ደስ የሚለው ቅን አማኞች ሲኦል የለም ብለው ያምናሉ፡፡ ሂንዱዚሞች፣ ቡዲዝሞች፣ ኮንፊሽስዝሞች፣ ከፊል አይሁዶችና ክርስቲያኖች ሲኦል የዘለአለም መፈራረጃ ነው ብለው አያምኑም፡፡

ቢሆንም በቁጥር የሚልቁት አማኞች ገረር፣ ጠንገር፣ ከረር ባለ ዕይታ ይተረጉሙታል፡፡ ስጋታቸው ሲኦል የለም ማለት እግዚአብሔር የለም ማለት ስለሚሆንባቸው ነው፡፡ እግዚአብሔርና ሲኦል የማይነጣጠሉ አድርገው ሰለዋቸዋል፡፡ ይህን የሲኦሉ ጌታ እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ሲሉ ያሞጋግሱታል፡፡ በዚያ በሲኦል ስለሚሆነው አንድ አጥማቂ የሆነ መፅሀፍ ለተጠማቂዎቻቸው ሲያነቡ ስምቻለሁ፡፡ መፅሀፉን አንድ ቀን እንደማገኘው ተስፋ አደርጋለሁ ንባቡ ከአዕምሮየ ሊጠፋ አይችልምና ሀረጎቹን አስታውሳቸዋለሁ፡፡ በእውነት ያ መፅሀፍ የፃፈው ሰው ምንኛ ጨካኝ ነው፣ ያን የሚያነቡ አይችስ ምንኛ መራር ናቸው፡፡ መፅሀፉን አጥማቂው ሲያነቡት በኩራት ቢሆንም ህፃናትና በህመም ውስጥ ያሉ እንዳያነቡት ተብሎ መታተም ነበረበት፡፡ ከጥቃቅን ነገሮች እስከ ታወቁት ሀጢአቶች ድረስ እየዘረዘረ ሀጢአተኞቹ ስለሚያጋጥማቸው መከራ ያወራል፡፡ ስጋዊ ድህነት ፈልገው የተሰባሰቡት ተጠማቂዎች ለስጋቸውም ለመንፈሳቸው ድካም አትርፈው ይመለሳሉ፡፡ በእርግጥ ሁኔታውን በተከታተልኩበት ሁለት ሳምንታት ድነናል ብለው ጮቤ እየረገጡ እየተሳሉና ስጦታ እየሰጡ የሚሄዱ ነበሩ፡፡ አጥማቂው ከመጡ ጀምሮ ታስረው የሚጮሁ ምህረት ያልወረደላቸው ምስኪኖችም ነበሩ፡፡ አማኞች የሚያነባጥሩት ከዳኑት ላይ ቢሆንም በጀርባ ስላለውና ስለአልዳኑት ምክንያት ማወቁ አይከፋም፡፡ እኔ ግን አጥማቂው የሚፈውሱት በሽታ ስላልነበረብኝ መሰለኝ ተጠምቄ ስለ ሲኦል የማይገቡ ትምህርቶችን ተምሬ ተለያየን፡፡ እኒህ አጥማቂ የዋሉልኝ ውለታ ቢኖር ጥርጣሬየን ጫፍ አስነክተውት ነበር፡፡ በኋላ እኒህ የሲኦል አቀንቃኝ አስማተኛ ናቸው እንዲሁም ዝናብ አልዘንብ ያለው እርሳቸው በአካባቢው በመኖራቸው ነው የሚል ተቋውሞና ትችት ስለደረሰባቸው ወደ አልሰማው ሸሹ፡፡

Created in Master PDF Editor

12. **የጸሎት ዋጋ**

አንደበቴም ያውጣ የምሥጋና ቅኔ

የአምላኬን ማዳን አይቻለሁ በዓይኔ

በገባኦን ሰማይ ጸሐይን ያቆመ

ዛሬም ጎብኝቶኛል እየደጋገመ

ወጥመድ ተሰበረ እኔም አመለጥኩኝ

ከኃጢአት ፍላፃ ከሞት አተረፍከኝ

የአናብስቱን አፍ በኃይሉ የዘጋ

የዳንኤል አምላክ ይሆናል ከእኔ ጋ(አንደበቴም ያውጣ ከተሰኘ መዝሙር የተወሰደ)

አማኞች ሀገራችን ካለ እናንተ ጸሎት ውጪ ሰላሟም ልማቷም ሊረጋገጥ አይችልም ሲባሉ ደስ ሊላቸው እንደሚችል በተቃራኒው ደግሞ በፀሎታችሁ ብዛት ሀገሪቱ ሰላሟም ልማቷም ተስተጓጉሏል ሲባሉ ሊከፋቸው እንደሚችል ማወቅ አያስቸግርም፡፡ ያም ሆነ ይህ የጸሎትን ዋጋ ከፖለቲካ አንጻር ሳይሆን ከነባራዊ ህይወት አንጻር መፈተሽ አለብን፡፡ *"ፀሎት ማለት ልመና ማለት ነዉ፡፡ ይህን ስጠኝ፣ ያን አድርግልኝ፣ ይሄን አታድርግብኝ እያልክ ጌታን መለማመጥ፡፡ ለምሳሌ ገንዘብ ስጠኝ ብለህ ትፀልያለህ ያዉ መቸም በፀሎትህ መሰማት እርግጠኛ ስለማትሆን ስራ መስራትህን አቁመህ የጌታን እጅ አታይም፡፡ ስራ ፈልገህ ትሰራለህ፡፡ ስራ ስለሰራህ ብቻ ብር ስታገኝ ግን በተዘዋዋሪ ጌታ እየሰጠህ ይመስልሃል፡፡ አሁን ፀሎቴ ሰመረ ትላለህ፡፡ ጌታን ከክፉ ነገር ጠብቀኝ ብለህ ከቤትህ ወተህ አደጋ ደርሶብህ ሰዉነትህ ሲጋጋጥ ምን ትላለህ? ጌታ አተረፈኝ፡፡ የሆነ በሽታ ይዞህ ታመህ ፀበል ሳያድንህ ቀርቶ ዶክተር ሲያድንህ በዶክተሩ በኩል ጌታ ፈወሰኝ ትላለህ፡፡"*<ከማመን መጠራጠር ይሻላል>

የብዙዎቹ ሃይማኖቶች ተከታዮች በጸሎት አማካኝነት አምላክ ያደረገላቸውን መልካም ነገር ይመሰክራሉ፡፡ አንድ ሰው በመኪና አደጋ ጉዳት ደርሶበት ከሞት ቢተርፍ ፈጣርን ያመሰግናል ለደረሰበት የአካል ጉዳት ግን ባለንብረቱን ካሳ ይጠይቃል፡፡ በዚ ሰው እይታ አጥፊ ሾፌሩ አዳኝ እግዝአብሔር ናቸው፡፡ ለእኔ ግን ሰቶ በመንሳት እና ገሎ በማዳን የሚመሰገን ጌታን ለመቀበል ይከብደኛል፡፡ እውነቱ ግን አማኝም የማያምንም ከጥበቃ ውጭ ናቸው፡፡ እኛ የማናምነው ልክ እደሚየምኑት እንተመማለን እንደ አማኖቹ ማረንማረን ባንልም የመዳን እድላችን ግን ከሚፀልዩት እኩል ነው፡፡<ከማመን መጠራጠር ይሻላል> ወንድሞቹን አማኞች እንዲህ ይላቸዋል፦

Created in Master PDF Editor

"ወንድሜ የማንፀልየዉም ካንተ የተለየ ህይወት አንኖርም:: በፀለየ ቢሆን ኖሮ አንተ ከኛ የተሻለ ሀብታም፣ ከኛ የተሻለ አዋቂ፣ ከኛ የተሻለ ደስተኛና፣ ከኛ ይልቅ በሽታ የማይነካዉ ጤነኛና ረጅም አመት የሚኖር ሰዉ ትሆን ነበር:: ግን አይሆንም:: ህይወት የፀለየ ያልፀለየ አትልምና ሁላችንንም እኩል ነዉ የምታኖረን:: ስለማንፀልይ ደመወዛችን አይቀርም:: ስለማንፀልይ የኛ ጤና አይታወክም:: ስለማንፀልይ ቶሎ አንሞትም:: በስመ አብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብለን አማትበን ስላልበላን ሳንጠግብ አንነሳም.... ልዩነታችን እኛ ህይወትን እንደ አመጣጡ ስንኖረዉ አንተ ግን እየቃዠህ ትኖራለህ::"

በጸሎቶች ውጤታማነት ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያስረዱን ለታካሚው ምንም ተጽእኖ የለውም፡፡ ምንም ያህል በማንማ በምንም አይነት መንገድ ቢፀለይ ያው ፀሎት ነው፡፡ ብዙ ሰወች ፀሎታቸው ካልሰመረ የጌታ ፍቃድ ባይሆን ነው ብለው ዝም ይላሉ፡፡ የፀሎት መልሱ እንደኛ ፍላጎት ካልሆነ ለምን እንፀለያለን? ሲጀምርስ ምን እነንደሚያስፈልገን ለሚያውቅ አምላክ እንዲያደርግልን ማስተወስ ተገቢ ነውን?ስለዚ መፀለይ ለራስ ከማውራት የዘለለ ጥቅሙ ምንድን ነው?ፀሎት ቢሰራ ኖሮ ስንቱ በዳነ ነበር፡፡ ወገኖቻችን ኮማ ውስጥ ሲሆኑ የወገን ደራሽ እያልን ሰው ከምናስቸግር ማቅ ለብሰን ፀልየን ባዳንናቸው ነበር፡፡ ግን አዝናሁ የሚድን ይድናል የሚሞት ይሞታል ይህ የተፈጥሮ ህግ ነው፡፡ፀሎትን በገመገመበት ሀተታው የዓለም ታሪክ የሚያስተምረን ይላል በዕውቀቱ ስዩም እግር አልባው ባለክንፍ በሚለው መጣጥፉ፦ *"የዓለም ታሪክ የሚያስተምረን ለስጋቸው የሚጨነቁ ሕዝቦች በልፅገው ለነፍሳቸው ብቻ የሚጨነቁ ሕዝቦችን መግዛት እንደሚችሉ ነው:: የዳርዊን አገር ከአቡነ ተክለሃይማኖት አገር በላይ ተሳክቶለታል፣ (እውነት ነው) ዋናው ነገር ጠፈሩ የምናስበው ያክል የዋህ አለመሆኑን ማወቅ ነው፣ ምድሪቱ ከፀሎታችን በላይ ላባችንን፣ ከእንባችን ይልቅ ደማችንን ትጠይቃለች::"*

ምን አልባት ለሚመስላቸው ሰዎች በጥቂቱ መፀለይ ተገቢ ይሆናል 'ሜልኮል ብትስቅብኝ ቢጠላኝም ዓለም' እያሉ አብዝቶ መፅለይ ግን ጊዜን እንደማባከን ይቆጠራል፡፡ ይልቁንም እግር እስከመቆረጥ ድረስ አካላዊ ጉዳት ያደርሳል፡፡ አወዛጋቢው መልአከ መንክራት ግርማ ወንድሙ እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሚሰብኩት ግን ትልቅ ሸክም ነው፡፡ አወዛጋቢው አጥማቂ የስግደትና የጸሎት ዓይነትና ሠዓቱን በሰበኩብት ስብከታቸው እንዲህ ይመክሩናል፡፡

> ያልሰገደ እና ያልፅለየ ትውልድ ራዕይ የለውም፡፡ ለሚሰግዱ ሠዎች እግዚአብሔር መንገድ አለው፡፡ በመንፈቀ ሌሊት 6 ሠዓት (?)፣ በነግህ ጊዜ 11 ሠዓት (ውዳሴ ማርያም፣ ሰይፈ መለኮት፣ ሠይፈ ሥላሴ ወይም ከቅዱሳን አንዱ)፣ረፋዱ በ3 ሠዓት (አርጋኖን እና መልክአ ገብርኤል)፣ከቀትሩ በ6 ሠዓት

Created in Master PDF Editor

(መልክአ ስላሴ እና መልክአ ሚካኤል)፣ በ9 ሠዓት (መልክአ መድኃኒዓለም እና መልከአ ኡራኤል)፣ በ11 ሠዓት (?) እና ማታ ከመኝታ በፊት በ3 ሠዓት (መልክአ ሩፋኤል እና አርጋኖን) መፅለይ አለብን:: በተጨማሪም በነዚህም በሰባቱ የጸሎት ጊዜያት (እግዚኦታ 12 ጊዜ፣ በእንተ ማርያም 12 ጊዜ፣ ኦ አምላክ 12 ጊዜ፣ ኦ ክርስቶስ 12 ጊዜ፣ ያድኅነነ እመዓቱ 12 ጊዜ፣ ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከን 12 ጊዜ፤ ማድረስ) እና ከቀዳሚትና ከእሑድ እንዲሁም ከታላላቅ በዓላቶችና ሥጋ ወደሙ ከተቀበሉበት ዕለት በስተቀር ሰባት ሰባት ጊዜ መስገድ ይገባል:: (የስንታየሁ እይታዎች፣ ስግደትና የጸሎት በመልአከ መንክራት ግርማ ወንድሙ)

ከላይ የተጠቀውሱትን ውዳሴ ማርያም፣ ሰይፈ መለኮት፣ ሠይፈ ሥላሴ፣ መልክአ ስላሴ፣ መልክአ ሚካኤል፣ መልክአ መድኃኒዓለም፣ መልከአ ኡራኤል፣ መልክአ ሩፋኤልእና ሌሎችን በእየቀኑ ማንበብ ስንት ሰዓት ሊፈጅ እንደሚችል መገመት ይቻላል:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ያለት ስራን አይበድልም ብትልም አንድ የመርካቶ ነጋዴ በቀን ለ7 ጊዜ ስፀልይ እና ሲሰግድ ደንበኞች ቆመው ይጠብቁታል ማለት ወይ? ደግሞስ ፀሎት ያስፈልጋል እንኳ ብንል 6 በ12፣ 72 ጊዜ ማረነ ማለት አንድ ጊዜ ማረነ ከማለት ይበልጣልን? ድንግል ማርያም ሆይ ብፅዕት ነሽ ብሎ መዘጋት ሲቻል ለከንፈርሽ፣ ለጉሮሮሽ፣ ለጡትሽ፣ ለሽንጥሽ፣ ለሆድሽ፣ ለኩላሊትሽ፣ ለአንጀትሽ፣ ለእንብርትሽ፣ ለማህፀንሽ፣ ለድንግልናሽ፣ ለተረከዝሽ፣ ለጫማዎችሽ፣ ለእግር ጥፍርሽ፣ ለመቃብርሽ፣ ማለቱ ፍይዳው ምንድን ነው? ምንም:: ለነገሩ እነእገሌ ዘብሔረ እንትን እንጀራቸውን የሚያበስሉት በዚህ ነው::

ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ክርስቲያኖች የፀሎት ሰዓት ሲደርስ የትም ሁነው መጸለይ እንደሚችሉም ታስተምራለች:: የግል ስራ የሚሰራው አያደርገውም እንጅ ቢችል ቤተክርስቲያን ሂዶ ባይችል በሩን ዘግቶ ሊፀልይ ይችላል:: ችግር የሚፈጥረው ወደ መስርያ ቤቶች እና ት/ቤቶች ስንሄድ ነው:: ተማሪዎች መምህሩን አስቁመው፣ ሲቪል ሰርቫንቶች ደንበኞችን አስቁመው፣ ወዘተ መልዕካ መልክ ማነብቡ ተገቢ ነውን? ይባስ ብሎም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት መፅሀፍት መነሻቸው እና መድርሻቸው ክርስቲያኖች በህይወታቸው ሳያነቡት እንዳይቀሩ የሚያሳስቡ ናቸው:: አስቡት አንድ ሰው ምንም ያህል አንባቢ ቢሆን ወይም እድሜ ዘመኑን ቢያነብ የቅዱሳኑን ገድል አንቦ አይጨርስም:: ለአራት ሽህ አመታት የተጻፉትን የፀሎት መጽሃፍት በ40 አመት አንቦ የሚጨርስ ማን ነው? አባ ሕርያቆስ ብቻ 10,000 (አስር ሽህ) ድርሰቶች እንድጻፉ ሰምቻለሁ:: ደግነቱ ከጥቂቶች በስተቀር ከካህኑ እስከ ምዕመኑ ድረስ የእለት እንጀራ የሚሰጠውን ስራ ሲያባርር ይውላል እንጅ ፀሎት እና ስግደትን ለሰሞነ ህማማት ትቷቸዋል:: እንኳንስ ሊፀልዩ ካህናቱ በሚፀልዩት ፀሎት መርዘም የሚያጉረመርሙም አሉ:: እሰይ ደግ አደረጉ:: መ/ር ግርማ ያልሰገደ እና

Created in Master PDF Editor

ያልፅለየ ትውልድ ራዕይ የለውም ብለውናል። ልጠይቃችሁ እድሜ ዘመኑን በጸሎት ያባከነን ሰው ምን ትሉታላችሁ? በእውቀቱ ስዩም እግር ዐልባው ባለ ክንፍ በሚለው መጣጥፉ እና እኔ በዚህ መጽሀፍ 'በሰማዩ ላይ አለቅጥ ሲያተኩር ምድሩን የሚከዳ ምድሩም የምትከዳው ማኀበረሰብ ተክለሃይማኖታዊ ይባላል' እንላለን።

13. አታላይ እና አስመሳይ የሃይማኖት መስራቾች፣ መሪዎችና ሰባኪዎች

ሰይጣን ለተክለ ኪዳን እንዲህ ብሎታል *"እናንተ እውነተኛ የእግዚያብሔር አገልጋይ ነን፤ ፓትርያርክ፣ ጳጳስ፣ ቆሞስ፣ መነኩሴ፣ቄስ፣ ዲያቆን፣ መምህር፣ ሰባኪ፣ ዘማሪ፣ መስካሪ...ወዘተ ነን በማለት ራሳችሁን የምታመጻድቁና በእውነትና በመንፈስ እግዚአብሔርን የማታመልኩ በእውነትም የማታገለግሉ፣ ሌላው ቢቀር ዲያብሎስ ከነሰራዊቱ ይታዘበናል የማትሉ፣ የጨለማ ስራ ተባባሪዎችና አስፈጻሚዎች፣ ለእኔም ለጨለማው ገዥ አገልጋዮቼና ምርጦቼ ሰዎች፤ በእውነተኛው የሕይወት መንገድ ውስጥና በእውነተኛ ወንበር ላይ ሆናችሁ እንደጻፎች፣ ፈሪሳውያን፣ አይሁድ ካህናት አለቆች ደግም አምላካችሁን የመሰቀል እድል ባለማግኘታችሁ ባዝንላችሁም፤ በተዝዋዋሪ ግን እሱን አምላካችሁን በሚያሳዝንና በሚያስቆጣ ተግባር ላይ ተሰልፍችሁ ስመለከት ነፍሴ እጅጉን ሐሴት ታደርጋለች።"* (የጨለማው ገዥ ተግባርና ንግግር፣ 2009 ዓ.ም፣18)

አታልይ መሲሆች ያልመጡብት ዘመን የለም። የተሳካላቸው ግን ጥቂቶች ብቻ ናቸው በተለይም እየሱስ እና ሙሀመድ። በእየዘመኑ እመኑብኝ እያሉ ወይም እያስባሉ ብዙዎች መተዋል። በኢትዮጵያ ደግሞ በተወዳጇ ማርያም ስም መተዋል። የመሲሆች እውነተኝነት በገዙት ልብ ብዛት ይመዘናል። መሪዎች ተከታዮች ያስፈልጓቸዋል ይልቁን ተከታዮች መሪዎች ያስፈልጓቸዋል ይባላል። አመራር መልካም ተጽእኖ ማሳደር ሲሆን መሪዎች ደግሞ ጠንቃቃ እና ችሎታ ያላቸው መሆን አለባቸው።ከታሪክ እነደምንረዳው በጊዜ ሂደት ማህበረሰቦች ከአነስተኛ ጎሳዎች ተነስተው ሀገር መመስረት ችለዋል።አመራር ለሀገር እና ለንግድ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን ለሃይማኖቶችም ያስፈልጋቸዋል።ያውም እራሱን ለእግዚአብሄር ያስገዛ፤ የበጎች እረኛ እና ሰማያዊ አደራ ያለበት። ግን ይህ በእውን አለን?

> "በእውነትና በስራ ብቻ እንጂ በአፍና በምላስ አንፋቀር ዘንድ አይገባንም። በአፋቸው የክርስቶስን ፍቅር እያስተማሩ በልባቸው ግን ፍቅር የሌላቸው፤ ሲሳደቡና ሲጋደሉ እርስበርሳቸውም ስለ ሀይማኖታቸው ሲወዛገቡ እንደሚኖሩት እንደ ሀገራችን ክርስትያኖች አንሁን። እንደዚህ ዓይነት ፍቅር ከእግዚአብሔር ዘንድ አይደለምና ምንም አይጠቅምም። ዳግኛም ከምላሳቸው ስር እባብ መርዝ እያለ፣ በአፋቸው የእውነትና የፍቅር(አስመስለው) እንደሚናገሩ ግብዞች አንሁን። እነሱ ልባቸው ሁልጊዜ መጣላትንና መከራከርን ያስባል። ፍቅራቸው ፍጹም

Created in Master PDF Editor

> አይደለምና የሀይማኖት ወገኖቻቸውን እየወደዱና በሀይማኖት የማይመስሏቸውን ሁሉ ግን እንደሚጠሉ ግብዞች አንሁን፡፡” የፈላስፋው ወልደ ህይወት ሐተታ ምዕራፍ 14 (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 301)

እሰቡት አንድ ሽፍታ አስገድዶ ቢደፍርና የህን ተገባር አንድ ፓስተር ቢፈፀመው የቱ ያናድዳል?ሽፍታው ለልማትም ለጥፋትም አንዴ ሽፍቷል ቢያሳዝንም የሚጠበቅ ጉዳይ ነው፡፡ ወጀሎች በሃይማኖት መሪዎች ሲቀነባበሩ ግን ጋራ ያጋባሉ፡፡ ምን አለፋችሁ በአለም ውስጥ በስመ ታማኝነት የአደንዥ እፅ ዝውውሩን ካጦፉት ካህናት እና ፓስተሮች ይገኙበታል፡፡ ከሩቅ ሳልሄድ በሀገራቸንን በሚካሄደው ህገ ወጥ የጦር መሳርያ ዝውውር እና ኮንትሮባድ የአስመሳይ አገልጋዮች እጅ እንዳለበት ይሰመኛል፡፡ በእየ ቤተ ክርሰቲያኑ በአገልጋዮች መካከል ያለውን ሙስና፣ ዘረኝነት እና ሸኩቻ አስቡት፡፡ በስመ የንስሃ አባት ከልጁ ጋር በፍቅር የሚከንፋንቄስ ምን ትሉታላችሁ?(ከፖሊስ ዘገባ በ2010 ዓ.ም የሰመሁት ነው) ፡፡

የእኔ ንስሀ አባት በሀይማኖት እና በሳይንስ የተሻለ እውቀት ካለቸው አገልጋዮች የሚመደብ ነው፡፡ ሲሰብክ ብትገኙ በእዝነ ልቦና መንግስት ሰማያት ደርሳችሁ ትመለሳላችሁ፡፡ ሲቀድስ ሰወች ብቻ ሳይሆን እንሰሳትም አሜን የሚሉ ይመስላኛል፡፡በማይረባ ነገር ሲሸወድ አየሁት፡፡ የሚያስተምርበት ት/ቤት የባህር ዛፍ እንጨት ለሰራተኞች በአነስተኛ ግዥ በእጣ ሲከፋፈል ለሱ ትናንሽ አስራቶች ደረሱት፡፡ በአይኔ እያየሁ የእሱን እጣ ለሌሎች የሌሎችን ለራሱ ወሰደ፡፡ ይህም ስርቆት መሆኑ ነው? ለእኔ ለልጁስ ምን ያስተምራል? አንድ ፕሮቴስታንት ጓደኛየ እንደነገረኝ የሚወደው ፓስተር ልፀልይልሽ እያለ ቢሮው ውስጥ ወሲብ ሲፈፅም ደርሶበታል፡፡መድረክ ላይ ሙዚቃ ሀጢአት ነው እያሉ አስተምረው ከስብከት መልስ ያዝ እጇን፣ ዝጋ ደጇን፣ ሳም ጉንጯን የመሳሰሉ ዘፈኖችን ከደፈሩ በጅፓስ ካፈሩ በኤር ፎን የሚያዳምጡትን ምን ትላላችሁ? ብዙ ብዙ ማለት ይቻላል፡፡

እኔ አገልጋዮች ከሚሰብኩት ህዝብ ልቀው መገኘት እናዳለባቸው ቢገባኝም የማገኛቸው ግን ደቀው ነው፡፡ አገልጋዮች መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸውየእግዚአብሔርወኪሎችናቸው ማለት ማታለል እንዳየሆን እሰጋለሁ፡፡ አንዳንዶቹ ሲሰብኩ ቃሉን ያዙት እኔን እርሱኝ በማለት ያልተዋሀዳቸውን ወንጌል ሲሰብኩ እና ነገ ለሚሰሩት ሀጢአት ቅድሚያ ንስሀ ሲገቡ ይታያል፡፡

> ቄሶች ይሄንን ስልጣን ሲፈልጉ ከመምህርነት ከፍ ያሉና በእናንተ ላይ አባት መሆን ይፈልጋሉ፡፡ እናንተን መቆጣጠርና እንደፈለጋቸው መዘወር ሲፈልጉ ‘የሃይማኖት አባት’፣ ‘የቀለም አባት’፣ ‘የምናምን አባት’ እያሉ ሁሉም እየተነሳ የራሱ ጥቅም ያለበትን አስተሳሰብ በእናንተ ላይ መጫን ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም ከወላጅ አባታችሁ በስተቀር ሌላ አባት አያስፈልጋችሁም፡፡ ለማንኛውም

Created in Master PDF Editor

የሃይማኖት አባቶቻችሁ እንዳስተማሯችሁ አክራሪ አትሁኑ፣ አክራሪ ስትሆኑ በጣም ውስንና ጅምላ በሆኑ አስተሳሰቦች ትታጠራላችሁ፤ የሃይማኖት አባቶቻችሁ የበላይና ተደማጭ ሆነው መቆየት የሚችሉት እናንተን በዚህ አጥር ውስጥ ማስቀመጥ ሲችሉ ብቻ ነው። ከዚህ አጥር መውጣት ከቻላችሁ ከሃይማኖት አባቶቻችሁ በላይ ስለምተሆኑባቸው ይፈራሉ። ፖለቲከኞችም እንዲዘሁ ናቸው፤ መላውን የሰው ልጅ እነሱ ባዘጋጁት ከረጢት (ርዕዮተ ዓለም) ውስጥ ማስቀመጥ ይፈልጋሉ። ከረጢቱ ከሌለ ልዩነት ሊጠፋ ነው፣ አክራሪነት፣ ዘረኝነት፣ ታዛዥነት ይጠፋል፤ የእነዚህ ነገሮች መጥፋት የፖለቲከኞችንና የሃይማኖት አባቶችን ህልውና ስለሚፈታተን ያስደነግጣቸዋል። (ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣ 32)

ታዲያ ከማንም ያልተሻለ እንዲያውም የባሰመጥፎ ስብዕና ያላቸው እኒህ አስመሳዮች መድረክ ላይ ወተው ስለ መሬትና ሰማይ፣ስለ ፍጡርና ፈጣሪ፣ ስለ ሞትና ድህነት ሌላም ሌላም ቢደሰኩሩ እንዴት ሊገባኝ ይችላል።ዲስኩሩ ይቅርና በእየ ፀበሉ እና በእየ አዳራሹ ታምራትን እናደርጋለን ቢሉም በሃሰት የተቀናበረ ወይም ምትሃት ሊሆን እንድሚችል መገመት አይከብብደኝም። ይባስ ብሎ ወንጌል እንዲህ ይላል፦

“ኢየሱስም መልሶ እንዲህ ይላቸው ጀመር። ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። ብዙዎች እኔ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና ብዙዎችንም ያስታሉ። ማርቆስ 13: 5-6 በዚያን ጊዜም ማንም እነሆ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም እነሆ ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ። ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፣ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ ያስቱ ዘንድ ምልክትና ድንቅ ያደርጋሉ።” ማርቆስ 13: 21-22

ስለዚህ በእየ ቦታው እየሱስን ተቀበል የሚሉን ሃሰተኛ ቢሆኑስ? የሰውን ልጅ በዝብዘው የበሉት እነዚህ አስመሳዮች ናቸው። በእርግጥ በሁሉም ሃይማኖቶች ውስጥ አንዳንድ ቀሳውስት ርህራሄ የተሞሉ፤ የሰውልጆች ደህንነታቸውን የሚደግፉ፤ ደግነት እና ሰብአዊነት የተላበሱ አሉ። ይህም ቢሆን የሀይመኖታቸውን ተክክለኛነት አያረጋግጥም። ሰው ያለ ሀይማኖት ደግ፣ ታጋሽ፣ ታማኝ፣ ሰብአዊ መሆን ይችላል። ጥያቄ አለኝ ብዙ ወንጀሎች እና የሰባዊ መብት ጥሰቶች የሚበዙት አማኝ በሚበዛባቸው ወይስ እምነት የለሽ በሚበዛበቸው ሀገራት ነው?

Created in Master PDF Editor

14. ሀማኖቶች የሚፍጥሩት ችግር

“Instead of understanding and following the teachings of Jesus, the Christians argued and quarreled about the nature of Jesus’s divinity and about the Trinity. They called each other heretics and persecuted each other and cut each other’s heads off.”– Jawaharlal Nehru

አንዳንድ በሀይማኖት ታሪክ ላይ ጥናት ያደረጉ ሰዎች Religion and War means Egg and Chicken ሲሉ ይደመጣሉ:: በተለይ የታላቁ ቆስጠንጢኖስ ክርስትናን መቀበልና መንግስታዊ ሀይማኖት ማድረጉ ክርስቲያኖችን ደም መላሾች እንዳደረጋቸው ይነገራል::ለዚህም ነው የክርስትናን የጭቆና አገዛዝ ታሪክ ያጠኑት “The Constantinian shift turned Christianity from a persecuted into a persecuting religion.” የሚሉት::በአለም መድረክ ብዙ የሚያሳዝንና የሚያስጨንቅ የጭፍጨፋ ታሪክ ቢኖርም ለአንባቢዎችና ለእኔ ቅርብ የሆነውን ላስታውስ::

ይህን መፅሃፍ ሳዘጋጅ ሀይማኖቶች በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ችግር ፈጥረው ይሆን የሚል ሀሳብ መጣብኝና የታሪክ መፅሃፍትን ማገላበጥ ጀመርኩ:: በተለይ ካሳሁን ደምሴ የጻፈውን ‘የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ዐበይት ፈተናዎች ከቅድመ ንጉስ ኢዛና እስከ ዘመነ ኢህአዴግ’ የተባለውን መፅሃፍ እንዳነበብኩ የሚከተለውን ጹህፍ ማስታወሻየ ላይ ጻፍኩ::

Imagine, If NO Religion,

- NO Pagans Killing
- NO Fereminatos Conflict
- NO Orthodox Vs Catholic Conflict
- NO Heresy Killing
- NO Yodit Gudit war
- NO Coptic colonization on Orthodox Tewahido church
- NO Dekike Estifanos Killing
- NO War of Ahmed Badley
- NO bete Tekilehaymanot Vs bete Eiwsitatiwes conflict
- NO Ahmed Gray war

Created in Master PDF Editor

NO Jihad on Debre Libanos, Mekane silasie, Atronus mariayam, Bete semayat, Debre Negodguad, Aksum tsion, and Lalibela churches.

NO Alfonzu Mendiz, Bermudiez, Painz etc.

NO Civil war of Ate Susenyos

NO Tewahido, Qibat, and Tsega Conflict

NO Conflict between Atse Tewodros Vs Orthodox church

NO Boru-Medaproclamation

NO Sudan (dirbush)conflict

NO Siso Mengist (one third ownership of Government by orthodox church)

NO Catholic and Protestant missionary

ካሳሁን ደምሴ በመጽሀፉ አንድ አሳዛኝ አዋጅ አስነብቦናል። አዋጁ የአልፎንሶ ሜንዴዝ አዋጅ ተብሎ ይጠራል። የአዋጁ ጭብጥ በኢትዮጵያ ታሪክ ቀደምት የሆነችውን ኦርቶዶክስ ቤ/ን ለማጥፋት ያለመ ነበር። ካሳሁን በዝርዝር እንዳስቀመጠው ዋና ዋናዎቹ አዋጆች የሚከተሉት ነበሩ።

- የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አባላት ሁሉ የካቶሊክን እምነት ተቀብለው እንደገና እንዲጠመቁ፣
- በግብፃዊው ጳጳስ ማዕረግ ክህነት የተቀበሉት ካህናት በሙሉ ተሽረው እንደገና በአልፎንሶ ሜንዴዝ እጅ ማዕረግ ክህነት እንዲቀበሉ፤
- በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ ከዚህ ቀደም በግብፃዊው ጳጳስ መባረካቸው አግባብ ስላልነበረ እንደገና በካቶሊክ ጳጳስ ሜንዴዝ እንዲባረኩ፤
- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የተወሰኑት በአላት እና አፅዋማት በአውሮፓዊውያን ቀን አቆጣጠር እና ባህል መሰረት እንዲፈፅሙ፤
- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ትውፊት መሰረት የተሳሉት የቀለም ስዕላት ተወግደው በሮማውያን ስርዓት እና ትውፊት መሰረት ከድንጊያ የተጠረበ የተቀረፀ ምስል እንዲቆም፤
- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሊቃውንቶች እና ከውጭ ከእህት አብያተ ክርስቲያናት የተተረጎመ የቤተክርስቲያን መፅሐፍት እንዲቃጠሉ፤
- ከኦሪት እምነት የተወረሱት ለታቦት የተሰጠው ክብር፣ ግዝረት፣ቅዳሜን እንደ ሰንበት ማክበር … ወዘተ እንዲቋረጥ፣
- አርብ እና እሮብ መፆሙ ቀርቶ ቅዳሜ እንዲፆም
- ቅዳሜን ሰንበት ብለው በማክበር በማይሰሩት ላይ ቅጣት እንዲጣል፣
- ገበሬዎች ቅዳሜ ስራ ሲፈቱ እያወቁ በቸልተኝነት ትዕዛዙን የማያስከብሩ ባለርስቶች መሬታቸው በመንግስት እንዲወረስ።

Created in Master PDF Editor

- የካህናት አፅም ከቤተክርስቲያን ቅፅረ-ግቢ ውስጥ ተቆፍሮ ወጥቶ እንዲቃጠል፣
- የኢትዮጵያ ባህረ ሃሳብን ወይም የቀን አቆጣጠርን አጥፍቶ በምዕራባውያን የዘመን አቆጣጠር እንዲተካ የሚሉት እና የመሳሰሉት ነበሩ፡፡

(ምንጭ፡- ካሳሁን ደምሴ፣ 'የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ን ዐበይት ፈተናዎች፣ ገጽ 175-177')

ኢትዮጵያን ማለት ሀይማኖት ሲያንብጣትና ሲያቀናት የኖረች ሀገር ናት፡፡ ይህች ምትሃተኛ ሀገር ይህን ሁሉ አልፋ ሽ ጊዜ ጠፍታ ሽ ጊዜ ለምታ ነው ዛሬ ላይ የደረሰችው፡፡ የዛሬው አኗኗራችንም ትላንት በተሰራ ቤት ነው፡፡ ሀይማኖቶቻችን የአኩሪ ታሪካችን መሪ ተዋናዮች የሆኑበት አጋጣሚ ቢኖርም ብዙ ጊዜ ግን መራራ በደልን ፈፅመዋል፣ የህዝቡን የማሰብና የመበልጸግ ህልም አኮላሽተውታል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለምን ድሃና ለኑሮ የማትመችሆነች ሲባል አንዳንዶቹ አይናቸውን በጨው ታጥበው ድሀና ለኑሮ የማትመች አይደለችም ብለው ውይይቱን በአጭር ያስቀሩታል፡፡ ሌሎች ደግሞ የየግላቸውን ምክንያትና መፍትሄ ይደረድራሉ፡፡ ከነዚህ ምክንያት አቅራቢዎች አንዱ የማደንቀው ዲ/ን ዳንኤል ክብረት ነው፡፡ ዳንኤል ክብረት ችጋራችን አረም ነው መፍትሄውም አረሙን መታገል ነው ይለናል፡፡ "አረምን ለማብቀል ሥርዓተ ትምህርት መቅረጽ፣ ዩኒቨርሲቲ መገንባት፣ የፖለቲካ ፓርቲ ማደራጀት፣ ሚዲያ መዘርጋት፣ ብዕርና ወረቀት ማባከን፣ ምስትርናና ዱክትርና መድረስ አያስፈልግም ነበረ፡፡ አረም እንዲሁ ይበቅላልኮ፡፡" ይለናል በቁጭት ይቀጥልናየእድገትና ብልጽግና መስፈርቶችን ይነግረናል፡- "የፖለቲከኞቻችን ብስለት፣ የምሁሮቻችን ብቃት፣ የትውልዱ ምጥቀት፣ የተቋሞቻችን ሥልጠት፣ የሐሳቦቻችን ጥልቀት፣ የሚዲያዎቻችን ፍጽመት፣ የሥልጣኔያችን ርቀት፣ የጥበበኞቻችን ልህቀት የሚታወቀው ባበቀልነው እህል እንጂ ባበቀልነው አረም ብዛት አይደለም፡፡ ለአረምማ እነዚህ ሁሉ አያስፈልጉትም፡፡"(ዳንኤል ክብረት፣ የቀለም ቀንድ ቅፅ 3 ቁጥር 11)

ትምህርት፣ ስልጣን፣ ተቋም፣ ፓርቲ፣ ፖሊሲ፣ እምነት፣ ሚድያና ጥበብ ፍይዳቸው ምንድን ነው? ዳንኤል ክብረት ይመልሳል፡-*"እነዚህ ያስፈለጉት ሲቻል አረሙን ቀድሞ ለመከላከል፣ ካልሆነም የበቀለውን አርሞ እህሉን አህል ለማድረግ ነበር፡፡ ለማስተማር እንጂ ለማደንቆር ምን ትምህርት ቤት ይሻል? ለማዳን እንጂ ለማሳመም ምን ሆስፒታል ያስከፍታል? ለፍትሕ እንጂ ለወንጀል ምን ዳኝነት ያስፈልጋል? ለመግባባት እንጂ ላለመግባባት ምን ቋንቋ ያስፈልጋል? ለልዕልና እንጂ ለውርደት ምን ኪነ ጥበብ ያሻል? ለዓለም ዓቀፋዊ እሴቶች እንጂ ለጎጠኝነት ምን ጥበብ መፍሰስ ያሻዋል? ለማጥገብ እንጂ ለማስራብ ምን ፖሊሲ ያስፈልጋል? ለሥልጣኔ እንጂ ለሥይጣኔ ምን ፓርቲ ማቋቋም ያስፈልጋል? ለጽድቅ እንጂ ለኃጢአት ምን የእምነት ተቋም ያሻል?አሁን ለዚህ ትውልድ ጥያቄው አንድ ነው፤ ለአረሙ እንድከም ወይስ ለእህሉ? እህሉን በማምረት ብርታትህን ታሳያለህ ወይስ አረሙን በማብቀል*

Created in Master PDF Editor

ስንፍናህን? የኢትዮጵያ መልክ የሚቀየረው ለዚህ ጥያቄ በምንሰጠው መልስ ነው።"(ዳንኤል ክብረት፣ የቀለም ቀንድ ቅፅ 3 ቁጥር 11)

ተወዳጁ ዳንኤል ክብረት ሀይማኖት ለሀገር ጎጅ ነው ብሎ ባያስብም በ16ኛው ክፍለ ዘመን በአገራችን ተከስቶ በነበረው የሃይማኖት ጦርነት ጊዜ ከ20 ዓመታት በላይ ገበሬው ተረጋግቶ በእርሻ ላይ ስላልነበር አገሩን አረም ወርሶት እንደነበርና በዚህ ቀውስና የእርስ በርስ እልቂት ከአገራችን ምድር የጠፉ የእህል ዓይነቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ በዚሁ መጽሄት ጽፏል።

ሌላኛው የምጠቅሰውከምክንያት አቅራቢዎች አንዱ <ከማመን መጠራጠር ይሻላል> ነው። የኢትዮጵያን የድህነት መንስኤ እንዲህ ያብራራዋል፦"ለሀገራችን እድገት ፀር የሆነዉን ችግራችን ከብሔርተኝነት በመቀጠል ህዝባችን እጅግ ሐይማኖተኛ በመሆኑና አብዛሃኛዉን ጊዜዉን በሀይማኖት ተቋማት ዉስጥ በማሳለፉ ነዉ። ይሄ ህዝብ እኮ ግማሹ ስራዉን ትቶ በቀን አምስት ጊዜ የሚሠግድ ግማሹ በሳምት ሶስትና አራት ቀናት አዳራሽ ዉስጥ ሀሌሉያ እያለ የሚያጨበጭብ ግማሹ ደግሞ አቦ፣ ጊዮርጊስ፣ ማርያም፣ ገብርኤል፣ ሚካኤል፣ ራጉኤል፣ እያለ ሻማ አብርቶ ታምር የሚጠብቅ አሳዛኝ ህዝብ ነዉ" ይላል። ብዙዎች የ<ከማመን መጠራጠር ይሻላል> ሀሳብ በንዴት የሚያውግዙት በወግ አጥባቂ አማኞች ላይ የተሰነዘረ ትችት ነው። የሚገርመው ብዙ ሙህራንም በድፍረት ሲመሰክሩት ይሰማል። አለማቀፋዊ ምስክርነትም አለው። "The less religious, more secular prosperous nations in the world such as France, Germany, Sweden, Norway, Great Britain, Japan, South Korea and the Netherlands have moved away from sectarianism toward secularism. These countries enjoy a higher standard of living as measured by health care, job security and opportunities for education. The more religious, less secular nations in the world such as Indonesia, The Arab world, and the African nations show the opposite." (atheistscholar.org)

የሚጠቅመን የነገሩን እውነታና ያስከተለውን ቀውስ መመርመር ነው፣ ምክረ ሃሳቦችንም መውሰድ መማር አለብን። ፈላስፋው ወ/ህይወት ስለስራና ስለአኗኗራችን መርህ በሐተታው ምዕራፍ 18 በሚደንቅ አገላለጽ አስቀምጦልን ነበር እንዲህ በማለት፦

> "ልብ እንደሌለው እንስሳም አትድከም፤ ነገር ግን ጥቅምና ትርፍ አንድታገኝና ድካምህም እንዲቀንስልህ ስራህን በብልሃት (በጥበብ) ስራው። እግዚአብሔርም ድካህምን ባርኮ ፍሬውን ባከማቸህ ጊዜ በሙሉ ልብህ አመስግነው። ከቤተ ሰዎችህም ጋር በደስታ ብላ፣ ጠጣ፣ የደስታና የድሎት በዓልም አድርግ። በፍሬ ላይ ፍሬ፣ በጥቅም ላይም ጥቅም እንዲጨምርልህ በስራህ ላይ ጠንክረህ ትጋ። ለኑሮየ ጥቂት ይበቃኛል፤ ለምን እደክማለሁ አትበል። ይህ ክፉ ነገር ስንፍና

Created in Master PDF Editor

ነውና ከቶ ጥቂት ይበቃኛል አትበል። ነገር ግን እስኪቻልህ ድረስ ያለ ዓመፃ ብዙ አከማች። በፊትህ ወዝ፣ በጥረትህም ባፈራኸው ነገር ሁሉ ተደሰት። የፈጣሪያችን ምሳሌውም ትሆናለህ።"(የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 305)

ይህ በተደጋጋሚ በጠኔ ሲገረፍ የኖረው አሳዛኝ ህዝብ ለምን ያ ሁሉ በጫንቃው ላይ አለፈ። በየዘመናቱ ለተነሳው ርሃብና ቸነፈር ታምር ጠባቂነቱና ባዕል አክባሪነቱ እንደምክንያት ይጠቀሱ ይሆን ማለቱ ተገቢ ጥያቄ ነው። ከዚህ አንጻር ለድንግል ማርያም ብቻ 33 ባዕላትን የሚታከብረው የኢትዮጵያ ሀይማኖቶች ፊታውራሪ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ መጠቀስ አለባት። ታምረ ማርያም 33 በአላትን በእመቤታችን ስም ምንም ስራ እንዳይሰራባቸው ይከለክላል። መጻህፉ የሚያዘው33ቱም እንደ እሁድ ሰንበት እንዲከበሩ ነው። 33ቱንም የማያከበሩ መወገዛቸውን አጽንኦት ሰቶታል። ወርቁ ፈቀደ ምን ነበር ያለው?

> *The source of religion is not reason, rather fear and anxiety. That is why many scholars said religion depletes human potency and impedes humans from actualizing both the natural and human world. Fear exerts frustration and desperation, but reason exerts energy and enthusiasm. Hence, throughout human history, religion snatches human freedom and capacity by inducing fear and frustration. To make the above concept more reliable, let me quote from the Ethiopian Orthodox Church scripture, "ራዕይ ማርያም" which instills fear and frustration in the believers mind. It is a type of warning for those people who work on any one of Christian holydays.* It is explained like this: በክርስቲያን በአላት ቀን በማጭድ ያጨደ በእሳት ማጭድ ይታጨዳል በዚህ ቀን ያረሰ በእሳት ማረሻ ይታረሳል (ራዕይ ማርያም 1961 ዓ.ም.) (ወርቁ ፈቀደ፣ 2015፣ የመመረቂያ ጽሁፍ)

አሁን ባለው የቤተ ክርስቲያኗ ዶግሞ በግልፅ ባይቀመጥም በብዓላት ቀን የሚሰራ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ቀሳውስት የተወገዘ ነው። ለዚህ የአርሶ አደር ልጅ ስለሆንኩ ያለፍኩበትን ስለማውቀው በድፍረት እናገራለሁ። አንድ ምስኪን አርሶ አደር 365 ቀን ሰርቶ ራሱን በምግብ ቢችል ምንድን ነው ችግሩ? እባካችሁ በእንጀራ ብቻ አይኖርም እንዳትሉኝ፣ እስካሁን በእንጀራ እንጅ በመንፈስ የኖረ አላውቅም፣ አታውቁምም። በድጋሜ ላረጋግጥላችሁ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያለው ያለቅጥ በወሳኝ የስራ ጊዜ ለቅዱሳን ሲባል ስራ ፈትቶ መዋል አሳዛኝ ነው። እስኪ አስቡት

በ1. ልደታ፣ዮሐንስ፣ራጉኤል፣እዮብ፣ኤልያስ ፣ ሶስና

በ2. በርቶሎሚዎስ፣ጴጥሮስ፣አባ ጉባ፣መሪና

በ3. በአታ ማርያም፣ፋኑኤል፣ዜና ማርቆስ

Created in Master PDF Editor

በ4. ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ፣አባ መቃርዎስ፣ አባ አብርሐ

በ5. ጴጥሮስና ጳውሎስ፣ገብረ መንፈስ ቅዱስ

በ6. ቁስቋም፣ኢየሱስ፣አርሴማ ቅድስት፣እያሱ

በ7. አጋዕዝተ አለም ስላሴ፣ዲዮስቆሮስ

በ8. ኪሮስ፣ማቲዮስ፣ ኪሩቤል አርባእቱ እንስሳ፣ ዘካርያስ

በ9. ሰልስቱ ምዕት፣ ቶማስ፣እስትንፋሰ ክርስቶስ፣አትናትዮስ

በ10. መስቀለ ክርስቶስ፣ናትናኤል ሐዋርያ፣ፀደንያ ማርያም

በ11. ሐና እና ኢያቄም፣አቡነ ሐራ

በ12. ሚካኤል፣ አባ ሳሙኤል፣ ናትናኤል ሐዋርያ

በ13. ፀጋ ኢየሱስ/ ዘርአ ብሩክ/፣ሩፋኤል፣እግዚአብሔር አብ

በ14. አቡነ አረጋዊ፣ገብረ ክርስቶስ/ገብረ መርአዊ/ ዘሚካኤል፣ሙሴ ፀሊም

በ15. ቂርቆስና እየሉጣ፣ሚናስ

በ16. ኪዳነ ምህረት፣ኤልሳቤጥ

በ17. እስጢፋኖስ፣ገሪማ፣ወለተ ጴጥሮስ፣አቡነ በትረ ማርያም፣ ያዕቆብ ወልደ ዘብዲዮስ፣ሙሴ

በ18. ማዕቀብ አልፋ፣ኢዩስጣቲዮስ፣ፊሊጶስ

በ19. ገብርኤል፣ስልስቱ ደቂቅ፣ ይመርሐነ ክርስቶስ

በ20. ዮሐንስ ሀፂር፣ ሕንፀተ ቤተ ክርስቲያን

በ21. ቅድስት ድንግል ማርያም

በ22. ሉቃስ፣ደቅስዮስ፣ኡራኤል፣ ብስራተ ገብርኤል

በ23. ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ

በ24. ተክለ ሐይማኖት፣ጎርጎርዮስ፣24ቱ ካህናተ ሰማይ፣ ክርስረቶስ ሰምራ

በ25. ቅዱስ መርቆሬዎስ፣አቡነ ሀቢብ

በ26. ዮሴፍ፣ ቶማስ ዘህንደኬ፣ አቡነ ሀብተ ማርያም

በ27. መድሐኔአለም፣አቡነ መባዓ ፅዮን ተክለ አልፋማርያም

በ28. አማኑኤል፣ አበው አብርሃም ይህሳቅ ያዕቆብ

በ29. በዓለ እግዚአብሔር (በዓለወልድ)፣ቅዱስ ላሊበላ፣ቅድስት አርሴማ

በ30. ቅዱስ ማርቆስ፣ ዮሐንስ መጥምቅ (ምንጭ፦ ደቂቀ ናቡቴ ድህረ ገፅ)

Created in Master PDF Editor

ባዕላቱ ከቦታ ቦታ በክብር ይለያያሉ:: 30ውን ቀን ያለስራ ማሳለፍ ለሚፈልጉ ግን ሁኔታው ምቹ ነው:: ለአማኞች ቅዱሳንን ማስታወስ የተቀደሰ ተግባር መሆኑ ችግር የለውም ነገር ግን በቅዱሳን ስም ስራ ፈትቶ መዋል ጠኔን መጥራት ነው:: አስቡት መስራት እንዴት የሚወግዝ ተግባር ይሆናል:: እኔ ባደኩበት ደብር ከሁለቱ ሰንበቶች፣ ከአመታዊ የቅዱሳን መታሰቢያና የታምራት ሳምንት በተጨማሪ በ5፣ በ7፣ በ12፣ በ19፣ በ21፣ በ23፣ በ24፣ በ27 እና በ29 የስራ ማቆም አድማ የሚደረግባቸው ቀናት ናቸው:: በእነዚህ ቀናት ብዙ ዘመድ መጠየቅ፣ የተጣላ ማስታረቅ እና የመሳሰሉ መልካም ተግባራት የሚደረጉ ቢሆንም በቀናቱ በስካር መንፈስ የሚፈፀሙት ግጭቶች ግን በክብረ ብዓላቱ ጥቁር ታሪኮችን እንዲፈጸሙ ሁኗል::በድብቅ ሲሰራና ሲያስራ የተገኘ ገበሬም መዛባባቸና የተወገዘ ይሆናል:: በረዶ፣ አንበጣ፣ ትል፣ ጎርፍ፣ እና ሌሎች ተፈጥሮአዊ ችግሮች ካጋጠሙ ለሃጢያን የመጣ ለጻድቃን ይተርፋል እየተባለ ይተረትበታል::

ለዚህ ነው <ከማመን መጠራጠር ይሻላል>*“ታድያ ይሄ ህዝብ በየትኛዉ ጊዜ ስራ ሰርቶ፣ ነግዶና ተምሮ ሀገሩን አና እራሱን ይቀይር? ድህነቱን በእግዚያብሄር ፈቃድ የተሠጠዉ ስጦታ አስመስሎ አሜን ብሎ የተቀመጠና ስራ ሰርቶ የተሻለ ኑሮ መኖር እየቻለ ለዘለላለም ወደ ሰማይ እያንጋጠጠ ፍርፋሪ የሚለምን ህዝብ እንዴት ሀገር ያሳድጋል”* የሚለው:: እኔም <ከማመን መጠራጠር ይሻላል>ም እያልን ያለው ህዝቡ ሰነፍ ነው ሳይሆን ሀይማኖት ጊዜውን ተሻምቶታል ነው::በየትኛውም ሀገር ያሉ ወግ አጥባቂ አማኞች አሳዛኝና ከተፈጥሮ የሸፈቱ ናቸው:: አብዛኛውን ጊዜአቸውን የሚያሳልፉት አንድን ነገር ደጋግሞ በማድረግ ነው:: ሁሌ ስለመለወጥ፣ ያለፈውን ስለመሻርና ስለ አዲስ ህይወት ቢጸልዩም ህይወታቸው ካለበት ፈቀቅ አይልም:: አንድ ሰው የቅዱስ ያሬድን መፅሃፍት በቃል ሽምዶ እድሜ ዘመኑን ሲያነበንብ ከሚኖር መጽሃፍቱን ተረድቶ በቀሪ ጊዜው ሌሎች መፅሃፍትን ቢያነብ የተሻለ የመረዳትና የፈጠራ ችሎታ ይኖረው ነበር:: አንድ ሰው እድሜ ዘመኑን ዳዊት ተሸክሞ ከሚዞር ከዳዊት በተጨማሪ ሌሎች መጽሃፍትን ያካተተ መለስተኛ ቤተ መጸሃፍት ቢኖረው መልካም ነበር:: ለሁሉም ቦታና ጊዜ የሚሰጥ ሰው ወግ አጥባቂ አይሆንም፣ ወግ አጥባቂ ካልሆነ አክራሪ የመሆን እድሉ ዝቅተኛ ነው፣ አክራሪ ካልሆነ ደግሞ ሰብአዊ መብት ይገባዋል፣ ሰብአዊ መብት ከገባው አያሸብርም፣ አሸባሪ ካልሆነና የሌሎችን የመኖር ነጻነት የማይነፍግ ከሆነ ያ ሰው ሰው ሆነ ማለት ነው:: ሙህራን እንደሚሉት በየትኛውም አስተሳሰብ ከሚገባን በላይ ከተጠመድን ከሰውነት ወጥተን አካራሪና አሸባሪ እንሆናለን:: በዚህ ጉዳይ ብሩህ አለምነህ እንዲህ ይላል፦

> በታሪክ ዘመናት ሁሉ ሃይማኖትና ፖለቲካ የአክራሪነት ምንጮችና አቀጣጣዮች ሆነው ታይተዋል:: ሃይማኖት ሰውንና ህብረተሰብን በስነ-ምግባር የማነፁን ያህል ሰብዓዊነት አድማሱ እንዳይሰፋ፣ ሁለንተናዊነትም የምደር ሰው ሁሉ መገለጫ

Created in Master PDF Editor

> እንዳይሆን ጠፍሮ ይዞናል። ተመራማሪነትንና የአስተሳሰብ ነፃነትን በመጋፋት ሰውን ለረጅም ዘመናት በድንቁርናና በድህነት እንዲኖር አድርጓል። ፍቅርንና ጋብቻን በተከታዮቻቸው መካከል ብቻ እንዲወሰን በማድረግ፣ እርድንና አመጋገብን ሃይማኖታዊ ድባብ በማላበስ ሰው ሁሉ በማእድ ፊት እኩልና በጋራ እንዳይቀርብ በማድረግ፣ ሙዚቃ የሰው ሁሉ ተፈጥሮ መሆኑን እንዳንገነዘብ፣ አንደኛው ሃይማኖት ሌላኛውን ሃይማኖት የሲኦል መግቢያ በር አድርጎ በመሳል ለተከታዮቻቸው የሚያስተምሯቸው ትምህርቶች ሁሉ ለአክራሪነት መደልፊያ ከማገልገላቸውም በተጨማሪ የፍቅርን፣ የወሲብን፣ የውበትን፣ የሰብዓዊነትንና፣ የመመገብን፣ የሙዚቃን፣ ወንድማማችነትን፣ ሁለንተናዊነትንና ተፈጥሯዊነትን ባለመገንዘብ፣ እውቅና ባለመስጠትና በማንቋሸሽ ሃይማኖት የሰውን ተፈጥሮ ተጋፍቷል። ስለዚህ የሃይማኖት አክራሪነት ይውደም! አክራሪ ኦርቶዶክስነት፣ አክራሪ ፕሮቴስታንትነት፣ አክራሪ ሙስሊምነት ሁሉ ይውደም፣ **ተፈጥሮን ከሃይማኖት በላይ ለማድረግ፣ ሰውነትንም ከሃይማኖት በላይ ለማንገስ** የሃይማኖት አክራሪነት ይውደም! (ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣28)

ይህ የብሩህ መፈክር በአደባባዮችና በሚድያዎች አይራግብ እንጅ ትልቅ የለውጥ ጥሪ ነው። በእያንዳንዳችን በጥቂቱም ቢሆን የአክራሪነት መንፈስ አድሮብናል። አክራሪ አይደለሁም ማለት እና አክራሪ አለመሆን ይለያያሉ። ተፈጥሮን ከሃይማኖት በላይ ለማድረግና ሰውነትንም ከሃይማኖት በላይ ለማንገስሁለገብ አስተሳሰብ ልናዳብር ይገባናል። ብሩህ ሀይማኖተኛ ይመስለኛ ይመስለኛል እያወገዘ ያለው ሀይማኖትን ሳይሆን አክራሪ ሀይማኖተኞችን ነው። አክራሪ ሀይማኖተኞች ለሰለምና ልማት እንቅፋቶች ናቸው፣ አክራሪ ሀይማኖተኞች ለውይይትና ክርክር ጆሮአቸው የተደፈነ ነው፣ የሚያስቡት በገጀራቸውና በጡንቻቸው ነው። እንዲህ በደነደነ አስተሳሰብ አጥር ከመታጠር እድሜ ልክ መታሰር ይሻላል።

ብሩህ ፍቅርንና ጋብቻን እንዲህ ያነግሰዋል፦ “ፍቅርንና ጋብቻን የፈጠረ አምላክ በእናንተ ፍቅር ይነግሳልና ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ እየተፋቀራችሁ ተጋቡ፤ ሃይመናታችሁን ዘላችሁ ፍቅርም ሆነ ጋብቻ እንዳትመሰርቱ የሚል ትዕዛዝ ፍቅርን ከፈጠረ አምላክ የተሰጠ ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔር በፍቅር ገደብ የለሽነት ይደሰታል እንጂ እናንተ እንደምታስቡት ፍቅርን በመገደብ አይከብርም።” የክርስቲያን ስጋ ቤት፣ የሙስሊም ስጋ ቤት፣ ወዘተ ለሚሉት ብሩህ አለምነህ እንዲህ ይላቸዋል፦“መመገብን የተገባ አድርጎ በምግብ የሚኮንን አምላክ የለንምና የክርስትያን፣ የሙስሊም ሳትሉ ለጤናችሁ የሚስማማውን ምግብ ሁሉ ፈላስፋው ዘርዓያዕቆብ እንዳለው በአንድነት ተመገቡ።”የብሩህ ልብ የሚነካ ምክር አሁንም ይቀጥላል፦

Created in Master PDF Editor

ሙዚቃንና ዳንስን ተፈጥሯዊ ባህሪያችን አድርጉ፣ በሙዚቃና በዳንስ የሚኮንን አምላክ የለንምና ዝፈኑ፣ ደንሱ። ስትደንሱ ትደሰታላችሁ፣ ስትዘፍኑም ጥልቁ ተፈጥሯችሁ ውስጥ ትገባላችሁ። ሙዚቃ እና ዳንስ ልክ እንደ ወሲብ፣ አካልና ከአምሮ ፍፁም የሚዋሃዱበትና ከመላው ዩኒቨርስ ጋርም ኅብረት የሚፈጠርበት ክስተት ነው። እግዚአብሔር ምን አይነት ጥልቅ ተፈጥሮ ውስጣችን እንዳስቀመጠ ማወቅ የምትችሉት በመመሰጥ አሊያም በሙዚቃ መሪነት ነው። ስለዚህ ሙዚቃን ኃጢያት አታድርጉት። ወደ ኃጢያት የማይመራችሁን ጥልቅ ሙዚቃዎች ሁሉ ያለጥርጣሬ በደስታ አዳምጧቸው፤ አብራችሁም አንጎራጉሩ። የሙዚቃን ውበት፣ የሙዚቃን ሃይል አድንቁ እንጂ የሃይማኖት አባቶቻችሁ እንደነገሯችሁ ሙዚቃን አታውግዙ። ፍቅርን በስዕል መግለፅ ኃጢአት አይደለም ፍቅርን በስጦታ፣ በግጥም በቃላትና በመሳም መግለፅ አልተከለከለም፤ ታዲያ ፍቅርን በሙዚቃ መግለፅ ስለምን እንደ ኃጢያት ይቆጠራል።

ብሩህ አሁንም ይቀጥላል፦

እኔ እንኳን ሙዚቃ አዳምጡ የምላችሁ ሙዚቃ ተፈጥሯችን ስለሆነ ነው፤ እናንተ ግን ሙዚቃን የምታወግዙት ከምን ተነስታችሁ ነው? መዝሙር የተገባ፣ ዘፈን ግን ያልተገባ ነው የሚለው አባባል በጣም ያናድደኛል። ማንኛውም ህብረተሰብ በየትኛውም ዘመንና አካባቢ የሚኖር ህዝብ ሁሉ ሙዚቃ አለው፤ ይዘፍናል፣ ይደንሳል። ሲደሰት፣ ሲያፈቅር፣ ሰውና ሀገር ሲናፍቀው፣ አምላኩን ሲያስብ፣ ሲተክዝ፣ ብሶት ሲሰማው .... ወዘተ ይዘፍናል። ይዘምራል፣ ያንጎራጉራል። ሙዚቃ ተፈጥሯችን ካልሆነ በስተቀር ሁሉም ሰው ሊጠቀምበትና ሊደሰትበት አይችልም። ተፈጥሯችን ውስጥ ጥልቅ የሆነ የህይወት ሚስጥር አለ፤ ሰው ሁል ጊዜ በእለተለት ኑሮው ስለሚጠመድ የአእምሮው ጥልቅ ተፈጥሮ ውስጥ ምን እንዳለ አያውቅም። ሚስጢራዊውን የህይወት ተፈጥሮ ለመገንዘብ ከእለተለት የወከባ ኑሮ ሰክን ብሎ ወደ ውስጥ ብቻ ማሰብ ያስፈልጋል። ጥልቁ ተፈጥሯችን ውስጥ አክራሪነት ሳይሆን ሰብአዊነትና ሁለንተናዊነት ነው ያለው። ፍቅር፣ ርህራሄ፣ እውነት፣ ወይም ሙዚቃዎችን ስትከታተሉ የምታለቅሱ ከሆነ ጥልቁ ተፈጥሯችሁ ውስጥ ደርሳችሁ የመመለሳችሁ ምልክት ነው። እናም ሙዚቃ ወደ ጥልቁ ተፈጥሯችሁ የምትሄዱበት መንገዣ ነው። ሆኖም ግን ሁሉም ሙዚቃዎች አይደሉም እንደዚህ አይነት ሃይል ያላቸው፤ የተወሰኑት እንጂ። ተፈጥሮን መቀስቀስ የሚችሉ ዜማዎች አሉ። ህይወታችሁን በእነዚህ ዜማዎች አበልፅጉት። (ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣29-32)

ከ<ከማመን መጠራጠር ይሻላል> በተጨማሪም ብሩህ ሀገራችንን ድሃ ያደረጋት ህዝባችን እጅግ ሐይማኖተኛ በመሆኑ የተስፋፋው ከፍተኛ ክርስትና በሚባለው ምንኩስና ነው ይላል፡፡

> “በምንኩስና ውስጥ ነግዶ ማትረፍ፣ ሰርቶ መበልፀግ፣ አምሮ መታየት ከንቱ ነው፤ በአለማዊ እውቀት መራቀቅም ሆነ በፈጠራ ክህሎት ልቆ መገነት እርባና ቢስ ነው፡፡ ምንኩስና ማዕቀብ የሚጥለው የግል ሀብትና ንብረት ላይ ብቻ አይደለም፡፡ ይልቅስ አመጋገብና አለባበስ ላይ፣ የወሲብና የውበት ስሜቶች ላይ፣ ጋብቻና ማህበራዊ ህይወት ላይም ጭምር ነው፡፡ አባ አንጦንስ ከልብ ስንራብ፣ ስንጠማ፣ ስንራቆት፣ ስናዝን፣ በጣር ላይ ስንሆን፣ ለእግዚአብሔር የተገባን እንሆናለንለ፡፡ እግዚአብሔርን እንድናገኘው ሐዘንን እናስቀድማት፤ ነፍሳችን እንድትድን ሥጋችንን እንጣላት ሲሉ አማኙን ይምክራሉ፡፡ ተፈጥሯችን ግን የሚያዘን የላመና የጣመ እንደንመገብ እንጅ ከፆም ብዛት የተነሳ እንድንጠወልግ አይደለም፡፡ በጋብቻ ህይወት እንድንኖር እንጅ በጭናችን እሳት ቋጥረን እንድንቃጠል አይደለም፡፡ በማህበራዊ ህይወት እንድንኖር እንጅ ከሰው ተነጥለን በብቸኝነት እንድንማቅቅ አይደለም፡፡” (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 41-42)

<ከማመን መጠራጠር ይሻላል> በውጭው አለም በተለይም በመካከለኛው ምስራቅ ያሉ ሶቆቃወችን እንዲህ ይገልፃቸዋል፡-

> “የእስልምናን የበላይነት እናረጋግጣለን ብለዉ የተደራጁት መንጋወች በየ ጊዜዉ በሚያደርሱት የሽብር ድርጊት ያደረሱት ጥፋት ቀላል አይደለም፡፡ እነሱ ያን ሁሉ ሽብር ሲያደርሱ የእስልምና ተከታዮችንና እስልምናን ከፍ የሚያደርጉ መስሏቸዉ ነበር፡፡ እስልምናን እንወክላለን የሚሉት መንጋወች ጥፋት ማስከተል ከጀመሩ ወድህ አለም ሙስሊሞችን (በተለይ አሜሪካ) የምታስተናግድበት መንገድ የተለየ እንድሆን አድርገዉታል፡፡ ለምሳሌ ያህል በቅርብ ጊዜ የተፈጠረዉ ISIS በሚያስከትለዉ ጥፋት ለእስልምና ተከታዮች ያተረፈዉ ነገር ቢኖር ስቃይ ብቻ ነዉ፡፡ በኢራቅ፣ በሶሪያና በየመን ያሉ ሙስሊሞች ለርሀብ፣ ለስደት፣ ለአካል መጉደልና የሞት አደጋወች እንዲደርስባቸዉ ያደረገዉ ይኸዉ መንጋ በጀመረዉ ጥፋትና ጥፋቱን እናስቆማለን በሚሉ ሀያላኖች ነዉ፡፡ ቤት ንብረታቸዉ የወደመባቸዉ፣ እናት አባት፣ እህት ወንድሞቻቸዉን በሞት የተነጠቁ ግለሰቦች በስደት መልክ ወደ ተሻለ ሀገር ገብተዉ እንዳይኖሩ እገዳ የተጣለባቸዉም ይኸዉ መንጋ በሚያስከትለዉ ጥፋት ነዉ፡፡ ይህ መንጋ ወደፊትም ብዙ ጥፋቶችን ባስከተለ ቁጥር የብዙ ሙስሊሞች ህይወት እየተመሰቃቀለ ይሄዳል፡፡”

Created in Master PDF Editor

15. God Is Not Great, but Christopher Hitchens

(with Richard Dawkins, Sam Harris, Charles Darwin, Carl Sagan, Michael Shermer, Lawrence Krauss, James Randi, Thomas Paine, A C Grayling, Derren Brown, Daniel Dennett, George H. Smith, Lemuel K. Washburn, David Hume, Karl Marx, Robert G. Ingersoll, Friedrich Nietzsche, Sigmund Freud, Madalyn Murray O'Hair, Bertrand Russell, Beloved Master Osho, Salman Rushdie, Armin Navabi, Douglas Adams, Ibn Warraq, Dan Barker, Stephen Hawking, Dr Einstein, Sean Carroll, John Loftus, Eric MacDonald, Steve Pinker, John Brockman, Galileo Galilei, Auguste Comte, Spinoza, Richard Carrier, Penn Jillette, Bill Maher, David Silverman, Michel Onfray, Christopher Mallard, Isaac Asimov, Mark Twain, Brian Greene, Ernest Hemingway, Denis Diderot, Neil deGrasse Tyson, Jerry A. Coyne, Hemant Mehta, Steve Wells, Darrel W. Ray,Guy P. Harrison, Arius (myself), Marshall Brian, Ayana Arsi Ali…and many more)

ከላይ ስማቸው የተዘረዘሩት ሳይንቲስቶች፣ ፈላስፎች እና ፅሐፊዎች ሕይወታቸውን ለአመኑበት ለገባቸው እወነት የተሟገቱ ናቸው፡፡ የፃፏቸው መፅሐፋትና የስሯቸው ምርምሮች የአለምን የአስተሳሰብ አድማስ አስፍተዋል፡፡ በተለይ እንዳንዶቹ ሕይወታቸውን አደጋ ላይ በመጣል እስከ መጨረሻው ዘምተዋል፡፡

አለም ብዙ የጨለማ ዘመናት አሳልፋለች፡፡ ይህ የጨለማ ዘመን አንድ መንገድ፣ አንድ ፖለቲካ፣ አንድ ሀይማኖት ብቻ መኖር የግድ ነው በሚሉ የሰይጣን ልጆች የተጠነሰሰ ነው፡፡ በእርግጥ የሚቻል ከሆነ አንድ መንግድ፣ አንድ የፖለቲካ ስርዓት አንድ ሀይማኖት ቢኖር መልካም ነው ግን አንድነት ለማምጣት ሲባል ልዩነትን መጨፍለቅ አግባብ አይደለም፡፡ አለማችን ባሳለፈቻቸው የጨለማ ዘመናት እንደሻማ እየቀለጡ የበሩ ፈላስፎች፣ ሳይንቲስቶች እና የሐይማኖት ሊህቃን (የበራላቸው) ዘመን የማይሽረው ለውጥ አስመዝግበዋል፡፡

የበራላቸው ሳይንቲስቶችና ፈላስፎች በወታደሮቻቸው ብዛትና ባከማቹት የጦር መሳሪያ ከሚመኩት ፖለቲከኞች እና <ና> ሲሉት በሚመጣው ሂድ ሲሉት በሚሄደው ምስኪን ህዝብ ከመመከት ጳጳሳት ጋር ፊት ለፊት ተፋጠዋል፡፡ እውነትን ሊሸፈኗት ይችሉ እንደሆነ እንጅ ሊያጠፏት አይችሉም፡፡ መሬት ክብና ማለት ሀጢአት ነበር፡፡ መሬት በፀሐይ ዙሪያ የምትዞር እንጅ ፀሐይ በመሬት ዙሪያ የምትዞር አይደለችም ማለት በሞት የሚያስቀጣበት የድንቁርና ዘመን አልፏል፡፡ ልብ ላለው ሰው መሬት በፀሐይ ዙሪያ ወይም ፀሐይ በመሬት ዙሪያ የሚለው እኩል አስተሳሰቦች ናቸው፡፡ እውነቱን ማረጋገጥ የሚቻለው በምርምር ነበር ነገር ግን የሮም ሊቃውንት ይህን አልፈለጉም በቅርቡ ንስሀ እስከገቡበት ጊዜ ድረስ፡፡

Created in Master PDF Editor

ግለሰቦች አለምን የመቀር ስልጣን አላቸው። አንድ ብሩህ ግለሰብ አለም ወደ ታላቅ ከፍታ ሊያመራት ይችላል። በተለይ በሳይንስና ቴክኖሎጅ የአንድ ግለሰብ ቅንጭላት የሰውን ልጅ ሕይወት በአጭር ጊዜ ሊለውጥ ይችላል። (የማጥፋትም ዕድል አለው)። ብዙዎች የሳይንስና የፍልስፍና ፈርጦች በጊዜያቸው መሳቂያ መሳለቂያ ብቻ ሳይሆን ጊዜ የሰጠው ሁሉ በትሩን የሚያሳርፍባቸው ተራ ግለሰቦች ነበሩ። ደስ የሚለው ነገር ሕዝብ እውነት እያደረ ሲገባው ንስሀ ይገባል። መሪዎቹ ባደረሱት ጥፋት ይፀፀታል። ለዚህም ነው በክፉ አሟሟት በግፍ ለተገደሉት ፈርጦች የማስታወሻ ሀውልት የሚሰራላቸው። ባለጊዜዎች ጃርዳይ ቡርኖን በእሳት ሲያቃጥሉት እውነት የምትቃጠል መስሏቸው ነበር ቡርኖም የሚረሳ መስሏቸው ነበር። ቡርኖን ያልረሰው ትውልድ ግን ስለ ሳይንስና ስለ ነፃ አስተሳሰብ አስተዋፅኦው በተቃጠለበት አደባባየ “አስቀድሞ ካየው ትውልድ በሳት ተቃጥለህ ከሞትክበት ቦታ” የሚል ማስታወሻ አስፍሯል።

የብዙ ሰዎች በሽታ ተቃርኖን መፍራት ነው። በተለይ በኢትዮጵያ መንግስታቶቻችን ሳይቀር 100% የፖርላማ መቀመጫ በአንድ ፖርቲ ተይዞ ያለና የነረ ስለሆነ አሁን አሁን ጥያቄዎችና ክርክሮች ሲደረጉ ይገርመናል። ፖርላማው በገዥና በተቃዋሚዎች ሲሞላ ሊኖር የሚችለው ክርክር ይናፈቀኛል። ያኔ እወነት እና መንግስት ፊት ለፊት የሚጋፈጡበት ጊዜ ነው። ሊዚያ እንዳያበቃን ግን በቤታችን እስከ ሀገራዊ ጉዳዮች ድረስ ተቃርኖን መለማመድ አለብን።

እኔ ኤቲስቶችን የማድንቅበት ዋነኛ ምክንያት ለተቃርኖ በራቸው ክፍት ነው። የብዙ ኤቲስት ማፅሀፍትን ሳነብ እንዳስተዋልኩት አንድ የሚጋሩት ቃል አለ አሰማኝ ነገር ከገየሁ ከዚያን ቀን ጀም አማኝ እሆናለሁ። እኔም ሁሌም የምለው ይሄን ነው። አቅሜ በፈቀደ መጠን ለተቃርኖ አስሣሰቦች የተጋለጥኩ ነኝ። ለዚያ ያበቃኝ አንድ ብቸኛ መንገድ ብቻ አለ ያም እኔ የማምነው ነው ብየ ባለማመኔ ነው። የምመካበት አስተሳሰብ ቢኖረኝ ይሄ ነው። ይህን አስተሳሰብ እንዳዳብርና ሁሌም እራሴን ለተቃርኖ ክፍት ህሉና እንዲኖረኝ የረድኝን ጠበብቶች አመሰግናለሁ። ክርስቶፎር ሂችን እና ጓድኞቹ የፃፏቸው መፅሐፍቶች እንዳምንባቸው እና ከትዕዛዛቸው እንዳልወጣ ሳይሆን እንዲህም አይነት አስተሳሰብ አለ ብየ እንድረዳና የራሴን መንገድ እንድቀይስ ነው። እኔ እስከሚገባኝ የሀይማኖት ስብከቶች አሳ እንደመስጠት ሲሆን የኤቲስት መፅሐፍቶች ግን የአሳ ማስገሪያ እንደመስጠት ነው። በርሃብ ለሚገኝ ሰው አሳ ከአሳ ማስገሪያ የተሻለ ቢመስልም ዘላቂነት ግን አይኖረውም። በተለይ በአለፊት 20 አመታት በተቀጣጠለው የNew Atheism እንቅስቃሴ ወቅት የተፃፈ ተፅዕኖ ፈጣሪ መፅሀፍት ተቃርኖዎችን በመተንተን እና አማራጭ ሐሳቦችን በማቅረብ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ጽሐፊዎቹ በግላቸውና በጠቅላላው በሰው ልጅ ያለውን የእውቀት ውስንነት አምነው የተነሱ ናቸው። የአወቁትን ሚስጢርና የተረዱትን እውነት ግን በፍርሃት ሊደብቁን አልፈለጉም። ይህን ለመረዳት Richard Dawkins,

Created in Master PDF Editor

Sam Harris, Michael Shermer, Lawrence Krauss, AC Grayling, Daniel Dennett, Armin Navabi, Ibn Warraq, Dan Barker, John Loftus, Richard Carrier, Steve Wells, Darrel W. Ray, እና Guy P. Harrison የጻፏቸውን መጽሃፍት መቃኘት በቂ ነው።

ሀልወተ እግዚአብሔርን መጠራጠር ይልቁን ፈጣሪ የሚባል ነገር እንደለለ መተንተን የተጀመረው ከሀይማኖት መፈጠር ጋር ተያይዞ እንደሆነ የታሪክ ጽሃፍት ይመሰክራሉ። በታሪክ በሚታወቁት ቀድምት የኤስያ፣ የአውሮፓ፣ የአፍሪካና የደቡብ አሜሪካ ስልጣኔዎች ውስጥ እንዲሁም በመካከለኛውና በዘመናዊ የአለም ታሪክ ውስጥ ኢ-አማኝና ተጠራጣሪ ሳይንቲስቶች፣ ፈላስፎችና ሙህራን ጉልህ ታሪክ ሰረተዋል። ጥቂቶች ለሰሩት ታሪክ ስማቸው ከመቃብር በላይ ቢሆንም አብዛኛዎች ግን ህይወታቸውና ስራቸው በአረመኔዎች ተቃጥሏል።

በዚህ ዘመን ጎልቶ ለሚንጸባረቀው ኢ-አማኝነት እድገትና በራስ የመተማመን መንፈስ በርካታ ታላላቅ የሳይንስ፣ የፍልስፍና እና የስነ ጹህፍ ፈርጦች ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል። እንደ ሰው ኑረው እንደሰው ለሞቱት RIP እያልኩ በህይወት ላሉት ደግሞ ምስጋናየን አቀርባለሁ። ታላቁን እግዚአብሔር የሚያስንቅና የሚገዳደር ስራዎችን አከናውነዋልና ስለድፍረታቸው፣ ስለከፈሉት ዋጋ መታወስ አለባቸው። እግዚአብሔር ከላይ በተዘረዘሩት ሰዎች እይታ ተራ ልብ ወለዳዊ ስነ ጹህፍ ነው። አማኞች የሚመኩበት የክብር ክብር የሚሰጡት የሰራዊት ጌታ እንደተራ ነገር መጠርጠሩ ይገርማል። ልዩነቱ ሰፊ ነው። ኢ-አማኞች እንደትረት የሚቆጥሩትን አካል አማኞች መወድስና ፋከራ ያቀርቡለታል።

> *"እምነት ሙሉ የሚሆነው ከመለኮታዊ አሳብ ጋር በመስማማት ብቻ ሳይሆን ስንመካበትና ስንፎክርበትም ነው። እግዚአብሔር የሚያስመካና የሚያስፎክር አምላክ ነው። እግዚአብሔር፦ ለጠሩት የሚደርስ፣ ለፈለጉት የሚገኝ፣ በእሳት የሚመልስ፣ ደመና ጠቅሶ ባሕር ተራምዶ የሚፈጥን፣ ያመኑትን የሚታደግ፣ እሳቱን ማጥፋት የሚችል፣ እሳቱ እያለም የመግደል አቅሙን የሚወስድ፣ የአንበሶችን አፍ የሚዘጋ፣ እልፍ አእላፋት ሠራዊትን የሚበትን፣ ኃያላንን ሣር የሚያስግጥ፣ ብርቱዎች ነገሥታትን በባሕር የሚያሰጥም፣ በማይታይ መሣሪያው ሲጥል የሚታይ፣ በማይታይ መንግሥቱ የሚታዩ ተራሮችን የሚያፈርስ፣ ለሕዝቡ የሚዋጋ፣ አፍሮ የማይገባ፣ የድምፅ አልባዎች አንደበት፣ የምስኪኑ ሞገስ ነውና በርግጥም ያስመካል።"* (http://betelhemm.blogspot.com/)

ይህ ጉደኛ ጦማር ጭራሽ የእግዚአብሔር ታላቅነት በታሪክ ከምናውቃቸው የጦር ጀነራሎች እያነጻፀረ ይተርክልናል። እስኪ ስሙት፦

Created in Master PDF Editor

“ሰዎች በሰዎች ተደግፈው ይፎክራሉ። የምኒልክ ባሮች፣ እኔ የአባ ዳኘው አሽከር፣ የኃይለሥላሴ ባሮች፣ እኔ የአባ ጠቅል አሽከር እያሉ ይፎክራሉ። ትልቁ አባ ዳኘው፣ ትልቁ አባ ጠቅል፣ ትልቁ አባ መላ፣ ትልቁ አባ ታጠቅ የሰማዩ ጌታ እግዚአብሔር ነው። አባ ዳኘው ሆኖ ከከሳሻችሁ የገላገላችሁ ተናገሩ? አባ ጠቅል ሆኖ ሁሉ ተክቶ የቆመላችሁ የት ናችሁ? አለሁ በሉ። አባ መላ ሆኖ መንገድ ያሳያችሁ ምነው ዝም አላችሁ? አባ ታጠቅ ሆኖ የዘመተላችሁ አለሁ በሉ ተናገሩ፣ ይህን ካልተናገራችሁ አንደበታችሁ ለመቼ ይሆናል? ሰው በሰው እንኳ ከፎከረ እግዚአብሔር ይበልጥ የሚያስመካ የሚያስፎክር አምላክ ነው። ትላንት የገዙ ዛሬም የሉም፣ ትላንት ያዘዙ ዛሬ ጥርኝ አፈር ሆነዋል፣ ትላንት ግርማቸው የሚያስደነግጥ ዛሬ ታሪክ ሆነዋል፣ ትላንት ባለፉበት መንገድ የሚሰገድላቸው ዛሬ ተወቃሽ ሆነዋል። እግዚአብሔር ብቻ ሳይለወጥ፣ ሳይናወጥ ለዘላለም ፀንቶ ይኖራል። የሚያስመካ የሰማዩ ጌታ ብቻ ነው።” (http://betelhemm.blogspot.com/)

ይህ ሁሉ ሰዋዊ እና ሰማያዊ መወድስ የሚቀርብለትን አምላክ የሚገዳደርና ጥያቄ የሚፈጥር ሰው መኖሩ ባራሱ ግርምትን ይፈጥራል። ግለሰባዊ እውነታን (አንድ ሰው ክቦና ክብክቦ የያዘውን ሃሳብ) ሌላኛው ተነስቶ መሰረተ ቢስ ሊያደርገው ይችላል። ሀይማኖቶች ግለሰባዊ እውነቶች ናቸው። ከትችት በመጠኑ የሚርቁት ነባራዊ ሃቅ ቢሆኑ ኑሮ ነው። ግለሰባዊ እውነቶች፣ መገለጦችና አረዳዶች አሜን ብሎ በሰሚ ሰሚ ለማያምን ሰው ጥያቄዎች ያስነሳሉ።

እኔ እስከሚገባኝ ክርስቶፈር ሂችንና ዳውኪንስን መሰል ኤቲስቶች አንድ የሚያደርጋቸው የጋራ ባህሪ አላቸው። ያም “Question Everything” የሚለው የህይወት ዘመን መመሪያ ነው። ይመለስም አይመለስም ከጥያቄ ነፃ የሚወጣ ምንም አይነት ጉዳይ የለም። በነፃ አዕምሮ ባለቤቶች ዘንድ ለማሰብና ለመጠየቅ እርም የሆነ ነገር የለም።

የነፃ አስተሳሰብ አራማጆች የራሳቸው ነፃ መውጣት ብቻ በቂ ስላልሆነ በርካታ ጥረቶችን ሲያደርጉ ይታያል። ለእኔ የእነዚህ ሰዎች ትግል ለአለም ከተተበተበችበት የዛገ የብረት እስራት ነፃ ያወጣታል የሚል ተስፋ አለኝ። በርካታ የብረት ሰንሰለቶች ተሰብረዋል፤ በዶግማቲካ መመሪያ የተሰሩ የመመለያ ግንቦች ፈርሰዋል፣ የቅኝ ግዛትና የባሪያ ንግድ ሰንሰለቶች ተበጥሰዋል ወዘተ። ስለዚህ አሁን በዋናነት የቀረን ሳናውቀው የጎዳን ነቀርሳ ዶግማቲካ አስተሳሰብ ነው። ይህን አስተሳሰብ የበላይነቱን በነፃ አስተሳሰብ ለመተካት ሰፊ ጥረት እንደሚያስፈልግ የነፃ አስተሳሰብ አረማጆች ያውቁታል። ምክንያቱም ሰዎች በተፈጥሮ የያዙትን አስተሳሰብ መተው አያወዱም በተለይ ደግሞ አዲስ አስተሳሰብ ለመቀበል ይፈራሉ። ይህ በበርካታ ምርምሮች

Created in Master PDF Editor

የተረጋገጠ ነው፡፡ ቢሆንም ግን በጊዜ ብዛት የመረጃ አቅርቦትም ተጨምሮበት ሁኔታዎች ይቀየራሉ፡፡

ማንም አስተሳሰብ በአንድ ጀንበር ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ክርስትና ከ2 ቢሊዮን በላይ ተከታይ ያፈራው በአንድ ጀንበር ስብከት አይደለም ብዙ መራራ ትግል እና ትዕግስትን ጠይቋል፡፡ ካፒታሊዝም በበርካታ ሀገራት የሚቀነቀነው ብዙ እልህ አስጨራሽ ትግሎችን አልፎ ነው፡፡ የሴቶች የእኩልነት መብት ብዙ ዋጋ ተከፍሎበታል፡፡ ቅኝ ግዛትን ለማስቀረት ሚሊዮኖች እራሳቸውን ለእውነት አሳልፈው ሰጥተዋል፡፡ በአለም የሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲረጋገጡ ያልተከፈለ ዋጋ የለም፡፡ ደስ የሚለው "መሀሉ ባይነገርም" ውጤቱ ግን ያማረ ፍሬ ነው፡፡ ዛሬም ብዙ የመብት ጥሰት ቢኖርም ከትላንት ግን በእጅጉ የተሻለ ነው፡፡ ነገ ደግሞ ከዛሬ የተሻለ እንደሚሆን አምናለሁ፡፡

16. **ብዛኞቹ ሳይንቲስቶች አምላክ የለሾች መሆናቸው**

ከእውታው ከምንረዳው በተጨማሪ በርካታ ጥናቶች እምነትና ትምህርት ተቃራኒ ዝምድና እንዳላቸው፡፡ ለምሳሌ 93% የአሜሪካው ብሔራዊ ሳይንስ አካዳሚ (National Academy of Science) አባላት አምላክ የለሾች ናቸው፡፡ በተለይም በተፈጥሯዊ ሳይንስ ውስጥ እንደ ኬሚስትሪ፣ ፊዚክስ፣ ጅኦሎጅ፣ አስትሮኖሚ እና ስነ-ህይወት ባሉት መስኮች ከዚህም ይልቃሉ፡፡

በእነዚህ አና በሌሎች ምክንያቶች እምነትን ከሳይንሳዊ እውነታዎች ጋር ማስታረቅ አይቻልም፡፡ ደግሜ እለዋለሁ ሳይንስና ሃይማኖት እዴትስ ይታረቃሉ? ቢቻል መጀመርያ ሀይማኖቶች እርስ በርሳቸው ይታረቁ ከዚያ ሳይንስና አንድ ሃይማኖት ወደ ድርድሩ ይሄዳሉ፡፡

በአጭሩ እያንዳንዱ ግለሰብ ሦስት አማረጮች አሉት፡፡ አንደኛ ቀድሞ የተገኘዉን እና ከሽ አመታት በፊት የተፃፈውን ማመን ነው፡፡ ሁለተኛ የሳይንስ ግኝቶችን መቀበል ሲሆን ሶስተኛው አማራጭ አለማሰብን መምረጥ ናቸው፡፡ ለኔ 3ኛው ምረጫ ውስጥ አይገባም ከሁለቱ ደግሙ እስከ ድክመቱም ቢሆን የሁለተኛውን እመርጣለሁ፡፡ የኤቲስቶችን ምስክርነቶች ብናይ ወደ ኤቲስትነት የሚቀየሩት ከትምህርት ባገኙት እውቀት መሰረት ነው፡፡ እኔ አዋቂ ነኝ ባልልም ከመሰረቱ ኢ-አማኝ እንድሆን የገፋፋኝ ሳይንስ ነው፡፡ የኤቲስቶች የህዝብ ስርጭት የሚያሳየውም ይህን ሃቅ ነው፡፡

በአለም አንድ ቢሊዮን ኢ-አማኞች እንዳሉ ይገመታል (ከስምንት ሠዎች አንዱ መሆኑ ነው)፡፡ የስርጭታቸውን ሁኔታ ያየን እንደሆን ኢ-አማኞች የሚኖሩት ትምህርት በተስፋፋበት፣ የኑሮ ደረጃቸው በተሻሻለበት፣ የድህንነት ስጋት ጥቅተኛ በሆነበት፣

Created in Master PDF Editor

የኢኮኖሚና የፖለቲካዊ መረጋጋት ባለበትና የሰዎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በአንፃሩ በተረጋገጡበት አካባቢ ነው። በተቃራኒው ያለውን ለቀባሪ ማርዳት ነው።

ይልቁንም በዘመናዊ ትምህርትና ምርምር ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው የሚኖሩ ሳይንቲስቶች እና ሙህራን ኢ-አማኝ ናቸው አሊያም ለዘበተኛ አማኝ ናቸው። በጣም ጥቂቶች ብቻ የሀይማኖቶችን አስተምህሮ እንደወረደ ይቀበላሉ። እንደወረደ የሀይማኖቶችን አስተምህሮ ከማይቀበሉት ግን የሀይማኖቶችን አስተምህሮ በራሳቸው አረዳድ በመተርጎም ሌሎች "ባለ አንድ አማኝ" ሀይማኖቶችን ይፈጥራሉ።

የተማረ ሁሉ ኢ-አማኝ ይሆናል ማለት ባይቻልም የሳይንስ ትምህርት ተፈጥሮን የሚገልፅበት ሀይማኖቶች ከሚገልፅበት የተሻለ በመሆኑ ሰዎች በተማሩ ቁጥር በእምነት ያላቸው እምነት ይሸረሽራል።

17. በቅዱሳን መፅሃፍት የተተረከው እግዚአብሔር ኢ-ሰብአዊ ነው

ሰባኪዎች በቅዱሳን መጽሃፍት የተጻፉት ኢ-ሰብአዊ ትምህርቶች ለመሸፋፈን የማይጥሩት ጥረት የለም። በእርግጥ ቅዱስ የሚል ስም በወጣለት መጽሀፍ ውስጥ ክፉ ነገር ተፅፎ ይሆናል ብሎ ለማሰብ ይከብዳል። የሚሰቀጥጥ ትረካና ህሊናን የሚያውክ አስተምህሮ በቅዱሳን መጽሀፍት ላንጠብቅ እንችላለን። ዘመን የማይሸራቸው በተባሉት መጽሀፍት ዘመን ድርጊቶችን ስናነብ ምን ሊረዳን ይችል ይሆን? ለኤቲስቶች መጽሀፍቱ የተፃፈበትን የፊውዳል ጊዜ የሚያሳዩ የታሪክ ሰነዶች እንዲሆኑ ሊረዷቸው ይችላሉ። አማኞች ግን ትምህርቶቹን በማድበስበስ ያልፏቸዋል ወይም ይህ በጊዜው የነበረን ውስን ታሪክ የሚገልፅ ለዛሬ ምንም የማይረባ ነው ይላሉ። ነገር ግን ሰባኪዎች ከጥቅሶች እንዷን ውብ ጥቅስ ጠቅሰው እንደሚያስተምሩ የማያምኑት መጥፎ ጥቅስ ጠቅሰው ፍታዊነቱን ቢፈትሹ ጥፋት የለውም። መልካሙን ያዙ ክፉውን ጥቅስ ተው የሚል ትዕዛዝ ያለ አይመስለኝም። በእርግጥ በኖረ መልካም ነበር።

ነገር ግን መጽሀፍቱ ለራሳቸው የሚመሰክሩት ሁሉም መልካም እንደሆነ እና አንዳችም ተቀባይነት የሌለው አለመፃፉን ነው። በእውነት በቅዱሳን መጽሀፍት የተፃፉት ሀሳቦች ሰብአዊ ናቸውን?... እዚህ ላይ ምሳሌ መጥቀስ አልፈልግም ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ዮሐንስ ራዕይ ያነበበ ይፍረደኝ።

ምን አልባት እግዚአብሔር ካለ ሰው ግዑዝ እቃ ነው። ለሰው ልጆች ክብር ሲባል እግዚአብሔር ባይኖር እመርጣለሁ የምለው ለዚህ ነው። ሰዎች የጎልያድን ውድቀት ሲያስታውሱ የዳዊትን ብርታት ሳይሆን የእግዚአብሔርን ጣልቃ ገብነት ነው። በዕውቀቱ ስዩም ግን በተለየ መነጽር ያየው ይመስለኛል።

Created in Master PDF Editor

“እግዜርና ዳዊት አብረው ተቧደኑ

ብቻውን ታጠቀ ጎልያድ ምስኪኑ

አንዳንዱ ተገዶ ለሽንፈት ሲፈጠር

በጥቅሻ ይወድቃል እንኳንስ በጠጠር” በዕውቀቱ ስዩም

በዚህ የአብርሃም ሀይማኖቶች በሚመኩበት ታሪክ ትልቅ ስህተት ተሰርቷል። ከዚህ ታሪክ ምንም ያህል በትጥር እግዚአብሔር ካልተጨመረበት ትሸነፋለህ የሚል ተስፋ የሚያስቆርጥና በሌላ ተስፋ ላይ የሚያንጠለጥል ትምህርት ይወሰዳል። ብዙዎቹ ዛሬም ድረስ <እሱ ያለው አይቀር> እያሉ ሲያፏጩ ይውላሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ጥፋትን በሙሉ ከሰው ልጆች ጫንቃ በመጣል ከትችት ነጻ ሊያወጡት ይጥራሉ። ቴወድሮስ ተ/አረጋይ መጋቢ ሃዲስ እሸቱ አለማየሁን የአዳም ሀጥያት እኛን ለምን ያስቀጣናል ሲል ለጠየቃቸው ሲመልሱ እንዲህ ነበር ያሉት።

“አዳም የሀጢያት መሰረትና ውሀ ልኩን ያስቀምጥ እንጂ እኛ ሁላችንም አንዳንድ የሀጢአት ብሎኬት እያመጣን ጥለናል። ሲሚንቶ ጨምረናል፤ ውሀ አጠጥተናል ሀጢያትን ለማሳደግ። ቆርቆሮ መቷል፣ ሚስማር አቀብሏል የሰው ልጅ። ቃየል አቤልን ገደለ። ከዚያ በኋላ በኖህ ጊዜ ብዙ ህዝብ በዝሙት ወድቋል። ዛሬም በዓለም ዙሪያ የምንሰራው ሀጢያት በጠቅላላ በአዳም ጥፋት ብቻ የመጣ ነው ተብሎ የሚወሰድ አይደለም። ሁሉም የየራሱን ድርሻ ወስዷል። ሀጢያቱም በአዳምና ሄዋን ብቻ ያበቃ አይደለም፤ እኛምጋር አለ። ይህም ሆኖ በአባታችን አዳም ጥፋት በእኛ ላይ ሞት መምጣቱም የሚደነቅ አይሆንም። አባትህ ተበድረው ቢሞቱ በህግም ቢሆን ቤትህን ሸጠህ ትከፍላለህ። ያለፈው መንግስት የተበደረውንም ያሁኑ መንግስት ይከፍላል። በግልባጩ በክፉ መንገድ አይተነው እንጂ እኮ ለአዳም የተፈጠረው ገነት ለእኛም ሆኗል። ለአዳም በገባው ቃል ኪዳን ነው ለእኛም የሞተልን። እኛ ግን ፍጥረታችን ሆኖ ሁሌም ባገኘነው ከማመስገን ይልቅ ባጣነው መማረር ይቀናናል።” (ፍልስምና፣ ቁጥር 2፣ 2004 ዓ.ም፣ 25)

ይህን የእሮሮ ጥያቄ የይህዋ ምስክሮች ታዋቂ አገልጋይ የሆኑት ግርማይ ተወልደ ሲመልሱ እንዲህ አሉ፦

“ስቃይና መከራ፤ በአጠቃላይ ኢ-ፍትሀዊ ሁኔታ በምደራችን እንደሚታይ ምንም ጥርጥር የለውም። ጥያቄው ለዚህ ተጠያቂው ማን ነው? ማነው ይሄን ያመጣው? የሚለው ነው። ሰው በሆነ ምክንያት ሲሞት "እግዚአብሔር ወሰደው" "መልአክ ወደሰው" የሚሉ አሉ። የተፈጥሮ አደጋዎች ሲደርሱ የእግዚአብሄር ቁጣ ነው ይባላል። መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ የተለየ ማብራሪያ ይሰጣል። 1ኛ ዮሐንስ 5፡19

Created in Master PDF Editor

"መላው ዓም በክፉ ስር እንደሆነ እናውቃለን" ይላል። ስለዚህ መላውን ዓለም እያተራመሰ ያለው ሰይጣን ነው። ግጭት እንዲነሳ፣ ደም መፍሰስ እንዲኖር፣ ሰው እንዲጠላላ የሚያደርገው ይህ የዓም ገዢ ነው። ጌታ ኢየሱስ ሰይጣንን "የዚህ ዓለም ገዢ" ብሎ ጠርቶታል። እንዲያውም ከጅምሩም ሰውን ወደ መከራ ማጥ የከተተው እርሱ ነው፤ ማለት አዳምና ሔዋንን በማሳሳት። ይህን ሁሉ አድርጎ ሲያበቃ ለክፉ ገጠመኞች ተጠያቂው አምላክ ነው ያስብላል። ያሳዝናል!" (ፍልስምና፣ ቁጥር 2፣ 2004 ዓ.ም፣ 117)

መ/ር እሸቱ ስለ እግዚአብሔር ፍትሀዊነት የጠየቃቸውን ቴወድሮስ ተ/አረጋይ መልሰው ጠየቁት። እኔ ልጠይቅህ አሉ መጋቢ ሃድስቴዎድሮስም ይቻላል አለ። እግዚአብሔር ርሃብን ማጥፋት ይችላል አይችልም አሉት።ቴወድሮስ ተ/አረጋይ መለሰ ይችላል። መ/ር እሸቱ ማብራርራት ቀጠሉ፡-

"በነገራችን ላይ እኛ መጥፎ የምንላቸውን ነገሮች በጠቅላላ ነው እንዲያጠፋልን የምንፈልገው። መጥፎ ከምንላቸው ነገሮች ውስጥ ርሃብ፣ ጥም፣ እርዛት፣ ሞት፣... ሁሉ ይጥፋ ነው የምንለው። እነዚህ ነገሮች ይጥፉ ማለት ግን ደስታችንን ማጥፋት ማለት ነው። እግዚአብሔር ሰይጣንን ማጥፋት ይችላል። ነገር ግን እሱን ከማጥፋት የሰው ልጅ ታግሎ የሚያሸንፍበትን ስልጣን ነው የሰጠው። ለእግዚአብሔር ርሃብን ከማጥፋት ይልቅ የሚበላውን ምግብ መፍጠር ነው የተሻለው። ርሃብን ማጥፋት አይደለም ተገቢው ነገር፤ የሚመግበውን ምግብ መስጠት ነው።" (ፍልስምና፣ ቁጥር 2፣ 39)

ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ በ <ፍልስምና ሁለት> ላይ መምህር እሸቱ የሰጡት መልስ መጥፎ የምንላቸው ነገሮች ይጥፉ ማለት ደስታችንን ማጥፋት ነው ወይ ሲል ኤቲስቱ ዜና ለይኩንን በ<ፍልስምና ሶስት> ቃለ ምልልስ ጠይቆት ነበር። ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው ነበር።

ዜና፡- ደስታችን ይጠፋል ምን አይነት መልስ ነው? የህይወት መከራ ይሰለቻል ወይስ ደስታ?

ቴዎድሮስ፡- ደስታም ራሱ ይሰለቻል።

ዜና፡- ማነፃፀሪያ ከሌለ ደስታ አይሰለችም። ሁሉም ፍፁም ልክ ከሆነ ለምን ትደከማለህ? ለምን ደስተኛ አትሆንም? የመኖር ትርጉሙ እኮ ደስታ ነው። የምሰራው የምለፋው ወድጄ አይደለም። በእኔ ፈቃድ ቢሆን ምን እንደማደርግ ታውቃለህ? ቀኑን ሙሉ መጽሐፍ ሳነብና ስዕል ሥስል መዋል ነው የምፈልገው።

ቴዎድሮስ፡- ምን ሊያደርግልህ ነው የምታነበውስ ሆነ የምትስለው?

Created in Master PDF Editor

ዜና፡- ለመደሰት፡፡ ደስታን ለማግኘት፡፡

ቴዎድሮስ፡- ምንም የጎደለህ ከሌለና ደስታህ ሙሉ ከሆነ የት ላይ ትጨምረዋለህ? አዲስና ተጨማሪ ደስታ አያስፈልግህም ማለት እኮ ነው፡፡ ሁሌ ሆድህ ከጠገበ ምግብ አያስፈልግህም፡፡ ህይወት ባይጎድለን ኪነጥበብን ለምን እንፈጥራት ነበር? ኪነጥበብ ችግራችን እንጂ የሙላታችን ውጤት አይደለችም፡፡

ዜና፡- አሁን የምትነግረኝ እኮ የዓለምን እውነታ ነው፡፡ የአምላክን አይደለም፡፡

ቴዎድሮስ፡- የአምላክንም ነው እንጂ፡፡

ዜና፡- እግዚአብሔር ቢኖር ኖሮ፣ ፍፁም አምላክ ቢሆንማ ፍፁም የሆነ ዓለምን ይሰራ ነበር፡፡ ምንም አይጎድልም ነበር፡፡ በፍፁምነት ስር እኛ ራሳችን እግዚአብሔሮች ነን፡፡ እግዚአብሔር እግዚአብሔርን መሆን ይሰለቸዋል? ሁሉም ነገር ፍፁም ቢሆን እኛም እግዚአብሔርን ነበር የምንሆነው፡፡ ስለዚህ አይሰለቸንም ነበር፡፡ ለነገሩ ከገነት የተባረርነውም እኛ አምላክ እንዳንሆንና ሳይሰለቸን እንዳንኖር ነው፡፡ አንድ ምሳሌ ላንሳልህና ፍሮለይን ፍራስል የምትባል በኦስትሪያ ሀገር ውስጥ አባቷ ለ25 ዓመታት ቤት ውስጥ ዘግቶ ሲደፍራት የኖረች ሴት አለች፡፡ የሚዲያ ክርክር ላይ ነው ያየሁት፡፡ አንድ ነውረኛ ቄስ ምን እንዳለ ታውቃለህ? በሰማይ ትካሳለች ነው ያለው፡፡

ቴዎድሮስ፡- አዎ፡፡ ወደዚያ ከሔድንማ…

ዜና፡- እንዴት አዎ ትለኛለህ? እንዴት በጤነኛ ጭንቅላት አፍ ኖሮህ አዎ ትለኛለህ? እንዴት አታዝንም? እንዴት ለእህትህ አታዝንም? እህትህ ብትሆን እኮ ቄሱን ትገድለዋለህ፡፡ ይሔን ደደብ ግን ማንም ሳይገድለው አደባባይ ላይ ወጥቶ እኮ ነው የ25 ዓመት ስቃይዋን በሰማይ ትካሳለች ብሎ የዘጋው፡፡ በምድር በመሰቃየቷ ምላሽዋ በመሰማይ ነው እንዴት ይላል? ይሔ ብልግና ነው መንፈሳዊነት? እግዚአብሔርስ እንዴት አላዳናትም? ኖሮ ከሆነ ዝም ያለው 25 ዓመት ሙሉ ስትጠራው ያላዳናት ምን አይነት አምላክ ቢሆን ነው? ባትጠራውስ አባቷ አይደለም? ቀላል ምሳሌ ልጥቀስልህ እንጂ ስድስት ሚሊዮን አይሁዳውያን ሲቃጠሉም ዝም ነው ያለው፡፡ ሰዎች በሃይማኖት እየተመሩ ጥፋት የሚፈፅሙት ለምን እንደሆነ ሁሌም እጠይቃለሁ፡፡ ኢ-አማኝ ሰው ግን የሚያደርገው ሁሉ በራሱ እየተመራ ስለሆነ፣ ማንንም ስለማያሳብብ፣ ለውድቀቱም ሆነ ውጤቱ ተጠያቂው እሱ ራሱ ስለሆነ ሃይማኖተኞች እግዚአብሔርን በመጠበቅ ስም (እሱ ሊጠብቃቸው ሲገባ እነሱ እየጠበቁት) የሚያደርሱትን ያህል ጥፋት አያደርሱም፡፡ ካጠፋም በራሳቸው እንጂ በማንም አያሳብብም፡፡ (ፍልስምና፣ ቁጥር 3፣ 107-108)

Created in Master PDF Editor

18. ሀይማኖትዊ አስተሳሰቦች አርጅተዋል

አስተሳሰብ ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ያረጃል፣ ይሞታል፣ ይቀባራል፣ ታሪክ ይሆናል:: ሀይማኖትዊ አስተሳሰቦችም እንዲሁ:: ሀይማኖታዊ አስተሳሰቦች ምንም ያህል ቢያረጁ ከሌሎች አንጻር ብዙ ይኖራሉ፣ ያኖራሉም:: ምክንያቱም በቄሶች ዘንድ እጅግ ልዩ ጥበቃ ይደረግላቸዋል:: ቄሶች ሀይማኖቱ ምንም ይሁን ምን መጠበቅ አለብት አይነት አቋም አላቸው የእንጀራ ጉዳይ ነውና:: እጅግ ከፍተኛ ደምወዝ፣ ጉርሻና ትርፍ የሚያገኙት እነሱ ናቸው:: ፓስተሮች ምን ያህል አትራፊ ነጋዴዎች እንደሆኑ አለም ያውቃል:: ጥቂት ቃል ብቻ ተናግረው ብዙ ያግበሰብሳሉ:: የማያከስር ንግድ የማይነጥፍ እንጀራ ያበስላሉ:: እነዚህን ሳይሰጡ የሚቀበሉ ነጋዴዎች ኦሾ እንዲህ ይገልጻቸዋል:: “The priests have been deceiving man more than anybody else. This is the worst profession in the world.--- And this is not all: Whenever somebody has realized the truth, these priests are against him. The priest has taken away the search for truth: He says there is no need for searching, it has already been found, you just have to have faith. The priest has made people miserable, because he condemns all the pleasures of the world. Obviously, they have to be, because if his truth is recognized by people, millions of priests in the world will be out of employment. And their employment is absolutely unproductive. <u>They are parasites</u>, they go on sucking the blood of man. From the moment the <u>child is born,</u> until he enters <u>his grave,</u> the priest goes on finding ways to exploit him.” (Zarathustra: A God That Can Dance 267-268)

አንድ ማንም የማይክደው ሀቅ አለ ሀይማኖቶች ለዘመናት ከሰውጅ ጋር ጋር ኑረዋል፣ አሁንም በብዛት እየኖሩ ነው:: በታሪክ በምናውቃቸው ስልጣኔዎች ሁሉ በርካታ የተለያዩ ሀይማኖቶች ነበሩ:: ብዙዎቹ ከእርጅና ብዛት አንቀላፍተዋል:: ዛሬ በጥንቶቹ የግብፅ፣ የቻይና፣ የማያ፣ የአዜቲክስና የሞሶፖታሚያ አማልዕክት ማመን እንደ መኝ ያስቆጥራል:: ቢሆን የያኔው ስልጡን ህዝብ ካለነሱ ህይወት እንደለለው በታሪኩ አስፍሮታል:: በRobert Wright በተጻፈው ‘The Evolution of God’ መጽሃፍ የጥንቶቹ ስልጣኔ ከአማልዕት ጋር የተሳሰረ መሆኑን እንዲህ ይገልጸዋል:: <<<u>Egypt:</u> “The cardinal features of that culture and society were determined by the existence and power of its all-pervading religious beliefs.”<u>China:</u> “The fate of human beings was inseparable from the extra-human world.”The <u>Maya</u>: “Everything in the Maya world was imbued, in different degrees, with an unseen power or sacred quality.” The <u>Aztecs</u>: “Existence revolved totally around religion. There was not a single act of public or private life which was not colored by religious sentiment.” <u>Mesopotamia</u>: “The gods constantly intervened everywhere and participated in everything.”>> ዛሬ እንዲህ የምንንቃቸው አማልዕክት ቀን ሳይጨልምባቸው ሀያላን ነበሩ::

Created in Master PDF Editor

19. God is Dead, Now Zen is the Only Living Truth

ተወዳጁና አወዛጋቢው ኦሾ (Raja Rajneesh) God is Dead, Now Zen is the Only Living Truth በሚለው ንግግሩ እግዚአብሔርን በሚከተሉት ባህርያት ገልጾታል፡፡ “God is a puppeteer, God is an insult to man, God is just like tomorrow, God is a lie, God is your insecurity, God is the original sinner, and God is the business of the priest.” ብዙ የማውቃቸው ሰዎች ኦሾን ይፈሩታል፣ ብዙዎቹ ከአርዮስ ቀጥሎ በክህደት ትምህርቱ 2ኛ ደረጃ ይሰጡታል፡፡ ንግግሮቹ ደፋር፣ ግልፅና እውነታን የተላበሱ ናቸው፡፡ የኦሾን እንግሊዘኛ መፅሃፍትና ንግግሮች 10ኛ ክፍልን ያጠናቀቀ ያለ ድክሽነሪ በቀላሉ ይረዳቸዋል፣ በአማረኛ ተተርጉመው ከተገኙ ደግሞ የ10 አመት ታዳጊ እንደ ትረት መፅሃፍት ሊረዳቸው ይችላል፡፡ የኦሾ ሃሳቦች በምዕራብና በምስራቁ አለም ፍልስፍና የተቃኙ በመሆናቸው ጉልበት አላቸው፡፡

የታላቁ አወዛጋቢ ፈላስፋ ኦሾ ሰራዎች በብዙ ቦታዎች ሲጠቀሱ መስማት የተለመደ ነው፡፡ ለጊዜው ግን God is dead now zen is the only living truth የሚለው መቃኘት ፈለኩ፡፡ በነገራችን ላይ ኦሾ የረቀቀን ፅንሠ ሀሳብ በቀላል ቋንቋ የሚያስረዳ፣ በቅንጭላቱ ውስጥ የአለምን ትልቁን ቤተ-መፅሀፍት ይዞ የሚዞር ፈላስፋ ነበር፡፡ ከምእራብ እና ከምስራቅ የተነሱ የሳይንስ በተለይም የፍልስፍና እሳቤዎች መታሪቂያቸው ኦሾ ነው፡፡ በዚህ የኦሾን ታላቅነት በሚመሰክረው God is dead መፅሀፍ የተፃፉት እያንዳንዱ ቃላት በደም ስር ሁለንተናን የሚቆጣጠሩ ናቸው፡፡ ኦሾ ንግግሩን ሲጀምር ታላቁን አስደንጋጭ ፈላስፋ ፍሬድሪክኒቸን ጠቅሶ ነው፡፡ ኦሾ ኒቸን ሲያሞግሰው በሰው ልጅ ታሪክ የእግዚአብሔርን መሞትና የሰውን ልጅ ነፃ መውጣት የአወጀ ነው ይለዋል፡፡

> “God is the greatest dictator, if you accept the fiction that he created the world and also created mankind. If God is a reality, then man is a slave, a puppet. All the strings are in his hands, even your life. Then there is no question of any enlightenment. Then there is no question of there being any Gautam the Buddha, because there is no freedom at all. He pulls the strings, you dance; he pulls the strings, you cry; he pulls the strings, you start murders, suicide, war. You are just a puppet and he is the puppeteer.
>
> Then there is no question of sin or virtue, no question of sinners and saints. Nothing is good and nothing is bad, because you are only a puppet. A puppet cannot be responsible for its actions. Responsibility belongs to someone who has the freedom to act. Either God can exist or freedom, both cannot exist together. That is the basic

Created in Master PDF Editor

implication of Friedrich Nietzsche’s statement: God is dead, therefore man is free.” (God is Dead, Now Zen is the Only Living Truth, pp 3)

ይህን ምስጢር የነገረ መለኮት ሙህራን ሊስብኩን እንደማይችሉ ይነግረናል። ኦሾና ኒቸ ግን አደረጉት። ኦሾ ስለራሱ እንደነገረን ኦሾ ከኒቸ እጅግ የተሻለ ዜናን አምጥቷል። ለምን ቢባል ኒቸ የምዕራቡ አለም ፈላስፋ ስለሆነ ስለሚዴቴሽን አልነገረንም። የኒቸ ፍልስፍና መልካም ነበር ግን ኦሾ እንዳረጋገጠው ጎደሎ ነው። የኦሾ ጥያቄ እዚህ ጋ ነው እግዚአብሔር ሞተ ከዚያስ? ሰው ነፃ ነው ከዚያስ? ምንም ጥርጥር የለውም እግዚአብሔር ከሞተ ሰው ነፃ ይሆናል። ነፃነቱ ግን ችግር አለው ሰው ያለምንም ተመልካችና ዳኛ ሁሉን ሊያደርግ ይችላል፣ ደጉንም ከፉውንም እኔ ግን የተፈጠረውን ክፍተት የሚሞላ ሃሳብ አለኝ ይላል።

“Friedrich Nietzsche was not aware of any meditations that is the other side of the coin. Man is free, but his freedom can only be a joy and a blessing to him if he is rooted in meditation. Remove God that is perfectly okay, he has been the greatest danger to human freedombut give man also some meaning and significance, some creativity, some receptivity, some path to find his eternal existence. Zen is the other side of the coin. Zen does not have any God, that’s its beauty. But it has a tremendous science to transform your consciousness, to bring so much awareness to you that you cannot commit evil. It is not a commandment from outside, it comes from your innermost being. Once you know your center of being, once you know you are one with the cosmos and the cosmos has never been created, it has been there always and always, and will be there always and always, from eternity to eternity, once you know your luminous being, your hidden Gautam Buddha, it is impossible to do anything wrong, it is impossible to do anything evil, it is impossible to do any sin.” (pp, 4)

ኦሾ ልክ ነው ኒቸ በመጨረሻው ዘመን አብዶ ነበር። ምን አልባት ኦሾ እንደገመተው ኒቸ ያበደው የእግዚአብሔርን መሞት ስለደረሰበትና በክፍተቱ የሚሞላው ሀይል ስላጣ ላይሆን ይችላል። የቅንጭላት ዕጢ ስለነበረበትና ብዙ የህይወት መሰናክሎች ስለጋጠሙት ለእብደት በቅቶ ሊሆን ይችላል።

ኦሾ አንድ ግብ ነበረው ብዙም የተሳካለት ባይመስለኝም ኒቸ በገደለው አምላክ ቦታ አዲስ መንፈስ መሙላት። ያ አማልዕክትን ማምለክ አይደለም ከራስ ጋር መታረቅ ነው ‹‹Meditation›› ይለዋል። በኦሾ እምነት እውነት መራራ ነው ለዚህ ማጣፈጫ ያስፈልገዋል። ኮሶ መራራ ነው መድሃኒትነቱን የሚፈልጉት ግን በማር ያጣፍጡታል። ኦሾም ለሽህ አመታት ብዙ ስንገበርላቸው የኖሩትን አማልዕክት አንዴ ስም አጠራራቸውን ማጥፋት ባዶነት ይፈጥራል ይላል። ይህ ባዶነት የህይወት

Created in Master PDF Editor

ትርጉም ባዶ እንዲሆን ያደርጋል ስለዚህ መራራውን የአማልዕክት ሞት በሚዲቴሽን አለሳልሰን መስማት አለብን፡፡

ኦሾ ልክ ነው መርዶ ተሎ አይነገርም፡፡ የቅርብ ቤተሰብ ለሞተበት ሰው ማርዳት ግድ ቢሆንም ነገሩን እንዲጠረጥርና በተለሳለሰ አማረኛ መናገር አለበት፡፡ ደርሶ እናትሽ በመኪና አደጋ ሞተች ማለት ምን ማለት ነው? ሞት የሚያረዱ ሰዎች ሞትን ማርዳት ብቻ ሳይሆን መርዶው የተነገረውን ሰው በቅርብ መሆንና ማፅናናት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ኒቺ ግን እንኳን ሊያፅናናን ለራሱም የሚያፅናናው ይፈልግ ነበር፡፡ ኦሾ ግን የአማልዕክት መሞት አያስጨንቀውም የመጣው ከምእራብ ሳይሆን ከምስራቅ ነው ከህንድ፡፡ ህንዶች ደግሞ የሚዴቴሽን የቆየ መልካም ባህል አላቸው፡፡ በምእራብ አለም ብዙ ገንዘብ፣ ዝና፣ ስልጣና፣ እውቀት እና እምነት ኑሯቸው እያሉ ራሳቸውን እስከ ማጥፋት ይደርሳሉ፡፡ ይህ በምስራቅ ብዙ የተለመደ አይደለም፡፡

ኦሾ ኒቸን ብቻ ሳይሆን የምዕራቡን አለም ፈላስፎችና ሳይንቲስቶችን ይወቅሳል፡፡ አማልዕክት መንግስተ ሰማያት፣ ገሀናም ወዘተረፈ የሚበሉ ቅራቅንቦዎች ፊክሽን መሆናቸው አውቀው እያለ የተፈጠረውን Vacuum የሚሞሉበት ጥበብ ግን ጎደላቸው ይላቸዋል፡፡

ኦሾ አማኝም ኢ-አማኝም አልነበረም፡፡ እኔ እንደገባኝ ፍላጎቱ እግዚአብሔር የሌለበት መንፈሳዊነት ማስረፅ ነው፡፡ ይህ እንዲስ ፍልስፍና አይደለም ጉተማ ቡብሃ አድርጎታል፡፡ ኦሾ እንደገና የጉተማ ቡድሃን የኑሮ መንገድ ሊያስተዋውቀው ፈለገ፡፡ ቡድሃ መንፈሳዊ ሀይማኖት ሲመሰርት እኔን አምላኩ አላለም፤ ከፈጣሪ ተልኬ የመጣሁ ነኝም አላለም፤ እግዚአብሔር አለም አላለም፤ ከራስ በላይ ሰማይ ነው ያለ ግን ይመስለኛል፡፡

ብዙ ሰዎች ስለዜን (Zen) መንፈሳዊነት ሲነግራቸው ሊሳለቁ ይችላሉ፡፡ ለምን ቢባል መንፈሳዊነት የሚመስላቸው አማልዕክት የሚመለኩበት ስርዓት አድገው ስለሳሉት በዜና መንፈሳዊ ፍልስፍና ግን አማልዕክት የሉም፤ ማምለኪያ የለም፤ ገነትና ሲኦል የለም፡፡ ይህን የዜን መንገድ ኦሾ ሳይንሳዊ ሃይማኖት ይለዋል፡፡ ልዩነቱ ሳይንስ ወደ ውጭ ሲሆን ዜን ወደ ውስጥ ነው፡፡ ዜን ምንድን ነው?

“Zen is the method to go beyond mind. So we will be discussing God and Zen together. God has to be negated, and Zen has to be planted deep in your being. The lie has to be destroyed and the truth has to be revealed. That’s why I have chosen God and Zen together. God is a lie, Zen is a truth.” (pp 13)ኦሾ ይህን ሲሰብክ አንዱ ጥያቄ ተነሳበትና ግን

Created in Master PDF Editor

በእውነት እግዚአብሔር ሙቷል? እንዴትስ ሞተ ብሎ ጠየቀ። ኦሾም መለሰ ሲጀመር እግዚአብሔር አልነበረም ሞተ ማለት ሀሳቡን ነው አለው።

> “The way I look at things, God has never been there, so how can he be dead? He was never born in the first place. It was invented by the priests, and it was invented for exactly these reasons: because man was in anxiety, man was in fear, man was in dread, man was in anguish. When there was no light, no fire – just think of those days of humanity – wild animals all around, and the dark night, no fire, the intense cold, no clothes, and the wild animals searching for their food in the night, and people were hiding in caves, sitting on the trees just to avoid... In the day, at least they could see that a lion was approaching, they could make some effort to escape. But in the night, they were completely in the hands of the wild animals.” (pp 13)

በእውነት ያስፈራል፣ ያባባል። ታዲያ ይህ ፍርሃት አማልዕክትን ለመፍጠር ቢበዛ እንጅ አያንስም። ሞትን እንደመፍራት ያለፍርሃት የለም። ሰው ብቻ ሳይሆን አያሰቡም የምንላቸው እንኳ ሞትን ይፈሩታል። ምን አልባት ሞትን የማይፈራው ብቸኛ ፍጥረት አሜባ ነው ለምን ቢባል አሜባ አይሞትም። ኦሾ እንዲህ ይላል።

> “Only one animal does not die, that is the amoeba. They are not the by-product of sex, so there is no death. Sex and death are absolutely connected. Just try to understand. Sex brings you into life, and life finally ends in death. Sex is the beginning, death is the end. In between is what you call life. The amoeba is a non-sexual animal, the only celibate monk in the whole world. It reproduces in a very different way. God must be immensely happy if he is there with the amoebas; they are all saints. They simply go on eating and becoming fatter and fatter, and at a certain point they divide into two. When one amoeba becomes so fat that it becomes impossible for him to move, he divides in two. This is a different way of reproduction. But because there is no sex involved, there is no male, no female. Both the amoebas start eating again. Soon they will be fat enough to divide again. So it is by a very mathematical method that they create. There is no death, an amoeba never dies – unless he is murdered!” (pp 14)

ስለዚህ ከአሜባ ውጭ ያለ ህይወት እንደሚሞት ማወቅ አለበት። ሞት ተስፋ የሚስቆርጥ ነገር አይደለም ህይወት በቂ ነውና። ምን አልባት በሞት መኖር ለሚሳቀቁ ኦሾ መድሃኒት አለኝ ይላል። ምንድን ነው? “So I want to destroy all your belief systems, all your theologies, all your religions. I want to open all your wounds so they can be healed. The real medicine is not a belief system; the real medicine is meditation. Do you know that both the words come from the same root: medicine and

Created in Master PDF Editor

meditation? Medicine heals the body, meditation heals your soul. But their function is the same, healing.” (pp 15-16)

ሌላኛው ጥያቂ ተነሳና ያለ እግዚአብሔር መኖር ይቻላልን? ብሎ ጠየቀ፡፡ መልሱን በቀጥታ መለሰ አወ፡፡ “So your question, ”Is it possible for man to live without God?” – I say unto you, it is only possible for man to live if he is without God. But this is only half. The fictitious God has to be replaced by an actual experience of truth in meditation; otherwise you will go insane.” (pp 20)

በሚሰብካቸው ትምህርቶች ከየአቅጣጫው ወቀሳና ትችት ይደርስበት የነበረው ኦሾ መንፈሳዊነትን እና አለማዊነትን ለማዋሀድ በመጣሬ ነው ይላል፡፡ ኮሚኒስቴች ስለእኔ የትችት መፅሀፍትን ይፅፋሉ መንፈሳዊነትና ሚዲቴሽንን ስለምሰበክ፡፡ መንፈሳዊያንም ይነቅፉኛል ስለ አለማዊነት ስለምስብክ ነበር ያለው፡፡

ሌላ መሰረታዊ ጥያቄ ተነሳ ይሁን እግዚአብሔር የለም እንበል ሁለንተን ማንፈጠረው? ኦሾ መለሰ መጀመር የሚባል የለም፤ መጨረሻም እንዲሁ፡፡ ሰዎች መጀመሪያ የሚባለው ነገር ይወዱታል ለምን ቢባል ከመጀመሪያው በፊት አምላክን ለማስገባት፡፡ ችግሩ ይላል ኦሾ እግዚአብሔር ዘለአለማዊ ነው ካልን መጀመሪያው የሚባለው ነገር እራሱ አይኖርም ይላል፡፡

> “Do you see the simple arithmetic? If there was somebody already to begin it, then you cannot call it the beginning, somebody was already there. If you think that God is a necessary thing... it gives you consolation that God created the world, so you have a beginning. But who created God? Again you fall into the same problem. And all the religions have said that God exists eternally, there is no creator of God. If that is true for God, why is it not true for existence itself? It is autonomous, it exists on its own. There is no need of any creator because that creator will require another creator, and you will fall into an absurd regress. You can go from A to Z. But who created Z? The question remains standing, you simply go on pushing. But the question is not solved because you have asked a wrong question. The universe has no beginning, it is not a creation by anybody. It has no end.” (pp 40)

ሌላኛው ጥያቄውን ቀጠለ “እግዚአብሔር ከሌለ መፀለይ ተገቢ ነውን?” ኧረ በጭራሽ “There is no place for prayer, because prayer is God-oriented. If there is no God, to whom can you pray? All prayers are false because there is nobody to answer them, nobody to hear them. All prayers are humiliations, insults, degradations. All prayers are disgusting! You are kneeling down to a fiction which does not exist.” (pp 42)

Created in Master PDF Editor

ሌላ ጥያቄ ተነሳ ኒቸ ስለፃፈው The Antichrist ምን አስተያየት አለህ? ኦሾ መለሠ "ኒቸ የኖረው ፀረ-ክርስቶስ ሆኖ ነው። ፀረ-ክርስቶስ የሚለውን እንደማዕረግ ይጠቀምበት ነበር። ሲፈርም እንኳ "Antichrist, Friedrich Nietsche" ነበር የሚለው። ይህን ቃል እስኪሞት ድረስ ተጠቅሞበታል። ኒቸ ለምን ፀረ-ክርስቶስ እንደሆነ ሲያብራራ ሰው ባሪያ ወይም በግ ሳይሆን Superman ብሎ ስለሚያስብ፤ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ወደ ባርነት ቀይሮታል ብሎ ስለሚያምን፤ በወንጌል ድሆች የተባረኩ ናቸው መንግስተ ሰማያት የነሱናትና መባሉ ስለሚያናድደው፤ ሀብታሞች መንግስተ ሰማይ ከሚገቡ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይሻላል መባሉ ስለሚያበሳጨው፤ ክርስቶስ ራሱን በግ እረኛ ሌሎችን በግ እና እራሱን አዳኝ ሌሎችን ሀጢአተኛ አድርጎ ማስተማሩ ስለከነከነው ነው ይላል።

አንዱ ደግሞ ጠየቀ ከPolytheism monotheism ይሻላልን? በጭራሽ ይልቅ ነገሮችን አከፋ እንጅ። "አሃዳዊ (Mono theism) አደገኛ ነው። የሰውን መንፈሳዊነት ያቀጭጨታል፣ እድገቱን ያስናክሉታል። የአይሁድ፣ የክርስትና እና የሙሀመድን ሃይማኖቶች እያቸው monotheistic ናቸው። ሙሀመድ በግልፅ ነው ያስቀመጠው አንድ ፈጣሪ አለህ፣ አንድ የመጨረሻ ታላቅ ነብይ ሙሀመድ፣ አንድ ቅዱስ መፅሀፍ ቁርዓን። ይህ የመጨረሻው የአምባገነናዊ ስርዓት ነው። አይሁድን አምላክ እሰበው ከእኔ ሌላ ወዮልህ ነው ሚለው። ክርስትናም አጠናክሮ ቀጥሎበታል። ህንድ ልውሰድህ በዚያ ደስ የሚል ነገር አለ ሂንዱይዝም። ህንድይዝም አንድ አምላክ፣ አንድ መጽሀፍ፣ አንድ ነብይ፣ አንድ መሲህ የሚባል የለውም። በህንድይዝም ሁሉም እግዚአብሔር ነው።

አንድ አምላክ ብቻ ማለት ሌሎችን ማጥፋት ማለት ነው። ይህ ትልቅ ስጋት ግጭትን ይፈጥራል። የሙሀመድ ሰዎች ወደ ህንድ መጡ ለሽህ ዘመናት የተገነቡ መንፈሳዊ ቅርሶችን አወደሙ ጥቂቶች ብቻ ለታሪክ ተረፉ በተደበቁ ቦታዎች የነበሩት። መቻቻል ከየት ይመጣል monotheistic ሃይማኖቶች ምን አተረፋልን? ጦርነት። በህንዲይዝም የሃይማኖት ጦርነት የለም፣ በክርስትና ግን የመስቀል ጦርነት የሚባል አለ።ብዙ አማልዕክት ካሉ የፈለከውን የመምረጥ ነፃነት አለህ፣ መቻቻልም ይኖራል። በሂንድይዝም የተነሱት ታላላቅ ሰዎች አንድ አቋም የላቸውም፣ ሁሉም የራሳቸውን ፍልስፍና ነበራቸው ይህ ድንቅ ነገር ነው።" ይላል።

ሌላው ኦሾ monotheistic ሃይማኖቶችን የሚተችበት ምክንያት የተስፋፋበትን መንገድ ነው። ለማስመሰል ካልፈለግን በስተቀር ከአብርሃም ዘመን እስከ ዛሬ ድረስ ጦርነት ነው። እንደ ኦሾ አመለካከት ያለምንም ጦርነት፣ ያለ ምንም ጫና በውይይትና በሠላማዊ መንገድ የተስፋፋው የቡድሃ ሀይማኖት ነው። የቡድሃ አስተሳሰብ Polytheism በመሆን የተሻለ ው። ማሳመን እንጅ ማዘዝ የሚባል የለም። ቡድሃ ደቀ

Created in Master PDF Editor

መዝሙሮቹን ሲሰበካቸው የነበረው ስለ እኩልነት ነው፡፡ በአሾ አገላለፅ “Never think for a single moment that you are inferior to me we are all equal” በመሠረቱ ቄስ የሚባል የለም ይላል ኦሾ፡፡ አንድ ብቻ እግዚአብሔር ከሌለ ቄሶች አያስፈልጉም፣ ቄሶች የሚያስፈልጉት የአንዱ እግዚአብሔር ወኪል እና መገናኛ ድልድይ ለመሆን ነው፡፡ ኦሾ ቡዲሂስት አይደለም ከአንድ አምላክ ሀይማኖት ግን ለብዙ አምላክ ሀይማኖቶችን ይደግፋል፡፡ ባለ ብዙ አማልዕክትን የሚደግፈው ነፃነት ስለሚሰጡ ነው፡፡

ሌላኛው ጠያቂ “እግዚአብሔር መተው ከባድ ነው የተስፋና የደስታ ምንጭ ነውና አለው” ኦሾም መለሰ እውነት ነው፡፡ “It is true. It is very difficult to drop an expectation, to drop a hope, because you don’t have anything real in your life. You are living only in the hope that tomorrow will be better. You are only living with the expectation that after death you will enjoy the pleasures of paradise eternally. Hence it is difficult to drop the idea of God. That’s why Christianity has such great appeal to the poor people of the world. It gives great consolation. It gives you expectation, which helps you tolerate the present misery, the pain, the present poverty, slavery. Your eyes are focused on the future, and the present goes on passing in misery. But as your eyes are no more focused on the present, the consolation helps to keep you alive, but just alive; just like vegetables. It keeps you vegetating.” (ገጽ 73) ኦሾ በአውሮፓ የነበረ የአንድ ታላቅ ኮከብ ቆጣሪን ታሪክ ያስተውሳል፡፡ በመላው አውሮፓ የነበሩ ባለስልጣን እና ከበርቴዎች ወደ ታዋቂው ኮከብ ቆጣሪ ይሄዳሉ፡፡ አንድ ቀን ኮከብ ቆጣሪው ሰማይ ሰማይ ሲያይ ይወድቅ እና ጉድጓድ ውስጥ ይገባል፡፡ የእርዳታ ጥሪውን የሰማች አንዲት አሮጊት ደረሰችና አዳነችው፡፡

ራሱን አስተዋወቃት የምድረ አውሮፓን ከበርቴዎች ብዙ ገንዘብ እያስከፈልኩ እጣ ፈንታቸውን የምነግራቸው እኔ ነኝ አላትና እሷ ግን ወደ ቤቱ ብትመጣ እንደማያስከፍላት ነገራት፡፡ የሚደንቀው የአሮጊቷ መልስ ነው፡፡ “ማፈርያ የመሬቱን ሳታውቅ እንዴት የሰማዩን ልትነግረኝ ትችላለህ፡፡ ወደ አንተ የሚመጡም ጅሎች ናቸው” አለችው፡፡ በእውቀቱ ስዩምም ይህን መሰል መጣጥፍ ፅፎ ነበር፡፡ ሰማይ ሰማዩን የሚያይ ምድርን የከዳ፣ ምድርም የከዳችው ነው ነበር ያለው፡፡ ወደ ኦሾ እይታ ደስታ እና ተስፋ ያሉት ውስጥ ነው፡፡ በራሳችን ውስጥ! So God is dead and can is the only living truth” ያለው ልክ ይሆን? ኦሾ ይቀጥል፦

Page 116, “God is the enemy of nature, because nature is truth and God is a lie. But the lie is dominating millions of people and telling them to withdraw from nature, which is the only truth. So there is no religiousness in a God-oriented person. What he has is a morality, which is nothing but a social convenience. It differs from place to place, from

Created in Master PDF Editor

country to country, from race to race. What seems to be religious to one fragment of humanity is not religious to another fragment of humanity, because every society has its own climate, its own heritage, its own past – which is different from other societies."

Page 120፣ "God-oriented religions certainly create a conscience, but not consciousness. And many people have the false notion that conscience and consciousness are one. Their root is one, but they are two separate branches moving in different, diametrically opposite directions. Conscience is forced on you by others. Consciousness is an evolution rising from your own depths to the ultimate heights. Conscience is just like a plastic flower."

Page 126 "You will find all God-oriented people serious and sad, because deep down there is doubt. God is not their experience, it is just a belief. And how can you make belief a truth? It will remain a belief. You can repress your doubt as much as possible in the unconscious, but it is there and very alive and kicking. It makes you sad because you are living a fictitious life, a life that is not your own, a life that others have imposed on you. And God is the most responsible for taking away your prestige, your dignity, your pride."

Page 206 "These are the three steps of enlightenment: First, the buddha will come behind you as a presence. You will feel it, it will surround you, it is an energy field; it will change your whole behavior, it will give you a new sense of direction in life. It will give you a new morality, of your own, a spontaneity in existence. It will give you a love for life, a cheerfulness you have not known, and courage. The moment you know you are eternal, all weakness disappears, all inferiority disappears."

20. እግዚአብሔር ቅዠት ነው (God is Delusion)

<<The God of the Old Testament is arguably the most unpleasant character in all fiction: jealous and proud of it; a petty, unjust, unforgiving control-freak; a vindictive, bloodthirsty ethnic cleanser; a misogynistic, homophobic, racist, infanticidal, genocidal, filicidal, pestilential, megalomaniacal, sadomasochistic, capriciously malevolent bully.>> (The God Delusion, page 31)

<<Faith's claim is based on the Bible being the word of God in some meaningful sense. But modern scholarship has shown us that the canonical Bible: is inconsistent with itself,is not supported by archaeology, contains fairy tales, contains failed prophecies, andcontains many forgeries.>> (The Christian delusion, page 148)

Created in Master PDF Editor

የኦክስፎርዱ ሳይንቲስት ሪቻርድ ዳውኪንስ The Selfish Gene, The Extended Phenotype, The Blind Watchmaker, River Out of Eden, Climbing Mount Improbable, Unweaving the Rainbow, A Devil's Chaplain, The Ancestor's Tale, The Greatest Show on Earth እና The God Delusion የተባሉ ድንቅ መፅሃፍትን ለአለም አበርክቷል። አብዛኛውን ዘመኑን ያሳለፈው የዳርዊያን ዝግመተ ለውጥ አስተሳሰብ ወደ ማህበረሰቡ እንዲዋሃድ በማድረግ ነው። በተለይ ደግሞ The Selfish Gene እና The God Delusion በምዕራቡ አለም ሳይንቲስቶችና ማህበረሰብ ትልቅ መነጋገርያና መካራከርያ ናቸው።

ኘ/ር ሪቻርድ ዳውኪንስ አፅናፈ አለምን የፈጠረ ሰዋዊ (Personal) የሆነ ፈጣሪ አለመኖሩን ለማስረዳት ከፃፋቸው መፅሐፍት "The God Delusion" ዋነኛው ነው። መፅሐፉ ከ35 በላይ በሚሆን ቋንቋዎች የተተረጎመ ሲሆን ከ4 ሚሊዮን በላይ ኮፒዎች ተሸጧል። በኢንተርኔት የተነበበበት (ዳውንሎድ) የተደረገበት ብዛት እጅግ ብዙ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። በአረበኛ ቋንቋ ብቻ እንኳ ከ3 ሚሊዮን ኮፒ በላይ ዳውንሎድ ተደርጓል። መጽሐፍ በበርካታ ሚድያዎች እና ጋዜጦች መወያያ እና መከራከሪያ ሆኖ ነበር። በምላሹመ በርካታ መጽሐፍት ተፅፈዋል። በታዋቂ ሰባኪዎች ዘንድ ከፍተኛ ትኩረት ተሰቶት የስብከት አጀንዳ ሁኖ ነበር። ከዚህ አንፃር ዳውኪንስ የተሳካለት ይመስላል። ዳውኪንስ መፅሐፉን የፃፈበት አላማ የአንባቢያንን ንቃተ ህሊና ለመቀስቀስ ወይም ለ(Consciousness Raising) ነበር።

ዳውኪንስ በመግቢያው ኤቲስትነት የተሻለ አኗኗር እንደሆነ፣ የተፈጥሮ ምርጦሽ ከሐይማኖት የተሻለ ተፈጥሮን እንደሚገልፅ፤ ህፃናት በወለጆቻቸው ሐይማኖት መጠራት እንደሌለባቸው እና ኤቲስቶች የሃሳብ ነፃነት ስላላቸው በዚህም ሊኮሩ እንደሚገባ ያስገነዝባል።

ዳውኪንስ ፈጣሪን እና ሀይማኖትን ከሁለት አቅጣጫ ያየዋል። የመጀመሪያም ክፍል "Einsteinian religion" ሲሆን በዚህ ሀይማኖት ፈጣሪ Non-interventionist ነው። ዳውኪንስ ይህን መሰል ፈጣሪ አለም የለምም ለማለት እንደሚከብድ ይናገራል። ስለዚህ የመፅሐፉ ትኩረት ይህ የአንስታየን አምላክ አይደለም። ሁለተኛው ክፍል "Supernatural religion" ሲሆን በዚህም የሚመለከው አምላክ Interventionist ነው። ይህ አምላክ በነገሮች ጣልቃ እንዲገባ ተደርጎ በመሳሉ ለማመንም ለመከድም ግልፅ በመሆኑ ደውኪንስ ትኩረት ስቶ ተችቶታል። እንደ ዳውኪንስ ገለፃ ሳይንስ በዚህ ዘመን ሁለንታ እንዴት እንደተገነባ እና በዘመኑ ያደረገውን ዝግመታዊ ለውጥ ከሐይማኖት በተሻለ ሁኔታ ያብራራል ይላል። ለእግዚአብሔር መኖር እንደዋነኛ ምክንያት የሚጠቀሰው የተፈጥሮን የውስብስብነት ሚስጢር በሳይንስ የተፈታና እየተፈታ ያለ መሆኑን ያስረዳል።

ዳውኪንስ የበርካታ አማኝ ሳይንቲስቶችን፣ ፈላስፋዎችን፣ በተለይም የስነ-መለኮት ሙህራን የሚያቀርቧቸውን ትንታኔዎች (Arguments) ፈትሿል፡፡ ተገቢ ምላሽም ሰቶበታል፡፡ ዳውንኪስ ፈጣሪ አለመኖሩን በእርግጠኝነት መናገር እንደማይችል አመለክቷል፡፡ ነገር ግን በሐይማኖቶች ስለፈጣሪ የተሰጡት አወዛጋቢ ባህሪያት አሳማኝ እንዳልሆኑ ጽፏል፡፡ ዳውኪንስ ስለ እግዚአብሔር ያለውን አቋም ሲያጠቃልል "The Universe Without a God Is Preferable to The Theory of a Universe with a God" ይላል፡፡ ዳውኪንስ በመፅሐፍ የአምልዕኮን ቅዣትነት ብቻ ሳይሆን የሐይማኖት እና የስነ-መግባርን ምንጭ እና እድገት ቃኝቷል፡፡ ዳውኪንስ እንዳለው ሀይማኖት እንደማንኛውም አስተሳሰብ ተፈጥሮአዊ ዕድገት አለው፡፡ በሳይንስ እይታ ሊጠና የሚገባው ጉዳይም ነው፡፡ በሌላ በኩልም ስነ መግባር (Morality) በሐይማኖት በኩል ሳይሆን ሳይንሳዊ ማብራሪያ ያስፈልገዋል፡፡ ስነ-ምግባር ከሐይማኖት ጋር መተሳሰሩ ልክ እንዳልሆነ ለማስረዳት ምክሯል፡፡

ሪቻርድ ዳውኪንስ በፃፈው "The God Delusion" መጽሀፍ በርካታ ፅንሰ ሀሳቦችን አንስቶበታል፡፡ ዳውንኪስ በዚህ መጽሀፍ በጠቅላላው ህዝብ ታዋቂ ይሁን እንጅ ሳይንቲስቶችን፣ ፀሀፊዎችን እና ፈላስፋዎችን የሚማርኩ በርካታ መጽሀፍትን ጽፏል፡፡ በተለይ "Selfish gene" የተባለው 1976 የታተመው መጽሀፍ ተፅዕኖ ፈጣሪ እንደሆነ ተመስክሮለታል፡፡ ሪቻርድ ዳውንኪስ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሳይንቲስት ስለመሆኑ በ2006 "Richard Dawkins- how a Scientist changed the way we think- Reflections By Scientists, Writers and Philosophers" የሚል መጽሀፍ ተፅፏል፡፡

ዳውንኪስ እንደማንኛውም ፀሐፊ ትችቶች ይደርሱበታል በተለይ ከአንተሊጀንት ዲዛይን አራማጆችና ተመሳሳይ አቋም ካላቸው ሰዎች፡፡ ዳውንኪስ ለአለፉት 40 ዓመታት የኖረው የአድናቆትና የትችት ጎርፍ ሲወርድበት ነው፡፡ ብዙ ትችት እና አድናቆት ማስተናገድ መቻል ብልህነት ነው፡፡ አንዳንድ ባለስልጣናት፣ ሙህራን እና በተለይ የሀይማኖት መሪዎች ብዙ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ‹‹አንቱ›› እየተባሉ ስለሆነ ትችትና አያውቋትም፡፡ ምን አልባትም በድንገት ትችት ከደረሰባቸው ጤናቸው ሊቃወስ ይችላል፡፡ ትችትን በፀጋ መቀበል ፈታኝ ነው፡፡ ቢሆንም ሰው እስከሆነን ድረስ በምንናገረው በምናስበው እና በምንኖረው የአኗኗር ዘይቤ እንከኖች ይኖሩብናል፡፡ እነዚህ እንከኖች ከሌሎች ትችት እንዲነሳሳብን ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ያለን አማራጭ ሁለት ነው፡፡

አንደኛ ላለመተቸት ፍፁም መሆን ይህ ደግሞ የሰው ልጅ ባህሪ አይደለም ስለዚህ ላለመተቸት መኖር የለብንም፡፡ ሁለተኛ ለትችት በራችን ከፍተን ከትችቱ መልካም

Created in Master PDF Editor

ትምህርቶችን ለመውሰድ መዘጋጀት፡፡ ይህ አማራጭ የሌለው አማራጭ ነው፡፡ ዳውንኪስም በተደጋጋሚ ይላል <<Open Your Mind>>

በነገራችን ላይ እግዚአብሔር ቅዠት ነውን? ማርሻል ብሬን Why Won't God Heal Amputees በሚል ድህረ ገጹ ላይ እንዲህ ይላል፦

<<Everything that we associate with religion is imaginary. God, the Bible, Jesus, the resurrection, prayer, the Ten Commandments, the creation story, your soul, everlasting life, heaven... every bit of it is the product of human imagination. The same goes for Allah, the Koran and so on. As a species we have believed all of this religious dogma for centuries, and many people believe it today to some degree. And yet, it is all fiction. It is just as fictional as were the gods of the Egyptians, the Romans and the Aztecs. The clear, unambiguous evidence is all around us. All religion is delusion. With any luck you can see that now, and you can start down the road to recovery -- you can begin the process of healing that will free you from your own personal delusions.>>

21. Bierf Answers to the Big Questions

እስቲፈን ሃውኪንግ አማኝም ኢ-አማኝም የሚያጨበጭብለት የጽናት ምሳሌና የሳይንስ ሊቅ ነው፡፡ አይበገሬ እስቲፈን ሃውኪንግን አማኞች የኛ ነው ኢ-አማኞችም የኛ ነው ሲሉት ኑረዋል፡፡ ኢ-አማኞችም የኛ የሚሉት በሳይንስ መስክ ባደረገው ትልቅ ምርምር እግዚአብሔር የሚባልን ነገር ከመሰረቱ ወደ መናድ ስለተጠጋ ነው፡፡ የህይወት ዘመን ህልሙም የእግዚአብሔርን ሀሳብ (the mind of God)ን ማወቅ እንደነበር ይነገርለታል፡፡ አማኞችም የኛ ነው የሚሉት እግዚአብሔር የሚለውን ቃል እንደበጎ ነገር ሲለሚያነሳና እስከቅርብ ጊዜ ለእግዚአብሔር ክፍት ቦታ ይተው ስለነበር ነው፡፡ ይህን ማለቱ መጽሀፍቱ በአማኞች ዘንድ እጅግ እንዲነበቡ ሁኗል፡፡

መ. ኃ. ዶ/ር መስቀል 'ከምድራዊነታችን ባሻገር፣ ሦስተኛ መጽሐፍ' ላይ እንዲህ ይላሉ፦ "እስቲፈን ሃውኪንግ ጠፈር ወሰን የሌለው የማይዘረጋ የማይሰበሰብ አስቀድሞ የነበረና የማይጠፋ ራሱን በራሱ የሚያቆይ ነው ብሎ ማሰብ ለፈጣሪ መኖር ምንም ክፍተት አለመስጠት ነው፡፡ ይል ነበር" ሲሉ አሞግሰውታል፡፡ ከጊዜ በኋላ ስለ አረመው አስተሳሰቡ ሲጽፉም "ነገር ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጠቅላላ ጠፈራዊ አካላትን የሚገዛ ሕግ መኖር አለበት፤ ይህም ሕግ በሰዎች ሊታወቅ ይችላል የሚል አስተሳሰብ አመንጭቷል፡፡ ይህንንም አስተሳሰብ በጉልህ የሚያንጸባርቅ "The Grand Desighn" የተባለ መጽሐፍ በቅርቡ ታትሞ ተሰራጭቷል፡፡ የሚገርመው ይህንን መጽሐፍ የጻፈው እስካሁን ስለ እግዚአብሔር መኖር ብዙ የተናገረ ይኸው እስቲፈን ሃውኪንግ ነው፡፡" ሲሉ በቁጭት ይተርኩታል፡፡ ተስፋ ያልቆረጡት የክርስቲያን ሳይንስ አራማጁ መ. ኃ. ዶ/ር መስቀል በዚህ "The Grand Desighn" መጽሐፉ ይላሉ፦ "በዚህ

Created in Master PDF Editor

መጽሐፉ አካል ከምንም ሊፈጠር ይችላል:: አካል ከምንም ተገኝቶ የራሱን ሕግ ተከትሎ የሚሄድ ከሆነ የበላይ ተቆጣጣሪ አያስፈልገውም፤ ስለዚህ የፈጣሪም መኖር አያስፈልግም:: ማንኛውም አካላዊ ክስተት ከተጠቀሰው አጠቃላይ ሕግ ስለማይወጣ ይህንን ውሱን የእንቅስቃሴዎች ሂደት የሚለውጥ - ከበላይ ሆኖ ተአምር የሚሠራ፥ የውጪ ኃይል መኖር አያስፈልግም ይላል:: ነገር ግን እግዚአብሔር የለም አይልም - ትንሽ የፍርኃትና የጥርጣሬ ክፍተት ትቷል::" ምን አልባት እስቲፈን ሃውኪንግ የሚጽፈው ይህን ያህል ተጽዕኖ የሚፈጥር ከሆነ የመጨረሻን መጽሀፍ ማንበብ የተሻለ ነው:: ድንቁ የክፍለ ዘመናችን ሳይንቲስት እስቲፈን ሃውኪንግ Brief Answers to the Big Questions ተብሎ በታተመው የስንብት መጽሃፍ ለእግዚአብሔር ክፍት ቦታ እንዴለለው አሳይቶበታል:: አማኞችም ሳያጉረመርሙ አልቀረም:: I am a scientist with a deep fascination with physics, cosmology, the universe and the future of humanity የሚለው ሃውኪንግ ስለ እግዚአብሔር መኖር አቋሙን ሲገልጽ የሚከተለውን ብሏል::

> <<Do I have faith? We are each free to believe what we want, and it's my view that the simplest explanation is that there is no God. No one created the universe and no one directs our fate. This leads me to a profound realisation: there is probably no heaven and afterlife either. I think belief in an afterlife is just wishful thinking. There is no reliable evidence for it, and it flies in the face of everything we know in science. I think that when we die we return to dust. But there's a sense in which we live on, in our influence, and in our genes that we pass on to our children. We have this one life to appreciate the grand design of the universe, and for that I am extremely grateful.>>

ይህ ታላቅ ሰው ሀሳቡን እየቀየረ ሳይሆን ሳይንስን ለህዝቡ ለማቅረብ የተጠቀመበት ስልት እንደሆነ ወዳጆቹ በተለይ ዳውኪንስ ያውቃል:: ሀውኪንግ በስንብት መጽሃፉ 10 ጥያቄዎችን በመጠየቅና ዘመኑ የሚፍቅደውን መልስ ሰቶበታል:: *Is there a God? How did it all begin? What is inside a black hole? Can we predict the future? Is time travel possible? Will we survive on Earth? Is there other intelligent life in the universe? Should we colonise space? Will artificial intelligence outsmart us? How do we shape the future?* ጥያቄዎቹ አንገብጋቢና እንቅልፍ የሚነሱ ናቸው:: መልሶቹም ምን ማድረግ እንዳለብንና እንዴት መኖር እንዳለብን የሚያሳስቡ የአባት ምክሮች ናቸው:: ሳይንስና ሳይንቲስቶች እስከዛሬ እንዳደረጉት ሁሉ ነገም ብዙ ጥያቄዎቻችንን ይመልሱልናል፣ በአይናችንም ታምር ያሳዩናል፣ በእጃችን አፋችንን እስክንጨብጥ ድረስ ያስደምሙናል:: እውነት ለመናገር ሳይንስ መ/ር ዶ/ር ዘበነ ለማ <በሰው ምንድን ነው> መጽሃፋቸው እንደሚሰብኩት ተስፋ የሌለው ተራራ አይደለም:: እውነተኛው ሳይንስ በደማቅ ታሪክ የተጎናጸፈና ስለ ነገ ብሩህ ተስፋ ያለው ነው::

Created in Master PDF Editor

የመኮፈስና ከኔ በላይ ላሳር ነው የሚል ንቀት ኑሮበት ግን አያውቅም። ምን አልባት ዶ/ር ዘበነ ለማ የሚያቀነቅኑለት ሀይማኖት ሊሆን ይችላል።

እኛ ግን ህይወት ቀያሪውን እውነተኛው ሳይንስ እንሰብካለን። የምንመሰክረው ያየነውን እንጅ ነበረ የሚባለውን አይደለም። ሳይንስ የሰውን ልጅ ህይወይት ቀይሯል፣ ማየት ማለት ይህ ነው። ሳይንቲስቶቹ science is the magic that works የሚሉት በሰው ልጅ ህይወት ያሳደረውን ተፅዕኖ ተመልክተው ሳይሆን አይቀርም። ታምረኛው ሳይንስ ባለፉት 400 ዓመታት በሚገርም ፍጥነት እየተመነደገ ነው።

የዛሬ 400 ዓመት ለኖረ ሰው እኛ ወደ ኋላ ሂደን ወይም እሱን ወደ አሁን አምጥተን ስለ ኢንዱስትሪ አብዮት፣ ስለ ስልክ፣ ስለ አውሮፕላን፣ ስለ ሬዲዮ፣ ስለ መኪና፣ ስለ ቴሌቪዥን፣ ስለ ሮኬት፣ ስለ አንቲባዮቲክስ፣ ስለ ራዳር፣ ኒኩሊየር ሀይል፣ ስለ ኮምፒውተር፣ ስለ ሮቦት፣ ስለ ኤቲ ኤም (ATM)፣ ስለ ባቡር፣ ስለ ፎቶ ግራፍ (ካሜራ)፣ ስለ ቴሌግራፍ፣ ስለ ኤሌክትሪክ፣ ስለ ሰማይ ጠቀስ ህንፃዎች፣ ስለ ዲጅታል አገልግሎት፣ ስለ ክትባት፣ ስለ የሰውነት አካል ንቅለ ተከላ፣ ስለ ሳተላይት፣ ስለ አርቴፍሻል ኢንተሊጅነስ (AI)፣ ስለ ኢንተርኔት፣ ስለ ሞባይል፣ ስለ ማህበራዊ ሚዲያ፣ ስለ ዲኤንኤ (DNA)፣ እንዲሁም በሁሉም የማህበራዊ እና የተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፎች የተመዘገበውን እጅግ አመርቂ ግኝቶች ብንነግረው ምን ይሰማው ይሆን? የግርምተ ሳይቴክ መጽሀፍ ፅሃፊ ሰለሞን ሙሉጌታ እንኳን 400 ዓመት 250 ዓመት በፊት የነበርን ሰው ዛሬን ብናስጎበኘው የሚሰማውን ስሜት መድነቅ፣ መገረም፣ ግር መሰኘት በሚሉ ቃላት ሊገለፅ አይችልም ይልቅስ በልብ ድካም የሚሞት ይመስለኛል ሲልበትላንት እና በዛሬ መካከል ያለውን የምድር እና የሰማይ ያህል ርቀት ለማስረዳት ሞክሯል።

ግን ይህን ሁሉ በጎ ነገር ያደረገው ሳይንስ ፍጹም አይደለም። አንደኛ ያልመለሰው ጥያቄ ከመለሰው ይበዛል፣ ሁለተኛ በሰው ልጆች ላይ ከባድ ስጋቶችን ደቅኗል።

ሳይንስና ቴክኖሎጅ የሰውን ልጅ ህይወት በማዘመን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ቢያደርግም በተፈጥሮ ከሚመጡ አለምአቀፋዊ ስጋቶች ያልተናነሰ ስጋት ግን ከፊታችን ደቅኖብናል። ሳይንስና ቴክኖሎጅ እንደ ስጋት የሚቆጠረው ችግሮች እንዲፈጠሩ በማድረግ ወይም በማባባስ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ሳይንቲስቶች Alien ከሚባሉ መኖራቸው ካልተረጋገጠ የጠፈር አካላት ጋር ለመገናኘት እየተሞከረ ነው እናም በአሊያኖች የመወረር አደጋ ውስጥ ነን። ሁለተኛ ሳይንስ የደቀነብን Artifical inteligence (AI) ነው። ብዙ ፀረ-AI አቀንቃኞች እንደሚሉት ሮቦቶች የሰውን ልጅ ስራ-አጥ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በህልውናው ላይም የተጋረጡ መሰናክሎች ናቸው። ሶስተኛ Gene editing ሰዎች ልጆቻቸው ከመደበኛው ወይም በተፈጥሮ ከሚሆነው ለየት ብለው እንዲወለዱ ከፈለጉ ሳይንሱ ሊያግዛቸው የተነሳ ይመስላል። በሰው ልጅ

Created in Master PDF Editor

ላይ ትንሽ የዘረመል ለውጥ ማካሄድ ለነበሩ ሰው ስጋት ነው። በተጨማሪም ለአየር ንብረት ለውጥና ለጅምላ ጨራሽ ጦርነቶች አቀጣጣይ ነው።

22. The stars died so that you could be here today.

የካርበን አተም የህይወት መሰረት (Building block) ነው። የካርበን ሞለኪውሎች (organic molecules) ህይወት ያላቸው አካላትን ገንብተዋል። ፕሮቲኖች፣ ፋቶች (fats) እና ከርቦሀይድሬቶች የተለያየ የካርቦን ውህዶች ናቸው። ይህ የህይወት ምሰሶ የሆነው ካርቦን የተገኘው ከቢሊዮን አመታት በፊት ከፈነዳ ኮከብ ነው። ሳይንቲስቶቹ supernove expiosion ይሉታል።

ካርበን እንማንኛውም ንጥረ ነገር የተገናበው ካፕሮቶን፣ ኤሌክትሮን እና ኒውትሮን ነው። ፕሮቶን፣ ኤሌክትሮን እና ኒውትሮን ድንቅ በሆነ ስብጥር በኬምስትሪ የሚታወቁትን ንጥረ ነገሮች አስገኝተዋል። የሶስቱ ምሰሶዎች ስምምነት እና ስብጥር በሶስቱ ስላሴዎች ማለትም በኤሌክትሮ-ማግኔቲክ፣ በጠንካራው ኒውክለር እና በደካማው ኒውክለር ሀይል ተሳስረዋል። ኤሌክትሮ-ማግኔቲክ ተመሳሳይ ሙል ያለቸውን ሲያገፋፋና ተቃራኒ ሙሉ ያለቸውን ሲያቀራርብ ጠንካራው የኒውክለር ሀይል ፕሮቶንን በአተም ማዕከላዊ አካል እንዲረጋጋ ያደርጋል። በኤሌክትሮ-ማግኔቲክ ሀይል እርስ በእርሳቸው የሚገፋፉት ፕሮቶኖች በጠንካራው የኒውክለር ሀይል ባለቡት እንዲቆዩ ሁኗል። ይህ ባይሆን ኑሮ በአተም ውስጥ አንድ ፕሮቶን ብቻ ይሆንና የኬሚስትሪው ፔሬዲክ ቴብል ሳይፈጠር ይቀር ነበረ፣ ምንም አይፈጠርም ነበር ማለት ነው።

ሌላኛው ደካማው ኒውክለር ሀይል ደግሞ በንኡስአተሞች (subatomic particles) የሚገኝ ሲሆን የኒውትሮን መገነጣጠል እንዲከሰት ያደርጋል። ኒውትሮን በዚህ በደካማው ሀይል መሰረት ሲገነጣጠል (radioactive split) ሲፈጠር ወደ አንድ ፕሮቶን፣ አንድ ኤሌክትሮን እና አንድ ፀረ-ኒውትሮን ይቀየራል። የዚህ የደካማው ሀይል ደካማ መሆን ኒውትሮን በቀላሉ እንዳይገነጣጠል ጠብቆታል። ይህ የፊዚክስ ህግ ነው፣ ጥልቁን የመተንተን አቅሙ ለጊዜው የለኝም።

<We are star dust> የሚለውን መፈክር ብዙ ሰዎች ይጋሩታል። ምን አልባት <አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ> ከሚለው ጋር ይመሳሰላል። ለኔ ከመፈክር የላቀ ትርጉም አለው።We are star dust ምን ማለት ነው?

ሰዎች እድሜያቸውን ሲጠየቁ ከተወለዱበት ቀን ጀምሮ በመቁጠር 20 አመቴ፣ 50 አመቴ ነው፣ የ80 አመት የእድሜ ባለፀጋ ነኝ ሊሉ ይችላሉ። እውነቱ ግን ከዚህ ይለያል። ሰው የተገነባው የዛሬ 13.8 ቢሊዮን አመት በቢግ ባንግ ወቅት ከተገኘው የሀይድሮጅን ንጥረ ነገር ነው። በምንጠጣው ውሃ (H_2O) ውስጥ ያለው ሀይድሮጅን

Created in Master PDF Editor

የተፈጠረው በቢግ ባንግ ወቅት ነው፡፡ ቀሪው የሰው ሰውነት የተገናበው ከዋክብት በሚፈነዱበት ወቅት ይህን ተያይዞ በነበረው ሂደት ከተፈጠሩ ንጥረ ነገሮች ነው፡፡ ስለዚህ እድሜአችን ከመቶ አመት ያነሰ ሳይሆን ቢሊዮን አመታትን አስቆጥረናል፡፡ ህንዶች ጥሩ አስተሳሰብ አላቸው ህይወት ይደገማል ብለው ያምናሉ፡፡ ይብዛም ይነስም ነገሩ እውነት አለው፡፡ እኛ ሰዎች በሰዋዊ አገላለፅ በሞትን ሰዓት ወደ እፅዋትና እና ወደ ነፍሳትነት እንቀየራለን ማለቴ እፅዋትና ነፍሳት ተመገቡን ማለት እነሱን ሆን ማለት ነው፡፡ ዙሩ ይቀጥላል፡፡ እናም አንድ ሰው ዳይኖሰር አልጠፋም ብሎ ቢከራከር ምክንያታዊ ሊሆን ይችላል፡፡ በዳይኖሶሩ አካል የነበሩት ንጥረ ነገሮች ወደ ሌሎች ፍጥረታት እስከተሸጋገሩ ድረስ በእኔ ውስጥ ዳይኖሶር የለም ብዩ መካድ አልችልም፡፡ የስነ ህይወት ሊህቃን የሰው ልጅ አመጣጥ ከዝንጀሮ መሰል እንስሳ ነው ሲሉ በርካቶችን አስደምመዋል፤ አስደንግጠዋልም፡፡ የፊዚክስ ሊህቃን ግን የባሰ ነገርን ነገሩን *we are made of stardust. We can be grateful that stars reduced stardust back out to the galaxy when they died because there could be no plants or life with out the death of stars.*

23. የሰውን ልጅ ተፈጥሮ ያላገናዘቡ፣ ሀይል የተቀላቀለባቸውና ፍትህ የጎደላቸው ትዕዛዛትና ስብከቶች

"ይህችን መፅሐፍ ይዞ የሚፀልይ የጭለማ ኃይል አይጋርደውም፣ አጋንንት አይቀርቡትም፣ በሌሊትም በቀንም የሚያስደነግጠው ነገር አይኖርም፡፡ ከልዩ ልዩ በሽታም የተጠበቀ ነው፡፡" ሰኔ ጐልጐታ

ኮመድያኑ George Carlin የሰውን ልጅ ተፈጥሮ ያላገናዘቡ፣ ሀይል የተቀላቀለባቸውና ፍትህ የጎደላቸው ትዕዛዛትና ስብከቶች በአጭር የኮመዲ ስራው እንዲ ነበር የገለጸው፦

> <<Religion has actually convinced people that there's an invisible man - living in the sky - who watches everything you do, every minute of every day. And the invisible man has a special list of ten things he does not want you to do. And if you do any of these ten things, he has a special place, full of fire and smoke and burning and torture and anguish, where he will send you to live and suffer and burn and choke and scream and cry forever and ever . . . But He loves you!>>

የምርጥ በአማረኛ የተዘጋጁ የፍልስፍና መጽሃፍት ጽሃፊው በፍልስፍና ፍቅር ያበደው ብሩህ አለምነህ አለማዊና መንፈሳዊ ህይውትን በአመዛዘነበት ጽህፉ እንዲን ነበር ያለው፦

Created in Master PDF Editor

> ቁሳዊው ማህበረሰብ ሃብት በማከማቸትና በተደላደለ ህይወት ሲያምን ክርስትና ግን <ገንዘባችሁን ለድሆች አከፋፍሉ> በማለት በመጠኑ እንድንኖር (1ጴጥ 5፡8) ያዛል፡፡ ቁሳዊው ማህበረሰብ ድህነትን በመፀየፍና ሀብትንና ሃብታምነትን በማሞገስ ሲኖር ክርስትና ግን ሃብታምነትን በማንኮሰስ ደህነትን ያፅናናል (ሉቃ 18፡24)፡፡ ቁሳዊው አለም በፈንጠዝያን በቡረቃ፣ በተድላና በደስታ የሚኖሩ ሰዎችን ሲያበረታታና ሲሸልም፣ የክርስትና መምህራን ግን "ከዚህ ዓለም ደስታ ርቀው፣ ዳዋ ጥሰው፣ ድምጸ አራዊትን፣ ግርማ ሌሊትን ታግሰው፣ ጤዛ ልሰው፣ ድንጋይ ተንተርሰው፣ የላመ-የጣመ ሳይቀምሱ፣ የሞቀ-የደመቀ ሳይለብሱ፣ እኖር ባይና እከብር ባይ ልቦና በሚሰራው ኃጢአት ሰውነታቸውን ሳያሳድፉ የሚኖሩትን መናንያንን ያሞግሳል፡፡ ዓለማዊያን ዘፈን ለሚወዱ የሙዚቃ መሳሪያዎችንና ኮንሰርቶችን ሲያዘጋጁ፣ ክርስትና ግን ዘፈንም ሆነ ዳንስ ሃጢያት ነው፤ መንግስተ ሰማያትም አያስገባም (ገላ 5፤21) ይላል፡፡ (ፍልስፍና 2፣ 3ኛ ዕትም፣ 176-177)

የሉቃስ ወንጌል 13፣33 እንዲህ የሚል መራራ ስብከት አለ "ወደ እኔ የሚመጣ ሊከተለኝም የሚወድ አባቱንና እናቱን፣ ሚስቱን እና ልጆቹን፣ ወንድሞቹንና እህቶቹን፣ የራሱንም ሰውነት እንኳ ቢሆን የማይጠላ ደቀመዝሙሬ ሊሆን አይችልም፡፡" በዚህ የሰውን ልጅ ተፈጥሮ ያላገናዘበ፣ ሀይል የተቀላቀለበትና ፍትህ የጎደለው ስብከት የተገረመው አገኘሁ አሰግድ *"እንዲያው ይቅርታ አድግልኝና እየሱስ፣ እንኳን እናትና አባቴን አሁን ታይፕ የማደርገውን ፅሁፍ እንኳ ትቼ ልከተለህ አልችልም፡፡ ካንተ በፊት እናትና አባቴን... ቤተሰቤን ነው የማውቀው፡፡ እና እናቴን ትቼ? አባቴን ትቼ? (አቦ) ስንቱን ትተን ስንቱን እንከተል፣ እናማ ይለፈኝ! አልከተልህም፤ አንዳትከተለኝ፡፡"*ብሏል፡፡ ብሩህ አለምነህም ፈላስፋው ዘርዓያዕቆብን ከተፈጥሮ በመራቅና ከምንኩስና ጋር በመወዳጀት የሚያስከትለውን ቅጣቶች ሲያጠቃልል እንዲህ ነበር ያለው፦

> በእነዚህ ቅጣቶች (ከምንኩስና ጋር በመወዳጀት ከሚመጡት) የተነሳ የሰው ልጅ ዘግይቶም ቢሆን ወደ ተፈጥሯዊ ባህሪው መመለሱ አይቀርም፡፡ ተፈጥሮ ከምናስበው በላይ በእኛ ላይ እጅግ ሀይለኛና ጉልበተኛ ናት፡፡ እናም ተፈጥሮ ላይ ማመፁ አያዋጣም፤ ከንቱ ድካም ነው፡፡ ሰዎች ተፈጥሮን የሚያሸንፉ እየመሰላቸው ነፍሳቸውን ሊያድኑ ስጋቸውን ጥለው ይመንናሉ፤ ቤተሰባቸውንና ሀብታቸውንም ሜዳ ላይ በትነው ይመነኩሳሉ፡፡ ከዚም የማያወጣ ፀሎት ለቅፅፈት ይሆንባቸዋል፡፡ በመሆኑም የሰው ልጅ ሀብትንና ብልፅግናን በማጥላላት እንዲሁም ተፈጥሯዊ ስሜቱን በመጨቆንና በማዋረድ (ራሱን በማሰቃየት) የገነባው ህብረተሰብ፣ ባህልና ሀይማኖት፣ ሞራልና ስነምግባር ሁሉ የማያዛልቅ ትምክህትና ትዕቢት ነው፡፡ (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 47)

Created in Master PDF Editor

ለፈላስፋው ዘርዓያዕቆብን ተፈጥሮ ሁሉ ነገሩ ናት። ከተፈጥሮ ህግ መሸሽ የሚያስከትለውን መዘዝ ጥንቅቆ ያውቃል።ብሩህ አለምነህ የዘርዓያዕቆብን የፍልስፍና አምድ ሲተነትን እንዲህ ይላል፦ "እግዚአብሔር የሚገልፀው በተፈጥሮ ህግና ስርዓት ውስጥ ብቻ ነው ይሄም የተፈጥሮ ህግና ስርዓት ብቸኛው እውነት ነው። ልቦና የማይደርስበት ሀይማኖታዊ አስተምህሮ መኖር የለበትም። በመሆኑም ሁሉም ሀይማኖታዊ አስተምህሮዎች በልቦና የሚፈተሹና የሚረጋገጡ መሆን አለባቸው። ሀይማኖታዊ አስተምህሮዎች ልቦናችን ከሚነግረን የተፈጥሮ ህጋጋት ጋር መጣላት የለበትም፤ የሚጣልም ከሆነ ስልጣኑ (ትክክለኛው) ሀይማኖት የሚለው ሳይሆን የተፈጥሮ ህግ (ልቦናችን) የሚነግረን ነው። እጅግ የተዋጣለትና ትክክለኛው የአኗኗር ዘዴ ከተፈጥሮ ህግና ስርዓት ጋር መስማማት ነው።" (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 8-9)

ዋው! እጅግ የተዋጣለትና ትክክለኛው የአኗኗር ዘዴ ከተፈጥሮ ህግና ስርዓት ጋር መስማማት ነው ምንኛ ደስ የሚል እይታ ነው። በቃ የሰው ልጅ በተፈጥሮ ላይ ያለው ስልጣን ኢምንት ስለሆነ የሚጠበቅብን የተፈጥሮን ህግ ማክበር ነው፣ ሞትንም ቢሆን እየመረረን መቀበል ነው። አንዳንዴ ግን እንዲህ ይባላል ለምሳሌ፦ ማቴዎስ 16፣18 ላይ "እውነት እላችኋለሁ፣ የሰው ልጅ (ኢየሱስ) በመንግስቱ ሲመጣ እስኪያዩት ድረስ እዚህ ቆመው ካሉት ሞትን የማይቀበሉ አሉ" ይላል። ለዚህ ተፈጥሮዐዊ ሞትን ወደጎን ለተወው አሳዛኝ ስብከት አገኘሁ አሰግድ መልስ ሲሰጥ "ይሄው ስንት ዘመኑ እስካሁን አልተመለሰም።ሞትን የማይቀበሉ አሉ የተባሉትም ሞተው አለቁ። ውይይ... ምን ገጥሞት ይሆን? በርግጥ እንዲህ አይነት ነገር መፃፍ ብዙዎችን እንደሚያናድድ ይገባኛል። ግን እኮ እመጣለሁ ብሎ ቀልጦ መቅረትም ይበልጥ ያናድዳል።"ይላል። አገኘሁ አሰግድ ቀጥሎም በግጥሙ፦

እዛ ወዲያ ማዶ፣ የእግዜር ስፍር ቃል

ያየ አመነዘረ፣ ሲል ህጉን ያረቃል፣

እኔ እዚህ ማዶ፣

እልቤ መሃል ላይ ሺዋን አፀድቃለሁ፣ ከ"ሺ"ዋ ወድቃለሁ።

እዛጋ ሰባኪው፣ተሰቅሎ አዳነህ ብለው ይነግሩኛል፣

ከመዳኔ በላይ ህመሜ ጣፍጦኛል።

አትይ፣ አታመንዝር ያለው ትዕዛዝ ቃሉ፣

"አትችለውን አድርግ" ይመስላል መሃሉ፣ (አገኘሁ አሰግድ፣ ከሸገር ብሎግ ተቀንጭቦ የተወሰደ)

Created in Master PDF Editor

ሀይማኖቶች የተመሰረቱበትን መሠረታዊ ፀንሰ ሀሳብ፣ የተስፋፉበትን አካሄድና ዛሬም ያላሻሻሉትን አቋም ሳስብ ምን ያህ ግትርነት እንደነገሰ ይታሰበኛል፡፡ የሀይማኖቶች አምድ በሀይል የተሞላ ነው በቃ ይህን አድርግ ወይም ያን አታድርግ ካደርክ ግን በእሳት አቃጥልሃለሁ፡፡ ሰባኪዎች እግዚአብሔር የምርጫ አምላክ ስለሆነ ማንንም እመኑብኝ ብሎ አያስገድድም ይላሉ፡፡ እንዴ ያላመነ ያልተጠመቀ አይድንም ማለት ምን ማለት ነው? ስጋየን ያልበላ ደሜን ያልጠጣ መንግስተ ሰማያት አይገባም ማለት ምን ማለት ነው? ንስሃ ያልገባ፣ ለካህን ያልተናዘዘ፣ ፍትሀት ያልተደረገለት ለገነት ብቁ አይደለም ማለት ምን ማለት ነው? ሙሐመድን የተቃወመና ቁርዓንን ያቃለለ፣ ያልተቀበለም የማይጠፋ እሳት ይዘንብበታል ማለት ምን ማለት? በእግዜር አሁን በሀይል ማሳመን ነው ወይስ ፍትሀ፡፡ ከእኔ በቀር ማንንም አታምልክ፣ ከእኔ በቀር የትም አትሂድ፣ ከእኔ በቀር የማንንም አትስማ ማለት ፍትሃዊነት ከሆነ በእውነት ፍትህ ገና አልገባንም፡፡ ነፃነትም ምን እንዳሆነ አልገባንም፡፡ ቢያንስ ፖለቲከኞቻችን እንኳ ተሻሽለው እኔን ምረጡ እኔን ከመረጣችሁ ይህንን ያን አሟላለሁ በሚሉበት ሁኔታ፡፡ ከአስፈለገም ሌሎችን ፓርቲዎች መምርጥ ከፈለጋችሁ ጉጅነቱ ይህ ነው ሂዳችሁ አቋማቸውን እዩ ለእናንተ አይጠቅሙም እኛ እንሻላለን በሚሉበት ዘመን አድርግ ያልኩህን ብቻ አድርግ፣ ካልሆነ ወዮልህ እያሉ እያስፈራሩ ነፃነቱ የቱ ጋ ነው?

የማንችስተር ዩናይትድ የእግር ኳስ ክለብ ደጋፊዎቹን ከእኔ ውጭ የማንንም ቡድን ብትደግፉ ወዩላችሁ ይላልን? አንበሳ ጫማ ፋብሪካ የእኔን ጫማ ካልተጫማችሁ እግራችሁ ይሰበር ይላልን? ሰይፉ ፈንታሁንስ የእኔን ፕሮግራም የማትከታተሉ አይናችሁ ይታወር ይላልን? ኮካ ኮላ ድርጅትስ ከእኔ ምርት ውጭ የምትበሉትና የምትጠጡት መርዝ ይሁናችሁ ይላልን? በጭራሽ እንደዚህ አይነት የሞተ ህግና ማስታወቂያ የለም፡፡ በአማልዕክት ቤት ግን ከመነሻው እስከ መጨረሻው የሚያወራው ስለ ግዳጅ ነው፡፡ እባካችሁ የቱ ጋ ነው የመምረጥ ነፃነቱ? የትም የለም፡፡

የሚያሳዝነው የተፃፉትን ዛቻና ማስፈራሪያ ከምንም ሳትቆጥሩትና ሳታምኑ ከቀራችሁ ሌላ ግዳጅ ይከተላል፡፡ አስተውሉ ክርስትና እና እስልምና ቢሊዮን ተከታዮች ያፈሩት በሰላማዊ መንገድ አይምሰላችሁ በጦርነት፣ በማስፈራራት እና በመደለል እንጅ ይህን ስል ብዙ ሰዎች የሚከላከሉባቸው አንዳንድ ምሳሌዎች ሊጠቅሱ ይችላሉ በጣም ጥቂት ምሳሌዎች ብቻ፡፡ ክርስትና የአውሮፓ እና የከፊል መካከለኛው ምስራቅ ሃይማኖት የሆነው እንዴት ነው? በመንግስታት አዋጅ ጥንታዊ አማልዕክታን በማውድምና በጣኦት የሚያምኑትን በማሳደድ አይደለምን?ክርስትና ወደ አፍሪካ የተዛመተው በቅኝ ግዛት ሰበብ አይደለምን? አፍሪካ ውስጥ ክርስትና በሠላም የተቀበሉት ግብፅና ኢትዮጵያ ቢሆኑ ነው፡፡ በእነዚህ ሀገራትም ብዙ ለህዝብ የተደበቁ ሻጥሮች ተሰርተዋል፡፡ በግብፅ ምድር እኔ ቅዱስ ቄርሎስ የፈጸሙትን ትረሳላችሁን?

Created in Master PDF Editor

በኢትዮጵያ ምድርስ በጎንደር፣ በወሎ በምስራቅና ደቡብ ኢትዮጵያ በሀይማኖት ሰበብ የሆነውን እንዳስታውሳችሁ ትፈልጋላችሁን? በቃኝ ወደ ውጭ ልውጣ፡፡ ክርስትና ወደ ደቡብ እና ሰሜናዊ አሜሪካ እንዴት ነው የተስፋፋው? በተለይ የካቶሊክን የእምነት መስፋፋት ከቅኝ ግዛት ነጥሎ ማየት ሞኝነት ነው፡፡ አንድ ወታደር አንድ ሰባኪ ወታደሩ ይማርካል ካህኑ ያጠምቃል፡፡ ክርስትና እንዲህ ነው እንዴ? ከሆነ እሺ! ችግሩ ሰዎች በግዳጅ ያመኑትን መጀመሪያ ለታይታ ከዚያ እንደ ልምድ በመጨረሻ የራሳቸው ያደርጉታል፡፡

እስልምናስ እንዴት ነው የተስፋፋው በሰላም ነውን? ምን አላበት በአንዳንድ ቦታዎች በንግድና በትምህርት ተስፋፍቷል፡፡ ዋናው ማስፋፊያ ሀይል ግን ጠበንጃ ነበር፡፡ ገና ሲጀመር ጀምሮ የሌለውን ተውትና በሙሀመድ ዘመን ይሆነው እንኳ ማሰብ በቂ ነው፡፡ ሙሀመድ ማለት ለኔ መንፈሳዊ ሰባኪ ሳይሆን ጀግና የጦር አዛዥ ነበር፡፡ ልክ እንደ ናፖሊዮን ቦናፓርቲ ልክ እንደ ታላቁ እስክንድር ከሁሉም የጦር ጀኔራሎች አንደኛው ነብዩ ሙሀመድ ነው፡፡ ተከታዮቹ ካልፌቶችም በእውነት መንገዱን ተከትለዋል እስከቻሉት እርቀት የፈቀደውን በዲፕሎሚሲ ያልፈቀደውን በጦር አንበርክከውታል፡፡ ሰባኪዎች ያሉትን ይበሉ የአለም ታሪክ የሚያስተምረው ግን ይህን ነው፡፡ ዋሸሁ እንዴ?

አይሁዶች ሀይማኖታቸው በዘር የሚተላለፍ ቢሆንም ግዛታቸውን በማስጠበቅና ግዛታቸውን ለማስፋፋት ሙሉ ታሪካቸውን ያሳለፉት በጦርነት ነው፡፡ መፅሀፍ ቅዱስን በደም ያጨቀዩት አይሁዶች ናቸው፡፡ መግደልና መገደል ልክ እንደ ተረት ተረት ይተረካል ምን ማስተማር እንደተፈለገ ግርም ያደርጋል፡፡

ሌለኛ ምን አልባት ሰዎች ሀይል የማይመስላቸው መደለል ነው፡፡ ማታለል የሀይማኖት መስፋፊያ መሳሪያ ከሆነ ቆይቷል፡፡ አሁን አሁን ደግሞ በጦር ሀይል ማሳመኑ ሲቀር በማታለል እየሆነ መጥቷል፡፡ የሚሽነሪ ት/ቤት፣ የሚሽነሪ ህክምና ጣቢና እና ሌሎች የሚሽነሪ ማህበራዊ አገልግሎቶች ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ናቸው፡፡ የሚሽነሪ ማህበራዊ አገልግሎቶች የተከፈቱት ህዝቡን ለማሰልጠን እና ህይወቱን ለማቅለል አያደለም ሀይማኖታቸውን ለማሰራጨት እንጅ በእርግጥ በበረካታ ድሃ ሀገራት ሚሽነሪዎች የዜጎችን ህይወት በመሠረታዊነት ቀይረዋል፡፡ግን ግን ግባቸው የድሆችን ህይወት ለመቀር ሳይሆን ሀይማኖታቸውንለማስቀየርና ባህላቸውን ለማስተው ነበር፡፡

ይህ የተሻለው ሀይል ነው፡፡ በትምህርት፣ በጤና፣ በመንገድና በውሃ አታሎ ጌታን መስበክ ሀይማኖትን ማስቀየር፡፡ በጥልቅ አስቡት ሚሽነሪዎች የት ነው ያሉት ድህነት በተንሰራፋበት አይምሰላችሁ ባህላዊ እምነቶች ባለባቸው ቦታዎች ነው፡፡ ስራቸው ሰው ማዳን አይደለም አሳ ማጥመድ ነው፡፡ ለዚህ ነው ለሰሩት ስራ የማላመሰግናቸው፡፡

Created in Master PDF Editor

እነሱ የሚፈልጉት ድህነት እና ባህላዊ ሀይማኖት የሚገኝበትን ቦታ ነው ከዚያ የሚታደን ሰው አይጠፋምና፡፡

ሀይማኖቶችበምንም ያስፋፉ በምንም ዛሬ ላይ ደርሶናል ዛሬስ ከትናንት ታሪካቸው ተምረዋልን? ምን ያደርጋል ውሸት አወ ተምረዋል፡፡ ግን የመጡበትን መንገድ ይዋሻሉ አሁንም ስውር የሆነ ሀይል ይጠቀማሉ፡፡ በሳይንስና ፊልስፍና ስራዎች ላይ ይዘምታሉ፡፡ ተቋዋሚዎቻቸውን ያድናሉ፡፡ በተለይ በአረቡ አለም የጭካኔ አገዛዙ ገና ይቀረዋል፡፡ ስለ ሙሀመድ አንዳች መጥፎ ነገር መተንፈስ ራስን እንደማጥፋት ይቆጠራል፡፡ ውይይትና ክርክር የሚባል አይታሰብም፡፡ ዝም ብለህ መውገር ነው፡፡ መንግስታት ሳይቀር የዚህ የባርባሪያን ስርዓት ድጋፊዎች ናቸው፡፡ በአረቡ አለም የመናፍቅ ደም ማፍሰስ ምን እንደሚያሽልም ባላውቅም በእየጊዜው ተሰቅለው ወይም ተወግረው ለሚሞቱት የተራማጅ አስተሳሰብ ሊህቃንን ሳስብ እንባየ ይመጣል፡፡ ቁርዓንን የሚያጋልጥ መጽሃፍ የሚጽፉ ሰዎችን ማደን ረብጣ ገንዘብ እንደሚያሽልም ታውቃላችሁ? <እባክህ ዝቅ በል ውረድ ወደ መሬት> የምለው ለዚህ ነው፡፡ እባካችሁ ወደ መሬት ወረዱና ከዋካው ስር ሁነን እናውራ፡፡

ይሁን ትላንትም እንደዋዛ አለፈ፣ ዛሬም ይሄው ኖረን ስለነገስ ሀይማኖቶች ምን ይላሉ፡፡ እንደ ዛሬው ይልቅስ እንደትላንቱ ሀይል ይጠቀሙ ይሆን? አላውቅም፡፡ ግን ወደ ቅዱሳን መፅሀፍት ልመልሳችሁ ኑረን ኑረን እንሞታለን ታዲያ ስንሞት የት ነው የምንሄደው፡፡ በእርግጥ ሲኦል ነው፡፡ አብዛኛው ባለማመኑ ቀሪው ደግሞ በአግባቡ ባለመከተሉ ሲኦል ይገባል፡፡ ማን ፈራጅ አደረገህ አትበሉኝ እንጅ 100% እርግጠኛ ነኝ በአግባቡ የተከተለ አንዳች ሰው የለም፡፡ ጥሩ ምሳሌ ልጥቀስ “ንፁህ የሆነ ይውገራት” ማንም፡፡ ሁሉም ማንነቱ የሞላው በሃጢአት ነው ይህን በሽታ ደግሞ ሀይማኖት አይፈውሰውም፡፡ አያሳዝንም እኔም፣ አማኞችም፣ሞሰለኒም፣ ሂትለርም፣ ማኦ ዘዳንግም፣ ጆሴፍ እስታሊንም፣ ደርዊንም፣ ጳጳሳትም፣ ካሊፎችም፣ በቃ ሁሉም ምስኪን ፃድቁን ጨካኙም ሲኦል ይገባል፡፡ በሰላም ያገኛኝን ያኔ ምን ብያችሁ ነበር እላችኋለሁ ሁላችንም ለሲኦል የታጨን ነን፡፡ሀይማኖት ምን ያህል ኢ-ፍትሃዊ እንደሆነና መሰረቱም አስገዳጅ ሀይል በመጠቀም እንደነበር ታላቁ ጽሃፊ ቶማስ ፔይን The age of reason በተባለው ተወዳጅ መጽሃፉ በተደጋጋሚ ገልጾታል፡፡ ለምሳሌ፦

- Some Christians pretend that Christianity was not established by the sword; but Christianity grounds itself originally upon the Bible, and the Bible was established altogether by the sword, and that in the worst use of it- not to terrify, but to extirpate. The Jews made no converts; they butchered all. The Bible is the sire of the Testament, and both are called the word of God. The Christians read both books; the ministers preach from both books; and this thing called Christianity is

Created in Master PDF Editor

made up of both. It is then false to say that Christianity was not established by the sword.

❖ What is that we have learned from revealed religion? Nothing that is useful to man, and everything that is dishonorable to his maker. What is it the Bible teaches us? rapine, cruelty, and murder.

❖ Of all the systems of religion that ever were invented, there is none more derogatory to the Almighty, more unedifying to man, more repugnant to reason, and more contradictory in itself, than Christianity. Too absurd for belief, too impossible to convince, and too inconsistent for practice. As an engine of power it serves the purpose of despotism; and as a means of wealth, the avarice of priests; but so far as respects the good of man in general, it leads to nothing here or hereafter.

24. ኢ-አማኞች ያዳበሩት ሰላማዊ የአኗኗር ዘይቤ

ሰበኪዎች ስለ ኢ-አማኞች የሚሰብኩትና ኢ-አማኞች የሚኖሩት የአኗኗር ዘይቤ ፍጹም የተለያየ ነው። ሰባኪዎች ሰው ኢ-አማኝ ከሆነ ተስፋ የሌለው፣ መሬት የዞረችበት፣ ስነ ምግባር የሌለው አረመኔ፣ ሀገሩን እና ሰውን የማይወድ፣ በደመነብስ የሚኖር፣ ክፉ መንፈስ ያደረበትና የትንቢተ መፈፀሚያ እንደሆነ ይሰብካሉ። የማያምን ሰው የፈለገውን ክፍ ነገር የማዕረግ ስልጣን ያለው እንደሆነ ይናገራሉ። ሲኦልን የማይፈራ ስለሆነ ክፉ ነገር የማድረግ እድሉ ከሚያምኑት የሰፋ እንደሆነ ይገምታሉ።

እውነቱን ማወቅ ለሚፈልግ ግን የሚያምኑ እና የማያምኑ ማህበረሰቦችን ማህበራዊ እሴቶችንና የአኗኗር ስልቶችን ማጥናት ይችላል። ያለ ብዙ ድካምና ወጭ በብዛት እራሳቸውን እና ሌሎችን የሚያጠፉ ተስፋ ቢሶች እነማን እንደሆኑ፣ ሰው ሁነው ተፈጥረው እንደ እባብ የሚኖሩ እነማን እንደሆኑ፣ በኋላቀርነት አረንቋ ውስጥ የሚኖሩት እነማን እንደሆኑ በመገመት ወደ ድምዳሜው መድረስ ይቻላል።

በእኔ እምነት ኢ-አማኞች ከአማኞች በተሻለ መልኩ ሰብአዊነትን የመላበስ፣ ሀገርና ስራ ወዳድ የመሆን በተለይም “በምክንያት” የመኖር እድሉ አላቸው። ሁሉም ይህን እድል ይጠቀሙበታልን? አይደለም አማኞች በመጽሀፍቱ የተቀሱትን መልካምና መጥፎ ትዕዛዛት እንደማይተገብሯቸው ሁሉ ኢ-አማኞችም የቀረበላቸውን ዕድል ላይጠቀሙበት ይችላሉ።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑ ጭራቅ ኢ-አማኝ ግዥዎችን ማስታወስ ይቻላል። ጨካኝ ኢ-አማኝ አንባገነን መሪዎችን ጨካኝ ያደረጋቸው ኢ-አማኝነታቸው ባይሆንም በጎ የመሆን እድላቸውን ግን እንዳልተጠቀሙት የታወቀ ነው።

Created in Master PDF Editor

በአንፃራዊነት ግን ሰዎች ክፉ የመሆን ዝንባሌያቸው ከሃይማኖታዊ ትዕዛዞች ሊመነጭ እንደሚችል ለማወቅ አይከበድም፡፡ "ተጋድሏቸው" የሚል ትዕዛዝ ያለበት መጽሀፍ እያመነ በጎ ስነ ምግባር የሚኖረው አማኝ መኖሩ ምን ያህል በጎ እንደሆነ ምስክር ነው፡፡ "ውገሯቸው" የሚል ትዕዛዝ ያለበትን መጽሀፍ የሚያምን ሰው መልካም ለመሆን ፈተኝ እንደሚሆንበት አልጠራጠርም፡፡

ኢ-አማኝ የራሱን፣ የሌሎችን እና የተፈጥሮን ሚዛን የጠባቀ የአኗኗር ዘይቤዎችን ለማረቀቅ እድሉ አለው፡፡ በአማኞች መጽሀፍት የተጠቀሱትን በጎ ምግባራት እንዳለ ወይም አሻሽሎ ስራ ላይ ሊያውል ይችላል፡፡ የአኗኗር ዘይቤዎቹ ለተሃድስ በራቸው ክፍት በመሆኑ ይተቻሉ፣ ያሻሽላሉ፡፡ በሃይማኖታዊ የአኗኗር ዘይቤ ግን ሁሉም ነገር ተቆጥሮ የተሰጠ በመሆኑ ለማሻሻል አመች አይደለም፡፡ የሙሴ 10ቱ ትዕዛዛት ዛሬም ያው እንደነበሩ ናቸው፡፡ መጨመር መቀነስ ማሻሻል አይቻልም፡፡ ኤቲስቶች የስነ-ምግባር መርሆቻቸውን ለማደስና የአኗኗር ዘይቤያቸውን ውብና ማራኪ ለማድረግ ዝግጁ ናቸው፡፡ በቅዱሳን መጽሀፍት ያሉትን መልካም ትምህርቶች ለመተግበር የሚከለክላቸው የለም፡፡ መልካም ትምህርት መጽሀፍ ቅዱስም ላይ ቁዕራንም ላይ ወይም በአዋልድ መጽሀፍት ላይ ይፃፍ ከእነዚያ መጽሀፍት ከተፃፉት እንዳትዋስ የሚል ትዕዛዝ ስለሌለ መልካምነትን የመከረኝ መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡ ኤቲስትነት መካድ ወይም መጥላት አለመሆኑ የአሜሪካ ኤቲስቶች ማህበር ያወጡትን መግለጫ ሃሳብ ማስታወስ ይቻላል፡፡

> "In modern sense, the essence of atheism is not the denial of God, but it is the lack of belief in God. This is because; atheists do not have interest to deny God if there is a concrete evidence for His existence. Thus, the mission of atheism is not primarily to deny God, but it is to oppose the ungrounded and absurdities of the definition of God that encounters reasons. So the purpose of atheism is to search for the truth (American atheists, 2015).

ኤቲስቶች ከተለያዩ መጽሀፍትና ከሰብአዊ እሴቶች በመነሳት ድንቅ የሆነ የሰው ልጅ ሊመራባቸው የሚገቡ የስነ ምግባር መርሆዎችን እና የኑሮ ልምምዶችን አስተዋውቀዋል፡፡

በተለይ በኤቲስቶች ተሻሽለው የቀረቡትን አዲሶቹን አማራጭ "አስርቱ ትዕዛዛትን" ሳስብ ነፃነት ከመታዘዝ ምን ያህል እንደሚልቅ ተረድቻለሁ፡፡ ለግንዛቤና ለግርምት ያህል የሙሴን 10ቱ ትዕዛዛት እንዲተኩ ታስቦ የቀረቡትን አማራጭ የስነ መግባር መርሆች እንይ፡፡

Created in Master PDF Editor

የክሪስቶፈር ሂችን አዲስ 10ቱ ትእዛዛት፦ጽሃፊው፣ አምደኛው፣ ጋዜጠኛው እና በሃይማኖትና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ትንታኔውየሚታወቀው ክሪስቶፈር ሂችን አዲስ አሥርት ትእዛዛትንጽፏል። እነሱም፦

1) Do not condemn people on the basis of their ethnicity or their color.
2) Do not ever even think of using people as private property, or as owned, or as slaves.
3) Despise those who use violence or the threat of it in sexual relations.
4) Hide your face and weep if you dare to harm a child.
5) Do not condemn people for their inborn nature — why would God create so many homosexuals only in order to torture and destroy them?
6) Be aware that you, too, are an animal, and dependent on the web of nature. Try and think and act accordingly.
7) Do not imagine that you can escape judgment if you rob people with a false prospectus rather than with a knife.
8) Turn off that fucking cell phone — you can have no idea how unimportant your call is to us.
9) Denounce all jihadists and crusaders for what they are: psychopathic criminals with ugly delusions. And terrible sexual repressions.
10) Be willing to renounce any god or any faith if any holy commandments should contradict any of the above.

የፐ/ር ሪቻርድ ዳውኪንስ ምክር፦ሪቻርድዳውኪንስ<The God Delusion> በተባለው መጽሃፉ የሚከተሉትን አስር የመልካም ሰው መገለጫ ባህርያትን እንድንከተል ይመክራል።

1. Do not do to others what you would not want them to do to you.
2. In all things, strive to cause no harm.
3. Treat your fellow human beings, and the world in general with love, honesty, faithfulness and respect.
4. Do not overlook evil but always be ready to forgive wrongdoing freely admitted and honestly regretted.
5. Live life with a sense of joy and wonder.
6. Always seek to be learning something new.
7. Test all things; always check your ideas against the facts, and be ready to discard even a cherished belief if it does not conform to them.
8. Never seek to censor/cut/ yourself off from dissent; always respect the right of others to disagree with you.

Created in Master PDF Editor

9. Form independent opinions on the basis of your own reason and experience; do not allow yourself to be led blindly by others.
10. Question everything.

የበርትራንድራስል 10ቱ ትዕዛዛት፡- በርትራንድ ራስል ፈላስፋ፣ ሎጅካን፣ የሒሳብና የታሪክ ምሁር፣ ጸሐፊ፣ ማኅበራዊና የፖለቲካ አክቲቪስት እንዲሁም የኖቤል ተሸላሚ ነው። ራስል የሚከተሉትን አስር ትእዛዛት ነድፏል።

1. Do not feel absolutely certain of anything.
2. Do not think it worthwhile to proceed by concealing evidence, for the evidence is sure to come to light.
3. Never try to discourage thinking for you are sure to succeed.
4. When you meet with opposition, even if it should be from your husband or your children, endeavour to overcome it by argument and not by authority, for a victory dependent upon authority is unreal and illusory.
5. Have no respect for the authority of others, for there are always contrary authorities to be found.
6. Do not use power to suppress opinions you think pernicious, for if you do the opinions will suppress you.
7. Do not fear to be eccentric (odd) in opinion, for every opinion now accepted was once eccentric.
8. Find more pleasure in intelligent dissent than in passive agreement.
9. Be truthful, even if the truth is inconvenient, for it is more inconvenient when you try to conceal it.
10. Do not feel envious of the happiness of those who live in a fool's paradise, for only a fool will think that it is happiness.

በበርካታ ሃገራት የሚኖሩ አምላክ የለሾች የተሳተፉበት አዲስ አስርቱ ትእዛዛት (The Atheists' New Ten Commandments) የሚከተሉት ናቸው። ከኦሪቶቹ 10ቱ ትዕዛዛት ጋር ቢነጻጸሩ የቱ ሚዛን ይደፋል?

1. Be open-minded and be willing to alter your beliefs with new evidence.
2. Strive to understand what is most likely to be true, not to believe what you wish to be true.
3. The scientific method is the most reliable way of understanding the natural world.
4. Every person has the right to control of their body.

Created in Master PDF Editor

5. God is not necessary to be a good person or to live a full and meaningful life.
6. Be mindful of the consequences of all your actions and recognize that you must take responsibility for them.
7. Treat others as you would want them to treat you, and can reasonably expect them to want to be treated.
8. We have the responsibility to consider others, including future generations.
9. There is no one right way to live.
10. Leave the world a better place than you found it.

(ምንጭ፦https://en.wikipedia.org/wiki/Alternativesto_the_Ten_Commandments)

ኤቲስትነት ስሙ በክፉ የባከነ ቢሆንም እውነተኛው አኗኗር ግን እውነቱን ይመሰክራል። Margaret Downey የተባለ ኤቲስት አክቲቪስት 50 voices of disbelief: why we are atheists. በተባለ ድንቅ ስብስብ መጽሃፍ My "Bye Bull" Story ሲል በሰጠው ርዕስ ኤቲስቲነትን እንዲህ ያብራራዋል።

"Do you want something to believe in? Look around you. The world is a beautiful and fascinating place. There is no need to imagine a heaven. Your heaven can be made in the here and the now with good life choices. Do you want life after death? Create a legacy worth remembering. When people speak of you, you will live again. Need someone or something to worship? Look in the mirror and decide to live every moment as if it were your last. With pride in yourself and acknowledgment of the fact that you only have one life, your home is your heaven and you are a god. As your own god, you are in complete control of your life with the ability to answer your own prayers through conscientious actions and self-determination. There is no need for an imaginary friend. We may never have a definitive answer about how the world came into existence, but making up a story about the existence of a god only inhibits further scientific inquiry. In my community of reason, questions are encouraged. There is no need to make up a story just to have an answer to a puzzling question. Unanswered questions bring about great scientific research, study, and much more interesting believable results. (50 voices of disbelief, page 14-15)

ሌላኛው Jack Dann እንደ ኤቲስት እንዲህ አስባለሁ ይላል።

"I hope to explore all the demons, ghosts, angels, and hobgoblins of my psyche; I hope to explore the limits of thought and possibility; I hope to embrace humankind's daily discoveries in art, science, and technology; and I will only blame myself and ourselves for the errors, petty cruelties, holocausts, wars, and killing fields of the past, present,

Created in Master PDF Editor

and future. I will reject the safety of teleology. I will not pray for redemption. I will not embrace superstition and irrationality to overcome my fears of death and uncertainty. And I will continue to peer into the deep well of mortality and try not to run because I am frightened. Amen . . . (50 voices of disbelief, page 199)

Peter Tatchell በበኩሉ “I renounced religion; embracing reason, science, and an ethics based on love and compassion. I don't need God to tell me what is right and wrong. We humans are quite capable of figuring it out for ourselves, as we have done in great secular emancipatory documents like the UN Universal Declaration of Human Rights. My atheism does not, however, lead me to hate religion or people of faith. Hate isn't part of my mindset. I have a rational critique of god-worshipping, but I also defend religious believers who suffer persecution and discrimination. All ideas, including religious ones, should be open to scrutiny and criticism. People ought to be free to criticize Christianity, Judaism, Islam, Hinduism, and other faiths – especially the violent, oppressive strands of these religions. The motive of my human rights campaigning is love. I love people. I love justice. I love peace. I love life. I don't like seeing other people suffer. I think to myself” (50 voices of disbelief, page 306-309)

ጦማሪው አገኘሁ አሰግድ ኤቲስትነትን ከሮም ጋር ያነጻጽረዋል። “ኤቲስትነት እንደ ሮም ነው። በአንድ ቀን አይገነባም፣ ገንብተው ሲገቡበት ግን ዓለም ነው። እርግጥ ገብቶ የሚቃኘ አይጠፋም። ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት መልካም መሆን እንደሚችል ይገባኛል። we are good without God እንዳሉት አበው።”

atheistscholar.org የተባለ ድህረ ገጽ ደግሞ ኤቲስቶች በብዛት የሚኖሩባቸውን ሀገራት ሁለንተና አማኞች ከሚበዙባቸው ሀገራት ጋር ያነጻጽረዋል። “The nations with the highest degrees of atheism include most of the nations of Europe, Japan, Canada, Australia, New Zealand, Taiwan, and Israel. However, atheism is virtually non-existent in most of Africa, South America, the Middle East, and Asia. Most nations characterized by high degrees of individual and societal security have the highest rates of atheism, and conversely, nations characterized by low degrees of individual and societal security have the lowest rates of atheism and the highest degrees of belief. High levels of atheism are strongly correlated with high levels of societal health, such as low poverty rates and strong gender equality (and DEMOCRACY). In many societies' atheism is growing. However, throughout much of the rest of the world particularly among the poorest nations with the highest birth rates atheism is nearly absent.” (atheistscholar.org)

ኤቲስቶችን የሚያስጨንቃቸው የፈጣሪ መኖር አለመኖር፣ የጸሎት መሰማት አለመሰማት አይደለም ይልቅስ ኑሮን ለማሸነፍ የሚደረግ ፍትጊያ እንጅ። ፈላስፋና

Created in Master PDF Editor

ደራሲ በዕውቀቱ ስዩም ምን ነበር ያለው፦ “አለም አቃፊ ነው:: መልካችን ሰልፊ ነው:: ችግራችን ሰፊ ነው፤ ጭቆና ተላላፊ ነው:: መንግስት ተጋፊ ነው:: ዛሬ ብርቱ ቢመስልም ነገ ረጋፊ ነው:: እኔን ያስጨነቀኝ *የኑሮ ጥፊ* ነው”

ፍቅርን ሰባኪዎች ይሰብኩታል ኢ-አማኞች ይኖሩታል:: ሰላምን ሰባኪዎች ይሰብኩታል ኢ-አማኞች ይኖሩታል:: በህይወት መለወጥን ሰባኪዎች ይሰብኩታል ኢ-አማኞች ይለማመዱታል:: ለእግዚአብሔር የሚሆን ክፍት ቦታ የለም::

Created in Master PDF Editor

ክፍል ሁለት

አማኞች በእግዚአብሔር ለማመን ለሚያቀርቧቸው ምክንያቶች መልስ

<<በእግዚአብሔር መኖር ላይ የተመሠረተ ሃይማኖት ደረጃዎች፡-

1ኛ ደረጃ. በአግዚአብሔር መኖር ተፈጥሮን መሠረት አድርጎ፡-

ፍጥረት ያለ ልዕለ ተፈጥሮ አካል ሊገኝ የሚችልበት ዕድል የለም፡፡ ፍጥረታትን ሁሉ ፈጥሮ የሚያስተዳድራቸው አካል መኖሩ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ሆኖም እያንዳንዷን የሰዎች እንቅስቃሴ የሚቆጣጠር አይደለም፤ ከፈጠረ በኋላ ሕግና ሥርዓትን ሠርቶ በዚያ እንዲተዳደር ትቶታል፡፡ ማስረጃው ተፈጥሮ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ያሉ የሃይማኖት መጻሕፍትን በአብዛኛው አይቀበሉም፤ ከተወሰኑት የምሥራቅ ሃይማኖቶች በስተቀር፡፡ አብዛኞቹ የግሪክ ፈላስፎች በዚህ ዕምነት አቋም ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡

2ኛ ደረጃ. አግዚአብሔር በተለያየ ሁኔታ መገለጡን የሚያምንና የሚቀበል፡-

አግዚአብሔር ፍጥረታትን ከመፍጠሩም በተጨማሪ ከፍጥረቱ ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤ በተለይም ለሰዎች ማንነቱን ገልጽዋል (ለምሳሌ በራዕይ፣ ሰዎችን በቀጥታ በተላያየ ነገር ላይ ተገልጾ በማነጋገርና ምልክቶችንና ታምራቶችን በማሳየት፣ በህልም…) ሆኖም እንደ እኛ ሰው በመሆን አልተገለፀም፡፡ የእስልምና ሃይማኖት፤ እንዲሁም ከእነዚህና ከምሥራቅ ሃይማኖቶች ጋር የተያያዘ አስተምህሮ ያላቸው አብያተ እምነቶች በዚህ ደረጃ ላይ ናቸው፡፡

3ኛ ደረጃ. እግዚአብሔር በሥጋ (ሰው በመሆን) አንደተገለጠ የሚቀበል፡-

እግዚአብሔር ፍጥረቱን ከመፍጠሩም በተጨማሪም ከፍጥረቱ ጋር ግንኙነት ያደርጋል፡፡ በዚህ ግንኙነትም በሰውነት እስከመገለጥ ደርሷል፡፡ በዚህ ሥር የሚገኙ በክርስትና ወስጥ የሚገኙ አባዛኞቹ ሃይማኖቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክና ፕሮቴስታንት፡፡ አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት ዶግማዎቻቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት አዕማዳተ ምሥጢራት የሚባሉት፡- ምሥጢረ ሥላሴ፣ ምሥጢረ ሥጋዌ፣ ምሥጢረ ጥምቀት፣ ምሥጢረ ቁርባንና ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ናቸው፡፡ ከእነዚህ አዕማደተ ምሥጢራት የወጣ አስተምህሮ የለም፡- ከወጣም የክርስትና መንፈስ አይኖረውም፡፡>> (ምንጭ፡-ማህበራዊ ሚድያ)

Created in Master PDF Editor

ማመንም አለማመንም ቀላል ውሳኔ አይደለም። ማንም ሰው የተወለደበትን ሀይማኖት የመቀበል ግዴታ የለበትም፣ መርምሮ ማመን አለበት።የሚቻለውን ያህል እውነትን መፈለግ አለበት። በተለይ በ21ኛው ክ/ዘመን ሳይመረምሩ ሀይማኖትን በዘር መውረስ ኋላ ቀርነት ነው። መርምረን የመሰለንንና የገባነን የመከተል መብታችን ግን የተጠበቀ ነው። እኔ ኤቲስት ስለሆንኩ ሰው ኤቲስት እንዲሆን አልጠብቅም ወይም ከኤቲስት ውጭ ያለው ሁሉ ስህተት ነው ብየ አላምንም ይልቅስ የተለያዩ ሀይማኖታዊ መጽሀፍትን በማንበብ ራሴን እፈትናለሁ። በየትኛውም እምነት ያለ ማንም ሰው እራሱን መፈተሽ ከፈለገ የሚከተሉትን መጽሀፍት እንዲያነብ እመክራለሁ። ሌሎች ተጨማሪ መጽሃፍትን፣ ዶክመንተሪዎችን፣ ስብከቶችን እና ክርክሮችን መከታተል ደግሞ የተቀደሰ ሀሳብ ነው።

1. Holy Bible (መጽሀፍ ቅዱስ)--(Religious)
2. Holy Quran (ቅዱስ ቁርዓን)--(Religious)
3. Encyclopedia of time: science, philosophy, theology, and culture edited By James Birx -- (Diverse issues)
4. The Age of Reason By Thomas Paine--(Critics of religion)
5. Mere Christanity By C.S. Lewis (Religious)
6. The Languge of God By Francis Collines (Religious)
7. Proving History and On the historicity of Jesus By Richard Carrier (Critics of Historical Jesus)
8. Reasonable Faith By Willam Lance Craig -- (Compatability of Religion & Science)
9. The Bible, The Qur'an and Science By Maurice Bucaille-- (Research on religion)
10. 50 Reasons People Give for Believing in a God by Guy P. Harrison- (Critics of religion)
11. A Chain of Miracles By Harun Yahya or Adnan Oktar- (Anti-Evolution)
12. A Short History of Nearly Everything By Bill Bryson- (History)
13. AllatRa by Anastasia Novykh-- (Spritiality)
14. The Kalam Cosmological Argument By William Lane Craig--(religion)
15. Answer to Non-Muslims’ Common Questions About Islam By Dr. Zakir Naik- (Islam)
16. The hidden humanity By Phillip Lindsay (Documentary Film)-- (Astrology)
17. Barbelo -The Story of Jesus Christ By Riaan Booysen- (Critics of religion)
18. Born Atheist By Tim Covell- (Critics of religion)
19. Brief Answers to the Big Questions By Stephen Hawking (Evolutionary)
20. Debunking the Myth of Science in the Quran By Ali Sina on Zakir Naik - (Critics of religion)

Created in Master PDF Editor

21. Faith versus fact: why science and religion are incompatible By Jerry A. Coyne. - (Critics of religion and evolutionary)
22. God is Dead, Now Zen is the Only Living Truth, by Osho- (Critics of religion)
23. How “God” Works: A Logical Inquiry on Faith By Marshall Brain- (Critics of religion)
24. The Creation of God, By Dr. Jacob Hartmann (Critics of religion, published on 1893 but still new)
25. Love Letters from Grampa – about Life, Liberty, and the Zen of Zero(Critics of religion)
26. Muslim Responses to Science’s Big Questions Report of the İhsanoğlu Task Force on Islam & Science, Edited by: Usama Hasan and Athar Osama (Religious Science)
27. My Ordeal with the Quran and Allah in the Quran By Abbas Abdul Noor and Translated by Hassan Radwan- (Critics of Quran)
28. (Some) Lectures from Robert G. Ingersoll - (Critics of religion)
29. The Choice By Ahmed Deedat-- (Religious)
30. The End of Christianity edited By John W. Loftus.- (Critics of religion)
31. The Evolution Cruncher by Vance Ferrell- (Very Anti-Evolution)
32. The Evolution of God by Robert Wright – (Evolutionary)
33. The Gospel of Flying Spaghetti Monster By Bobby Henderson (Religion)
34. The God Delusion & The Magic of Reality By Richard Dawkins-- (Evolutionary)
35. The Skeptic’s Annotated Bible By Steve Wells - (Critics of Bible)
36. We Believe in Jesus By 3rd Millennium Ministries (በኢየሱስእናምናለንተከታታይመጽሃፍት፣ተርጓሚእሸቴበለጠ)- (Religious)
37. Why I Am Not a Muslim By Ibn Warraq- (Critics of Islam)
38. Why There Is No God By Armin Navabi- (Critics of religion)
39. Why people believe weird things: pseudoscience, superstition, and other confusions of our time By Michael Shermer - (Critics of religion)
40. ሀይማኖት አበው ቀደምት በኪዳነ ወልድ ክፍሌ- (Religious)
41. ዓምደ ሀይምማኖት በብርሀኑ ጎበና-- (Religious)
42. ትምህርተመለኮት በዓሥራገብረማርያም--(Religious)
43. አጠቃላይ የነገረ መለኮት ትምህርት 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ መጽሀፍት-- ቄስ ኮሊን ማንሰል፣ (በፍትህ አምላክ እንየው የቀረቡ ስነ-መለኮታዊ መጽሃፍት)
44. እስልምናን ለመገንዘብ አጭር ሥዕላዊ ማስረጃ መፅሀፍ በI.A. Ibrahim (ኢብራሂም)፣ አማረኛ ትርጉም ባህረዱንሙሳኢሌቦሮ-- (Religious)

Created in Master PDF Editor

45. ከምድራዊነታችን ባሻገር፣ ሦስተኛ መጽሐፍ፣ ሳይንስ፥ እምነት፥ ሥልጣኔ - ማስታወሻና ማስተዋያ በመ. ኃ. መስቀል --(Anti-Evolution or long age creastionalist)
46. ምንትኑ ውእቱ ሰብእ በመ/ር ዶ/ር ዘበነ ለማ-- (Anti-Evolution)
47. የጨለማው ገዥ ተግባርና ንግግር በተክለ ኪዳን-- (Anti-Evolution)
48. የሳይንስ ኑዛዜ በሰለሞን ዮሃንስ (Anti-Evolution)
49. በትረ ሃይማኖት በቀሲስ መዝገቡ ካሴ (Theology)
50. ኢትዮጵያ የአለሙ መፍረጃ በተጨማሪም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በንቡረ እድ ኤርሚያስ ከበደ--(Anti-Evolution)
51. መድሎተ ጽድቅ በዲ/ን ያረጋል አበጋዝ-- (Theology)
52. እስልምና እና ክርስትና ንጽጽራዊ አቀራረብ፣ በዶ/ር ሙሃመድ ዒሊ ኣልኩሊ- (Islam)- (ዘላለም መንግሥቱ በሚያዘጋጀው ዕዝራ ስነ ጽሑፍ ላይ ሰፊ ምላሽ ተሰቶበታል)
53. የህይወት ትርጉም በዋለልኝ እምሩ-- (Philosophy)
54. የዕውቀት ማህደር ዶ/ር ኬኬ እንደጻፈው፣ (ከቅጽ 1-4)- (Diverse issues)

ከላይ የተዘረዘሩትን የተመረጡ መጽሃፍት የተለያየ አመክንዮ ትከትለው ወደ እውነት ለመገስገስ የሚያግዙ ናቸው:: እውነት አንድ መጽሃፍ በቃል በመሸምደድ እንደማይገኝ እርግጠኛ ነኝ:: ምን አልባት ግን እውነት በተቃርኖዎች ውስጥ ትገኝ ይሆናል:: ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋል የሚባለው የተለያዩ ተቃርኖዎችን የያዙ መጽሃትን ለሚያነቡ ነው:: ሁሌ ጥዋት ጥዋት እየተነሱ ውዳሴ ማርያም የሚያነቡ አንባቢዎች ሊባሉ አይችሉም ብየ እገምታለሁ::

ወደ ቀደመ ነገሬ ልመለስ:: የዚህ መጽሃፍ አላማ እግዚአብሔር አለመኖሩን መጠቆም ብቻ ሳይሆን ለመኖሩ እንደማስረጃ የሚቀርቡ ምክንያቶችንም መሞገት ነው:: እናም ከተለያዩ መጽሃፍት፣ ስብከቶች እና ክርክሮች ላገኘኋቸው ማብራሪያዎች እንደሚከተለው ምላሽ እሰጣለሁ::

1. የእግዚአብሔር መኖር በተለያየ መልኩ ተግልጧል

"የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን መኖር ለመረዳት ብዙ ተመራምሯል:: በምርምሩም የእግዚአብሔርን መኖር ወደማወቅ የሚያደርሱ መንገዶችን አግኝቷል:: ለማንኛውም ነገር ምክንያት አለው:: ለሥዕል ሠዓሊ፣ ለመጽሐፍ ጸሐፊ፣ ለወንበር ጠራቢ አለው:: ለሚንቀሳቀስ ነገር ሁሉ አንቀሳቃሽ አለው:: በዚህ መሠረት <ፍጥረት ያለፈጣሪ የተገኘ አይደለም> ወደሚለው እምነት ተደርሷል:: ፍጥረት ሁሉ ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ፣ አእምሮ ከሌለው ጀምሮ

Created in Master PDF Editor

ከፍተኛ አእምሮ እስካለው ድረስ የእግዚአብሔርን መኖር ወደማወቅ ይመራል።" (የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ን እምነ ትናሥርዓተ አምልኮ፣ ገጽ፣1)

እንደማስረጃም ከመጽሀፍ ቅዱስ የሚከተሉትን ይጠቅሳሉ።

- ዘፍ. 1:1 "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።"
- ኢሳ. 42:5 "ሰማያትን የፈጠረ የዘረጋቸውም፥ ምድርንና በውስጥዋ ያለውን ያጸና፥ በእርስዋ ላይ ለሚኖሩ ሕዝብ እስትንፋስን፥ ለሚሄዱባትም መንፈስን የሚሰጥ አምላክ እግዚአብሔር"
- ኢዮብ 12:7-9 "እንስሶችን ጠይቅ ያስተምሩህማል፣ የ ሰማይንም ወፎች ጠይቅ ይነ ግሩህማል፣ ወይም ለምድር ተናገር እርስዋም ታስተምርሃለች፣ የባሕርም ዓሣዎች ይነግሩሃል፣ የእግዚአብሔር እጅ ይህን እንዳደረገ፣ ከእነ ዚህ ሁሉ ይህን የ ማያውቅ ማን ነው?"
- ጥበብ 13:1-10 "እግዚአብሔርን የማወቅ ጉድለት በልባቸው ያለባቸው ሰዎች ሁሉ በእውነት ከንቱ ናቸውና በእነዚህ በሚታዩ ፍጥረቶቹ በዚህ ዓለም የሚኖር እርሱን ያውቁ ዘንድ ተሳናቸው፣ ሥራውን እያዩ ፈጣሪያቸውን አላወቁም፣ … ፀሐይና ጨረቃን አይተው የፈጠራቸውን ይወቁ…"
- ሮሜ 1:21 "የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና"

"I have a message for you. I am <Sook Kah-lon Ah-hos>, the timeless Lenape spirit. I lived in the flesh on the American continent almost fifteen thousand years ago, many millennia before civilization existed. I am the person who created Shiva. I also created Odin for the north, Quetzalcoatl for the Aztecs, Zeus for the Greeks, Yahweh for the Jews, Ishtar for the Babylonians, Venus for the Romans, and thousands of gods around the world, including Vishnu, Brahma, and the elephant god Ganesha for the Indian Subcontinent." (ምንጭ፦ ከኦሾ መጽሃፍት ከአንዱ)

በእርግጥ ፈጣሪ በተለያየ መንገድ ሊገለጥ ይችላል። መገለጥ ሁሉ ግን ከፈጣሪ ነው ማለት ግን አይቻልም። ሁሉም ሀይማኖቶች ይብዛም ይነስም የተመሰረቱት በመገለጥ ነው። ቶማስ ፔይን የተባለው አብዮተኛ እና ፀሀፊ The Age of reason በሚለው መፅሀፍ የራሱን አቋምና የቤተ እምነቶችን ማንነት በተነተነበት ፅሁፍ እንዲህ ብሎ ነበር። *"I do not believe in the creed professed by the Jewish church, by the Roman church, by the Greek church, by the Turkish church, by the Protestant church, nor by any church that I know of. My own mind is my own church. All national institutions of*

Created in Master PDF Editor

churches, whether Jewish, Christian or Turkish, appear to me no other than human inventions, set up to terrify and enslave mankind, and monopolize power and profit.” በሀይማኖቶች መካከል ያለውን ልዩነት ታሳቢ አድርጎ ሁሉም ከጌታ ልዩ ተልዕኮ የተሰጠን ትክክለኛ መንገድ እኛ ብቻ ነን ለሚሉትም ቶማስ ፔይን እንዲህ ብሎ ነበር፡፡ *“Each of those churches show certain books, which they call revelation, or the word of God. The Jews say, that their word of God was given by God to Moses, face to face; the Christians say, that their word of God came by divine inspiration: and the Turks say, that their word of God (the Koran) was brought by an angel from Heaven. Each of those churches accuse the other of unbelief; and for my own part, I disbelieve them all.”*

መገለጥ (አስተርዮ-Revelation) ምንድን ነው? መገለጥ ከፈጣሪ ጋር የሚደረግ ቀጥተኛ ወይም ተዘዋዋሪ ንግግር ነው፡፡ በስነ-መለኮት ሁለት አይነት መገለጦች እንዳሉ ይነገራል፡፡ አንደኛው በተወሰነ ቦታ ለተወሰነ ጊዜ ለተመረጠ ሰው ብቻ የሚደረግ መገለጥ ነው፡፡ የአለም ሀይማኖቶች የተመሰረቱት በዚህ የመገለጥ አይነት ነው፡፡ ከጥንት እስከዛሬ ሰዎች ከፈጣሪ ጋር የመነጋገር እድል አግኝተዋል፡፡ (በህልማቸውም ቢሆን)፡፡ ያለ ልዩ መገለጥ የተቋቋመ ሀይማኖት ያለ አይመስለኝም፡፡ በዚህ ልዩ መገለጥ የሚገርመው ነገር አምላክ ለ100,000 ሰዎች በተለያየ ጊዜ ሁኔታ እና ቦታ ሲገለጥ የተለያየ ማንነት መላበሱ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ የሚገለጠው የሚገለጥባቸው ሰዎችን ስሜት ተከትሎ መሆኑ ነው፡፡ በነገራችን ላይ መገለጥ (Religious Experience) እውን ይሁን? <21st century sociology: A reference handbook>ገጽ 300 ይመልሳል፦

> No matter how skeptical one may be about their meaning, there is no doubt that many people have religious or mystical experiences. Indeed, most of the world’s major religions trace their origins to such events. The experience Moses had when Yahweh gave him the Ten Commandments, Mohammad’s experience as the Angel Gabriel revealed Allah’s words in the Koran, and Siddhartha Gautama’s great enlightenment experience under the Bodhi tree are just a few examples of religious experiences that have literally changed the course of human history. But how, then, is the social scientist to understand such events? Freud, Durkheim, and Marx along with many of the other founders of the sociology of religion would dismiss such experiences as hallucinations. … Like other experiences, they come in all ranges of intensities and in countless different forms.

እኔ ማንም አምላክ ነኝ ባይ ያልተገለጠልኝ ቢሆንም ተገለጠልኝ የሚሉ ቴሌቫንጋሊስቶችን ለማየት ታድያለሁ፡፡ አስቡት እግዚአብሔር የሚያናግረውን ሰው

Created in Master PDF Editor

በአካል ወይም በሚዲያ ማየት መታደል አይደለምን? ቅዱሳን በተለይም ድንግል ማርያም የምታናግራቸው ሰዎች የሚናገሩትን መስማት እና የሚፅፉትን ማንበብ እድለኛ አያስብልምን? ያስብል ነበር ችግሩ የሚያነቡት ከልባቸው መዝገብ የተፃፈውን ነው።

በዚህ ብዙ ምስክርነቶች በመያዥጎድጉደው ልዩ መገለጥ ዙሪያ ቅሬታ ማንሳት ቡጢ የሚያስቀምስ ቢሆንም የገባኝን መተንተን ግን የራሴ ልዩ መገለጥ ስለሆነ ጥያቄ ማንሳቴን አልተውም። መሰረታዊ የሆነው ጥያቄ የዛሬዎቹ ቴሌቫንጋሊስቶችም፣ የድሮዎቹ ቅዱሳን ነብያት፣ ሐዋርያትና አባቶች ከፈጣሪ ዘንድ የሚደርሳቸው መገለጥ የተለያየ አንዳንዴም ፈፅሞ ተቃራኒ መሆኑ ነው። ለምሳሌ፡- አምላክ ለክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ፣ አምላክና የዘለዓለም ንጉስ መሆኑን ሲገልጥላቸው (ልዩነቶች እንዳሉ ሆኖ) ለሙስሊሞች ደግሞ ነብይ ብቻ እንደሆነ ተገልጦላቸዋል። ይህ በእየቦታው የሚለያየው ልዩ መገለጥ ጥያቄ ቢነሣበት አይገርምም። ለ100,000 ሰዎች 100,000 ህልውና ተላብሶ የሚገለጥን አምላክ የማምለክ ግዴታ ያለብን አይመስለኝም። There is no reason to believe any of the dogmas of traditional theology and, further, that there is no reason to wish that they were true ነበር ያለው Bertrand Russell.

የጣኦታት ካህናት፣ ሙሴ፣ የብሉይ ኪዳን ነብያት፣ የአዲስ ኪዳን ሀዋርያትና ነብያት፣ሙሃመድና ተከታዮቹ፣ያሬድ ኢትዮጵያዊ፣ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፣ ከቫቲካኑ ፖፕ እስከ አጥቢያ ቤተ-ክርስቲያን የሚገኙ አገልጋዮች፣ በተለይ በተለይ ደግሞ የፕሮቴስታንት ቴሌቫንጋሊስቶች እና የኦርቶዶክስ ታአምራት ድርስናት ሌሎች አዋልድ መፅሐፍት ጸሐፊዎች ተገልጦልናል የሚሉትን እውነት ያለ መቀበል መብት አለን። ለምን እኛን አይመለከተንም የሚመለከተን ቢሆን ኑሮ ለሁሉ የሚበቃ ጌታ በሶስተኛ ወገን ሳይሆን በቀጥታ ይገለጥልን ነበር። የተገለጠለት ሰው የተገለጠበትን ነገር ይመርምርና ይመን ሽክሙን በሌሎች ጫንቃ ላይ ማራገፍ ግን ተልዕኮው አይደለም። እግዚአብሔር ለልጆቹ እንዲህ ብኋል በላቸው አይልም። በባህሪው ለሁሉ በቂ ስለሆነ ማንንም አይልክም።

ስለፈርዖን መናገር ከፈለገ ሙሴን መላክ አይጠበቅበትም። ስለ ኢትዮጵያዊነት ለመስበክ ተክለ ኪዳንን፣ ንቡረዕድ ኤርሚያስ ከበደን፣ እህተ ማርያምን እና ቴሌቫንጋሊስቶችን መላክ አይጠበቅበትም። ሁሉን የሚገዛ አምላክ ለሁሉም የመናገር ብቃት አለው። በአጭሩ ልዩ መገለጦች ሁሉ “Mythology” ናቸው። ይህ መራራ እውነት ነው።

ሁለተኛው መገለጥ ለሁሉ የሚበቃ ሁሉንም የሚመለከት መገለጥ ነው። በአለም ላይ ይህን አይነት መገለጥ ገና አልተከሰተም። ብዙዎች ስነ-ፍጥረት በራሱ የፈጣሪን

Created in Master PDF Editor

መኖር ይገልጣል ቢሉም ሰነፍ ድምዳሜ መሆኑ ግን ይታወቃል::የሚመሰል ነገር ሁሉ እውነት ነው ለማለት ይከብዳል:: የፍጥረት መኖር የፈጣሪን መኖር ያስረዳል ከማለታችን በፊት የሁለንታን ታሪክ በመጠኑም ማጥናት ይጠበቅብናል:: ጥልቅ የሳይንስ ምርምሮችን ያደረጉ የኮስሞሎጅና የአስትሮኖሚ ሳይንቲስቶች እንደሚነግሩት የሁለንታ አፈጣጠር በሃይማኖቶች ከሚሰበከው የተለየ ነው:: የፍጥረታት አፈጣጠርም እንዲሁ::

በምንም መንገድ ይሁን በመገለጥ ማመን ሀይማኖትን እውነት አያደርገውም መገለጥ ምልዕ አይደለምና:: ፀሐይ እንኳን የምትገለጠው ለከፊሉ የአለም ህዝብ ነው፣ በአንዴ ለሁሉም አትገለጥም:: በታሪክ ግን የፀሐይን ያህል እንኳን ለህዝብ የተገለጠ አንድም አመልዕክት የለም:: የፀሀይን በሚያመልኩ ሰዎች የሚያፌዙ ምንኛ ሞኞች ናቸው:: ከሁሉም አማልዕክት የተሻለ የተገለጠችው አምላክ ጸሀይ ናት::

ሰባኪዎች እግዚአብሔር በመጽሃፍ ቅዱስ እራሱን ገልጧል ይላሉ:: ይህ ቅዱስ መጽሃፍ በበራላቸው ዘንድ ግን የፈጣሪን መገለጥ እንደማያሳይ ይታመናል:: ቶማስ ፔይን መፀሐፍ ቅዱስን በተለይም ብሉይ ኪዳንን እንዲህ ገልፆታል:: “Whenever we read the obscene stories, the voluptuous debaucheries, the cruel and torturous executions, the unrelenting vindictiveness, with which more than half the Bible is filled, it would be more consistent that we called it the word of a demon, than the word of God. It is a history of wickedness, that has served to corrupt and brutalize mankind; and, for my part, I sincerely detest it, as I detest everything that is cruel.” የአዲስ ኪዳን መሰረት የሆኑትን 4ቱን የወንጌል መፅሀፍትም እንዲህ ይገልጻቸዋል:: “The four books, Matthew, Mark, Luke, and John, are altogether anecdotal (unreliable). In several instances they relate the same event differently. . . .I believe, impossible to find in any story upon record so many and such glaring absurdities, contradictions and falsehoods as are in those books.”ስለ ሙሴ መፅሐፍት “Genesis is an anonymous book of stories, fables, and traditionary or invented absurdities, or of downright lies. The story of Eve and the serpent, and of Noah and his ark, drops to a level with the Arabian tales, without the merit of being entertaining; and the account of men living to eight and nine hundred years becomes as fabulous immortality of the giants of the Mythology.” ብሎ ነበር::

ቶማስ ፔይን Mystery, Miracle, and Prophecy ስለሚባሉ የመገለጥ መንገዶች ሲጽፍ ምን ነበር ያለው፦

- proceed to speak of the three principal means that have been employed in all ages, and perhaps in all countries, to impose upon mankind. Those three means are Mystery, Miracle, and Prophecy. The two first are incompatible with true religion,

Created in Master PDF Editor

and the third ought always to be suspected. With respect to mystery, everything we behold is, in one sense, a mystery to us. Our own existence is a mystery.

- In the same sense that everything may be said to be a mystery, so also may it be said that everything is a miracle, and that no one thing is a greater miracle than another. The elephant, though larger, is not a greater miracle than a mite, nor a mountain a greater miracle than an atom. To an almighty power, it is no more difficult to make the one than the other, and no more difficult to make millions of worlds than to make one. Everything, therefore, is a miracle, in one sense, whilst in the other sense, there is no such thing as a miracle.
- As mystery and miracle took charge of the past and the present, prophecy took charge of the future and rounded the tenses of faith. The supposed prophet was the supposed historian of times to come.
- Upon the whole, mystery, miracle, and prophecy are appendages that belong to fabulous and not to true religion. They are the means by which so many Lo, heres! and Lo, theres! have been spread about the world, and religion been made into a trade. The success of one imposter gave encouragement to another, and the quieting salvo of doing some good by keeping up a pious fraud protected them from remorse.

ቶማስ ፔይን እያለ ያለው ታምራትና ማፅሃፍት የእግዚአብሔርን መኖር አይገልጡም ነው። በእኔ እምነት ግን አለመኖሩን ይገልጣሉ ይህን ታምራትን ያየ ይናገር መጽሃፍትን ያነበበ ይመስክር።

ወንጌል በድረ-ገፅ አገልግሎት እውን እግዚአብሔር አለን ለሚለው ጥያቄ መልስ በሰጠበት ጹህፉ<ፈጣሪ በፍጥረቱ ስለመገለጡ>እንዲህ ይላል፦

> “ሰው ሆይ እነዚህን ጉዳዮች አስባቸው ስለ ጠፈርና በውስጡ ስላለው ነገር፦ ስለ ከዋክብት፣ ስለፈለኮች፣ ስለጋላክሲዎች፣ ስለተክሎች፣ ስለ እንስሳት፣ ስለ ሰዎችና ስለሰዎች አእምሮ።ሁሉን ለመፍጠር የምትችል እንደሆንክ ራስህን ለአንድ አፍታ አስብ። በእውነት እንዲህ አይነት ውበት፣ ግርማ፣ ብዛት፣ የምህንድስና እወቀትና ምጥቀት የተጎናፀፈ ፍጥረት የምትፈጥር ይመስልሃልን? እያንዳንዳቸው በአማካይ 100 ቢሊዮን ከዋክብት ያሏቸው ከ1 ትሪሊየን በላይ ጋላግሲዎችን ዲዛይን ማድረግ ትችል ይሆን? ምንም ማገናዘቢያ ሳይኖርህ፣ ከምንም ተነስተህ፣ ብርሃንን ከፈጠርክ በኋላ 186,000 ማይልስ በሰከንድ እንዲሮጥ ልታዘው ታስብ ይሆን? ድምፅንስ ፈጥረህ በሰዓት 660 ማይልስ እንዲጓዝ ትወስነው ይሆን? ለሳይንስ የታወቁትን አቶሞችንና ንዑስ አቶሞችን ታበጃቸው ነበር? እነዚህን አቶሞች ወደ ውስብስብ ሞሎኪውሎች በመቀየጥ ለቁጥር አታካች የሆኑ ተግባራት እንዲከውኑ ታዛቸው ይሆን? እርስ በእርሳቸው ተደጋጋፊ ከመሆናቸው

በላይ በዕፅዋት አለም ውስጥም ጭምር ይህንን ባሕሪ በተግባር የሚገልጡ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ እንስሳትን ምንም አይነት ኮድ ሳትኮርጅ ትፈጥር ይሆን? ለነዚህስ የሚሆን አስፈላጊውን የምግብ አይነት ሁሉ ታበጅላቸው ይሆን? አንተና የአንተ አእምሮ በነሲብ በሆነ እድል ምክንያት ካለመኖር ወደመኖር መጧል ብለህ ራስህን እንዳትሰድብ እንደመከርኩህ ሁሉ እነዚህ አስገራሚና እጅግ ውስብስብ የሆኑ ፍጥረታት ሁሉ በድንገትና በእድል ተገኝተዋል ብለህ ፈጣሪን እንዳትሰድብ ልምከርህ፡፡ ሞኞች ይህን ብለው ከሆነ አንተ ይህን የሞኝነት መንገድ ልትከተል አይገባህም፡፡ በማስተዋል ከመረመርክ የእግዚአብሔርን መኖር ለማረጋገጥ መጽሐፍ ቅዱስን መጥቀስ ግድ አይልም፡፡ የተገለጠው ፍጥረት እርሱን በግልጥ ይሰብካሉና፡፡”(ወንጌል በድረ-ገፅ አገልግሎት፣ እውን እግዚአብሔር አለ?)

ወንጌል በድረ-ገፅ አገልግሎት ሁሉን ለመፍጠር የምትችል እንደሆንክ ራስህን ለአንድ አፍታ ብታስብበእውነት እንዲህ አይነት ውበት፣ ግርማ፣ ብዛት፣ የምህንድስና እወቀትና ምጥቀት የተጎናፀፈ ፍጥረት የምትፈጥር ይመስልሃልን ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ እንዴ! እንኳን ሁሉን ለመፍጠር የሚያስችል እውቀት ኑሮንሳይኖረንም ቢሆን በመጠኑ የሰው ልጅ እኮ ፈጣሪ ነው፡፡ (ስራ ፈጣሪ፣ ባህልን ፈጣሪ፣ ሳይንስን ፈጣሪ፣ ፍልስፍናን ፈጣሪ፣ ሀይማኖትን ፈጣሪ፣ ውስብስብ ማሽኖችን ፈጣሪ ነው፡፡) ይልቅስ በበጎነት ከተረዳነው የተፈጥሮ ምርጦሽ ድንቅ ነገርን ያደርጋል፡፡ ሰባኪዎች የተፈጥሮ ምርጦሽ በዕድል ወይም ራንደም ይመስላቸዋል፡፡ እንዲህም ይላሉ ወንጌል በድረ-ገፅ አገልግሎት ላይ በተጻፈው ተመሳሳይ አካሄድ “Even the simplest of life forms are too complex to have come together by random chance. There are not enough molecules in the universe, or time since the beginning, to allow for these possible ways to come together in even this simple life form, let alone to produce human beings. The human eye alone defies explanation by the randomness of evolution. It is the equivalent of the monkey typing Hamlet.” በእርግጥ አንድ ጦጣ ኮምፒውተር ቢሰጠው የሸክስፊርን ሀምሌት ወይም የሀዲስ አለማየሁን ፍቅር እስከመቃብርን ሊደርሰው ይችላል ማለት ሞኝነት ነው፡፡ ሰባኪዎች እንደሚሉት ዝግመተ ለውጥ በፕሮባብሊቲን (Probablility) ህግ ብቻ የሚካሄድ አይደለም፡፡ ዳውኪንስ የዝግመተ ለውጥ ኮር ስለሆነው የተፈጥሮ ምርጦሽ እንዲህ ይላል፦ “Natural selection is not random, nor does it operate by chance. Natural selection preserves the gains and eradicates the mistakes. The eye evolved from a single, light-sensitive cell into the complex eyeof today through hundreds if not thousands of intermediate steps, many of which still exist in nature.”

የሰው ልጅ ቅንጭላቱ፣ አይኑና ማንኛውም ስሪቱ ገራሚ ነው፡፡ ታዲያ ይህን ማን አደረገ? Creation ሳይሆን Evolution ነው፡፡ Intelligent design ሳይሆን

Created in Master PDF Editor

unintelligent design ነው። በሰው ሰውነት ውስጥ ያሉትን ኬሚካሎች ከእንስሳት የሚለየው ማንሰላሰል የሚችል ቅንጭላት መኖሩ ነው። ሌላው ሌላው ነገር ሁሉ ያ ተመሳሳይ ነው። የማሰብ ለውጡም የመጣው በሂደት ነው በዝግመተ ለውጥ።

ኤቲስቶች ሁሉን እናውቃለን አንልም። የማናውቀውን ነገር ግን እግዚአብሔር ነው ብለን አናምንም። አለማወቅ የእግዚአብሔር ህልውት ማረጋገጫ አይሆንም። በሰውነታችን ውስጥ፣ በተፈጥሮና በጠፈረ ውስጥ ለህሊና የሚከብዱና ሳይንስ ያልደረሰባቸው ሚስጢሮች አሉ። ያ ማለት ግን እግዚአብሔር አለ ማት አይደለም ቤርመዳ ትሪአንግል ምንም ይሁን ምን ሚስጡሩ እስኪፈታ መጠበቅ ነው። ምክንያቱም ለሽህ ዘመናት የማይታወቁት ውስብስብ ጥያቄዎች ተመልሰዋልና። የሰው ልጅ እውቀት መቸም መሉዕ ሊሆን አይችልም፣ የሁሉንም ጫፍ ላይነካ ይችላል። ግን በጎደለ ቦታ አማልዕክትን ማስገባት ተገቢ አይደለም።

2. የእግዚአብሔርን መኖር ታሪክ ይመሰክራል

> "በዚህ ዓለም አምልኮ የሌለው ሕዝብ እንዳልኖረ የሰው ልጅ ታሪክ ያስረዳል። ከጥንት ጀምሮ እስከ አለንበት ዘመን ድረስ የአምልኮቱ ዓይነት ይለያይ እንጂ ከትክክለኛ እምነት ውጭ የሆኑ ወገኖች ባዕድ አምላክ ወይም ብዙዎች አማልክትን ያመልካሉ። ይህም ሁሉ የሚያሳየው ምንም እንኳን ሁሉም እኩል እግዚአብሔርን ወደማመን ደረጃ ባይደርስም ጥረቱ የሚያረጋግጠው የአንድ እውነተኛ አምላክን መኖር ነው። እግዚአብሔር ባይኖር ሰው ይህን የአምልኮ ጠባይ ከየት ሊያገኝ ቻለ?" (የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ን እምነትናሥርዓተ አምልኮ፣ ገጽ 1)

መሰረቱ ቢለያይም አብዛኛው የአለም ህዝብ እምነት ነበረው። ልክ ነው ሁሉም ባይባልም ሰዎች ያምናሉ። ምናልባት ጥቂቶች ሁሉንም ሊጠራጠሩ ወይም ሊክዱ ይችሉ ይሆናል። በተለይህ በፍልስፍናው ሰፈር ሁሉም ነገር ምናብ ነው፣ እውነተኛ ህልውና ያለው ነገር የለም የሚሉ እንዳሉም ሰምቻለሁ። ማመን የሰው ልጅ አስተሳሰብ አንዱ ገፅታ ነው። አማኞችም እኔም የምናምንበት ነገር መኖሩ ሊያበሳጭን አይገባም። የገባንን እያመነን፣ ያመነውን እየመሰከረን መኖር ደስተኛና ውጤታማ እንድንሆን ያደርገናል። ችግሩ ማመኑ ላይ ሳይሆን የምናምነው ነገር ተጨባጭነትና ምክንያታዊነት ላይ ነው። በሆነ ነገር ማመን ብቻ በቂ አይደለም። የማምነው ነገር ስህተት ቢሆንስ ብለን መጠየቅ ግን አለብን። ብዙዎች ዝም ብለው የሚያምኑትን ለመከላከል መደንፋት ይወዳሉ፣ የሚቃረኑዋቸውን እጅግ ይጠላሉ፣ የሚሞግቷቸውን ያለስማቸው ስም ይሰጣሉ፣ ያለግብራቸው ግብር ያወርሳሉ።

ለኔ በጎ አማኝ ማለት የሚያምነውን የማይቀበሉትን የሚያከብርና የማምነው ከሚያምኑት በምን ይሻላል ብሎ ራሱን የሚመረምር ነው። በምኖርበት ማህበረሰብ

Created in Master PDF Editor

እንደተረዳሁት ብዙዎች የማያምኑትን ማወቅ አይፈልጉም፣ የሚያምኑትንም ለማወቅ አይጓጉም። ሰዎች ማወቅን የሚፈሩት ወደው አይደለም በማወቅ ማግስት የሚፈጠርባቸውን አይን ያወጣ ጥያቄ ለማድበስበስ እንጅ፣ እውነትነው ጥቂት ባወቅን ቁጥር ብዙ ጥያቄ ይፈጠርብናል ግን ጥያቄዎቹን ከማዳፈን መጋፈጥ አይሻልም? በእርግጥ ከጥያቄዎቹ ብዛትና ብርታት አንፃር ዝም ብሎ ማዳፈን ይሻላል የሚሉ አይጠፉም። ግን እንዴት ውስጣዊ ጥያቄን በአመድና በገል ማዳፈን ይቻላል? እኔ በረመጥ ውስጥ ከመቃጠል መንደድ ይሻላል እላለሁ። በታሪክም ሰዎች ጥያቂዎቻቸውን ለማዳፈን ሀይማኖትን ፈጠሩ እንጅ እግዚአብሔርን አላገኙትም። ዛሬም የሌለውን የሚፈልጉት አዳዲስ ታሪክ እየጻፉ አዳዲስ ሀይማኖት እየመሰረቱ ነው።ታድያ ታሪክ እንዴት ለማመን ምክንያት ሊሆን ይችላል? በእውነት ታሪክ ለፈጣሪ መኖር ምስክር ነውን?

የሰው ልጅ በዋሻ እያለም፣ በአደን እና ፍራፍሬ በመልቀም ሲተዳደር እያለም፣ እርሻና እንስሳትን ማላመድ ሲጀምርም፤ የግብይትና ከተሞችን መመስረት ሲጀምርም፤ ጎሳዎችን መመስረት ሲጀምረም፣ መንግስት መመስረት ሲጀምርም፣ በፊውዳል ስርዓት ሲተዳደርም፣ በኢንዱስትሪው አብዩት ዘመንም ዛሬም በሳይንስና ቴክኖሎጅ ዘመንም እንደየ እድገት ደረጃው የተለያዩ አማልዕክትን ሲያመልክ እንደኖረ ይታወቃል። የሰው ልጅ ታሪክ ከሀይማኖት የተለየ አይደለም። ቢሆንም እምነት ባለበት ሁሉ ግን ጥርጣሬና አለማመንም እንደነበር መዘንጋት የለብንም። በእርግጥ የሰው ልጅ በታሪኩ ከአለማመን ይልቅ ለማመን ያደላል ይህም የሆነው ሰዎች ፈጣሪን የመፈለግ ዝንባሌ ስላላቸው ነው። ሰዎች ከጥንት እስከ ዛሬ የማመን ዝንባሌ አላቸው ማለት ግን ፈጣሪ አለ ከማለት ጋር ግንኙነት የለውም። የምንመኘው ነገር ሁሉ ህልውና ላይኖረው ይችላል። ህልውና የሌለውን እንዲኖር የምንፈልገውን አምላክ እንዲኖር ስንጥር መኖራችን ታሪክ ይመሰክራል። ሰዎች ፈጣሪን የመሻት ጥማታቸው “ለማይታወቅ አምላክ” እያሉ አምልዕኮ ሲያቀርቡ እንደነበር ይታወቃል። ይህን ጥማት ሲግመንድ ፍሮይድ እና ሌሎች የስነ-ልቦና ሙህራን ተመራምረው illusion መሆኑን አረጋግጠዋል።

የሰው ልጅ አምላኩን በፅኑ መፈለጉ ብቻ ሳይሆን በታሪክ አምላክህ ነኝ ወይም አምላክ ልኮኛል እያሉ የመጡት ቁጥር የትየሌሌ ነው፡ አንዳንዴ ደግሞ በሚገርም ሁኔታ አምላካችን አንተ ነህ ብለው ሰዎች ከመካከላቸው ሰውን ወደ አምላክነት ከፍ ሲያደርጉ በታሪክ ተመዝግቧል። ለዚህም በንጉስነት የምናውቃቸው አፄ ሀይለ ስላሴ ይጠቀሳሉ። ጃንሆይ ለብዙዎቻችን ተራ ሰው እና እንደ ሀገር እንደመራ ንጉስም ደካማና ጠንካራ ጎን ያላቸው የራስ መኮነን ልጅ ነበሩ። ስለራስ ተፈርያን እምነትና የአምልዕኮ ስርዓት ምርምር ባለደርግም ጃንሆይን እንደ መሲህ ወይም እንደ አምላክ እንደሚቆጥሯቸው ግን አውቃለሁ። ከዚህ የምንረዳው ተስጥኦ ያላቸው ሰዎች እንኳን ከአምላክ ዘንድ

Created in Master PDF Editor

ተልኮን ነው ብለው ባይሉ እንኳ ለመንበርከክ እንቸኩላለን፡፡ ይህ የሚያሳየው የሰው ልጅ ከውሃ ጥም በላይ አምላኩን በመጠማት እየተሰቃየ መሆኑን ነው፡፡ ውሃ የጠማው ሰው ውሃን ሊተካ የሚችልን ነገር ወይም የደፈረሰ ውሃ ካገኘ ከመጠጣት ወደ ኋላ እንደማይል ሁሉ (ከተሜዎች ላይገባችሁ ይችላል) የአምላክ ፈለጋ ጥማቱንም ለመወጣት ማጣራት ላያደርግ ይችላል፡፡ ታሪክ የሚመሰክረው ይህን ነው፡፡

ብዙ ሰባኪዎች ከሰው ልጅ ህልውና እና ባህል ጋር አብሮ የኖረው የዝግመተ ለውጥ አስተሳሰብ ሳይሆን ሀይማኖት ነው ይላሉ፡፡ አወ! የሰው ልጅ በእየ ጊዜው አዳዲስ ሀይማኖቶችን እንደ ፈላስፋው፣ አዳዲስ አማልዕክትን እንደፈጠረው እና ስራውን የሚያቀላጥፉ ካህናት፣ ነብያትና ሀዋርያት እንደ ሾመው ሁሉ በተቃራኒ አቅጣጫም የሚፈጠሩትን አማልዕክት፣ የሚመሰረቱትን ሀይማናቶችና የሚሸሙትን ነብያት፣ ሀዋርያትና ካህናት ሲሞግቱ የኖሩ እንዳሉ የሀይማኖት ታሪክ ምስክር ነው፡፡ በኋለኛው የዳርዊን ዘመን ግን ሚዛን የሚዳፈ አስተሳሰብ ብቅ አለ፡፡ በእርግጥ አስተሳሰቡ የቆየ ነው ወደ ህዝብና ወደ ትምህርት ስርዓቱ የተቀለቀለው ግን በደርዊን ዘመን ነው፡፡ ይህ የአለማችን ድንቁ አስተሳሰብ እንደሆነ የተመሰከረለትና ዳራዊንንም አለምን ካስደመሙ ሳይንቲስቶች አናት ላይ ያስቀመጠው፣ “The origion of species” የተባለውን መፅሀፍም የአለምን አስተሳሰብ በእጅጉ ከቀየሩ መፅሐፍት አንዱ እንዲሆን ያስቻለው ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ “ዝግመተ ለውጥ” ይባላል፡፡ አሁን አሁን ሳይንስ ሁሉ ከዝግመተ ለውጥ አስተሳሰብ የተቀዳ እስኪመስል ድረስ Evolutionary የሚል ቅፅል ስም ወይም Evolution of የሚል ምዕራፍ የሌለበት የትምህርት ዘርፍ አላጋጠመኝም፡፡ ሌላው ቀርቶ በቤተ-ክርስቲያናት በሚሰጡ የስነ-መለኮት ትምህርት እንኳ ተፅእኖው በጉልህ ይንፀባረቃል፡፡

ያለፈ ታሪካችንን ገምግመን እንደተረዳነው ሰዎች ተፈጥሮአዊ የሆነ የማምለክ ዝንባሌ አለን፡፡ ታላቁ ሳይንቲስት ዳርዊን የነገረን ግን ይህን ዝንባሌ መልሰን እንድናጤነው ነው፡፡ የዳርዊንን እግር ተከትለው የመጡት ፈላስፎችና ሳይንቲስቶች ደግሞ (በተለይ ፍሮይድ) ይህ የማምለክ ዝንባሌ ቅዠት መሆኑን ነግረውናል፡፡ ወንድሞች እና እህቶች ማመንም አለማመንም መብት ነው፡፡ ለማመንም ለአለማመንም ግን ምክንያታዊ መሆን ያስፈልጋል፡፡ ለማመን የሚያበቁትም ለአለማመን የሚገፋፉትም ምክንያቶች ከእጃችን ናቸው፡፡ ለእኔ በሰው ልጅ ታሪክ የተመለኩት አማልዕክት፣ የተመሰረቱት ሀይማኖቶችና እኔ ልንገራችሁ ያሉን ካህናት፣ ነብያትና ሀዋርያት አልበቁኝም፣ አንሰውብኛል፡፡(በቁጥር ሳይሆን በሃሳብ)፡፡ ምን አለበት ከታሪክ አጣቅሸ፣ እውነትን ተንተርሸና እውናዊ መገለጥን አምኘ ላሳምንህ እችላለሁ ለሚለኝ ሰው እንደመሆኔ የማመን ጉጉት አለብኝ፡፡ ምን አልባት የኔ ችግሬ አሜን! አሜን! ለማለት አልቻኩልም፡፡ በማመንም ባለአለማመንም አስተሳሰቦች የተሞረደ ስነ ልቦና እንዳለኝ

Created in Master PDF Editor

ይሰማኛል፡፡ በግሌ ግን እስከማውቀው ድረስ በታሪክ ጥያቄየን የሚመልስ ሀይምኖታዊ አስተሳሰብ አልተነሳም፡፡

3. የሕይወትን ውስብስብነት በሳይንስ ሊገልጽ አይችልም

"Belivers say Science only deals with the here-and-now and thus cannot answer histor- ical questions about the creation of the universe and the origins of life and the human species. The answer is Science does deal with past phenomena, particularly in historical sciences such as cosmology, geology, paleontology, paleoanthropology, and archeology. There are experimental sciences and historical sciences. They use different methodologies but are equally able to track causality. Evolutionary biology is a valid and legitimate historical science." (Why people believe weird things, 142)

ምድር እውን በሆነች ከአንድ ቢሊዮን ዓመታት በኂላ፣ የዛሬ 3.5 ቢሊዮን ዓመት ገደማ፣ ሕይወት ያላቸው አካላት በምድር ላይ እውን እንደሆኑ ይገመታል፡፡ ሕያውነት ከግዑዝ ኬሚካሎች፣ ሞሊኪዩሎች፣ መካከል በውቅያኖስ ውስጥ ከተካሄዱ ውስብስብ መስተጋብሮች መኻል በአጋጣሚ በሞሊኪዩሎች ውህደት እንደተከሰተ ይታመናል፤ ግን ይህን ለመገመት እንጂ ለማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ሆኖም ለግምት የሚያበቁ ብዙ መረጃዎች አሉ፡፡ . . . ይህም አጋጣሚ በብዙ የሳይንስ ምሁራን ዕይታ፣ ቢሊዮን ዓመታት በፈጀ፣ በውቅያኖስ ውስጥ የተካሄደ ተፈጥሯዊ ሙከራ ተደርጎ ይታያል፡፡ ንዑስ ዘአካላት ከሌላ ኀላኤት ነወ የመጡ ሕይወት እዚህ እኛ ኀላኤት ላይ አልጀመረችም የሚሉም አልጠፉም፡፡ ዘአካላት ሕያውነትን የትም ይጀምሩ፤ የአጀማመራቸው ሁኔታ ያው ነው ከግዑዛን ወደ ሕይወት ባለፀጋነት፡፡ በዝግመተ ጉዞ ደግሞ አሁን ያሉት እንስሳት እና እፀዋት ተገኙ፡፡ ዘአካላትም (የሕይወት ባለፀጋዎች) ሆኑ ግዑዝ አካላት የተገነቡባቸው ሞሊኪዩሎች የመሠረታዊ ግንባታው ግብዓቶች ያው አቶሞች ናቸው፡፡ (ሽብሩ ተድላ፣ የህያው ፈለግ፣ 2010 ዓ.ም፣41)

የስነ መለኮት ሰበኪዎች ሳይንስ ሁሉንም ውስብስብነት፣ ምንጩንና ሂደቱን ማብራራት አይችልም ይላሉ፡፡ይቀጥሉና ተፈጥሮን ለሳይንስ የማይደረስበት እንዲሆን ያደረገው እርሱ እግዚአብሔር ነው ስለዚህ የሁለንታን ሚስጢር፣ ስነ-ስጥረትን፣ የሰውን ማንነት እና ከተፈጥሮ ጋር ያለውን ቁርኝት ማጥናት ያለበት ሀይማኖት ነው ይላሉ፡፡ በእርግጥ ሀይማኖት ውስብስብ ጥያቄዎችን ሲመልስ ለዘመናት ኑሯል፡፡ በተለይ በዘመናቱ የተነሱት ታላላቅ የሀይማኖት መሪዎች የሰውን አስተሳሰብና አኗኗር እስከመቀየር የደረሱ አብዮተኞች ነበሩ፡፡

Created with Master PDF Editor

በአጠቃላይ በሀይማኖት በኩል ሙሴ፣ኢየሱስእናመሐመድ ዘመን የማይሽራቸው አብዮታዊመሪዎች ናቸው። ሙሴ፣ ኢየሱስ እና መሐመድ ዘመናዊው አማልክትን አስተዋውቀውናል። ዘመኑ ያለፈባቸውን የኒዮሊቲክ፣ የግብፃዊእና የግሪክ ሃይማኖቶች ከምዕራብ በሦስቱ የአብርሃምን ሃይማኖቶች (አይሁዳዊነት, ክርስትና እና እስልምና)፤ ከደቡብ እስያ በዴሀሚክ (Dharmic) እና ከምስራቅ እስያ በታኦይስት (Taoist) ተቀይረዋል። ሆኖምግን ዛሬ ሰዎች ከዚህም ከዚያም እነዚህ ሀይማኖቶች በተራቸው በሌላ በተሻለ አስተሳሰብ እንዲቀየሩ እየጠየቁ ነው። በእውኑ ሀይማኖት ያረጅልን? ለአብዮቱ መስፋፋት የግሪክ፣ የግብጽ፣ የቻይና እና የሌሎች ባህሎች ቀደምት ስልጣኔ ሊመሰገን ይገባል፣ ከስልጣኔዎች በፊት የነበሩ ስልጣኔዎች ናቸውና።

“ሰዎች ጦረኛ በነበሩበት የብሉይ ኪዳን ዘመናት እግዚአብሔርም ጦረኛ ሆኖ ተገልጿል። የሰዎች ንቃት ጎሊና ወደ ፍቅርና ሰብዓዊነት ማዘገም ሲጀምር ደግሞ እግዚአብሔር በክርስቶስና በነቢዩ መሐመድ ፍፁም አፍቃሪና ፍፁም ሰብዓዊ ሆኖ ተገልጿል።” (ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣ 97)

በመሠረቱ መለኮታዊ አስተሳሰብ በተፈጥሮ ውስጥ ከሳይንሳዊ ግንዛቤ በላይ የሆኑ ኃይሎችአሉ ብሎ ያምናል። ጥርጥር የለውም ማንም ሳይንቲስት የሚቀበለው ሀቅ ነው ይህ ማለት ግን ሳይንቲስቶቹ <ሁሉ በእርሱ ሆነ> ብለው አላንቀለፉም በእየቀኑ ይመራመራሉ እንጅ።

ጋሊልዮ (1564-1642) የዘመናዊ ሳይንስ አባት በ1616 ከጳጳሱ ኡርባን (Urban) ጋር የነበረው ክርክር መሬት የጽንፈ ዓለም ቋት ማዕከል ናትን የሚል ነበር በወቅቱ መናፈቁ ጋሊልዮ በደማቅ ምርምሮቹ የመጀመሪያውን ወደ አለምአቀፋዊነት የሚመራውን አብዮት አፈነዳው።ይህ የለውጥ አብዮት ለ 400 ዓመታት ያህል በመካሄድ ላይ ነው። ኒውተን፣ አንስታይን፣ ዳርዊን እና ሃውኪንግ አስተዋፅኦ ካደረጉ በርካታ የሳይንስ ሊቃውንት መካከል በጣም ጎልተው ይገኛሉ። የሃይማኖት ባለሥልጣናት ስለ ተፈጥሮ ያላቸውን ግንዛቤ ቀስ በቀስ በመሻሻል ከሳይንስ እውነታውን ለመቀበል ተገድደዋል። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በ1758 የፀሐይ ማዕከልነት (ሄልዮሴንትሪክ)ን የሚደግፉ መጻሕፍትን መከልከል አቆመች ይልቅስ የመናፍቁ ጋሊልዮ መሬት የሁለንታ መዕከል አይደለችም የሚለውን ተቀበለች። የውስብስብነት መፍቻ ቁልፉ ከካቶሊክ ጳጳሳት ወደ ሳይንቲስቶች ተሸጋገረ።

በቅርብ አሥርት ዓመታት የአብዮቱ ፍጥነት እየጨመረ መጥቷል። የስነ ከዋክብት ተመራማሪው ካርል ሳጋን (1934-1996) ሳይንስን ለህዝብ በማድረስ ለቀጣዩ ጸሐፊዎች መሠረት ጥሏል። ሃይማኖታዊ ቀኖናን በግልጽ የሚተቹ በድፍረት የሚጽፉ እና በሌሎች ሚዲያዎችን የሀይመኖት መሪወችን በጥያቄ የሚሞግቱ

Created in Master PDF Editor

ሳይንቲስቶች እየታዩ ነው። በዛሬው ጊዜ በአምላክ መንፈስ አነሳሽነት በንጉስ ነገስቱ ትዕዛዝ የተሞላው የአኗኗር ዘይቤ ከዙፋኑ ወርዷል።

ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ፣ ጅኦሎጅ፣ ባዮሎጅ፣ ኮስሞሎጂና አስትሮኖሚ ከተፈጥሮ ሳይንስ ፊሎሶፊ፣ ሳይኮሎጅ፣ ሶሾሎጅ፣ ፖለቲክስና ሲቪክስ ከማህበራዊ ሳይንስ ከግዙፉ ከሁለንታ እስከ ትንሻ ፓርቲክል ድረስ ያለውን ሚስጢር ለመፍታት በስራ ላይ ናቸው። ሳይንስ በእየ ቀኑ የበዙ ሚስጢሮችን ይፈታል፣ ጥያቄ እየፈጠረ መልስ ይሰጣል፣ መልስ ያላገኘለትን አላውቅም ይላል። ሳይንስ ለሰው ልጅ ህይውት ብርሃን፣ ህይወትና መንገድ ነው። ብርሃንነቱ በስራ እንጅ በስብከት፣ በጦርነትና በማስገደድ አይደለም። ህይወትነቱ በአኗኗር በማሰልጠን (አንዳንዴም በማሰይጠን) እንጅ በትርክት አይደለም። መንገድነቱ አማራጮችን በመስጠት እንጅ በሮችን በመቆለፍ አይደለም። በሳይንስ መመካት ጽድቅ እንዳልሆነ ሁሉ በሳይንስ ማፌዝ ሀጢዓት አይደለም።ነገር ግን በሆነልን ነገር እየተደነቅን የደከሙልንን እያመሰገንን መጠቀም አለብን። “If you want to know how the world came to be read about geology, evolution, physics, chemistry, and biology. If you want to know more about morals and ethics, read about sociology, psychology, law, and history. If you want a hero to model your life after, read biographies of great freethinking people who influenced the world, such as Thomas Paine, Thomas Jefferson, Benjamin Franklin, Alexander Graham Bell, Nicolaus Copernicus, Galileo Galilei, Sir Isaac Newton, and all those who dared to seek answers and changes to better the world.” (50 voices of disbelief, page 14)

ሁሉንም ነገር በጥልቀት ከመረመርነው ውስብስብ ነው፣ ለዚህም ሲባል ነው ሳይንስ ብዙ ዘርፎች እንዲኖሩት የተደረገው። ተስፋ መቁረጥ አያስፈልግም። ዳርዊን ምን ይላል መሰላችሁ “Ignorance more frequently begets (brings) confidence than does knowledge. It is those who know little, and not those who know much, assert that problem will never be solved by science.” ይህን ውስብስብነት የሚያጠናው አዕምሮ በራሱ ውስብስብ መሆኑ ትልቅ እንቆቅልሽ ነው። ሳይንቲስቶቹ ይህን መርማሪና አመራማሪ አዕምሮ “The huge human brain, approximately 1,350 cubic centimeters, is the most complex organic structure in the known world.” ይሉታል።

ይሁን ምን ችግር አለው ካላልን በስተቀር ሳይንስ ከሃይማኖት ጋር ውስብሰብነትን ለማብራራት እኩል ድምፅ የላቸውም። መንገዳቸውና አተረጓጎማቸው በመረዳት ውጤቱን አለመቀበል ይቻላል። ሳይንስ የውስብስብነትን ሚስጢር ለመፍታት ከጥያቄ ሲነሳ ሀይማኖት ከመልስ ተነስቶ ወደ ጥያቄ ይሄዳል። ‘ሁሉ በእርሱ ሆነ’ ብለን ከመለስን በኋላ ለምን፣ በማን፣ እንዴትናመቸ ብለን መጠየቅ አንችልም። አማረም ከፋም የውስብስብነትን ሚስጢር መፍታት ያለበት ሳይንስ ነው። ሳይንስ ያልፈታውን

እንቆቅልሽ አለ ማለት የሳይንስን ድክመት ቢያሳይ እንጅ የሃይማኖትን ጥንካሬ አያሳይም።

ድሮ የሃይማኖት ዋናው ተግባር ጥንታዊ ሰው (primitive man) ሊረዳው ላልቻለው እንደ መብረቅ እና እሳተ ገሞራ ለመሳሰሉት የተፈጥሮ አደጋዎች መልስ መስጠት ነበር። ለዚህም እልፍ አማልክትን እካባቢው እና ጊዜውን አስመስሎ ፈጥሮአል።አሁን በሰለጠነው አለም ስለ ተፈጠሮ አምላክ እንዲያብራራ አይጠየቀም። ለበርካታ ተፈጥሯዊ ሂደቶች በሳይንሳዊ ዘዴ አማካኝነት የተሻለ ገለፃ ማቅረብ ይቻላል።ይልቅስ መፅሀፍ ቅዱሳው አስተሳሰብ ሰባኪዎች እንደፈለጉ አቅንተው እና አጉብጠው ካልተረጎሙት በቀር ስለ ስነ-ፍጥረት አሳማኝ መረጃ አይሰጥም። በተለይ በመጽሐፍ ቅዱስ የስን- ፍጥረት ታሪክ ውስጥ እያንዳንዱ የፍጥረት ቀን በሺህ፣ በመቶ ሺህ፣ ወይም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዓመታት ርዝመት ሊኖረው ይችላል የሚላው በሬ ወለድ አተረጓጎም ያስቅኛል።ሳይንስን አንዳንድ ሰዎች በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የባልቴቶች ወሬ ሲያስመስሉት ይታያል የሚለው ደረጀ ፀጋዬ የሳይንስን አሰራር እንዲህ ያብራራዋል፦

> *“የሳይንስ ጥናት ተፈጥሮን ከመመልከትና ከመመርመር ይጀምራል። ከዚህም በመነሳት ለሚያጠናው ውጫዊ ነባራዊ አለም አእምሯዊ ምስለ ተምሳሌት (Model) ያቀናብራል። ይህንንም ምስለ ተምሳሌት በአመክንዮ፣ በቁሳዊና በሂሳብ ዘዴዎች ማቅረብ ይቻላል። በጉዳዩ ዙሪያ ሁኔታዎች በፈቀዱትና በተቻለ መጠን መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላየመረጃዎቹን ውስጣዊ ትስስርና አሰራር የሚገልጽ ሃሳብ (hypothesis)ይበጃል። አዲሱ ሃሳብ በተቻለ መጠን ከዚህ ቀደም ከተረጋገጡና ተቀባይነትካላቸው ሃሳቦች ጋር ቢጣጣም ይመረጣል። ዋናው ነገር ግን በዚህ መንገድየተቀናበረው ሃሳብ ተጨማሪ ሳይንሳዊ ትንበያዎችን (Predictions) ማፍለቅመቻሉና በሙከራ መረጋገጡ ነው። ይህን የማያሟላ ሃሳብ ከተቻለ ይሻሻላልካልሆነም ይተዋል። ይህንን ፈተና ያለፈ ሃሳብ ወደ ሳይንሳዊ መላ ምት(Scientific theory) ደረጃ ከፍ ይላል። ሳይንሳዊ መላ ምት እንደውበደመነፍስ ተነስተው የሚጽፉት ሃተታ መናፍስት ሳይሆን በጥንቃቄ የተቀመረውስጣዊ ትስስር እና ስምምነት (Self consistent) ይዘት ያለውየሚጠናውን ነባራዊ አለም በሁለንተናዊነት ለመግለጽ የምንጠቀምበት ሰፊሃሳብ ነው።”*(ደረጀ ፀጋዬ፣ የኢ-አማኒው ኑዛዜ)

ወደ ሳይንሱ የተጠጉት ሰባኪዎች ስለ ስነ ፍጥረት በተለይም ስለ መሬት ውስብስብነት ምንጩ እግዚአብሔር እንደሆነ ለማስረዳት ይሞክራሉ። መሬት ይላሉ፦ “መሬት እስካሁን ከታወቁት ፕላኔቶች ሁሉ ለተክሎች እና ለእንስሳትና ለሰው ሕይወት ተስማሚ ከባቢ አየር ያላት ብቸኛ (?) ፕላኔት ናት። ምድር ከፀሐይ በትክክለኛ ርቀት

Created in Master PDF Editor

ላይ ትገኛለች ምድር ትንሽ ከፀሐይ ብትርቅ ሁላችንም በብርድ ባለቅን ነበር፡፡ ምድር ወደ ፀሐይ ትንሽ ብትቀርብ ኖሮ ደግሞ ሁላችንም ተቃጥለን ባለቅን ነበር፡፡ ምድር አሁን ካለችበት በክፍልፋይ ለውጥ ብታደርግ በምድር ላይ ሕይወት አይኖርም፡፡ ምድር በፀሐይ ዙሪያ በሰዓት 67,000 ማይል በምሕዋርዋ ስትሽከረከር ቦታዋን ሳትለቅና ለገጽታዋ ትክክለኛውን ሙቀትና ቅዝቃዜ እየሰጠች ነው፡፡" በትክክል ተናግረዋል ችግሩ መሬትን ማን እንዲህ እድለኛ አደረጋት፣ ሌሎች ሚሊዮን ፕላኔቶችስ ለምን እድለ ቢስ ሆኑ? አማኞቹ እግዚአብሔር ይላሉ እኔ ግን የእድሉን እጣ ያወጣው እውሩ ዝግመተ ለውጥ ነው እላለሁ፡፡ እውሩ አምላካችን እድለኞችን እያስከተለ እድለ ቢሶችን ወደ ቅሬትነት እየቀየረ በዝግመት ጉዞውን ቀጥሏል፡፡ብዙ አማኞች እንደሚያምኑት እንዲሁም United Church of God "A Planet Perfect for Life" በሚል ርዕስ የፈጣሪን መኖር ለማረጋገጥ ባሰፈረው ጹህፍ የመሬትን እድለኘነት እንዲህ ይተነትኑታል፣ ጹህፉን ያገኘሁት የበፍቄ አለም ከሚል ድህ-ገጽ ነው፡፡

"የመሬት ከባቤ አየር (atmosphere) ለሕይወት ጠቃሚ የሆኑ ቅይጦችን በተገቢው ምጣኔ ይዟል፡፡ ለምሳሌ የኦክስጅን መጠን በከባቤ አየር ውስጥ ከ21 በመቶ ቢበልጥ ኖሮ ዓለማችን በቀላሉ በእሳት የምትቀጣጠል፣ ብሎም መርዛማ ስፍራ ትሆን ነበር፡፡ የናይትሮጅን መጠን 78 በመቶ ባይሆን ኖሮ በዝናብ ታጥቦ የሚወርደው መብረቅ አመጣሽ ኬሚካዊ ውሁድ ስለማይኖር ወይም መጠኑ ስለሚያንስ ተክሎች ተፈጥሯዊ ማዳበሪያ አያገኙም፣ ሕይወት አይኖራቸውም፣ ስለዚህ እንስሳትም አይኖሩም ነበር፡፡ ይልቁም መሬት አሁን ካላት መጠን ትንሽ ብትገዝፍ የመሬት ስበት መጠን ስለሚጨምር ብዙ ሃይድሮጅን በመሬት ክበብ ላይ ይሰበሰብና ምድሪቱን ለሕይወት የማትመች ስፍራ ያደርጋታል፡፡ መጠኗ ካሁኑ ትንሽ አነስ ቢል ኖሮ ደግሞ ስበቷ ስለሚቀንስ ኦክስጅን ከከባቢ አየሩ ይርቃል፣ ውሃ በቀላሉ ይተናል ስለዚህ ለሕይወት የማትመች ስፍራ ትሆናለች፡፡ ሌላው መሬት በፀሀይ ዙሪያ የምትሾርበት 66,600 ማይል በሰዓት የሆነ ፍጥነት ጥቂት ቢቀንስ በፀሀይ ተስቦ ለመንደድ፣ አሊያም ቢጨምር ከፀሀይ ርቆ ወደበረዶነት (ለመቀዝቀዝ) መንስኤ ይሆን ነበር፡፡ በተጨማሪም አሁን መሬት ከፀሀይ አንፃር ያላት የ23.5 ዲግሪ ዝንባሌ ባይኖር ኖሮ ወቅቶች እንዳይፈራረቁ፣ ምድርም ለሕይወት የማትመች እንድትሆን የማድረግ ተፅዕኖ ይኖረው ነበር፡፡ በስርዓተ ፀሀይ ውስጥ ለምሳሌ ጁፒተር ትልቋ ፕላኔት መሆኗ ይታወቃል፡፡ ሁሉም እስከዛሬ የታወቁት ፕላኔቶች አንድ ላይ ቢጨመቁ እንኳን ጁፒተር ከእጥፋቸው ትበልጣለች፡፡ የጁፒተር ትልቅ መሆን ለምድር እስከዛሬ አለመጥፋት ባለውለታ ሆኗል፡፡ ምክንያቱም ጁፒተር በግዙፉ ሰውነቷ የበራሪ ከዋክብትን (comets) አቅጣጫ በማስቀየርና አንዳንዴም ራሷን ሰውታ በመጋጨት ምድርን ሊያጠፉ

Created in Master PDF Editor

አቅም ካላቸው ግጭቶች ሰውራታለች::" (የበፍቄ ዓለም፣ https://befeqe.wordpress.com/)

የክርስቲያን ሳይንስ አቀንቃኞች መሬትን ለህይወት በተለይም ለሰው ምቹ ያደረገው ፈጣሪ ሆን ብሎ ነው ቢሉም መሬት ግን ያን ያህል ምቹ አይደለችም:: እንዲያውም ታሪኳን ወደ ኋላ ብንቃኝ በመከራ የተሞላ ነው:: የ21ኛው ክ/ዘመን ቁጥር 1 ሳይንቲስት ስቴፈን ሃውኪንግ ስለ መሬት እንዲህ ነበር ያለው <<*The Earth is under threat from so many areas that it is difficult for me to be positive. The threats are too big and too numerous. The Earth is becoming too small for us. Our physical resources are being drained at an alarming rate. We have presented our planet with the disastrous gift of climate change. Rising temperatures, reduction of the polar ice caps, deforestation, over-population, disease, war, famine, lack of water and decimation of animal species>> (Brief Answers to the Big Questions)*

መሬት ለቢሊዮን አመታት ለምንም ህይወት የማትመች ነበረች፣ በሂደት ግን ተፈጥሮዓዊ አቀማመጧና ቅርጿ አግዟት የፍጥረታት የመላመድ ትግል ተጨምሮበት በአንጻራዊነት ምቹ ፕላኔት ለመሆን በቅታለች::ወገኖች መሬት ታሪኳ የጥፋት ነው:: መሬት ከትክክለኛው አቅጣጫዋም ወጥታ ታውቃለች ወደፊም ከዚህ አንጻራዊ ምቹ ጎዳና ትወጣለች:: ይህን ለመረዳት በጅኦሌጅስቶችና በቅሪት ተመራማሪዎች የተደረሰባቸውን ታላላቅ የእልቂት ዘመናት (great extinction) ዘመናት ምንጮችን ማስታወስ በቂ ነው:: በቅርብ ሚሊዮንና ሽህ አመታት እንኳ ሙቀት ሲጨምር በጎርፍ ሲቀንስ በበረዶ ፍጥረታት ሲሰቃዩ ኑረዋል፣ ለውጡን ያልቻሉትም ወደ <u>ነዳጅ ዘይትነት</u> ተቀይረዋል:: በሰማይ አካላት ስንቴ እንደተደበደበች እራሷም አታውቀውም:: ክርስቲያን ሰባኪዎች መሬት ምቹነቷ የቱ ጋ ነው?

ሰላሟ፣ ውበቷና ምቹነቷ ከሌሎች ፕላኔቶች አንጻር ካላየነው ምድር ላይ ሲለሚካሄደው ሰቆቃ በእየቀኑ በአለም አቀፍ ሚድያ የሚሰራጩትን ዜናዎች ማስተዋልም በቂ ነው::ሪቻርድ ዳውኪንስ እንዲህ ይላል፦ "The total amount of suffering per year in the natural world is beyond all decent contemplation. During the minute that it takes me to compose this sentence, thousands of animals are being eaten alive, many others are running for their lives, whimpering with fear, others are slowly being devoured from within by rasping parasites, thousands of all species are dying of starvation, thirst, and disease. The universe that we observe has precisely the properties we should expect if there is, at bottom, **<u>no design, no purpose, no evil, no good, nothing but pitiless indifference</u>**."

በሁለንታ ላለው መመቸት ወይም አለመመቸት ዝግመታዊ ለውጥ ውስብስብነቱን ያስረዳል:: ይህን የዝግመተ ለውጥ ከፈጣሪ ያልተናነሰ ታላቅነትና ሀያልነት የገባቸው

Created in Master PDF Editor

የክርስቲያን ሳይንስ አራማጆች ዝግመተ ለውጥ ውስብስብነትን ይፈታል ግን በፈጣሪ ትዕዛዝ ነው ይላሉ:: ለምሳሌ እራስን በራስ መለወጥ (mutation) እና ጠቃሚውን መርጦ መውሰድ (natural selection)፥ ሁለቱም ዳርዊን የተጠቀመባቸው የዝግመተ ለውጥ ፍልስፍና መሠረቶች እኛም ባግባቡ እንጠቀምባቸዋለን የሚሉት መ. ኃ. ዶ/ር መስቀል 'ከምድራዊነታችን ባሻገር፣ ሦስተኛ መጽሐፍ' ላይ ባጭሩ ይላሉ፦ ባጭሩ:- "ማንኛውም አካላዊ ሕያው ካለ ፈጣሪ ወይም መላእክት እርዳታ የአካባቢ ሁኔታዎችን ተከትሎ ሲንቀሳቀስ፥ ራሱን በራሱ መለዋወጥ እንዲችል - ምድራዊነትን በደንብ አድርጎ እንዲያውቅበትና በራሱ እንዲኖር፥ ዝግመተ ለውጥ ውስጣዊ የተፈጥሮ ጠባዩ እንዲሆን አስፈልጓል፤ ይህ መልካምእንደሆነ እግዚአብሔር አይቶ ፈቅዷል ማለታችን ነው:: እግዚአብሔር አንዴ ፈጠርኩ ብሎ አይተውምና፤ ፍጡራኑ በምድር ላይ እየተራቡ እንዲበዙለት ስለፈለገ ፍጡራኑ የአካባቢያቸውን ሁኔታ እያቸነፉ የሚዘልቁበትንም መንገድ በውስጠ ባህሪያቸው (በ ዲ.ኤን.ኤ.) ውስጥ ፈጥሮላቸዋል:: ዝግመተ ለውጥን የራሳቸውን ውስጣዊና ውጫዊ ጠባይ መለወጫ መሳሪያ አደረገላቸው ማለት ነው" (ገጽ፣ 91) የDNAን ሀይል ለማብራራትም "ይህች ምድር ከተፈጠረች ጀምሮ ብዙ ለውጥ ተከስቷል:: በነኚህ ለውጦች መካከል ሁሉ ባህር መሬትን ሲከድንና ሲገልጥ፣ በበራድ ዘመን መሬቱ በበረዶ ሲሸፈን፣ የጎርፍ መጥለቅለቅም ሲከተል፣ ነፋስ፥ ውርጭና ሙቀት ሲለዋወጥ፥ የሞተው ሞቶ የተረፈውም ሲባዛ፤ ይኸው እስካሁን አካላዊ ሕይወት ከባህርም ከየብስም አልጠፋም፤ እግዚአብሔር በፍጡራኑ ውስጥ ሁሉ ሕያዋን እንደ አካባቢው ሁኔታ እራሳቸውን እንዲለውጡ የሚያስችል ዲ ኤን ኤ የተባለ የኮምፕዩተር ኮድ ፈጥሮላቸዋልና::" ይላሉ:: (ገጽ፣ 92)

እዚ ላይ የክርስቲያን ሳይንስ አራማጆች ውስብስብነትን የሚያስረዳ ሌላ ውስብስብ መንገድ አግኝተዋል ክሬሽን ሳይንስ የሚባል:: ግኝታቸውም ሳይንሳዊመሆኑን አብክረው ያስረዳሉ፣ በስርዓተ ትምህርቱም ስፊ ሽፋን እንዲሰጠው ባለስልጣናትን ይወተውታሉ:: Michael Shermer ግን ስለክሬሽን ሳይንስ እንዲህ ይላል፦ "Creation-science is scientific in name only. It is a thinly disguised religious position rather than a theory to be tested using scientific methods, and therefore it is not appropriate for public school science courses, just as calling something Muslim-science or Buddha-science or Christian-science would not mean that it requires equal time." (Why people believe weird things, page 141):: ብዙዎቹ የክርስቲያን ሳይንስ አራማጆች ፍጥረት ከቀላል ተነስቶ ውስብስብ እንዲሆን ዲዛይኑን ያዘጋጀው እግዚአብሔር ነው ይላሉ፣ በዲ. ኤን ኤ በኩል መሆኑ ነው:: በውስብስቡ ዲ.ኤን.ኤ(DNA) ሕዋስ ውስጥ ያለው የመረጃ ስልትፕሮግራም ነው::ዲ.ኤን.ኤ ከአራት ኬሚካሎች የተሠሩ ናቸው::እነርሱም ኤ(A)፣ ቲ(T)፣ ጂ(G) እና ሲ(C) ናቸው:: በሰው ህዋስ ውስጥ ያላቸው አቀማመጥ CGTGTGACTCGCTCCTGAT… አይነት ነው:: በእያንዳንዱ ሰው ሕዋስ (cell)

Created in Master PDF Editor

ውስጥ ወደ ሦስት ቢሊዮን የሚሆኑ የፊደል ፕሮገራሞች አሉ ይባላል። ህዋሱን ምን ማድረግ እንደሚገባው የሚነግሩ ማለት ነው።የክርስቲያን ሳይንስ አራማጆች ይጠይቃሉ፣ ይመልሳሉም "ይህ የሚያስደምመው ለምንድነው? ይህ የመረጃ ፕሮግራም በሰው ሕዋስ ውስጥ እንዴት ተዘረጋ? እነዚህ ተራ ኬሚካሎች ብቻ ሳይሆኑ የሰው አካል እንዴት መገንባት እንዳለበት መመሪያ የሚሰጡ ናቸው።ይህንን የተቀነባበረ መረጃ የባዩሎጂ ሳይንስ ሊያሰረዳን አይችልም።" በእርግጥ የDNAን ሚስጢር ለመረዳት የሚቀሩ ነገሮች አሉ፣ ቢሆንም ይህንም የደረሰበት ሳይንስ ስለሆነ ነገን ተስፋ ማድረግ መልካም ነው እንጅ መጠጊያ ቁጥቋጦ መፈለግ ከዝናብ አያስጥልም።

ስለውስብስብነት አሰሳ ሳደርግ <የሀበሻ ተማሪዎች> የሚል ድህረ ገጽ አገየሁ። ውስብስብነትን የአምላክ መኖርን ማራጋገጫ ብቻ ሳይሆን ውስብስብነት እጅግ ውስብስብ በመሆኑ ከእግዚአብሔር ውጭ ማንም አያውቀውም የሚል ሰነፍ አምክንዮ ያለው የክርስቲያን ሳይንስ ተረማምዶበት አየሁ። ገጹ አእምሮን በተመለከተ እንዲህ ነው የሚለው፦

> *"የሰው ጭንቅላት/አእምሮ በአንድ ጊዜ ብዙ መረጃዎችን የማስተናገድ አስደናቂ ችሎታ አለው። አእምሮህ የምታያቸውን ቀለሞች በዙሪያህ ያለውን የአየር ሁኔታ ምድር ስትረግጥ በእግሮችህ ላይ ሚሰማህን ጫና፣ በዙሪያህ ያሉትን ድምፆች፣ የአፍህን ድርቀት፣ያስተናግዳል። አእምሮህ ስሜትህን፣ ሃሳብህን፣ ትውስታህን ሁሉ ያስተናግዳል። ይህን ሁሉ እያደረገ የሰውነትህን ሥራዎች ማለት እንደ እስትንፋስ፣ የዐይን ሽፋሽፍት እንቅስቃሴ፣ የረሃብ ስሜትና የእጆችህን እና የጡንቻዎችህን እንቅስቃሴ የመከታተል ችሎታ አለው።"*

ዓይንን በተመለከተም *"ዓይን ሰባት ሚሊዮን ቀለማትን የመለየት ችሎታ አለው። በሚያስደንቅ ሁኔታ በአንድ ጊዜ 1.5 ሚሊዮን መልዕክቶችን ለማስተናገድ ይችላል።"* ገጹ ከዚህ የውስብስብነት አመክንዮ ተንስቶ ወደ ድምዳሜ ይሄዳል። *"ዝግመተ-ለውጥ(evolution) በአካል ላይ በሚያተኩር የለውጥ ትንታኔ ላይ ያተኩራል። ሆኖም ዝግመተ-ለውጥ ስለ ዓይን ወይም ስለ አንጎል ጅማሮ ወይም ሕይወት የሌለው ቁስ አካል መቼ ሕይወት እንዳገኘ ሊያስረዳ አይችልም።"*

እውነቱ ግን ይህ አይደለም ሳይንስ በተቻለ መጠን ለነገ የሚተውም የጥናት መስክ የለም ይልቅም ሕይወት የሌለው ቁስ አካል መቼ ሕይወት እንዳገኘ ለማስረዳት ያልቆፈረው ጉድጓድ የለም። ኪዚያም አልፎ ህይወት አይደለም ቁስ አካል እራሱ ከየት እንደመጣ በማብራራት ላይ ነው። ምን አላባት የድህረ ገጹ ባለቤቶች ገና ወደ ሳይንሱ ጠልቀው ያልገቡ ተማሪዎች ሊሆኑ ስለሚችሉ ስለ ታላቁ ፍንዳታና ስለሲንጉላሪቲ ሰምተው አያውቁ ይሆናል። የሰሙትና የገባቸው አማኞች እማ በውዝግብና በመደናገር

Created in Master PDF Editor

ላይ ናቸው። ሳይንሱን ከእምነታቸው ጋር ለማስታረቅም ከፍተኛ ትግል እያደረጉ ነው።

የስነ መለኮት ሙህራን ሳይንስን (በተለይም Big bangን እና Evolutionን) በተመለከተ ጥሪት ያለ ተቃውሞ ወይም ድጋፍ የላቸውም። አንዱ ይደግፋል ሌላው ይቃወማል፣ ልክ በውስጣቸው እንዳለው ንትርክ።Big bangን እና Evolutionን በተመለከተ የሚያፌዙት እንዲህ ይላሉ፦

“ሁላችንም በተንቀሳቃሽ ፊልም አልያም በአካል ከፍተኛ ፍንዳታዎችን ሰምተናል፤ አይተናል። እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ። ከነዚህ ፍንዳታዎች በኋላ ፍንዳታዎቹ ያስከተሏቸው ስርዐት ያለው ውጤት ተመልክታችሁ ታዉቃላችሁ? ፍንዳታው የፈጠረው ምርጥ ስርዐት፣ ፍንዳታው የፈጠረው ውብ ነገር ምንድን ነው? መልሳችሁ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አይሳነኝም። ፍንዳታ ስርዐት አልባነትን ከማስከተል ሌላ ምን ሊፈይድ፤ ፍንዳታ ያነን ነገር ወደ አለመኖር ከማሻገር የዘለለ ምን ሊያመጣ። በቃ ይኸው ነው፤ ከባድ ፍንዳታ፤ ቀጥሎ ቀውስ፣ ፍርስራሽ። ሌላ ምን ሊሆን። ይህ መንደርደርያ ለማሰብ ወደሚከብደኝና ብቻዬን ፈገግ ወደሚያሰኘኝ ፍልስፍና መንደር ጎራ ያደርገናል። የቢንግ ባንግ መላምት/Big bang theory/ ይሰኛል። የታላቅ ፍንዳታ መላምት መሆኑ ነው። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ሲቀበሉት በኩራት ነው። እስቲ ይህ ጉዱይ እናንተን ያኮራ ይሆን ያሸማቅቅ ለማየት ወደማዕዱ እንዝለቅ። ምሁሩ ዶክተር ራንግአንታን እኔ ይላሉ፤ <እኔ፣ ሕይወት የታላቅ ፍንዳታ ውጤት ነው የሚለውን መላምት፣ ከአንድ የማተሚያ ቤት ቃጠሎ ውስጥ አንድ ጥሩ መዝገበ-ቃላት ማግኘት ተቻለ ከሚለው የቅዠት ሃሳብ ለይቼ አላየውም።> ሲሉ የዚህን ፍልስፍና ስር አልባ አመክንዮ ገልፀዋል።ሌላው ሳይንቲስ፣ ሰር ፕሮፌሰር ፍሬድ ሆይል፣ በታላቅ ፍንዳታ ምክንያት ሕይወት ሊፈጠር ይችላል የሚለውን መላምት ሲተቹ እንዲ ይላሉ፦<በዚ መልክ ሕይወት ሊገኝ ይችላል ብሎ ማሰብ በቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች መካከል የነፈስ ከባድ አውሎንፋስ ተረፈ ምርቶቹን አላትሞና አጋጭቶ ሲያበቃ አንድ ቦይንግ 747 አውሮፕላን እነሆኝ ሊል ይችላል ብሎ ከማሰብ የተሻለ ነው ብየ አላየውም።> ብለዋል።”(ምንጭ፦ ወንጌል በድረ-ገፅ አገልግሎት፣ https://ethiopiansite.com/)

ተወዳጁ የእስልምና ሰባኪ ዶ/ር ዛኪር ናይክ ደግሞ በተቃራኒው እንዲህ ይላል፦ “The creation of the universe is explained by astrophysicists as a widely accepted phenomenon, popularly known as ‘The Big Bang’. It is supported by observational and experimental data gathered by astronomers and astrophysicists for decades.” (The Qur’an & The Modern Science, page 7)

Created in Master PDF Editor

ጸረ ቢግ ባንግና ጸረ ዝግመተ ለውጥ አራማጆች የጥቂት ሳይንቲስቶችን ሂስ እያጣቀሱ ማፌዝ አሁን አልተጀመረም፣ አዲስ ክስተት አይደለም:: ሲጀመር ሁሉም ስይንቲስቶች በBig bang እና በEvolutionን ማመን አይጠበቅባቸውም:: ቁጥራቸው በፐርስንት ሲገለጥ ምንም መሆኑንግን ልብ ይሏል::

አሁን አሁን ደግሞ የስነ መለኮት ሰበኪዎች ሳይንሱን የመቀበል አዝማሚያ ይታይባቸዋል:: ቢሆንም ግን እየተከተሉት ያለው ስትራቴጅ ሳይንሱን ወደ እምነት በማስረግ ወይም ሀይማኖቱን ወደ ሳይንሱ በማስጠጋት ነው:: እነዚህ ሰዎች ዝግመተ ለውጥን ከተቀበሉ በኋላ ሕይወት ያለው ነገር በራሱ ሊመጣ እንደማይችል ወይም ሕይወት ያለው ነገር ሕይወት ከሌለው ነገር ሊገኝ እንደማይችል ያምናሉ:: ይልቁንም ዝግመተ ለውጥን የመራው ፈጣሪ ነው ይላሉ:: አዳዲስ የሳይንስ ግንኝቶች ሲገኙ ይህ ግኝት የእግዚአብሄር መኖርን የበለጠ የሚረጋገጥ ነው በማለት በራሳቸው ስሌት ይመነዝሩታል:: እነዚህ ሰዎች ሳይንስን እስከመጀመርያው የሁለነታ መፈጠር ድረስ ይሞግታሉ:: በሁለንታ ውስጥ ያሉ ነገሮች በሙሉ የተገኙት ቢግ ባንግ (Big Bang) ተብሎ በሚጠራ አንድ ድንገተኛ ፍንዳታ የተነሳ ለሚባለው መላምት ይህን ፍንዳታ እንዲካሄድ ያደረገው ማን ነው በማለት ይጠይቁና መልሱን እራሳቸው ፈጣሪ ነው ብለው ይመልሳሉ::የተቀበሉት ሳይንስ ከመጻፍ ቅዱስ ጋር እንዳይጋጭባቸው መጻፍ ቅዱስ ከፈጥረታት አፈጣጠር፣ ከአዳምና ሔዋን ሰብዕና ጀምሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት ታሪኮች ምሳሌዎች ናቸው ሲሉ ይደመጣሉ:: ፈጣሪ ግን የነገረን ቢግ ባንግን እንዳፈነዳው ሳይሆንለህጻን አእምሮ በሚመች ትረታዊ ትረካ በመጀመሪያ ሰማያትንና ምድርን፣ባሕርንና በውስጣቸው ያሉትን ነገሮች ሁሉ በአንድ ሳምንት እንደፈጠረ ከዚያም ባሉበት እንዳፀናቸው ነው::የመፅሀፍ ቅዱሱ አተራረክ ግልፅ ነው ሁሉን ቻይ፣ ሁሉን አዋቂ፣ ወሰን የለሽ የሆነው አምላክ ሁለንታን እና በውስጡ ያሉትን በሽርፍራፊ ሰከንድ መስራት ሲችል ስድስት ቀን ማባከኑ ጥያቄ ቢያስነሳም::

በዶ/ር መ. ኃ. መስቀል በተጻፈው ‘ከምድራዊነታችን ባሻገር’ ሦስተኛ መጽሐፍ ገጽ 16-17 የፍንዳታውን ጉዞ በተመለከተ “በሳይንቲስቱ አልበርት አይነስታይን መላ ምት መሠረት፣ ኃይል ወደ አካል፣ አካልም ወደ ኃይል ይለወጣል:: ይህንን የአይነስታይን መላ ምት መነሻ በማድረግ፣ አካላዊው ጠፈር ከ12 እስከ 15 ቢሊዎን ዓመታት ባለው ጊዜ ውስጥ፣ በታላቁ ፍንዳታ (the Big Bang) ተጀመረ::” እንዴት ለሚሉ ይቀጥላል፦“በታላቁ ፍንዳታ ንድፈ ሃሳብ መሠረት እፍጋታ (density) ወደ ዘለአለማዊነት የሚጠጋ ኃይል ነበረ:: ይህ ኃይል በባዶነት (vacuum) የተከበበ፣ ዙሪያውም እጅግ ቀዝቃዛ ነበር:: ከታላቁ ፍንዳታ በፊት በዚህ ኃይል ውስጥ የታመቀው ሙቀት ዘለአለማዊ (ከግምት በላይ) ነበር::” ይለናል:: በዚህ ሀያል እፍግታ ምንም ቁስ አካል በሌለው ሀይል ውስጥ ምን ይከሰት ነበር?“በውስጡ በተቃራኒ የሚካሄዱ የግፊትና የጉተታ ክስተቶች ነበሩ:: ይህ ኃይል እነዚህን ቅራኔዎች ይዞ

Created in Master PDF Editor

ለዘለአለም መቆየት ስላልቻለ በአንድ የተወሰነ ጊዜ ፈነዳ::ከፍንዳታው በኋላ ወዲያውኑ ዙሪያውን በከበበው ቅዝቃዜ ምክንያት ሙቀት ቀነስ ሲል ቁስ አካል (matter) ተፈጠረ::" የቁስ አካል ከሀይል መፈጠር የአጽናፈ አለምን እንቆቅልሽ ይፈታል:: ሲንጉላሪቲ (singularity) እና ኢቮልሽን (evolution) የሚባሉት ምርምሮች ነብስ የሚዘሩት ከዚህ ጋ ነው::ምናልባት ይላሉ ዶ/ር መ/ኃ መስቀል "ምናልባት በዚህ ቀነስ ባለ ሙቀት ሊኖሩ የሚችሉ እንደ ኢሌክትሮን እና እንደ ኒውትሪኖ ያሉ እጅግ ጥቃቅን ቁስ አካሎች ብቻ ይሆናሉ:: የዚያን ጊዜ ገና ጠፈር አልተዘረጋም፣ ከዋክብት አልተፈጠሩም፤ ሁሉም እጅግ ጥቃቅን ቁስ አካሎች ብቻ ያሉበት እንደ ጥምል ጋስ - ጢስ (nebulae) ያለ ነበር::"

በቢግ ባንግ የመጀመርያዎቹ ሶስት ደቂቃዎች በተለይም የመጀመርያዎቹ ጥቂት ሰከንዶችና አሁን ላለው ማይንድ ብሎውይንግ አጽናፈ አለም ትልቅ ሚና እንደነበራቸው ሳይንቲስቶች ይናገራሉ:: እኔ እንደተረዳሁት በአሁኑ ወቅት በአስትሮኖሚ በተለይም በቲወረቲካል ፊዚክስ ዘርፍ የሚጠኑት ጥናቶችና የሚጻፉት መጽሃፍቶች ስለ ቢግ ባንግን ያስከሰቱት ሀይሎችና የሁይሎቹ ትርምስ በተፈጠረበት ቅጽበት ስለነበረው ሁኔታ ነው:: ጉዳዩን በቤተ ሙከራ ለማረጋገጥም ሳይንቲስቶችበፈረንሳይና በስዊስ መካከል ጀኔቫ አጠገብ በሚገኘው በታሪክ ትልቁ የምርምር ጣቢያ CERN (Conseil Européen pour la Recherche Nucléaire) ላይ ጥረት እያደረጉ ነው:: ይህም ሳይንስ በርካታ ጥያቄዎች እየፈጠረና እየተፈጠረበት ቢሆንም በቀመሩ ውስጥ ግን God የሚባለውን ቃል ገሸሽ እያደረገው ይመስላል:: ድሮ ድሮ ታታሪ የክርስቲያን ፈላስፋዎችና ሳይንቲስቶች ቦንቡን ማን አፈነዳው ሲሉ ነበር፣ አሁን ግን ይህን የሚሉበት ሞራል እየቀነሰ ነው:: ምን አልባት የቅዱሳን መጽሀፍትን ጉዳይ ተወት አድርገው በሳይንስ ውስጥ በጊዜ፣ በርቀት፣ በመሳርያ፣ በገንዘብና በሌሎች ተግዳሮቶች ተመልሰው የማያልቁትን እንቆቅልሾች ይህ የእግዚአብሔር ስራ ነው እያሉ መመጻደቅ ነው:: ደግሞም ያዋጣል::

መፅሃፉ እንደማያዋጣቸው የሚያውቁት የምዕራቡ አለም ሰባኪዎች የክርስቲያን ሳይንስ የሚባል ዘርፍ አቋቁመዋል:: ዋና ተግባራቸውም የሀይማኖታቸውን መፅሃፍ በመደለዝ፣ በመጠምዘዝ ወደ ሳይንስ ማስጠጋት ነው:: አበው ሲተርቱ ይላል በፍቃዱ "አበው ሲተርቱ ‹‹እሾህን በእሾህ›› ይሉ ነበር:: United Church of God የተባለ የመጽሃፍ ቅዱስ አማኒዎች ማሕበርም የሚተገብረው ይህንኑ ነው:: ሳይንስ፣ በተለይም ከ19ኛው ክፍለዘመን ወዲህ ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኘ በመምጣቱ፤ ማሕበሩ ሳይንሳዊእውነታዎችን ይዞ አምልኮተ መጽሃፍ ቅዱስን የሚቃረኑ ድምዳሜዎችን ለመዋጋት መጽሄት በማሳተም ስራ ተጠምዷል::" (የበፍቄ ዓለም፣ https://befeqe.wordpress.com/)

Created in Master PDF Editor

ከክርስቲያኖች ይልቅ ከሳይንስ ጋር ለመወዳጀት ሌት ተቅን የሚጥሩ ሙስሊም ሰባኪዎች አሉ። አንድ የሳይንስ ግኝት ሲገኝ የሚመስል ጥቅስ ፍለጋ ቁርአን ያገላብጣሉ ሲሆን የሚመስል ካልሆንም ለማለት ተፈልጎ ነው በማለት ቁርአኑን ወደ ሳይንስ ያመጡታል። ቁርአን እና ሳይንስን እጅ እና ጓንት ማድረግ የሚፈልጉት በዝግመተ ለውጥ የሚያምኑ ሙስሊሞች ቁርአን ሰማይና ምድር በስድስት ዘመናቶች ተፈጠሩ ሲል በጣም ረዥም በሆነ ዘመን እንደተፈጠሩ ያሳያል ስለዚህ ሳይንቲስቶች ምድርና ሰማይ የተፈጠሩት በዘመናት ነው ለሚለው የቁርአን አባባል ተቃውሞ የለውም ይሉናል።በተለይም በቁርአን ምዕ 21 ቁጥር 30-33 ባለው ትርጓሜ መሰረት ሁለንታ በአንድ ላይ ተጣብቀው አንድ ነጥብ በነበሩ ቁሶች ተለያይተው እንደተፈጠሩ እናም አሁን የምናየውን አለም በሂደት እንዲህ ሊሆን እንደቻለ ያነሳሉ።*"እነዚያም የካዱት <u>ሰማያትና ምድር የተጣበቁ የነበሩና የለያየናቸው</u> መኾናችንን አያውቁምን ሕያው የኾነንም ነገር ሁሉ ከውሃ ፈጠርን። በምድርም ውስጥ በእነሱ እንዳታረገርግ ጋራዎችን አደረግን። ይመሩም ዘንድ በእርሷ ውስጥ ሰፋፊ መንገዶችን አደረግን። ሰማይንም (ከመውደቅ) የተጠበቀ ጣራ አደረግን። እነርሱም ከተዓምራቶቿ ዘንጊዎች ናቸው። እርሱም ሌሊትንና ቀንን፣ ፀሐይንና ጨረቃንም የፈጠረ ነው። ሁሉም በፈለካቸው ውስጥ ይዋኛሉ።"*

በተጨማሪም ስለ መሬት አፈጣጠር ለሁሉም መሪ ሁኖ ለሙስሊሞች በሙሃመድ ላይ የወረደው ቁርአን ምዕ 79 ቁጥር 28-33፦ *"ከፍታዋን አጓነ፤ አስተካከላትም። ሌሊቷንም አጨለመ። ቀንዋንም ገለጸ። <u>ምድርንም ከዚህ በኋላ ዘረጋት።</u> ውሃዋንና ግጦሿን ከእርሷ አወጣ። <u>ጋራዎችንም አደላደላቸው።</u> ለእናንተና ለእንስሶቻችሁ መጣቀሚያ ይኾን ዘንድ ይህን አደረገ።"*

ከዛሬ 1400 ዓመታት በፊት በበረሃማው የአረብያ ምድር የወረደው ቁርአን ሳይንሳዊ እውነቶችን ሊይዝ የቻለው የአምላክ ቃል ስለሆነ ይባላል። በቁርአን እና በቢግ ባንግ (Big Bang) ፅንስ ሀሳብ መካከል ያለው መስማማት ደስ የሚያሰኝ ቢሆንም ችግሩ ሳይንቲስቶች ጥረው ግረው ያገኙትን እውነት እኛ ከ1400 አመት በፊት እናውቀዋለን ማለት የግኝት መብትን ይጋፋል።መጽሐፍተ ቅዱሳትና የዝግመተ ለውጥ ጽንሰ ሐሳብ ሊስማሙ ይችላሉ የሚሉት የሃይማኖታቸውን እድሜ ለማስረዘም ካልሆነ በስተቀር ሌላ ትርፍ አያገኙም። ቁርአኑም በቀጥታ ስለ ሳይንሳዊ ግኝቶች አያወራም ለማለት ተፈልጎ ነው ብለን ካልተረጎምነው በስተቀር። ቁርዓን መተርጎም ያለበት በቀጥታ እንደሆነ ብዙዎች ይናገሩራሉ። "እውነታው ግልፅ ነው! አላህ ለራሱ በቁርኣኑ ወይም በመልዕክተኛው አንደበት ያፀደቀውን ሁሉ <u>ያለ ማመሳሰልና ያለ ትርጉም ማጣመም እንቀበላለን፤</u> ለርሱ ልቅና በሚገባ መልኩ የባህሪያቱን ጥቅል መልዕክት እናረጋግጣለን። ይህ ነው የነብያትና የተከታዮቻቸው ጎዳና! <u>ይህ ነው ውዝግብን የሚፈታው ቀላሉ የመፍትሄ አካሄድ!</u>" (የአማኞች ጋሻ፣ ገፅ 281)

Created in Master PDF Editor

አንዳንዶቹ ደግሞ በሳይንስ ድክመቶች የሚጨፍሩ እና በሳይንስ ቲወሪዎች መካከል ባለው ልዩነት የራሳቸውን እንጀራ የሚያበስሉ ናቸው:: ለምሳሌ አብዛኛው የሳይንሱ አለም ሙህራን በዝግመተ ለውጥ ቢያምኑም በሂደቱ ላይ ግን ያልተፈቱ እንቆቅልሾች አሉ:: ከዚህ ተነስተው ሕይወት ያላቸው ነገሮች በሙሉ ከአንድ አካል እየተሻሻሉ አልመጡም ይላሉ፣ በሳይንስም ይዘባበታሉ::

> *"የዝግመታዊ ለውጥ ሳይንሳዊ ሐይማኖት ሕይወት ያለው ነገር ሁሉ በዝግመታዊ ለውጥ ሂደት ተገኝቷል ብሎ ያምናል፤ ይህ ማለት አሁን በምንኖርበት አለምም ጭምር በዚ የለውጥ ሂደት ላይ የሚገኙ ሕይወት ያላቸው ነገሮች አሉ ማለት ነው:: አልያም ቅሪታቸውን ማግኘት እጅግ ቀላል ይሆን ነበር ማለት ነው:: ለምሳሌ:- የሰው ልጅ ለሱ የቅርብ "ዘመድ" ከሆነው ጦጣ ነው ኢቮልቭ ያደረገው:: እንግዲህ እንዲህ የሚሉት የዚህ "ሳይንሳዊ" ሃይማኖት አራማጆች (የዝግመታዊ ለውጥ ፋናወጊዎች) የጦጣነት ዘመናቸውን አጠናቀው ሰው መሆን የቻሉ እድለኞች ናቸው ብለን ብናስብ፣ በመላምቱ መሰረት እነሱ ወደደረሱበት የሰውነት ደረጃ ለመድረስ እድሜ ያላደላቸው <u>በሰውና በጦጣ ዝርያ መካከል</u> የሚገኙ ሰው መሰል ጦጣዎች (ከፊል ሰው ከፊል ጦጣ) በአሁኑ ሰአት በአለማችን በብዛት መገኘት ነበረባቸው:: ሆኖም እነዚህ ከፊል አንዱን ከፊል ደግሞ ሌላውን የሚመስሉ እንስሳት ይህ የዝግመታዊ ለውጥ ሃይማኖት ከተጠነሰሰበት ወቅት ጀምሮ አልታዩም፤ ከዛም በፊት የሉም:: በቅሬተ አካል ምርምር ውስጥ እስከ አሁን ድረስ አንድም ይህንን የሂደት ቅርፅ ክፍተት ሊያስረዳላቸው የሚችል ማስረጃ በቅሬታ አካል ሬከርድ ውስጥ ማግኘት አልቻሉም:: ምንም ተጨባጭ ማስረጃ የለም::"* (ወንጌል በድረ-ገፅ አገልግሎት፣ እውን እግዚአብሔር አለ?)

ሰባኪዎች በድፍረት በቅሬተ አካል ምርምር ውስጥ እስከ አሁን ድረስ አንድም ኢቮሉሽንን ሊያስረዳ የሚችል ማስረጃ በቅሬታ አካል ሬከርድ ውስጥ አልተገኘም ከተገኘም የተጭበረበረና የማስመሰል ስራ የተሰራባት ነው ይላሉ:: ---"Creationists to simultaneously draw on the authority of science and attack the basic workings of science. Science constantly builds upon the ideas of the past, and it is cumulative toward the future. Scientists do make mistakes aplenty and, in fact, this is how science progresses. The self-correcting feature of the scientific method is one of its most beautiful features. Hoaxes like Piltdown Man and honest mistakes like Hesperopithecus are, in time, <u>exposed.</u> Science picks itself up, shakes itself off, and moves on." (Why people believe weird things, pp153)

ዝግመተ ለውጥ መጥፎ አመለካከት መሆኑን ለማስረዳት ያልተፈነቀቀለ ድንጋይ የለም:: ዝግመተ ለውጥ ከጅምሩ ፅንሰ ሃሳቡ በዳርዊን መልክ መያዝ ሲጀምር ጀምሮ በትችና በተቀመሞ የተሞላ ነው:: በወቅቱ ዝግመተ ለውጥ መቀለጃና የኮመዲ ርዕስ

Created in Master PDF Editor

ሆኖ ነበር፡፡ ዛሬም እጅግ አማኝ ከሆኑ የሃይማኖት መሪዎች እስከ አንዳንድ ሳይንቲስቶች የዝግመተ ለውጥ እሳቤ ይተቻል፡፡ በእኛም ሀገር አቢጊዳን አጥንቶ ካልጨረሰው የ10 ዓመት ልጅ እስከ ተማሩት ሊቃውንት ድረስ ዝግመተ ለውጥ ይተቻል፡፡ እነ መ/ር ዶ/ር ዘበነ ለማ ሳይንስን በተለይም የዝግመተ ለውጥ አሻራ ያረፈባቸውን የሳይንስ ዘርፎች በማንቋሸሽ መፅሀፍ አሳትመዋል፤ ገናም እንደሚያሳትሙ ቃል ገብተዋል፡፡ እነ መ/ር ዶ/ር ሮዳስ ታደሰ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ቀርፀው ሃሳቡን ይወርፋሉ፣ የሚመስሏቸውን እንግዶች ብቻ እየጋበዙ ያስወርፋሉ፡፡ አንድንዶችም ዝግመተ ለውጣዊ አሳተሳሰቦች ከስርዓተ ትምህርቱ እንደወጡ ይጎተጉታሉ፡፡ ይህ ሁሉ አዲስ ነገር አይደለም ፍርሀት ነው፡፡ ለትውልድ የእውነትን መንገድ ለማጥበብ መጣጣር ነው፡፡ ዝግመተ ለውጥ መተቸቱ መልካም ነገር ነው ሰው ስለሚተቸው ነገር ማወቅ በራሱ ትልቅ ድል ነው፡፡

በግሌ ዝግመተ ለውጥ በእየ ቤተ እምነቱን በእየ መገናኛ ብዙኂን ሲተች ስሰማ እጅግ ደስ ይለኛል፡፡ ፅንሰ ሃሳቡ መተቸት ሲጀመር ስለሚተቸው ነገር ማወቅ የሚፈልጉ ሙህራን ይወለዳሉ፡፡ ከዚያም የሚባልለትና የሆነው ተቃርኖ ሲያገኙት ከጎኑ ይቆማሉ፡፡ እኔ ዝግመተ ለውጥ የሚተችበት መፅሀፍና ሚዲያ የምፈልገው ፅንሰ ሀሳቡ ምን ያህል ተፅንኖ እንዳደረሰና የሰባኪዎች ስጋት የት ደረጃ እንደደረሰ ለማወቅ ነው፡፡

እመኑኝ ከጥቂት አመታት በኂላ ቄሶች ስለ ዝግመተ ለውጥ ይመስክራሉ፡፡ በአውሮፓና በሌሎች በአደጉት ሀገራት የሆነው ይህ ነው፡፡ እስከ ቫቲካኖቹ ጳጳሳት ድረስ በዝግመተ ለውጥ ሃሳብ እንደተማረኩና እንደሚቀበሉትም መስክረዋል፡፡ በእኛም ሀገር ጳጳሳት ዛሬ በልባቸው ነገ በቃላቸው ሊመሰክሩት እንደሚችሉ ባለ ሙሉ ተስፋ ነኝ፡፡ መቸም በሳይንስና በስነ መለኮት እውቀት ያለው ሰው ሁለንታ የተፈጠረው መ/ር ዘበነ እንዳሉት የዛሬ 7511 ዓመት ነው ብሎ ለማስብ ይከብዳል፡፡ ሄዋን የሉሲ እናት ናት እንደማለት የሚያስቅ ቀልድ አለ፡፡ የቀደምት ስልጣኔዎች የተኮረጀውን የኖህ መርከብ ትርክትንም አሜን ለማለት ልቦና አይፈቅድም፡፡ እባቡ፣ የአዳምና የሄዋን ንግግር ምናባዊ መሆኑንና ሌሎች ይህን ተከትሎ የመጡ ትርክቶችም ልብ ወለድ ድርሰቶች መሆናቸውን የመርዳት ዝንባሌ ጨምሯል፡፡ አሁን አሁን ሰባኪው ከሃይማኖቱ ሳይወጣ ከኢቮሉሽን በመዋሃድ የጥርጣሬውን ዋዜማ ይመሰክራል፡፡

ዛሬ ቁጥር ቀላል የማይባል የአለም እማኖች ዝግመተ ለውጥን እንደ እውነተኛ ሀሳብ ተቀብለውታል፡፡ ቤተ ክርስቲያናትና መስጊዶችም የድጋፍ መግለጫ መስጠት ከጀመሩ ሰነባብቷል፡፡ ብዙዎች እምነታቸው ከሃይማኖታቸው እንዳይጋጭ እውነት እና እውነት አይጋጩም ይላሉ፡፡ የሚገርመው የዚህ መግለጫ ጥንታዊ ታሪኩ ቢታይ በከፋ ተቃውሞ ነበር፡፡

Created in Master PDF Editor

ወደ ተችዎች መሰረታዊ ተቃውሞ ስመለስ ዝግመተ ለውጥ ትክክል እንዳልሆነ በለውጡ ውስጥ በመረጃ እጥረት ያልተደረሰባቸውን ሚስንግ ሊንኮች (missing links) መጥቀስ የተለመደ ትምህርታቸው ነው።የሰው ልጆች የመጡት ከእንስሳት ለምሳሌ ያህል እንደ ዝንጀሮ እና ጦጣ መሰል እንስሳት በዝግመተ ለውጥ ተሻሽለው ከሆነ በሰዎች እና በእንሰሳቱ የማሰብ ችሎታ መካከል ይህን ያህል ልዩነት ሊኖር የቻለው እንዴት ነው በማለት አግባብነት ያለው ጥያቄ ይጠይቃሉ። ጥያቄው የሚነሳው አለም 7,000 አመት እድሜ ያላት ናት ብሎ ከሚያስብ ሰው ከሆነ ትክክል ይመስላል ምክንያቱንም በሰባት ሽህ አመት ጦጣ መሰል ወደ ሰውነት ሊያድግ አይችልምና። ቢሆንም የሁለንታ እድሜ 14 ቢሊዮን አመት አካባቢ ስለሆነ ምንም ነገር ወደ ማይመስለው ሊቀየር ይችላል።

“በመጀመሪያ አንድ ህዋስ ያላቸው ባክቴሪያና አልጌ መሰል ፍጥረታት ተገኙ፤ ከዚያም በዙ ህዋስ ወዳላቸው ነፍሳት አደጉ፤ ቀስ በቀስም አካላቸው ውስብስብ እንቅስቃሴና ቅርፃ ያላቸው ግዙፍ እንስሳትና አትክልቶች በሂደት ተፈጠሩ። በአሁኑ ጊዜ የምናያቸው ጥቃቅን ነፍሳት፣ ግዙፍ ዛፎች፣ እንስሳትና 120 ትሪሊዮን የኒውትሮኖች ግንኙነት ያለው የሰው ጭንቅላት የተፈጠሩትን በንጥረ ነገሮች ላይ የተከሰተው ህይወት አስገኝ ውህደትና የአራት ቢሊየን አመታትን ያስቆጠረ የእድገትና የለወጥ ሂደት ውጤት ነው።” (የህይወት ትርጉም፣ 2002 ዓ.ም፣ 108)

ሳይንስ በእየሰከንዱ እራሱን በማሻሻል የተፈጥሮ አዳጋዎችን ምክንያት ከማወቁም በላይ አዳጋዎችን በመተንበይ የሰው ልጅ እራሱን እንዲጠብቅ እየተደረገ ነው። በእርግጥ የተፈጥሮ አደጋዎች የሚደርሱት ተፈጥሮአዊ በሆነ እና የሰው ልጅ ተፈጥሮን በማዛባቱ ምክንያት ነው። ሳይንስ እረፍት አይሰጥም ምክንያቱም ሳይንስ ስራው ጥያቄዎችን ከመመለስ ይልቅ ጥያቄዎችን መጠየቅ ነው። የሳይንስ ጥያቄዎች መጠየቅ ካቆሙ የሳይንስ ግኘት የሚባል አይኖርም ሁሉም ባለበት ይቆማል። ሀይማኖት ግን ከመጠየቅ ይልቅ ሳይጠየቅም ቢሆን መመለስ ይውዳል። መመለሱ ባልከፋ ችግሩ ምላሹ የተዘበራረቀ መሆኑ ነው። በጣም የሚገርመው ደግሞ ሳይንስን ጥላሸት ለመቀባትና የሀይማኖታቸውን ጉድና ጉድጓድ በሳይንስ ድክመት ሊሸፍኑ የሚሞክሩ መኖራቸው ነው።

በቅርቡ መ/ር ዶ/ር ዘበነ ለማ ሰው ምንድን ነው የሚል መጽሃፍ አሳትመዋል። መጽሃፉ በአንድ አመት ብቻ ለ6ኛ ጊዜ ታትሟል። መ/ር ዶ/ር ዘበነ ለማ የሰውን ማንነት ለመረዳት በምናባቸው በሦስት ተራራዎች (ሳይንስ፣ ፍልስፍና እና ሀይማኖት) የሚኖሩ ሰዎችን አስተሳሰብ ቃኝተዋል። ሳይንሱን ከጅምሩ የሚወርፉት መ/ር ዶ/ር ዘበነ ለማ “ሳይንስ ለአለም የማውቅላት እኔ ነኝ ካለ ሰንብቷል። ሌሎች የሚመክሩትንም አይሰማም። ለዚህ ትልቁ ችግሩ ሚስቱ ትሁን ባለቤቱ ባላውቅም፣

Created in Master PDF Editor

ይህን ሁሉ የምታደርገው ገንዘብ ናት::" ሲሉ ይሳለቃሉ:: መ/ር ዶ/ር ዘበነ ለማ ሳይንስን ከሀይማኖት ጋር ሊታሰብ የማይገባው ኢምንት የማይረባ ነገር እንደሆነ ይልቅም በእየዘርፉ 'ሎጅ' የሚል ቃል የተጨመረበት ሁሉ እንደሚያናድዳቸው በመጽሃፉ አብራርተውታል:: በሀገር ውስጥም በውጭም ስለ ሳይንስ መጥፎ እይታ ያላቸው የተማሩ ሰዎች እንዳሉ አውቃለሁ የመ/ር ዶ/ር ዘበነ ለማ ጥላቻ ግን ይለያል:: ዶ/ር ዘበነ ማወቅ ያለባቸው አንድ ነገር ቢኖር ሙሉ ህይወታቸው በሳይንስ ውጤቶችና ትሩፋቶች የተመሰረተ መሆኑ ነው:: ከኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ ሲሄዱ በተክልየ ክንፍ ነው እንዴ የበረሩት? መ/ር ዶ/ር ዘበነ ለማ በእውቀት ቢያንስ በዱክትርና ይበልጡኛል በእውነት እንደምበልጣቸው ግን እርግጠኛ ነኝ:: እኒህ ጸረ-ሳይንስ ሰው የሰውን ውስብስብ ማንነት ከሳይንስ በተሻለ ፍልስፍና ባይመልሰውም ሊሞክረው ይችላል ይላሉ:: እንደማስረጃም በምናባቸው ስለነፍስ መኖር ከሚያስተምሩ ጋር ውይይት ያደርጋሉ:: ቢሆንም በፍልስፍና ዘርፍ ያለው ሁሌ የመጠየቅ ዘይቤ ስለስለቻቸው፣ እግዚአብሔር ሞቷል እስከማለት የደረሱ ፈላስፋዎች ስላጋጠሟቸውና ድንጋጤ የሚጭሩ የፍሮይድን ትንታኔ በመስማታቸው ዶ/ር ዘበነ ለማ ወደ እውነተኛው ተራራ ወደ ሀይማኖት ሄዱ የሰውን ማንነት ፍለጋ::መ/ር ዶ/ር ዘበነ ለማ በምናባቸው እንዲህ ያስባሉ፦ "ስለ ሰው ማንነት እውነቱን እዚህ ይነግሩኃል:: ሀሰት የተባለ ከቶ በነሱ ቤት የለም:: ስለ ሰው ማንነት በዚህ ተራራ ያሉ ሁሉም ሊነግሩህ ይችላሉ:: የሁሉም ሀሳብ አንድ አይነት ነው:: እንደነዚያ የሁለቱ ተራራ ነዋሪዎች (ሳይንስና ፍልስፍና) የተዘበራረቀ አይደለም:: ሁሉም በአንድ ሀሳብ ይስማማሉ፣ የሚጠጡት ከአንድ ምንጭ ነው:: ሁሉም ቃላቸው አንድ ነው:: በዚህ ቅዱስ ተራራ ሆነህ ሌሎች ተራራዎችና ኮረብቶች እንደትቢያ እንኳን ለመታየት አቅም ያንሳቸዋል:: በፍልስፍና ሆነህ ሳይንስ ጠጠር እንደሆነብህ በቅዱሱ ተራራ ስትኖር ድግሞ ሁለቱም እንደጠብታ ውሃ እንኳን መሆን አይችሉም::"(ምንትኑ ውእቱ ሰብእ፣ ገጽ 11-27፣ 6ኛ እትም)መ/ር ዘበነ ይህን ህልም ያዩት በየትኛው የእንቅልፍ ደረጃ ላይ ሁነው እንደሆነ አላውቅም:: ነገር ግን በእውናቸው እንዲህ የውሸትና የጉራ ማዕት ሊታሰባቸው አይችልም:: ቢያንስ ቢያንስ በሀይማኖት ተራራ የሁሉም ሀሳብ አንድ አይነት ነው አይሉም ነበር:: ዶ/ር እንዲያው በፈጣሪ በሳይንስ ዘርፎች መካከል ከሚነሳው መጠነኛ ልዩነት አንጻር በ100,000 አማልዕክት ያለው ልዩነትና ውግዘት እንዴት ተረሳወት? ይቅርታ ለካ በእንቅልፍ ልብዎ ነው፣ ሲነቁ ጊዜ በሰፊው እንወያያለን፣ እድሜና ጤና ይስጠን::

ሳይንስና ፍልስፍና ከሀይማኖት የተሻለ ታሪካዊና ነባራዊ ጥቅም ያላቸው ዘርፎች ናቸው:: ሳይንስና ፍልስፍና የሚሰጡን ጥቅሞች ውስጥ ምክንያታዊነትን እንድናዳብር፣ ስነ ምግባር እንዲኖረን፣ ከዕውቀት ማዕድ እንድንቋደስ፣ በተፈጥሮ ለመዝናናትና ለመዳሰት፣ ታላላቅ ስኬቶችንና ግኝቶችን እንድንጎናጸፍ፣ ማንነታችንና

Created in Master PDF Editor

አፈጣጠራችንን እንድናውቅ፣ የተሻለ ደስተኛ ህይወት እንድንኖር፣ ስህተቶችን እንድናውቅ፣ ታሪክን እንድንረዳና አለምን ሁሌም የተሻለች ምቹ እንድናደርጋት ያግዙናል የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በሳይንስና በፍልስፍና የተገራ ማህበረሰብ ዝግ አዕምሮ አይኖረውም፣ ዶክማቲክ፣ አክራሪና አሸባሪ አይሆንም፡፡ የተሻለ ውብ የአኗኗር ዘይቤን ይከተላል፡፡ ለውሳኔ አይቸኩልም፡፡ ለውስጣዊ ግፊት እንጅ ለውጫዊ ግፊት ተገዥ አይደለም፡፡ ጦር ለመማዘዝ፣ ቦንብ ለመጥመድና ሁሉን አጥፍቶ ጠላቴ የሚላቸውን ወንድሞቹን ለማጥፋት አይቸኩልም፡፡ ማንም አካል ሊሳሳት እንደሚችል ያምናል፡፡ ለለውጥና ለንስሃ ዝግጁ ነው፡፡ ለሁለት መንግስት ስለማይገዛ ለማን መገዛትና እንዴት ስርዓት መያዝ እንዳለበት ያውቃል፡፡ ለሁለት መንግስት የማይገብር ማህበረሰብ ደግሞ ጫናው ይቀልለታል፡፡ ሁለቱ መንግስታት ከሚፈጥሩት ሽኩቻም ነፃ ይሆናል፡፡ በወንጌል እንደተባለው ለሁለት መንግስት መገዛት አይቻልም፡፡

ሳይንስ በተለይም የዝግመተ ለውጥ አስተሳሰብን አምረው የሚተቹት የሀገራችን ሰባኪዎች ሳይንስ የጋረጠብን ስጋት ታይቷቸው ከሆነ መልካም ነው፡፡ ነገር ግን ሀይማኖታቸው ስለተነካ ከሆነ ትዝብት ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን ማንኛውም ሀሳብ ሀይማኖታዊም ይሆን ሳይንሳዊ፣ ልብ ወለዳዊ ይሁን እውናዊ፣ ፖለቲካዊም ይሁን ማህበራዊ ለድጋፍና ለትችት መጋበዝ አለበት፡፡ በሳይንስ ላይ የስድብ ናዳ እያወረዱ የሁሉ ነገር መሰረት የሆነውን ሀይማኖቴን አትተች ማለት ከየትኛው ክፍለ ዘመን የማይጠበቅ ጅልነት ነው፡፡ በሰለጠነ መንገድ መከራከር አለብን ጉዳዩ ምንም ይሁን ምንም፡፡ ብዙ ጊዜ አክራሪ ሰዎች የውስብስብነት ምንጭና መፍትሄ ናቸው ስለሚባሉት አማልዕክት ተቃውሞ የሚያነሳን ሰው እንደሰየጠነ ይቆጥሩታል በጭራሽ አይደለም፡፡ የውስብስብነት ቁልፉ ዝግመተ ለውጥ እንደሆነ ያወቀም የጥንቱን አስተሳሰብ መጠየፍ የለበትም፡፡ በአሮጌው ላይ አዲስ ጨርቅ ጥፎ መልበስ ተገቢና አስፈላጊ ነው፡፡ የተቀደደውን አሮጌ ልብስ አውልቆ ራቁትን መሄድ ግን እብደት መሆኑን ማንም ያውቃል፣ ካበዱት በስተቀር የተቀደደን ልብስ ለመቀየር ወይ መጣፍ አለብን ወይ አዲስ መግዛት አለብን፡፡

የተቀደደ ልብስ ከመልበስ ጠጋግኖ ጥፎ መልበስ ይሻላል፡፡ ከተቻለ ደግሞ አዲስ ልብስ መልበስን የመሰለ የለም፡፡ እንደኔ አረዳድ ሀይማኖት ያረጀ የተቀደደ አስተሳሰብ ነው ለዚህ መፍትሄው አንደኛ የክርስቲያን ሳይንስ ተከታዮች እንደሚያደርጉት የሀይማኖትን ቀዳዳ በሳይንስ መጣፍ ነው፡፡ ሁተለኛው መቀየር ነውበዝግመታዊ ለውጥ ሳይንስ፡፡ ሁሉም የሳይንስ ዘርፎች ዝግመታዊ ለውጥን የሚደግፉ ናቸው፡፡ ዝግመታዊ ለውጥን ከአሮጌው ሀይማኖት የሚለየው በየትኛውም ሀገር በልዩ ልዩ ቋንቋ፣ በልዩ ልዩ እምነቶችና ባህሎች ውስጥ ሁነው ሰዎች የሚመሰክሩለት መሆኑ ነው፡፡ በአንድ ትልቅ ቤተ መፅሐፍት ያሉ የተለያዩ የጥናት ዘርፎችን፣ መማሪያና

Created in Master PDF Editor

አጋዥ መፅሀፍትን የመጀመሪያ ምዕራፍ ብታዩ የሚጀምሩትየዘርፉን ዝግመታዊ ለውጥን በመዳሰስ ነው፡፡

ብዙዎቹ የማህበራዊ ይሁን የተፈጥሮ ሳይንስ መፅሀፍት የዳርዊንን ስም ሳይጠሩ ማለፍ አይቻላቸውም፡፡ ወዳው ሳይሆን አማራጭ ስለሌላቸው ነው፡፡ በአካዳሚው አለም ስራውን ከጠቃሳችሁ የስራውን ባለቤት መጥቀስ እንደግዴታ ስለሆነ ነው፡፡ ለመሆኑ ዝግመተ ለውጥ ለክርክር የሚበቃ ምን እውነት አለው? ውስብስብ ስለሆነው ተፈጥሮስ መልስ ይኖረው ይሆን? እንዲህ ከደቂቅ እስከ ረቂቅ የሚወዛግበው የዳርዊን ቲወሪ ምን ፋይዳ አለው? ዝግመተ ለውጥን ለመደገፍም ሆነ ለመቃወም ስለ አስተሳሰቡ ማወቅ አለብን፡፡ ደርሶ ዘራፍ ማለት ወይም ፊደል ሳንቆጥር በሰሚ ሰሚ ጉዳዩን ማጣጣል ስለማይገባ መመርመር አለብን፡፡ በተለያዩ የአለም ሀገራት በተለያዩ የሳይንስ ዘርፎች የሚገኙ ሙህራን እንዳረጋገጡት ዝግመተ ለውጥ ክፍተቶች ቢኖሩበትም የማይካድ ሀቅ ነው፡፡ ሳይንቲስቶች እውነትነቱን ስለመሰከሩ ይልቁም ጳጳሳት እውነት ከእውነት ጋር አይጋጭም ስላሉ አይደለም የዝግመተ ለውጥ እውነታ ከሰው ልጅ መመራመር በፊትም ነበር፡፡ ዳርዊን ወይም ዳውኪንስ ዝግመተ ለውጥን አልፈጠሩትም ተነተኑት እንጂ፡፡ በዋናነት የዝግመተ ለውጥን ሀሳብ የሚያጠናክሩት የቅሬታ አካል(Fossil) እና የጀነቲክስ (Genetic) ማስረጃዎች ናቸው፡፡

የአማኞችን ቀልብ ለመግዛት ፖለቲከኞች በአሜሪካ የፕሬዘዳንት ምርጫ ድርስ ዝግመተ ለውጥ ሀጢአት ነው ቢሉም በእየ መዛግብቱ የተደረደሩት ማስረጃዎች ግን እውነቱን ያሳብቃሉ፡፡ ፖለቲከኞች በዝግመተ ለውጥ ጥናት የሚያደርጉና ዝግመተ ለውጥን የሚቀበሉ እንደ ዜጋ አይቆጠሩም ቢሊም በአለም የሣይንስ ማህበረሰብ ውስጥ ግን ዝግመተ ለውጥ የማያወላዳ እውነት ነው፡፡ Evolution is real የሚያሳዝነው ደግሞ አማኝ ፖለቲከኞችና ሀብታም ቤተክርስቲያናት ረብጣ ገንዘብ መድበው ዝግመተ ለውጥና ለማጥፋት ካልቻሉ ከሚያምኑት ጋር ለማዋሀድ ጥረት እያደረጉ ነው፡፡ ዝግመተ ለውጥን ደግፈንም ተቃውመንም በንጮህ የተፈጥሮን ህግ አንሸርም፡፡ ነገር ግን የዝግመተ ለውጥን ሀቅ መካድ ለተፈጥሮ ያለንን ዝንባሌ ያዛባዋል፡፡ ለአየር ንብረትና ለተፈጥሮ ጥናት የምናውለውን ገንዘብ፣ የሰው ሀይልና በተለይም ሞራል ይጎዳል፡፡

ብዙ ሰባኪዎች ዝግመተ ለውጥ ሰው መጥፎ እንዲሆን ያደርጋል ይላሉ፡፡ ይህ መሰረተ ቢስ መከራከሪያ ነው፡፡ ዝግመተ ለውጥን የሚቀበሉት ከሚቃወሙት የበለጠ ወንጀለኞች አይደሉም፣ ይልቅ በተቃራኒው ነው፡፡ ሀይማኖቶች አሉን የሚሏቸው መልካም እሴቶች በሙሉ በዝግመት ከሚያምኑት ይገኛሉ፡፡ ደስ የሚለው የሀይማኖቶቹ መልካም እሴቶች በደንብ ተብራርተውና ተሻሽለው ይሰበካሉ፡፡ በጌታ ልለምናችሁ በዝግመት የሚያምን በዝግመት የማያምንን በጀምላ ሲገደል

Created in Master PDF Editor

አይታችኋልን? በዜናዎችስ እገሌ የተባለ የዝግመተ ለውጥ አራማጅ ዝግመተ ለውጥን ካልተቀበላችሁ በማለት አስረ፣ ገደለ፣ አሳደደ፣ መዘበረ፣ አጥፍቶ ጠፋ የሚል ስምታችኋልን? እዚህ ላይ አንድ ሀሳብ ይሰንዘራል የኮሚኒስቶቹ ጉዳይ። የማርኪዝም ፍልስፍና ዝግመታዊ ለውጥን ይቀበላል፣ ፅንሰ ሀሳቡን የተቀበሉት አንዳንድ ኮሚኒስት ሀገራት ግን ማርክስ ሀይማኖት ቢጠፋ መልካም ነው ያለውን ሀይማኖቶኞች መጥፋት አለባቸው እንዳለ በሚያስብል አተረጓጎም ተረድተውታል። እነዚህ ጥቂት የኮሚኒስት አምባገነኖች ኮሚኒስትነትን አመለኩት እንጅ ሀይማኖትን ካለበት ፈቀቅ አላደረጉትም።

ይልቅስ ሰዎች ዝግመታዊ ለውጥ አስተሳሰብን ከኮሚኒስት አምባገነኖች ጋር በማያያዛቸው የትርጉም መፋለስ ተፈጥሯል። በሀገራችንም በደርግ የሆነውን በማሰብ ኮሚኒስት አምላክ የለሽ ነው። አምላክ የለሽም ኪሚኒስት ነው የሚል የተዛበ አስተሳሰብ እንዲራመድ ሁኗል። ዝግመተ ለውጥን ከኮሚኒስት ሀገራት ይልቅ ካፒታሊስት ሀገራት ተጠቅመውበታል። ስለዚህ ሲጀመር ዝግመተ ለውጥ የሰውን እና የተፈጥሮን ምንነት የመረዳት ሂደት ስለሆነ ወደ ወንጀል አይገፋም እንዲያውም የተሻልን ልበ ሰፊ እንድንሆን ያደርገናል። በሳይንስና ፍልስፍና የአለም ብርሃን የሆኑ ባለታሪኮች የዝግመተ ለውጥን እውነት የተቀበሉ ናቸው። በስነ ጽሁፍ በሙዚቃ በትምህርት በተለይም በሳይንስና ቴክኖሎጅ አለምና የላቀ ደረጃ ያደረሷት ዝግመትን የተረዱና የገባቸው ናቸው። ምን አልባት በይፋ ኤቲስት ሳይሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ የሳይንስ አለም ጊያንቶች ዳርዊን፣ አንስታየን፣ ጋሊሊዮ እና ኒውተን በዝግመተ ለውጥ የሚያምኑ እንጅ በይፋ ኢ-አማኞች አልነበሩም። ያ ማለት ግን አማኝ ሰባኪዎች እንደሚያራግቡት አማኞችም አልነበሩም። ከእውነትም ከማህበርሰቡም ሳይለቁ በራሳቸው አለም ነው የኖሩት።

በአንድ ወቅት የፊዚክሱ ሊቅ አንስታየን በአማልዕክት ላይ ትችት መሰል ንግግር በማድረጉ ወደ ጀርመን እንዲመለስ ከሰልፍ ያልተናነሰ ተቃውሞ ደርሶበታል። ብዙ ሊህቃን በአብዛኛው ህዝብ ላለመንቀፍ ሲሉ እመነታቸውን ይደብቃሉ ወይም ያስመስላሉ። ታላቁ ሳይንቲስት እስተፊን ሀውከንግ ለብዙ ዘመናት በሚያምን ሰብእና ሲታይ ቆይቶ የስንብቱ ቀናት ሲደርሱ እግዚአብሔር የለም የሚለውን መግለጫውን አሰማ። በሞቱ ማግስትም "Brief Answers To The Big Questions" የሚል በራስ መተማመን የተሞላ መጽሀፍ ጽፎ ለዘለአለሙ ተኛ። ይህን የመምሰል ታሪክ ከጥንት ጀምሮ ታላላቅ ፈላስፎችና ሳይንቲስቶች ሲያደርጉት ኑረዋል። በኢትዮጵያ እንኳ ፈላስፋው ዘርዓ ያዕቆብ አንፀባርቆታል። እኔ እንኳ ከዚህ ልምድ በመነሳት ሀይማኖታዊ አቋሜን ከጥቂት ሰዎች ውጭ ለማንም አላካፍልም። ኢየሱስ ክርስቶስ ለውሾች አትስጡ ያለውን አልረሳም። መልሰው ስለሀሳቡ የሚረግጡኝ አሉና።

Created in Master PDF Editor

የምታስቡትን ነገር ሁሉ የምትናገሩት ከሆነ ልዩ ጥበቃ ያስፈልጋችኋል፡፡ ሃሳብን ሳይሆን ሰውን ለማሳደድ ቆርጠው የተነሱ ዱርየዎች በእየቦታው አሉ፡፡ ቀስ በቀስ እስኪሰለጥኑ ድረስ መታገስ አለብን፡፡ ይህን እምለው እኔ አይደለሁም የኢትዮጵያን የHuman index መረጃዎችን አገላብጡ፡፡ በድህንነትና በኑሮ ምቾት ከአለም ሀገራት በ160ዎቹ ውስጥ ነን፡፡ የምንበልጣቸው ሀገር በእርስ በእርስ ጦርነት ያሉትን ብቻ ነው፡፡ ይህን የሚያሳዝና ታሪክ ለማጥፋት በመንግስት በህዝብ እንዲሁም በተቋማት የሚደረጉትን ውይይቶችና ሙከራዎች አደንቃለሁ፡፡ የተቻለኝንም ለማድረግ ቁርጠኛ ነኝ፡፡ ሀገሬን በወሬና በስም ሳይሆን በተግባር እቆምላታለሁ፡፡ በተለይ ምክንያታዊነት እና ሳይንስ እንዲያብቡ ጥረቴን እቀጥላለሁ፡፡ ለማሳመን ቢከብድም የዝግመተ ለውጥን እውነታ ለማስረዳት እሞክራለሁ፡፡ የተቆለፈበት ቁልፍ መፍቻው ዝግመተ ለውጥ ነውና፡፡

ደስ የሚለው ዝግመተ ለውጥ እንደ እስትሪንግ ቲወሪ (string theory) ወይም እንደ ካልኩለስ (calculus) ወይም እንደ ኳንተም ፊዚክስ ለመረዳትና ለማስረዳት ከባድ አይደለም፡፡ ዝግመተ ለውጥ የሚጠናው "How life changes over the time" የሚለውን በአንፃራዊነት ቀለል ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ የሰው ልጅ ታሪክ ከዋሻ ጀምሮ ሜትሮፖሊታን ከተሞችን እስከገነባበት ያለውን በመረጃ የተሰናዳ እውነታን በመመርመር ብቻ እንኳ ወደ ዝግመታዊ ለውጥ ያደላ ውጤት ላይ እንደርሳለን፡፡ ጀነቲክሙቸሽን (genetic mutation) እና ተፈጥሮአዊ ምርጦሽ (Natural Selection) የሚባሉትን የለውጥ ሂደቶች ስናጠና እንዲሁም ታሪክን በማስተዋል ስለዝግመተ ለውጥ ብዙ እንረዳለን፡፡ ዋናው ነገር ግን ቅን ልቦና ነው፡፡ ቅን ልብ የለለው ኤቴስት እግዚአብሔር ጨርቃ ላይ ሆኖ ቢጣራ አይሰማም፣ ቅን ልብ የሌለው አማኝም ለሚሊዮን አመታት የነበሩትን ስነፍጥረታት በኮርበን ዲቲንግ አመታቸውን እየቆጠርን ብናስጎበኘው አይገባውም፡፡ ይህ አይነቱ ሰው ሳይኮሎጅስቶች የሚሉትን ይበሉት እኔ ግን ሞኝ ይመስለኛል፡፡

ዝግመተ ለውጥ ደስ የሚል የጥናት ዘርፍ ነው፡፡ ውሎ አደራቸው ከፅንሰ ሃሳቡ ጋር የሆኑ ሰዎች Evolution is a fasicillating subject የሚሉት እውነት አለው፡፡ የማይቀበሉት እራሱ ይወዱታል፡፡ አንዳንዴም እንደ ፍራንሲስኮሊንስ (francis collils) ያሉ ምርጥ ሳይንቲስቶች ከእየሱስ ክርስቶስ ጋር ደምረው ያምኑበታል፡፡ መደመር የሚባለው የጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አህመድ ፍልስፍና እዚህ ላይ ይሰራ ይሆን?

ስለ ኢቮልሽን እውነታ ወግኖ ለመከራከር ብቻ ብዙ መጽሀፍት መጻፍ ይቻላል፡፡ የአለም ቤተ መፅሀፍትና ቤተ-መዘግብት ሙዜሞችና የምርምር ጣቢያዎች የሚመሰክሩት ስለሆነ፡፡ ለሚገባው አንድ ቃል በቂ ነው ቢባልም ካስፈለገ ጉዳዩ ብዙ ስለሚያስወራ ታሪኩን ከፅንሰቱ ጀምሮ ለማስረዳት እየተመራመርኩ ነው፡፡ ሙህር ነኝ

Created in Master PDF Editor

ባልልም በአንባቢነቴ ግን አልጠራጠርም በአለኝ ጊዜ በ16 ክ/ዘመን እንግሊዘኛ ከተፃፉት መፅሀፍትና እስከእንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ በሚቀል እንግሊዘኛ የተፃፉትን መፃህፍት ለማንበብ እጥራለሁ። እድሜ ለጎግልናለላይብረሪ ጀነሲስ። ጥረቴም የተቆለፈበትን ቁልፍ መፍቻ መፈለግ ነው። ምርምሬ የእድሜ ልክ ምርምር ነው እድሜ ዘመኔን ከመታሰር እድሜ ዘመኔን ብማር መርጫለሁ። እስካሁን ከተማርኩት የተረዳሁት የውስብስብነት ምንጩ ኢቮልሽን መሆኑን ነው በሂደቱ ጥያቄዎች ቢኖሩኝም።

በተለይ የተፈጥሮን ውስብስብነትና ውበት በማየት ይህ ሁሉ እንዴት በአጋጣሚ ሊሆን ይችላል ብሎ መጠየቅ መልካም የሆነ አመክንዮ ነው። ፍጥረት እጅግ ውስብስብና ውብ ነው። መሬት እጅግ ማራኪ ናት። ሶላር ሲይስተም ደግሞ እጅግ ይረቃል። ሚልክወይ ጋላክሲ ደግሞ እጅግ ይደንቃል። እልፍ ሲባል እልፍ እንደሚባለው ወደ Dark matter, Dark energy, Black Hole, Singularity ጥናት ሲገባ ደግሞ ከአእምሮ በላይ የሆነ ድንቅ ነገር አለ። ታዲያ ይህን ሁሉ ማን አደረገ ለሚለው ከእምነት እግዚአብሔር ብንል የሚከፋ አይደለም። አይደለም ብንልም እግዚአብሔር አይቀየምም። ይህን ሁሉ ያደረገው ኢንተለጀንት ዲዛይነር (እግዚአብሔር) በመፅሀፍቱ እንደተገለፀው አይነት የሚቆጣ አይደለምና።

ስለዚህ ሳይንቲስቶች ጨረቃ ላይ ወይም በህዋ ላይ ሁነው ያነሱትን የመሬት ፎቶ እያዩ መደነቅ ብቻ ሳይሆን እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ ማለት መሰይጠን አይደለም መሰልጠን ነው እንጅ። መሬትና በመሬት ያለው ብቻ አይደለም በሁለንታ ያለው ሁሉ የራሱ የሆነ ውበት አለው። መሬት የራሷ ውበት እንዳላት ሁሉ የህዋ አካላትም የየራሳቸው ድንቅ ውበት አላቸው። ውበት የት መጣ በአጋጣሚ ወይስ በፈጣሪ? በፈጣሪ ከሆነ ምርምር አያስፈልገውም መልካም እንደሆነ አየ የሚለው በቂ ነው። ውበት የመጣው በተፈጥሮአዊ ሁደት ከሆነ ግን እንዴት ያስብላል? እንዴት? መልሱ አጭር ነው ገና ከጅምሮ ሀይል ወደ ቁስ ሲቀየር ውበት ጀመረ። ለነገሩ ሀይልም በራሱ ውበት ነው። ልክ የመጀመሪያዎች ፓርቲክሎች ከሀይል ሲፈጠሩ ተፈጥሮ መልካም እንደሆነ አየች ወደደችውም። ቀጠለችና አተሞችን ሰራች ወደደችው ከአተሞች ክምችትም ንጥረ ነገሮችን ሰራች እጅግ ወደደችውና ሰራዋን አሳምራ ቀጠለች። የጋዝ ደመናዎችን፣ አቧራዎችን፣ የመጀመሪያዎቹን የህዋ አካላት፣ ከላክሲዎችን፣ ስርዓተ ፀሀዮችን፣ ፕለቴቶችን፣ ህይወትን ሰራች። ዛሬም ትሰራለች አታርፍም በተፈጥሮ አሰራር ሰንበት የለም። ሁሌም ስራ ላይ ናት ተፈጥሮ ውብ የሆነችው ስራ ፈት ስላልሆነች ነው። ሁሌም ትታደሳለች። አበቦች ያብባሉ፣ ይረግፋሉ፣ እጽዋት አረንጓዴ ይለብሳሉ፣ ይደርቃሉም እንስሳት ይፈጠራሉ፣ ይሞታሉም።

ይህ በእርግጥ ውበት ነው ተፈጥሪአዊ የሆነ ውበት ሰው ሰራሽ ማስዋቢያዎች ያልተቀለቀለበት ፍፁም እውነት የሆነ ውበት፡፡ ግን ምንም እንኳ ተፈጥሮ ውብ ብትሆንም ለእኛ ለሰዎች ውበት የማይመስለን እና የማንቀበለው የውበት አይነት አለ፡፡ ጦርነት፣ ርሃብ፣ ስደት፣ እልቂት፣ ሙቀት፣ ቅዝቃዜ፣ በርሃማነት፣ ውርጭ፣ ጎርፍ ሱነሚ የመሬት መንሸራተት እና መንቀጥቀጥ ለተፈጥሮ ውበት ሊሆን ይችላሉ እንጅ ለሰዎች አይደለም፡፡ ይህን ሳስብ ተፈጥሮ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነች ተረዳሁ ግን አልጠላትም፡፡ አብዛኛዎችን መከራዎች እራሳቸውን ሰዎች የፈጠርናቸው ናቸው ቢያንስ እንኳ መቀነስ የምንችላቸው ብዙ አስከፊ ነገሮች አሉ፡፡ ከተለያዩ መረጃወች እንዳገኘሁት ዛሬም የባሪያ ንግድ ተጧጥፏል፤ በአለም ከሚኖረው ህዝብ ግማሹ በቀን 2 ዶላር እንኳ አያገኝም፣ ወደ 1 ቢሊዮን የሚጠጋ ህዝብ ትምህርት አላገኘም፤ ወደ 1 ቢሊዮን በላይ የሚሆን ህዝብ ንፁህ መጠጥ ውሃ አላገኘም፤ በእየቀኑ ከ25,000 የማያንሱ ህፃናት በድህነት ምክንያት ይሞታሉ፤ የአለም ግማሹ ህፃናት የሚኖሩት እጅግ በክፉ ድህነት ውስጥ ነው፡፡ በጣም የሚያናደው ይህ ሁሉ ሆኖ እያለ ሀገራት ብዙ ቢሊዮን ዶላሮችን ለጦርነት ዝግጅት ያውላሉ፡፡ ስለ ገነት እየሰበኩን መሬትን አርማጌዶን ለማድረግ ይቸኩላሉ፡፡ በእርግጥ የራሳችንንም ውበት የተፈጥሮንም ውበት ለማጥፋት እየተጣደፍን ነው፡፡ የሚደንቀው ደግሞ የጥፋቱ መንገድ ጠራጊዎች የእግዚአብሔርን ፍቅር አዳኝነትና የስነ ምግባር አባትነት የሚሰብኩን ናቸው፡፡ የውበት አምላክ የት ነው ያለው?

ተፈጥሮ የውበት ማዕከል ብቻ አይደለችም የጥፋትም እንጅ፡፡ መጠፋፋት ከጥንት ከመሰረቱ ነው፡፡ ለተፈጥሮ ግን መጠፋፋትም ውበቷ ነው እስኪ በአማዞን ጥቅጥቅ ደን የሚሆነውን አስቡት፡፡ በዚያ ጥቅጥቅ ደን ውስጥ ፍርሃት፣ ጭንቅና ሞት ነግሷል፡፡ በሆሊውድ የሚታዩትን ሆረር ፊልም በእውነት ከዚያ ታያላችሁ፡፡ ሁሉም ይበላላል፡፡ ለመያዝና ለማምለጥ የሚደረገው ሩጫ የ100 ሜትር አይደለም፣ የ10,000 ሜትርም አይደለም፣ የማራቶንም አይደለም፣ ማቆሚያ የለውም፡፡ በዚህ ደን ውስጥ በአንድ ደቂቃ ውስጥ ምን ያህል ነብስ ይጠፋል፤ ምን ያህሉስ ታመው ይሞታሉ፤ ምን ያህሉስ የተወለዱበትን አንደኛ ቀን ሳያከብሩ ይበላሉ፤ እንሰሳት በምግብ ሽሚያ በሚፈጥሩት አቲካራ ምን ያህሉ ይሰዋሉ፤ ዋው ከግምት በላይ ነው፡፡

በዚህ የመጠፋፋትና የመጥፋት ሂደት ሳይንቲስቶች ከ98% በላይ ዝርያዎች እንደጠፉ ይገመታሉ፡፡ ልክ ይመስሉኛል ከባህር ውስጥ እስከ ቤታችን ድረስ ብንቃኛው በህይወት ያለው ስነፍጥረት እጅግ በዝቶ ሊታየን ይችላል ግን የጠፋው እጅግ እጅግ ይበዛል፡፡ ማደንና መታደን ለተፈጥሮ ውበት ነው ለእግዚአብሔርስ? ፍጥረት እርስ በእርስ እየተበላላ እንዳይጠፋና አውዳሚ በሽታዎች እንዳይኖሩ ማድረግ ምን ይሳነዋል? በእርግጥ ሁሉንም ማድረግ ይችላል ግን ባይኖርስ?

Created in Master PDF Editor

ያም ሆነ ይህ የተፈጥሮን ውስብስብነትና የሰውን የማንነት ሚስጢር ለመፍታት ሀይማኖት ድርሻ እንዳለው ይሰማኛል:: ቢሆንም ከሳይንስና ከተፈጥሮአዊ ፍልስፍና አንጻር ግን እዚ ግባ የሚባል ውል ያለው መልስ የለውም:: አንዱ ቅዱስ ነይ ባይ ድንጋይ ዳቦ ነበር ካለ አለ ነው:: ከማመን ያለፈ ደጋግሞ መጠየቅ፣ መጠራጠርና መመራመር የተጠሉ ናቸው:: መ/ር ዘበነና ሌሎች የወንጌል ሰባኪያን የሚያንጸባርቁት ይህን ነው:: አዲስ ነገር የለም ያው የተጻፈውን ደግሞ መጻፍ ነው::

መ/ር ዘበነ 'ምንትኑ ውእቱ ሰብ' ያሉት መጽሃፋው ሶስት ክፍል ሲኖረው የመጨረሻው ክፍል የኢትዮጵያን ታሪካዊና ወቅታዊ ጉዳዮች የተነተኑት በመንቃትና ባለመንቃት መሀከል ሁነው ስለሆነ የመጽሃፉ አንድ ክፍል ሁኖ መጠቃለል አልነበረበትም፣ ቢጋነንም እውነት አለው:: የመጀመርያዎቹ ሁለት ክፍሎች ግን አንዳች የሰውን ምንነት ለመረዳት የሚያስችል ጥበብ የላቸውም፣ ነባራዊ አለሙን አያሳዩምና ቅዠቶች ናቸው:: ለነገሩ ከ100,000 አማልዕክት በአንዱ ከሚያምን ጽሃፊ በሀይማኖታዊ ትንታኔ የሰውን ማንነት መረዳት ይቻል ይሆን ማለቴ ስህተት መሰለኝ?

ሀይማኖት ስራውን ጨርሷል፣ ሊጠየቁ የሚችሉት ጥያቄዎችን ሁሉ አስቀድሞመልሷልያለን አማራጭ መልሱን ማውቅ ነው:: <u>ሀይማኖት እንደታረደ በሬ ሲሆን ሳይንስ እንደሚታረስ በሬ ነው::</u> የሞተን በሬ የሚበላ ስጋውን በልቶ፣ የማይበላ ስጋውን ጥሎ፣ ቆዳውን ሽጦ መሰናበት እንጅ ሌላ ምን ይደረጋል::ሳይንስ ግን በስራ ላይ ያለ ታታሪ፣ምርታማ የአርሶ አደር በሬ ነው:: "Every day we are told of some wonderful discovery of science. But what has theology discovered? The scientist is searching for the truth; the theologian is trying to save his idols. Of all the great inventions and discoveries that go to make human life easier, happier, richer and more glorious, not one can be laid to the work of theology. These triumphs all belong to science." ነበር ያለው Lemuel K. Washburn::

ሳይንስ እንዲህ ባልጠነከረበት ሰወች የተፈጥሮን እና የህይወትን ውስብስብነት የሚረዱት ከሀይማኖታቸው ወይም ሀይማኖት ወለድ ከሆነው ባህላቸው ተነስተው ነበር::

> እንደሌሎች የወቅቱ የዓለም ህዘቦች ሁሉ የብሉይ ኪዳን እስራኤላውያንም ሳይንሳዊ ዕውቀታቸው ዝቅተኛ ስለነበር እያንዳንዱን ተፈጥሯዊ ክስተት እነሱ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት ምክንያት የተፈጠሩ አድርገው ያስቡ ነበር:: በዚህም ለምጽን በሀጢያተኛ ሰዎች ላይ የሚመጣ የእግዚአብሔር ቁጣ ያደርጉታል፤ አስቀድሞ የነበረውን የኖራ ዲንጋይ የሎጥ ሚስት ወደ ጨው

Created in Master PDF Editor

ሃውልትነት ተቀይራ ነው ይላሉ፤ ተፈጥሯዊ የሆነውን ሴቶችን የወር አበባ የእግዚአብሔር እርግማን ነው ይሉታል፤ የፀሐይ ግርዶሹን የነቢዩ ኤልያስ ተአምር ነው ይላሉ፤ በራሱ ተፈጥሯዊ፣ የፀሐይ ግርዶሹን የነቢዩ ኤልያስ ተአምር ነው ይላሉ፤ በራሱ ተፈጥሯዊ ሂደት የሚፈጠረውን ቀስተ ደመና ለኖህ የተሰጠው ቃል ኪዳን ነው ይላሉ፡፡ የተፈጥሮን ክስተቶች ሕጋቸውን፣ አመጣጣቸውንና አካሄዳቸውን ስለማያውቁ እግዚአብሔር የትየለሌ የሆነውን ፍጥረቱንና ሌሎች የዓለም ህዘቦችን ሁሉ ትቶ ከእነርሱ ጋር ብቻ በፈጠረው ግንኙነት ውስጥ እነዚህ ነገሮች እንደተከሰቱ ያምናሉ፡፡ (ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣ 115)

ይህን የሚያደርግ እግዚአብሔር እንኳ ቢሆን ሳይንቲስቶች የፈጣሪን እቅድ ማወቃቸው እፁብ ድንቅ ነው፡፡ ታላቁ ሳይንቲስት እስቴፈን ሀውኪንግ የሳይንስ ግብ የፈጣሪን ሃሳብ ማወቅ ነው ይል ነበር፡፡

የአማልክት መኖር ከመፍትሔው ይልቅ ተጨማሪ ጥያቄዎችን ያስነሳል፡፡የፈጣሪን መኖር ለማስረዳት ፈላስፋው ዊሊያም ፔሊ በቴሌሎጂካያዊ ሙግት (Teleological argument) አማካኝነት ያሰረዳል፡፡ሁለንታ ውስብስብ በመሆኑፈጣሪ እንዳለ ያሰረዳል፡፡ ይህን በምሳሌ ለማስረዳት ያህል በባህር ዳርቻ ላይ ስትንሸራሸሩየእጅ ሰዓቱ ብታገኙ የሰዓቱን ውስብስብነት በመረዳት ብቻ በሆነ አዋቂ እንደተሰራ መረዳት ይቻላል በምንም አይነት የእጅ ሰዐት እራሱን አይፈጥርም በድንገትም አይሆንም ይላል፡፡

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ብዙ ሳይንቲስቶችና ፈላስፋዎች ይህንን ጉዳይ በሁለት ጎራ ተከፍለው የሚገቱበታል፡፡ ከፈላስፋው ዊሊያም ፔሊ ተቃራኒ የተሰለፉት ታታሪ ሳይንቲስቶችና ፈላስፋዎች ውስብስብ ስርዓቶች ያለፈጣሪ ሊፈጠሩ እንደሚችሉ የዝግመታዊ ለውጥ (Evolution by natural selection) አስተሳሰብን በማስረዳት ይሞግታሉ፡፡ ቀላል ስሪት ሴሎች (cells)በጊዜ ብዛት ምን ያህል ውስብስብ ሊሆኑ እንደሚችሉ ያስረዳሉ፡፡በተጨመሪም አንዳንድ ሳይንቲስቶችና ፈላስፋዎች ውስብስብ ስርዓቶችን ውስብስብ ፈጣሪ ከፈጠራቸው እርሱን ማን ፈጠረው ይላሉ፡፡ በግሌ ይህ አስተሳሰብ አያረካኝም፡፡

4. የእግዚአብሔር መኖር በቅዱሳን መፅሀፍት ተገልጧል

<<መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ የተለየ መጽሐፍ ነው፡፡ በስርጭት ደረጃ ወደር የማይገኝለት የምን ጊዜም ምርጥ መጽሐፍ ነው፡፡ በብዙ ሰዎች በመነበብና በብዙ ቋንቋዎች በመተርጎም ረገድ ወደር የማይገኝለት መጽሐፍ ነው፡፡ የሥነ ቁፋሮና የታሪክ ምሁራን ትክክለኛነቱን ደግመው ደጋግመው አረጋግጠዋል፡፡ አንድ ዕውቅ የሥነ ቁፋሮ ምሁር እንዲህ አለ "የመጽሐፍ ቅዱስን መረጃ

Created in Master PDF Editor

የተጻረረ አንድም የሥነ ቁፋሮ ግኝት እንዳልተገኘ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡" ያጠኑትና ያመኑት ሰዎች እስከ ዛሬ ከተጻፉት መጻሕፍት መካከል ምርጡ መጽሐፍ መሆኑን ይመሰክሩለታል፡፡ የእግዚአብሔርን የልብ ሐሳብ ለማግኘት የምናነበው ብቸኛው መጽሐፍ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት ሕብረት ሊኖረን እንደሚችልና ከእርሱ ጋር ሕብረታችንን እንዴት ማሳደግ እንደምንችል ይነግረናል፡፡>> (ምንጭ፦ እውነት ለሁሉ ድህረ ገጽ)

ክርስቲያኖች መፅሀፍ ቅዱስ የሚባል አላቸው፣ ሙስሊሞች ቅዱስ ቁርዓን የሚባል አላቸው፣ አይሁዶች ብሉይ ኪዳን አላቸው፣ ሂንድይዙሞች በሃጋቫድ ጊታ (Bhagavad Gita) አላቸው፣ላተር ደይ ሲያንት ወይም ሞርመኖች የሞርመን ቅዱስ መፅሀፍ አላቸው፡፡ ሌሎችም እንዲሁ ይብዛም ይነስም፡፡ ሁሉም አንድም ቃል እንኳ በስህተት እንዳልገባ ያስረዳሉ፣ ያምናሉም፡፡

የሚሳዝነው ግን ከመፅሀፍቱ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ የጠፋውን (አምላክ) አታገኙትም፡፡ በእርግጥ ስነ ፅሁፍ፣ ስነ ጥበብና ታሪክ ዘግበው መያዙ መልካም ነገር አለው፡፡ እንደማይገሰስና እንደማይከሱስ፣ እንደማይሻሻል አድርጎ ማሰብ ግን ውድቀት ነው፡፡ የሰማ ሳይሆን ያነበበ ማንም ሰው ይሰማኛል፡፡ በመፅሀፍቱ ውስጥ የማይረቡና ህፃናት ሊደርሱባቸው የማይገቡ ደንቃራ ትዕዛዞች አሉባቸው፡፡ ፖለቲከኞችና የፖለቲካ ቅጥረኛ ሙህራን ስለመፅሀፍቱ አውግተው አይጠግቡም፡፡ እኔ ግን ፖለቲከኛም የፖለቲከኞች የውሸት አበልም አልተከፈለኝም፡፡ ስለዚህ እውነቱን እመስክር ዘንድ ነፃነቱ አለኝ፡፡ መፅሀፍቱን ያነበበ እና ቅን ልቦና ያለው ይረዳኛል፡፡ በመጽሀፍ ቅዱስና በቁርዓን ከተፃፈው ውስጥ ለዚህ ትውልድ ከሚጠቅመውና ከማይጠቅመው የቱ ይበዛል? እኔ በሁለቱም መጽሃፍት መጥፎነቱ ይበዛል እላለሁ፡፡ ጭቅጭቅ አያስፈልገውም ማንበብ በቂ ነው፡፡ ችግሩ መልካም ጥቅሶችን ፈልጎ ይሄውና ማለት የተለመደ መሆኑ ነው፡፡ እኔ ግን በእያንዳንዱ ገጽ አድሎ ወይ ሽብር ወይ ባርነት ወይ ሴቶችን ዝቅ ማድረግ ወይ ግድያ ወይ ዘረኝነት ወይ ውሸት ወይ ተራ ትረት ወይ ስህተት ወይ ተቃረኖ ላገኝ እችላለሁ፡፡ እርግጠኛ ነኝ በእያንዳንዱ ገጽ፡፡ can you believe me? ተወዳጁ የ<How God Works> መጽሃፍ ጽሃፊ ማርሻል ብሬን Why Won't God Heal Amputees በሚል ድህረ ገጹ ላይ እንዲህ ይላል፦

> How do we know, for sure, that God did not write the Bible? We simply read the Bible and note how uncomfortable it is in so many places. We note that God is a huge proponent of slavery in the Bible. We note that God is a huge misogynist in the Bible. We note that God kills huge numbers of babies and small children in the Bible, and we know that this is both an atrocity and horrifically disgusting. We note that God, who is supposed to be all-knowing, knows no more than the primitive men who actually wrote the Bible. And so on. Anyone who takes the

Created in Master PDF Editor

time to actually read the Bible will rapidly reach the conclusion that the Bible was written by primitive men, not by an all-knowing God.

ችግሩ ምን መሰላችሁ ብዙዎች መፅሀፍትን አይተዋቸው አያውቁም። ቁርዓን ማጥናት ፈልጌ አንድ ሙስሊም የሰራ ባልደረባየን የአማርኛ ቁርዓራን እንዲያውሰኝ ጠየኩት የለኝም ነበር ያለኝ። ገብያ ላይ ፈለኩ አላገኘሁም ደግነቱ ጎግል ላይ አገኘሁት። አንዳንዶቹ ደግሞ መፅሀፍት አላቸው ግን ለማንበብ ይፈራሉ፣ የሚያስታቸው ይመስላቸዋል። አወ ትክክል ናቸው ከእምነት ለመውጣት እንደ ቅዱሳን መፅሀፍት የሚመራ የለም። የሙሴን መፅሀፍት አንቦ ኤጭ ይሄን ነው አንዴ መፅሀፍ ቅዱስ የምንለው የሚል ይኖራል። የሙሴ መፅሀፍት ለስነ-ምግባር ልዐልና፣ ለሳይንሳዊ ምርምር፣ ለተፈጥሮአዊ ፍልስፍና እና ለመንፈሳዊነት እንቅፋቶች ናቸው። ይህን ስል ያለምንም መሳቀቅ ነው በመፅሀፍቶቹ የሚያምኑት እንኳ አልተሳቀቁም።

በተለያየ መልኩ በቃልም ጭምር ሃይማኖቶች የየራሳቸው መጻሕፍት አሏቸው። እነዚህ መፅሃፍት(በስም) ቅዱሳን መጻህፍት ተብለው ይጠራሉ።መፅሀፍቱ ቅዱስ የሚል ስያሜ የተሰጣቸው በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ወይም በቀጥታ ፈጣሪ ያፃፉቸው ተደርጎ ስለሚቆጠር ነው። የእነዚህ ሃይማኖቶች ተከታዮቹ የቅዱሳን መጻህፍት የእኛ አምላክ መኖሩንያረጋግጣል ይላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ እና ቁርአን በበርካታ አማኞች ለሀይማኖታዊ እና ታሪካዊእውነቶችን እንደ ማስረጃ አና መመሪያ ይጠቀሙበታል። አማኞች የእነርሱ መፅሐፍ ሙሉ በሙሉ ፍጹም እውነት እንደሆነ ይናገራሉ። ለምን ቢባሉም የጻፈው ወይም ያጻፈው መለኮታዊ ስለሆነ ነው ይላሉ።አማኞች መፅሃፋቸውን እየጠቀሱ ያመኑባቸውን ጥቅሶች እስከ ቤታቸው ጣሪያ ድረስ ሲቆልሉ እኔ ግን ከቤቴ ጣሪያ አልፎ ጨርቃ የሚደርስ የማላምንበት ምክንያት አለኝ። ምክንያት ስላለኝ ነው የምዘምርልህ የሚለውን ምክንያት ስላለኝ እንዲህ የምነቅፍህ ብለውስ? በእግዚአብሔር ለአለማመኔ አንዱ ዋነኛ ምክንያት መፅሃተ ቅዱሳት ናቸው።እንደ መፅሃፍተ ቅዱሳት በቅራኔና በጥላቻ የተሞላ መፅሃፍ እስካሁን አላጋጠመኝም። ቅዱሳን መፅሃፍት አንድ ብቸኛ አስተሳሰብን የሚያራምዱ የውግዘት መፅሃፍቶች ናቸው።

ሦስቱ የአብርሀም ሀይማኖቶች በተለይም የክርስትና ሀይማኖት የተመሰረተው በውግዘት ነው። ለምን ቢባል ያለምንም ማስረዳት እንዲህ አታድርግ እንዲህ ደግሞ አድርግ ነው የሚሉት። ሲጀመር አዳምን እፀ በለስን እንዳይበላ አወግዘው እንጅ ለምን እንዳይበላ እንደከለከለው አልነገረውም። ይልቁንስ ከበልህ ትሞታለህ የሚል ሊመጣ የሚችለውን ውጤት ነግረው። በወቅቱ በእግዚአብሔር እና በአዳም መካከል መግባባት አልተፈጠረም። ነገሩ ተረት ተረት ቢሆንም አዳምና ሄዋን በእባብ አንሳሽነት እፀ

Created in Master PDF Editor

በለስን በሉ፡፡ (ደግ አደረጉ)፡፡ ከዚያም ውግዘቱን ስለተላለፉ ለዘለዓለም እስከ ዘርማንዝርታቸው ተቀጡ፡፡ አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ ማለት ይህ ነው፡፡

ሁሉም አታድርጎች እና አድርጎች መጥፎ አይደሉም ቢሆንም መሰረታዊ ችግራቸው ለምን የሚለውን ማብራራት አለመፈቀዳቸው ነው፡፡ ቤቱ ክርስቲያንም ከምስራቹ የወሰደችውን የውግዘት ባህል አጠናክራ ቀጥላበታለች፡፡መጽሀፍቶቿቸው መጽሀፍተ ውግዘት ናቸው፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ያለው ታሪክ እንደሚነግረውን የፃፉት የሚሠብኩት ስለዓለም ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ ችግሮች መፍትሔ ለማፈላለግ ሳይሆን የተለየ አተያይ ያላቸውን ሰዎች ለማውገዝ ነው፡፡ ብቻ የቤተክርስቲያን ዶግማ አይቃወስ እንጅ ሌላው የራሱ ጉዳይ ነው፡፡ አስቡት በአለም መድረክ ከኒቂያው ጉባኤ ጅምሮ ታላላቅ ሀይማኖታዊ ስብሰባዎች የተካሄዱት ደም አፋሳሽ ጦርነቶችን ለማስቀረት ሳይሆን ተራ ግለሰብ ወይም ቡድን ለማውገዝ ነው፡፡በ325 ዓ.ም የኒቂያ ጉባኤ፣ በ381 ዓ.ም የቆንስጣንጢኖስ ጉባኤ፣ በ431 ዓ.ም የኤፌሶኑ ጉባኤ እና በ451 የቀልኬዶን ጉባኤ ከመወጋገዝ ውጭ ምን ፋይዳ ነበራቸው፡፡

ውግዘትን የምጠላው ወድጀ አይደለም ከብዙ መልካም ነገሮች ስለሚያራርቀን ነው፡፡ ሰው በተፈጥሮው መመገብ፣ መጠጣት፣ መስራት፣ መጨፈር፣ መደነስ፣ መዝናናት፣ ማጌጥ፣ መጋባት ይፈልጋል፡፡ ሀይማኖቶቻችን እንዳንበላ ፆም፣ እንዳንጠጣ ክልከላ፣ሁሌም ተግተን እንዳንሰራ ባዕላት፣ እንዳንዝናና ቅጣት፣ አምሮብን እንዳንታይ ሂጃብ፣ እንዳንጋባ ምንኩስናን ፈጠሩብን፡፡ የሚያሳዝነው ከተፈጥሮ ጋር መጋጨት ውጤቱ ሽንፈት ነው፡፡ ምግብ እና መጠጥን የከላከሉን፣ አንዳንዴ ተፈቅዷል በሚል ቁንጣን እስኪያዛቸው ይበላሉ፣አልፎ ተርፎም ጥንብዝ ብለው እስኪሰሩ ድረስ ይጠጣሉ፡፡ ሰውን እንዳይሰራ ከልክለው ቤተ እምነቶቻቸው ያስመጡና የራሳቸውን ስራ ያሰራሉ፡፡ መጨፈር መዳነስን መዝናናትን ይከለክሉና የራሳቸውን የመጨፈር የመደነስ ስልቶችን ፈጥሮው ይዘፍናሉ፡፡ (ይዘምራሉ)፡፡ መጋባትን አማራጭ የማጣት ምንኩስናን የተቀደሰ እንደሆነ አሰተምረው ራሳቸው ሲሞክሩት ብዙዎቹ ይተውታል፡፡ ቀሪዎች ደግሞ በተለያየ መልኩ ስጋዊ አምሮታቸውን በተለያየ ምለኩ ያስታግሱታል፡፡ በተለይ የግብር ሰዶማዊይነት ስራዎች እንደሚሰሩ ይታመናል፡፡

ሰው በተፈጥሮው ከተፈጥሮ መሸሽ ይከብደዋል፡፡ ፍቱኑ መድሀኒት ከተፈጥሮ ጋር ተስማምቶ በልክ እየበሉ፣ እየጠጡ፣ እየተዝናኑ፣ እየተጋቡ እና እየተኳኳሉ መኖር ነው፡፡ የእግዚአብሔርሽልማት በሰማይ ነው የተፈጥሮ ቅጣት ግን በምድር ነው፡፡ እግዚአብሔርከጾምክ በሰማይ አጠግብሀለሁ ሊልህ ይችላል ተፈጥሮ ግን ባልበላህ ጊዜ በጠኔ ያሰቃይሀል፡፡ እግዚአብሔር ባትጋባ መንግስትን ተወርሳለህ ስል ተስፋ ይሰጥሀል ተፈጥሮ ግን ሀጉን ባለማክበርህ ከማይመስልህ ፍጡር ጋር እስክተገናኝ ድረስ ያቃጥልሀል፡፡ ወንድሞችና እህቶች ሰው እንዳያስብ፣ እንዳይናገር፣

Created in Master PDF Editor

እንዳያስተምር እና የግሉን ህይወት ከተፈጥሮ ጋር ተስማምቶ እንዳይኖር ሀይማኖት እንቅፋት ሆነብን፡፡ የሰው መሰልጠን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ትልቁ እንቅፋት ውግዘት ነው፡፡ ውግዘት ከአብርሀም ሀይማኖቶች በፊት የነበሩት፣ የአብርሃም ሀይማኖቶች፣ እና በዚህ ወቅት ያሉትም የጠፉትም ሌሎች ሀይማኖቶች የሚጠቀሙበት ጥልቅ የማስፈራሪያ መሳሪያ ነው፡፡ ምን አልባት አንዳንድ የሩቅ ምስራቅ እምነቶች ውግዘታቸው የተጋነነ ስላልሆነ በጅምላ መተቻቸት መልካም አይመስለኝም፡፡

በእውን ውግዘት ያስተምራልን? ከስህተትስ ይመልሳልን? ፈላስፋው ወልደ ህይወት በፍቅር እንጅ በውግዘት የሰው ልጅ ከጥፋቱ ሊመለስ እንደማይችል በተነተነበት በሀተታው ምዕራፍ 14 እንዲህ ያስገርመናል፦ *"ሰው ሁሉ በተፈጥሮ እኩል ነው፡፡ ሁላቸውም የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆኑ ልብ አድርገን እናውቅ ዘንድ ይገባናል፡፡ እኛ ግን በሃይማኖት የማይመስሉንን ብንጠላቸው እንበድላለን፡፡ <u>እያንዳንዱ ሰው እውነት የመሰለውን ያምን ዘንድ ስልጣን አለውና፡፡</u> ሃይማኖት ግን <u>**በእውቀትና በትምህርት እንጂ በሀይልና በውግዘት**</u> በሰው ልብ ሊጸናና ሊቀና አይችልም፡፡ ሰዎችን ስለ እውቀታቸው ልንጠላቸው እንደማይገባን ሁሉ፣ እንዲሁም ስለ ሃይማኖታቸውም ልንጠላቸው አይገባንም፡፡"* (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 301)

ውግዘት የቃል ብቻ አይደለም በተግባርም ይገለፃል፡፡ የተለየ አስተሳሰብ እና ፍልስፍና ያላቸውን ሰዎች በአደባባይ መውገር፣ መስቀል፣ ማሰር እና ማሰቃየት የሚሊዮን ሰዎች እጣ ፈንታ ሁኖ አልፏል፡፡ በተግባር የሚገለፀው ውግዘት ምን ያህል ደም እንዳፈሰሰ ማወቅ አልችልም፡፡ ምን አለፋችሁ እነዚህ በዳቦ ስማቸው ቅዱሳን መፅሃፍት የሚባሉት የውግዘት መፅሃፍት (በተለይ ብሉይ ኪዳን) እንዳንራመድ ካሰሩን በላይ እንዳንኖርም ከልክለውን ቆይቷል፡፡ውግዘት በተለየም በሀይል የሚገለፀው ውግዘት ከቤተ እምነቶች መጥፋት ያለበት ፀረ ሰው አስተሳሰብ ስለሆነ ቢጠፋ መልካም ነው፡፡ የውግዘት ምዓት የታጨቀበት መፅሃፍ ቅዱስም ወደ መዝገብ ቤት ቢገባና በቅርስነት ተመዝግቦ ቢጎበኝ አይከፋም፡፡ እኔ ይህን ልበል እንጅ አማኞች ስለ መፅሀፍ ቅዱስ ክብርና ቅድስና ተናግረው አይሰለቹም፡፡ ተስፋለም ከላሊበላ በድህረ ገጹ (http://tesfalem7.blogspot.com/) ባሰፈረው የቅዱሱ መፅሃፍ መወድስ መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች መጻሕፍት በምን እንደሚለይ በርካታ ምክንያቶችን ሰጥቶ ተንትኖታል፡፡ሌሎችም ብዙ ይተርካሉ፡፡

I. **ትንቢቱ የተረጋገጠ እውነት በመሆኑ፡-** መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በመረጣቸው ነቢያት የራሱን አምላካዊ ፈቃድ የገለጠበት ፍጻሜውንም በወሰነው ጊዜ እንዳከናወነ የተመዘገበበት ቅዱስ መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የተስፋና የፍጻሜ መጽሐፍ ነው፤ በብሉይ ኪዳን በትንቢት የተነገሩት ከሰው አእምሮ እና ከተፈጥሮ ሕግ በላይ የሆኑት አምላካዊ እቅዶች በአዲስ ኪዳን በትክክል

Created in Master PDF Editor

ተፈፅመዋል፡ “ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች” የሚለው የትንቢት ቃል ለተርጓሚው ለስምየን አረጋዊ አእምሮ ቢከብድም ጌታ እንደቃሉ ከድንግል ማርያም ያለ ወንድ ዘር በመወለድ ፈጽሞታል፡፡ ኢሳ. 7፡14፤ ማቴ. 1፡23፡፡ ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገሩ የትንቢት ቃሎች ለጸሐፊዎች ቢከብዱም ተፈጽመዋል፡፡ ያልተፈጸሙትም በጊዜያቸው ይፈጸማሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ፍጻሜ ያገኙና ያላገኙ ትንቢታትተመዝገበ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ወደፊት ስለሚሆነው በእርግጠኝነት የሚናገር ብቸኛ መጽሐፍ ነው፡፡ መዝ. 49፡2

መልስ፦የክርስትና እምነት ተከታዮች በመጽሐፍ ቅዱስ የተተረከውን ነገረ ክርስቶስን እንደ ልዩ ድንቅ ክስተት ይቆጥሩታል፡፡ ታሪኩንም ከመጽሐፍ ቅዱስ በፊት የትም ያልተጻፈ ያልተነገረና በመንፈስ ከተረዱት ነብያት ውጭ የማይታወቅ ተስፋ አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ በሀይማኖት ላይ ጥላቅ ምርምር ላደረጉት ግን መጽሐፍ ቅዱሱና መሪ ተዋናዮቹ በዘመኑ ሲነገሩ ከነበሩት ትርክቶች አንዱ ነው፡፡ ልዩነቱ ብዙዎች ተመሳሳይ ትርክቶች ሳይሳካላቸው ሲቀር ክርስትና በተለይም በጳውሎስ ጥረት Survival of the Fittest መሆን ችሏል፡፡መጽሐፍ ቅዱስን ብዙ ህዝብ ስላመነበት ብቻ እውነተኛ ነው ካለልን በስተቀር በታሪኩ ከሌሎች አማልዕክት የተለየ እውነት አላስተዋወቀም፡፡ ትንቢት ማስነገር፣ በድንግልና መወለድ፣ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን፣ ተዘዋውሮ መስበክ፣ ታምራትን ማድረግ፣ ተንሳዔ ሙታን እንዳለ ማሳወቅ፣ የእምነቱን መሰረታዊ ዶግማዎች ማስተማርና ወደ ሰማይ ማረግ የተለመደ ነው፡፡

የRobert Wright ‘The Evolution of God’ መጽሃፍ ከክርስቶስ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አንድ የከሸፍን አምላክነት ያስታውሳል፡፡“Ever hear of Apollonius of Tyana? Like Jesus, he lived in the first century CE. According to stories later told by his devotees, he traveled with his disciples from town to town doing miracles: curing the lame and the blind, casting out demons. These powers emanated from his special access to the divine–he was the son of God, some said –as did his gift of prophecy. He preached that people should worry less about material comforts and more about the fates of their souls, and he espoused an ethic of sharing. He was persecuted by the Romans, and upon death he ascended to heaven. This imparted a nice symmetry to his life, since his birth had been miraculous in the first place; before he was born, his divinity had been proclaimed to his mother by a heavenly figure.” ይህ የRobert Wright ምሳሌ በአራቱ ወንጌላት የተተረከውን ዋናዋና ክንውኖች በአጭር ያቀነባበረ ነው፡፡ አንድ ወንጌልን የተረዳ ሰው ክርስቶስ በምዋለ ስጋው ምን

Created in Master PDF Editor

ስራ ቢባል የሚጠቅሰው Apollonius of Tyana ያደረገውን ነው። ታድያ ወንጌል የነገረን የምስራች ምንድን ነው? ወንጌልን ልዩ የሚያደርገው የተፈጸመ ትንቢትስ የቱ ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ስላለፈውና ወደፊት ስለሚሆነው በእርግጠኝነት የሚናገር ብቸኛ መጽሐፍ ነው የሚለው ተቀጻላ ስም እንዴት ሊመጣ ይችላል? ክርስቲያኖች ከሊቅ እስከ ደቂቅ የሚመኩበት በብሉይ ኪዳን በትንቢት የተነገሩት ከሰው አእምሮ እና ከተፈጥሮ ሕግ በላይ የሆኑት አምላካዊ እቅዶች በአዲስ ኪዳን በትክክል ተፈፅመዋል የተባሉትስ የትኞቹ ታሪኮች ናቸው። በአዲስ ኪዳን ታምር ተብሎ የተጻፈው በሌሎች ባህሎችና እምነቶች ተከናውኗል ተብሏልና። ለምሳሌ ይላል ሳይንቲስቱ Michael Shermer፦ fore example, Virgin birth myths likewise spring up throughout time and geography. Among those alleged to have been conceived without the usual assistance from the male lineage were: Dionysus, Perseus, Buddha, Attis, Krishna, Horus, Mercury, Romulus, and, of course, Jesus of Nazareth. Consider the parallels between **Dionysus,** the ancient Greek God of wine, and **Jesus.**Both were said to have been born from a virgin mother, who was a mortal woman, but were fathered by the king of heaven; both allegedly returned from the dead, transformed water into wine, introduced the idea of eating and drinking the flesh and blood of the creator, and were said to have been liberators of mankind.” (50 voices of disbelief, page 73)

በጣም የሚገርመው ደግሞ አብዛኛዎቹ ታሪኮች የተፈጸሙት ከክርስቶስ በፊት ነው።ክርስቶስ ከቅድመ ልደቱ እስከ ዳግም ምጸቱ ያደገውንና የሚያደርገውን ሌሎችም በተለይ የግብጽና የግሪክ አማልዕክት እንደሚያደርጉት አስነግረው ነበር።ከሰው ልብ ጠፍተው በታሪክ ብቻ የሚገኙት ክርስቶሶች ስለጠፉ ብቻ ሃሳዊ ነበሩ ማለት ነውን?

II. ስለፍጥረታት አፈጣጠር በእርግጠኝነት ስለሚናገር፦ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፍጥረታት አፈጣጠር ሲናገር በመላምታዊ አመክንዮ አይደለም፤ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ በማለት በእርግጠኝነት ይናገራልና። ዘፍ. 1፡1።

መልስ፦ቅዱሳት መጻሕፍት በተደጋጋሚ ወጥነትና እርግጠኝነት የሌላቸው የተሳሳቱ ናቸው።

በእያንዳንዱ ጉዳይ ስነ ፍጥረትን ጨምሮ ቅዱሳት መጻሕፍት በእርግጠኝነት የሚነግሩን የለም። አማኝ ሊህቃን ሳይቀሩ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ስነ-ፍጥረትና ሌሎች መሰረታዊ ክስተቶች የሚተርኩት ምሳሌዊ በሆነ መንገድ ስለሆነ ሚስጢሩ

Created in Master PDF Editor

የተገለጸላቸው ሊተረጉሙት ይገባል ይላሉ፡፡ ይህ አተያይ በቅዱሳት መጻሕፍት የተተረኩትን የብዙ ትርክቶች ከትረትነት ለማውጣት የሚደረገው ጥረት አካል ነው፡፡

እያንዳንዱ ቅዱስ መጽሐፍ በውጡ በስህተቶች፣ በአለመግባባቶች እና በአንድ ጉዳይ ተፃራሪ ሀሳቦችን በማራመድ የተሞሉ ናቸው፡፡ እነዚህ መጻሕፍት እርስ በርስ እንደይስማሙ ያደረጋቸው የተጻፉት ባለፉት ሽህ ዘመናት በተነሱ በርካታ ደራሲያን በመሆኑ ነው፡፡ የአንዱ ደራሲ ሀሳብ ከሌለው እንደሚለይ መወቅ አይከብድም፡፡

ሌላው አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ስህተቶች ከሚታዩ ነባራዊ ህጎች ጋር የማይጣጣሙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የእርግጠኝነት ተምሳሌት የተደረገው ዘፍጥረት፡፡ ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 <እግዚአብሔር በመጀመርያው ቀን ሰማያትን ና ምድር ፈጠረ፡፡ በሦስተኛው ቀን ተክሎች ፈጠረ ከዚያም በአራተኛው ቀን ከዋክብት፣ ፀሐይ፣ ጨረቃ እና ሌሎች ፕላኔቶችን ፈጠረ፡፡> ከዘፍጥረት እንደምንረዳው ከፀሃይ በፊት መሬት፣ ከፀሃይ በፊት ተክሎች ተፈጥረዋል፡፡ ይህ ቅደም ተከተል ስሜት አይሰጥም ለምን ብትሉ እጽዋት ለመኖር የፀሀይ ብርሀን ያስፈልገቸዋል፣ ፅሃይም ከመሬት በፊት ቢልዮን አመታትን ኑራለች፡፡ ሙሴ ይህን ሲጽፍ እንዴት እንደዳለስተዋለው ይገርመኛል፡፡ ይህ እኮ የፈጣሪ ታምር ነው ካላችሁ ሌላ አውነት ልንገራችሁ ሁለንታ የተፈጠረው በዝግመተ ለውጥ እንጅ በአንድ ሳምንት የኮንትራት ውል አይደለም፡፡ እግዚአብሔር አለምን የፈጠረው በስድስት ቀን ነው የሚለው መፅሃፍ ቅዱሳዊ ትንታኔ ከሳይንስም፣ ከታሪክምና ከስነ ልቦንም ጋር የማይሄድ ነው፡፡

ይህም ሆኖ እያለ አንዳንድ ሰባኪዎች ዓለም በቢሊዮን በሚቆጠሩ ዓመታት ውስጥ ተፈጥሮ እንዳለቀ ሳይንስ አረጋግጧል ይህ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ዓለም በስድስት ቀናት ውስጥ ተፈጥሮ እንዳለቀ ከሚተርከው ጋር አይጋጭም ይላሉ፡፡ እንዴት ስንላቸው መፅሃፉን በራሳቸው ከሳይንሱ ጋር እንዲሄድ አድርገው ይተረጉሙታል፡፡ እንዲህ ይላሉ መጽሐፍ ቅዱስ ዓለም በስድስት ቀናት ውስጥ ተፈጥሮ እንዳለቀ እንድናምን አይጠይቀንም፡፡ በዘፍጥረት ላይ የተጠቀሰው ቃል እግዚአብሔር በቢሊዮን ዓመታት ውስጥ ዓለምን እንደፈጠረ አድርጎ ለማሰብ የሚያስችል ክፍተት አለው ይላሉ፡፡

የክርስቲያን ሳይንስ እንዲህ ይላሉ፦ “መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ ብሎ ነው፡፡ ከምንም ነገር ተነስቶ በአንድ አፍታ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ፡፡ ይህ ለዓለማችን ፍጹም የሆነ አጀማመር ነበር፡፡ ሳይንሲስቶች «ቢግ ባንግ ቲዎሪ» የሚሉት ዓይነት መሆኑ ነው፡፡ ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቀሪው ቁጥሮች እግዚአብሔር አምላክ ሌሎችን ፍጥረታት በቀደም ተከተል ሲፈጥር እንመለከታለን፤ የምድርን ከባቢ አየር፣ ጸሐይንና ጨረቃን በየሥፍራቸው ማስቀመጥ፣ ከመሬት ላይ ውሃውንና የብሱን መለየት፣ ዕጽዋቶችን ተክሎችንና

Created in Master PDF Editor

አዝርዕቶችን እንዲሁም በባህርና በምድር ላይ የሚኖሩ እንስሶችንና ነፍሳትን፣ በመጨረሻም ሰዎችን ፈጠረ። ዋናው ጥያቄ ታዲያ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ዓለምን ማለትም ሰማይንና ምድርን በስድስት ቀናት ውስጥ ፈጥሮ ጨረሰ ይላልን የሚለው ጥያቄ ነው።" ጥያቄው ተገቢ ቢሆንም መልሱ ግን ተጨማሪ ዲሪቶ ለቅዱሱ መፅሃፍ የሚያለብስ ነው። የመሿለኪያው 6 ቀን ሲተረጎም እንዲህ ነው፦

የዘፍጥረት መጽሐፍ ላይ የሰፈረው እግዚአብሔር በስድስት ቀን ውስጥ ተፈጥረው እንዳለቁ የሚገልጽ ቢመስልም፤ ማስተዋል ያለብን ነገር ዘፍጥረት የተጻፈው በዕብራይስጥ ቋንቋ ነው። የዕብራይስጥ ቋንቋ ከእንግሊዝኛ ቋንቋና ዛሬ ከሚነገሩት ሌሎች ቋንቋዎች ጋር ሲነጻጸር የቃላት ሃብቱ አነስተኛ እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ ነው። ስለዚህ አንዳንድ አገላለጾች ለዘመኑ አንባቢዎችና ለተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች፥ ግልጽ ላይሆኑ ይችላሉ፣ ወይም አሻሚ ትርጉም ይዘው ሊገኙ ይችላሉ። እንደዚሁም « ቀን » (በእብራይስጥ «ዮም» የሚለው ቃል) 24 ሰዓትን ፣ ወይም ብርሃንማውን ቀን፣ ወይም ዛሬ ፣ ወይም ዘላለም፣ ወይም ቀጣይነት ያለው ቀን፣ ወይም ያልተወሰነ ቀን ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ስለዚህ ስድስት ቀን ርዝመቱ ያልታወቀ ቀን ነው ማለት ነው። የግድ ስድስት ቀን እያንዳንዱ 24 ሰዓታት ያሉት ቀናት ማለት ላይሆን ይችላል።

ይህን መሰሉን ቆርጦ ቀጥል ትርጓሜ እኔ ብቻ ሳልሆን ብዙዎች ክርስቲያኖች በተለይ ኦርቶዶክሶች አይቀበሉትም። አንዴ ከአፍ የወጣ ስህተት ስለሆነ አምኖ መቀበል ወይም አለም የተፈጠረችው የዛሬ 7,511 አመት በ6 ቀን ነው ብሉ ድርቅ ማለት ይሻላል። መጽሐፍ ቅዱስ ወጥነት የሌላቸውና የተሳሳቱ ሀሳቦች የተከማቹበት መሆኑን መቀበል የከበዳቸው ቴሌቫንጋሊስቶች መቸም ቢሆን ከሚወርድባቸው የትችት ዝናብ ለመጠለል ቁጥቋጦ መፈለጋቸውን አይተውም፣ እንጀራ ነዋ።

III. **የሰው ፈጠራ (ልብ-ወለድ) ባለመሆኑ፡-** መጽሐፍ ቅዱስ የጠቢባን ምርምር ውጤት የሆነ ፍልስፍና፤ የደራሲያን የምጥ ፍሬ የሆነ ልብወለድ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎቹ በራሳቸው ተነሳሽነትና ጥረት የደረሱት የፈጠራ ድርሰት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ በሰዎች መግባቢያ ቋንቋና ፊደል የተጻፈ ቢሆንም እንኳ ቃሉ የእግዚአብሔር ነው። ኤር. 1፡9፤ ዘካ. 6፡9፤ዮሐ. 2፡22፤ ራዕ. 20፡12።

መልስ፦ ሃይማኖታዊ ጽሑፍዎች ሰው ሰራሽ ልብ ወለድ ናቸው።

በቁርዓን እና መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሚገኙ ስህተቶች ቀላል ማብራሪያ አለ ሰነዶቹ በሰዎች የተፃፉ ስለሆነ ነው። የመፅሀፎቹ ምንጭም አፈ ታሪኮች ናቸው። የተፃፉትም

Created in Master PDF Editor

ድርጊቶች ከተከናወኑ ብዙ ዘመናት በኋላ በመሆኑ መዛባቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል:: በተጨማሪም የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በአብዛኛው ማን እንደፃፋቸው በግልፅ አይታወቅም:: ሙሴ፣ ነብያት፣ ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስፃፉት የሚለውን የጨመሩት በኋለኛው ዘመን ነው እንጅ እራሳቸው ደራሲዎቹ እኔ ፃፍኩት አላሉም::

ኦሪት የተጻፈው በእግዚአብሔር ገላጭነት በሊቀ ነብያት ሙሴ ነው ይባላል:: ነገር ግን ሙሴ ሙቶ እንኳን ይጽፍ ይሆን የሚል ጥያቄ የሚያጭር ዘዳግም ላይ ስለ አሟሟቱ ይተርካል:: ዘዳ. 34:4-8 *“እግዚአብሔርም ለዘርህ እሰጣታለሁ ብዬ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም የማልሁላቸው ምድር ይህች ናት፤ በዓይንህ እንድታያት አደረግሁህ፥ ነገር ግን ወደዚያች አትሻገርም አለው:: የእግዚአብሔር ባሪያም ሙሴ እንደ እግዚአብሔር ቃል በዚያ በሞዓብ ምድር ሞተ:: በቤተ ፌጎርም ፊት ለፊት በሞዓብ ምድር በሸለቆው ውስጥ ተቀበረ፤ እስከ ዛሬም ድረስ መቃብሩን ማንም አላወቀም:: ሙሴም በሞተ ጊዜ ዕድሜው መቶ ሀያ ዓመት ነበረ፤ ዓይኑ አልፈዘዘም፥ ጕልበቱም አልደነገዘም:: የእስራኤልም ልጆች በሞዓብ ሜዳ ሠላሳ ቀን ለሙሴ አለቀሱለት፤ ለሙሴም ያለቀሱለት የልቅሶው ወራት ተፈጸመ::”* ምን አልባት ይህን መሰል አንቀጾች የጨመሩት የሙሴ ተከታዮች ከሆኑ ራሳቸውን ማስተዋወቅ ነበረባቸው የትኛው አንቀጽ ላይ ሙሴ መጽሃፍ እንደተው ደንበር ቢበጅለት መልካም ነበር::

ማቴዎስ ፃፈው የተባለው ወንጌል ማትዮስ ለመፃፉ ምን ማስረጃ የለም:: ሲጀመር ማትዮስ ነው የፃፈው ያሉት መፅሀፉ ከተጻፈ ብዙ አመታት በኋላ እንደሆነ ክርስቲያን ሰባኪዎች ሳይቀር ያምናሉ:: በተለይ በቅርቡ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት ስልጠና እየወሰድኩ መምህራችን ይህን የጻፈው እገሌ እንደሆነ ይታመናል እያሉ ሁሉን መጽሀፍ በይታመናል መጨርሳቸው ደንቆኛል:: የአይን ምስክር አያስፈልግም ግን ለምን እኔ ጻፍኩት አይሉም፣ ለትህትና ነው እንዳትሉኝ:: ማትዮስ ፃፈው በተባለው ወንጌል ውስጥ እንዲህ ሚል ፅሁፍ እናገኛለን “እየሱስ ከዚያ ተነስቶ ሲሄድ ማትዮስ የሚባል አንድ ሰው በቀረጥ ማስከፈያ ኬላ ተቀምጦ አየ ተከተለኝ አለው እሱም ተነስቶ ተከተለው::” ፀሀፊው ማትዮስ ቢሆን ኖሮ እየሱስ ከዚያ ተነስቶ ሲሄድ እኔን በቀረጥ ማስከፈያ ኬላ ተቀምጬ አየኝ ተከተለኝም አለኝ እኔም ተነስቼ ተከተልኩት ብሎ ይነግረን ነበር:: የወንጌሉ ፀሀፊ ሌላ ሰው ሊሆን እንደሚችል መገመት ቀላል ቢሆንም የመፅሀፍ ቅዱስ ሊቃውንት ያፀደቁት ግን ማትዮስ ብለው ነው:: ይህ መፅሃፍ ማንነቱ ከማይታወቅ ሰው የተገኘ ነው ሊባል ነው::

የዮሐንስ ወንጌል እውን በዮሐንስ ተፃፈ ለሚለው ምሁራን አልተፃፈም ይላሉ:: ለምን ቢባል ወንጌሉ በዮሀንስ ላለመፃፉ የዘብዴዎስ ልጅ ማርቆስ ፃፈው በተባለው ወንጌል

Created in Master PDF Editor

ውስጥ ዮሐንስ አሳ አጥማጅ እንደነበረ ይጠቅስና ዮሐንስ ማንበብ እና መፃፍ እንደማይችል፣ ያልተማረ እንደነበረ ከሐዋርያት ስራ 4፥13 እንረዳለን:: ምን አልባት የሞላባቸው መንፈስ ቅዱስ በአንዴ ሊህቃን አድርጓቸው ከሆነ አላውቅም:: በጣም አስገራሚ የሆነው ነገር ይህ ወንጌል የግሪክን ቋንቋ ትምህርት በተረዳ ሰው እንደተፃፈ የክርስቲያን ምሁራን መስማማታቸው ነው:: ከነበረው ታሪካዊ ሁኔታ አንፃር እና የስነ መለኮት ሙህራንን ዋቢ አድርጎ <መርፌው> የተባለ የዋርካ ጦማርተኛ ጥንታዊ የተባሉት ወንጌሎች በእየሱስ ደቀ መዝሙር እንዳልተፃፉና ወንጌሎችን የፃፉት ፀሀፊን ማንነት እስካሁን አልታወቀም ሲል ያስረዳል::

መርፌውእንዲህ ይላል<<አንድ መፅሀፍ ወይም ፅሁፍ መለኮታዊ ሚሰኘው ክርስትያኖች በጉባኤ ሲያፀድቁት ብቻ ነው? ያውም በሁለተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ:: ደስ አለህም ጎረበጠህም እነዚህ ፀሀፊያቸው የማይታወቁ ፅሁፎች እስከ ሁለተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ድረስ መለኮታዊ አልነበሩም ከዛ በኂላ ነው መለኮታዊ የሚል ስያሜ የተሰጣቸው:: ሁሉም ፅሁፉ ከእየሱስ ደቀ መዝሙር ነው ይላል ግን ማረጋገጫ ሚሆን ነገር የለም:: ከዛ በዘለለ ስለ እየሱስ የተፃፉት ጥንታዊ ፅሁፎች ሁሉ ስምምነት የላቸውም:: እነዚህ ጥንታዊ ፅሁፎች ላይ አብዛኛው ውድቅ ተደርገዋል ምክንያቱም የእየሱስን አስተምሮ ስለሚንዱ አልፎ ተርፎ ተቀባይነት ባገኙ ወንጌሎች ውስጥ እራሱ ግጭት ሞልቶ ተርፏል:: አንዱ ከአንዱ ሲጋጭ ታየዋለህ:: ይህ ደግሞ ክርስትና እምነትን መሰረት ይንዳል::>>

ይህን በምሳሌ ለማስረዳት መርፌው 7 ምሳሌዎችን ይጠቅሳል፦

፩ኛ፦ መፅሀፍ ቅዱስ በመንፈስ ተፃፈ ለሚለው

የክርስት እምነት መሰረታዊ ዶክትራይን አንዱ የፅሁፉ መለኮታዊነት ነው:: ይህንም በተመለከተ ጴጥሮስ ፃፈው በተባለው ግን ጴጥሮስ ባልፃፈው 2ኛ ጴጥሮስ ላይ ሰፍሮ እናገኘዋለን ይልና 2ኛ ጴጥሮስ በቅዱስ ጴጥሮስ እናዳልተጻፈ እውቁና በአንደኛ ሲል ያሞገሰውን የመፅሀፍ ቅዱስ ሊቅ ብሩስ መተዝገርን ይጠቅሳል:: ይህ ሊቅ ስለ2ኛ ጴጥሮስ መልዕክት የጻፈውን እንደማስረጃ ያቀርባል:: “Although the author of this letter calls himself ‘Simon Peter, a servant and apostle of Jesus Christ’, and makes reference to his being present at the transfiguration of Jesus Christ. several features of its style and contents have led nearly all modern scholars to regard it as the work of an unknown author of the early second century who wrote in Peter’s name.”

መርፌው ገና ከጅምሩ ጴጥሮስ ነው የፃፈው ሲል በመዋሸት በጴጥሮስ ስም የፃፈው ይህ የማይታወቅ ፀሀፊ ስለ መፅሀፍት መለኮታዊነት ‘ከሁሉ በፊት ይህን ልታውቁ

ይገባቹሀል፣ መፅሀፍ ያለው የትንቢት ቃል ሁሉ ማንም ሰው በገዛ ራሱ መንገድ ሚተረጉመው አይደለም ምክንያቱም ትምቢት ከእግዚአብሄር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የተናገሩት እንጂ ከቶ በሰው ፍቃድ አይደለም (2ጴጥ 2፡ 20-21)’ ቢልም እንኳን ሌሎቹን መፅሃፍት ሊያድን ለራሱ ውድቅ ከመሆን የዘለለ ቦታ የለውም ሲል ያብራራል።

ሌላው መርፌው መፅሀፍ ቅዱስ በመንፈስ አለተጻፈም ለማለት የሚያቀርበው በእየጊዜው በተጨመሩና በተቀነሱ ወሳኝ ቃላት እንዲሁም በጥንቶቹና አሁን ባሉት መፅሃፍተ ቅዱሳን ያለው ልዩነት ነው። በመሆኑም የትኛውም አይነተት ንባብ የሚያመጣው በማኑስክሪፕቶች ላይ የሚታየው የትርጉም ለውጥ የመፅሀፍ ቅዱስ ተአማኒነትን ዜሮ ያደርገዋል ወይም አንዱ እውነተኛ ሌላውን ሀሰተኛ ያስብለዋል። ስንት ትውልድ በዚህ የሀሰት ትምህርት መተታለሉን ያስብና ይህ ሆኖ ሳለ በጥንታዊ ፅሁፎች ላይ ያለው የንባብ ልዩነት በክርስትና ዶግማ ላይ ለውጥ አላመጡም የሚሉ ተምረው ያልተማሩ ሚሽነሪዎችን አይቼ በጣም አዝኛለው ይለናል እኔም አዝናለሁ።

፪ኛ፦ ተመሳሳይ ታሪክ ላይ የታየ ተቃርኖን በተመለከተ

መርፌው እንዳለው በተለያዩ ጊዜያት ተመሳሳይ ትረካ አንበን ከሆነ ተመሳሳይ መስሎን እንዲሁ በዝምታ ልናልፈው እንችላለን እኔም ቀደም ብየ ተቃርኖዎችን በጥቂቱም ቢሆን ስዘረዝር የሚከተለውን አላስተዋልኩትም ነበር። እውነት ነው በመንፈስ ቅዱስ የተፃፈ ፅሁፍ ተቃርኖ ሊኖረው አይገባም። ይህን በመንፈስ ሽፋን የተጻፈው ወንጌል ውስጥ ተመሳሳይ ታሪክ ግን ነጭ ተቃርኖን መመልከት ከጀመርን ውለን አድረናል ይልና ለምሳሌ ማተዮስ 19፡17 እና ማርቆስ 10፡18ን ያነጻጽራል።

ማት 19፡ 17 “ከዛም አንድ ሰው ወደ እየሱስ ቀርቦ መምህር ሆይ የዘላለምን ህይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ልስራ ሲል ጠየቀው። እየሱስም ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ መልካም የሆነ አንዱ ብቻ ነው"

ማር 10፡ 18 ። " አንድ ሰው ወደ እርሱ እየሮጠ መጣ በፊቱም ተንበርክኮ ቸር (መልካም) መምህር ሆይ የዘላለምን ህይወትን ለመውረስ ምንማድረግ ይገባኛል አለው እየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት ለምን ቸር ትለኛለህ ከአንዱ እግዚአብሄር በቀር ቸር የለም"

ማትዮስ ላይ ሰውየው ስለ መልካም ስራ ሲጠይቀው እየሱስ መልሱ ለምን ስለመልካም ስራ ትጠይቀኛለህ መልካም አንዱ ብቻ ነው ሲል የመለሰለት። ማርቆስ ላይ ግን ሰውየው ስለመልካም ስራ ሳይሆን የጠየቀው እየሱስ ራሱን ነው መልካም ያለው። እየሱስም ምላሹ ለምን መልካም ትለኛለህ የሚል ነው። እንጂ ለምን ስለ መልካም ስራ ትጠይቀኛለህ የሚል አልነበረም። ሁለቱ ሲመዛዘኑ አንዱ ፀሀፊ

Created in Master PDF Editor

የማስታወስ ችሎታው ደካማ ነው ታሪክን በማዛባት ይታወቃል ማለት ነው በመሆኑም ዘገባው ውድቅ ነው ቢሆንስ ሲል መርፌው ይመክራል።

፫ኛ፦ የእየሱስ ሸወዳ በተመለከተ

ዮሐንስ 7፡ 8-14 እንዲህ ይነበባል *“እናንተ ወደዚህ በዓል ውጡ፤ እኔስ ጊዜዬ ገና ስላልተፈጸመ ወደዚህ በዓል ገና አልወጣም። ይህንም አላቸውና በገሊላ ቀረ። ወንድሞቹ ግን ወደ በዓሉ ከወጡ በኋላ በዚያን ጊዜ እርሱ ደግሞ በግልጥ ሳይሆን ተሰውሮ ወጣ። አይሁድም። እርሱ ወዴት ነው? እያሉ በበዓሉ ይፈልጉት ነበር። በሕዝብም መካከል ስለ እርሱ ብዙ ማንጐራጐር ነበረ፤ አንዳንዱም። ደግ ሰው ነው፤ ሌሎች ግን አይደለም ሕዝቡን ያስታል ይሉ ነበር። ዳሩ ግን አይሁድን ስለ ፈሩ ማንም ስለ እርሱ በግልጥ አይናገርም ነበር። አሁንም በበዓሉ እኩሌታ ኢየሱስ ወደ መቅደስ ወጥቶ ያስተምር ነበር።”*

ተመልከት ይላል መርፌው <<ተመልከት እየሱስ ደቀመዛሙርቱን ጊዜዬ ስላልደረሰ ወደ በአሉ አልሄድም ብሎ ሸውዷቸው ሲያበቃ ተደብቆ ወደ በአሉ መሄዱ በጣም ይገርማል። አትወሽ የሚለውን የአስርቱ ትእዛዛትን የዘነጋው ይመስላ። እንደ ወንጌሉ እየሱስ መሄዱ እንዳይታወቅበት በስውር መሄዱ በውሸት ያስከስሰዋል። ተመልከት የክርስትና ጥንታዊ የተባሉ ፅሁፎች ላይ ብረዛ እና ክለሳ ሲያስተናገዱ ነበር ማለት ነው። እናም እየሱስን በውሸት የሚፈርጅ ይህ ፀሀፊው የማይታወቅ ወንጌል እንዴት በመንፈስ ቅዱስ ሊፃፍ እንደቻለ መንፈስ ስለሌለብኝ መሰለኝ ሊገባኝ አልቻለም። ወደፊትም አይችልም።>>

፬ኛ፦ የትንቢት ማዛባት በተመለከተ

ማርቆስ ወንጌል 1፡2 እንዲህ ቢል አይገርምም “በነብዩ ኢሳያስ እንዲህ ብሎ ተፅፏል መንገድህን ሚያዘጋጅ መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ" ይህን ቃል በቃል ማንም በኢሳያስ መፅሀፍ ውስጥ ሊሳየን አይችልም። ይህ አንቀፅ ቃል በቃል ሚገኘው ኦሪት ዘፅአት 23፡20 ላይ ነው። ሙሴ ነብይ ስለሆነ አንቀፁ ችግር የለውም ሲሉ ከችግር ለመውጣት የሚያደርጉትን ተራ ሙከራ አይተናል ይህ ግን አያስኬድም። መርፌው እንዳስረዳን ማርቆስ ትንቢቱን ቢያስታውሰውም ነብዩ ግን ተምታቶበታል። ማርቆስ በደፈናው በመፅሃፍ እንዲህ ተብሎ ነበር ማለት ነበረበት።

፭ኛ፦ የስላሴ አስተምሮ እና ጥንታዊ ፅሁፎች

መርፌው ከ1611 ኪንግ ጀምስ ቅጂ 1ኛ ዮሐንስ መልእክት 5፡7 እንዲህ የሚል ቃል በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ቢጨምር አይገርምም ይላል። "በሰማይ ሶስት አሉ አብ፣ ቃልና መንፈስ ቅዱስ ሶስቱም አንድ ናቸው" እኔ አርዮስ የምጠቀምባቸው ቅጂዎች

Created in Master PDF Editor

1ኛ ዮሐንስ መልእክት 5:7-8 ግን “መንፈስም እውነት ነውና የሚመሰክረው መንፈስ ነው። የሚመሰክሩት መንፈሱና ውኃው ደሙም ሦስት ናቸውና፤ ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ።” ይላሉ። እንደ መርፌው ሀተታ ይህ የኪንግ ጀምስ ቅጂ ቃል ከአራተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ባሉት የመፅሀፍ ቅዱስ መዛግብት ውስጥ እንዳለ ምሁራን ነግረውናል። ግን ከዛ በፊት በተገኙት መዛግብት ላይ የለም። በእነዚህ በአራተኛው ክፍለ ዘመን መዛግብት ላይ የሚገኘው ንባብ ከዛ በፊት ባሉት መዛግብት ግን ይህ ንባብ አይገኝም። እናስ? ይህ አንቀፅ ሆን ተብሎ ሂሳብ የማይፈታውን ስላሴ(1=3) ለማፅደቅ የተጨመረ ነው ይላል ተንታኙ መርፌው።

ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ጦማሪው ይቀጥላል “ነገረ ስላሴ እኩል ስልጣን ያላቸውን ሶስት አማልክትን ታስተምሩ ዘንድ ሽፋን ለማግኘት እናንተው ክርስትያኖች የጨመራቹሁት መሆኑ ነው። ምንም ቢጎረብጣችሁም ግን በኋላ ላይ የጨመራችሁት በመሆኑ ጥንታዊ ፅሁፉን ሚተቹ ምሁራን ከመፅሀፋችሁ ውስጥ አሽቀንጥረው ጥለውታል እናም እስካሁን ድረስ የስላሴን ፅንሰ ሀሳብ ሊያራምድ የሚችል አንድም የአዲስ ኪዳን አንቀፅ የለም” ሲል መርፌው ያብራራል፣ መርፌው ይህን ይበል እንጅ ስለ ሚስጥረ ስላሴ ከዚህ አውዛጋቢ ጥቅስ ውጭ ብዙ ምንባቦች አሉ። መርፌው ሙስሊም ስለሆነ ወደ መደምደሚያው ቢገሰግስም ክርስቲያኖች ብዙ መጥቀስ ይችላሉ፣ ፍየል ወድያ ቅዝምዝም ቢሆንም ነገሩ።

፭ኛ፦ ጥንታዊ ፅሁፎች እና አዲስ ኪዳን

“ይህ በብዙ መስመር በማይታወቅ ሰዎች የመጣው አዲሰ ኪዳን ወደ አምስት ሺ ጥንታዊ መዛግብትም ቢኖሩትም አንድም ያሁኑ አዲስ ኪዳን ከ አምስት ሺውም ጋር አልተመሳከረም። ሁለትም አምስት ሺውም ኢስናድ (ማስረጃ) አልባ ነው። ሶስትም እነዚህ አምስት ሺ መዛግብት አብዛኛዎቹ ፀሀፊያቸው አይታወቅም አራትም በመዛግብቱ ላይ ሁነኛ ለውጥ ተደርጎባቸዋል። አምስትም አምስት ሺውም አይስማሙም። ስድስትም የአምስት ሺው ኦርጅናል የለም፣ ኮፒውም የለም፣ የኮፒውም ኮፒ የለም። ከዛ በኋለ የመጡ ፅሁፎች ላይ የተሰተዋለው ልዩነት በመንፈስ የሚለውን የክርስትና መሰረትን መሰረቱ እንደተመታ ቤት ያፈራርሰዋል። በመሆኑም ይህ በብዙ ማኑስክሪፕቶች ላይ የተስተዋለው ልዩነት እንዲሁም 80 እስከ 90 ፐርሰንት ማኑስክሪፕቱ በውሸታም በቀጣፊነት መፈረጅ እንዲሁም በሁሉም ላይ ያለው ልዩነት መፅሀፍ ቅዱስ ዘገባው የተለያየ እንዲሆን”መደረጉን የሚጠቅሰው መርፌው ጥንታዊ ፅሁፎች እና የዛሬዎቹ ቅጅዎች ሊታረቁ በማይችሉ ስብከቶች የተሞሉ መሆናቸውን አስረድቷል።

Created in Master PDF Editor

፯ኛ፦ ኦርጅናል ፅሁፉ መቼም አይመለስም

መርፌው ለምን ለሚለው ጥያቄ ያነሳና ከሙህራን አገኘሁት የሚለውን መልስ ይሰጣል። የምሁራኑ የመጀመሪያ ምላሽ ፅሁፉ ስለሌለ ይሉናል። የሆነ ሆኖ ኦርጅናሉን ትክክለኛ ፅሁፍ እስከ ትንሳኤ ድረስ መመለስ እንደማይቻል የግሪኩን አዲስ ኪዳን አርቃቂ እና አዘጋጅ ኮሚቴ ውስጥ አንዱ የሆነው ዴቪድ ፓርከር እንዲህ ቢል አይገርምም ሲል የአርቃቂውን ንግግሩን በቀላል እንግሊዘኛ ያስነብበናል። *"The text is changing. Every time that I make an edition of the Greek New Testament, or anybody does, we change the wording. We are maybe trying to get back to the oldest possible form but, paradoxically,* ***we are creating a new one.*** *Every translation is different, every reading is different, and although there's been a tradition in parts of Protestant Christianity to say there is a definitive single form of the text, the fact is you can never find it. There is never ever a final form of the text"* ከመርፌው ሀተታና ከሌሎች የስነ መለኮት ሙህራን እንደምንረዳው ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ የመጽሐፍ ቅዱስ መፅሀፍት ደራሲ የለሽ ወይም ሰዋዊ ፍልስፍናዎችና ድርሰቶች መሆናቸውን መዘንጋት እንደለለብን ነው። ልክ እንደማገኛውም የጥንት ትውፊቶች እና አፈ ታሪኮች ከትክክለኛ ይልቅ እጅግ ምናበዊ እና ልብ አንጠልጣይ እዳንዴም ሆረር የሆኑ ልብ ወለድ መፅሀፍት እንደሆኑ ይሰማኛል። አብሶም መፅሀፍቶቹ እርስ በእርሳቸው ይኮራረጃሉ። በዙ ፀሀፊዎች አንደሚሉት እኔም እንደተረዳሁት መፅሀፍ ቅዱስ በመካከለኛው ምስራቅ እና በአካባቢው ከነበሩ አፈታሪኮች እና እምነቶች የተወረሰ ነው። የክርስቶስን ታሪክ ከልደት እስከ ሞት የደገሙት ከክርስቶስ በፊትም በኋላም ብዙ ተነስተዋል፣ በተለይ የጥንቶቹ አማልዕክት አወላለድ፣ አኗኗር፣ ስብከትና አሟሟት ከወንጌል ጋር መመሳሰሉ መጽሃፍ ቅዱስን በአይነ ቁራኛ ለሚመለከቱት ትዝብትን ይፈጥራል። ይህ የታሪክ መኮራረዥ በቀደምት የሞሶፖታሚያ እምነቶችም ተንጸባርቋል። "The gods of early Mesopotamian civilization were much like their ancestors, the gods of chiefdoms and of hunter-gatherer societies" ነበር ያለውRobert Wright. የአሁኖቹም ከሞሶፖታሚያና ከአካባቢው አማልዕክት ብዙ ኮርዥዋል።

IV. **በእግዚአብሔር መንፈስ የተመሩ (የተነዱ) ቅዱሳን ሰዎች የጻፉት በመሆኑ፡-** መጽሐፍ ቅዱስ የተለዩና የተመረጡ ሰዎች የጻፉት ቅዱስ መጻሕፍት ነው። የእግዚአብሔርን የቅድስና ጥሪ ሰምተው፣ በበጉ ደም ተዋጅተው፣ በፈቃዱ ተመርተውና በኑሮ ሥርዓታቸው አክብረውት ያረፉ ሰዎች ቅዱሳን ይባላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ባከበራቸው ቅዱሳን ያጻፈው መጽሐፍ ነው። 2ኛጴጥ. 1:20። መጽሐፍ ቅዱስ በተመረጡ ጣቶች የተጻፈ ምርጦችንም የሚያፈራ አምላካዊ ቃል ነው።

Created in Master PDF Editor

መልስ፦ አገኘሁ አሰግድ የተባለ የሸገር ብሎግ አምደኛ መጽሃፍ ቅዱስን በእስራኤላውያን ፍቅር ያበደው መፅሐፍ ይለዋል። እልፍ ምሳሌ መጥቀስ ቢቻልም ጦማሪው የጠቀሰው ሉቃስ 13፤33/ ዘዳግም 14፤12 እና ማቴ 10፤5 ብቻ ነው። በእውነተኛውና በቅዱሱ እግዚአብሔር መንፈስ እየተነዱ ሳይሆን በብሔርተኝነት እየተነዱ የጻፉት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ሉቃስ 13፤33 ላይ "ነቢይ በእየሩሳሌም ሊሞት አይገባውምና" ይለናል። ለምን? እስራኤል ምንድን ናት? ሌላው ምንድን ነው?የክርስቶስ ዘር ከእስራኤላውያን ይመዘዛል። በዘሩ እስራኤልን እንጂ ቀሪውን ዓለም አይወክልም ማለት ነው።ዘዳግም 14፤12 እንዲህ ብሎ ሆሆይ ያስብለናል፤"የበከተውን ሁሉ አትብሉ፤ ይበላው ዘንድ በሀገርህ ዘንድ ለተቀመጠ መፃተኛ ወይም ለባዕድ ስጠው፤ አንተ ለአምላክ ለእግዚኣብሔር የተቀደስክ ሕዝብ ነህና"ምን ማለት ነው? ሌሎች የበከተውን ይብሉ የሚል ምን ዓይነት ዘረኛ አምላክ ነው? ለእግዚሐብሔር የተቀደስክ ሕዝብ ነህ ማለትስ ምን ማለት ነው? ሌላው የተረገመ ነው ማለት ነው? አስቂኝ ኦኮ ነው። ማቴ 10፤5 ላይም ይህ ተፅፏል፤"በአህዛብ መንገድ አትሂዱ፣ ወደ ሳምራዊያን ከተማም አትግቡ። ነገር ግን <ከእስራኤል ወገን> ወደ ጠፉ በጎች ሂዱ። ሄዳችሁም መንግስተ ሰማያት ቀርባለች እያላችሁ አስተምሩ።" ይሄ እንግዲህ እየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለስብከት ዘመቻ ሲያሰማራ የተናገረው ነው። በድጋሜ በዚሁ በማቲዎስ ክፍል ላይ አንዲት "ከነዓናዊት ሴት" ክርሰድቶስን እየተከተለችው ልጇን እንዲያድንላት ትማጠነዋለች። እሱ ግን ሊያዳምጣት አልወደደም። ደቀመዛሙርቱ ሲጠይቁት፤ "<ከእስራኤል ቤት> ወደ ጠፉ በጎች ብቻ እንጂ ወደ ሌላ አልተላኩም" ይላቸዋል። በእየሱስ ስም ያስባላል ይላል አገኘሁ አሰግድ"ይህ ምን ማለት ነው? እሺ ይሄም ይሁን፣ ቀርባ ስትሰግድለት ምን አላት? <የልጆችን እንጀራ ወስዶ ለውሾች መስጠት መልካም አይደለም አላት> እግዜር ያሳያችሁ እንግዲህ፣ እስራኤላውያንን ልጆች ሌሎቹን ውሾች እያለ ነው ዓለምን ሊያድን መጣ የተባለው እየሱስ ክርስቶስ?" ይለናል ታዛቢው አገኘሁ አሰግድ።

(አገኘሁ አሰግድ፣ http://www.shegerblogs.com/author/agegnehu/)

V. **ዘመን የማይለውጠውና የማይሽረው በመሆኑ፦** ብዙ መጻሕፍትን ዘመን ሽሯቸዋል፤ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ዘመን ተሻጋሪ ነው። በዘመን ብዛት የተረሱ በርካታ መጻሕፍት አሉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ግን በየዘመናቱ እጅግ ተፈላጊ መጽሐፍ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የተረሳውን የሚያስታውሰው አምላክ ቃል በመሆኑ አይዘነጋም፤ በየጊዜው ተሽሎ ለሚነሳው ትውልድ የሕይወት ሥርዓት መሪ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ለዘላለም ጸንቶ ይኖራልና። ኢሳ. 40፡8።መጽሐፍ ቅዱስ በየዘመናቱ የገጠሙትን የአመለካከት ጽንፎችና የኢ-አማንያንን ጦርነቶች አልፎ

በሺዎች የሚቆጠሩ ዓመታትን ያስቆጠረው አምላካዊ ቃል ስለሆነ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ብርቱ ተቃውሞዎችን አልፎ ለዚህ ትውልድ የደረሰው እግዚአብሔር በረዳቸው የታመኑ ምስክሮች መስዋእትነት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በዘመን የማይሻርና በትውልድ የማይሻሻል ቅዱስ መጽሐፍ ነው፡፡መጽሐፍ ቅዱስ ከሁሉም መጻሕፍት በላይ የእድሜ ባለጠጋ (አረጋዊ) ነው፡፡

መልስ፡ እውነት ለሁሉ (http://www.ewnetlehulu.org) በተባለ ድህረ ገጽ እንዳገኘሁትከእስልምና ወደ ክርስትና ሀይማኖቱን የቀየረው ፉአድ መስሪ ስለመጽሃፍ ቅዱስ በተለይም ስለ ኢንጅል ስለሚባለው የክርስቶስ ወንጌል ዘመን የማይሽረው ያልተበረዘ ስለመሆኑ ምስክርነት ሲሰጥ *“ኢንጂል እንደረተበረዘ የሚናገሩ ብዙ ሰዎች ስለ መነሻውና መልእክቱ ያላቸው ግንዛቤ የተሳሳተ ነው፡፡ አባባላቸው በጥናትም ሆነ በአምክንዮአዊ ማስረጃ የተደገፈ አይደለም፡፡ ካለማወቃቸው የተነሳ ብዙዎችን ከእውነተኛ መንገድ ወደተሳሳተ መንገድ መርተዋል፡፡”* ይላል፡፡ፉአድ መስሪ ኢንጅል አልተበረዘም ለማለት ካቀረባቸው ምክንያቶች ዋነኛው <ከሃያሉ ፈጣሪ በላይ ኃይል ያለው የለም> እናም የፈጣሪን ቃል የሚለውጥ ሀይል የለም ሲል ይከራከራል፡፡ ማንኛውም ስለ መጽሃፍ ቅዱስ መበረዝ ማወቅ የሚፈልቅ የተለያዩ ቤተ-ክርስቲያናት የሚጠቀሙባቸውን መጽሃት ማወዳደር ነው፡፡ለፉአድ መስሪና ተመሳሳይ ሃሳብ ላላቸው የምመክረው ይህንኑ ነው፡፡

በእርግጥ መፅሐፍ ቅዱስ በሰዎች ተበርዟልን? ተበርዟል ብቻ ሳይሆን አሁን ያሉት ቅዱሳን መፅሀፈት ተሻሽለው ታርመው ታርመው ‘አሰር ውሀ’ እንድሆኑ እረዳለሁ፡፡ አባ ገብረ ሃና ቀልደኛ ሰው እንደነበሩ በታሪክ ሰምቻለሁ ቢሆንም ከእረኝነት ህይወቴ ጀምሮ የአባ ገብረ ሃና ትረቶች እና ቀልዶች እየተባሉ የሰማኋቸው ሁሉ አለቃ የተረቷቸው ስለመሆኑ እጠራጠራለሁ፡፡ ለምን ቢባል አንደኛ አለቃ በወቅቱ ትረቶች እና ቀልዶች አልጻፉም አላጻፉም ስለዚህ ካላቸው ተወዳጅነት አንጻር ሰዎች የሰሟቸውን እና እራሳቸው የፈጠሩትን ቀልድ እንኳ በአለቃ ስም ሊያስስተላልፉት ይችላሉ፡፡ ሁለተኛ ቀልዶቹ በአለፉት ብዙ አመታት ሲጨመረባቸው፣ ሲቀነስባቸው እና ሲሻሻሉ ቆይተው ከዚህ በመድረሳቸው ያልተበረዙትን የአለቃ ቀልዶች ማወቅ ከባድ ነው፡፡ ሦስትኛ በሀገራችን ከአባ ገብረ ሃና ውጭ ቀልደኛ የለም እንዴ አንዳንዴስ ይህ ሰው ምናባዊ ይመስሉኛል፡፡ አሁን በአባ ገብረ ሃና ቦታ የሀይማኖት መስራቾችን ትምህርት ገምግሙት፡፡ ፍርዱን ለእናንተ ትቻለሁ፡፡

VI. **ለሁሉም የሚናገር መጽሐፍ ስለሆነ፡-** መጽሐፍ ቅዱስ ድሀና ሀብታም፣ የተማረና ያልተማረ፣ ትንሽና ትልቅ ሳይልሁሉን በየአድራሻው ይናገራል፡፡ ፊት አይቶ የማያደላው እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የላከው የፍቅር ደብዳቤ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስማንነትን በግልጥ በስልጣን ቃል ይናገራል፡፡

Created in Master PDF Editor

መልስ፦ የፍቅርደ ብዳቤ???

WARNING: from zen of zero
This “holy book” is bad.
It will mess with your mind.
It should never be taken seriously.
If taken seriously, severe mental damage will occur.
Keep this book out of reach of children and those who are childish.
As antidotes (cures), require extensive study in logic, science, and critical thinking.

VII. **የሚያነቡትንና የሚሰሙትን የሚባርክና የሚያንጽ በመሆኑ፡-** በዓለማችን አንባቢያንን የሚያንጹ መጻሕፍት ሊኖሩቢችሉም እንኳ ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ ውስጣዊ ማንነትን የሚሠራ መጽሐፍ የለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ የሕይወት መምህር ነው፡፡ አንባቢያንና ሰሚዎች ከመታነጽ አልፈው የሚባረኩበትም መጽሐፍ ነው፡፡ መዝ. 22፡4፣ 2ጢሞ. 3፡17፣ ራዕ. 1፡3፡፡መጽሐፍ ቅዱስ የሚያንጻቸውና የሚባርካቸው የታላቅነትን ምስጢር በማወቅ ስኬትን ይጎናጸፋሉ፡፡ ንግሥት ቪክቶሪያ ‘የእንግሊዝ አገር ታላቅነት ምስጢሩ መጽሐፍ ቅዱስ ነው’ በማለት መጽሐፍ ቅዱስ የታላቅነትን ምስጢር እንደሚያጎናጽፍ መስክራለች፡፡

መልስ፦የሚገርም አባባል ነው “በዓለማችን አንባቢያንን የሚያንጹ መጻሕፍት ሊኖሩ ቢችሉም እንኳ ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ ውስጣዊ ማንነትን የሚሠራ መጽሐፍ የለም፡፡” ወዘተ. እንዴ መጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ምንድን ነው የተጻፈው በተለይ በተለይ አሮጌው ኪዳን ላይ የሚባርክና የሚያንጽ ማግኘት አይከብድም?፡፡ መጽሃፍ ቅዱስ ብቻ አይደለም ሌሎችም ቅዱሳን መጽሃፍት እንዲሁ ናቸው፣ ብዙዎቻችን የምናውቀው ቄሶች መርጠው በማይገባን ቋንቋ የሚያነቡልንን ስለሆነ አይፈረድብንም፡፡ የተጻፉትን ምናባዊ ትዕዛዛት፣ የተፈጸሙትን ጭካኔ የተሞላባቸው ታሪኮች ሳስብ የመጻፉ ደግነት፣ አናጺነትና ባራኪነት አልታየኝ አለ፡፡ ሁሉንም ቅዱሳን መጽሃፍት የተቸው ኦሾ ምን ነበር ያለው፡፡ “Why should God write these things? Every scripture gives intrinsic evidence that they are written by men, and very stupid men, primitive men. The so-called holy scriptures are not even to be counted as good literature they are childish, crude, ugly. But because they are written in languages which are dead... and some are in languages which have never been in use by common people. --- The scriptures are man-made, the statues of God are man-made, the temples and churches are man-made, but thousands of years of conditioning has given them a certain sacredness, holiness. And there is nothing sacred in them, nothing holy in them.” (Zarathustra: A God That Can Dance፣ 267)

VIII. የሁሉ ምንጭ በመሆኑ፡-መጽሐፍ ቅዱስ የሃይማኖትና የስነ-ምግባር፣ የኪነጥበብና የስነ-ጽሁፍ፣ የሥራ-አመራርና የፍትሕ፣ የግብርናና የጤና፣ የእውነተኛ መጻሕፍትና የእውነተኛ ትምህርቶች ምንጭ ነው።

መልስ፡-በመጽሃፉ በየትኛውም መንገድ ለየትኛውም ዘርፍ የሚጠቅም እዚ ግባ የሚባል ማስረጃ የለም። መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጅ በሕይወቱ ውስጥ ሊጠቀምበት የሚችል መጽሐፍ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ የእውቀትና የምርምር መጽሐፍ አይደለም፣ ለስነ ምግባርና ሰብዓዊት ልዕልና እገዛ አያደርግም። ሳይንስና ቴክኖሎጅ ማበብ አያገለግልም። አንድ የሙስሊም ሙህር (ኡስታዝ ሐሰን ታጁ) ምን ነብር ያለው "ሳይንስና መጽሐፍ ቅዱስ እንደ እሳትና ጭድ የማይስማሙ ተጻራሪ ነገሮች ናቸው።" በትክክል ገልጾታል። የዕለት ተዕለት ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሥራዎቻችንን ለመሥራት እገዛ አያደርግም።መጽሐፍ ቅዱስ የሃይማኖትና የስነ-ምግባር፣ የኪነጥበብና የስነ-ጽሁፍ፣ የሥራ-አመራርና የፍትሕ፣ የግብርናና የጤና፣ የእውነተኛ መጻሕፍትና የእውነተኛ ትምህርቶች ምንጭ ነው ለሚሉት Lemuel K. Washburn በ1911 ባሳተመው Is the Bible Worth Reading and Other Essays በሚል መጽሃፉ እንዲህ ብሎ ነበር "No! There is absolutely no information in the Bible that man can make any use of as he goes through life. The Bible is not a book of knowledge. It does not give instruction in any of the sciences. It furnishes no help to labor. It is useless as a political guide. There is nothing in it that gives the mechanic any hint, or affords the farmer any enlightenment in his occupation. If man wishes to learn about the earth or the heavens; about life or the animal kingdom, he has no need to study the Bible." በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥበብ ያዘሉ አንዳንድ ቃሎች መኖራቸውን አልክድም የሚለው ጽሃፊው Lemuel K. Washburn ዘፍጥረትን፣ ዘፀአትን፣ ዘኁልቊ፣ መጽሃፈ ነገስትን፣ መዝሙረ ዳዊትን ወይም ወንጌላት በማንበብ በህይወት ላይ እውነተኛና ሀቀኛ ኑሮ ለመመስረት ይጠቅማልን? ይላል።

"መጽሐፍ ቅዱስ እኮ፣ የኃጢአታችን ውጤት እንጂ የጽድቃችን ውጤት አይደለም፣ አርፈን ገነት ብንቀመጥ አንድ ሺህ ገጽ መጽሐፍ አይጫንብንም ነበር፣ አዳምና ሔዋን ተንቀዠቅዠው ከገነት ከወጡ በኋላ ነው፣ አንድ ሺህ ገጽ ጉዳችንን የሚዘረዝር ኀጢአት ተዘርዝሮ፤ እርሱማ የጉዳችን ማኑዋል ነው፣ ጠባያችንን አይገልጥም፤ ለዚህ ነው እኔ የኀጢአት ውጤት ነው፣ በነገራችን ላይ ብሉይ ኪዳንም ኾነ አዲስ ኪዳን፣ ቁርአንም ኾኑ ሌሎቹም መጻሕፍት በጠቅላላ ከገነት ከተባረርን በኋላ ለስደተኛ የተጻፉ መጻሕፍት ናቸው፤ ስደተኛውን ለማረጋጋት የተጻፉ መጻሕፍት ናቸው እንጂ፣ ማኑዋልማ ሊኾን አይችልም፤ በግል ልታወራኝ ትችላለህ፣ እኔ የገባኝ ይህ ነው" መጋቢ አዲስ እሸቱ።

Created in Master PDF Editor

IX. መፅሀፍ ቅዱስ የመሬት ቁፋሮ ሳይንቲስቶች ታሪካዊነቱንና እውነተኝነቱን ያረጋገጡለትና ታላላቅ ሰዎች ምስክርነት የሰጡት ተወዳጅ በመሆኑ

መልስ፦ በእርግጥ እንደ መፅሀፍ ቅዱስ ብዙ የተነበበ ተወዳጅ መጽሀፍ የለም። ነገር ግን መፅሀፍ ቅዱስ ብዙ መሰረታዊ ችግሮች አሉበት። ለምሳሌ:- እስር በራሱ ስምምነት የለውም ታሪኩ በአርኬወሎጅ አልተረጋገጠም፣ በርካታ ተረቶችን በውስጡ ይዟል፣ የትየሌለ ትንቢቶቹ አልተፈፀሙም፣ በተለይ ደግሞ ከመካከለኛው ምስራቅ ስልጣኔዎች የተኮረዠ ነው። ከዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እና 2 የእርስ በእርስ ግጭት እንስቶ እስከ ዮሐንስ ራዕይ ድረስ በግጭት የተሞላ ነው።

በመፅሀፍ ቅዱስ በአርኬወሎጅ መረጋገጥ ያለባቸው በርካታ ታሪኮች አሉ። ከእነዚህ ታሪኮች አንዱና ዋነኛው የኖህ ጊዜ የምድር በውሃ መጥለቅለቅ ነው። አርኬሎጅስቶች በብዙ ሚሊየን አመታት በምድር ላይ የተከሰቱትን መጥለቅለቆች አለቶችን በማጥናትና የቅሬተ አካላት እንድሜን በመለካት ነግረውናል። ነገር ግን ባለፉት 8,000 ዓመታት እንዲህ አይነት መጥለቅለቅ መከሰቱን ማረጋገጥ ሳይሆን አለመከሰትን አረጋግጠዋል። የታሪክ አጥኝዎች እንደ ሚሉትም የኖህ የጥፋት ዘመን እና የኖህ መርከብ (Noah's Ark) ታሪክ የተኮረጀው ከጊልጋሚሽ (Goilgamesh) ታሪክ ነው።

የሱመሪያኑ ንጉስ ጊልጋሚሽ ከኖህ ታሪክ ጋር ተመሳሳይ ታሪክ ጽፎ ማለፉን አርኬዎሎጅስቶች አረጋግጠዋል። ጊልጋሚሽ እንደተረከው አማልዕክት አለምን ማጥፋት ፈለጉ ግን አንድ ሰው (Hanpistim) የሚባል ግን እንዲተርፍ ተፈለገ። አማልዕክት ይህን ሰው መርከብ እንዲሰራ አዘዙት። ይህ ሰው እራሱን እና ቤተሰቦችን እንዲሁም እንስሳትን ከምአቱ ለማትረፍ መርከቡን ሰርቶ ጨረሰ። የውሃው መጎደል በሆነ ጊዜ መርከቧ በናሲር (Nisir) ተራራ አረፈች። ውሃው መጉደል እንደጀመረ ደጉ ሰው እርግቦቹን ላካቸው። የመጨረሻዋ እርግብ እንደወጣች ስትቀር ውሃው ሙሉ በሙሉ መጉደሉን አወቀ። Copy Paste ይሉብታል ይሄ ነው። የኖህን መርከብ ታሪክና የተለያዩ የመፅሀፍ ቅዱስ ታሪኮችን ከአመጣጣቸውና ከአርኬዎሎጅ ትንታኔ አንፃር ትችቱን John W. Loftus በአዘጋጀው 'The Christain Delusion' ላይ ያስፈረው Pual Tobin"Modern archaeology is no friend of the bible" ብሏል።

መፅሀፍ ቅዱስ የመካከለኛው ምስራቅ እና የሜዲትራሊያንን አካባቢ ጥንታዊ አፈ ታሪኮች ቀንጭጭቦ የያዘ ድንቅ መፅሀፍ ነው። ይህን ለመረዳት በአካባቢው ስልጣኔዎችና ስለ ፍጥረታት አፈጣጠር፣ስለስላሴ፣ ስለስደት፣ ስለጦርነት፣ ስለመስዋእት፣ ሰለንፋር ውሃ፣ ስለ በድንግልና መወለድ፣ ስለነብያትና ደቀ መዝሙራት መረጣ፣ ስለፈውስ እና ተንሳኤ የነበራቸውን አፈ-ታሪክ ማስታወስ ያስፈልጋል።

Created in Master PDF Editor

ሚስጢረ ስላሴ የክርስትና አዲስ አስተምሮ ተደርጎ ይወሰዳል፣ ነገር ግን የቆየ ባህል ነው። በህንድ ብራሊማ (Brahma)፣ ቪሽኑ (Vishnu) እና ሽቫ (shiva)፤ በግብፅ ኦስሪስ (Osiris the father)፣ ኢሲስ (Isis the mether) እና ሆሩስ (Horvs the son)፤ በግሪክ ዚወስ (Zeus)፣ ሂራ (Hera) እና አፖሎ (Appollo)፣ እንዲሁም በሌሎች ቅደመ ክርስትና የፖጋን (Pagan) ስልጣኔዎች የነገረ ስላሴ አስተምህሮ ነበር። ከክርስትና በፊት የነበሩት የነገረ ስላሴ ትምህርቶች ለአዲሱ ምስጢር ስላሴ ማሟማቂያ ነበሩ ወይም አዲሶቹ ክርስቲያኖች ቀደምት ባህላቸዋን ላለመተው ሶስት አማልዕክት አሉ የሚለውን እምነታቸው አስቀጥለዋል።

ስለ ዳይንስስ? (Dionysus) እና ክርስቶስን ማነጻጸርም ይቻላል። ዳይንስስ ከአባቱ ዚወስ (Zeus) እና ከሟች እናቱ ከሰመለ (Semele) ተወለደ። ዳይንስስ አዳኝ መምህር ሁኖ ወደ አለም ቢመጣም ተሰቅሎ ተገደለ። በመልካም ፍቃዱ ከሞተ በኋላም በክብር ተነሳ። ይህ ቅድመ ክርስቶስ ጌታ ለተከታዮቹ ስጋየን ብሉ ደሜን ጠጡ የሚል አስተምህሮ እንደነበረው ይነገራል። ክርስትናን ወደ ኋላ ተመልሶ ማጥናቱ መዘዙ ብዙ ነው። አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል።

ይህን መሰል ታሪኮችን ስታነቡ መፅሀፍ ቅዱስ ያበረከተልን አዲስ ነገር ምንድን ነው ልትሉ ትችላላችሁ። በተለይም በርካታ የስነ መለኮት ሙህራን ሳይቀር የሚሰማሙበት የመፅሀፍቱ ደራሲዎች አለመታወቅና የለየላቸው ተቃርኖዎች በመፅሀፍ ላይ ያለንን ጥርጣሬ ያንሩታል። ይህን የተረዳው ሳይንቲስት Isaac Asimov“properly read the bible is the most potent for atheism ever concived” ይላል።

የሆነ ነገር በመጽሐፉ ውስጥ ተጻፈ ማለት እውነት ነው ማለት አይደለም። ግልጽ ነው ለዘመናት እውነት የነበሩ መፅሀፍት አሁን ተረቶች ሁነዋል፤ ሐሰት መሆናቸውም ታውቋል። መጽሐፍ ቅዱስ መጻፉ ስለ እውነተኝነት መረጋገጫ ሊሆን አይችልም። በተጨማሪም ቅዱሳት መጻህፍት እርስ በርስ የሚጋጩ ናቸው። በተለያዩ ቅዱሳን መፅሀፍት ብቻ አይደለም በአንድ መፅሀፍ ብቻ ለቁጥር የሚታክቱ የተፋለሱ ጹሑፎች አሉ። ከዚህ በመነሳት መፅሀፍቱን የጻፉት ሊሳሳቱ የሚችሉ የሰው ልጆች ናቸው ቢሎ መደምደም አይከብድም። መፅሀፍቱ በአፈ ታሪኮች የተሞሉ ቢሆኑም በውስጣቸው አንዳንድ ታሪካዊ እውነቶች ሊኖሩ ይችላሉ።

Created in Master PDF Editor

X. ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም።

መልስ፦ ከሁሉም የሚያሳዝነኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ውስጣዊ ቅራኔዎች ናቸው። ለምሳሌ የክርስቶስ የትንሣኤ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዱ እጅግ ወሳኝ የሆነ ክስተት ነው። ይህን ልዩ ክስተት በተመለከተ በአራቱ ወንጌላውያን መካከል ያለው ልዩነት ያስደነግጣል። እየሱስ እንዴት እንደተያዘ ወንጌላውያን ስምምነት ላይ አልደረሱም። እዩ፦ የማቴዎስ ወንጌል 26÷46-50 እንዲህ ይላል፦ *"ተነሡ፥ እንሂድ፤ እነሆ፥ አሳልፎ የሚሰጠኝ ቀርቦአል አላቸው። ይህንም ገና ሲናገር፥ እነሆ፥ ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ይሁዳ መጣ፥ ከእርሱም ጋር ብዙ ሕዝብ ሰይፍና ጐመድ ይዘው ከካህናት አለቆችና ከሕዝቡ ሽማግሎች ዘንድ መጡ። አሳልፎ የሚሰጠውም። የምስመው እርሱ ነው፤ ያዙት ብሎ ምልክት ሰጥቶአቸው ነበር። ወዲያውም ወደ ኢየሱስ ቀረበና። መምህር ሆይ፥ ሰላም ለአንተ ይሁን ብሎ ሳመው። ኢየሱስም። ወዳጄ ሆይ፥ ለምን ነገር መጣህ? አለው። በዚያን ጊዜ ቀረቡ እጃቸውንም በኢየሱስ ላይ ጭነው ያዙት።"* ሉቃስ ወንጌል 22÷47-48 እንዲህ ይላል፦ *"ከአሥራ ሁለቱ አንዱም ይሁዳ የሚባለው ይቀድማቸው ነበር፥ ሊስመውም ወደ ኢየሱስ ቀረበ። ኢየሱስ ግን። ይሁዳ ሆይ፥ በመሳም የሰውን ልጅ አሳልፈህ ትሰጣለህን? አለው።"* የዮሐንስ ወንጌል 18÷4-9 እንዲህ ይላል፦ *"ኢየሱስም የሚመጣበትን ሁሉ አውቆ ወጣና። ማንን ትፈልጋላችሁ አላቸው። የናዝሬቱን ኢየሱስን ብለው መለሱለት። ኢየሱስ። እኔ ነኝ አላቸው። አሳልፎ የሰጠውም ይሁዳ ደግሞ ከእነርሱ ጋር ቆሞ ነበር። እንግዲህ። እኔ ነኝ ባላቸው ጊዜ ወደ ኋላ አፈግፍገው በምድር ወደቁ። ደግሞም። ማንን ትፈልጋላችሁ? ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም። የናዝሬቱን ኢየሱስን አሉት። ኢየሱስ መለሰ። እኔ ነኝ አልኋችሁ፤ እንግዲህ እኔን ትፈልጉ እንደ ሆናችሁ እነዚህ ይሂዱ ተዉአቸው አለ።"* እስኪ ፍረዱ ቢያንስ ቢያንስ በዚህ በእየቀኑ በሚታወስ ክስተት ተማሳሳይ ዘገባ ቢቀርብ ምን አለበት? አራቱ እንዲህ የተለያዩ አምስተኛው የባርናባስ ወንጌል ምን ተፅፎበት ይሆን???

እየሱስ እንዴት እንደተያዘ ወንጌላውያን ስምምነት ላይ አልደረሱም በቂ አይደለም ስለስቅለቱና አቀባበሩም ልዩነት አላቸው እዩ፦ ማቴወስ 27፡37 "ይህ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ ነው የሚል የክሱን ጽሕፈት ከራሱ በላይ አኖሩ።" ማርቆስ 15፡26 "የክሱ ጽሕፈትም። የአይሁድ ንጉሥ የሚል ተጽፎ ነበር።" ሉቃስ 23፡38 "ይህ የአይሁድ ንጉሥ ነው ተብሎ በግሪክና በሮማይስጥ በዕብራይስጥም ፊደል የተጻፈ ጽሕፈት ደግሞ በእርሱ ላይ ነበረ።" ዮሀንስ 19፡19 "ጲላጦስም ደግሞ ጽሕፈት ጽፎ በመስቀሉ ላይ አኖረው፤ ጽሕፈቱም። የአይሁድ ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ የሚል ነበረ።"

ማቴዎስ (ማቴዎስ 27 57-60) ሲዘግብ "በመሸም ጊዜ ዮሴፍ የተባለው ባለ ጠጋ ሰው ከአርማትያስ መጣ፥ እርሱም ደግሞ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነበረ፤ይኸውም ወደ

Created in Master PDF Editor

ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው። ጲላጦስም እንዲሰጡት አዘዘ። ዮሴፍም ሥጋውን ይዞ በንጹሕ በፍታ ከፈነው፥ ከዓለት በወቀረው በአዲሱ መቃብርም አኖረው፥ በመቃብሩም ደጃፍ ታላቅ ድንጋይ አንከባሎ ሄደ።” በሐዋርያት ሥራ ውስጥ **በተለያዩ ሰዎች ተወስዶ ተቀበረ** ይላል። (ሐዋርያት ሥራ 13 27-29) ክርስቲያኖች የቱ ነው ትክክል?

ሌላው የተምታታ ትረካ በማቴዎስ 28፣2-5 በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ መግደላዊት **ማርያምና** ሁለተኛይቱ **ማርያም** መቃብሩን **ሊያዩ** መጡ። እነሆም፥ የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ። መልኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ። ጠባቆቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ እንደ ሞቱም ሆኑ። መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው። እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና አላቸው። በተጨማሪም በማርቆስ (16፣5) ወደ መቃብሩም ገብተው ነጭ ልብስ የተጎናጸፈ (አንድ) **ጎልማሳ** በቀኝ በኩል ተቀምጦ አንደዩ ቢተረክልንም ሉቃስ (24፣4)እነርሱም በዚህ ሲያመነቱ እነሆ **ሁለት ሰዎች** (መላእክት ለማለት ይመስለኛል) የሚያንጸባርቅ ልብስ ለብሰው ወደ እነርሱ ቀረቡ ይለናል። ሉቃስ ብቻ አይደለም ዮሀንስም በ20፣11-12 **ማርያም እያለቀሰች** ከመቃብሩ በስተ ውጭ ቆማ ነበር። ስታለቅስም ወደ መቃብር ዝቅ ብላ ተመለከተች፤ **ሁለት መላእክትም ነጭ ልብስ ለብሰው** የኢየሱስ ሥጋ ተኝቶበት በነበረው አንዱ በራስጌ ሌላውም በእግርጌ ተቀምጠው አየች በማለት **የሴቶቹን ቁጥር** በአንድ ቀንሶ **የመላእክትን ቁጥር በአንድ ጨምሮ** ይነግረናል። ወዳጆቸ የቱ ነው ትክክል?

ግርም የሚለው የሴቶቹና የሽቶው ጉድይ፦ ማርቆስ 16:1 “ሰንበትም ካለፈ በኋላ መግደላዊት ማርያም የያዕቆብም እናት ማርያም ሰሎሜም መጥተው ሊቀቡት ሽቱ ገዙ።” ሉቃስ 23:55-56 “ከገሊላም ከእርሱ ጋር የመጡት ሴቶች ተከትለው መቃብሩን ሥጋውንም እንዴት እንዳኖሩት አዩ። ተመልሰውም ሽቱና ቅባት አዘጋጁ። በሰንበትም እንደ ትእዛዙ ዐረፉ።” ሉቃስ 24:1 “ነገር ግን ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው ከእነርሱም ጋር አንዳንዶቹ ወደ መቃብሩ እጅግ ማልደው መጡ።” ማቴወስ 28:1 “በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ።” ማርቆስ 16:1 “ሰንበትም ካለፈ በኋላ መግደላዊት ማርያም የያዕቆብም እናት ማርያም ሰሎሜም መጥተው ሊቀቡት ሽቱ ገዙ።” ማርቆስ 16:2 “ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን እጅግ በማለዳ ፀሐይ ከወጣ በኋላ ወደ መቃብር መጡ።” ዮሀንስ 20:1 “ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን መግደላዊት ማርያም ገና ጨለማ ሳለ ማለዳ ወደ መቃብር መጣች ድንጋዩም ከመቃብሩ ተፈንቅሎ አየች።”

Created in Master PDF Editor

መጨረሻ ምን ነበር ያለው? ሉቃስ 23፡46 "ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ። አባት ሆይ፥ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ። ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ።" ዮሀንስ 19፡30 "ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ። ተፈጸመ አለ፥ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ።"

ሌላ መማምታታት፦ ማቴወስ 28፡8-9 "እነሆም፥ ነገርኋችሁ። በፍርሃትና በታላቅ ደስታም ፈጥነው ከመቃብር ሄዱ፥ ለደቀ መዛሙርቱም ሊያወሩ ሮጡ። እነሆም፥ ኢየሱስ አገኛቸውና። ደስ ይበላችሁ አላቸው። እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት።" ዮሀንስ 20፡13-16 "እነርሱም። አንቺ ሴት፥ ስለ ምን ታለቅሻለሽ? አሉአት። እርስዋም። ጌታዬን ወስደውታል ወዴትም እንዳኖሩት አላውቅም አለቻቸው። ይህንም ብላ ወደ ኋላ ዘወር ስትል ኢየሱስን ቆሞ አየችው፤ ኢየሱስም እንደ ሆነ አላወቀችም። ኢየሱስም። አንቺ ሴት፥ ስለ ምን ታለቅሻለሽ? ማንንስ ትፈልጊያለሽ? አላት። እርስዋም የአትክልት ጠባቂ መስሎአት። ጌታ ሆይ፥ አንተ ወስደኸው እንደ ሆንህ ወዴት እንዳኖርኸው ንገረኝ እኔም እወስደዋለሁ አለችው። ኢየሱስም። ማርያም አላት። እርስዋ ዘወር ብላ በዕብራይስጥ። ረቡኒ አለችው፤ ትርጓሜውም። መምህር ሆይ ማለት ነው።"

አንድ ልጨምር ማርቆስ ኢየሱስ የሞተው ፋሲካ በዓል ከተከበረ በኋላ ነው ሲል (ማርቆስ ምዕ 14-15) ዮሐንስ ወንጌላዊ ደግሞ አይደለም የፋሲካን እራት ከመድረጉ በፊት ነው ይላል (ዮሐንስ ምዕ 18-19) እባካችሁ ይህም የኢዲቲንግ ችግር ነው?

XI. ብዙ ቅዱሳን ቢጽፉትም የእግዚአብሔር መንፈስ ስላለበት አንዱ ከሌላኛው ጋር አይጣረስም።

መልስ፦ እውነቱን ግን ራሱ መጽሃፍ ቅዱስ ምስክር ይሆናል። ልዩነቱና ተቃርኖው በተለያዩ ጻህፍት መጻፉ ብቻ ሳይሆን በአንድ ጽሃፊም ከምዕራፍ ምዕራፍ ይቃረናል፣ በጣም የሚገርመው በአንድ ምዕራፍ ውስጥ የተጣረሰ ሃሳብ ይታይበታል። በምንም አታድኑትም፣ ለማስተካከልም ከባድ ነው። እንደማስረጃ ሙህራኑ የነቀሷቸውን ተቃርኖዎች ከመፅሃፉ እያመሳከርኩ እንደሚከተለው እዘረዝራለሁ። እናንተም አንቧቸውና ንስሀ ግቡ፣ የአማልዕክት አምላክ<ዝግመታዊ ለውጥ> ይቅር ይላችኋል ለዚህ እኔ ምስክር ነኝ። ቢያንስ አንቡትና ተገረሙ፣ ተደነቁ ንቁም።

=ዘፍጥረት 6፡19-20 "ከአንተ ጋር በሕይወት ይኖሩ ዘንድ ሥጋ ካለው ከሕያው ሁሉ ሁለት ሁለት እያደረግህ ወደ መርከብ ታገባለህ፤ ተባትና እንስት ይሁን። ከወፍ እንደ ወገኑ፥ ከእንስሳም እንደ ወገኑ፥ ከምድር ተንቀሳቃሽም ሁሉ እንደ ወገኑ በሕይወት ይኖሩ ዘንድ ሁለት ሁለት እየሆኑ ወደ አንተ ይግቡ።ዘፍጥረት 7፡2-3 "ከንጹሕ እንስሳ ሁሉ ሰባት ሰባት ተባትና እንስት፥ ንጹሕ ካልሆነ እንስሳም ሁለት ሁለት ተባትና እንስት፥ ከሰማይ ወፍ ደግሞ ሰባት ሰባት ተባትና እንስት እያደረግህ በምድር ላይ ለዘር ይቀር ዘንድ ለአንተ ትወስዳለህ።

Created in Master PDF Editor

=ዘፍጥረት 1:20 “እግዚአብሔርም አለ። ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ፥ ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ።” ዘፍጥረት 1:24 “እግዚአብሔርም አለ። ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ፥ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትንም እንደ ወገኑ፥ ታውጣ፤ እንዲሁም ሆነ።”

= ዘፍጥረት 1:28 “እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው። ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም፤ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።” ዘሌዋውያን 12:6 “የመንጻትዋ ወራትም በተፈጸመ ጊዜ፥ ለወንድ ልጅ ወይም ለሴት ልጅ፥ የአንድ ዓመት ጠቦት ለሚቃጠል መሥዋዕት፥ የርግብም ግልገል ወይም ዋኖስ ለኃጢአት መሥዋዕት ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ወደ ካህኑ ታምጣለት።”

= ዘፍጥረት 2:18 “እግዚአብሔር አምላክም አለ። ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት።” 1ኛ ወደ ቆሮ 7:1 “ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው።” 1ኛ ወደ ቆሮ 7:9 “ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ።” 1ኛ ወደ ቆሮ 7:27 “በሚስት ታስረህ እንደ ሆንህ መፋታትን አትሻ፤ በሚስት አልታሰርህ እንደ ሆንህ ሚስትን አትሻ።”

= “የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች ባገቡ ጊዜ ልጆችን ወለዱላቸው፤ እነርሱም በዱሮ ዘመን ስማቸው የታወቀ ኃያላን ሆኑ።” የይሁዳ መልእክት 6 “መኖሪያቸውንም የተዉትን እንጂ የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁትን መላእክት በዘላለም እስራት ከጨለማ በታች እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ ጠብቆአቸዋል። እንዲሁም እንደ እነርሱ ዝሙትን ያደረጉና ሌላን ሥጋ የተከተሉ ሰዶምና ገሞራ በዙሪያቸውም የነበሩ ከተማዎች በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል።” ማር 12:25 “ከሙታንስ ሲነሡ በሰማያት እንዳሉ መላእክት ይሆናሉ እንጂ አያገቡም፥ አይጋቡምም።”

=ዘፍጥረት 32:30 “ያዕቆብም። እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ፥ ሰውነቴም ድና ቀረች ሲል የዚያን ቦታ ስም ጵኒኤል ብሎ ጠራው። ዮሀ 1:18 “መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።”

=ዘፍጥረት 14:19 “አብራም ሰማይንና ምድርን ለሚገዛ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው” መዝ 24:1 “ምድርና ሞላዋ ለእግዚአብሔር ናት፥ ዓለምም በእርስዋም የሚኖሩ ሁሉ።” ማቴ. 4:8-9 “ደግሞ ዲያቢሎስ እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ ወሰደው፥ የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ። ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው።”

=ዘፍጥረት 37:28 “የምድያም ነጋዶችም አለፉ፤ እነርሱም ዮሴፍን አንሥተው ከጕድጓድ አወጡት፤ ለእስማኤላውያንም ዮሴፍን በሀያ ብር ሸጡት፤ እነርሱም ዮሴፍን ወደ ግብፅ ወሰዱት።” ዘፍጥረት 37:36 “እነዚያ የምድያም ሰዎች ግን ዮሴፍን በግብፅ ለፈርዖን ጃንደረባ ለዘበኞቹ አለቃ ለጲጥፋራ ሸጡት።”

=ዘፍጥረት 6:3 “እግዚአብሔርም። መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም፥ እርሱ ሥጋ ነውና፤ ዘመኖቹም መቶ ሀያ ዓመት ይሆናሉ አለ።” ዘፍጥረት 11:12-13 “አርፋክስድም መቶ

Created in Master PDF Editor

ሠላሳ አምስት ዓመት ኖረ፥ ቃይንምንም ወለደ፤ አርፋክስድም ቃይንምን ከወለደ በኋላ አራት መቶ ዓመት ኖረ፥ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ፤ ሞተም። ቃይንምም መቶ ሠላሳ ዓመት ኖረ፥ ሳላንም ወለደ፤ ቃይንምም ሳላን ከወለደ በኋላ ሶስት መቶ ሠላሳ ዓመት ኖረ፥ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ፤ ሞተም።"

=ዘፍጥረት 1:31 "እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፥ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ" ዘፍጥረት 6:6 "እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥ በልቡም አዘነ።"

=መክ 10:19 "ሁሉም ለገንዘብ ይገዛል።" 1ኛ ጢሞ 6:10 "ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና"

= 1ኛ ሳሙኤል 17:49-50 "ዳዊትም እጁን ወደ ኮረጆው አግብቶ አንድ ድንጋይ ወሰደ፥ ወነጨፈውም፥ ፍልስጥኤማዊውንም ግምባሩን መታ፤ ድንጋዩም በግምባሩ ተቀረቀረ፥ እርሱም በምድር ላይ በፊቱ ተደፋ። ዳዊትም ፍልስጥኤማዊውን በወንጭፍና በድንጋይ አሸነፈው፥ ፍልስጥኤማዊውንም መትቶ ገደለ፤ በዳዊትም እጅ ሰይፍ አልነበረም።" 2ኛ ሳሙኤል 21:19 "ደግሞም በጎብ ላይ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሰልፍ ነበረ፤ የቤተ ልሔማዊውም የየዓሬኦርጊም ልጅ ኤልያናን የጦሩ የቦ እንደ ሸማኔ መጠቅለያ የነበረውን የጌት ሰው ጎልያድን ገደለ።"

= መዝ 12:6 "የእግዚአብሔር ቃላት የነጹ ቃላት ናቸው።" ትንቢተ ሚልክያ 2:3 "የመሥዋዕታችሁንም ፋንድያ በፊታችሁ ላይ እበትናለሁ፤ ከእርሱም ጋር በአንድነት ትወሰዳላችሁ።"

=መጽሀፈ ሳሙኤል ካልዕ 24:1 "ደግሞም የእግዚአብሔር ቍጣ በእስራኤል ላይ ነደደ፥ ዳዊትንም። ሂድ፥ እስራኤልንና ይሁዳን ቍጠር ብሎ በላያቸው አስነሣው።" መጽሀፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 21:1 "ሰይጣንም በእስራኤል ላይ ተነሣ፥ እስራኤልንም ይቈጥር ዘንድ ዳዊትን አንቀሳቀሰው።"

=መጽሀፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 22:2 "አካዝያስም መንገሥ በጀመረ ጊዜ ዕድሜው አርባ ሁለት ዓመት ነበረ፥ በኢየሩሳሌምም አንድ ዓመት ነገሠ" 2ኛ ነገስት 8: 26 "መንገሥ በጀመረ ጊዜ አካዝያስ የሀያ ሁለት ዓመት ጕልማሳ ነበረ፤ በኢየሩሳሌምም አንድ ዓመት ነገሠ።"

= ኢሳ 45:7 "ብርሃንን ሠራሁ፥ ጨለማውንም ፈጠርሁ፤ ደኅንነትን እሠራለሁ፥ ክፋትንም እፈጥራለሁ፤ እነኒዚህን ሁሉ ያደረግሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ።" አሞጽ 3:6 "ክፉ ነገር በከተማ ላይ የመጣ እንደ ሆነ ያደረገው እግዚአብሔር አይደለምን?" መዝ 5:4 "ክፉ ከአንተ ጋር አያድርም።"

=መጽሀፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 11:11 "የዳዊትም ኃያላን ቍጥር ይህ ነበረ፤ የሠላሳው አለቃ የአክሞናዊው ልጅ ያሾብአም ነበረ፤ እርሱ ጦሩን አንሥቶ ሦስት መቶ ሰው በአንድ ጊዜ ገደለ።"መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 23:8 "የዳዊት ኃያላን ስም ይህ ነው። የአለቆች አለቃ የሆነ ከነዓናዊው ኢያቡስቴ ነበረ፤ እርሱም ጦሩን አንሥቶ ስምንት መቶ ያህል በአንድ ጊዜ ገደለ።"

Created in Master PDF Editor

=ማቴዎስ 9፡18 “አንድ መኰንን መጥቶ። ልጄ አሁን ሞተች፤ ነገር ግን መጥተህ እጅህን ጫንባት፥ በሕይወትም ትኖራለች እያለ ሰገደለት።”ማርቆስ 5፡22-23 “ኢያኢሮስ የተባለ ከምኵራብ አለቆች አንዱ መጣ፤ ባየውም ጊዜ በእግሩ ላይ ወደቀና። ታናሽቱ ልጄ ልትሞት ቀርባለችና እንድትድንና በሕይወት እንድትኖር መጥተህ እጅህን ጫንባት ብሎ አጥብቆ ለመነው።”

= ማቴ 5፡16 “መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።” ማቴ 6፡1-2 “ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፤ ያለዚያ በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም። እንግዲህ ምጽዋት ስታደርግ፥ ግብዞች በሰው ዘንድ ሊከበሩ በምኩራብ በመንገድም እንደሚያደርጉ በፊትህ መለከት አታስነፋ፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል።”

= መዝ 121፡4 “እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋምም።” መዝ 44፡23 “አቤቱ፥ ንቃ፤ ለምንስ ትተኛለህ? ተነሥ፥ ለዘወትርም አትጣለን።”

= ዮሀንስ 5፡31 “እኔ ስለ እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር ምስክሬ እውነት አይደለም።” ዮሀንስ 8፡14 “ኢየሱስ መለሰ አላቸውም። እኔ ስለ ራሴ ምንም እንኳ ብመሰክር ከወዴት እንደመጣሁ ወዴትም እንድሄድ አውቃለሁና ምስክርነቴ እውነት ነው”

= ማርቆስ 1፡11-13 “በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምፅ ከሰማያት መጣ። ወዲያውም መንፈስ ወደ ምድረ በዳ አወጣው። በምድረ በዳም ከሰይጣን እየተፈተነ አርባ ቀን ሰነበተ ከአራዊትም ጋር ነበረ፥ መላእክቱም አገለገሉት።” ዮሀንስ 1፡35 “በነገው ደግሞ ዮሐንስ ከደቀ መዛሙርቱም ሁለት ቆመው ነበር” ዮሀንስ 1፡44 “በነገው ኢየሱስ ወደ ገሊላ ሊወጣ ወደደ፥ ፊልጶስንም አገኘና። ተከተለኝ አለው።” ዮሀንስ 2፡1-2 “በሦስተኛውም ቀን በገሊላ ቃና ሰርግ ነበረ፥ የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች፤ ኢየሱስም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱም ወደ ሰርጉ ታደሙ።”

=1ኛ ነገስት 8፡46 “የማይበድልም ሰው የለምና”1ኛ ዮሀንስ 1፡8-10 “ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው። ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም።” ምሳሌ 20፡9 “ልቤን አነጻሁ፥ ከኃጢአትም ጠራሁ የሚል ማን ነው?” ይህን ሁሉ ይልና 1ኛ ዮሀንስ 3፡9 “ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ። ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፥ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔርም ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም።”

=ማርቆስ 15፡32 “አይተን እናምን ዘንድ የእስራኤል ንጉሥ ክርስቶስ አሁን ከመስቀል ይውረድ አሉ። ከእርሱም ጋር የተሰቀሉት ይነቅፉት ነበር።” ሉቃስ 23፡39-43 “ከተሰቀሉት ከክፉ አድራጊዎቹም አንዱ። አንተስ ክርስቶስ አይደለህምን? ራስህንም እኛንም አድን ብሎ ሰደበው። ሁለተኛው ግን መልሶ። አንተ እንደዚህ ባለ ፍርድ ሳለህ እግዚአብሔርን ከቶ አትፈራውምን? ስለ አደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው፤ ይህ ግን ምንም ክፉት

አላደረገም ብሎ ገሠጸው። ኢየሱስንም። ጌታ ሆይ፥ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ አለው። ኢየሱስም። እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው።"

=ማቴወስ 5:17-18 "እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም። እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ።" ዕብራውያን 7:19 "ሕጉ ምንም ፍጹም አላደረገምና፥ ስለዚህም የምትደክም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትእዛዝ ተሽራለች፥ ወደ እግዚአብሔርም የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ ገብቶአል።"

= ማቴ. 26:52 "ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ።" ዮሐ 14:27 "ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም።" ማቴ 10:34-37 "በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም። ሰውን ከአባቱ፥ ሴት ልጅንም ከእናትዋ፥ ምራትንም ከአማትዋ እለያይ ዘንድ መጥቻለሁና፤ ለሰውም ቤተ ሰዎቹ ጠላቶች ይሆኑበታል። ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም" ሉቃ 12:51 "በምድር ላይ ሰላምንም ለመስጠት የመጣሁ ይመስላችኋልን? እላችኋለሁ፥ አይደለም፥ መለያየትን እንጂ።"

=ማርቆስ 15:25 "በሰቀሉትም ጊዜ ሦስት ሰዓት ነበረ።" ዮሀንስ 19:14 "ለፋሲካም የማዘጋጀት ቀን ነበረ፤ ስድስት ሰዓትም የሚያህል ነበረ፤ አይሁድንም። እነሆ ንጉሣችሁ አላቸው።"

=ማቴወስ 21:19 "በመንገድም አጠገብ በለስ አይቶ ወደ እርስዋ መጣ፤ ከቅጠልም ብቻ በቀር ምንም አላገኘባትምና። ለዘላለሙ ፍሬ አይገኝብሽ አላት። በለሲቱም ያንጊዜውን ደረቀች።" ማርቆስ 11:19-21 "ማታ ማታም ከከተማ ወደ ውጭ ይወጣ ነበር። ማለዳም ሲያልፉ በለሲቱን ከሥርዋ ደርቃ አዩአት። ጴጥሮስም ትዝ ብሎት። መምህር ሆይ፥ እነሆ፥ የረገምሃት በለስ ደርቃለች አለው።"

=የሀዋርያት ስራ 9:7 "ከእርሱም ጋር በመንገድ የሄዱ ሰዎች ድምፁን እየሰሙ ማንን ግን ሳያዩ እንደ ዲዳዎች ቆሙ።" የሀዋርያት ስራ 22:9 "ከእኔ ጋር የነበሩትም ብርሃኑን አይተው ፈሩ፥ የሚናገረኝን የእርሱን ድምፅ ግን አልሰሙም።"

=ማቴ 6:5-6 "ስትጸልዩም እንደ ግብዞች አትሁኑ፤ ለሰው ይታዩ ዘንድ በምኵራብና በመንገድ ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ስትጸልይ፥ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል።" 1ኛ ጢሞ. 2:8 "የተቀደሱትን እጆች እያነሱ እንዲጸልዩ እፈቅዳለሁ።"

= 1ኛ ጢሞ. 5:8 "ነገር ግን ለእርሱ ስለ ሆኑት ይልቁንም ስለ ቤተ ሰዎቹ የማያስብ ማንም ቢሆን፥ ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው።" ማቴ 6:31 "እንግዲህ። ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ"

Created in Master PDF Editor

=የሀዋርያት ስራ 26:16 “ነገር ግን ተነሣና በእግርህ ቁም፤ ስለዚህ እኔን ባየህበት ነገር ለአንተም በምታይበት ነገር አገልጋይና ምስክር ትሆን ዘንድ ልሾምህ ታይቼልሃለሁና። የሀዋርያት ስራ 9:7-8 “ሳውልም ከምድር ተነሣ፥ አይኖቹም በተከፈቱ ጊዜ ምንም አላየም፤ እጁንም ይዘው እየመሩ ወደ ደማስቆ አገቡት።” የሀዋርያት ስራ 22:10 “ጌታ ሆይ፥ ምን ላድርግ? አልሁት። ጌታም። ተነሥተህ ወደ ደማስቆ ሂድና ታደርገው ዘንድ ስለ ታዘዘው ሁሉን በዚያ ይነግሩሃል አለኝ።”

=የሀዋርያት ስራ 1:18 “ይህም ሰው በዓመፅ ዋጋ መሬት ገዛ በግንባሩም ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰነጠቀ አንጀቱም ሁሉ ተዘረገፈ።” የሀዋርያት ስራ 1:18 “ይህም ሰው በዓመፅ ዋጋ መሬት ገዛ በግንባሩም ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰነጠቀ አንጀቱም ሁሉ ተዘረገፈ።” ማቴወስ 27:5 “ብሩንም በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ።”

መፅሀፍቱ ከውግዘት እና እርስ በእርሳቸው ከመቃረን ነጻ ቢሆኑ ኑሮ እውነትም ቅዱሳን ይሆኑ ነበር።እንደ ስሙ ብሩህ የሆነው ብሩህ አለምነህ በቅዱሳን መፅሀፍት የተገለጠው አምላክ በተቃርኖዎች የተሞላ መሆኑን እንድሚከተለው ያብራራል፦“በክርስትና ሆነ በእስልምና ውስጥ የተሰበከው እግዚአብሔር የባህሪ ተቃርኖዎች ያሉበት ነው። የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል፤ አንደኛ በአንድ በኩል እግዚአብሔር በራሱ ምልዑ እና ፍፁም ነው ይላሉ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር የሚፈልግ (በተለይ ምስጋና እና ስግደት)፣ የሚቆጣና የሚቀጣ ነው ይላሉ። መፈለግ፣ መቆጣት፣ መቅጣት… የሚባሉት የእግዚአብሔር ስሜቶች፣ እግዚአብሔርን በሰው ላይ ጥገኛ ያደርጉታል። ይሄም ጥገኝነት እግዚአብሔርን ከፍፁምነትና ከራስ በቅነት ይከለክለዋል። ሁለተኛ እግዚአብሔርና ሰይጣን በቦታና በጊዜ ጎን ለጎን ሊኖሩ አይችሉም፤ እግዚአብሔር ግን በሀሉም ቦታና ጊዜ ውስጥ ነዋሪ ከሆነ ሰይጣን በየትኛው ቦታና ጊዜ ውስጥ ነው የሚኖረው? ሦስተኛእግዚአብሔር ሰውን እና አለምን የፈጠረበት አላማ አለው ይላሉ። ዓላማ ሁሉጊዜ ወደ ግብ የሚወስድ በመሆኑ የዓላማ መኖር ያለመሟላትና ከፍፁምና የመጉደል ምልክት ነው። በመሆኑም፤ እንዴት እግዚአብሔር ፍፁምንና አላማን በአንድነት ባህሪው ውስጥ ሊይዝ ይችላል።”(የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ ገጽ 26)

በተጨማሪም ይህን የእግዚአብሔር መኖር በቅዱሳን መፅሀፍት ተገልጧል የሚለው አስተሳሰብ አሳማኝ አለመሆኑን ለማስረዳት የሚከተሉትን ነጥቦች ከቁርዓን እንይ፦

ቁርዓን!የእስልምና ኃይማኖት መመሪያ የሆነው ቅዱስ ቁርአን ንጽሕናው የተጠበቀና ከውሸትም የጠራ መሆኑን ቁርአኑ በሚገባ ያስተምራል ይላሉ የሙስሊም ሙህራን። በቁርአንለሁሉ ነገር ማብራሪያ፣ እንዲሁም ለሙስሊሞች መመሪያ፣ እዝነትና ብስራት እንዲሆን በሙሃመድ ላይ የወረደ መሆኑ ቢነገረንም በርካታ ሳይንሳዊ ስህተቶች ግን በግልጽ የሚታዩ ናቸው። ለምሳሌቁርአን እንደሚያመለክተው ምድር ጠፍጣፋ እንደሆነች እና የፀሐይ መውጫና መግቢያበምድር ክፍሎች እንደሆነ ለማስረዳት

Created in Master PDF Editor

ቁርአን 18፡86 በሚያስቅ ሁኔታ እንዲህ ይላል (አንድ ተጓዥ) ወደ ፀሐይ መግቢያም በደረሰ ጊዜ ጥቁር ጭቃ ባላት ምንጭ ውስጥ ስትጠልቅ አገኛት፣ ባጠገቧም ሕዝቦችን አገኘ፡፡ እንዲህ ያሉ ስህተቶች መፅሀፉ የተፃፈበትን ጊዜ ግምት ውስጥ ካስገባን ትክክል ይመስላል፡፡

ነገር ግን ቁርአን የተጻፈው ሁሉን አዋቂ በሆነ ይልቁንም ከሰመያት ሁኖ ምድር ጠፍጣፋ እንዳለሆነች እና ፀሀይ ምንጭ ውስጥ የምትጠልቅ ሰባራ ድንጋይ አለመሆኗን እያየ ለነብዩ ሙሐመድ ለምን ምድር ጠፍጣፋ ናት እንዳለው ይገርመኛል፡፡ ሙስሊሞች ቁርአን ቀጥተኛ እና ትክክለኛ ቃል ነው የሚለውን እምነታቸውን ይቀበላሉ እኔ ግን እመኑበት ከቻላችሁ ፈትሹት እላለሁ፡፡ ሰዎች እንዲህ ያስባሉ "ቁርዓን ከመፅሀፍ ቅዱስ ላይ ተፈለፈሎ የተበተነ ጥሬ ነው፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ በሶስተኛው ክ/ዘ ሲፃፍ፣ ቁራን በሰባተኛው ክ/ዘ ተፃፈ፡፡ ምንም እንኳን መሰረቱን መፅሐፍ ቅዱስ ላይ ቢያደርግም፣ በራሱ የጨመራቸው ክፍሎች እንዳሉ ግን አይካድም፡፡ የመፅሐፍ ቅዱስን ክፍል እነ መሐመድ በሚመቻቸው መልኩ ጨመርመር አድርገው ፃፉት፣ መፅሐፍ ቅዱስ ላይ ያሉ አንዳንድ ታሪኮችን ሰፋ እና ለወጥ አደረጓቸው፡፡" (አገኘሁ አሰግድ፣ ሸግር ብሎግ ድህረ ገጽ)፡፡

<ከማመን መጠራጠር ይሻላል> የተባለ ኤቲስት ቁራንን በተቸበት ጹሁፉ እንዲህ ይላል፦

> *"ይህ መፅሐፍ በኔ እይታ አለም ላይ ካሉት አሳስፈላጊ መፅሐፎች የመጀመሪያዉ ነዉ፡፡ ዉስጡ ያለዉ ሀሳብ ለማንበብ የማይመች የተጣመመና ደረቅ ነዉ፡፡ ቁራንን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ አንብቦ ፈገግ የሚል ሰዉ ካለ ጅል መሆን አለበት፡፡ መፅሐፉ ምንም ፈገግ የሚያስብል ሀሳብ የለዉም፡፡ መፅሐፉ የተፃፈዉ በጨካኝና አረመኔ ሰወች መሆን አለበት፡፡ መፅሐፉ ከክርስቲያኖችና ከአይሁድ መፅሐፎች የተኮረጀ ቢሆንም ፀሀፊወቹ የተኮረጀ ላለማስመሰል ብለዉ ዉስጡ ያለዉን ሀሳብ ባጠቃላይ አምባገነናዊ አድርገዉታል፡፡ቁራን ላይ እርስ-በርሳችሁተዋደዱ....ተፋቀሩ...ተከባበሩ የሚሉ ትዛዞችን አታገኙም፡፡ ለምሳሌ ቁራን 8:39 እዉከትም እስከማትገኝ ሃይማኖትም ሁሉ ለአላህ ብቻ እስከሚሆን ድረስ ተጋደሉዋቸው፣ ቢከለከሉም አላህ የሚሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነው፡፡ በዚህ ጥቅስ መሰረት እዚች አለም ላይ መኖር የሚችለዉ እስልምናና ተከታዮቹ ብቻ ናቸዉ፡፡ ቁራንን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ 14ቱንም ምዕራፎች ብታነቧቸዉ የምታገኙት...ያዟቸዉ፣ ዝረፏቸዉ፣ ቁረጧቸዉ፣ ፍለጧቸዉ፣ እረዷቸዉ የሚሉ አረመኒያዊ ትዛዞችን ነዉ፡፡ ቁራን እንደ-መፅሐፍ ቅዱስ (ተሻሽሎ የቀረበ) አድስ ኪዳን ስለሌለዉ ተሸሯል ማለት አይቻልም፡፡ አለማችንን ሰላም የሚነሷት*

Created in Master PDF Editor

አሸባሪወችም ምንጫቸዉ ይኸዉ ቅዱስ ተብየ መፅሐፍ ነዉ::"<ከማመን መጠራጠር ይሻላል>

<ከማመን መጠራጠር ይሻላል> ይህን ይበል እንጅ በቀጥታ በቁራዓን ውስጥ የማያምኑትን ግደሉ የሚል አላገኘሁም:: በእርግጥ ብዙ በተዘዋዋሪ የተጠቀሱ መልዕክቶችን ማግኘት ይቻላል:: በተለይ ምዕራፍ 9 ቁጥር 29 የተጻፈው አሳማኝ የጦርነት አዋጅ ይመስላል:: እንዲህ ነው የሚለው *"ከእነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች እነዚያን በአላህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑትን፣ አላህና መልክተኛው እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እውነተኛውንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ኾነው ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው::"* ምን አይነት ውጊያ እንደሆነ ተርጓሚዎችና ታዛቢዎች ይገምግሙት::

ሙስሊሞች ስለ ቁራን ሲናገሩ አላህ ስለራሱና ስለሌሎች ከሁሉ በላይ የሚያውቅ ከመሆኑ ባሻገር ንግግሩ አማኞች ተገንዝበውት እንዲመሩበት የወረደ በመሆኑ በሁሉም ጉዳዮች ላይ ከሁሉ በላይ እውነትን ገልፆ በማብራራት ወደ ቅን ጎዳና የሚመራ ቃል ነው ቢሉም ለእንደ እኔ አይነቱ ግን ለማንበብ የማይማርክ፣ ቁንፅል፣ ወጥነት የሌለው፣ የተድበሰበሰ፣ ጀምሮ የማይጨርስ፣ ሳይጀምር የሚጨርስ፣ ተደጋጋሚና አሰልች ነው::

ቁራዓን በርካታ ሙስሊሞች እንደሚሉት ከሆነ በቁርአን ዘመናዊ የሳይንስ ፈጠራዎችን እና ግኝቶችን አስቀድሞ ይታወቃሉ ይላሉ:: እነዚህ መሰሉ የይገባኛል ጥያቄዎች አሳዛኝ ናቸው:: ቁርአን ሳይንሳዊ ግኝቶችን የያዘ ቢሆን ኖሮ ቁርአንን ያጠኑ በርካታ ቁጥር ያላቸው አማኞች የሳይንስ ፈጠራዎችን እና ግኝቶችን ከሳይንቲስቶች ቀድመው ባቀረቡ ነበር:: ሙስሊም የኖቤል ተሸለሚወችም ቢያንስ ከአይሁድ ተሸለሚዎች ባላነሱ ነበር:: በእርግጥ ብዙ ሙሲሊም ሳይንቲስቶች እና ፈላስፎች እንደነበሩ እና እንዳሉ አውቃለሁ:: በግል ጥረቱ ይሆናል እንጅ በቁራን እየተመራ መድሃኒት የፈጠረ ሳይንቲስት የለም:: ሲጀመር ቅዱስ ቁራን እኮ ይላል <ከማመን መጠራጠር ይሻላል> የቁራንን ኦርጅናሊቲ በገመገመበት ፁህፉ፦

"የቁራን አመጣጥ እራሱ ግራ የሚያጋባ ነዉ:: ቁራንን ከአላህ ዘንድ ተቀበልኩ ያለዉ አንድ በመካ ይኖር የነበረ መሀመድ የሚባል ሰዉ ነዉ:: ይህ ሰዉ ቁራንን ተቀበልኩ ያለዉ ጅብሪል ከሚባል መልአክ ነዉ:: ግን ቁራንን ከመልአክ ለመቀበሉ ማረጋገጫ የለም:: ከጅብሪል ጋር የተነጋገሩት ንግግር እራሱ በጣም አስቂኝ ነዉ:: መፅሐፉ 14 ምዕራፎች ያለዉ ሲሆን ከፈጣሪ ወደ መሀመድ ሲወርድም ተከፋፍሎ ነዉ ይላሉ:: ሁሉም የቁራን ቻፕተር ከአላህ ወደ መሀመድ ለመድረስ 24 አመት እንደፈጀበት ይናገራሉ:: ይህ ጥያቄ ያስነሳል:: እንዴት አንድ መፅሐፍ ከፈጣሪ ወደ ምድር ለመዉረድ 24 አመት

Created in Master PDF Editor

> ይፈጀበታል? አላህ ቁራንን ለማዉረድ 24 አመት ከፈጀበት እሱም የሚመራዉ በእቅድ ማለት ነዉ። እኛ ሰወች ነገሮችን ለመስራት እቅድ የምናወጣዉ ሁሉንም ነገር በአንድ ጊዜ ማድረግ ስለማንችል ነዉ። እኛ በቦታና በጊዜ ዉስን በመሆናችን ሁሉን ነገር በአንድ ጊዜ ማድረግ ስለማንችል ሁሉንም ነገር በዕቅድ ለመስራት እንገደዳለን። ፈጣሪ ግን ሁሉን ነገር በአንድ ጊዜ የማድረግ ችሎታዉ ስላለዉ እቅድ አያስፈልገዉም። ስለዚህ ፈጣሪ አንድን መፅሐፍ ለማዉረድ 24 አመት ፈጀበት የሚለዉ አባባል ዉሸት ነዉ። መፅሐፉ ከፈጣሪ ዘንድ ለመምጣት 24 አመት ፈጀበት የሚሉን መፅሐፉን በሂራ ዋሻ ከክርስቲያኖችና ከአይሁዶች መፅሐፍ እስከሚገለብጡ የፈጀባቸዉን አመት ነዉ።”

የሙስሊም ሙህራን ነብይ ሙሃመድ መፃፍና ማንበብ የማያችሉ ነበሩ ቢሉም። ይህ ሴራ አስቀድሞ የተጠነሰሰ ማምለጫ እንደሆነ ይነገራል።ቅዱስ ቁራንን ከመፅሀፍ ቅዱስ መኮረጁን በተመለከተ <ከማመን መጠራጠር ይሻላል> እንድህ ይላል፦

> ቁራን ከብዙ ቅዱሳን ተብየ መፅሐፎች የተኮረጀ መፅሐፍ ሆኖ ሳለ ሙስሊሞች ግን የፈጣሪ ቃል እንደሆነ ይሰብኩልናል።ነገር ግን እራሱ ቁራንየተኮረጀ መሆኑን ይናገራል። እንደት? ካላችሁኝ ቁራንን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ስታነቡት ከመፅሐፍ ቅዱስ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ታገኙታላችሁ። የቁራን ፀሐፊወች መፅሐፉ ከመፅሀፍ ቅዱስ ጋር እንዳይመሳሰል ያደረጉት ጥረት ቢኖር መፅሀፍ ቅዱስ ላይ ያለዉን ታሪክና የሰወች ስም መቀየር ነዉ። አዳምን ወደ አደም፣ ሄዋንን ወደ ሀዋ፣ አብርሀምን ወደ ኢብራሂም፣ ዳዊትን ወደ ዳዉድ፣ ኢየሱስን ወደ አልመሲህ ኢሳእያለ ይቀጥላል። የመፅሐፍ ቅዱስ ታሪኮችንም ቁራን ላይ ሲገለብጡ ብዙ ታሪኮችን አዛብተዋቸዋል። ይህን ሁሉ አድርገዉም መፅሐፉ ከመመሳሰል ስላልዳነላቸዉ ሌላ አማራጭ ተጠቅመዋል።ሌላዉ አማራጭ ደግሞ እራሱ መፅሐፍ ቅዱስም በአላህ ነቢያቶች እንደተፃፈና አሁን ደግሞ በቁራን እንደተተካ በመስበክ ነዉ። በዚህም ምክንያት መፅሐፍ ቅዱስን የራሳቸዉ ስያሜ ሰጡት። በሙሴ የተፃፈዉን ኦሪት (ለሙሳ የወረደ ተዉራት) የዳዊትን መዝሙር (ለዳዉድ የወረደ ዘቡር) አራቱን ወንጌሎች ደግሞ (ለአልመሲህ ኢሳ የወረደ ኢንጅል ብለዉ ስያሜ ሰጡት) ይህን ያደረጉበት ሌላዉ ምክንያታቸዉ አላህ ለምን ቁራንን በአዳምና ሀዋ ዘመን አላወረደዉም የሚል ጥያቄ ብታነሱባቸዉ መልሳቸዉም ቁራን ከመዉረዱ በፊት መፅሐፍ ቅዱስ ነበረ የሚል ነዉ። ታድያ መፅሐፍ ቅዱስ ከአላህ ዘንድ ከመጣ ለምን በቁራን መተካት አስፈለገዉ ካላችሁ ደግሞ መፅሐፍ ቅዱስ በሰወች ስለተበረዘ ይሏችኋል።

Created in Master PDF Editor

ግን ችግሩ በአረቂ ለሰከረ ቢራ እንደመጨመር ነው። ሁለቱም መጽሃፍት ስህተቶች ስለመሆናቸው እርስ በእርሳቸው ማጠያየቅ ተገቢ ነው። ሙስሊሞች “መጽሃፍ ቅዱስ ተበርዟል” የሚል ሃሳብ ሲያነሱ ክርስቲያኖች ደግሞ “ቁርአን ውስጥ የተባለው በሙሉ መሐመድ አላህ እንደነገረው የተናገረው ነው፤ መሐመድ ደግሞ በዐይን እማኞች በተላለፉት ሐዲሳት ከተጻፈው የሕይወት ታሪኩ አንጻር ሲታይ እንኳንስ ለመጨረሻ ነብይነት መመረጥ ይቅርና ጭራሽ ለነቢይነት የሚያበቃ ስብዕና አልነበረውም።” በተጨማሪም “ቁርአን የፈጣሪን ንግግር በመላበስ የተጻፈ ጽሑፍ ቢሆንም ደራሲው ሥጋ ለባሽ በመሆኑ በበርካታ ታሪካዊ ስህተቶች የተሞላ ጽሑፍ ሆኖ ተገኝቷል። እነዚህ ስህተቶች ደግሞ ቁርአን የአፅናፈ ዓለም ፈጣሪ ከኾነው እውነተኛው አምላክ ዘንድ እንዳልመጣ የሚያሳዩ የማንቂያ ምልክቶች ናቸው።” (እውነት ለሁሉ ድህረ ገጽ)

በቅዱሳን መፅሐፍት አንድም እንኳ ስህተት፣ ተቃርኖ እና ኢ-ፍትሐዊነት መገኘት የለበትም። ቢሆንም በመፅሐፍቱ ትክክለኛነት፣ ፍትሐዊነት፣ መሪነት፣ ቀጣይነት፣ ተጨባጭነት፣ አስተማሪነት፣ መንፈሳዊነት፣ መልካምነት፣ ግልፀኝነት አይታይባቸውም። ታድያ እንዴት እንመነው። ማቴወስ ያለውን ሉቃስ ካፈረሰው፣ ማርቆስን እንዴት እንመነው። ሁሉም እኮ የአንዱ መፅሐፍ አካሎች ናቸው። ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 ስህተት ካለ ሙሉ ያን አንቀጽ ወይም ምዕራፍ ብቻ ላይሆን ሙሉ መፅሐፉን ያለማመን መብት አለን።

5. ሰዎች የሚሰጡት ምስክርነት የእግዚአብሔር መኖር ያረጋግጣል

<<እኔ የቀድሞ ወሃቢ ሙስሊም ስኾን ተወልጄ ያደግሁት በሳዑዲ አረብያ በሚኖር ሙስሊም ቤተሰብ ውስጥ ነበር። ለሃይማኖቴ ያደርኩና እያንዳንዱን የእስልምና አስተምሕሮ በያንዳንዱ የሕይወቴ ገፅታ ላይ ለመተግበር የምተጋ ፅኑ ሙስሊም ነበርኩ። እስልምና በምድር ላይ የመጨረሻው እምነት መኾኑን፤ በፈጣሪ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ብቸኛ ሃይማኖትና ወደ ሰማይ የሚወስድ ብቸኛ መንገድ መኾኑን፤ እስልምናን ያልተቀበሉ ወገኖች ወደ ገሃነም እንደሚወርዱና አላህን እንደ አምላካቸው፣ መሐመድን ደግሞ እንደ መልእክተኛው ካልተቀበሉት በስተቀር ሥራቸውና አምልኳቸው ሊያድናቸው እንደማይችል፤ ደህንነት በእስልምና በሥራ የሚገኝ መኾኑንና ለአላህ ክብር ሲጋደሉ ከሞቱት ሙስሊሞች በስተቀር ሌሎቹ ዋስትና እንደሌላቸው፤ ሙስሊሞች የሌሎች ሕዝቦች የበላዮች መኾናቸውን፤ ክርስቲያኖችን ጨምሮ ሙስሊም ያልኾኑት በሙሉ ከሃዲያን መኾናቸውን፤ ክርስቶስ ሰው ብቻና በአላህ የተላከ ነቢይ መኾኑን፤ አምላክ ወይንም የፈጣሪ ልጅ አለመኾኑን፤ አለመሰቀሉን፣ በመስቀል ላይ አለመሞቱንና አለመነሳቱን፤ ይልቁኑ ወደ ሰማይ ማረጉንና በመጨረሻው ዘመን እስልምናን ለመመለስ፣ መስቀልን ለመሰባበር፣

Created in Master PDF Editor

ደጃልን ለመግደልና ክርስቲያኖችን ወደ እስልምና ለመመለስ ተመልሶ እንደሚመጣ አምን ነበር። ነገር ግን ከልጅነቴ ጀምሮ ከተማርኳቸው ትምሕርቶች ኹሉ ይልቅ በልቤ ውስጥ ጠልቆ የገባው አላህን የማያመልኩትን፣ መሐመድን የማይከተሉትንና እስልምናን የማይቀበሉትን ክርስቲያኖችና አይሁድን የመሳሰሉትን ወገኖች በሙሉ መጥላት ነበር።

. . . ክርስቶስን ካመንኩበት ጊዜ ጀምሮ መታወሬ ቀርቶ እውነትን ማየት የሚችል ሰው ሆኛለሁ። ሙስሊም ኾኜ ዕድሜ ልኬን የኖርኩበትን የሐሰት ዓለም ተረድቻለሁ። እስልምና የሚያስተምረውን የሐሰት ትምህርት፣ ተወዳጅ የኾነው ሙስሊሙ ሕዝቤ አሁንም ድረስ የሚኖርበትንና የሚያምነውን ሐሰት ይበልጥ ተገንዝቤያለሁ። እነዚህ ውሸቶች መሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሷል የሚለውን ይጨምራሉ። ነገር ግን እኔ መጽሐፍ ቅዱስን መርምሬ መሐመድ በፍጹም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳልተጠቀሰ አረጋግጫለሁ። ሌላው ውሸት በቁርአን ውስጥ ሳይንሳዊ ተዓምራት ይገኛሉ የሚለው ነው። ይህም ማጭበርበርያ ብቻ መኾኑን አረጋግጫለሁ። ከነዚህ ተዓምራት ተብዬዎች መካከል አንዱ እንኳ የሳይንስ ሽታ ያለው የለም፣ አከተመ። መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል የሚል ሌላ ውሸትም አለ። ቁርአን ግን መጽሐፍ ቅዱስ መበረዙን በአንድም ቦታ እንደማይናገር አረጋግጫለሁ። ይልቁኑ ቁርአን ከአምላክ ዘንድ ስለመኾኑ ለማረጋገጫነት መጽሐፍ ቅዱስንና የመጽሐፉን ሰዎች በዋቢነት ይጠራል። መጽሐፍ ቅዱስ ከተበረዘ ቁርአን እንዴት ኾኖ ነው መጽሐፍ ቅዱስንና የመጽሐፉን ሰዎች ለምስክርነት የሚጠራው? መጽሐፍ ቅዱስ ስላልተበረዘ ትምሕርቶቹ እውነት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስ እኔን ከኃጢአትና ከሰይጣን እስራት ለመፍታት ወደ ምድር የመጣ አምላክ መኾኑን ይናገራል። በኔ ፋንታ ስለ ኃጢአቴ በመስቀል ላይ ለመሞት እንደመጣና የዘላለምን ሕይወትና የኃጢአቴን ስርየት ዋስትና ሊሰጠኝ ከሰማይ እንደወረደ ይናገራል።>>

(ምንጭ፦ አስደናቂ ፍቅር በሙቲዓ አል-ፋዲ፣ እውነት ለሁሉ ድህረ ገጽ የተወሰደ)

ሰዎች በህልም፣ በማሰላሰል፣ በራዕይ እና በአደንዛዥ እፆች ንቃተ-ህሊናቸው ከፍ ስለሚል ያልተለመዱ ምሥጢራዊ ክስተቶችና እና መንፈሳዊ መገለጦችን ሊያስተውሉ ይችላሉ። ይህ እይታም ስለ ተጨባጩ ተፈጥሮ ጥልቀት ያለው አስተያየት መስሎ ይቀርባል። ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱ ግንዛቤ ስውር የሆኑ እና ግላዊ ናቸው። በአጠቃላይ ለእኔ እውነተኛ የሆነ ለሁሉም እውነት አይደለም። እውነት የተረጋገጠ እና የማያምኑት እንኳ ሊክዱት የማይችሉ አለምአቀፋዊ ነው።

Created in Master PDF Editor

እናንተ ያለ በቂ ማስረጃ የቀረበን ትረካ እንደ ትክክለኛ እውነታ ትቀበላላችሁን? በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ማረጋገጫ የሌለው ወይም በእውነተኛ ምስክርነት ላይ የማይመሠረት አይነት ጋዜጣዊ ሪፖርቶችን አሜን ተላላችሁን? "እምነት ይላል ቅዱስ ጳውሎስ እምነት ምንም አይነት ተጨባጭ መረጃ በሌለን ነገር፣ ተስፋ ባደረግነው ነገር፣ እርግጠኛ የሚያደርገንና ነገንም የማያስረዳን ነው፤" ዕብራ 11፡1 ለሳይንሱ ግን "እምነት ብቻውን የስንፍና መፈልፈያ፣ የንቃተ ህሊና ዝቅተኛ ደረጃ፣ ተስፋ ለቆረጠ ሰው የሚሰጥ ሃሳባዊ ዳቦ ነው። ካርል ማርክስም ሃይመኖት የህዝቦች አደንዛዥ ዕጽ ነው፣ ይላል። ሰዎች ከጥንት ዘመን ጀምሮ በብዙ ነገሮች ሲያምኑ ነበር፤ አብዛኛው እምነታቸው የተፈጥሮን አደጋዎች መቆጣጠር ካለመቻላቸው የተነሳ የተፈጠሩ ነበሩ። ተፈጥሮን መቆጣጠር ሲችሉና ሌሎች ቴክኖሎጂዎችንም እያበለፀጉ ሲሄዱ ግን የበፊት እምነቶቻቸው ከንቱ እንደነበር ደረሰብት፣ ስለዚህም የጦርነት፣ የአውሎ ንፋስ፣ የጉርፍ፣ የፍቅር፣ የፀሐይ … አምላኮቻቸውን ሁሉ ገደሏቸው።" (ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣ 115)

ትልቁ የማናረጋግጠው ቢያንስ ታማኝ ምስክር እንኳ የሌለው ከሞት በኋላ ህይወት አለ ብሎ ማመን ነው። ከሞት በኋላ ህይወት አለ ማለት ሲጀመረ አንሞትም ወይም ነብስና ስጋ ተፋቱ እንደማለት ነው። ነፍሳችን የማትሞት ከሆነ ደግሞ በቀብራችን ልንገኝ ነው፣ የቀብራችንን ስነ ስርዓቱን ልንታደም ነው ማለት ነው። ይህን በሚች በቀብሩ መገኘትን በተመለከተ ሀይለ ጊዮርጊስ ማሞ ጆን ዊዝደም እና አንቶኒ ፍሊው ያሉትን እንዲህ አስነብቦናል፦

> "ጆን ዊዝደም ሲናገር የራሴ ቀብር ላይ መገኘት ምን ሊመስል እንደሚችል መገመት እችላለሁ። ወዳጆቼ በጥቁር ሱፍና ከረባት አጊጠው፤ አበቦችን ደርድረው፤ በሬሳ ሳጥን ውስጥ ከአበቦች ስር የሚታይ ፊት፣ ምንአልባት ፊቱን ሳይ እደነግጥ ይሆናል… ብሏል። አንቶኒ ፍሊው ድግሞ፡- ከሞት በኋላ ህይወት ካለህ ከራስህ ቀብር ላይ ትገኛለህ… እንግዲህ በቀብርህ ላይ ከተገኘህ ደግሞ አልሞትክም ማለት ነው… ከመሞትህ በፊት አስቀድሞ የሞተውን ጓደኛህን እንደቀበርክ ሁሉ ዛሬም ራስህን እየቀበርክ ነው፤ የሚያሳዝነው ግን በቀብርህ ላይ መገኘትህን ማንም አለማወቁ ነው" ይለናል። (ጥበብ ቅጽ አንድ፣ 2009፣ 97)

ከሞት በኋላ ህይወት አለ ብላችሁ ተስፋ ካደረጋችሁ ከዚያ በኋላ በተመረጡ ግምቶች ላይ ብቻ የተመሰረተ እምነት ይኖራችኋል። እውነት ባይሆንም ማመኑ ባልከፋ ነበር ነገር ግን ብዙ ግምቶች መጥፎ፣ ባዕድ እና አጉል እምነቶችን ይፈጥራሉ። እውነት ለመናገር ዘላለማዊነትን የሚጠላ አልን? በጭራሽ እንዲያውም ለዘለአለም ከመሞት ሊኖር ይችላል በሚባለው ሲኦል ግዛነበ እሳት ውስጥ በህይወት መኖር ይሻላል። ነገሮች ግን እኛ ሰወች ለራሳችን የሰጠነው ግምት እንጅ ከእንሰሳት የምንመደብ ለማዳ

Created in Master PDF Editor

አጥቢ እንስሳ ነን። እኛ የማንሞት ከሆን እንስሳትም አይሞቱም ከእንስሳት የተለየ ስሪት የለንምና። የጠቢቡ ሰለሞን መፅሃፍም ይህን ሲመሰክር “የሰው ልጆችና የእንስሳ ዕድል ፈንታ አንድ ነው፤ ድርሻቸውም ትክክል ነው፤ አንዱ እንደሚሞት ሌላውም እንዲሁ ይሞታል፤ የሁሉም እስትንፋስ አንድ ነው፤ ሁሉም ከንቱ ነውና። ሰው ከእንስሳ ብልጫ የለውም። ሁሉ ወደ አንድ ቦታ ይሄዳል። ሁሉ ከአፈር ነው፤ ሁሉም ወደ አፈር ይመለሳል።” (መፅሀፈ መክ.3፡19-20)

ስለዚህ ሰው እራሱን ከሌሎች ፍጥርታት ልዩ አድርጎ የሚያየው ራስ ወዳድ ስለሆንን ነው። ይህ ራስ ወዳድነት የሃይማኖት ዋነኛ መሰረት ነው። ነገር ግን ከልክ ያለፈ ራስ ወዳድነት ከንቱ ምኞት ነው። የሃይማኖትን ከንቱኑት አገኘሁ አሰግድ እንዲህ ያብራራዋል።

> <<ተሰቀለልህ ሲሉኝ ድምፄ እስኪዝል ዘምሬያለሁ። መዳፌ እስኪግል አጨብጭቤያለሁ። እግሬ እስኪደክም ቆሜ አስቀድሻለሁ። በዚህ ሁሉ አልረካም ነበር። ትንሿ መንፈሳዊ ማፈንገጥ፣ ከፈጣሪ እንዳቀያየመኝ አስባለሁ። መሳት፣መሳሳት ሰዋዊ ሁነት መሆኑን እዘነጋለሁ። ሰው ማለት ለኔ፣ የሃጢያት ወንዝ አቋርጦት የሚያልፍ ካናል ነበር። እኔም ለራሴ እንደዛው ነበርኩ። በምህረቱ ያልጠፋን፣ በበደላችን የከፋን ሆኖ ይሰማኛል። ፀሎቴ ሁሉ፣ ‘እንደ ምህረትህ እንጂ፣እንደ በደሌ አትይብኝ’ በሚል ሃረግ የተዘመዘመ ነበር። አስር በጎ ስራዬ፣ሩብ በማትሞላ ሃጢያቴ የሚፈረካከስ ይመስለኝ ነበር። ከዛ በቀደመው ጊዜ ደግሞ፣ ክርስቶስ ራሱ ኦርቶዶክስ ይመስለኝ ነበር። አቻዎቼ ከሚቋምጡለት ‘አዲስ ፊልም ቤት’ ይልቅ ሰንበት ትምህርትቤት ይማርከኝ ነበር። ያልገባኝን ጥቅስ እና መዝሙር ሳንቸለችል ነበር። ዓለምን በዝሙት ምክንያት ያጠፋ ጌታ፣ሎጥ ከልጆቹ ሲወልድ ዝም ብሎ ይመለከት ነበር ሲሉኝ፣ዝም ብዬ ተቀብያለሁ። የድሮ እባብ ያወራ ነበር ሲሉኝ አምኛለሁ። ጥርጣሬ ነክቶኝ ሲያልፍ ‘የሚፈትነኝን ሰይጣን አባርልኝ’ ስል ተንበርክኬ ማልጃለሁ። እግዜር እረኛዬ መሆኑን እንጥሌ እስኪነድ ዘምሬያለሁ። ሲገባኝ፣ ‘እግዜር እረኛ ነው፣ ብለው ሲናገሩ፣ አንተ በግ ነህ ነው ለካ ሚስጥሩ።’>> (አገኘሁ አሰግድ)

ስለ ምስክርነት ለማወቅ የተወሰነ ቅኝት ማድረግ በቂ ነው። አንዳንዴ ሀይማኖታዊ ምስክርነቶች የፖለቲካ ድጋፍና ተቋሙሞ ይመስላሉ። ለዚህ ጉዳይ መረጃ ለማሰባሰብ የተለያዩ ሀይማኖቶችን የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ተከታትያለሁ። መጨረሻ ላይ እራሴን ጠየቁ ግን ለምን እንዲህ ይሆናል። በተለይ በፈውስና በተአምራት ዙሪያ የሚሰጡ የምስክርነት ፕሮግራሞች እንኳን አማኞችን የማላምነውን እኔን እንኳ ያምታታሉ፣ ያስገርማሉ፣ ያስደንቃሉም። አንዳንዴ በአሜሪካና በእንግሊዝ ሚዲያዎች የሚተላለፉትን የአይዶል ውድድሮች እየተከታተልኩ ይመስለኛል። በእርግጥ በሚድያ

Created in Master PDF Editor

ለውድድርና ለሰርፕራይዝ ተብሎ በሚደረጉት ተአመራትና በፈውስ ቻናሎች በሚተላለፋት ምስክርነቶች መካከል ያለው ልዩነት እና ስርዓት አልገባኝም፡፡ ከልጅነቴ ጀምሮ ስለ ተአምራት ስሰማ ስላደኩ የቱንም ተአምር ልጠራጠር ግድ ይለኛል፡፡ ለምስክርነት የሚያበቁት ታአምራት ከየት እንደመጡ ለማወቅ ወይም ከጀርባቸው ያለውን መጋረጃ ገልጦ ለማየት ጊዜ ያስፈልገኛል፡፡ ተአምራትን እና ተአምራትን ተከትሎ የሚመጡትን ትርክቶችና ምስክርነቶች ሳስብ አንድ ምርጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ንግግር ትዝ ይለኛል፡፡ “ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እስኪያስቱ ድረስ ድንቅ ተአምራትን ያደርጋሉ፡፡”

6. ያልተጠበቁ ክስተቶች እና ተአምራት የእግዚአብሔር መኖር ያረጋግጣሉ

<< . . . ለብዙ ዘመናት አልጋ ላይ ተኝቼ

የሚረዳኝ አጣሁ ጠሉኝ ዘመዶቼ

የእኔ ጌታ አምላኬ ወደ እኔ መጣና

አልጋህን ተሸከም አለኝ ፈወሰና፡፡

አሥራ ሁለት ዓመት ደም እየፈሰሰኝ

ምራቅ እየተፉ ሁሉም ሲያንቋሽሿኝ

የጌታዬ ልብሱን ጫፋን ብዳስሰው

ኃይልም ከእርሱ ወጣ ደሜን ቀጥ አረገው፡፡

ሰካራም ዘማዊ ወንበዴ ነበርኩኝ

የአመጸኞች መሪ ደምን ያፈሰስኩኝ

ዛሬ ግን ታሪኬን ጌታ ቀይሮታል

ለኃያሉ ጌታ ምስጋና ይገባዋል>> (የወደደኝ ጌታ ከሚል መዝሙር የተቀነጨበ)

"ተአምር" ማለት ከተፈጥሮ ህግጋት ጋር የሚቃረን ክስተት ነው፡፡ እናም ለክስተቱ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ መንስኤ መጥራት የተለመደ ነው፡፡ በሂደት ብዙ እንደታምር የሚቆጠሩ ክስተቶች ሳይንሳዊ ማብራሪያ ቢገኝላቸውም ዛሬም ድረስ እንቆቅልሽ የሆኑ ክስተቶች ግን አሉ፡፡ አንድ በገዳይ ካንሰር ወይም በኤች አይ ቪ የተያዘ ሰው ቢድን የዳነበትን ምክንይት አለማወቅ እንጅ የእግዚአብሔርን መኖር አያረጋግጥም፡፡ ቢሆንም እንኳ የእግዚአብሔርን የማዳን ስራ ከሚሊዮን ውስጥ ለአንዱ በሎተሪ መልክ የሚደርስ ከሆነ ያስተዛዝበናል፡፡ ምን አልባት የእናንተ አምላክ ቁማር ተጫዋች አይደለም፡፡ ነው እንዴ? በሚያሳዝን ሁኔታ የእኔ ፈጣሪ ግን የዘለአለም ስራው ቁማር

Created in Master PDF Editor

ማጫወት ነው። ቁማርተኞቹ ደግሞ ፍጥረታት ናቸው። በቁማሩ ያሸነፉት ይድናሉ የተሸነፉት ይሞታሉ። በእርግጥ <ከቫክተሪያነት ወደ ሰውነት የማደግ ቁማር> ለኔ ታአምር ነው።

እስኪ እግዚአብሔር ከተለያዩ በሽታዎች በታምሩ (በፀሎት እና በፀበል) ፈወሰን ለሚሉት የሚከተሉትን ሀሳቦች ላቅርብ፡

1ኛ. አትፍሩ የታመመ ሁሉ አይሞትም፣ ያለምንም ህክማና በቂ አረፍት በመውሰድ ሰውነታችን በሽታ የመከላከል አቅሙን ክፍ በማድረግ ልትድኑ ትችላላችችሁ። ስንፀልይ ወይም ፀበል ስንጠመቅ እንድናለን ብሎ ማመን በራሱ ትልቅ የሆን አዕምሮአዊ ተፅእኖ አለው። ለዚህ ይመስለኛል ፀበል ከሚጠመቁበት ተሽሏቸው ሳለ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ እንደገና የሚያገረሽባቸው። ጸብሉ ቢያድናቸው ኑሮ መልሶ ባላማማቸው ነበር።

2ኛ. የሁለችንም ህይወታችን በአስደናቂ ክንውኖች የተሞላነው። በጣም ብዙ ክስተቶች ያጋጥመናል አንዳንዶቹ እጅግ አስገራሚዎች እና እጃችን በአፋችን እንድጨብጥ የሚያደርጉ ናቸው። በስታስቲክስ እና በህክምንም ልዩ የሆኑ ክስተቶች ይከሰታሉ ተብሎ ይጠበቃል።ደስ የሚለው እነዚህ መልካም ወይም መጥፎ ክስተቶች ሰው አይመርጡም ራንደም (random) ናቸው።

በአጠቃላይ በጣም አነስተኛ የሆኑ ታምራትን በማየት የተፈጥሮ ሕጎች ተሰብረዋል እናም ከተፈጥሮ በላይ የሆነ አምለክ አለ ማለት አጥጋቢ መከራከርያ አይደለም። ሆኖም አንድ ክስተት ምንም ያህል ያልተለመደ ቢሆንም በተለየ መልኩ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ እግዚአድሔር ቢኖር ነው እንጅ ከማለት ምክንያቱን አላውቅም መለት ይሻላል ምክንያቱም ያን ክስተት ያቀናበረው ፈጣሪ ስለመሆኑ ማስረጃ የለንም።

ታምራት እንዴት ይፈጠራሉ ለምትሉ በተፈጥሮም በሰውም ይፈጠራሉ። ችግሩ አማኞች በተፈጥሮ እና በሰው የተከናውኑትን ታምራት እግዚአብሔር እንዳደረጋቸው አድርገው ያቀርባሉ። ለዚህ አሳዛኝ ቆርጦ ቀጥል ወሬ ብሩህ አለምነህ በሀገራችን የተከሰቱትን ሁለት ምሳሌዎች ያቀርባል።

> አንደኛው ምሳሌ የሚሆነን ቅዱስ ላሊበላ ነው። በማህበረሰባችን ውስጥ ቅዱስ ላሊበላ ወቅር አብያተ ክርስቲያናትን የሰራው በመላዕክት እርዳታ እንደሆነ ይታመናል። የሰውን ልጅ ህይወት ወደ ጠርዝ መግፋት ማለት ይሄ ነው። ቅዱስ ላሊበላ መንፈሳዊ መሪ እንደነበር ማንም አይክደውም፤ ሆኖም ግን ንጉሱ ባለሙያዎችን አሰባስቦ በዕውቀቱና በችሎታው የሰራውን ስራ ምስጋናውን ለእግዚአብሔር መስጠት ተገቢ አይደለም። ሁለተኛው ምሳሌ ቅዱስ ያሬድ ነው። ቅዱስ ያሬድ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክ የምትጠቀምባቸውን አራቱን የዜማ

Created in Master PDF Editor

ትምህርቶች ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬ እና መዋስዕት ድርሰታቸውን ከነዜማቸው የቀመረ፣ የ14ቱን ቅዳሴዎች ዜማቸውን ያቀናበረ ታላቅ ሊቅና ድምፃዊ ነው። ሆኖም ግን ቤተክርስቲያኗ የቅዱስ ያሬድን ችሎታና እውቀት ከያሬድ ነጥቃ ለእግዚአብሔር ትሰጠዋለች፤ እንዲህ በማለት፦ ቅዱስ ያሬድ ዜማውን ሊደርስ የቻለው ሀይማኖታዊ መፅሀፍትን መሰረት በማድረግ ንባብን ለዜማው እንዲስማማ በማቃናትና መሰረተ ሀሳቡን ሳይለቅ ንባቡ ከነሚሥጥሩ በመንፈስ ቅዱስ ተገልያለት እንጅ እንዲህ በዘፈቀደ ከልቡ አንቅቶ (አፍልቶ)፣ ከአፉ አውጥቶ አልተናገረውም። (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 159-160)

ያሳዝናል ቅዱስ ላሊበላን እና ቅዱስ ያሬድን የምናድንቃቸው በእግዚአብሔር በኩል ነው። እንዲያውም ከአማኞች አስተሳሰብ እንድምንረዳው ሁለቱ ቅዱሳን የእግዚአብሔር አሻንጉሊቶች ናቸው። አድርጉ የተባሉትን ብቻ ስላደረጉ፣ ተሸከሙ የተባሉትን ብቻ ስለተሸከሙ እንደ ስልቻ ወይም እንደ ፌስታል ልንቆጥራቸው እንችላለን።ይህ ሰዎችን ዝቅ የማድረግና ለፈጠራቸው የሚገባውን እውቅና አለመስጠት ደካማ ጎናችን ነው። ለህሊናችን የሚከብዱንን የሰው ልጅ ቅንጭላት ምጡቅነት ማሳያዎች ወደ ሠማይ መግፋት የስራዎቹን የባለቤትነት መብት እንደመሻር ነው። ሠዎች ጥቁር ቀለም ሲቀቧቸው የሰይጣን ነጭ ቀለም ሲቀቧቸው የእግዚአብሔር የሚሆኑ አይደለም። ለነገሩ ህዝቡም የሚወድው ይላል ነጋድረስ ገብረህይወት ባይከዳኝ

የሀገራችን ህዝብ እውነቱን ሲሰማ አይወድም፤ ቢሰማም አይገባውም። እንድ ንጉስ እንዲህ አድርጎ ጥሮ ነገሠ፤ ከነገሠም በኋላ በእንዲህ ያለ ምክንያት ይህንን ፈፀመ፤ ይህንንም ተወ። በእንዲህ ያለ ምክንያትም ወደቀ ወይም ለማ። ከሚሏቸው ይልቅ አገሌ ከሰማይ ወይም ከጠንቋይ እንደዚህ አይነት ትንቢት መጥቶለት ለመንግስት የተወለደ ሰው መሆኑን አውቆ እና ታውቆ እገሌና እገሌ ታጠቁለት። አገሌና እገሌም ሰይጣን አሱቷቸው ተዋግተውት አሸነፋቸው። … በፍካሬ ኢየሱስ የተተነበየውም ጊዜ ተፈፅሞ ሞተ ብለው ቢዋሿቸው ይወዳሉ።… እንደ ኢትዮጵያችን ነገስታትና ገዥዎች ብዙ የቅዱሳን እና የአጋንት እርዳታ የሚያስፈልገው ሰው በአለሙ ታሪክ ከቶ አልተሰማም። (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 161)

ይህ ቆርጦ ቀጥል አስተሳሰብ በነጋድረስ ገብረ ህይወት ባይከዳኝ ዘመን ያለፈ አይደለም። ዛሬም እነ ዶ/ር አብይ ንጉስ (ጠቅላይ ሚኒስተር) የሆኑት ተተንብዮላቸው እንደ ሆነ ይናገራሉ ያስነግራሉ። ኢህአዴግ እና ፓርላማው በተለይም ሽግግሩን ያፈጠነው ህዝብ ምንም ናቸው። እግዚአብሔር እጃችሁን አንሱ ሲላቸው ዶ/ር አብይን መረጡ። እውነቱ ግን ብዙ እናቶች ልጆቻቸው ጠቅላይ ሚኒስተር (ንጉስ?) እንዲሆኑ

Created in Master PDF Editor

ይመኛሉ። የአንዷ እናት ይሰምራል የሌሎቹ ይከሽፋል ወይም እስከ ሚኒስተርነት ድርሰው ይወርዳሉ። መተንበዩ ግን መልካም ነው በተስፋ እንድንዘጋጅ እና ወደ ፊት እንድንገሰገስ ይረዳናል። ዶ/ር አብይና ኢትዮጵያ የተገናኙበት ሁኔታ የጻድቃን ቀጠሮ ይመስላል።ይህን ጉዳይ ዶ/ር አብይ ቢያውቁት አይከፋም። ወገኖች እናንተ ምን ትሆናላችሁ ተብላችሁ ነበር? ምንስ ሆናችሁ?

በነገራችን ላይ ስለ ዶ/ር አብይ የፕሮቴስታንት ነብያት የሚሉትን እና ከጅርባ ያለው ህዝብ እንዴት እንደሚጮህ ብትሰሙ የገብረ ህይወት ባይከዳኝ ትንታኔ ይገባችኋል።ትንቢቶቹ አንዳንዶቹ እንዲሁ የሚታወቁ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ የውሸት ክምሮች ናቸው። የህዝቡን ልብ ቀጥ ሲያደርጉት የሰማያት ጌታ እንዲህ ይላል ብለው ይጀምራሉ። ከዚያም ይጮሃሉ ህዝቡንም ያስጮሁታል ይገርማል ነብይነት እንዲህ ከሆነ በአፍንጫየ ይውጣ።

7. ግብረ-ገብነት የሚመነጨው ከእግዚአብሔር ነው እናም ግብረግብነት ስላለ እግዚአብሔር አለ

The greatest tragedy in mankind's entire history may be the hijacking of morality by religion. – (Arthur C. Clarke)

ሀይማኖት የሌለው ሰው ልጓሙ እንደተፈታ ፈረስ ነው-- (ከስብከት የሰማሁት)

Science . . . has been accused of undermining morals– but wrongly. The ethical behavior of man is better based on sympathy, education and social relationships, and requires no support from religion. Man's plight would, indeed, be sad if he had to be kept in order through fear of punishment and hope of rewards after death. – (Albert Einstein)

ብዙዎች ቅዱሳት መጻሕፍት ሰዎች መንግስተ ሰማይን ለመውረስ እንዴት መኖር እንዳለባቸው ተዕዛዛትን እና ህጎችን አስቀምጠዋል። የመጻሕፍቱ ህጎች ከዘመናዊ የወንጀል ህጎች ጠንከር ያሉ ናቸው። የሚሰጡት ሁለት አማረጭ ነው ህጎችን ላከበሩ የዘላለም ህይወት ለካዱ ዘለአለማዊ ቅጣት። እነዚህን ደንቦች የሚከተሉሰወችእግዚአብሔርን አዋቂ፣እና መልካም ሥነ ምግባር ያላቸውእንደሆኑ ይታመናል በተቃራኒው በራሳቸው ህግ የሚመሩ ኤቲስቶች ደግሞ መጥፎ ስብእና እንዳላቸው ይሰበካል፣ ይዶለታል። ስለነባራዊ አለሙ ግን ኦሻ እንዲህ ይላል፦ *"There are three hundred religions in existence in the world today. There are also millions of murders, suicides, rapes, robberies and continuous warfare, either in this part of the world or in another part of the world. What are these religions doing? And everybody*

Created in Master PDF Editor

is religious! Nobody is disloyal to his religion; he robs, he murders, he rapes, but he remembers that he is a Christian, that he is a Hindu, that he is a Mohammedan, that he is a believer in God, that he is a follower of Gautam Buddha.What does all this following mean? Sheer deception, not only to others, but to yourself. It is strange– so strange that it is almost unbelievable – that there are three hundred religions in the world and there is no peace, no joy, no celebration, no holiness, no divineness anywhere. All these religions are fake." (The Rebel, pege 93)

እንደ እውነቱ ከሆነ አምላክ የለም ባዮች እንደቡድን ከማንኛውም ቡድን ይልቅ የማይታመን ወይም ሥነ ምግባር ጉድለት እንዳለበቸው የሚገለፅምንም ማስረጃ የለም እንዲያውም በተቃራኒው እንደሆነ ይነገራል፡፡ በግለሰብ ደረጃ ካየን አጭበርባሪ፣ ሌባ፣ ከሀዲ፣ ገደይ እና ብልሹ እግዚአብሄርን አማኞች አሉ፡፡ አሳፋሪ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች እንዳሉ ሁሉ አሳፋሪ ለሰባአዊነት የማይገዙ ኤቲስቶች አሉ፡፡ ስለዚህኤቲስቶች እንደማንኛውም ኃይማኖተኛ ግለሰብ መልካም ባህሪን ወይም መጥፎ ባህሪን ይይዛሉ፡፡

እውነቱ ከምትጠብቁት ነገር ተቃራኒ ነው፡፡ ኤቲስት ዜና ለይኩን ለቴዎድሮስ ተ/አረጋይ እንደነገረው "አንዳንድ ሃይማኖቶች በእግዚአብሔር ስም የሚሰሩት ነውር ልክ የለውም፡፡ መጥቶ በድፍረት ሀጢያተኛ ነህ ይልሀል፡፡" (141, 104) አንዳንድ ኤትስቶች እንደሚሉት ሃይማኖቶች ሁከትን ያበረታታሉ፡፡ ለምን ብትሉ በአለም ታሪክ የተከሄዱት አብዛኛዎቹ ጦርነቶች መነሻቸው ሀይማኖታዊ ነው፡፡ *"If there is no evidence that religion generally makes people more likely to do the right thing, there is ample evidence that religion has led people to commit a <u>long litany of horrendous crimes.</u> Starting with God's command to Moses to slaughter the Midianites – men, women, boys, and non-virginal girls – and continuing through to the Crusades, the Inquisition, the Thirty Years War, and innumerable conflicts between Sunni and Shiite Muslims, we arrive in the present with one of the greatest threats to peace: religious fanatics who blow themselves up, based on the confident belief that this will assure them a place in paradise." (50 voices of disbelief, page 290)*

ደረጀ ፀጋዬ ሃይማኖት የሰላም ስጋት መሆኑን በአተተበት ጹህፉ እንዲህ ይላል "ሃይማኖት አልባ አለም ቢያንስ በሃይማኖት ምክንያት ከሚነሳ ትርምስ ነጻ ትሆናለች፡፡ ሃይማኖት የቆሰቆሰችው እንጂ ያበረደችው ጦርነት ስለመኖሩ ሰምቼ አላውቅም፡፡" ይላል (ደረጀ ፀጋዬ፣ የኢ-አማኒው ኑዛዜ) በሀገራችን የተካሄዱትን ጦርነቶች ሳስብ በእርግጥ ሀይመኖት የጦርንት ምንጭ ነውን የሚለው ጥያቄ ያስጨንቀኛል፡፡ ለምሳሌ የዮዲት ጉዲትን ወረራ፣ የግራኝ አህመድን ጦርነት እናለ7 አመት የዘለቀውን በአፄ ሱሰንዮስ ካቶሊክ መሆን የደረሰው የእርስ በእርስ ጥርነት

Created in Master PDF Editor

ማስታወስ በቂ ነው። ይህ ማለት ግን ሁልጊዜ በሃይማኖት እና በዓመፅ መካከል ቀጥተኛ ግንኙነትአለ ማለት አይደለም። ሀይመኖት ብዙ ጦርነቶችን እንዳስነሳ ሁሉ ሊከሰቱ የሚችሉ ጦርነቶችን እንዳስቀረ አምናለሁ። (መረጃ ባይኖረኝም)።

ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ በፍልስምና ቁጥር 3 ኤቲስቱን ዜና ለይኩንን ሃይማኖት ሌላው ሌላው ቢቀር በስነ ምግባር ትምህርት ቤትነቱ እንኳ አስፈላጊ አይሆንምን ሲል ይጥይቀዋል።

> ዜና ይመልሳል፡- “አይሆንም። ግብረገብነትን ሃይማኖት አይደለም የፈጠረው።ቡድሂስቶች ጋ ሂድ። (ኤቲስቶች ጋም እንሂድ) ከእኛ የበለጡ ደጎች ናቸው። ክርስትና ወይም እስልምና አይደለም ደግ ያደረጋቸው። ክርስትናን ወይም መጽሀፍ ቅዱስን አያውቁም። ማንኛውም ሃይማኖተኛ ጥቅምን አስቦ ነው እግዚአብሔርን ያመነው። ዘለዓለማዊ ህይወትን ለማግኘት ሲል። እኔ ደግ ስሆን ግን ምንም አስቤ አይደለም። ደግ መሆን ስላለብኝ ነው። አንተ ላይ ክፉ የማላደርገው እኔ ላይ ክፉ እንዲደረግ ስለማልፈልግ ነው። ይህ ደግሞ የሃይማኖት ህግ አይደለም። በሃይማኖት ስም አይደለም እንዴ ብዙ ሞትና እልቂት የደረሰው? አሜሪካ ውስጥ አንድ የካቶሊክ ቄስ አንድን ውርጃ የሚሰራ ዶክተር ቤቱ በር ላይ ገደለው። ከዚያ ሄዶ እጁን ለፖሊስ ሲሰጥ የእግዚአብሔርን ስራ ሰራሁ ነው ያለው ይህን የሰማ ስቲቨን ዊልበርግ የተባለ የፊዚክስ ሊቅ ምን አለ መሰለህ? ያለ ሃይማኖት ጥሩ ሰዎች ጥሩ፣ መጥፎ ሰዎች መጥፎ ሲሰሩ ታገኛለህ። ነገር ግን ጥሩ ሰዎች እርኩስ ነገር እንዲሰሩ ከፈለግህ ሃይማኖት ያስፈልግሃል ማለት ነው።” (ፍልስምና፣ ቁጥር 3፣ 2005 ዓ.ም፣ 101)

ዜና ይቀጥልና ሩቅ ሳትሄድ ይላል፡

> ሩቅ ሳትሄድ ሃይማኖተኞች የሚያምኑበትን ገሀነምን እግዚአብሔር ለምን ፈጠረው? ልጆቹ ምንስ ቢያጠፉ የሚመክርና ወደ ትክክሉ የሚመልስ እንጂ ህይወታቸውን በእሳት የሚለበልብ አምላክ እንዴት ኖረ? እኔ እንኳን ሰው የሆንኩት ፍጡር በልጄ ላይ ይህን አላደርግም። ክርስቶስ መሞቱን ራሱ አግባብ ነው? የልጅ ሞት ምን ያስተምራል? የእሱ ሞት አስተማረ የተባለውን ሁሉ ሳይሞት ማስተማር አይቻልም ነበር? እግዚአብሔር ሁሉን ይችላል እያልን እኮ ነው። ያለዚህ ስቃይና መከራ ሀጢያት ሁሉ እንዲጠፉ ማድረግ ለምን አይቻልም? ለምንድን ነው እኛ ለንፅፅር ደስታና መከራ የሚፈራረቅብን? አሟልቶ ስላልሰራን ወይም ሊሰራን ስለማይችል አይመስልህም? (ፍልስምና፣ ቁጥር 3፣ 2005 ዓ.ም፣ 101-102)

Created in Master PDF Editor

ሀይማኖቶች እንደሚሰብኩት እግዚአብሔር የግብረ ገብነትን ጉዳይ ያስተማረን በቅዱሳን መፅሐፍት ነው። በእርግጥ ቅዱሳን መፅሐፍት በተደረሱበት ዘመን የተዋጣላቸው የስነ-ዜጋ እና የስነ- ምግባር መማርያ መፅሐፍት ነበሩ። አሁን ገን መሻሻል ብቻ ሳይሆን መቀየር ሳይኖርባቸው አይቀርም። ለምን?

የሃይማኖት ጽሑፎች ጥንታዊ ናቸው፤ እናም የአሁኑን ዘመን እሴቶች አያንጸባርቁም። በተጻፉበት ዘመን ትልቅ መህበራዊ አስተዋፅኦ ነበራቸው። በጊዜ ሂደት አርጅተዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ወይም በቁርዐን ብዙ ጊዜ ያለፈባቸው እና ከዚህ ትውልድ ጋር የማይሰማሙ ትዕዛዛት አሉ በተለይ የባርያ ንግድን፣ የሞት ፍርድን እና ምንፍቅናን በተመለከተ። ክርስቲያኖች ለግብረ ገብነት ትልቅ ምሳሌ የሚጠቅሱት አስርቱን ትዛዛትነው። አስርቱን ትዛዛት ለእስራኤላዊን እንደተሰጣቸው የሚተርክል ኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 20 ነው። አስተውሉ አስርቱን ትዛዛት የሚባል የለም። ዘጸአት ምዕራፍ 20 እና 21 የተሰጡት ትዕዛዛት ብዙ ናቸው አብዛኛወቹ የሚያልቁት ግደሏቸው በሚል አሳፋሪ ቃል ነው። ቢሆንም ክርስቲያኖች ለሆድ የማይጎረብጡትን መርጠው 10ቱ ትዕዛዛት ይላሉ። እባካችሁ ዘጸአት ምዕራፍ 20፣ 21 እና 22 ሙሉውን አንብት።

ያም ሆነ ይህ እግዚአብሔር እና መጽሐፍ ቅዱስ የመልካምነት እና የግብረገብነት ምንጭ አለመሆናቸውን አንይ፦ለምሳሌ የባርያንግድን እና አያያዝን እንደ ምሳሌ እንውሰድ አሁንም በባርያ ንግድ የሚስማሙ አንዳንድ ሰዎች ቢኖሩም አብዛኛዎቹ ዘመናዊ ክርስቲያኖች የባርያ ንግድን ያወግዛሉ። አማኞች ቢያወግዙም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ባርነት፣ስለ ባሪያ ባለቤትነት እና አያያዝ ዝርዝር ደንቦች አሉት። ለምሳሌ፡- በዘሌዋውያን ምዕራፍ 25 ከቁጥር 44 እስከ 46 እንዲህ ይላል

> ‹‹ወንድ ባሪያና ሴት ባሪያ መግዛት ብትፈልግ ግን በዙሪያችሁ ካሉት ከእነርሱ ከአሕዛብ ወንድና ሴት ባሪያዎችን ግዙ። ደግሞም በእናንተ መካከል ከሚቀመጡት መጻተኞች፥ በምድራችሁም ውስጥ ከወለዱአቸው በእናንተ መካከል ከሚቀመጡት ከዘራቸው ውስጥ ባሪያዎችን ግዙ፤ ርስትም ይሁኑላችሁ። ከእናንተም በኋላ ልጆቻችሁ ይወርሱአቸው ዘንድ ተዉአቸው፤ ከእነርሱም ባሪያዎችን ለዘላለም ትወስዳላችሁ፤ ነገር ግን የእስራኤልን ልጆች ወንድሞቻችሁን በጽኑ እጅ አትግዙአቸው።››

ዘፀአት መዕራፍ 21 ከቁጥር 20 እስክ 21 ባሪያን ስለመደብደብ በተመለከተ በግልፅ አንድ ባሪያ ቢመታ እና በጥቂት ቀናት ውስጥ ቢሞት ባለቤቱ ይቀጣል ነገር ግን ባሪያው ከአንድ ወይም ከሁለት ቀን በኋላ ዳግመኛ ድኖ ቢነሳ ባለቤቱ አይቀጣም ምክንያቱም ባሪያው ንብረቱ ስለሆነ ነው ይላል።በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሳዛኝ

Created in Master PDF Editor

የሆነው ባርነት ብቻ አይደለም። በተለይየሞት ቅጣት የሚያስፈርዱ ተራ ወንጀሎች ተዘርዝረዋል።ኦሪት ዘሌዋውያን መፅራፍ 20 ከቁጥር 8 እስክ 17 እንዲህ ይላል፡-

> ሥርዓቴን ጠብቁ፥ አድርጉትም፤ እኔ የምቀድሳችሁ እግዚአብሔር ነኝ።ማናቸውም ሰው አባቱን ወይም እናቱን ቢሰድብ ፈጽሞ ይገደል፥ አባቱንና እናቱን ሰድቦአልና፤ ደሙ በራሱ ላይ ነው።ማናቸውም ሰው ከሌላ ሰው ሚስት ወይም ከባልንጀራው ሚስት ጋር ቢያመነዝር አመንዝራውና አመንዝራይቱ ፈጽመው ይገደሉ። ማናቸውም ሰው ከአባቱ ሚስት ጋር ቢተኛ የአባቱን ኀፍረተ ሥጋ ገልጦአል፤ ሁለቱ ፈጽመው ይገደሉ፤ ደማቸው በላያቸው ነው። ማናቸውም ሰው ከምራቱ ጋር ቢተኛ ሁለቱ ፈጽመው ይገደሉ፤ ጸያፍ ነገር አድርገዋል፤ ደማቸውም በላያቸው ነው።ማናቸውም ሰው ከሴት ጋር እንደሚተኛ ከወንድ ጋር ቢተኛ ሁለቱ ጸያፍ ነገር አድርገዋል፤ ፈጽመው ይገደሉ፤ ደማቸው በላያቸው ነው።ማናቸውም ሰው እናቲቱንና ልጂቱን ቢያገባ ርኵሰት ነው፤ በመካከላችሁ ኃጢአት እንዳይሆን እርሱና እነርሱ በእሳት ይቃጠሉ።ማናቸውም ሰው ከእንስሳ ጋር ቢገናኝ ፈጽሞ ይገደል፤ እንስሳይቱንም ግደሉአት። ማናኛይቱም ሴት ወደ እንስሳ ብትቀርብ፥ ከእርሱም ጋር ብትገናኝ፥ ሴቲቱንና እንስሳውን ፈጽመው ይገደሉ፤ ደማቸው በላያቸው ነው።ማናቸውም ሰው የአባቱን ልጅ ወይም የእናቱን ልጅ እኅቱን ቢያገባ፥ ኀፍረተ ሥጋዋንም ቢያይ፥ እርስዋም ኀፍረተ ሥጋውን ብታይ፥ ይህ ጸያፍ ነገር ነው፤ በሕዝባቸውም ልጆች ፊት ይገደሉ፤ የእኅቱን ኀፍረተ ሥጋ ገልጦአልና ኃጢአቱን ይሸከማል።

የኦሪት ግፍ በዚህ አያበቃም ዘፀአት ምዕ 31 ቁጥረ 14-16

> ለእናንተ ቅዱስ ነውና ሰንበትን ጠብቁ፤ የሚያረክሰውም ሰው ሁሉ ፈጽሞ ይገደል፥ ሥራንም በእርሱ የሠራ ሰው ሁሉ ከሕዝቡ መካከል ተለይቶ ይጥፋ። ስድስት ቀን ሥራን ሥራ፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ የዕረፍት ሰንበት ነው፤ በሰንበት ቀን የሚሠራ ሁሉ ፈጽሞ ይገደል። የእስራኤልም ልጆች ለልጅ ልጃቸው ለዘላለም ቃል ኪዳን በሰንበት ያርፉ ዘንድ ሰንበትን ይጠብቁ።

አሁንም የኦሪት ግፍ በዚህ አያበቃም ዘፀአት ምዕ 21 ቁጥር 12-17

> ሰው ሰውን ቢመታ ቢሞትም፥ እርሱ ፈጽሞ ይገደል። ባይሸምቅበትም፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ድንገት በእጁ ቢጥለው፥ የሚሸሽበት ስፍራ እኔ አደርግልሃለሁ። ሰው ግን ቢደፍር፥ ባልጀራውን በተንኰል ቢገድለው፥ እንዲሞት ከመሠዊያዬ አውጥተህ ውሰደው። አባቱን ወይም እናቱን የሚመታ ፈጽሞ ይገደል። ሰውን ሰርቆ ቢሸጥ፥ ወይም በእጁ ቢገኝ፥ እርሱ ፈጽሞ ይገደል።

Created in Master PDF Editor

አባቱን ወይም እናቱን የሚሰድብ ፈጽሞ ይገደል እያለ ይቀጥላል። በብሉይ ኪዳን በተለይ በኦሪት እግዚአብሔር ምን ያህል ሆረር ገፀ ባህሪ እንደተላበሰ አስቡት። ክርስቲያኖችን እና አይሁዶች ይህን ሁሉ ትዕዛዝ ስላልፈፀማችሁ በወረቀት ከተፃፈው መመሪያ በልባችሁ የታተመው ሰበአዊነት እንደሚበልጥ አወኩ።

አይሁዶች ዛሬም ድረስ ወዳጆቻቸውን ይወግራሉ ብየ አላምንም ቢያደርጉትም መንግስት ዘብጣያ ያወርዳቸዋል። ክርስቶስ ምስጋና ይግባውና ክርስቲያኖች እርስ በእርሳቸው ከመወጋገር በሚያድን መልኩ ንጹህ የሆነ ይውገራት በሚል ትምህርቱ የሰው ደም የጠማቸውን አሳፍሮ አሰናብቶአል።ይህን መሰረት አድርገው ክርስቲያኖች በአደባባይ መስቀልን እና ጥምቀትን እንጅ ውግራትን ሲያከብሩ አይተይም። ጥያቄ አለኝ ግን ለመሆኑ ኦሪት ተሽሮአል?

በእስልምና ትምህርት በቂ እውቀት ባይኖረኝም ግድያን በተመለከተ ማንኛውም ሰው እስልምና ሀይማኖቱን ቢተውና ቢተችቁዕራን መገደል አለበት እንደሚል አውቃለሁ። ለምሳሌ፦

- ቁዕራን 2:190-191 "እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን (ከሓዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ። ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎን አይወድምና። ባገኛችኋቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው። ከአወጧችሁም ስፍራ አውጧቸው። መከራም ከመግደል ይበልጥ የበረታች ናት። በተከበረው መስጊድም ዘንድ በርሱ ውስጥ እስከሚጋደሉዋችሁ ድረስ አትጋደሉዋቸው። ቢጋደሉዋችሁም ግደሉዋቸው፣ የከሓዲዎች ቅጣት እንደዚህ ነው።"
- ቁዕራን 4:89 "(እነርሱ) እንደ ካዱ ብትክዱና እኩል ብትኾኑ ተመኙ! በአላህም ሃይማኖት እስከሚሰደዱ ድረስ ከነሱ ወዳጆችን አትያዙ። (ከእምነት) ቢያፈገፍጉም ያዙዋቸው፤ (ማርኩዋቸው)። ባገኛችሁበትም ስፍራ ግደሉዋቸው። ከእነሱም ወዳጅንና ረዳትን አትያዙ።"
- ቁዕራን 8:39 "ሁከትም እስከማትገኝ ሃይማኖትም ሁሉ ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ተጋደሏቸው። ቢከለከሉም አላህ የሚሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነው።"
- ቁዕራን 9: <ከማመን መጠራጠር ይሻላል> "እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እነዚያን በአቅራቢያችሁ ያሉትን ከሓዲዎች ተዋጉ። ከእናንተም ብርታትን ያግኙ። አላህም ከሚጠነቀቁት ጋር መኾኑን ዕወቁ።"

ይህ በቁርዓን የተከተበው ሃተታ ግልፅነት የጎደለው ቢሆን የሚያወራው ተቃዋሚዎችንና እስልምናን ያልተቀበሉትን ስለመግደል ነው። ዛሬም በአረቡ አለም እስልምናን ትታችኃል፤ ነብዩን ተችታችኃል እና አላህ ተሳድባችኃል በሚል ጎዳና ላይ ንፁህ ደም ይፈሳል። የሚገርመው በመንግስት ደረጃ የሚደገፍ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የሚፈፀም ግድያ መሆኑ ነው።እኔ እማስበውን ካላሰብክ ብሎ

Created in Master PDF Editor

ሰው ሰውን እንዴት ይገድላል፡፡አስቀደሜ እንዳልኩት እስልምናን እና ቁዕራንን ለመተቸት በቂ ጥናት ያላደረኩ ቢሆንም ለዚህ ፁሁፍ ስል ቁዕራንን ሳገላብጥ በዚህ ቅዱስ መፅሀፍ ያገኘሁትን ላካፍላችሁ፡፡ እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ የሆነው አለህ የሚለንን ስሙ፡-

1ኛ. ቁዕራን 4:34 ‹‹ወንዶች በሴቶች ላይ ቋሚዎች (አሳዳሪዎች) ናቸው››፡፡

2ኛ. ቁዕራን 3:85 ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ እርሱ ተቀባይ የለውም፡፡ እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው፡፡

3ኛ. ቁዕራን 4:56 እነዚያን በተአምራታችን የካዱትን በእርግጥ እሳትን እናገባቸዋለን፡፡ ስቃይን እንዲቀምሱ ቆዳዎቻቸው በተቃጠሉ ቁጥር ሌሎችን ቆዳዎች እንለውጥላቸዋለን፡፡ አላህ አሸናፊ ጥበበኛ ነውና፡፡

4ኛ. ቁዕራን 7:50 የእሳትም ሰዎች የገነትን ሰዎች «በእኛ ላይ ከውሃ አፍስሱብን ወይም አላህ ከሰጣችሁ ሲሳይጣሉልን» ብለው ይጠሩዋቸዋል፡፡ እነርሱም «አላህ በከሓዲዎች ላይ እርም አድርጓቸዋል» ይሏቸዋል፡፡

5ኛ. ቁዕራን 17:97 አላህም ያቀናው ሰው ቅኑ እርሱ ብቻ ነው፡፡ ያጠመማቸውም ሰዎች ከእርሱ ሌላ ለእነርሱ ፈጽሞ ረዳት አታገኝላቸውም፡፡ በትንሣኤ ቀንም ዕውሮች፣ ዲዳዎችም ደንቆሮዎችም ኾነው በፊቶቻቸው ላይ እየተጎተቱ እንሰበስባቸዋለን፡፡ መኖሪያቸው ገሀነም ናት፡፡ ነዲድዋ በደከመች ቁጥር መንቀልቀልን እንጨምርባቸዋለን፡፡

6ኛ. ቁዕራን 18:29 «እውነቱም ከጌታችሁ ነው፡፡ የሻም ሰው ይመን፤ የሻም ሰው ይካድ» በላቸው፡፡ እኛ ለበደለኞች አጥሯ በእነሱ የከበበ የኾነችውን እሳት አዘጋጅተናል፡፡ ከጥም እርዳታንም ቢፈልጉ እንደ ዘይት ዝቃጭ ባለ ፊት በሚጠብስ ውሃ ይረዳሉ፡፡

7ኛ. ቁዕራን 22:19-22 እነዚያም የካዱት ለእነርሱ የእሳት ልብሶች ተለክተውላቸዋል፡፡ ከራሶቻቸው በላይ የፈላ ውሃ ይምቧቧቸዋል፡፡ በሆዶቻቸው ውስጥ ያሉ ቆዳዎቻቸውም በእርሱ ይቀልጣሉ፡፡ ለእነሱም መቅጫ ከብረት የሆኑ መዶሻዎች አሉ፡፡ ከጭንቀት ብርታት የተነሳ ከእርሷ ለመውጣት በፈለጉ ቁጥር ከእርሷ ውስጥ እንዲመለሱ ይደረጋሉ፡፡ «በጣም የሚያቃጥልንም ቅጣት ቅመሱ» (ይባላሉ)፡፡

8ኛ. ቁዕራን 40:49-50 እነዚያም በእሳት ውሰጥ ያሉት ለገሀነም ዘበኞች «ጌታችሁን ለምኑልን፤ ከእኛ ላይ ከቅጣቱ አንድን ቀን ያቃልልን» ይላሉ፡፡ ዘበኞቹም «መልእክተኞቻችሁ በተዓምራቶች ይመጡላችሁ አልነበሩምን? » ይላሉ፡፡ ከሓዲዎቹም «እንዴታ መጥተውናል እንጅ፤ ግን አስተባበልናቸው» ይላሉ፡፡ «እንግዲያውስ ጸልዩ፡፡ የከሓዲዎችም ጸሎት ከንቱ ቢሆንም» ይሏቸዋል፡፡

9ኛ. ቁዕራን 9:3 (ይህ) ከአላህና ከመልክተኛዉ በታላቁ ሐጅ ቀን የወጣ አላህ ከአጋሪዎቹ ንጹሕ ነው፣ መልክተኛዉም (እንደዚሁ)፤ (ከክሕደት) ብትጸጸቱም እርሱ ለናንተ በላጭ ነዉ

Created in Master PDF Editor

(ከእምነት) ብትሸሹም እናንተ አላህን የማታቅቱት መሆናችሁን ዕወቁ፤ በማለት ወደ ሰዎች የሚያደርስ ማስታወቂያ ነው፤

10ኛ. ቁዕራን 9:5 የተከበሩትም ወሮች ባለቁ ጊዜ አጋሪዎቹን በአገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሉዋቸዉ፤ ያዙዋቸዉም፤ ክበቡዋቸውም፤ ለነሱም (መጠባበቅ) በየመንገዱ ተቀመጡ፤ ቢጸጸቱም፤ ሶላትንም በደንቡ ቢሰግዱ፣ ግዴታ ምጽዋትንም ቢሰጡ፣ መንገዳቸውን ልቀቁላቸዉ አላህ መሐሪ አዛኝ ነውና።

11ኛ. ቁዕራን 9:29 ከነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች፣ እነዚያን በአላህ በመጨረሻዉ ቀን የማያምኑትን፣ አላህና መልክተኛዉ እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እዉነተኛዉንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ሆነዉ ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው።

ወድ አማኞች ከእነዚህ ትምህርቶች ግብረ ገብነትን ትማሩ ይሆን? እናንተ ብትሆኑ በልጆቻችሁ ላይ ይህን ሁሉ በደል ታደርሱ ይሆን? ተስፋ አደርጋለሁ እናንተ እስከዚ ድረስ ክፉ ለመሆን ህሊናችሁ አይፈቅድም።

የእስራኤልም ንጉሥ በቅጥር ላይ በተመላለሰ ጊዜ አንዲት ሴት ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፥ እርዳኝ ብላ ወደ እርሱ ጮኸች። እርሱም እግዚአብሔር ያልረዳሽን እኔ እንዴት እረዳሻለሁ ከአውድማው ወይስ ከመጥመቂያው ነውን አለ። ንጉሡም ምን ሆነሻል አላት፤ እርስዋም። ይህች ሴት ዛሬ እንድንበላው ልጅሽን አምጪ፤ ነገም ልጄን እንበላለን አለችኝ። ልጄንም ቀቅለን በላነው፤ በማግሥቱም። እንድንበላው ልጅሽን አምጪ አልኋት፤ ልጅዋንም ሸሸገችው ብላ መለሰችለት። (መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ምዕ. 6፥26-29)

እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው። ለአሮን እንዲህ ብለህ ንገረው። ከዘርህ በትውልዳቸው ነውር ያለበት ሰው ሁሉ የአምላኩን እንጀራ ያቀርብ ዘንድ አይቅረብ። ዕውር፥ ወይም አንካሳ፥ ወይም አፍንጫ ደፍጣጣ፥ ወይም ትርፍ አካል ያለው፥ወይም እግረ ሰባራ፥ ወይም እጀ ሰባራ፥ ወይም ጉባጣ፥ ወይም ድንክ፥ ወይም ዓይነ መጭማጫ፥ ወይም እከካም፥ ወይም ቋቍቻም፥ ወይም ጃንደረባ፥ ነውረኛ ሁሉ አይቅረብ። ከካህኑ ከአሮን ዘር ነውር ያለበት ሰው የእግዚአብሔርን የእሳት ቍርባን ያቀርብ ዘንድ አይቅረብ፤ ነውረኛ ነው፤ የአምላኩን እንጀራ ያቀርብ ዘንድ አይቅረብ። (ዘሌዋውያን ምዕ 21፥16-21)

ሁሉም ሃይማኖቶች ሁሉን ቻይ፣ ሀያልና ሁሉንም አፍቃሪ አምላክእንደሚያመልኩ ይናገራሉ። ሆኖም ግን እውነታ ከዚ ይቃረናል። አገኘሁ አሰግድ‘ላኩኝ የማይል ደብዳቤ’ በሚል ርዕስ ሸገር ብሎግ ላይ በጻፈው መጣጥፍ እንዲህ ነበር ያለው *“አምላክ ሆይ! የትም ቦታ አለህ አይደል? እንደ መፅሐፉ እውርም ዲዳም የምታደርግ አንተ ነህ።እንዲህ የሚያደርገው <ክብሩን ሊገልፅ ሲፈልግ ነው> ይባላል። ቆይ ያንተ ክብር*

Created in Master PDF Editor

አካል ካልጎደለ አይገለፅም? ላንተ የክብር መግለጫነት ሲባልስ፣ የገዛ ፍጡራንህን ማሰቃየት አለብህ? እንደምን ሆኖስ ሁሉ በእጅህ፣ ሁሉ በደጅህ እየተባለ የክብር መሻት ደጅህ ተገኘ? ክብር እኮ የኛ የተራዎቹ ጥያቄ ነው:: አንተን እንደምን ያስጨንቅሀል? ዳንኤል በአንበሳ ጉድጓድ በወደቀ ጊዜ፣ ሕይወቱን ያዳንክ አንተ፤ ዛሬ አንዲት ሕፃን በሕይወት እያለች በእሳት ስትቃጠል፣ የሁለት ዓመት ህፃን፣ በ40 ዓመት ወፈፌ ስትደፈር መመልከት እንደምን አስቻለህ?” እንደኔ እምነት አምላክ ቢኖር አስጨናቂ ነገሮች በሰዎች ላይ ሲከሰቱ፤ በየቀኑልጆች በአሳዛኝ ሁኔታ በርሃብና በጦርነት ሲሞቱ፤ የተፈጥሮ አደጋዎች ሚሊዮኖችን አፈናቅለው ሚሊዮኖቸን በወጡበት ሲያስቀሩ እና ወረርሽኝ ተነስቶ ህዝብ እንደቅጠል ሲረግፍ ደስ የሚለው አይመስለኝም:: <u>ደስ ካላለው ማስቀረት አለበት ካላስቀረው አይችልም ካልቻለ ደግሞ የለም ማለት ነው::</u>

ኤቲስት አክቲቪስቶች እግዚአብሔር ራሱ ጻድቅና ሩኅሩኅ አምላክ አይደለም ይላሉ:: ልክ ነው በተለይ የኦሪቱ እግዚአብሔር እምቢተኛ እና ጭካኔ የተሞላ፤ባለመረዳት ያላመኑበትን ገሃነም የሚያስገባ በተጨመሪም በተሳሳተ መንግድ ያመኑትን ሙስሊም፣ ሂንዱ፣ ቡዲስትዊ እና ይሁዲ በሲኦል ውስጥ የሚያቃጥል አምባገነን ነው:: (ዮሐንስ 3 18-36፤ 2ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 6 እስከ 10 እና ራዕይ ምዕራፍ 21 ቁጥር 8) ይህ የሲኦል ጽንሰ-ሐሳብ በክርስተና ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሃይማኖቶችም ተመሳሳይ ይዘት አለው:: ይህን ሳስብ ማመን ግድ ቢሆንብኝ በግሃነብ እንዳለ የሚታመነውን ምስኪኑ <u>ሰይጣንን</u> አመልክ ነበር እላለሁ:: ለምን ብትሉ ታላቅ የምድራችን ፈላስፋ ይሰሐቅ አሲሞቭ ይመልሳል፦ ‹‹ከገሀነም ይልቅ የምፈራው ገነትን ነው:: ገሀነም ውስጥ በእሳት እየተቃጠልክ ስለምትሰቃይ ሌላ ለውጥ ወይም ደግሞ መሰልቸት ትዝ አይልህም:: ነገር ግን ገነት ከገባህ ከሳምንት በላይ አትቆይበትም፣ ይሰለችሃል፣ ይታክትሃልም:: መከራን ካለወቅህ ደስታን እንዴት ታውቀዋለህ:: ደስታን ደስታ ያደረገው የመከራ መኖር ነው:: መከራን ስትረሳ ደስታ ትርጉሙ ይጠፋልና:: ስለገነትና ገሀነም ሳስብ ወይም ስሰማ ደስታን የሚሰጠኝ የሚጠብቀኝ የገነት አሊያም የገሃነም ሕይወት ሳይሆን ነገር ግን ገነትና ገሃነም የሚባል ነገር **አለመኖሩን ይበልጥ እርግጠኛ ስለሚደርገኝ ነው››** ይላል:: (ጥበብ ቅጽ አንድ፣ 2009፣ 135)

<u>ሁሉን ቻይ፣ ደግ፣ መሃሪ፣ ሩህሩህ፣ ፍትሃዊ እና አባታችን</u> የሚሉት ፈጣሪ ምንም ማድረግ የማይችል፣ ቀናተኛ፣ ጨካኝ፣ አሳሳችእና አዳይ (ሙሰኛ)ስም ሁኖ እናገኘዋለን:: የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት፣ ደግነት፣ መሃሪነት፣ ሩህሩህነት፣ ፍትሃዊነት እና አባትነት በመዝሙር ሲሆን ነው እንጅ በተግባር ሲሆን ቅር ያሰኛል::

Created in Master PDF Editor

በንፁሕ ደሙ ያዳነን

ከወደቅንበት ያነሳን፣

ብዙ ነው የእርሱ ውለታ

እንዘምራለን ለጌታ፣

እስከ ሺህ ትውልድ ይምራል

ፍቅር ነውና ይራራል፣

አይዝልም የእርሱ ትከሻ

መጨረሻ ነው መድረሻ:: (ምንጭ፦ ስሙ ያልተገለፀ ገጣሚ)

ሌላ ተወዳጅ መዝሙር ልጨምር፦

<<ይላል አንደበቴ እግዚአብሔር ቅዱስ ነው

አይተወኝምና ወላጅ እንደሌለው

ትላንት የጠበቀኝ የነገም ተስፋዬ

ትላለች ነፍሴ ፍቅር ነህ ጌታዬ

የትላንት ሕይወቴን ዞር ብዬ ሳየው

ማምለጫ የሌለው አጥሩም እሾህ ነው

ወደርስቴ ወጣሁ ይድረስ ምስጋናዬ

ደጆች ቢዘጉብኝ በር ሆኖኝ ጌታዬ/2/

በጥልቁ በረሃ ምግብ መጠጥ ሆኖኝ

መንገዴን አቀና እጄን በአፌ አስጫነኝ

በእሳትና ውሃ መካከል አልፌ

ተመስገን እላለሁ ቅኔ ሞልቶት አፌ/2/

የብቸኝነቴን መዐበል ገስጿል

ለኔ ብርሃን ሆኖ ለከሳሽ ጨልሟል

ቀስቱን እያለፈ ታደገኝ ከስቃይ

የጌታዬ ሃሳብ ፍቅር ነው በኔ ላይ /2/

ትላንት ዛሬ ነገ ዘላለም ጠባቂ

የልቤን ፍላጎት ሳልነግርው አዋቂ

Created in Master PDF Editor

በባህሪው ቅዱስ የሌለው አምሳያ

ስሙ መደቤ ነው መልህቄን መጣያ /2/>>

(ምንጭ፦ ይላል አንደበቴ ከሚል መዝሙር የተወሰደ)

ሁሉን አለመቻል፡- በመጽፍት “በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን? የዛሬ ዓመት እንደ ዛሬው ጊዜ ወደ አንተ እመለሳለሁ፤ ሣራም ልጅን ታገኛለች።” (ዘፍ. 18፡14) በወንጌልም “ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና።” (ሉቃ. 1፡37) ተብሏል። በስብከትም ሃይማኖተኞች የሚያመልኩት አምላክ ሁሉን እንደሚችል ይናገራሉ እንጂ በግልጽ ምንም ማድረግ አይችልም። እስኪ ምን ማድረግ ይችላል? ይህን ሃጢአት የምጽፍበትን ማይክሮሶፍት ወርድ ማስቆም ይችላል።አማኞች እንዲህ ይላሉ በሁሉም ነገር መቶ በመቶ(100%) እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ትክክለኛ ነው። ጥበቡ ወሰን የለውም። ስለ አንድ ነገር ሁለንተናውን ያውቃል። የጀርባ ታሪኩንና የወደፊቱን ስለ አንድ ነገር መረጃ አንሰጠውም፤ ምክር አንሰጠውም፤ አንድ ነገር እንዲሰራ አናባብለውም፤ እርሱ ያደርጋል። ችሎታ ስላለው፤ ሃሳቡም ቅንና ንፁሕ ስለሆነ። እግዚአብሔር አይሳሳትም፤ ደግሞም አያታልለንም፤ ሁል ጊዜ በማንኛውም ሁኔታ ትክክለኛ ነገር እንደሚሠራ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ መሆን እንችላለን ወዘተ ይላሉ። ሀሳባቸው በተግባር ሲመዘን፣ በአማክንዮ ሲበጠር ግን ገለባ ነው።“*ፍፁማዊና ሁሉን ቻይ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ልክ እንደ ሰው የሚመኝ፣ የሚፈልግ፣ የሚደሰት፣ የሚያዝን፣ የሚታገስ፣ የሚራራ… ወዘተ እንደሆነ ይታመናል። እነዚህ ሁለቱ የሁሉን ቻይነት ባህሪና ሰዋዊ ስሜቶች አንድ ላይ ተስማምተው የሚኖሩ አይደሉም። ፍፁማዊና ሁለን ቻይ የሆነ አምላክ በውስጡ ምኞትንና መደሰትን የመሳሰሉ ሰዋዊ ስሚቶች ሊኖሩት አይችልም። ፍፁማዊነቱና ሁሉን ቻይነቱ እግዚአብሔርን ምኞትና ስሜት አልባ ያደርገዋል። እግዚአብሔር የሚፈልግ (የሚመኝ) ከሆነ የሁሉን ቻልነትና የፍፁዊነት ባህሪ ሊኖረው አይችልም። ምክንያቱ የፍፁማዊነት ባሕሪው የመፈለግ ስሜቱን ይገድልበታልና። ፍፁማዊ የሆነ ነገር በሁሉ ነገር ምልዑ ስለሆነ እጥረት ስለሌለበት ከውጭ የሚፈልገውና የሚመኘው ነገር ሊኖር አይችልም። እናም እግዚአብሔር በሁለመናው ፍፁማዊ ከሆነ ሰዎች ላይ በስማት ጥገኛ ሊሆን አይችልም። በሰዎች ስራም ሊቆጣም ሆነ ሊደሰት አይችልም። አለበለዚያ እግዚአብሔር የሚፈልግ፣ የሚደሰት፣ የሚያዝን፣ የሚራራ፣ የሚያፈቅር…. ወዘተ ስሜቶች ካሉት በራሱ ፍፁም ሊሆን አይችልም፤ ያልተሟላና ሰዎች ላይ ጥገኛ ነው ማለት ነው። እግዚአብሔር ፍፁም ከሆነ ግን ያለጥርጥር ስሜት አልባ ነው የሚሆነው፤ ከሰዎችም ሆነ ከዚህ ዓለም የሚፈልገውም አንዳች ነገር የለውም።”* (ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣ 92-93)

Created in Master PDF Editor

ደግ፣ መሃሪና ሩህሩህ አለመሆኑ፦"If Jesus could heal a blind person he happened to meet, then why not heal blindness?" ይል ነበር ክርስቶፎር ሂችን:: አማኞች እግዚአብሔርደግ፣ መሃሪና ሩህሩህ ስለመሆኑ ይመሰክራሉ:: የፈጠራቸው ፍጡራን ሲበድሉ፣ እግዚአብሔር ድካማቸውን በመረዳት ይታገሳቸዋል:: ለፍጡሩ በጎነትን ማሳየት ደስ ስለሚያሰኘው፣ በሕይወታቸው መልካሙን ያደርግላቸዋል፣ ከመከራም ያሳርፋቸዋል ይላሉ:: እኔም ከ2ኛ ደረጃ እስከ ዩንቨርስቲ ድረስ በሰንበት ት/ቤቶችና በግቢ ጉባዔያት በተደጋጋሚ የሚዘመረውን (በተለይ አርብ አርብ) 'ምሕረቱ ለዘላለም ነውና' የሚለውን የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ 136ን ስዘምር ነበር:: እስኪ መዝሙር 136 ከቁጥር 10-20 ያለውን ዘምሩትና የዘላለም ምሕረቱን አሳዩኝ::

10 ከበኵራቸው ጋር ግብጽን የመታ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤

11 እስራኤልንም ከመካከላቸው ያወጣ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤

12 በጸናች እጅ በተዘረጋችም ክንድ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤

13 የኤርትራን ባሕር በየክፍሉ የከፈለ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤

14 እስራኤልን በመካከሉ ያሳለፈ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤

15 ፈርዖንንና ሠራዊቱን በኤርትራ ባሕር የጣለ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤

16 ሕዝቡን በምድረ በዳ የመራ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤

17 ታላላቅ ነገሥታትን የመታ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤

18 ብርቱዎችንም ነገሥታት የገደለ፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤

19 የአሞራውያንን ንጉሥ ሴዎንን፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤

20 የባሳንን ንጉሥ ዐግን፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤

ቀናተኛነት፡- አምላክ በሃይማኖተኞች ዓይን ቀናተኛ ተደርጎ ተስሏል:: ፍጡሮቼ በሰራሁላቸሁ ነፃ አእምሮ ሌላ አመለኩ ብሎ ቁጣውን ያዘንባል ሲሉ መጽሃፈ አምልኮዎቹ ይነግሩናል:: ለምሳሌ፦ዘፀአት 23:23 *"አንተ ግን ቃሉን ብትሰማ፥ ያልሁህንም ሁሉ ብታደርግ፥ ጠላቶችህን እጣላቸዋለሁ፥ የሚያስጨንቁህንም አስጨንቃቸዋለሁ:: መልአኬ በፊትህ ይሄዳልና፥ ወደ አሞራውያንም ወደ ኬጢያውያንም ወደ ፌርዛውያንም ወደ ከነዓናውያንም ወደ ኤዊያውያንም ወደ ኢያቡሳውያንም ያገባሃል፤ እኔም አጠፋቸዋለሁ:: ለአማልክቶቻቸው አትስገድ፥ አታምልካቸውም፤ እንደ ሥራቸውም አትሥራ፤ ነገር ግን ፈጽመህ አፍርሳቸው፥ ሐውልቶቻቸውንም ሰባብራቸው::"*እስኪ እግዜር ያሳያችህ የማይቆጠሩ አምላኪዎች

Created in Master PDF Editor

ያሉት ጌታ እንዴት ጣኦቶች በጥቂት ሰዎች ተመለኩ ብሎ ይቀናል። ጭራሽ በይፋ እኔ አምላክህ ቀናተኛ ነኝ ይላል።

ጨካኝነት፡- የሃይማኖተኞች አምላክ በየዓለማቱ እየተከሰተ ላለው የተፈጥሮ አደጋ፣ ረሃብ፣ ጦርነትና ለሁሉም ችግርተጠያቂ ነው፤ ያለ ፈጣሪ እውቅና የሚከናወን ጉዳይ የለም ተብለን ተምረናልና። ሂትለር ላጠፋው ጥፋት ፈጣሪ መከሰስ አለበት። ሂትለር እኮ ተዋናኝ ነው አድርግ የተባለውን የፈጣሪ ፍቃድ ብቻ ነው የሚያደርግ። ሂትለር በራሱ ነፃ ፍቃድ እና ሀይል ቢያደርገውም እንኳ ከአምላክ ጋር ሲነፃፀር ግን ቅዱስ ሊባል ይችላል። በጭካኔ ተግባሩ የማይጸጸት የማውቀው እግዚአብሔርን ብቻ ነው፣ ሰይጣን እንደተፀፀተ ለተክለ ኪዳን ነግሮታል። *"እኛ ሰይጣናት እንደ እናንተ ደግሞ ወደ መንግስተ ሰማያት ወደ መጀመሪያ መኖሪያችን <u>የመመለስ ዕድል ቢሰጠን</u> ኖሮ ሌት ተቀን እግዚአብሔር ደስ በሚሰኝበት ተግባርና ሀሳብ ውስጥ በተመላለስን ነበር! ነገር ግን እኔ ዋነው አለቃቸው ዲያቢሎስ የተባልኩ ሆነ ሠራዊቶቼ ሰይጣናት የተባሉት ሁሉ <u>በነጻ ኅሊናችን ተመርተን</u> በእግዚያብሔር ላይ ዓመጻና ክህደት በመፈጸማችን እንዲሁም እንዳንዶቹ 'እኔ ነኝ የፈጠርኳችሁ ለእኔ ተገዙ፣ እኔን አምልኩ' ስል፣ እንደነ ሚካኤልና ገብርኤል መቃወምና ከእነርሱ ጋር መሰለፍ ትተው 'ምናልባት ጌታችን ሊሆን ስለሚችል ከእርሱ ጎን መሰለፍ አለብን ያሉት ሁሉ ጸጋቸው ተገፎ በመሳሌያዊ ባሕርያ (በረቂቅ አካል) ተገልጸው ፍዳቸውን በዚህች ምድር ያያሉ።።"* (የጨለማው ገዥ ተግባርና ንግግር፣ 2009 ዓ.ም፣38)ዘፍጥረት 7:21-23 *"በምድር ላይ ሥጋ ያለው የሚንቀሳቀሰው ሁሉ፥ ወፉም፥ እንስሳውም፥ አራዊቱም፥ በምድር ላይ የሚርመሰመሰው ተንቀሳቃሹም ሁሉ፥ ሰውም ሁሉ ጠፋ። በየብስ የነበረው በአፍንጫው የሕይወት ነፍስ እስትንፋስ ያለው ሁሉ ሞተ። በምድር ላይ የነበረውም ሁሉ ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ድረስ፥ እስከሚርመሰመሰውም ሁሉ ድረስ፥ እስከ ሰማይ ወፍ ድረስ ተደመሰሰ፤ ከምድርም ተደመሰሱ። ኖኅም አብረውት በመርከብ ከነበሩት ጋር ብቻውን ቀረ።" ዘፍጥረት 7:21-23 "እግዚአብሔርም በሰዶምና በገሞራ ላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ እሳትና ዲን አዘነበ፤ እነዚያንም ከተሞች፥ በዙሪያቸው ያለውንም ሁሉ፥ በከተሞቹም የሚኖሩትን ሁሉ፥ የምድሩንም ቡቃያ ሁሉ ገለበጠ። የሎጥም ሚስት ወደ ኋላዋ ተመለከተች፥ የጨው ሐውልትም ሆነች።"*

በጣም ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔር ጭካኔ እንደመልካም ነገር ሲዘክሩት መስማት የተለመደ ነው። ለምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፦ምሳሌው በእግዚአብሔር አስደናቂ ተአምራት፣ በጸናች እጁና በተዘረጋች ክንዱ ከ430 ዓመታት መራርና እንደ መርግ ከከበደ ከግብጽ የባርነት ሕይወት ነጻ የወጡ እስራኤላውያን፤ ቀይ ባሕርን ከፍሎ በማሻገር ጠላቶቻቸውን ፈርኦንና ሠራዊቱን ዓይናቸው እያየ በባሕረ ኤርትራ ሲሰጥም ያዩ በሊቀ ነብያት ሙሴ የሚመራው ሕዝቦች ታሪክ ነው። ታሪኩን ፍቅር ለይኩን በአዲስ አድማስ ድህረ ገፅ እንዲህ በኩራት ይተርከዋል፦ "ሙሴ የሚመራው ሕዝብ

Created in Master PDF Editor

አመጸኛ፣ ገልበጥባጣና ነውጠኛ ሕዝብ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ሙሴን፦ ‹‹ይህን እንደ ቀስት የሚገለባበጥ ጠማማ፣ አመጸኛና ሸንጋይ ሕዝብ ከምድረ ገጽ ***አጥፍቼ አንተን ለሌላ ታላቅ ሕዝብ እሾማሃለሁ፡፡››*** *ባለው ጊዜ ‹‹ይህን ሕዝብ በምድረ በዳ አጥፍተህ የአሕዛብ መሳለቂያ ከምታደርገን* ***እኔን ከሕይወት መጽሐፍ ደምስሰኝ!››*** *አለ፡፡ ትሑቱና የዋሁ ሙሴ ብዙ ዋጋ የከፈለላትንና የናፈቃትን የተስፋይቱን ምድር በሩቅ ከመሳለም ባለፈ ለማየት አልታደለም፤* ***አጥብቆ ፈጣሪውን ቢማጸንም አልሆነም፡፡*** *የገዛ ሕዝቡና ወገኑ አምላኩን በተፈታተነበት ግብዝ ጥያቄ ተሰነካክሎ፣ ሙሴ ቅዱሱን የያሕዌን ስም ባለመቀደሱ ምክንያት ከተስፋይቱ ምድር እንዲጎድል ሆነ፡፡ ሙሴ ብቻ ሳይሆን ከግብጽ ባርነት ከወጡት ስድስት መቶ ሺህ ከሚሆኑ ሕዝቦች መካከልም የተስፋይቱን ምድር በዓይናቸው ለማየት፣ በእግራቸው ለመርገጥ ዕድሉን ያገኙት ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ፡፡* ***ኢያሱና ካሌብ ብቻ፡፡*** *ሌሎቹና በበረሃ በድናቸው የአሸዋ ሲሳይ ሆኖ ነው የቀረው፡፡"*(https://www.addisadmassnews.com/) ይህን እጅግ አሳፋሪ የጭካኔ ታሪክ መፅሃፍ ላይ መጻፉ ገርሞን እያለ ጭራሽ ያልሰማችሁ ስሙ በሚል መጽሄት ላይ ይለጥፉታል፡፡ ለነገሩ እግዚአብሔር እኮ እንዲህ ተብሎ ተዘምሮለታል፦

በሰማይና በምድር በባሕርና በጥልቆች ሁሉ፥ እግዚአብሔር የወደደውን ሁሉ አደረገ፡፡

ከምድር ዳር ደመናትን ያወጣል፤ በዝናብ ጊዜ መብረቅን አደረገ፤ ነፋሳትንም ከመዛግብቱ ያወጣል፡፡

የግብጽን በኵር ልጆች ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ድረስ መታ፡፡

ግብጽ ሆይ፥ በመካከልሽ በፈርዖንና በባሪያዎቹ ሁሉ ላይ ተኣምራትንና ድንቅን ሰደደ፡፡

ብዙ አሕዛብን መታ፥ ብርቱዎችንም ነገሥታት ገደለ፡፡

የአሞራውያንን ንጉሥ ሴዎንን፥ የባሳንንም ንጉሥ ዐግን፥ የከነዓንን መንግሥታት ሁሉ ገደለ፤

ምድራቸውንም ርስት አድርጎ ለእስራኤል ለሕዝቡ ርስት ሰጠ፡፡ (መዝ. 135: 6-12)

ሰዎችን ለዘመናት በእሳት ማሰቃየት የሚፈልግ ፈጣሪ ምድር ላይ አሉ ተብለው በጭካኔያቸው በታሪክ የምናቃቸው ሰዎች እንኳን ይህን ያህል ጭካኔ ሳያሳዩ ነው ጨካኝ የሚል ስም የሰጠናቸው፡፡ ፈጣሪ ለዘላለምመጠኑ ምድር ላይ ከምናውቀው እሳት ሀይሉ የማይገናኝ በሆነ እሳት እጠብስሀለሁ እያለ ቢሆንም ጨካኝ ሳይሆን ፍቅር፣ ሩህሩህ፣ አባት፣ አዳኝ፣ ህይወት፣ መንገድ እናመጠጊያ በማለት እንገልፀዋለን፡፡

አሳሳች፦እግዚአብሔርታምራቱን ለመግለፅ በሰው ልብ ውስጥ ገብቶ ሰዎችን ሊያሳስት እንድሚችል የሙሴ መፅሃፍ ይነግረናል፡፡ኦሪት ዘጸአት ከምዕራፍ 6 እስከ 12 ያለውን መረዳት እግዚአብሔር ምን ያህል አሳሳች እንደሆነ ለማወቅ አይከብድም፡፡

Created in Master PDF Editor

“እግዚአብሔርም ሙሴን ተአምራቴ በግብፅ አገር ብዙ እንዲሆን ፈርዖን አይሰማችሁም አለው። ሙሴና አሮንም ተአምራቶች ሁሉ በፈርዖን ፊት አደረጉ፤ እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ አጸና፥ የእስራኤልንም ልጆች ከአገሩ አልለቀቀም።”ዘፀአት 11: 9-10 ክርስቲያን ሰባኪዎች የልበ ደንዳነት መለኪያ የሚያደርጉት ፈርዖን ጥፋቱ የቱ ጋ ነው? የተሰጠውን ገጸ-ባህሪ በሚገባ ተጫውቷል፣ ሊሸለም እንጅ ሊወቀስ አይገባም።

ስብሐት ገ/እግዚአብሔር እንዳለው “እኔም አንተም ገፀ ባህሪያት ነን። ልዩነቱ ደራሲያችን ሰው ሳይሆን ፈጣሪ ራሱ መሆኑን ነው። በሰው ቃላት ሳይሆን በስጋና ደም የፃፈን። ፈጣሪ እየፃፈን፣ እየፃፈን ከልጅ ልጅህ ተወልጄ ኃጢያትህን እከፍልልሃለሁ ከሚለው ጋ ሲደርስ የገዛ ድራማው ነሸጠውና <ይኼኛውን ገፀ ባህሪ እንኳን እኔ ራሴ መጫወት አለብኝ> ብሎ ዙፋኑ ፊት የሚቆመውን ገብርኤልን ልኮ ድንግል ሆይ ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ አስባለ።” (ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣ 49) ያሳዝናል የአምላክ የመጨረሻው የጭካኔና የአሳሳችነት ጥጉ ፍጥረታትን እንደ አሻንጉሊት መጫወቻ ማድረጉ እና ተጫውቶብን ስንሰለቸው ወደ እሳት መጣሉ ነው።

ይህ ነው ህይወትን ባዶ የሚያደርገው እምነት፣ እኔ አሻንጉሊትና ማስተላለፊያ ቱቦ ነኝ ብሎ ማመን። አሻንጉሊትነት ቢሆንም በጌታ የተባረከ የህይወት ትርጉም ነው የሚባለው አተያይ የማይዋጥልን እንዲህ እንላለን፦ *“እግዚአብሔር ሕልውና ቢኖረውኳ እኛ የእርሱ እቃዎች ወይም አገልጋዮች ሁነን በመፈጠራችንና በእርሱ ሐሳብና ስራ ውስጥ የእኛ ሀሳብ፣ ፍላጎት ወይም ፍቃድ ስለሌለ የእግዚአብሔር የሆነ ነገር የእኛ ሕይይት ትርጉም ሊሆን አይችልም። የእግዚአብሔር ሐሳብና ሥራ ሁሉ ለእርሱ ነው፣ ሰውን ጨምሮ የተፈጠረው ሁሉ የእርሱ ነው፣ የእርሱ ነገር የእኛ ነው ማለት አንችልም፤ የእኛ ያልሆነ ነገር ደግሞ የሕይወታችን መገለጫ፣ ትርጉምና ግብ ሊሆን አይችልም።”* (የህይወት ትርጉም፣ 2002 ዓ.ም፣ 36) ምን አልባት ሰዎች ሁሉ በእርሱ የሆነ ያለ እርሱ አንዳች የማይሆን ሲባልላቸው ደግነት ይመሳላቸዋል እውነቱ ግን ጣልቃ ገብነት ነው። ብዙ ፈላስፎችና ሳይንቲስቶች ከዚህ ጣልቃ ገቢ ጨካኝ ፈጣሪ ለመሸሽ አንድ ሃይል አለ ይላሉ።

ማዳላት፦እግዚአብሔር በፍርዱ ማዳላት የሌለበት እውነተኛ በቅዱስ መጽሃፍ ተመስክሯል። “እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለምና፥ እንደ አምላካችንም ጻድቅ የለምና፤ ከአንተ በቀር ቅዱስ የለም።” (1ሳሙ 2:2)፣ “ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።” (2ጢሞ 4:8)፣ “ከመሰዊያውም። አዎን፥ ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥ ፍርዶችህ እውነትና

ጽድቅ ናቸው ብሎ ሲናገር ሰማሁ፡፡” (ዮሐንስ ራእዩ 16፡7) በሃይማኖተኞች ዓለም ሁሉም ሰዎች የፈጣሪ ፍጡራን ቢሆኑም ጥቂቶቹ ግን የአምላክ ልጆች ናቸው፤ አንዳንዶቹ ፈጣሪ ቀድሞ በጻፈላቸው እኩይ ገፀ-ባሕሪ ተላብሰው ሲተውኑ ሌሎቹ ደግሞ ለመጽደቅ እንዲችሉ ሁነው ይመረጣሉ፣ አንዳንዶቹ አዕምሮ ዘገምተኛ ሁነው ሲፈጠሩ ሌሎቹ ባለብሩሕ አዕምሮ ይሆናሉ፡፡ ግን እግዚአብሔር ብሔሩ ምንድን ነው? ማንን ይወዳል ማንን ይጠላል? እስኪ እንይ፡- *“ሙሴም አለ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በእኩል ሌሊት እኔ በግብፅ መካከል እወጣለሁ፤ በግብፅም አገር ያለ በኵር ሁሉ፥ በዙፋኑ ከሚቀመጠው ከፈርዖን በኵር ጀምሮ በወፍጮ እግር እስካለችው እስከ ባሪያይቱ በኵር ድረስ፥ የከብቱም በኵር ሁሉ ይሞታል፡፡ በግብፅም አገር ሁሉ አስቀድሞ እንደ እርሱ ያልሆነ ኋላም ደግሞ የማይሆን ታላቅ ጩኸት ይሆናል፡፡’*ዘፀአት 11፡ 4-6 ከዚህ አንጻር ስመለከተው እግዚአብሔር የእስራኤል ጠ/ሚኒስተር ይመስለኛል፡፡ ይህ ዛቻ የብሔርተኛ ፖለቲከኞች የበላይነት ማሳያ እንጅ የፈጣሪ አይደለም፡፡

የሰላምና የፍቅር አምላክ እግዚአብሄር ቢኖር ኑሮ ቢያነስ ልጆቹን፣ ፍጥረቱን ለዘላለም አይጎዳም፣ በአጋጣሚ በተሳሳተ አምላክ በሚያምኑም ስቃይ አይፈርድም፣ የተሳሳተ ቅዱስ መጽሐፍን በመከተል ወይም የተሳሳቱ ቤተ እምነቶች በማገልገል ሲኦልን አይሸልምም፡፡ ልጁን በእሳት በመለብለብ የሚደሰት አባት የለም፡፡ አምላክ የሆነ ብሔር፣ የሆነ ግለሰብና የሆነ ሀገር ላይ ያነጣጠረ መሆን የለበትም፡፡ ሲያድን፣ ሲባርክምና ሲያጠፋ ሚዛናዊ መሆን አለበት፡፡ ደግሞስ የሰው ልጅ ሁሉ እኩል ይወደው ዘንድ እኩል ሊያፈቅረን፣ ተገቢ መልስ ሊሰጠን ይገባል፡፡ እውነቱን ግን <ከማመን መጠራጠር ይሻላል> በብስጭት እንዲህ ይላል፡-

> *“በኤች አይ ቪ፣ በካንሰር፣ በደም ብዛት፣ በስትሮክ፣ በልብ ህመም፣ በስኳር ህመም፣ በጭንቀት፣ በርሃብ፣ በጦርነት፣ በቆሻሻ ክምር፣ በኢሊኖ ድርቅ.... ስንሰቃይ ለምን ዝም ጭጭ ይለናል? ሌላዉ ቢቀር ምንም የማያዉቁ ህፃናት እነኝህን በአደጋወች ሲሰቃዩና ህይወታቸዉ ሲጠፋ ለምን ዝም ይላቸዋል? ታድያ እንደዚህ ያለዉ ሳይፈልጉ ለፈጠራቸዉ ፍጡራን ርህራሄ የሌለዉ አምላክ እንዴት ፈጣሪ ሊባል ይችላል? እኛ ስንቸገር አይረዳንም፡፡ እሱ ግን የኛን ፍላጎት ረግጠን እሱን ብቻ እንድናመልከዉ ያዘናል፡፡ አትደሰቱ የናንተን ፍላጎት ተዉት... ለኔ ብቻ ስገዱ፣ ዘመሩ፣ አጨብጭቡ ወ.ዘ.ተ ይለናል፡፡ ጥራችሁ ግራችሁ ብሉ ብሎ ከረገመን በሁዋላ እንደገና ሁሉን ጠይቁ እሰጣችሁዋለሁ ብሎ ስንጠይቀዉ ዝም ካለን በሁዋላ እኛ ምን እየበላን እንድናጨበጭብለት ፈለገ?”*

Created in Master PDF Editor

በአጠቃላይ በዚህ ዘመን ካሉት አማልዕክት አንዳንድ በጎ ነገሮች ባይጠፉም የስነ-ዜጋና ስነ-መግባር ትምህርት ምንጭ ሊሆኑ አይችሉም። ስነ ምግባር በሰወች የጋራ ጥረት የሚመሰረት ነው። ፈረንጆቹ ሶሻል ኮንትራት (Social Contract) የሚሉት ታላቅ የስምምነት ሰነድ ነው።እንደምሳሌም 1948 የጸደቀውን የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ ተጠቃሽ ነው። ይህን ድንጋጌና የአማልዕክትን ድንጋጌ የሚያነጻጽር ሰው እኛ ሰዎች አማልዕክትን ምን ያህል እንደበለጥናቸው ይረዳል።

ሳይንስስነ ምግባር እድገት ከሰው ልጆችን ለውጥና እደገት ጋር የሚያድግ የተሰጠን ሳይሆን እንደ ሰው ለመቀጠል በግንኙነቶች የሚፈጠርና በጊዜ ሂደት የሚቀየር እንዲሁም በቦታ የሚወሰን ነው ይላል። ስለዚህም ግልፅ ነው ሥነ ምግባር ከሃይማኖት ውጭ ሊሆን ይችላል። በእርግጥግብረ ገብነት በሰዎች ብቻ የተወሰነ አይደለም እንስሳትን ተመልከቱ ወንጌል አልተሰበኩም ቁርአን አልቀሩም አንዳንዴ ከሰው የተሸለ ርህራሄ ታያላችሁ። በአጠቃላይ በአብዛኛው የግብረ ገብነት ምንጩ ማህበራዊ ግንኙነት እንጅ አምላክ አይደለም። የመጽሃፍት ሰዎች የሚሰብኩት ጦረኛ፣ ቀናተኛ፣ ጨካኝ፣ አሳሳች እና ሙሰኛ ለስነ መግባር መሰረት ነው ማለት ለሂትለር የኖቬል ሽልማት እንደመስጠት ነው። እና የስነ መግባር መሰርቱ የት ነው ለምትሉኝ ከ100 አመታት በፊት Morality is not the offspring of theology የሚለው Lemuel K. Washburn በሚገባ መልሶታል። የስነ መግባር መሰረቱ ሀይማኖት ሳይሆን እራሱ ሰውና ተፈጥሮ ናቸው። "There is nothing that tends to perpetuate the weakness of humanity more than religion. Men have been taught for ages that they were dependent upon God for all they have. This kind of teaching must be corrected; it is false.Man is dependent upon man.No God will help or hurt him. What he wants to escape is his own condemnation. In order to develop an independent spirit in man it is necessary to increase his responsibility. Man must be taught to rely upon his own strength, upon his own body and mind. He must learn his relations to Nature and abide by the laws of his being." (Lemuel K. Washburn, page 52)

ሰዎች አማኞችም ኤቲስቶችም የስነ መግባር ተገዥ ሊሆኑ ላይሆኑም ይችላሉ። የስነ መግባር ሊህቃን የሰው ልጅ በስነ መግባር ስላመጣው መሻሻል በርካታ መላምልቶችን አስቀምጠዋል። ምን አልባት ሀይማኖት (Divine command theory) አንዱ መላምት ቢሆን እንጅ ዋና ምንጭ አይደለም። ይህም ቢሆን በትችቶች የተሞላ ዝቅተኛ ግምት ከሚሰጣቸው መላምልቶች የሚመደብ ነው። ይህ ሁኖ እያለ ሰባኪዎች ያለ ሀይማኖት ሰው መልካም አይሆንም እያሉ ይሰባካሉ በተለይ የኛ ሰፈር ሰባኪዎች።

Created in Master PDF Editor

ሰባኪዎች ስለ ኤቲስቶች ክፉነት ሲያነሱ የሩሲያውን እስታሊንን፣ የቻይናውን ማኦ ዘዱንግን እና የከምቦዲያውን ፓል ፖት ሳያነሱ አያልፍም። እነዚህ ጨካኝ መሪዎች ኤቲስቶች ነበሩ። ጨካኝ ጨፍጫፊም ነበሩ። መጠየቅ ያለበት ነገር እነዚህን ሰዎች ጨካኝ ያደረጋቸው የትኛው የኤቲስት ዶግማ ነው? ኤቲስት በተፈጥሮው ጨካኝ ቢሆን ኖሩስ በአለም ላይ ያሉት ግማሽ ቢሊዩን ኤቲስቶች አለምን በሰዓታት ማጥፋት አይችሉም ነበር? ሳዳምሁሴን፣ ኡመር አልበሽር፣ የመስቀል ጦርነቱ አስጀማሪ ፓፕ ኦርባን 2ኛ እና በዙ አሳዳጅ አማኞች እንዳሉ ሁሉ አንዳንድ መጥፎ ኤቲስቶች ሊኖሩ ይችላሉ።

ኤቲስት መሆን ክፉ አያደርግም? አማኝ መሆንም ብቻውን ደግ አያደርግም። አማኝ መሆን ብቻውን ደግ ቢያደርግ ኑሮ መሬት እንዴት ገነት በሆነች ግን አይደለም ፅንፈኞች ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ክቡሩን የሰው ልጅ ህይወት ይቀሰፋሉ። ይቅር አይበላቸው።

8. አምላክ ባይኖር ኖሮ በአምላክ ማመን ባልተስፋፋ ነበር

እግዜርን ጠርቶ የለም ማለት መኖሩን በግማሽ መመሥከር ነው የሚለው ፀሃፊና ጦማሪ የሆነውየኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አማኝ እንደሆነ የሚገልጸው ካሳሁን አለሙ በተጠየቅ ድህረ ገጹ እንዲህ አስነብቦናል፦

> *ሌላውን ውዝግብ አንተወውና **እግዚአብሔር የሚል ስም** መኖሩ ብቻ የመኖሩ ዋና መስካሪ ነው። ምክንያቱም አንደኛ የሌለ ነገር ስም አይኖረውም። ኢ-አማኒያን የሚከራከሩት ግን እግዚአብሔር ብለው በመጥራት ነው፤ ስለዚህ ‹እግዚአብሔር› በማለት ስም ሠጥቶ እንደገና ‹የለም› ብሎ መከራከር እርስ በራሱ የሚጋጭ ክርክር ነው። መቼም ቢሆን ህልውና ወይ ከስም ጋር እኩል ይከሰታል ወይም ነገሩ ከተከሰተ በኋላ ስም ይወጣለታል እንጂ፤ ህልውና የሌለው ነገር ስም የለውም። ሁለተኛው ምክንያት እግዚአብሔር የለም በማለት መከራከራቸው የሚመሰክረው መቃወማቸውን እንጂ ምክንያታዊ መሆናቸውን አይደለም። ማለትም ኢ-አማንያን ‹እግዚአብሔር የለም› ብለው ሲከራከሩ ‹እግዚአብሔር መኖሩ ይታመንበታል፤ እኛ ግን አናምንበትም› ማለታቸው ነው። በሌላ አባባል ‹እግዚእብሔር አለ፤ ግን አላምንበትም› እንደ ማለት ነው።*(ካሳሁን አለሙ፣ ተጠየቅ ድህረ ገጽ)

ካሰሽ ተረጋጋ ስም ያለው ሁሉ ነባራዊ ህልውና አለው እንዴ? ለነገሩ ይህ ፍልስፍና የቆየ መሰረት አላው ስነ ኑባሬ (Ontological Argument) ይባላል። የፍልስፍናው መሰረት እንዲህ ነው፦ “ህልውና የሌለውን ነገር ልናስብ አንችልም።”

Created in Master PDF Editor

ስነ ኑባሬ (Ontological Argument) አቀንቃኝ የክርስቲያን ፈላስፎች እንደሚሉት “አንድን ህላዌ ከሁሉም የሚበልጥ ነው ካልነው ያ ህላዌ በሐሳብም፣ በእውንም አለ ማለት ነው። በሐሳብም ሆነ በእውን የሚኖረው ያ ህላዌ ደግሞ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ሞኞች እግዚአብሔር የለም ይላሉ። . . . የማንኛውም ሀሳብ ምንጩ ህላዌነት (Existence) ነው። በመሆኑም ነፍሳችን እግዚአብሔርን የምታስበው እንዲሁ ከሞት በኋላ ህይወት ስላለ ነው። ነፍሳችን ስለ ዘላለማዊነት የምታስበውም እንዲሁ ከሞት በኋላ ህይወት ስላለ ነው።” (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 24-25)

ይህን ስነ ኑባሬ ፍልስፍና ውድቅ የሚያደርግ ሌላ ፍልስፍና አለ፣ ይህን የትችት ፍልስፍና የተጠነሰሰው ገና እነ ቅዱስ አስለም ስነ ኑባሬ መታሰብ ሲጀምር ነው ከወቅቱ ተችዎችም የጋኒሎ ትችት በዋናነት ይጠቀሳል ብሩህ አለምነህ እንዲህ አስታውሶታል፦

> ሐሳብና ህልውና/ኑባሬ (Idea and Existence) አይነጣጠሉም፤ የምናስበው ሐሳብ ሁሉ ተዛማጅ የሆነ ህልውና አለው፤ ህልውና የሌለውን ነገር ልናስብ አንችልም በሚለው አንሰለም መከራከሪያ የምንሄድ ከሆነ የሁሉንም ነገር ህልውና ማረጋገጥ እንችላለን ማለት ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው ከደሴቶች ሁሉ የሚልቅ እጅግ ውብ የሆነ ደሴት ይኖራል ብሎ ያስባል። በአንሰለም ሀሳብ ከሄድን ይህ ደሴት በአካልም (በእውንም) ይኖራል ማለት ነው። ሆኖም ግን እስከ ዛሬ ድረስ ይሄንን ገነት የመሰለ ደሴት አልተገኘም። ስለዚህ የምናልመው ነገር ሁሉ በአካል ይኖራል ብሎ ማሰብ ጅልነት ነው። (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 25)

ካሳሽ ዝግመተ ለውጥ የሚል ስም አለ እውነት ነው ማለት ነው? የሰው ልጅ ለ100,000 አማልዕክት ስም አውጥቷል እውነት ነው ማለት ነው? ሁሉም በአካላዊ ህልውና አሉ ማለት ነው? ዘኦስ የሚባል ስም ካለ ዘኦስ አለ ማለት ነው? ባዕል (Baal) የሚባል ስም አለ ማለት ባዕል በአካላዊ ህልውና አለ ማለት ነው? እግዚአብሔር የሚለው ስም መኖሩ ብቻውን የመኖሩ ዋና መስካሪ ሊሆን ይችላልን? በፍልስፍና ከሚያስቁኝ አመክንዮዎች ዋናው ይህ ነው “ስም የወጣለት ሁሉ ህልውና ቢኖረው ነው” የሚለው።

ሀይማኖት እንደውሃ ደራሽ አስተሳሰብ አይደለም። ሰዎች በተፈጥሮ ሳይቀር የማምለክ ዝንባሌ እንዳላቸው አጥኚወች ይመሰክራሉ። ቅደመ ሃያቶቻችን ማሰብ ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ ይሆናል ያሉትን ሁሉ ሲያመልኩ ኑረዋል፣ ለልጆቻቸውም አወርሰዋል። ልጆቻቸውም እየጨመሩና እየቀነሱ ዛሬ ላይ ደረሰናል። ገና ብዙ ሀይማኖቶችና እግዚአብሔሮች ይወለዳሉ፣ ያድጋሉ፣ ይሞታሉ።

Created in Master PDF Editor

አማኞች ስለ ሀይማኖቶች መስፋፋት ምክንያቶችን እና አስተዋፅዖዎችን ሲዘረዝሩ እንዲህ ይላሉ፦ 'ሃይማኖት በዓለም ታሪክ ውስጥ ትልቅ ሚና ተጫውቷል።'የአለም አብዛኛው ህዝብ ኃይማኖተኛ ነው፡፡ብዙባህሎች እና ስርዐቶች በሀይማኖት የተቀረፁ ናቸው፡፡ ሃይማኖትተስፋፍቶ የሚገኘው እና ተፅእኖው እንዲህ ከፍተኛ የሆነው በውስጡ እውነት ስላለው ነው፡፡ ደግሞስ ሀይማኖት እውነት ባይሆን ብዙ ሰዎች እንዴት በእግዚአብሔር እመኑ?

ይህ የመከራከርያ ሀሳብ አሳማኝ አይደለም፡፡ ታላቁ ፈላስፋ ኦሾ ምን ነብር ያለው፡፡ "--- religions have not been teachers of truth. These religions have been just enslavers of humanity. They were trying to bring as many people into their herds as they could, because numbers bring power." (The Rebel፣ page, 198) በመጀመሪያ ሃይማኖቶች እና ባህሎች በተናጠል አልመጡም፡፡ በሀይማኖት ውስጥ ባህል፤ በባህል ወስጥ ሀይማኖት አለ እንጅ ባህልን የፈጠረው ሀይማኖት ነው ማለት አይቻልም፡፡ በመሰረቱ ሀይማኖት ቋሚ፣ የማይሻሻል እና የማየቀየር ነው ባህል ግን እንደጊዜው እና እነንደቦታው የሚታደስ ነው፡፡ ለዛ ነው ብዙ ጎጅ ባህሎች ሲቀየሩ የምናየው፡፡ ባህልን እና የአኗኗር ስርዐትን የሰጠን ሀይማኖት ቢሆን ኖሮ ሰዎች ፈጣሪአችን ይቆጣናል መጥፎም ቢሆን የእምነት ባህላችን አንተውም ባሉ ነበር፡፡ የአኗኗር ስርዐትን የሰጠን ሀይማኖት ቢሆን እንኳ ለበለጠ ትችት ይገብዛል እንጅ መከራከርያ አይሆንም፡፡

ሌላው ብዙ ሰዎች የሚያምኑት እውነት ስለሆነ ነው ይባላል፡፡ ብዙ ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን ያለጠፋችው እውነት ስለሆነች እንጅ ለማጥፋት ከሀዲያን ብዙ ጥረው ነበር ይላሉ፡፡ ይህን መከራከርያ ለሚያቀርቡ ሰባኪያን እውነት ማለት የጀምላ አስተሳሰብ ማለት አይደለም በሉልኝ፡፡ እውነት እውነት ነው ማንም ባይቀበለውም፤ሀሰት ደግሞ በተከተይ ብዛት አውነት አይሆንም በእድሜ ብዛትም፡፡

> ለዲሞክሪተስ እውነት አተሞች ብቻ ናቸው፤ ለፊዚክስ ባለሙያዎች እውነት ገና ያልተደረሰበት የሒሳብ ሕግ ነው፤ ለማርክሲስቶች እውነት ተጨባጩ ዓለም ነው፤ ለሐሳባዊ ፈላስፎች እውነት ነባራዊ የሃሳብ ሕግጋት ናቸው፤ ለፖለቲከኞች እውነት የተከታዮቻቸው ብዛት ነው፤ ለሃይማኖተኞች ደግሞ እውነት እምነት ነው፡፡ (ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣ 114)

ይህ ትንታኔ እውነትን አንፃራዊ አስመስሎታል፡፡ እውነት በእየመስኩ ሊኖር እንደሚችል አምናለሁ፡፡ በካፒትሊዝም እና በኮሚኒዝም ስርዓት ውስጥ እውነት ሊኖር ይችላል፡፡ በአማኞች በኢ-ኢማኞች ፍልስፍና ውስጥ እውነት ሊኖር ይችላል፡፡ ችግሩ እውነቱ ከሐሰቱ ጋር በመቀላቀሉ እውነቱን ማወቅ የድንጋይ

Created in Master PDF Editor

ተራራ ውስጥ 100 ግራም ወርቅ እንደማንጠር ነው። እውነት የትም ሊኖር ይችላል ቢያንስም ቢበዛም። የሚጨንቀው ነገር ይላል ብሩህ፦

> እያስጨነቀን ያለው ተፈጥሮ በሰጠችን አቅምና በምኞታችን መካከል ያለው አለመመጣጠን ነው። ሳይንሱ በትንሹ ከፍ ቢያደርገውም ተፈጥሯዊ አቅማችን በስሜት ህዋሶቻችን አቅም የተወሰነ ነው፣ ምኞችን ግን ከቦታ - ጊዜ አውታር ውጭ ድረስ የተዘረጋ ነው። አቅማችን ኖሮ ኖሮ መሞት ነው፤ ምኞታችን ግን ዘለዓለማዊ ሆኖ መኖር ነው። አቅማችን ትናንትን ማስታወስ፣ አሁንን ማወቅ ነው፤ ምኞታችን ግን ከትናንት እስከ ነገ ድረስ በንቃት መመላለስ፣ የወደፊቱንም አስቀድሞ ማወቅ ነው፤ አቅማችን አካላችን የቆመበት አካባቢ ብቻ ያሉትን ክስተቶች መከታተል ነው፤ ፍላጎታችን ግን በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ በንቃት መገኘት ነው፤ አቅማችን ቤተክርስቲያን ሄዶ መፀለይ ነው፤ ምኞታችን ግን ከፈጠረን ኃይል ጋር በአካል መገናኘት ነው። (ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣ 114)

ምኞት እውነት አይደለም። ምን አልባት ሞኝነት ነው ይህን ቅዱስ ጳውሎስ ሳይቀር መስክሯል።

> በአቅማችንና በምኞታችን መካከል ያለውን ክፍተት እግዚአብሔር ሳያስተውለው አልቀረም። እግዚአብሔር በሰው ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ክፍተት መኖሩን ካወቀ ደግሞ ክፍተቱን የሚሞላበት መላ መፍጠር አለበት፤ ልክ በአዳም ክፍተት ውስጥ ሄዋን እንደተሞላች ሁሉ በአቅማችንና በምኞታችን መካከል ያለውን ክፍተትም የሚሞላበት ነገር መኖር አለበት። እግዚአብሔር ይሄን ክፍተት ለመሙላት የመረጠው ነገር አስገራሚ ነው ሞኝነትን መረጠ (እምነትን)። እምነት ሞኝነት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ራሱ የእምነትን ሞኝነት ሲገልጽ እንዲህ ይላል "በእግዚአብሔር ምክንያት፣ ዓለም እግዚአብሔርን በጥበቧ ስላላወቀች… እግዚአብሔርም ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የዓለምን ሞኝነት መረጠ" 1ቆረ፣21 እና 27። በሃይማኖታዊ አስተሳሰብ የሰው አቅምና ምኞቱ የሚስተካከሉት በእምነት ውስጥ ሲኖር ብቻ ነው። (ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣ 114-115)

በእርግጥ በአለም ያለው ሃይማኖት አንድ ብቻ ቢሆን ኖሮ ተክክለኝነቱን ለመወሰን አስቸጋሪ ይሆን ነበር። ነገር ግን በዓለም የተለያዩ ሃይማኖቶች አሉ፤ አንዳቸውምከአንዳቸው አይስማሙም። የሚገርመው ሁሉም የእኔው ሀይማኖት ብቻ ነው እውነት ይላሉ።በምንም መስፈርት እርስ በርሱ የሚጋጩ ሃይማኖቶች ሁሉም ትክክል ናቸው ማለት አይቻልም ይልቁንስ ሁሉም ስህተቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ሁሉም የሚያስተላልፉት የሰሙትን ነው እንጂ አንድስ እንኳ ፈጣሪን ያየው የለም። ተክለ ጊዮርጊስ ማሞ የታላቁ ፍልስፍ ፍሬድሪክ ኒቼን እንድህ ያትተዋል፦ "የምታምነው ለመኖሩ ማስረጃ ማቅረብ ካልቻልክ እምነትህ ውሸት ነው፤ አባቴ ለእኔ ያስተላለፈው

Created in Master PDF Editor

እምነት አያቴ የነገረውን ነው፤ አያቴም የቅድመ አያቴን ይዞ ለአባቴ አስተላለፈው፤ እንግዲህ እኔ የምንኖርበት እምነት አስቀድሞ ሌሎች የኖሩበትን እንጅ እኔ በማስረጃ አረጋግጬ ያገኘሁት አይደለም ማለት ነው:: ስለዚህ ለእምነትህ ማስረጃ የለህምና ውሸት ነው::”

ፈላስፋው ወ/ህይወትም እንዲህ ይላል፦ *“እምነት ግን ሳይመረመርና ከአዋቂነት ተፈጥሮ ባህርይ ጋር ሳይስመማ ማመን የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም:: ስለዚህም ሳንመረምርና ሃይማኖታቸውም እውነት መሆኑን ሳይታወቅ በአባቶቻችን ሃይማኖት እናምን ዘንድ አይገባንም:: እግዚአብሔር ዕውቀትን ለአባቶቻችን ብቻ አልሰጠም፤ ለእኛም ከእነሱ የሚበልጥ ዕውቀት ሰጥቶናል እንጂ:: አባቶቻችንን ሃይማኖት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው እኛ ካልመረመርነውና ካላወቅነው እውነት መሆኑን እንዴት ልናውቅ እንችላለን?”* (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 290)

በታሪክ ለዘመናት ገናና የነበሩ እምነቶች እና አስተሳሰቦች ሀሰትነታቸው በማስረጃው ተረጋግጦ ወደ መዝገብ ቤት ተመርተዋል:: እስከ ቅርብ ጊዜ ጂኦሴንትሪዝም (Geocentrism) ወይም ምድር የሁለንታ ማዕከል ናት የሚለውን ሀሳብ እንደ እውነት ይታውቅ ነበር:: ምስጋና ለጋሊሊዮ፣ ኮፐርኒከስ እና ኬፕለር ይሁን እንጅ ዛሬ መሬት በፀሀይ ዙርያ ከሚዞሩ ፕላኔቶች አንዷ ናት የሚለው ነባራዊ ሀቅ ሁኗል:: ቢሆንም ዛሬም ድረስ መሬት ስትሽከረከር እና ስትዞር አላየነም ስለዚህ መሬት የሁሉ ማዕከል ናት የሚሉ አልጠፉም:: ጥያቄው መሬተስ የሁለንታ ማዕከል መሆኗን እንዴት አወቃችሁ ነው?

ቁጥሩ ይብዛም ይነስምእምነትበእውነት ላይ ምንም ተጽእኖ የለውም::የሮሙ ጳጳስ አሊያም የኢራኑ የሀይመኖት መሪ ቢያምኑም ባያምኑም ምድር ሁልጊዜ በፀሐይ ዙርያ ትሽከረከራለች:: ጥያቄው አምላክ ባይኖር ኖሮ በአምላክ ማመን ለምን ተስፋፋ ከሆነ “just as genes are transmitted from body to body, down the generations, memes are transmitted from mind to mind.” ነው መልሱ ፕ/ር ዳውኪንስ እንዳለው::

9. እግዚአብሔር በመኖሩ ለጸሎት መልስ ይሰጣል

ጸሎት የብዙዎቹ ሃይማኖቶች አንዱ ዋነኛ ስርዐት ነው::ፀሎትምኞትን፣ተስፋን፣ ምስጋናን እና ፍርሀትን ለኃያሉ አምላክ የመናገር ማራኪ ጥበብ ነው:: ጸሎት የሰመረ እንደሆነ በራስ የመተማመን መንፈስ ከፍ ይላል:: ሆኖም ግን ጸለቱ በትክክል ካልሰራስነ ልቦነዊ ቀውስ ያስከትላል:: እሰቡት የሚወዳት ሚስቱ በሰላም እንድትገላገል 9 ወር ሲፀልይ የከረመ ባል ፍሬውን ሳትሰጠው በወሊድ ምክንያት ብትሞት ምን ይሰመው? ያሳዝናል ቢሆንም ደስ የሚለው አማኞች ከዚህ ቀውስ ለመሸሽ

Created in Master PDF Editor

የእግዚአብሄር ፍቃድ ባይሆን ነው እንጅ በማለት ይፅናናሉ፡፡እኛ የማንፀልየው ግን የአማኞች አማልዕክት ጀሮ አላቸው አይሰሙም የኛው ግን ጆሮ የለውም፣ ይሰማን ዘንድም አንጸልይም፡፡ የሆነ ሁኖ አማኞች ዛሬም

ቶሎ በል ቶሎ በል፣

አንድዬ ቶሎ በል፣

እንደ ዘመኑ ሰው ነገ ዛሬ አትበል፡፡ ሲሉ ይደመጣል፡፡

እስኪ የጸሎትን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ግልፅ እና ቀጥተኛ የሆነ አንድ ምርመር እንስራ፡፡ በአንድ ሆሲፒታል ከባድ ቀዶጥገና የሚደረግላቸው 400 ህሙማንን ለ200ው እንዲፀለይላቸው ለቀሪዎቹ 200ው ደግሞ እንዳይፀለይላቸው ብናደርግ የትኞቹ ስኬታማ ይሆናሉ? ለእኔ የስኬት እድሉ እኩል ነው በተለያዩ ምርምሮች ተረጋገጠ ሀቅ ነው፡፡ በመሰረቱ በፀሎት ለመዳን ሆስፒታል መሄድ የሚያስፈልግ አይመስለኝም ምክንያቱም ያዳነው ህክምናው ወይስ ፀሎቱ የሚለውን መወሰን ስለማይቻል፡፡

ይህ መከራከርያ ያላዋጣቸው ሰባኪያን በግሌ የፀለይኩት ሁሉ ተመልሶልኛል፤ ከበሽታየ ተፈውሻለሁ፤ ስራ አግንቻለሁ፤ ትዳር መስርቻለሁ፤ ማትሪክ ሚኒስተረን አልፌአለሁ፤ ነግጀ አትርፌአለሁ እና ሎተሪ ደርሶኛል እያሉየስኬት መዕት መዘርዘራቸው ባይበቃ ህዝቡን ኑ ልፀልይላችሁ እያሉ ስራ በማስፈታት ላይ ናቸው፡፡ በእየ አዳራሹ ጥንቆላ ስሙን ቀይሮ እየተሰበከ ይገኛል፡፡ በፈጣሪ ልለምናችሁ በቴሌቪዥን ወይም በዩቲብ አንድ የድህነት ወይም የመፈወስ ቪዲዮ ተመልከቱ፡፡ ትዕግስት ከለላችሁ በመጀመርያ ትስቃላችሁ ቀጥሉ ትበሳጫላችሁ ከዚያም ትዘጉታላችሁ፡፡እኔ መሳለቅ ባይሆንም ቤቴ ቁጭ ብየ ከደበረኝ የፈውስ ቻናሎችን እየከፈትኩ እዝናናለሁ፡፡ በእርግጥ ብዙ ትምህርትም እግረ ምንገዴን እማራለሁ፡፡

ቢሰሙትም ባይሰሙትም ፀሀፊው <ከማመን መጠራጠር ይሻላል> የኢትዮጲያን የሀይማኖት አባቶች እንዲህ ሲል ይገስጻቸዋል፦ *“የኢትዮጲያ ሸሆች፣ ቄሶች እና ፓስተሮች ሆይ ለብዙ ክፍለ ዘመን ስትፀልዩ ኑራችሁ ለሀገራችሁ ምን አደረጋችሁ? የፀሎታችሁ ዉጤት የታለ? ህዝቡ በየ ቀኑ ይሰግዳል፡፡ ዛሬ ገብርኤል ነው፣ ከነገወድያ ማሪያም--- እያለ ስራ አይሰራም፡፡ በተጣበበ ጊዜው ሰርቶ ከሚያገኘዉ ላይ ለመቅደሳችሁ ማሰሪያ (በተለይም ለደሞዛችሁ) መባ፣ አስራት በኩራት፣ ዘካ ምንትስ እያላችሁ ትቀበላላችሁ፡፡ ቆይ ግን የናንተ ስራ ምንድነዉ? ህዝቡን በጥሩ ስነምግባር ማነፅ አልቻላችሁም፡፡ በጣም ብዙ ሌባ፣ ዘረኛ፣ አስመሳይ፣ ዘራፊና ስራ ፈት ማህበረሰብ ነዉ የተፈጠረዉ፡፡ --- አሁንም ችግር ላይ ነን፡፡ አሁንም የሚራቡ ሚሊየኖች አሉ፡፡ አሁንም በዘረኛ ፓለቲከኞችና ተከታዮቻቸዉ የሚሞቱ የሚሰደዱ*

Created in Master PDF Editor

አሉ:: አሁንም በሽታወች ህዝቡን እየፈጁ ነዉ:: አምላካችሁ ፀሎት መስማት አቆመ እንዴ? ወይስ እናንተም እንደ ህዝቡ የለት እንጀራየን አታሳጣኝ እያላችሁ ነዉ ምትፀልዩት?”

ይህ ወቀሳ በተለየ መልኩ ራሷን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብላ ለምትጠራው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ይመለከታታል:: የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንበቅዳሴ ሰአት የማትፀልይለት የለም ህይወት ስላለው እና ስለለው ወንዞች ሳየቀር በዛ ወሰኝ ሰአት ይፀለይላቸዋል:: ቢሆንም ሰዎች በየቀኑ በግፍ ይሞታሉ፤ ቤተሰብበፍቺ ይበተናል፤ በጦረነት እና በመኪና አደጋ ሰዎች አካል ጉዳተኞች ይሆናሉ፤ ወጣቶችየሚሰሩትም ሲብስም የሚበሉት ያጣሉ ኧረ ስንቱ! ለዚህ እኮ ነው ፀሎት ለራሳችን ከማውራት ውጭ ጥቅሙ ምንድን ነው የምለው:: እባካችሁ አስረዱኝ:: ይህን ስል ምንአልባት እግዚአብሄር በሦስት መንገድ ለፀሎት መልስ ይሰጣል ልትሉኝ ትችላላችሁ:: ሶስቱም እሽ፣ አልፈቅድም እና ታገስ ናቸው:: ለምሳሌ ብዙ ሰዎች የተሳፈሩት ጀልባ ቢገለበጥ እና ሁሉም ወደ እግዚአብሄርቢፀልዩ የተወሰኑት ፈጣን የነፍስ አድን ሰራተኞች ደርሰው ከሞት ቢያተርፏቸው፤ የተወሰኑትን ደግሞ ለመሞት ሲያጣጥሩ ቢደርሱላቸው እና ቀሪዎቹ ቢሞቱ የእግዚአብሄር ፍርድ ልክ ነው ትላላችሁ? እኔ እግዚአብሄር ፍትሀዊ አይደለም ባይ ነኝ:: ይህን ጉዳይ እማናምነው ብቻም ሳይሆን የሚያምኑት እንኳ በንግግር፣ በስነ-ጹሁፍ እና በሙዚቃ ይገልጹታል:: ለምሳሌ የእህቶቿ ባርነት ያሳዘናትሃሊማ አብዱራሂም የዘመናትን ብሶት ከገበታ በታች በሚለው ዜማዋ እንዲህ ትላለች፦

“አቤት ጌታዬ ወዴት ጌታዬ

የእርሳቸው ሰማይ ለኔም ሰማይ...አቤት ጌታዬ

ከሰማዩ ስር ጥቁር ደመና

ከደመናው ስር ጥቁር አሞራ...አይ የሱ ሥራ!

ከአሞራው ሥራ የጌቶች ጣራ

ከጣራው በታች ትልቅ ወጋግራ...አይ የሰው ሥራ!

ከወጋግራው ስር ዙፋን ላይ ጌቶች

ቀፈታቸው ስር የጌታዬ እግሮች

ከዚያ ዝቅ ብሎ የእንጨት ገበታ

ከሱ ስር እኔ እግር አሽታ::

Created in Master PDF Editor

ከገበታ በታች ነኝ ከገበታ

እንጨት ሲበልጠኝ የት ሄድዋል ጌታ?”

ይህ ነው እንግዲህ የእግዚአብሄር ፍትህ አንዱን ጌታ ሌላውን ባርያ፣ አንዱን አዳኝ ሌላውን ታዳኝ፣ አንዱን ገዥ ሌላውን ተገዥ፣ አንዱን አሸናፊ ሌላውን ተሸናፊ፣ አንዱን ወላድ ሌላውን መሃን፣ አንዱን አትራፊ ሌላውን ከሳሪ፣ አንዷን ባለሃብት ሌላዋን ሴተኛ አዳሪ…፡፡ እኔ እምለው ባርያ፣ ታዳኝ፣ ተገዥ፣ ተሸናፊ፣ ምሃን፣ ሴተኛ አዳሪእናከሳሪ እንዲሆን የሚጸልይ ይኖር ይሆን? “እግዚአብሔር ግን ገፀ ባህሪያትን ሕይወት ሰጥቶ በስጋ ይፈጥራል፡፡ <እናንተ የእግዚአብሔር ሸክላዎች ናችሁ> ብሎናል ቅዱስ ጳውሎስ፡፡ ሸክላ፣ ሸክለ ሠሪው ላይ ምን ቅሬታ አለው? ሸክላ ሠሪው እንደወደደ አንዱን የክብር ዕቃ አድርጎ ሳሎን ያስቀምጠዋል፣ ሌላውን ደግሞ ምድጃ አድርጎ መሬት ላይ ያስቀምጠዋል፡፡ ኢየሱስን አሳልፎ የሰጠው የይሁዳ ድርጊትም አስቀድሞ የታወቀ እና የተወሰነ ነው፡፡ ይሁዳ የተጻፈለተን ከመተወን ውጭ ነጻ ፍላጎት የለውም፡፡ በመሆኑም መላው ክርስቲያን ይሁዳ ላይ ጣቱን መቀሰሩ ተገቢ አይደለም፡፡ የዓለም ታሪክ ሁሉ የእግዚአብሔር እንጂ የሰዎች ታሪክ አይደለም አንዳች ማድረግ አትችሉም ተብለናልና፡፡ በዓለም ላይ ለሚያጋጥሙ ዘግናኝ ተፈጥሯዊና ማኀበራዊ አደጋዎች ሁሉ ኃላፊነት የሚወሰደው እግዚአብሔር ነው፡፡ ዓለማችን ያስተናገደቻቸው አሰቃቂ የጦርነት ታሪኮች ሁሉ የሰው ታሪክ ሳይሆን የእግዚአብሔር ታሪክ ነው ማለት ነው፡፡” (ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣ 53-59) ይህ ልብ ወለዳዊ ትወና የሰወችን ሚና እና የመኖር ትርጉም ባዶ ያደርገዋል፡፡ ሰው ምንም እንደሆነ ባውቅም ምንምነታችንን ለመሸፈን የፈጠርነው አምላክ ደግሞ ምንምነታችንን እጅግ አላቀው፡፡ አሳማኙ የህይወት ድራማ ግን እንዲህ እተርከዋለሁ፦

ህይወት ድራማ ነው፣ ቲያትር ነው፡፡ መጋረጃው ይከፈታል ተዋናዮች ይተውናሉ፡፡ ተመልካቾች ስቀው ወይም አዝነው ሳይጨርሱ መጋረጃው ይዘጋል፡፡ ሌሎች ተዋናዮች ይመጣሉ እንሱም እንደመጀመሪያዎቹ ታይተው ይጠፋሉ፡፡ ወይም ጊዜያቸው ገና ከሆነ ልብስ ቀይረው ይመጣሉ፡፡ ህይወትም እዲህ ነው እጅግ እጅግ ብዙዎቹ እንደመጡ ይሄዳሉ፡፡ እድለኞች የሆኑ ብቻ ለታዳጊነት፣ ለወጣትነት፣ ለጉልምስና ብሎም ለእርጅና ይበቃሉ፡፡ የፍጥረት መቃብር መቆፈር የሚጀምረው በልደታቸው ቅፅበት ነው፡፡ የድራማው ጊዜ አጭር ነው በጣም አጭር፡፡ እና የህይወት ድራማ ለማስረዘም ማንን ይግባይ እንበል? ወደ ማን እናጋጥጣለን? ወደ ማን አቤት እንላለን? ወደ ማንም! ታዲያ ምን ተሻለን? የሚሻለን እማ በዚህ አጭር ጊዜ የትወና ብቃታችንን አሳይተን ደስታና ሀዘኑን፣ ዘፈንና ለቅሶን፣ ውበትንና ጥፋትን፣ አጣጥሞ ማለፍ ነው፡፡ በህይወት ድራማ ውስጥ የተፈጥሮን ህግ መተላለፍና የድራማውን ታሪክ፣ የገፀ ባህርያትን ምንነት፣ የትወናውን ግጭት፣ መቼትና ጭብጥ አለመረዳት እንደስንፍና ይቆጠራል፡፡ ህይወት ተፈጥሮ የደረሰችው ፍጡራን በጥበብ

Created in Master PDF Editor

የሚተውኑበት አጭር መሳጭ ድርስት ነው፡፡ ለድርሰት ህይወት የሚዘራበት ተዋናኝ እንደሆነ ሁሉ ለህይወትም ትርጉም የምንዘራበት እራሳችን ሰዎች ነን፡፡ አኗኗራችን በጥረታችንና በአጋጣሚዎች የተሞላ እንጅ ጸሎት በሚሉት ቃለ ምልልስ አይደለም፡፡

ኤቲስቶች ያለ ጸሎት ህይወታቸውን የሚመሩት በእግዚአብሔር ትዕግስት ብዛት ወይም በአማኞች ጸሎትና ምልጃ አይደለም ፀሎት ምንም ልዩነት የማይፈጥር በመሆኑ እንጅ፡፡ ልዩነት የሚፈጥር ቢሆን ኑሮ ፍፁም እንከን የለሽና ፈፅሞ ሊሳሳት ለማይችለው መሃሪ አምላክ እንደመጸለይ ቀላል ነገር አልነበረም፡፡ ነገር ግን የሚገርመው ይላል <ከማመን መጠራጠር ይሻላል>“የሚገርመዉ ደግሞ ቁራን እና መፅሐፍ ቅዱስ ላይ ያለዉ አምላክ ፍፁም እንከን የለሽና ፈፅሞ ሊሳሳት የማይችል ተደርጎ መገለፁ ነዉ፡፡ ቁራን እና መፅሐፍ ቅዱስ ላይ ያለዉ አምላክ እንደሚባለዉ እንከን የለሽ ከሆነ ለምን እንከን የለሽ የሆነች አለምን አልፈጠረልንም? የመሬት መንቀጥቀጥ፣ የፅሳተ ገሞራ ፍንዳታ፣ ሱናሚ፣ አዉሎ ንፍስ፣ የመሬት መንሸራተት፣ ድርቅ፣ የተለያዩ ወረርሽኞች፣ በጎርፍ መጥለቅለቅ… የመሳሰሉት የተፈጥሮ አደጋወች መንስኤያቸዉ ምንድነዉ? ለምን እነኝህን የመሳሰሉ አደጋዎች የሌሉበት ፍፁም እንከን አልባ አለምን አልፈጠረልንም? በነኝሁ ቅዱሳን መፅሐፎች አንኳኩ ይከፈትላችሁል፣ ጠይቁ ይሰጣችሁዋል… የትኛዉንም ነገር ብትለምኑኝ አደርግላችሁዋለሁ የሚለዉ አምላክ ለምን በቃሉ አይገኝም፡፡”

የሚያሳዝነው አንዳንድ ፆለቶች ተቃራኒ በመሆናቸው ለእግዚአብሄርም የሚያስቸግሩ ይመስለኛል፡፡ ለምሳሌ ጦርነትን ለማሸነፍ መፀለይ፤ የእግር ኳስ ጨዋታ ለማሸነፍ መፀለይ፤ ማራቶን ለማሸነፍ መፀለይ እና ጠ/ሚኒስተር ለመሆን መፀለይ፡፡ እኔ ምለው የቅዱስ ጊዮርጊስ ስፖርት ክለብ ተጫዋቾች እና የቡና ስፖርት ክለብ ተጫዋቾች ጭዋታውን ለማሸነፍ ፀልየው ቢጀምሩ አንዱ ካሸነፍ የአሸናፊው ፀሎት ሰምሯል አቻ ከወጡ እኩል ተደምጠዋል ማለት ይሆን?እባካችሁ ለእግዚአብሄር እዘኑለት በረባ ባረባው ዳይለማ ውስጥ አታስገቡት፡፡ አንድ ሰው ለሚፈልግ ክፍት የስራ መደብ ለማለፍ አንዷ ወርቅ ጥላ ተሳላለች፤ ሌላዋ የመጀመርያ ወር ደሞዝዋን ተሳላለች፤ አንዱ አስር ፐርሰንት (10%) ይሳላል እና ሌላው እመቤቴ አደራሽን ብሎ ይመለሳል፡፡ የትኛው ይሳካ ይሆን?ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም ፅሎት በተለይም ለኢትዮጵያዊያን አማኞች ሀላፊነትን መሸሽት ነው ይላሉ ስሟቸው፦

“በእግዚአብሔር ሚያምኑ ህዝቦች ሁሉ የሱን (እግዚአብሔርን) የበላይነትና ኃያልነት ሳይጠራጠሩ ይቀበላሉ፡፡ ኢትዮጵያውያን እምነት ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንዲያደርግልን እንፈልጋለን፡፡ የሚቻል ቢሆንማ እሱው አርሶ ቢያበላን ደስ ይለን ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ለክፉውም ሆነ ለደጉ፣ ለሐዘኑም ሆነ ለደስታው ኃላፊነቱ በሙሉ የእግዚአብሔር ነው እንጂ

Created in Master PDF Editor

> የራሱ እንዳልሆነ አድርጎ ነው የሚያስበው፡፡ ለማናቸውም ነገር ህዝቡ ችግሩን ለመድኃኔዓለም፣ ለኢየሱስ፣ ለአላህ፣ ለማርያም፣ለገብርኤል፣ለአቦ .... አስተላልፎ እነሱ እንደ ችሮታቸው ያድርጉት ብሎ ይጠብቃል፡፡ ከዚያ በኋላ ለሚሆነው ነገር ሁሉ ኃላፊነቱ የኢትዮጵያውያን አይደለም፡፡ በመሆኑም ፀሎት ማለት ለኢትዮጵያውያን ኃላፊነትን ማውረድ ማለት ነው፡፡ (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣223)

ፀሎታችን እኮ ለመልካም ነገር ብቻ ቢሆን ባልከፋ፡፡ ነገር ግን አያሳድግህ፣ ይድፋህ፣ ይግደልህ፣ አይመልስህ፣ አይማርህ ወዘተ. መሆኑ ነው፡፡ አስቡት እርግማናችን እኮ ፅሎት ነው፡፡ እንዲህም ተብሎ ይጸለያል፦ <<ድንግል ሆይ የሚጻረረኝን የሚቃወመኝን ሰው አፉን ለጉሚው፣ አንደበቱን ዲዳ አድርጊ፣ ጉሮሮውን ዝጊ፣ ጆሮውን አደንቁሪ፣ ኃይሉንም አዳክሚ፣ አንገቱን ቆርጠሽ ጣይ፣ በላየ የሚያንዣብበውን የጠላት ዲያብሎስን ክንፍ ስበሪ፣ አይኑን አሳውሪው፣ እጁን ሽባ አድርጊው እግሩንም አሳጥሪው ሊያጠፋኝ የሚያሴረውን ጠላት አጣድፈሽ ከጥፋት ገደል ጣይው፣ በዚህ አለም የሚጠላኝን የሚቃወመኝን ሰው ከምድር ላይ ነቅለሽ ጣይልኝ ----፡፡ ---ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ በጠላቶች አንገት የብረት ዛንጅር አግቢባቸው፣ የመለከታቸውን ድምጽ አክብጅው፣ በእግር ብረት እሰሪያቸው፣ በእግራቸው ወጥመድ በከንፈራቸውም ልጓም በአፍንጫቸው ጉንፋን ላኪባቸው፣ ሊሄዱበትም ወዳልፈቀዱበት መንገድ መልሻቸው፣ በልቦናቸውም ፍርሃትን መንቀጥቀጥን አሳድሪባቸው፣ መሸበርንና መንቀጥቀጥን ጨምሪባቸው እንደሴቶች ይሁኑ፡፡ ከጽኑ ነፋስ ኃይል የተነሳ ዛፍ ሲንቀሳቀስ ቅጠሉ እንረዲረግፍ እንዲበተን እንዲሁ ይሁኑ፥ በርሃብ፥ በቸነፈር፥ እህልን በማጣት ቅሰፊያቸው፣ በሜዳ ሰይፍ ልጆቻቸውን ያጥፋቸው፣ በቤታቸውም ውስጥ ፍርሃት ያስጨንቃቸው፣ እሳት፥ በረዶ፥ ረሀብ፥ ቸነፈር ይፍጃቸው፣ ይህ ሁሉ የእግዚአብሄር የምጽአቱ ጽዋ በጠላቶቼ ላይ ይውረድ እድል ፈንታቸው ጽዋ ትርታቸው ይሁን------->> (ምንጭ፦ ሰኔ ጎለጎታ እና አርጋኖን የፀሎት መጽሃፍት)እግዚያብሄር አምላክና ሌሎች ቅዱሳን ፀሎትን የሚሰሙ ቢሆን ኖሮ ማን ይኖር ነበር፡፡“ደስ የሚለዉ ነገር ይሄ አላህ ወይም እግዚያብሄር የሚባለዉ አምላካችሁ የማንንም ፀሎት አይሰማም፡፡ የሚሰማ ቢሆንማ ኖሮ አልቆልን ነበር፡፡ ጎበዝ የብዙ ሰዉ ፀሎት እኮ እንትናን ድፋልኝ ነዉ፡፡ እኔኳ ስለ እግዚያብሄር በተናገርኩ ቁጥር ስንቱ ‘ያንተን ነገርማ ጌታ ያሳየኝ’ ብሎ ፀለየብኝ፡፡ ፀሎታቸዉኮ ሰዉን ብቻ ሳይሆን ሀገርንም እስከማጥፋት ነዉ፡፡ አላህ እስራኤልን ያጥፋት ብሎ ዱአ የሚያደርግ ሙስሊም አለ፡፡ እንደሚመስለኝ ከሆነ እነኝህ አምላክ ተብየወች ፀሎት የሚሰሙ ቢሆን ኖሮ አለማችን አሁን ባለችበት ሁኔታ አትገኝም ነበር፡፡ ደስ የሚለዉ ስልለለሉ አይሰሙም፡፡”<ከማመን መጠራጠር ይሻላል>

Created in Master PDF Editor

አስደንጋጩ ፈላስፋና ጸሃፊ በዕውቀቱ ስዩም አንድ አስደንጋጭ እግር አልባው ባለክንፍ የሚል ጽሁፍ መጽሄት ላይ አውጥቶ ነበር። የፁሁፉ አስደንጋጭነት እስከመደብደብ አድርሶታል። መደብደቡን የሰሙ አድናቂዎቹ የኛ አገር ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግርና እኛ ችግሩን የምንመለከትበት መነጽር እግር አልባ ባለክንፍ ሳይሆን <u>እግርም ክንፍም አልባ</u> ያስብለናል ብለዋል።"አመክንዮአዊነት የጎደለው ክርክር ትተን እውነትን መጋፈጥ መጀመር አለብን። የማይጨበጥ ታሪክ እያወራን በችግር ቀንበር ውስጥ እየማቀቅንና በእርጥባን መኖር ይበቃናል። በእውቀቱ የተናገረውን በሃሳብ መሞገት ሲያቅተን ለጡጫ እንጋበዛለን። በቃን ከእንቅልፍ እንንቃ። ተረት ተረት እናቁም ሲሉ አሳስበዋል።"እኔ በዕውቀቱ ስዩም በጻፈው ጽሁፍ የደረሰበት የአካል ጉዳት ለእውነት ማበብ እነሶቅራጠስ እና ሌሎችም ከከፈሉት መስዕዋትነት ጋር አያይዘዋለሁ።(በዕውቀቱ ስዩም ከአካላዊ ጉዳቱ ካገገመ ዘመናት ተቆጥረዋል፣ ታሪኩ ግን አይረሳም) በዚህ ወቅት ኢትዮጵያ ማለት የሶቅራጦሷ አቴንስ ማለት ናት።

ዋናው ነገር የበውቀቱ ጽሁፍ እግዚአብሔር በመኖሩ ለጸሎት መልስ ይሰጣል የሚለውን መከራከርያ የሃገራችንን ታሪክ እና ነባራዊ ሁኔታዎችን በማመዛዘን ውድቅ ያደርገዋል ይልቁንም ምንማድረግ እንዳለብን መፍትሔውን ይጠቁመናል።

> *<<በአገራችን የተከሰቱ መከራዎች <u>ከተፈጥሮ</u> የፈለቁ በመሆናቸው መድህናቸውም <u>ተፈጥሮአዊ</u> ነው። ረሃብን እንውሰድ፦ ረሃብ ለሃገራችን አምስተኛ ወቅት ማለት ነው። ክረምት፣ ጥቢ፣ በጋ፣ በልግ አራቱ ወቅቶች ሲሆኑ <u>ጠኔ አምስተኛ ወቅት</u> ሆኖ ይከተላል። ዑደቱ ሳያቋርጥ ይመላለሳል። መከራን <u>የእግዚአብሄር ፈቃድ</u> ነው ብሎ የሚያምን ሕዝብ መከራን አስቀድሞ መከላከል የእግዜርን ፈቃድ <u>መጻረር</u> ይመስለዋል።እና ባንዱ ዘመን ድርቅ ይከሰታል። ድርቁ አስቀድሞ የቀንድ ከብቱን ይፈጃል። ሰዎች ረሃቡ ሲጠናባቸው ፈረስና አህያ መብላት ይጀምራሉ። (ከሙሴ ትዕዛዝ የጨኻራ ትዕዛዝ ያይላል) ባስ ሲልም ልጃቸውን የሚበሉ ወላጆች ይኖራሉ። ባጤ ሚኒሊክ ጊዜ አንዲት እናት ልጇን ከበላች በኋላ የሚከተለውን እንጉርጉሮ አይሉት ተረብ አወረደች።*
>
> *<u>"ዳግመኛ ለመውጣት በሌላ መንገድ</u>*
>
> *<u>ተመልሶ ገባ ልጅ በናቱ ሆድ"</u>*
>
> *እንዲህ ዓይነቱ መረን የለቀቀ መከራና እልቂት ሲደጋገም መሪዎች በመጀመሪያ የሚወስዱት እርምጃ <u>የክተት ፀሎት ማወጅ</u> ነው። ተፈጥሮ ግን ለፀሎት <u>ደንታ የላትም</u>። ታግለህ ጣል አለበለዚያ የራስህ ጉዳይ በሚለው የተፈጥሮ ሕግ ውስጥ 'ኪሪያላይሶ' ቦታ የለውም። ሰዎች በመቅደሳቸው በረንዳ ላይ ይሄኔ እኒያ የሕዝብ*

Created in Master PDF Editor

አለቆች የእግዜሩን መንገድ ለጊዜው ቸል ብለው ወደ ተፈጥሮ መንገድ ይዞራሉ:: በተፈጥሮ መንገድ ውስጥ አንበሳ ሲርበው ወደ አደን እንጅ ወደ ቤተ መቅደስ አይሄድም:: ሮጥ ሮጥ ብሎ ሚዳቆን ሰብሮ ይመለሳል:: የኛ ነገስታትም የአንበሳውን አርአያ ተከትለው በእምነት የማይመስላቸውን ሀብታም ጎሳ ይጠሩና ከብቱን ነድተው ሲሳዩን ዘርፈው ይመለሳሉ:: እነሱ ሞአ አንበሳ ሲሆኑ በርዕዮተ ዓለም የማይመስላቸውን ሕዝብ ሚዳቋ እንዲሆን ይፈርዱበታል:: በዚህ ዓይነት ክፉ ቀንን በዝርፊያ ሲሳይ ይሻገሩታል::>>

የበውቀቱ ሀተታ እና ምክር ለመዋጥ የሚከብድ መራራ እውነት ነው:: አልሰማነውም እንጅ የበውቀቱን ምክር ከክፉ ቀን በፊት ፈላስፋው ዘረዐ ያዕቆብ ነግሮን ነበር። ምን ነበር ያለው “ዋሾዎች ሁሉ የተፈጥሮን ሥርዐት ሊያፈርሱ ይሞክራሉ ግን ደካማ ውሸታቸውን ያሳያሉ እንጂ አይችሉም::” በውቀቱ አማኝ ይሁን ኢ-አማኝ አላቅም፣ ዋናው ነገር የጸሎትን ከንቱነት ከበቂ በላይ በጹህፉ አስረድቷል። ኢትዮጵያ ብዙ የተባለላት የጌታ እናት በአስራት የተቀበለቻት ቅድስት ሀገር እንደሆነች ተሰብኮልናል። በዚህ ተቃውሞ የለኝም የኔም ምኞት ያ ነበር።

ታሪካችንን ወደ ኋላ ላየው እና አሁናዊ እውነታውን ለተረዳ ግን ጥርጣሬ ይፈጥራል። በብዙ ሀገራት ርሃብ ተከስቷል፣ ሁሌ እጇን ወደ ፈጣሪ በምትዘረጋው የሆነው ግን ጠኔና ችጋር ነው:: ጸለተኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ስላሳለፈው ችጋር የሀገርና የውጭ ሙህራን ብዙ ጽፈዋል። ፕ/ር መስፍን ወልደ ማርያም የታሪካችን አንዱን ክፍል ችጋርን በሸገር ብሎግ አምዳቸው እንዲህ ይገልጹታል፦ “ችጋር ምንድን ነው? ሰፊ ቦታንና ብዙ ሕዝብን የሚሸፍን፣ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ፣ ምንም የሚላስ የሚቀመስ ጠፍቶ እንስሳት (ሰውንም ጨምሮ) ዕለት በዕለት የራሳቸውን አካል እስኪያልቅ ድረስ ‹‹እየበሉ›› በመጨረሻም የሚሞቱበት ሁኔታ ነው” ለፕ/ር መስፍን ወልደ ማርያም ረሃብ ከችጋር አንጻር ቀላል ነው:: “ረሀብ አካል ሲዳከም አካልን ለመገንባት የሚደረግ ጥሪ ነው::” ነበር ያሉት። ዋናው ነገር ረሃብና ችጋርን ማወዳደር አይደለም ችጋር ማን ላይ እንደሚጠና ማወቁ ነው። በ1951 ዓ.ም. በትግራይ ችጋርን በዓይኔ አይቻለሁ፤ በጆሮዬ ሰምቻለሁ፤ በአካሌ ቀምሼዋለሁ፤ ጠኔ ይዞኝ ተደግፌ ወደቤቴ ገብቻለሁ የሚሉት በችጋር ዙርያ ሰፊ ጥናት ያደረጉት ፕ/ር መስፍን እንደሚሉት “ችጋር የሚያጠቃው ገበሬዎችን ነው:: እነዚህ ገበሬዎች የገጠሩ ሕዝብ፣ ማለትም የአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የመጨረሻ ደሀዎች ናቸው፤ ኑሮአቸው ሁልጊዜም በችጋር አፋፍ ላይ ነው::” እኔ እንደሚገባኝ የገጠሩ ህዝብ ገራገርና ለጸሎት የሚተጋ ነው:: እንዴ! የሁለት ሰዓት መንገድ እየሄደ እኮ ነው በተስኪያን የሚስመው፣ ወዳሴ የሚደግመው፣ ርሃቡን ቻል አድርጎ እኮ ነው ቅዳሴውን የሚያደርሰው። ላመነውም እምነቱም ሟች መሆኑን ታሪክ ምስክር ነው። ታድያ ለምን ጾለቱ አይሰማም? የኦሾን ፍልስፍና አላነበበም፣ የኒቸን የእግዚአብሔር ሙቷል ዜና አላራገበም፣ እንደዳውኪንስ

Created in Master PDF Editor

እግዚአብሔር ቅዥት ነው አላለም፣ እንደ ስቴፈን ሀውኪንግ እግዚአብሔር የለም አላለም፣ የዳርዊንን የተፈጥሮ መርጦሽ ሳይንስ አልተማረም ግን ለምን ጸለቱ አልተሰማም? ሀጢዓቱ ምንድን ነው? ወይስ እግዚአብሔር በችጋር ይከብራልን?ፀሎት የእግዚአብሄርን መኖር እንደማያስረዳ ከዚ በላይ እንዴት ላብራራው።

10. **ከአምላክ ጋር ግልአዊ ግንኙነት እንዳለኝ ይሰማኛል**

አንዳንድ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ስላላቸው የግል ግንኙነት ሲናገሩ ይደንቃል። እግዚአብሔር እንደሚያነጋግራቸው፣ በራዕይ እንደሚታያቸው፣ እና ለህዝቡ መልዕክት እነደላከ አድርገው አቅርበው እና አድቀው ይነግሩናል። በእርግጥ እነዚህ ሰዎች ሀሰተኛ ናቸው ማለት አይቻልም ምክንያቱም ሰዎች ራዕይ ሲያዩ፣ የእግዚአብሔርን ድምጽ ሲሰሙ፣ አለበለዚያ አንድ ልዩ መንፈሳዊ ስሜት ሊሰማቸው ይችላል።ኦሾ እንዲህ ይላል "All the history of the saints who have experienced God, talked with God, has to be researched with more psychological insight. They are not different than madmen. All their pretensions, declarations that they are the only son of God, that they are the only prophet of God, that they are the only reincarnation of God are nothing but mad assertions." (The Rebel, page 352) እነዚህን ሰዎች እግዚአብሔር መኖሩን ብቻ ሳይሆን የት እንዳለ፣ ምን እየሰራ እንደሆን፣ ምን እንዳቀደ ልንጠይቃቸው እንችላለን። ምን አልባት በምርምር ዘርፍ እንደሚባለው የመጀመርያ ደረጃ ምንጮች (Primary Source) ሊሆኑ ይችላሉ። ችግሩ እግዜሩ በግል የሚገለጥላቸው በግላዊ ቋንቋ ስለሆነ ምስክርነቱ እንቶፎንቶ ነው። ኦሾ "It will be a real shock if you can realize that these people were surrounded by hallucinations (illusion); they had created their own reality around themselves. Their gods are their imagination, their messages are from their own minds, the scriptures they have left behind are manufactured by them. No book is written by God, because I have gone through all those books – they are not even worth calling good literature. What to say about their holiness? They are third class literature, but people have worshipped them." (The Rebel, page 352) እነዚህ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ሃልዎት ያሉትን ቢሉ የትንሿ ፀሀይ አምላክ ለሁላችንም የሚሞቅ ግንኙነት ሊኖረው ስለሚገባ ይህን መሰል ትርክቶች ከተራ ወሬ ዘለው አያውቁም።

ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ግላዊ ግንኙነት ሊኖረው ይችላል። ሰዎች እስካለሙ ድረስ ከሚያልሙት ህልም ውስጥ እግዚአብሔር አንዱ ነው። ቅንጭላታችን ከሚሰራቸው ስህተቶች አንዱ የምንጨነቅበትን ጉዳይ በፊልም ቀርፆ በህልማችን ማሳየቱ ነው። ምን አልባት አንዳንዶቹን ብዙም ላንጨነቅባቸው እንችላለን ቢሆንም አስበንባቸዋል። ከዚህ ተነስቶ ቅንጭላት በፊልም መልክ ይጋብዘናል። በተለይ ከአንድ ሀይማኖት ወደ ሌላ ሀይማኖት የሚቀይሩ ሰዎች የሚሰጡትን ምስክርነት አድምጡ። አንድ ቀን ጌታ፣ ማርያም፣ አላህ፣ ነብዩ፣ ቅዱስ እከሌ ወይም እንዲህ አይነት ሰው እንዲህም

እንደዚያም ብሎ ተናገረኝ፡፡ ከዚህ ፀበል ሂደሽ ተጠመቂ አለኝ፡፡ መቀነት የታጠቀች መልከ መልካም ሴት ወደ እኔ ነኝ አለችኝ ሌላም ሌላም ሚሊዩን ህልማቸውን በእንባ እያጠቡ ያካፍሉናል፡፡

ብዙዎቹ እየዋሹ አይደለም፣ የዋሸው ቅንጭላታቸው ነው፡፡ ብታምኑም ባታምኑም ሳያልም የሚያድር አንደም ሰው የለም፡፡ እንዲያውም አንድ ሰው በአንድ ሌሊት ለቁጥር የሚታክቱ ህልሞችን ያያል፡፡ እና በህልማችንን ያየነውን ሁሉ ጌታ ነው ማለት አለብን፡፡

ያም ይሁን ይህ ሰዎች በተገለጠላቸውና በሳሉት መጠን እግዚአብሔርን ያዩታል፡፡ ነገሩ አፈ ታሪክ ቢሆንም አፄ ቴዎድሮስ ይህን መሰል ጥያቄ እያነሱ ካህናቱን ይፈትኗቸው እንደነበር ይተረካል፡፡ ታሪኩን የአዲስ አድማሱ አምደኛ ፍቅር ለይኩን እንዲህ ያስታውሰናል፡-*“አፄ ቴዎድሮስ ብዙ ከተባለለትና ከተጻፈለት አፍሪካዊው ናፖሊዮን ካሰኛቸው ከጀግንነታቸው፣ ከጭካኔያቸው፣ ከፍርድ አዋቂነታቸውና ኢትዮጵያን ለማዘመን ከነበራቸው ታላቅ ራእይ ባሻገር በተለያዩ ጊዜያት ስለ ፈጣሪ ህልውና ከቤተ ክህነቱ ተጠሪዎች ነን ባዮች ደብተራዎችና ካሕናት ጋር ያደረጓቸው እንደ አንዳንድ የዋኃን አገላለጽ ‹‹ፈጣሪን መፈታተን›› ዓይነት ጥያቄዎችን እያነሱ ካሕናቱንና የቤተ ክርስቲያኒቱን ሊቃውንቶች በጥያቄ በማጣደፍ ያስጨንቁ ነበር ይባላል፡፡ እናም በአንድ ወቅት አፄ ቴዎድሮስ በዙፋናቸው በተሰየሙበት ግብር ገብቶ መኳንንቱና መሳፍንቱ፣ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንቱና ካሕናት በታደሙበት ግብዣ ላይ ንጉሡ አንድ ጥያቄ አነሱ እንዲህ ሲሉ፡-‹‹<u>ለመሆኑ እግዚአብሔር አለ… ካለስ ምን እየሰራ ነው…!?</u> በማለት ጥያቄያቸውን ወርወር አድርገው የሊቃውንቱንና የካሕናቱን መልሳቸውን ለመስማት ጓጉተው መይሳው ካሳ ከዙፋናቸው ላይ ተመቻቹ፡፡ሊቃውንቱና ካሕናቱ ሁሉ የመሰላቸውንና የንጉሥን ልብ ያሳርፋል ያሉትን መልስ ሁሉ ወደ አፄ ቴዎድሮስ መወርወር ጀመሩ፤ ይሁን እንጂ ከእነዚህ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ነን ከሚሉ ሊቃውንትና ካሕናት ዘንድ ንጉሡ ቴዎድሮስ ልባቸውን የሚያሳርፍ በቂ ምላሽ አላገኙም፡፡ እናም በቁጣ ሆነው ሊቃውንቱንና ካሕናቱን በመገላመጥ ከግብር ቤቱ በራፍ ላይ ደበሎውን ለብሶ አኩፋዳውን ይዞ ከንጉሥ ገበታ የሚተራረፈውን እንጀራ የሚጠብቀውን አንድ ምስኪን የቆሎ ተማሪ ወደ ዙፋናቸው አስጠርተው ተሜ፡- ‹‹እግዚአብሔር አለን… ካለስ ለመሆኑ ምን እየሰራ ነው…!? አሉት፡፡ ተሜም ለጥ ብሎ እጅ ከነሳ በኋላ ‹‹ንጉሥ ሆይ ሺህ ዓመት ይንገሱ! እግዚአብሔር መንግሥትዎን ያስፋ፣ ጠላትዎን ያጥፋ! ጃንሆይ እግዚአብሔርማ አለ! የቀን ተሌት ሥራውም ለእያንዳንዳችን መልካም ሆነ ክፉ ስራችን ምላሽ/ብድር/ ሰፍሮ <u>የሚመልስበትን ቁና ሲሰፋ መኖር ነው!››</u> በማለት መለሰ፡፡”* (ምንጭ፡- ፍቅር ለይኩን፣ እግዚአብሔር አለ ካለስ ምን እየሰራ ነው?)

Created in Master PDF Editor

በእየ ቤተ እምነቱ የስብከት አደራሾች ስሙ <እግዚአብሔር እንዲህ ይላል> እያሉ ያልተፃፈ የሚያነቡት ቴሌቭንጋስቶች እግዚአብሔር አናግሯቸው አይደለም። እግዚአብሔር እዩ ጩፋን መሰል ቴሌቫንጋሊስቶች መርጦ የሚገለጥበት ምክንያት የለውም። የሁሉ ጌታ እስከሆነ ድረስ ለሁሉም ይገለጣልም እንጅ።

አማኞች አምላክን አቅርበው ቢሳሉትም ፈላስፎች ግን እግዚአብሔር የት ነው እያሉ ዛሬም ይጠይቃሉ።

> እግዚአብሔር የት ነው ያለው? በውስጣችን ወይስ ከውጭ? አብዛኛዎቹ ሃይማኖቶች እግዚአብሔር ከእኛ ውጭ ሆኖ የራሱ ሕልውናና መገኛ ቦታ እንዳለው ያስተምራሉ። የሰው ልጅ ሲሞትም ነፍሱ እግዚአብሔር ወደሚገኝበት ቦታ ይሄዳል። ሆኖም ግን እግዚአብሔር የሚገኝበትን ቦታ <መንግስተ ሰማያት> ከማለት ውጭ በትክክል የት እንደሆነ ለእነዚህ ሃይማኖቶችም ግልጽ አይደለም። ይህ መንግስተ ሰማያት የት ነው? ዩኒቨርስ ውስጥ ወይስ ከዩኒቨርስ ውጭ? ዩኒቨርስ ውስጥ ከሆነስ በየትኛው አቅጣጫ? እግዚአብሔር የሚገኝበት የተለየ ቦታ ካለ እሱ የማይገኝበት ሌላ ቦታ አለ ማለት ነው፣ ይሄ ከሆነ ደግሞ እግዚአብሔር በቦታ የተወሰነ ነው ማለት ነው። (ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣ 84)

የሰው ልጅ ከትላልቅ ጥበቦቹ አንዱ በህሊናው ውስጥ የሚቀረፀው ፊልም ነው። ይህን ፊልም ነው አማኞች መገለጥ የሚሉት። የፊልሙ ዋና ገፀ ባህሪ እግዚአብሄር (ወይም ሌላ መንፈስ) ሲሆን ብዙ ጊዜ የታሪኩ ጭብጥ ወዮላችሁ ነው። የፊልሙ ደራሲ ሳብ ኮንሽስ ማይንድ (Subconscious mind) ሲሆን ዳይሬክተሩ ባለ ራዕዩ ነው። እናንተም ቢሆን በአጋጣሚ እንዲህ አይነት ራዕይ አይታችሁ ከሆነ የሁሉንም አይነት እምነት ሰዎች ሊያዩት የሚችሉ እና ከሌላ አለም ሳይሆን ከተደበቀው የአዕምሮአችሁ ክፍል የመጣ መሆኑ እወቁ።

ሃይማኖት ለአንዳንድ አማኞች በጣም የግላዊ ይሆን እና አምላክን በራሳቸው ወርድ እና ቁመት ይፈጥሩታል። በስብከት ብዛት ይህ ግላው ህልም ወደ ሀይማኖትነት ያድጋል። የአለም ሀይማኖቶችን ብዛት ለሚጠይቁ ሰዎች መልሱ በባለ ራዕዮች ቁጥር ይወሰናል ማለት ነው። ምን አለባት በቴሌፓዚ ካልሆነ በስተቀር ሰዎች ተማሳሳይ ህልም አያልሙም። ነብይ እዩ ጩፋና መ/ር ግርማ ወንድሙ ተመሳሳይ ህልም አያልሙም።

የሩቅ ምስራቅ ሀይማኖቶች የእግዚአብሔር መኖሪያ በተመለከተ መልካም አመክንዮ አላቸው። ምን አልባት ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት አለን ካሉ የመስራቆቹ ሀይማኖቶች ተከታይ መሆን አለባቸው። በምስራቆቹ ሀይማኖቶች እግዚአብሔር የሚኖረው በሰው ህልውና ውስጥ ነው፤ ወይም በተፈጥሮ ውስጥ ነው። ያለ ተፈጥሮ

Created in Master PDF Editor

እግዚአብሔር ቦታ የለውም ይላሉ፡፡ የምዕራቡ ሀይማኖቶች ግን እግዚአብሔር ከሰውነታቸው ውጭ እንደሆነ ያስባሉ፡፡ ወይም የሚኖርበት ቤት ይሰሩታል፡፡ በምእራቡ ሀይማቶች የሚታነፁት ድንቅ የአምልኮ ቤቶች እግዚአብሔር ከሰው ልብ ውጭ ስለመሆኑ ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡

> እግዚአብሔርን ከእኛ ውጭ እንደሚኖር የምናስበው ለስነ ልቦናችን ስለሚመች ነው፡፡ የሰው ልጅ ስነ ልቦና ደግሞ ከሕልውናው ደህንነት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው፡፡ ልጅ እያላችሁ የሚንከባከባችሁና የሚጠብቃችሁ ወለጅ አባት ነበራችሁ፤ ካደጋችሁ በኋላ ግን ሌላ አባት ከውጭ (በምናብ) ፈጠራችሁ፤ የሰው ልጅ የደህንነት ስጋቱን ለመቅረፍ የሚንከባከበውና ስለእሱ ደህንነት ግድ የሚለውን አምላክ በሰማይ ፈጠረ፣ ይላል ዚግመንድ ፍሮይድ፣ አሾም የሰው ልጅ ነፃ መሆንን አይሻም፤ በሰማይ የሚኖር አባት ይኖረው ዘንድ ይፈልጋል፣ ቢያንስ ቅሬታ የሚያቀርብለትና የሚፀልይለት አባት ይፈልጋል፤ የሚንከባከበው ጠባቂ አባት ይፈልጋል፡፡ በሰማይ የሚኖር አባት ከሌለ የጠፋ ይመስለዋል፡፡ በስነ ልቦና ሰው አባት የመፈለግ አባዜ አለበት፡፡ አባታዊ ምስልን ስለምትፈልጉ የሚንክባክባችሁ አባት ከውጭ ፈጠራችሁ፡፡ ራሳችሁ የፈጠራችሁት አምላክ በመሆኑ ስትሰግዱ በተዘዋዋሪ ለራሳችሁ እየሰገዳችሁና ራሳችሁን እያመለካችሁ ነው፡፡ እውነቱ ግን ይሄ አይደለም፤ እግዚአብሔር የሚገኘው ከውጭ ሳይሆን እናንተ ውስጥ ነው፤ እግዚአብሔር ሰው ሳይሆን የመጨረሻው የደህንነት ስሜት፣ የመጨረሻው የምቾት ስሜት፣ እንዲሁም እኔ የዚህ ዓለም አካል ነኝ፣ ይህ ዓለምም የእኔ ነው፤ እኔ ከሌለ ዓለም የመጣሁ ፍጡር አይደለሁም፤ የሚያስብልን የመጨረሻው ስሜት ነው፡፡ በመሆኑም እግዚአብሔር ከእናንተ ውጭ ሕልውና የለውም፡፡(ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣ 82-86)

እግዚአብሔር ከሰውና ከተፈጥሮ ውጭ ህልውና የለውም የሚለው አስተሳሰብ በምስራቆቹ ሀይማኖቶችና በፍልስፍናው ዘርፍ የተለመደ ነው፡፡ የምዕራቦቹ ደግሞ ከውስጣቸው የተደበቀውን አምላክ በራዕያቸው እያዩ ከውጭ እንደአለ አድርገው ይተርኩልናል፡፡

በብዙ በሀይማኖቶች ውስጥ ራዕይ ትልቁ በሰዎች እና በእግዚአብሔር መካከል የተፈጠረ ድልድይ ነው፡፡ እነዚህን ግላዊ ግንኙነቶችንበመጠቀም ለእግዚአብሔር መኖር እንደ ማስረጃ መጠቀም አሳማኝ አይደለም፡፡ ሲጀምርም ራዕዩ ጭረሹን ሆን ተብሎ የተፈጠረ ማተለያ ሊሆን ይችላል፡፡ እውነት ቢሆንም እንኳ ሁሉን የሚችል አምላክ ለሁለችንም ይገለጥልናል እንጅ እንዱን ልጅ ከሌላኛው ልጁ አያበላልጥም ካበላላጠ ግን የፍትሀዊነት ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ብዙ ጊዜ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ከሆነ የሌሎች አህጉራት ፈጣሪ ማን ነው የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡

Created in Master PDF Editor

ለነገሩ ዋና ዋናዎች እምነቶች የተነሱት መካከለኛው ምስራቅ ነው። ምንአልባትም የእነዚህ አካባቢ ሰዎች ብዙ ራዕይ የሚያዩ ሳይሆን አይቀርም።

እውነት ለመናገር እግዚአብሔር አለ ከማለትና የለም ከማለት አለ ማለት የተሻለ ይመስላል። ሲጀመርም እኮ የሃይማኖትን ታሪክ ያጠኑት እንደሚሉት የአመልዕክት ሚና የሰው ልጅ የሚያጋጥመውን ፍርሃት ስጋትና ዘለአለማዊ ሞትን በመቅረፍ ጊዜአዊ ደስታን መፍጠር ነው። ከዚያም ነገሮች ተደጋግመው ሲነገሩ የሰው ልጅ ነገሮችን እንደ እውነት መውሰድ ጀመረ።

አሁን ግን ሰዎች ያለ ሃይማኖት ደስተኛ ሁነው እየታዩ ነው። ይማራሉ፣ ቤተሰብ ይመሰርታሉ፣ ቤት ይሰራሉ፣ ልጆች ይወልዳሉ፣ ተስፋ ያደርጋሉ፣ በአጠቃላይ አማኝ እንደሚኖረው ይኖራሉ። ነገሩ ይህ ከሆነ ደግሞ ጥንት ለደስታ ምንጭ ብለን የፈጠርናቸውን አሻንጉሊት አማልዕክት ወደ ቤተ መዛግብት ልከን ወደ ቤተ ሙከራ ማተኮር አለብን። ለሁሉም ግዜ አለው በአማልዕክት ለማመንም ለአለማመንም ጭምር።

አሁን ነገሮች ተቀይረዋል፣ ማመንም አለማመንም ለደስታ ላይ ያላቸው ተፅዕኖ ተመሳሳይ ነው። የሚያምኑት በእግዚአብሔር ድንቅ ስራ ተመስጠው መንፈሳቸውን በደስታ ሊሞሉ ይችላሉ። የማያሞኑትም በተፈጥሮ ሊመሰጡ ይችላሉ፣ በተፈጥሮ ውበትም ይደሰታሉ። የተፈጥሮ ነገር እያሰቡ ይዘምራሉ፣ ይሞዝቃሉ፣ ይደንሳሉ፣ ይዝናናሉ፣ ይደሰታሉ። አስደንጋጭ የሚሆነው ዜና ደግሞ የሚያምኑት ከማያምኑት ደስተኛ በመሆናቸው በጥናቶች መረጋገጡ ነው። ዴንማርክ፣ ሰውዘርለንድ፣ ካነዳ፣ አይስላንድ፣ ፊንለድ፣ ሲውድንና ኦስትሪያ ሰዎች ደስተኛ ሁነው የሚኖሩባቸው ናቸው። በእነዚህ ሀገራት ከሌሎች በተለየ ለሃይማኖት ደንታ የላቸውም ወይም ኤቲስት ናቸው። ታዲያ ምን እናድርግ? አሳዛኙ ዜና ይቀጥላል ሀገራት ዜጎቻቸው አማኞች በሆነ ቁጥር ደስታ ይርቃቸዋል። ለዚህም የአፍሪካና የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ተጠቂ ናቸው። በደስታ ደረጃ የመጨረሻውን ሲይዙት በአማኝ ብዛት ግን የመጀመሪያዎቹን ደረጃዎች ተቆነጥጠዋል። ታዲያ ምን ይደረግ?

ደስታ ያለው እዚህ ነው። ከዚህ ከኛ ሰፈር ደስታን ለመፈለግ ሰማያትን አታናጉ። ደስታ ያለው ልብ ውስጥ ነው። ልብ የማያልቅ ደስታ፣ የሚጣፍጥ ዜማ፣ የማይነጥፍ ምአዛ፣ የሚያረጋጋ ተስፋና መጽናናት፣ ወረት የሌለው ፍቅር፣ ምንም ሳይሆን ሁሉንም የመሆን ጥበብ ተቀብሮበታል።አውጡና ተጠቀሙበት።

11. **በእግዚአብሔር ማመን የተሻለ ነው፣የእኔ ማመንም ማንንም አይጎዳም**

ከማወቃቸው የአማኞች መከራከርያ በመጠኑ ሊያሳምን የሚችን የሂሳብ ስሌት ያለው መከራከርያ ነው። እንድ የምወደው ጓደኛየ እግዚአብሔር ቢኖርም ባይኖርም

Created in Master PDF Editor

ካለማመን ብታም ይሻላል ይለኛል፡፡ ልጁ ልዲርስብኝ የሚችለውን መገለል በማሰብ ነው፡፡ እስኪ ማመን ካለማመን የሚሻልብቸውን ነጥቦች እንይ፡፡

1) በእግዚአብሔር ብታምኑ እና እርሱ ቢኖርየዘላለም ህይወት ታገኛላችሁ-መልካም
2) በእግዚአብሔር ብታምኑ እና እርሱ ባይኖር ምንም ነገር አይቀርባችሁም-አይ አይ
3) በእግዚአብሔር ባታምኑ እና እርሱ ቢኖር ለዘላለም በሲኦል ትቀጣላችሁ-ወየው ለኔ
4) በእግዚአብሔር ባታምኑ እና እርሱ ባይኖር ምንም ነገር አትጎዱም-ዋው!

ከእነዙህ ሎጅኮች በመነሳት አማኞች ለሚወዷቸው ኢ-አማኞች ምክር ሲለግሱ እግዚአብሔር ቢኖርም ባይኖርም ብታምኑ ይሻላል ይላሉ፡፡ ሂሳቦቹ ማመን ባይጠቅም እንኳ እንደማይጎዳ ለማስረዳት የተሰሩ ስሌቶች ናቸው፡፡ እውነቱ ግን ማመን የማሰብን ነጻነት ይገድባል እናም የታጠረ ኖሮ እንድንኖር ያደርጋል፡፡ ይህ ደግሞ የሰው ልጅ በራሱ ላይ የፈጠረው ታለቁ እስር ቤት ነው፡፡ ያልተዘጋው ማዕከላዊ ይህ ነው፡፡

በግሌ የሚወዱኝ አማኞች ለሰጡኝ ምክርያላችሁትን በፍርሀት ወይም ፅድቅን በሂሳብ በመስራት ለመቀበል ይከብድኛል፡፡ እሽ እግዚአብሔር አለ ብልስ የትኛዉ እግዚአብሔር ይሆን፡፡ ምን አልባት የወላጆቸ አምላክ እንዳይሆን ሀይማኖት የግል ነው ሀገር የጋራ ነው ከተባለ ስንት ዘመን አለፈ፡፡ እንዲህ ሂሳብ ከመስራት በነፃነት ኖሮ በነፃ መሞት ይሻላል፡፡ በእውነት እላችኃላሁ እግዚአብሔር ካለ እውነትን ሲፈልጉ የመሸባቸውን ምስኪን መናፍቃን አላስጠጋም አይልም፡፡ አንድ ሽህ ፐርሰንት (1000%) እርግጠኛ ነኝ፡፡ ለዚህ ነው ሰውን እንጅ እግዚአብሔር የማልፈራው፡፡

ምን አለእግዚአብሔር ኖሮ እኛ ብቻ ነን ትክክል ለሚሉት መንግስቱን ከእነርሱ ጋር አውርሶን ባዩት፡፡ ለነገሩ ከዚያም ይከሱን ይሆናል፡፡ ለእግዚአብሔር ምነው ድካማችንን ከንቱ አደረከው፤ ከጠላቶቻችን ጋር እንድንኖር ፈረድክብን፤ ወንጌልህን ሰብክን ከከሀዲይን ጋር ደመርከን የሚሉት ይመስለኛል፡፡

ብዙ አማኞች የሚገርም መራከሪያቸው ይህ ነው ማመን ካለማመን የተሻለ ነው፡፡ የሚያምኑትን ነገር ማስረዳት አይችሉም ወይም አይፈልጉም፡፡ በማመናቸው አለመክስራቸውን ግን ያውቃሉ፡፡ ግን በእውነት ዝም ብሎ ካለማምን ማመን ይሻላል ብሎ ማመን ኪሳራ የለውም? እኔ በእስልምና አመንኩ ልበል በቀን 7 ጊዜ መስገድን፣ በሀሩር አየር ንብረትና በተጨናነቀ ሁኔታ መካ መዲና መመላለስን፣ በተለይም ሙሉ ህይወቴንና ማንነቴን ለአላህ መስጠትን ከኖርኩበት በኂላ ልሞት አንድ ደቂቃ ሲቀረኝ የኖርኩበት ኖሮ ሁሉ ትረት እንደሆነ ባውቅ አይቆጨኝም? በጣም ይቆጫል፡፡ ብዙ

Created in Master PDF Editor

ሰዎች ሀይማኖታቸውን መቀየራቸውን በሚድያ ያውጃሉ፣ ስለአዲሱ እምነታቸውም ምስክርነት መስጠት የተለመደ ነው፡፡ ከእነዚህ ሰዎች የታዘብኩት ቢኖር ያለፈ ታሪካቸውን እጅግ ይቆጨበታል፡፡ ያባከኑት ጊዜ፣ ገንዘብና ጉልበት ከስሮ እንደቀረ ይሰማቸዋል፡፡ ወደ ኋላ ሳይመለሱ ሲምሉ ሲገዘቱ የምትሰሚቸው የደረሰባቸው ኪሳራ ስለሚከነክናቸው ነው፡፡ ቁሳዊ ነገሩን ተውት የማይታመንን ማመን በራሱ ወደር የለሽ ኪሳራ ነው፡፡ የማይጠገኑት ስብራት፣ የማያክሙት ህመም፣ ይቅር ያማይሉት ጠባሳ ነው፡፡

እምነትን ሲተውት እንጅ ሲያምኑት እውነት ነው፡፡ የጥንቶቹን የግሪክ፣ የግብፅ፣ የሮም፣ የፐርሻ፣ የየመን፣ የአክሱም፣ የኩሽ፣ የአዜቲክስ፣ የሩቅ ምስራቅ፣ የደቡብ አሜሪካና የአፍሪካ አማልዕክትን እሰቧቸውና ተገረሙ፡፡ ዛሬም ድርስ ዛፍ የሚያመልኩ፣ ለህመማቸው እንቁላል ለመናፍስቱ የሚጥሉ፣ ለወንዝና ተራራ የሚሰግዱ፣ እንዲሁም እጅግ በበዙ እምነት ወለድ ልማዶች የተተበተቡ ወገኖቻችን መኖራቸውን በማሰብ ብዙ መስራት እንዳለብን መረዳት እንችላለን፡፡ ከእነዚህ ባህላዊ ጎጅ እምነቶች አንፃር ክርስትና እና እስልምና መልካም ናቸው፡፡ እንዲያውም ታላቅ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ ዛሬ ወደ ክርስትና ወይም ወደ እስልምና የተቀየሩ አካባቢዎችን የኋላ ታሪክ ስናስታውስ ለመስማት የሚቀፉ እምነቶች እናውቃለን፡፡ ስለዚህ በብዙ ከመክሰር ትንሽ መክሰር ይሻላልና ከጎጅ ባህላዊ እምነቶች ያለቀቁን የአብርሃም ሀይማኖቶች ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ ታዲያ የአብርሃም ሀይማኖቶች ይህን መሰል የተቀደሰ ስራ ከሰሩ ለማን በኢ-አማኞች ይተቻሉ? መልሱ አጭር ነው አንደኛ እነሱም ከአሮጌዎቹ የወረሱት አላስፈላጊ ልምምዶች ስላሉና በመሰረታዊነት ስህተት ስለሆኑነው፡፡ አሁን ጊዜው ሌላ ምንም የማያከስር እና ፆም፣ ስግደት፣መስዋዕት፣ አስራት በኩራት የማይጠየቅ የህይወት ዘይቤ ስለተገኘ ነው፡፡ የማያከስረው እውነተኛ ህይወት አይሰበክም ይኖራል እንጅ፡፡ ሳይንቲስቶች ለግራቪቲ፣ ለሪላቲቪቲ፣ ለኢቮሉሽን፣ለማግኔቲዝም፣ ለኢነርጅ፣ ለግዜና ቦታ፣ ለሴሎች፣ ለአተሞችና ለኳርክስ፣ ለፓርቲክሎች ሲፀሙና ሲጸልዩ ሰምታችኋል? አይመስለኝም አሜን የሚለው ቃል በእውነት ቤት ዋጋ የላትም፡፡

እውነት እንደ እምነት ባይሆንም ትንሽ ኪሳራ ሊኖረው ይችላል፡፡ ያም ትንሽ ኪሳራ ብዙ ትርፍ ያመጣልና በድምር ውጤት ትርፍ ያመዝናል፡፡ እንደፈለሰፋው አርተር ስኮፔንሃወር አባባል እውነት ሶስት ነገሮች ያልፋል፡፡ በመጀመሪያ ይሾፍበታል፣ ቀጥሎ ከፍተኛ ተቃውሞ ይደርስበታል በመጨረሻም ያሸፉበትና የተቃወሙት ይመስክሩለታል፡፡ በሳይንስ ታሪክ ያልተወገዘ ምርመርና ግኝት የለም፡፡ የእውነት ልጆች ለብዙ ትርፍ ሲሉ ጥቂት ከስረዋል፡፡ ኪሳራው የደረሰባቸው በአለም ላይ ያለው ጨለማ ሁሉ የአንዲትን ሻማ ብርሃን ሊያጠፋ አለመቻሉን ለማሳየት ባደረጉት ትግል የደረሰባቸው ሰቆቃ ነው፡፡ የገሃነም ደጆች አይችሏትም የተባለው ለማን ነበር?

Created in Master PDF Editor

ካለማመን ማመን ይሻላል የሚል መከራከሪያ የሚያቀርቡት አመኞች ሳይሆኑ ቁመርተኞች (Gamblers) ናቸው። ሎተሪ ከሚቆርጥና ሎተሪ ከማይቆርጥ የቱ ነው ሽልማቱ ሊደረሰው የሚችለው? ምን ጥርጥር አለው ሎተሪ የቆረጠው እድል አለው። አንድ ለብዙ ሚሊዮነኛ በፐርሰንት ሲገለፅ 0.0000001% ነው። ሂሳቡ መልካም ነበር ግን ሎተሪውን የያዘው እጣ ሳይወጣ ቢቀርስ እድሉ 0% ይሆናል ማለት ነው። ሎተሪውን የገዛበት ገንዘብም ከተስፋው ጋር ከሰረ።

ሙስሊሞች ሙስሊም ያለሆነ በእሳት እንደሚቃጠል ይተረካሉ። ይህ ለክርስቲያኖች ምንም አይደለም። ክርስቲኖችም አምኖ ያልተጠመቀ እንደማፀድቅና የእግዚአብሔር መንግስት ወራሽ እንደማይሆን ይሰብካሉ። ይህ ለሙስሊሞችና ለሌሎች አያስጨንቅም። ሁሉም ሌሎች ሀይማኖቶች የማይቀበሏቸውን ለመቅጣት ሲኦል መሰል የመቀጣጫ ቦታ አዘጋጅተዋል። ይህ ለክርስትና እና ለሙስሊሞች ምንም አይደለም። ልክ እንደዚህ ሁሉ ኤቲስቶች ስለአማኞች ገነት እና ሲኦል አይጨነቁም፣ አይፈሩምም። እናም ጊዜአቸውን የገነት መግቢያ ካርድ በመግዛት ሳይሆን በምርምር ነው የሚያሳልፉት። አንዱን በመሆን ሌላኛውን በማይሆንበት የሃይማኖት ስርዓት ውስጥ ወይም በአንድ ሃይማኖት እንኳ የድህነት ሰንሰለቱ ረዥም በሆነበት መንገድ ከመኖር ለምን ነፃ ሆኖ ለማንም ሳይሆኑ እራስን በራስ ማስተዳደር አይቀልም። የማን ነሽ ይሉኛል የማን ልበላቸው የሚለው ድንቅ የትዝታ ዘፍን ለሀይማኖቶችም ቢዘፈን።

ሁሉንም እርግፍ አድርጎ ትቶ ወደ ማንነት መመለስ እጅግ ይቀላል እንጅ አይከብድም። የማይወርድ ሸክምና እረፍት የሌለው ሸብር ተሸክሞ ከመኖር ሸክምን አራግፎ በሰላም መኖር አይሻልም? በእውነት ሰዎች እድሜ ዘመናቸውን በከንቱ ለከንቱ ነገር ሲያውሉት ሳይ አዝናለሁ። ህፃናት ፊደል እንኳ ሳይቆጥሩ ለእድሜ ዘመን እስራት ሲታጩ ያሳዘነኛል። ትልቅ የሀብት ብክነት ይመስለኛል። እድሜን ያህል ሀብት ማባከን አያስቆጭም? ምርጫችን ትክክል ነው ጊዜአችንን አልባከነም የምትሉ ከሆነ ጥያቄ አለኝ። ሃይማኖታችሁን ስትመርጡ ወይም ሲመርጥላችሁ ሁሉንም አማልዕክት ታሳቢ አድርጋችሁ ነው ወይ? ከሆነ መልካም ነው ግን ትክክለኛው የሎተር ቁጥር ለማግኘት ብዙ አመታት ምን አልባትም እድሜ ዘመናችሁን መሞከር አለባችሁ። ስጋቴ ምን መሰላችሁ ከ100,000 አማልዕክት እውነተኛውን አምላክ ለይቶ ለማውጣት ከ100 አመት በላይ ጥናት ይጠይቃል ወይም አምላክ በአጭሩ ትክክለኛው አምላክ እኔ ነኝ ሊላችሁ ይገባል። ይህ ደስ የሚለውን አቋራጭ መንገድ ነው። ችግሩ ግን በህልማችሁ ወይም የራሳችሁን ድምፅ መልሳችሁ እንዳትሰሙት ነው። ምክንያቱም ሰዎች የራሳቸውን ፍላጎት በህልማቸው ይሰማሉና። ማርያምን የሚወድ ሰው ማርያም ትገለጥለታለች። ጊዮርጊስን የሚወድ ሰው ጊዮርጊስ ይገልጥለታል።በመናፍስት የሚያምን መነፍስት ይገለጡለታል። በእስልምና የሚያምን

Created in Master PDF Editor

ሰው ሙሀመድ ይገለጥለታል፡፡ ምንም ድንቅ ነገር የለውም ከተደበቀው አእምሮአችን ውስጥ እያወጣን ከማንበብ በስተቀር፡፡

አሁንም ቢሆን መቆመር እንፈልጋለን ለሚሉ ግን አንድ ሞክር አለኝ፡፡ ሁሉንም አማልዕክት አምልኩ፡፡ ግን በሞክሬ ተፀፀትኩ ምክንያቱም 100,000 አማልዕክት ለማምለክ ጊዜ የላችሁም፣ ለግብር የሚሆን ገንዘብም ላይኖራችሁ ይችላል፡፡ የተሻለ ነገር ልምክራችሁ ሁሉንም በልባችሁ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ ጣሏቸው፡፡ ከዚህ ነፃና ከቁማር ሱስ ነፃ ትሆናላችሁ፡፡ ሁሌ በመንፈሴ ከጨለማ ውጡ ማርና ወተት ወደምታዘንበው እየሩሳሌም ኑ የምላችሁ ለዚህ ነው፡፡ ከጨለማ ውጡ፣ ከቁማር ውጡ ወደ ገነት ኑ፡፡ ሁላችሁም ተጋብዛችኋል፡፡

ሌላው መከራከርያ የአማኞች ማመን ለማያምኑትና ሌሎች አማልዕክትን ለሚያመልኩት ጉዳት የለውም የሚል ነው፡፡ የአማኞች ማመን ለማያምኑትም ለራሳቸው ለሚምኑትም ጉዳት አለው፡፡ ብዙዎቹ በይፋ አይናገሩት እንጅ ሽብርተኝነት እና ሀይማኖት ከጥንት ጀምሮ እጅና ጓንት ናቸው ይባላል፡፡ የኖባል ተሸላሚው ሳይንቲስት እስቴፈን ዊንበርግ “በሀይማኖት ወይም ያለ ሀይማኖት መልካም ሰዎች መልካም ስራ ይሰራሉ መጥፎ ሰዎች መጥፎ ስራ ይሰራሉ፡፡ መልካም ሰዎች መጥፎ ለመስራት ግን ሀይማኖት ያስፈልጋቸዋል” ብሎ ነበር፡፡ ዝርዝር ውስጥ ሳልገባ ለሽህ አመታት የሃይማኖት ልዩነት በፈጠረው ጦርነት የፈረሰው ደም የሰው ልጅ አይደለም እንዴ? ሽሂት ሙስሊሞች ሱኒ ሙስሊሞችን፣ ሰኒዎችም ሽሂቶችን ስንቴ አሳደዋል፡፡ ካቶሎኮችሽ ኦርቶይክሶችን እና ፕሮቴስታንቶችን ስንቴ ገረፈዋል፡፡ ምሳሌ ማንሳት ስላለብኝ እንጅ ጠባሳ እየቆጠርኩ አይደለም፡፡ ተቆጥሮም አያልቅም፡፡ ይህ ማለት ግን አማኞች የአለም ስጋት ናቸው ማለት አይደለም እጅግ ጥቂቶቹ ብቻ ስጋት ናቸው፡፡ አብዛኛው አማኞች አክራሪ አይደሉም ከማንም ጋር በሰላም ለመኖር ዝግጁ ናቸው፡፡ ሰባኪዎች እንኳ ቢያነሳሷቸው እጃቸውን በወንድሞቻቸው አያነሱም፡፡ ይልቅስ ተጋብተው፣ ተዋልደውና ተከባብረው መኖር ይፈልጋሉ፡፡ የረሳቸውን ሀይማኖት የሚጠብቁትና አጥባቂ የሚባሉት አማኞች በዘመናዊ መንገድ ይከራከራሉ እንጅ ሰይፍ ይዘው ግዳይ አይጥሉም፡፡ ቢሆንም በሀይማኖቶች ውስጥ ያሉ በአንዳንድ ሀይማኖታዊ መፅሀፍት የሚራገበውን ፅንፈኝነት የሚያቀነቅኑ ልባቸው የተሰለበ፣ ቅንጭላታቸው የላሸቀና ልባቸው የደነደነ አክራሪዎች ለአለም የሽህ አመታት ስጋቶች ናቸው፡፡

የማንም ማመን ማንንም የማያጎዳው ቀይ መሰመሩን እስከለለፈ ነው፡፡ የሰውን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እየገፈፈ የእኔ ማመን ማንንም አይጎዳም ማለት ቀልድ ነው፡፡ የአርዮስ ኤቴስት መሆን ማንንም የማይጎዳው ሰዎችን በለበሱት ልብስ፣ ከአንገታቸው ባለው ማተብ፣ ከራሳቸው ባለው ቆብ፣ በሚናገሩትና በሚፅፉት ሀሳብ መፈረጅ እስካልጀመረ ነው፡፡ በተቀጠርኩበት ስራና በማህበራዊ ህይወቴ

Created in Master PDF Editor

የማይመስሉኝን ማግለል የሚመስሉኝን ማቅረብ የጀመርኩ ቀን ሞትኩ ማለት ነው፡፡ በእየ አካባቢያችን የሚሆነውን ለቀባሪ ማርዳት ነው ሰው ፍትህ የሚያገኘው እንዴት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ከእነዚህ የአደልኦ ምንጮች አንዱ ሀይማኖት ነው፡፡ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ሰዎች በተፈጥሮ የራስን የማቅረብ ሱስ አለብን፡፡ በዚህ አካባቢ ብዙ ደስ የማይል የተተበተበ ስርዓት አለ፡፡ እንደሚስተካከል ባለ ሙሉ ተስፋ ነኝ፡፡ “መልካም ይሁንልን” ብያለሁ፡፡

12. የእግዚአብሔርን ባህሪ መተንተን አንችልም

እግዚአብሔርን ማወቅና ስለእርሱ መተንተን እንደማንችል በመጻፈ ኢዮብ ምዕ 11 ከ 7-10 እንድህ ተጽፏል፦ “የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን? ወይስ ሁሉን የሚችል አምላክ ፈጽመህ ልትመረምር ትችላለህን? ከሰማይ ይልቅ ከፍ ይላል፤ ምን ልታደርግ ትችላለህ? ከሲኦልም ይልቅ ይጠልቃል፤ ምን ልታውቅ ትችላለህ? ርዝመቱ ከምድር ይልቅ ይረዝማል፥ ከባሕርም ይልቅ ይሰፋል፡፡እርሱ ቢያልፍ፥ ቢዘጋም፥ ጉባኤንም ቢሰበስብ፥ የሚከለክለው ማን ነው?” ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልዕክቱ 11:33-35 ላይ መጽሃፈ ኢዮብን ያጠናክረዋል፡፡ “የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፥ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም፡፡ የጌታን ልብ ያወቀው ማን ነው? ወይስ አማካሪው ማን ነበር? ወይስ ብድራቱን ይመልስ ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው?” በድጋሜም 1ኛ ቆሮ. 1:20 “ጥበበኛ የት አለ? ጻፊስ የት አለ? የዚች ዓለም መርማሪስ የት አለ? እግዚአብሔር የዚችን ዓለም ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን አላደረገምን?” ሲል ይጠይቀናል፡፡

ብዙዎቹ የአዋልድ መጽሃፍትም የእግዚአብሔርን ነገር በምስጢር አስረውታል፡፡ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞች ስለእግዚአብሔር ምስጢራት እንዲህ ያስባሉ፦ “ምሥጢራተ-ቤተ-ክርስቲያን በክርስቶስ ክርስቲያን ለተባሉ ሰዎች ብቻ የሚሰጡ በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ፀጋን ረቂቅ ሀብትን የሚሰጡ ናቸው፡፡ እነሱም ምሥጢረ ጥምቀት፣ ምሥጢረ ሜሮን፣ ምሥጢረ ቁርባን፣ ምሥጢረ ንስሐ፣ ምሥጢረ ክህነት፣ ምሥጢረ ተክሊል እና ምሥጢረ ቀንዲል ናቸው፡፡” በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔርን ባህሪ ለመተንተን ሲጣጣሩ ይታያል፡፡ ለምሳሌ ሊቀ ካህናት ኃይለሥላሴ ዓለማየሁ <ትምህርተ ሃይማኖት> ሲሉ በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ድህረ ገጽ ላይ ባሰፈሩት ጽሁፍ እንዲህ ይላሉ፦ “በከሃሊነቱ ዓለምን የፈጠረ እግዚአብሔር የማይታይ፣ የማይመረመርና የማይዳሰስ፣ እንደሆነ ቢታወቅም፣ ባሕርዩ ከሚገለጽባቸው አያሌ መገለጫዎች ጥቂቶቹን በምሳሌነት መመልከት ይቻላል፡፡ እነሱም፦ፈጣሪ፣ ከሃሊ፣ ምሉእ፣ ዘለዓለማዊ፣ ቅዱስ፣ ፍጹም፣ ማእምር /አዋቂ/ እና ጥበበኛ የሚሉ ናቸው፡፡” ይላሉ፡፡

Created in Master PDF Editor

ብዙ አማኞች የመከራከርያ ሃሳቦችን ላለማቅረብ ማስረጃ አያስፈልገንም እምነት ብቻ በቂ ነው፤ እምነት የሌለው እውነትንአያውቅም፤ እግዚአብሔር እርሱ በገለፀልን መጠን እንጅ በምርመር ማወቅ አይቻልም ይላሉ። እግዚአብሔር በሰው አዕምሮ ሊገለፅ የማይችል መንፈስ በመሆኑ ህልውናውን እና ባህሪውን ለማወቅ የሚደረገው ምርምር ከንቱ ልፋት ነው በማለት የሽህ አመታት የፈላስፎችን እና የሳይንቲስቶችን ጥረት እና የደረሱባቸውን ድምዳሜዎች ከምንም እንዳይቆጠሩ እና ከሰፊው ህዝብ ፊት እንዳይቀርቡ ተደርገዋል። ይልቁም የማይገለጥ የተከደነ፥ የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለም የሚለውን የወንጌል ቃል ሽረውታል። (ማቴ. 10÷26) እውነትን ፈላጊ መናፍቅ ግን አልበርት አንስታየን እንዳለው ሁሉንም ይጠይቃል (Question everything)። ሰነፍ በልቡ እግዚአብሔር የለም ይላል ከማለት ሰነፍ በልቡ እግዚአብሔር አለ ይላል ቢባል እንዴት መልካም ነበር።

ስለእግዚአብሔር ማወቅ ካልተቻለ እንዴት በእየ ቤተ እምነቱ ስለ ፈጣሪ ባህሪ እና ተዕዛዛት ሊሰበክ ይችላል ብለን ስንጠይቅ ባህሪው የገለፀላቸውን አስተማሩን ይሉናል። ሲቀጥለም እግዚአብሔር መቸ፣ የት፣ ለማን፣ እንዴት እና ለምን ተገለጠ የሚሉትን ጥያቄዎች እየተነሱ መጨረሻ የሌለው ሙግት ውስጥ እንገባለን። ይህንም የሚፈቅዱም ዘመናዊ አማኞች ከሆኑ እንጅ የልምድ አማኞችስ የእምነታቸውን ልዕልና የሚያሳዩት ቡጢ በመሰንዘር ነው።*“ዓለማውያን (ምዕራብያውያን) በምክንያት ሲሟገቱ ኢትዮጵያውያን ግን ገና ‹‹የዘራፍ›› ዘመን ላይ ነን። ይህንን ለመናገር ያደፋፈረኝ በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ትችት መሰንዘር በሃገራችን ቡጢ የሚያስቀምስ ሃጢያት መሆኑን ስለማውቅ ነው።”* ያለው ልክ ነው። (የበፍቄ ዓለም፣ https://befeqe.wordpress.com/)

በአጠቃላይ ሳንመረምር የምንቀበለው ማንኛውም አስተሳሰብ ውርስ እንጅ እውነት ሊሆን አይችልም። አስተሳሰብን መውረስ መጥፎ ባይሆንም አለማሻሻል ግን ሞኝነት ነው። ለምሳሌ ከአዳም የወረስነውን ቅጠል የመልበስ ጥበብ ወደ ጅንስ ካልቀየርነው ሙተናል። ከሽ ዘመናት በፊት የተነገሩንን የዚያን ዘመን እውነት መሰል አስተሳሰቦች አለመቀየር ለስልጣኔአችን ትልቅ ማነቆ ነው። ያለፈውን ዘምን እናዳለ መጣልም መቀበልም አግባብነት የለውም። የተሻለ የሚሆነው ንቁ በሆነ ህሊና አለምን በመቃኘት ወደ እውነት ጥግ መገስገስ ነው። ምንም እንኳ የእግዚአብሔርን ህልውና በምርምር ማወቅ ባይቻልም አለ ብሎ መደምደም ግን የባሰ መሀይምነት ነው ካልሆነም የስንፍናዎች ሁሉ ስንፍና ነው።

13. አምላክ ላለመኖሩ ማስረጃ የለም

ኤቲስቶች ደጋግምው እንደሚሉት ማረጋገጫ የማቅረብ ሸክም (The burden of proof) ያለበት አማኝ ነው። ቢሆንም እግዚአብሔር የለም የሚሉትም ከባድ ጥያቄ ከፊታቸው አለ። አለመኖሩን እንዴን እናውቃለን? My response is twofold ይላል Michael Shermer,“First, the burden of proof is on the believer to prove God’s existence, not on the nonbeliever to disprove God’s existence. I can just as easily argue that I cannot prove that there is no Isis, Zeus, Apollo, Brahma, Ganesha, Mithras, Allah, Yahweh, or even the Flying Spaghetti Monster. Second, there is evidence that God and religion are human and social constructions based on research from psychology, anthropology, history, comparative mythology, and sociology.”በእርግጥ በእየ ቤተ እምነቶቹ የሚሰበኩትን አማልዕክት አለመኖራቸውን ለማስረዳት የእምነቶቹን መሰረት መገምገም በቂ ነው። ከባድ የሚሆነው በምዕራቡ አለም ‹‹አንድ ፈጣሪ›› አለ ማንም ምንም ሊያወራለት የማይችል በረባ ባረባው ጣልቃ የማይገባ የተደበቀ ጌታ የሚሉት ነው። ይህ ፈጣሪ ነብያትን አይልክም፣ ቅዱስ መፅሀፋ አያፅፍም እናም ስለማናኛውም የሰው ልጅ ጥያቄ መልስ አይሰጥም። ማንነቱን ያልገለፀን አምላክ አለመኖሩን ለማስረዳት የሚችል ማንም ሰው የለም። ይህ ማለት ግን የሆነ ፈጣሪ ይኖር ይሆናል የሚል ምናባዊ ፍልስፍና እንጅ ፈጣሪ ስለመኖሩ ማስረጃ አለ ማለት አይደለም።

የመጽሃፍቱ አማልዕክት ስላለመኖራቸው በርካት ያሉ ማስረጃዎችን እና ትንታኔዎችን ማቅረብ ይችላል። በተለይም መልዕክተኞች፣ ቅዱስት መፅሀፍት፣ አዋልድ መጽሀፍት፣ ስብከቶች፣ ታአምራት እና የአምልዕኮ ስርዓቶች ወሳኝ የመረጃ ምንጮች ናቸው።

እኔ ላለማመን ሁለት አይነት ማስረጃዎች አሉኝ። አንደኛ ለማመን የሚያበቃ ማስረጃ የለም። ሁለተኛ ለአለማመን የሚያበቁ በርካታ መረጃዎች አሉኝ። በእርግጥ እግዚአብሔር አለመኖሩን ሳይንስና ፍልስፍና በግልፅ ሊነግሩን አይችሉም በተለይ በፍልስፍና የእግዚአብሔር የመኖር እድል ሃምሳ ሃምሳ ነው። ሳይንስ ግን እስካሁን የሚያገኛቸው ግኝቶች ሁሉ ከመኖሩ ይልቅ አለመኖሩን የሚያሳብቁ ናቸው። እኔ እያወራሁት ያለሁት ስለ አንስታየኑ ሰዋዊ ያልሆነ ፈጣሪ አይደለም። ላለመኖሩ ማስረጃ የማቅረብ የምችለው ስለ ሰዋዊ አምላክ ነው። በአንሳታየኑ ፈጣሪና በመፅሀፍቱ ፈጣሪ መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ። የአንስታየኑ God of physical constant ሲሆን ሰዋዊዩ ግን God of tribe (የጎሳ አምላክ) ነው።

Created in Master PDF Editor

የጎሳ አማልዕክት ጣልቃ የሚገቡና ማንነታቸውን ያሳወቁ በመሆናቸው ነን ካሉት ተነስተን አለመሆናቸውን ለማስረዳት አንቸገርም። ያፃፉትን መፅሀፍ፣ የላኩትን መልዕክተኛ፣ የገቡትን ቃል ኪዳን፣ ያሳለፉትን ታሪካዊ ኩነት በእውነት እና በቅንነት ሚዛን ላይ መዝነን ወደ ቤተ መዛግብትና ሙዝየሞች ማውረድ እንችላለን።

አማልዕክት ምንም ያህል መስዋዕት ይሰዋለቸው፣ ምንም ያህል አማኝ ይኑራቸው፣ ምንም ያህል ረዥም ታሪክ ይኑራቸው በእውነት ሚዛን ሳይመዘኑ ማሳለፍ ተገቢ አይደለም። ደስ የሚለው ብዙዎቹ ተፈትሸው ባለማለፋቸውና የአምላክነት ቁም ነገር ስላልታየባቸው ሙዝየም ውስጥ በሽልፍ ተደርድረው እየተጎበኙ ነው። በዚህ ዘመን የሚመለኩትም ወደ ሽልፍ ላለመውረዳቸው ዋስትና የላቸውም። ጊዜ ያልቀየረው ነገር የለም። ታላላቆቹ የግሪክ፣ የግብፅ፣ የሮም፣ የአዜቲክስ እና የሌሎች ጥንታዊ ስልጣኔ አማልዕክት በሙዝየም ይቀመጣሉ ብሎ ያሰበ አማኝ ነበርን? በአማልዕክቱ እውነተኛነት እርግጠኛ ስለነበሩ ልጆቻቸውን ሳይቀር መስዋእት ያደርጉ ነበር። ጽሃፍት በድጋፍና በተቃውሞ ብዙ ቢሉም ለእኔ በገባኝ አግባብ ግን አማልክ ለመኖሩ <አሳመኝ> ምክንያት የለም ብቻ ሳይሆን ላለመኖሩ በቂ ማስረጃ አለ።

14. እግዚአብሔር ከለለ ሁሉም ነገር ከየት መጣ?

የሁለንታ አመጣጥ ከዋነኞቹ ያልተመለሱ ጥያቄዎች መካከል አንዱ ነው። በዚህ ጉዳይ የሰው ልጅ ለብዙ ሺህ ዓመታት ሲያወዛግብ ቆይቷል፣ አሁንም እንደተወዛገበ ነው፣ ወደ ፊትም ይቀጥላል። ይህ ሳይንስ እና ፍልስፍና በአሳማኝ ማስረጃ ሊመልሱት ያልቻሉት ታላቅ ክፍተት ነው። የዛሬዎቹ እምነቶች የሚመኩበት ክፍተት ነው። አለማወቅን መሸከም የከበደው የሰው ልጅ ይህን ክፍተት ለሞሙላትሃይማኖቶችን ይጠይቃል። እነሱም የተለያየ መልስ በመስጠት ይበልጥ ያወዛግቡታል።

ቅዱስ ጳውሎስ ለዕባራዊያን እንደተናገረው ዓለማት በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠሩ የሚታየውም ከማይታው እንደሆነ ክርስቲናኖች ያስተምራሉ። ማብራርያው ቀላል ነው እግዚአብሔር አለሙን የፈጠረውም ከምንም ነው። እኛ ሰዎች አንድን ነገር ለመስራት ጥሬ ዕቃ የግድ ያስፈልገናል ከምንም ተነስተን ምንም ነገር መስራት አንችልም በዓለም ላይ የምናያቸው የሰው ልጅ ሥራዎች ሁሉ የተለያዩ ንጥረ ነገሮችን በማሰባሰብ የተሠሩ ናቸው። ሰው ምን ቢያውቅ መሥራት የሚችለው ካለው ነገር ላይ ተጠቅሞ ነው። እግዚአብሔር ግን ዓለማትን የፈጠራቸው ያለምንም ነገር ከምንም ነው። ይህ የአማኞች አመለካከት ትክክል ይመስላል፣ ችግሩ ሁለንታ ሲጀመር አልተፈጠረም። የሁለንታ ዕድሜ አማኞች አለ ከሚሉት ፈጣሪ ጋር እድሜው እኩል ነው፣ ማለትም ዘመን አይቆጠርለትም።

Created in Master PDF Editor

ይህ አስተሳሰብ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ተቀባይነት ካገኘው ቢግ ባንግ ቲወሪ ጋር አይጋጭም፡፡ ቢግ ባንግ የሚለው ሁለንታ የተፈጠረው የዛሬ 14.6ቢሊዮን አመት ከምንም ቁስ ከሌለው ሀይል ነው፡፡ ከቢግ ባንግ በፊት ምን ነበር? ቢግ ባንግ ያቀጣጠለው ሀይል (energy) ከየት መጣ? ብሎ መጠየቁ ተገቢ ነው፡፡ መልሱ የፍልስፍና መልስ ነው፣ ከቢግ ባንግ በፊት የነበረውና ቢግ ባንግን ያቀጣጠለው ሀይል የመጣው ከዚያ በፊት ከነበረው ሁለንታ ነው፡፡ የአንዱ ሁለንታ መጨረሻ የሌላኛው ሁለንታ መጀመርያ ነው፡፡ እናም የሁለንታ እድሜ 14.6 ቢሊዮን አመት ገዳማ ነው ሲባል የሁሉንም ተረኛ ሁለንታዎች ድምር እድሜ ሳይሆን የአሁኑን ሁለንታ መሆኑ ነው፡፡

የzen of zero ጽሃፊ ደግሞ እንዲህ ይላል፦ *Before the beginning of our universe, total nothingness existed everywhere. This total nothingness ("the Dao") had two options: either just sit there, everywhere, for evermore, or start fluctuating. After a long, long time of doing nothing, total nothingness started to fluctuate, similar to the way that quantum mechanical systems are now known to behave. For a long, long, time, and in each and every fluctuation, everything was perfectly symmetrical: a positive fluctuation in anything was exactly balanced by a negative fluctuation of exactly the same thing. As a consequence of the perfect symmetry of these fluctuations, still and in total, nothing existed.Then it happened. Of the innumerable fluctuations, one broke its symmetry. No one knows how it happened. Perhaps what we now call a positive fluctuation in energy precipitated as a string or as a particle of energy (i.e., it became a mass of "solidified, positive energy") and was then unable to recombine with its negative counterpart. --- But whatever the details, the dam broke, positive energy flooded out, leading to what's called "inflation" (or the Big Bang) and eventually to our universe and us."*

በነገራችን ላይ ሁሉም ነገር ፈጣሪ ያስፈልገዋል ካላችሁ ያ ፈጣሪ ከሁሉም ቀድሞ መኖር አለበት፡፡ ግን እሱን ማን ፈጠረው? መልሳችሁን መገመት ቀላል ነው እሱ በማንም አልተፈጠረም፡፡ እግዚአብሔር ፈጣሪ ካላስፈለገው እና ለዘለአለም የሚኖርከሆነ ሁለንታም ለዘለአለም ይኖራል፡፡ ሰለዚህ ሁለንታ እና እግዚአብሔር እኩል ዘላለምአዊ እድሜ ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡ ማንም መንፈስ ከጊዜ እና ከቦታ ውጭ ሊኖረ አይችልም፡፡ በቀላሉ መንፈሱ የኖረበት ጊዜ እና የሰፈፈበት ቦታ የሁለንታ አካል ነው፡፡እድሜውን ለያይቶ ማስላት ያስፈለገው በተካታታይ ሁለንታዎች መካከል የቁስ አካል ውርርስ እንደለለ በመገመቱ ነው፡፡ አሮጌው ሁለንታ ከቢሊዮን አመታት መለጠጥ በኋላ ይኮማተራል፣ ወደ ሀይልነት ወደ ወናነት ይቀየራል፡፡ ያ ምንም ቁስ የሌለበት ሀይል ወደ አዲሱ ህዋነት ያድጋል፡፡ ዋለልኝ እምሮ የሳይንሱን አለም ትንታኔ እንዲህ ዘግቦታል፦ *"እየሰፋ ያለው ህዋ ይጥበብ እንበል፤ ወይም በህዋ*

Created in Master PDF Editor

ውስጥ ያሉት ግዙፍ አካላት ወደ ፊት መለጠጡን (መስፋቱን) አቁመው ወደ ኋላ እየጠበቡ ይመለሱ እንበል። ይህ ማለት ጋላክሲዎች እየተራራቁ መሄዳቸውን ቀርቶ እየተቀራረቡ፣ በጣም እየተቀራረቡ፣ እጅግ በጣም እየተቀራረቡ ይምጡ እንበል። በዚህ ሁኔታ ህዋ ብንረዳው በጋላክሲዎች መካከል ያለው ክፍት ቦታ ሊጠፋና ህዋ በሙሉ አንድ ግዙፍ አካል ይሆናል። የዚህ ግዙፍ አካል ወዳስገኙት አተሞችና ፓርቲክሎች ስንመነዝረው ደግሞ በጣም ትንሽ የሆነ ቁስ አካል እናገኛለን። ቁስ አካሉን ደግሞ አርሱን ወደ አስገኙት ቅንጣቶች ስንመነዝረው አሁንም መጠኑን ከቁስ አካሉ እጅግ ያነሰ ቁሳዊ ተፈጥሮ ወደ ሌለውና ሐይል ብቻ ወደ ሆነው ቁስ አልባ ወና ነገር ላይ እንደርሳለን። ይህ ማለት ቢሊዮን አመታትን ወደ ኋላ ሄደን መጨረሻ ላይ የምናገኘው ነገር ምንም አካል፣ ይዘትና መጠን የሌለው፣ ቦታ የማይዝ እጅግ በጣም --- በጣም --- በጣም ትንሽ የሆነ ነገር ግን ከፍተኛ ሙቀት፣ እፍግታ እና ሐይል ያለው ወና ነገር ይገኛል። በዚህ መንገድ ከተረዳነው ከምንም ነገር በላይ ግዙፍ የሆነው ህዋ በሂደት የተገኘው ትንሽ የመጨረሻ ትንሽ (ባዶ ከሆነ) ነገር ግን ከፍተኛ እፍግታ (እምቅታ)፣ ሙቀትና ኃይል ከሆነ ነገር ነው ማለት ነው።” (የህይወት ትርጉም፣ 2002 ዓ.ም፣ 63)

እንቅጩን እግዚአብሄር ከለለ አጽናፈ ሰማይ እንዴት ተፈጠረ ለሚለው ጥያቄ በቂ መልስ አለ። ፍልስፍናዊና ሳይንሳዊ ቲወሪዎችን መተንተን። እስከአሁን አላወኩትም ማለትም ይቻላል አለማወቅ ሀጢዓት አይደለም ይባል የለ እንዴ። ይህ ማለት ግን መላምልት ማስቀመጥ አይቻልም ማለት አይደልም። ለምሳሌ እኔ ሁለንታ የተፈጠረ ሳይሆን ለዘለአለም እየተለዋወጠ የኖረ እና የሚኖር ነው ብየ አስባለሁ።በተጨማሪም እኛ ካለንበት ሁለንታ ውጭ እጅግ በጣም ብዙ ሁለንታዎች ሊኖሩ ይችላሉ ብየ እገምታለሁ። እያመንኩ ሳይሆን እየገመትኩ ነው። (ይህን ጉዳይ Evolution from the big bang to the big crunch በሚለው መጽሃፌ ለመተንተን እሞክራለሁ)። ልጅ እያለሁ የሰማዩን አድማስ በማየት ሰማይ ከመሬት ጋር የገጠመ ይመስለኝ ነበር። ከዚህም የተነሳ ሰማይና ምድር የሚገናኙበትን ለማየት ተራራ እወጣ ነበር። አሁን ከዚያ አባዜ ተላቅቄ ሁለንታ መነሻ መድረሻ፣ መውጭ መግቢያ፣ መጀመርያ መጨረሻ የለውም የሚል አስተሳሰብ አራምዳለሁ።ምክንያታዊ ፍልስፍና እና ሳይንሳዊ ድጋፍምአለኝ።

ማን ፈጠርን ወይም ሁሉም ነገር ከየት መጣና መጨረሻው ምን ይሆን የሚሉ ጥያቄዎች የዘመናት ጥያቄዎች ናቸው። የክርስቲያን ሳይንስና ፍልስፍና ሙህራን ተፈጥሮአዊ ሳይንስና ፍልስፍናን እስከ ጥግ ድረስ መሞገታቸው የቆየና የተለመደ ነው። ፍጥረትን ብቻ በማየት የፈጣሪን መኖር ማወቅ ይችላል የሚለው የቆየ አባባላቸው ነው። ያለ አምላክ ጣልቃገብነት እንዴት ቢሊዮን ፕላኔቶች ትሪሊዮን ከዋከብት በቢሊዮን የብርሀን አመት ለዘርጋ ይችላል? ህይወትስ እንዴት ያለ ፈጣሪ

Created in Master PDF Editor

በራሱ ሀይል ይፈጥራል? ኧረ እንዴትስ ሆኖ ነው ህይወት ከሌለው ግዑዝ ወደ ትል፣ ከትል ወደ አሳ፣ ከአሳ ወደ ተሳቢና በራሪ የሚቀየረው? እንዴት ነው ከዝንጀሮ መሰል ሰው የሚኮነው?

በእውነት ተፈጥሮን ከትንሹ አቶም እስከ ሁለንታ ድረስ ስንቃኘው የእግዚአብሔር ድንቅ ስራ ልናደንቅ እንችላለን። ግን ይህን ያደረግነው ፈጣሪ መሆኑን እንዴት እንወቅ? ሁሉንም እንግዚአብሔር እንደወደደና እንደፈቀደ አደረገ ማለት ቀላል፣ ምቹና እረፍት ነው። ግን ባይሆንስ ብሎ መመርመር መባረክ ነው። ምክንያቱም ይህን ሁሉ ያደረገ አማኞች የማይቀበሉት የአማልዕክት አምላክ አለ። ስሙ እውረ አምላክ ይባላል። ዘመኑ አይቆጠርም አልፍና ኦሜጋ ነው። ይህ ዘመን የማይቆጠርለት እውር አምላክ የዛሬ 15 ቢሊየን አመት ገዳማ ታላቁን ፍንዳታ አፈነዳው። ምኑን አፈነዳው? ያፈነዳው ድንቅ የሆነ ነገርን ነው ምንምን (nothing)ን።ማስረጃህ ምንድን ነው?

የቢግ ባንግ ፅንሰ ሃሳብ እውነት ሊሆን እንደሚችልና ሁለንተም እውን የሆነውን የዛሬ 13.8 ቢሊዮን አመት እንደሆነ የሚያስረዱ 3 ዋና ዋና መረጃዎችን ሳይንቲስቶች አግኝተዋል። አንደኛው የህዋ አካላት እየተራራቁ መሄድ መጀመሪያ ተቀራርበው እንደነበሩ ፍንጭ ይሰጣል። ስለዚህ ሁለንታ እየሰፋ የሚሄድ ከሆነ መነሻ አለው ማለት ነው። ሁለተኛው ደግሞ በፍንዳታው የተፈጠሩት ሀይድሮጅን እና ሂሊየም የተባሉት ቀላሎቹ ንጥረ ነገሮች መሆናቸው። በፍንዳታው ወቅት የነበሩት ብቸኛ ንጥረ ነገሮች ሀይድሮጅን እና ሂሊየም እንደሆኑ እና ምክንያቱም በዚህ ታላቅ የኒውክለር ሪያክሽን (Nuclear Reaction) ወቅት ከሀይድሮጅን እና ከሂሊየም ወጭ ከባድ የሚባሉት ሊፈጠሩ እንደማይችሉ በመረጋገጡ። ሶስተኛው እና ዋናው ደግሞ CMBR የሚባለው ነው። CMBR (Cosmic Micro Wave Background Radiation) ማለት ሁለንታ በተፈጠረበት ቅፅበት የነበረው የብርሃን ቅሬት ነው። ይህ የብርሃን ቅሬታ ታላቁ ፍንዳታ መካሄዱን ብቻ ሳይሆን እድሜውንም ለማወቅ አስችሏል።

ይህ አዲስ ፍልስፍና አይደለም ከጥንታዊ የአለም ስልጣኔዎች ጀምሮ አባቶች ለልጆቻቸው ሲነግሩት የኖሩት የትረታቸው አካል ነው አሁን ግን ሳይንስ ሆነ። ይህ ለብዙዎች ያስቃል እንዴት ምንምነት ወደ ሆነ ነገር ይቀየራል። (How nothing becomes something? Ok! No problem) ምንጩ ሀይል ነው Energy። ሀይል ወደ ቁስ ሲቀየር ቢግ ባንግ ሆነ። ጥያቄውና ሳቁ ሊቀጥል ይችላል። ሀይሉ ከየት መጣ? ቀላል ጥያቄ ነው ከሁለንታ በፊት ከነበረው ሁለንታ፣ የመጀመሪያው ሁለንተናስ ከየት መጣ ከሱ በፊት ከነበረ ሌላ ሁለንታ። እሽ እሱስ ይሁን ህይወት እንዴት ጀመረ? ህይወት ሁለንታ ውስጥ ካለው ጥበብ አንፃር የሚገርም መዋቅር

Created in Master PDF Editor

የለውም። በህይወት ውስጥ ያለው ሁለንታ የተገነባበት ውህድ ነው። ሁለንታ በፍንዳታ ከተፈጠረ ህይወትም እንዲሁ ፈነዳ። ከSingle cell ተነስቶ ትልቅ ቅንጭላት ያለው ሰው እስከ መሆን ደርሰ። ለእውሩአምለክ ለዝግመተ ለውጥ ምን ይሳነዋል።

ይህ ፍስልፍና ድንጋይ ላይ የተፃፈ ወይም ብራና ላይ የተከተበ ከአማልዕከት የወረዳ አይደለም። ሰዎች በድካማቸው ጥረው ግረው ያገኙት ነው። ስለዚህ እያደገ እየተሻሻለ የሚሄድ ከሁሉም የተሻለ እይታ ነው። አሁን ሁለት አማራጮች አሉን የሚመረመሪው Evolution did it እና የማያመረመረው God did it ሁለቱም ጤናማ አማራጮች ናቸው። ሰው የገባውን ሊመርጥ ይችላል እውነቱ ግን አንድ ነው። በነገራችን ላይ Evoluation did it የሚለው ይመርመረል እንጅ ተመርምሮ አላለቀም። ገና ጥቂት መቶ አመታት ነው። በጥቂት አመታት የመለሳቸውን የጥያቄዎች ብዛት ስናስብ ግን በቀሪዎች ጥቂት መቶ አመታት ምን ያህል ሊሰራ እንደሚችል ማሰብ ይደነቃል። የማይመለሱ ጥያቄዎች እንኳ ቢኖሩ God did it ለማለት ምንም ምክንያት የለም። ያለመረጃ Evolution did it የሚለውን መቃወም ከተቻለ ያለ በቂ ማስረጃ God did it የሚለውን ውድቅ ማድረግ ይቻላልና። Ignorance for something can’t be the proof Gods Existence ሲባል ሰምታችኋል? እናማ ሁሉም ነገር የሚታየውም የማይታየውም የመጣው ከምንም ነው። አይደለም እንዴ?

15. **እግዚአብሔር ረድቶኛል፣ ፈውሶኛል፣ አድኖኛል፣ ጠብቆኛል፣ ጸሎቴን ሰምቶኛል ወ.ዘ.ተ**

<<የሰማዩን መንግስት እርስቱን ለሰጠን

ከጨለማ አውጥቶ ብርሃንን ላሳየን

ለዚህ ድንቅ ውለታው ምስጋና ያንሰዋል

በእርሱ ደስ ይበለን ክብር ይገባዋል . . .

ከአለት ላይ የፈለቀ ውሃ ጠጥተናል

ሰማያዊ መና አምላክ መግቦናል

በቃዴስ በረሃ ምንም በሌለበት

በኤርትራ ባህር ወጀብ በበዛጀት

ለእርሱ መንገድ አለው ከቶ ምን ተስኖት

Created in Master PDF Editor

ልባችሁ አይፍራ በፍጹም እመኑት . . .

(ምንጭ፦ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን ከሚል መዝሙር የተቀነጨበ)

"ኢየሱስ በብርቱ የሚጠብቀን ስለሆነ፣ ከኃጢአት ጋር በምናደርገው ጦርነት ብርቱ መተማመኛ አለን። ፈተናን ለመቋቋም፣ በኃጢአት ምክንያት ከሚመጣብንም መዘዝ ለማምለጥ፣ በምልጃው፣ በጠበቃነቱና በይቅርታው ከተደገፍን አንዳችም የሚጎዳን ነገር የለም። ከኃጢአት ጋር በምናደርገው ጦርነት የሚመራን ታላቁና ብርቱ ተዋጊ የሆነው ንጉሥ ኢየሱስ ነው። ምንም እንኳን እኛ በአግባቡ ባንዋጋም እርሱ አይተወንምና አንሸነፍም። እርሱ ዘወትር ይከላከልልናል፣ ይጠብቀናልም፣ ይቅር ይለናል ያነፃናልም፣ ይከራከርልናል ከፍርድም ነፃ ያደርገናል። በስተመጨረሻውም፣ ወደ እርሱ የማይሻር ዘላለማዊ መንግሥት ያመጣናል።" (በኢየሱስ እናምናለን፣ትምህርት አምስት፣ገጽ 57)

"የሰው ልጅ በዓለም ላይ ሲኖር ያለ እምነት ምንም ሊተገብር አይችልም። ዕምነት ለሰው ልጆች ማኅበራዊ ሕይወትና የአእምሮ እረፍት መሠረት ነው። ሃይማኖት ደግሞ ከማመንም በላይ ነው፤ መታመንን ይፈልጋል።" (ካሳሁን አለሙ፣ ተጠየቅ ድህረ ግፅ)

ነገሮች ሲያወሯቸው ቀላል ናቸው። የመዳን ነገር ሲነሳ ቴሌቫንጋሊስቶችን የሚቀድማቸው የለም። አዳራሽ ተከራይተው በቂ ካልሆነም ሰፊ ማዳ ተፈልጎ መዳን በነፃ ይቸበቸባል። ከዛሬ ጀምሮ ድነሻል፣ ከዛሬ ጀምሮ ከበሽታዎች ሁሉ ተፈውሰሃል፣ ከዛሬ ጀምሮ ነፃ መጥታችኋል፣ ከዛሬ ጀምሮ ይህን የፈውስ ፕሮግራም በቴሌቪዥን የምትከታተሉ የጌታን ስም እጠራለሁ በእያላችሁበት ከታሰራችሁበት የተፈታችሁ ሁኑ ወዘተ ይላሉ ህዝቡ ያጨበጭባል፣ ይጨፍራል። ጌታን በአካል አይቶታልና ደስ ይለዋል። እነሱም ይላሉ ጌታ ሲናገር ነው ስሙት ከዚያ ጌታ ይናገራል አቤት የውሸት ብዛት ሰው ውሸትን ከፖለቲከኞች ጋር ያያይዘዋል ውሸት ግን መያያዝ ያለበት ከቴሌቫንጋሊስቶች ጋር ነበር። የውሸታቸው ልክ የለውም። እኔ ውሸታም አይደለሁም የሚል እንፈታተን ከነብይ እዩ ጩፋ ጀምሮ እስከ የኛ ሰፈር ፈዋሾች ድረስ። ግን የሚገርመኝ ከጀርባ ምን እያተሰራ ነው። ብዙዎቹ ዳንን በለው በነጋታው ሀኪም ቤት ለሀኪም ቤት ይመላለሳሉ። አንዳንዶቹም በቅንነት ምስክርነታቸውን ያስተባብላሉ። ፈዋሾች ሆይየእኔን ጥያቄ ለመመለስ እንዳታስቡ ጥያቄው ከበድ ነው ለማጭበርበር አይመችም። ወይም በቀጥታየምፈልገው በአንድ አከባቢ የሚኖሩ አካል ጉዳተኞች ወደ ፈዋሾች እኔ ባለሁበት ይሄዱና እጅ የሌላቸው እጅ፣ እግር የሌላቸው እግር፣ አይን የሌላቸው አይን ተሸልመው ሲመለሱ ማየት ነው። ይህን የሚያደርግ ካለ አቅሜ ነውና 50,000 ብር አስይዛለሁ። እንወራረድ!! ሀምሳ ሰው ድኖልኝ 50,000 ብር ብሸነፍ ደስታውን እችለዋለሁን? የሚሰሙ ጸሎቶች እንዳሉ አውቃለሁ አካል

Created in Master PDF Editor

ጉዳተኛን ማዳን ግን አይመስለኝም። ለምን አንዱ ተሳክቶ አንዱ አይሳካም? እግዚአብሔር በመኪና አዳጋ የደረሰባቸውን አካል ጉዳተኞችን ለምን አያድንም? ምን አልባት አማኞች መልስ፦

- አካል ጉዳተኛን ማደን የእግዚአብሔር ፍቃድ ባይሆንስ ይሉኝ ይሆናል። የለም እግዚአብሔር በወንጌሉ እንዲህ አይነት አድሎ አልሰበከም። HIV የያዛቸው ይድናሉ አካል ጉዳተኞች ግን አይድኑም አላለም።
- እግዚአብሔር የሁሉንም ሁሉንም ፀሎት ይመልሳል ግን መልሱ አይሆንም ሊሆን ይችላል ሊሉኝ ይችላሉ። አይቻልም የሚባል መልስ ቢኖር ኑሮ የፈለጋችሁትን ጠይቁ ይሠጣችኋል ባልተባለ ነበር።
- እግዚአብሔር ይህን ሰው የማያድነው እኛ ለማስተማር ነው ይሉኝ ይሆናል። አዝናለሁ እግዚአብሔር ስለትራፊክ የሚያስተምረን እንዲህ ከሆነ ከትሪፊክ ፖሊሶች በምን ተለየ። የትራፊክ ፖሊሶች ጥፋት የሚያጠፉ ሹፌሮችን ለምን እንዲሚቀጡ ቢጠይቋቸው ለማስተማር ነው መልሳቸው። እንደሰወኛ ልክ ነው። እግዚአብሔር ግን ሁሉን አዋቂ ስለሆነ ሌላ ማስተማርያ ዘዴ ማምጣት ይችል ነበር። ግን?
- የሰው ልጅ ሙሉ ነፃነት ነው። ይህ ሰው በመኪና የተገጨው የትራፊክ ደንብን መጣስ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ እግዚአብሔር የሰጠውን እግር በአግባቡ ስላልተጠቀመበት ተቀማ። እግዚአብሔር የሚያድነው ሳያውቅ በደረሰብን በሽታ ነው ይሉኝ ይሆን።እኔ እምለው ከመወለዳቸው በፊት አካል ጉዳተኛ ሆነው የሚወለዱትስ የራሳቸው ነፃነት ነው ወይስ የወላጆቻቸው ኃጢአት?
- እግዚአብሔር አካል ጉዳተኞችን ይረዳል። ሳይንቲስቶችን እና ኢንጅነሮችን አነሳስቶ አርቲፊሻል እግር አድርጓል ይሉኝ ይሆናል። እዚህ ጋ በሳይንቲስቶቹ ድካም ሳይሆን በእግዚአብሔር ፍቃድ አርቲፊሻል እግር ተመረተ እንበል። ይሁን ልስማማ ግን ለምሳሌ Small box የተባለው በሽታ ሚሊዮኖችን ለብዙ ዘመናት ከገደለ በኋላ ሳይንቲስቶቹ በ20ኛው ክ/ዘመን ክትባቱነ አገኙት። እግዚአብሔር ለምን እስከ 20 ክ/ዘመን ክትባቱን አዘገየው።
- “እግዚአብሔር አትፈታተን ተበሏል” ይሉኝ ይሆናል ካንሰር ከታመመ እና ለአካል ጉዳተኛ ደህንነት መለመን አንዱ ከአንዱ የተለያ አይደለም። ጌታ ሁሉን ቻይ ስለሆነ አይደለም እንዴ?
- እግዚአብሔር ለሁሉም መልስ አለው ይታገስ። ስንት ዘመን ይታገስ። ምን አልባት ከሞተ በኋላ።

Created in Master PDF Editor

ሀ አማኝ እና ለ ኢ-አማኝ ሁነው ስለ ፀሎት ቢከራከሩ

ለ. አምላክ ማንኛውንም የአማኞች ፀሎት ሊመልስ ቃል ገብቷል። ለምሳሌ ለችግራችን የሚሆን ብር እንዲሰጠን መሰል ጥያቄዎችን ብንጠይቅ መልስ የምናገኝ ይመስልሃል?

ሀ. ጥያቄው አስፈላጊ ከሆነ እንደፍቃዱ ይመልሰዋል። ብር ላይዘንብልን ይችላል። ብር እንድናገኝ ግን ስራ ያመቻችልናል።

ለ. ለምሳሌ እኔ አልፀልይም ስራ አግኝቻለሁ እንዴት?

ሀ. ባታምንበትም ልጁ ነህ፡- ስለሚወድህ ነው።

ለ. ይሁን እስኪ አንተ እግዚአብሔር የምትወድ እንደሆንክ አውቃለሁ። እኔን ለማሳመን ሲባል አንድ ጥያቄ ጠይቀው።

ሀ. እሺ

ለ. ይህ ከፊታችን ያለው ተራራ እንዲንቀሳቀስ እዘዛው ብለህ ለምን!!

ሀ. እግዚአብሔርን አትፈታተን ተብሏል።

ለ. አየህ የብዙ አማኞች የመጨረሻ መልስ ይህ ነው። ታዲያ መፅሐፍ ውስጥ ያለ መሠረታዊ ጥያቄ ነው የጠየኩት እውነት እልሀለሁ ተራሮች በግልጽ መንቀሳቀስ ካቆሙ ሚሊዮን አመታት አለፈ።

ሀ. ተራራ ሲንቀሳቀስ ነበር ልትለኝ ነው።

ለ. አዎ! የሰው ልጅ በዝግመታዊ ለውጥ ከዚ ከመድረሱ በፊት መሬት ሳትረጋጋ በዙ ለመግለፅ የሚከብዱ የመሬት መናወጥ ነበር። ራስ ዳሽንን አማልክት ሳይሆኑ ተፈጥሮ እንደፈጠረችው አምናለሁ።

ሀ. እኔ ደግሞ እግዚአብሔር ውብ አድርጎ ተፈጥሮን እንደፈጠራት አምናለሁ።

ለ. እሺ ወንድም! -----------

ፀሎት ከፈጣሪ ጋር የሚደረግ ንግግር ነው። ፀሎቱ ስለ አለማዊ ወይም መንፈሳዊ ጉዳይ ሊሆን ይችላል። ፀሎት ፀሎቱን ወደ ሚሰማው ፈጣሪ የሚደርሰው ከብርሃን ፍጥነት በላይ በሆነ መንገድ ነው አማኞች እንደሚሉትም ፀሎቱ እንኳ ሳይፀለይ ምን ልንፀልኝ እንደምንችል የሚያውቅ ፈጣሪ አስቀድሞ ይደርሰዋል። በእየሚድያው እግዚአብሔር ፀሎቴን ሰማኝ የሚል ምስክርነት መስጠት የተለመደ ነው። በመፅሐፍ

Created in Master PDF Editor

ቅድስም በማርቆስ ወንጌል 11፣22-24፤ በማቴውስ ወንጌል 7:7-11፣ 17:20፣ 21:21፣ 18:19 በተደጋጋሚ ስለ ፀሎት ተሰሚነት አበክሮ ተሰብኳል። በተጨማሪም ዮሐ 14:14፣ ማር 9:23፣ ሉቃስ 1:37

- ማርቆስ ወንጌል 11፣22-24 "ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። በእግዚአብሔር እመኑ። እውነት እላችኋለሁ፥ ማንም ያለው ነገር እንዲደረግለት ቢያምን በልቡ ሳይጠራጠር፥ ይህን ተራራ። ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ቢል ይሆንለታል። ስለዚህ እላችኋለሁ፥ የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ፥ ይሆንላችሁማል።"
- በማቴውስ ወንጌል 7:7-11 "ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል። የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል። ወይስ ከእናንተ፥ ልጁ እንጀራ ቢለምነው፥ ድንጋይን የሚሰጠው ከእናንተ ማን ሰው ነው? ዓሣስ ቢለምነው እባብን ይሰጠዋልን? እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠትን ካወቃችሁ፥ በሰማያት ያለው አባታችሁ ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መልካም ነገርን ይሰጣቸው?"
- በማቴውስ ወንጌል 17:20 "እውነት እላችኋለሁ፥ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፥ ይህን ተራራ። ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል፤ የሚሳናችሁም ነገር የለም።"
- በማቴውስ ወንጌል 21:21-22 "እውነት እላችኋለሁ፥ እምነት ቢኖራችሁ ባትጠራጠሩም፥ በበለሲቱ እንደ ሆነባት ብቻ አታደርጉም፤ ነገር ግን ይህን ተራራ እንኳ። ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ብትሉት ይሆናል፤ አምናችሁም በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ አላቸው።"
- በማቴውስ ወንጌል 18:19-20 "ደግሞ እላችኋለሁ፥ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።"
- ዮሐንስ 14: 12-14 "እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፥ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፤ አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ። ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።"
- ማርቆስ 9:23 "ለሚያምን ሁሉ ይቻላል።" ሉቃስ 1:37 "ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም።"

Created in Master PDF Editor

ግን

- ✓ የአካል መቆረጥ አደጋ የደረሰበት የተቆረጠ አካሉ ያለ ህክምና የተሰራለት የምታውቁት ሰው አለ?
- ✓ ከቦታ ቦታ የተንቀሳቀሰ ተራራ የምታውቁት አለ?
- ✓ ደመና ጠቅሶ ከቦታ ቦታ የሚጓጓዝ የምታውቁት ሰው አለ?
- ✓ የተፈጥሮን ህግ (Natural law) የሚጥስ የፀሎት ክንውን አይታችኋል?
- ✓ የመከሰት ዕድልን (Probability) የሚጥስ የፀሎት ውጤት አይታችኋል? ወይስ 1 ሚሊዮን ዜጎች 1 ሚሊዮን ብር የሚያስገኝ ሎተሪ ቢቆረጡና ሁሉም ይደርሳቸዋል?
- ✓ ፀሎት ስጋዊ መድሀኒትም ጭምር ከሆነ ለምንድን ነው ዜጎችና መንግስታት ቢሊዮን፣ ትርሊዮን ዶላር ለህክምና ወጭ የሚያደርጉት ተማሪዎችስ ለምን ህክምና ይማራሉ? ለምን የፀሎት አሰልጣኝ አይሆኑም?
- ✓ በፀሎት ምክንያት ሳይከሰት የቀረው የትኛው በሽታ ነው? የትኛው የተፈጥሮ አደጋ ነው? የትኛው ርሃብና መከራ ነው? የትኛውን ወንጀል ነው?

አማኞች ሆይ መጽሃፍ እንዳለው የተከለከለ ፀሎት የለም። እናማ ዝናብ እንዲዘንብም እንዳይዘንብም ፀልዩ፣ ጥፋታችሁ እንዳይታወቅባችሁ ፀልዩ፣ የጤፍ ዋጋ እንዲቀንስ ወይም እንዲጨምር ፀልዩ፣ ልጃችሁ አገልጋይ፣ ነብይ ወይም ዘማሪ እንዲሆን ፀልዩ፣ ወደ መስሪያ ቤቶች ለስራ ስትሄዱ በተሎ እንድትስተናገዱ ፀልዩ፣ ጨረታ እንድታሸንፉ ወይም ሎተሪ እንዲያደርሳችሁ ፀልዩ፣ የምትወዱትን የቴሌቪዥን ፕሮግራም እያያችሁ መብራት እንዳይጠፋ ፀልዩ፣ በሚቀጥለው ጨዋታ የምትደግፉት የእግር ኳስ ቡድን እንዲያሸንፉ ፀልዩ፣ ያመረታችሁት ምርት ተፈላጊ እንዲሆን ፀልዩ፣ መልካም ፀባይ ያለው/ያላት የትዳር አጋር እንዲገጥማችሁ ፀልዩ፣ የአሜሪካ ዲቪ (DV) እንዲደርሳችሁ ፀልዩ፣ የትራፊክ አደጋ እንዳያጋጥማችሁ፤ እንዳትታመሙ እና ሁሌ አሸናፊ እንድትሆኑ ፀልዩ፣ ለራሳችሁ፤ በቤተሰቦቻችሁ፣ ለሀገራችሁ እና ለአለም በሙሉ ስለሁሉም መልካም ነገር ፀልዩ።

እግዚአብሔር ፀሎቴን ይሰማል፣ አላህ ፀሎቴን ሰማኝ፣ ክርሽና ፀሎቴን ሰማኝ፣ ፀሀይ ፀሎቴን ሰማኝ፣ ጁፒተር ፀሎቴን ሰማኝ፣ የአባቴ ውቃቤ ፀሎቴን ሰማኝ ወ.ዘ.ተ ማለት የተለመደ ነው። መልካም ነው አማልዕክት ዛሬ ሳይሆን ከድሮ ጀምሮ ፀሎትን ይሰማሉ። የታመመ ያድናሉ፤ ዝናብ ያዘንባሉ፣ ምርት ያትረፈርፋሉ፣ እውቀት ይገልፃሉ፣ ዘመን ያፈራርቃሉ፤ ቤትን ይባርካሉ፣ ጠንካራ፣ ጤናማና ደስተኛ ያደርጋሉ፣ መልካም ባለቤትና የተባረኩ ልጆችን ይሰጣሉ፣ ከአደጋ ይሰውራሉ ብዙ ውለት ይውላሉ። የዋሀ እንዲሀ ባይምን ነው የሚገርመው። ጠርጣሬው አርዮስ ግን ከዚህ ጀርባ ያለውን መመርመር ይፈልጋል። ለምን ፀሎታችን ይሰማል? መልካም

Created in Master PDF Editor

ፀሎት የሚሰማና የማይሰማ አለ። ፀልያችሁ ከተሳካ ተሰማ ይባላል፤ ካልተሳካ ደግሞ የጌታ ፈቃድ ስላልሆነ ነው ይባላል። እዚህ ላይ ፍሬን ያዙ የማይሰማ፣ የማያሳካ ፀሎት አለ።ማርሻል ብሪን Why Won't God Heal Amputees በሚል ድህረ ገጹ ላይ እንዲህ ይላል፦"In every situation where we statistically analyze the effects of prayers, looking at both the success AND the failure of prayer, we find that prayer has zero effect. Every time a Christian says, "The Lord answered my prayer," what we are seeing instead is a simple coincidence or the natural effects of self-talk. Christians never discuss failed prayers, but if we look at all the prayers that fail as well as the prayers that work, a statistical analysis proves that God does not answer prayers."

አንዳንዶቹ ፀሎቶች የመሆን እድላቸው ወደ 100% የተጠጋ ነው። ለምሳሌ የጥንት ሮም ሰዎች ለጁፒተር ወቅቱ ተሎ እንዲገባ ቢፀልዩ ወቅቱ ሲደርስ የተፈጥሮ ኡደት ስለሆነ ክረምቱ በሰዓቱ ይገባል የመሰብሰቢያው ወቅትም በጊዜው ይመጣል። ማያውያንና አዜቲኮች ቢጸልዩም ባይፀልዩም ወቅቶች ኡደታቸውን ጠብቀው ይለዋወጣሉ። በሂሳብ አያያዝ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተመረቀ ስራ ፈላጊ ጌታየ እባክህ ባንክ ውስጥ አስቀጥረኝ ብሎ ቢማፀን ውጤት ካለውና ለፈተናው ካነበበ ያልፋል። በዋርኒግ ተመርቆ ለፈተናም ሳይዘጋጅ በእየ ገዳሙ እየሄደ ቢሳል ግን ምን አልባት የሚመጥነውን ስራ ያገኝ እንደሆነ እንጅ በታምር ብቁ የሆኑ ብቻ ከሚገቡበት አይገባም። አንድ ገበሬ "ጌታየ እባክህ ሰብሌን ከተባይና ከብቶችን ከበሽታ ጠብቅልኝ" ብሎ ቢፀልይ ሊሰምርለት ይችላል።

አንድ የ12ኛ ክፍል ተማሪ "እባክህ ጌታየ ዩኒቨርስቲ የመግቢያ ውጤት ላምጣ" ብሎ ቢጸልይ ሊሳካለት ይችላል። ውጤቱ የሚወሰነው በልጁ ዝግጁና በፈተናው የክብደት መጠን ነው። የማለፍ እድሉ ከ50% በላይ ወይም በታች ሊሆን ይችላል። ሲያንቀላፋ ከርሞ፣ መፅሀፍት በሄዱበት ሳይሄድ ፀልዮ ብቻ ካለፈ በእውነት ታምር ነው ግን ኮርጆ እንዳይሆን። እግዚአብሔር የሚኮርጅበትን የሚያመቻች ከሆነና የተሳሳተውን መልስ እያስተካከለ የሚሞላ ከሆነ በእውነት እግዚአብሔር የስንፍና አምላክ ነው። በየትኛውም ሀይማኖት፣ በምንም አይነት ጉዳይ፣ በምንም አይነት ሁኔታ ፀሎት ሊሰማም ላይሰማም ይችላል። መርሳት የሌለበት ፀሎታችሁ እንዲሰማ ጠንክራችሁ ሰሩ። ያኔ ፀሎቱ ባይሳካም ስራው ይሳካል። ፀሎት የመሰማት እያሉ ከ0% እስከ 100% ነው። አንድ ሰነፍ ገበሬ ግማሽ ሄክታር ጤፍ አርሶ ጌታ ሆይ 200 ኩንታል እንዲሆን ጥላህን ጣልበት ቢል ተመኝቶ ያቀራል እንጅ አይሆንም። የሁለቱ አሳ ነገር ድሮ ነው አሁን አይሰራም። ማን ሞኝ አማኝ ነው ሰርጉን በ2 አሳና በ3 እንጀራ ለመሸየት ፀሎት የሚያደርግ? ማንም አይኖርም። ውሃውስ ጠላ ይሆንላችኋልን

Created in Master PDF Editor

በጭራሽ ይህን የሚሞክር ሞኝ በዚህ አለም የለም። ምን አልባት አንዳንድ ፓስትተሮች ካልሞከሩት በስተቀር እነሱ የማይሞክሩት የለምና በእርግጥ መሆን ነበረበት።

ይሞላን ውሃ በበትሩ እንዲሰነጠቅለት የሚለምን የለም። እስራኤል መጎብኘት የሚፈልግ ምስኪን አቅመ ቢስ ድሃ ክንፍ እንዲሰጠው አይጠይቅም። ከጠየቀ ግን ምስኪን ድሃ ብቻ ሳይሆን እብድም ጭምር ነው። ግሸን፣ ጣና፣ አክሱም፣ ደብረ ዳሞና ደብረ ሊባኖስ መሳለም የፈለገ በመኪና እና በአውሮፕላን ካልሆነም በእግሩ ይኳትናል እንጅ እንደተባለው ደመና ጠቅሶ እንዲሄድ አይፀልይም፤ ካሰበው እራሱ ህመሙ ጀምሮታል ማለት ነው።

ጸሎት የሚሰማ ቢሆን እኮ እንዴ ስንት ነገር ነበር መሰላችሁ። አማኝ በሚባሉት በድሃ ሀገራት በርካታ ህፃናት በእየቀኑ ከእናታቸው እቅፍ ህይወታቸው ያልፋል። በእውነት እናት ልጇ ከሞት እንዲተርፍ አትፀልይም ማለት ይቻላልን? ልጆችም አጥንታቸው ሳይጠነክር ወላጆቻቸውን በሞት ይነጠቃሉ ምን አልባት ልጆች ሚያውቁት ስሌለለ ላይፀልዩ ይችላሉ እንበል ግን እንደሚያስፈልጓቸው የሚያውቅ ጌታ ቢያተርፍላቸውስ? ስንቱ በዚህ ጉደይ የወላጆችን ፍቅር ሳያይ በባርነትና በጎዳና ተዳዳሪነት ህይወቱን ይገፋል። በእውነት ፀሎት፣ ፈውስ፣ ድህነትና ስኬት የሚያስገኝ ከሆነ መንግስት ሀገራዊ የፀሎት ጊዜ ማወጅ አለበት፣ ጠቅም ያለ የስራ ማስኬጃ በጀት መመደብ አለበት። ስለ ፀሎት ስኬት የሚሰብኩትን የሀገራችን ቴሌቫንጋሊስቶች የቀን አበል እየተከፈላቸው፣ ፅዱ ሆቴል እየተያዘላቸው፣ የሚንቀሳቀሱበት ጀት ተግዝቶላቸው መስበክ አለባቸው። በሚድያወቻችንም በፀሎታቸው ምክንያት ዶክተሮች ያላዳኑትን የተለያዩ በሽታዎችና የአካል ጉዳቶች መዳናቸው የሚገልፅ የምስክርነት ፕሮግራም መቀረፅ አለበት። ከዚህ የተሻለ የጤና ፕሮግራም የለም። ኑ ካለባችሁ የነበስ፣ የስጋ፣ የኑሮ በሽታ ተፈወሱ የሚል ማስታወቂያዎች መነገር አለባቸው። ግን ይህ ሁሉ ህልም ነው ቅዠት። ምን አልባት ይህን ጉዳይ የአክሽን ፊልም ልንሰራበት እንችላለን። በፊልም ደረጃ ችግር የለውም የሞተውን ማስነሳት፣ የተበጠሰውን አካል መቀጠል፣ የማያስፈልገውን ማውጣት፣ የሚያስፈልገውን መትከል ይቻላል። አክሽን ፊልም ሰዎች ፈላጎት የሚሰምርበት መንግድ ነው። በፀሎት የማይሳኩ በአክሽን ፊልም ይተገበራሉ። በአክሽን ፊልም መፅሀፍ ቅዱስን እንዲወረደ መተግበር ይቻላል። በእውነታው ግን አይታሰብም። ዘ ፓሽን ኦፍ ክሪስት ፊልምን ተጋበዙልኝ።

ተስፋ ማስቆረጥ አልፈለኩም እያስረዳሁ ያለሁት እውነታውን ነው። ፀሎታችሁ በሰማና እኔ ባፈር ደስ ይለኛል። ድሮ ሲሆን ነበር ተብሎ በመፅሐፍት እንደተፃፈው ጥምቀት ላይ ከሚዘመሩ መዝሙሮች በጣም ደስ የሚለኝ መዝሙር አለ። “እሰይ ፀሎቴ ሰመረ እሰይ ጸሎቴ ሰመረ የዛሬ አመት ተስየ ነበረ …” መዝሙሩ

የሚዘወተረው በእናቶች አካባቢ ስለሆነ ዜማው በጣም ይመስጠኛል፣ እየዋሹም አይመስለኝም እውነት ለማገር ብዙዎቹ ጭራሽ አልተሳሉም። የተሳሉትም ስለታቸው የተጋነነ ስለማይሆን የመሳካት እድሉ ከፍተኛ ነው። ያልተሳካላቸውም ቢሆኑ ለወጉ ሲሉ <እሰይ ፀሎቴ ሰመረ> ማለታቸውን አይተውም። አንዘምርም ብለው ቢያኮርፉስ ምን ይጠቅማሉ። ያም ይሁን ይህ እንደ አገር መሆንን የመሰለ የለም። ዋናው ነገር ፀሎት ይሳካልን ለሚለው አጭሩ መልስ ከ0% እስከ 100% እድል አለው ነው። ሰባኪዎች ግን ዛሬም የሰዎችን ምስክርነቶች እየደረደሩ ስለ እግዚአብሔር ጠባቂነትና ፀሎት ሰሚነት ይሰብካሉ፣ ውለታውንም ያውጃሉ።ፈጣሪ አምላክ እንዲህ ይላል ለተክለ ኪዳን እንደነገረው፦

<<ምን ያላደርግኩላችሁ ነገር አለ? በምድራዊ ሕይወታችሁ የሚያስፈልጋእሁን ከመስጠት በተጨማሪ ነቢያትን እያስነሳሁ የሕወትን መንገድ ገልጸኩላችሁ፤ ከዛ በተጨማሪ ማስተዋሉ ካላችሁ እጅግ የሚከብደውን ሊሆን የማይችለውን ነገር ግን የሆነውን፤ ከአእምሯችሁ በላይ የሆነውን በሰማይ ያሉ ሠራዊቶቼን (እጅግ ብዙ በጣም እጅግ ብዙ ከቁጥር በላይ የሆኑ መላእክትን) ያሰገረመ፤ ባደረጋችሁት የዓመጻ ድርጊት ደግሞ እጅግ ያሳዘነና ያስቆጣ ታላቅ ውለታ አድርጌላችኋለሁ።ይኸውም አምላካዊ ባሕርዬን ዝቅ አድርጌ ይህን ደካማና ጎስቆላ ሥጋችሁን ገንዘብ አድርጌ ልክ እንደ እናንተው ሰው ሆንኩላችሁ። ሁሉን ባለጠጋ የማደርግ በረት ውስጥ ተወለድኩ፤ ሄሮድስ ሕፃናትም ሲገል አቅምና ኃይል እንደሌለው ከእናቴ ድንግል ማርያም፣ ከአሳዳጊዬ የዮሴፍና ሰሎሜ ጋር በመሆን ወደ ግብፅ ተሰደድኩ፤ ተንከራተትኩ፣ ከዚያም ተመልሼ በገሊላ ናዝሬት እንደ ሰው ጥቂት በጥቂቱ አደኩ፤ ተመላለስኩ፤ ዘመን የማይቆጠርልኝ በለበስኩት ሥጋ ተቆጥሮልኝ በሠላሳ (30) ዓመቴ ለሕዝቡ የሕይወትን ቃል አስታማርኩ፤ ግን እናንተ የሕይወትን ቃል አልቀበል አላችሁ። በዚህም አላበቃችሁም፤ በእውነት እየኖርኩ ስለ እውነት እየመሰከርኩ እንደ ሐሰተኛና ወንጀለኛ እኔን እውነተኛ ፈራጅ ዳኛውን በምድራዊ ዳኛ ፊት አቆማችሁኝ፤ በሐሰት ወንጀላችሁኝ፣ ገረፍችሁኝ፤ ዘበታችሁብኝ ተፋችሁብኝ፤ ስደባችሁኝ፤ በጥፊ መታችሁኝ፤ የብርሃን አክሊል የማድል አምላክ የሾህ አክሊል አደረጋችሁብኝ፤ መስቀሉን አሸከማችሁኝ እንደ አቅመ ቢስ አዳፍችሁኝ፣ ያም አልበቃ ብሏችሁ በችንካር እጆቼንና እግሮቼን በመስቀል ላይ መታችሁኝ፤ ሰቀላችሁኝ፣ የእናንተ ጭካኔ ምኑ ይነገራል! በመስቀል ላይ ሁኜ ሞቴን (ነፍስ ከሥጋዬ መለየትን ሰጠባበቅ) ተጠማሁ ብላችሁ እንኳን ሳትራሩልኝ መራራ ሐሞትን አቀረባችሁልኝ፤ አላዘናችሁልኝም።(የመጨረሻው ፍርድ አፈጻጸም ውሳኔ፣ 2ኛ ዕትም፣ 38)

አማልዕክት ለስጋም ለነፍስም እረፍት የሚሰጡ የተመሰገኑ መናፍስት ናቸው፣ በቅዱሳን መጽሃፍት እንደተጻፈ ውለታቸውም ከአዕምሮ በለይ ነው። ሰዎችን ከጥንት ጀምሮ ሲጠብቁ፣ ሲያደኑና ሱታደጉ ኑረዋል ይባልላቸዋል፣ ወረት የሌለው ፍቅር ያለው ከአማልዕክት ዘንድ ብቻ ነውም ይባላል። ግለሰቦችም የአማልዕክቶታችን ስም እየጠሩ የዋሉላቸውን ውለታ ይመሰክራሉ። በተለይ ከጥፋቶች እንዴት እንዳተረፏቸው ሲመሰክሩ በኩራት ነው። እነዚህ ሰዎች ያልገባቸው አንድ ነገር አለ የዳኑትና የተጠበቁት በታምር ሊሆን ይችላል በፈጣሪ ግን ላይሆን ይችላል። በታምራት በየትኛውም አካባቢ፣ በየትኛውም እምነት በማያምኑትም ጭምር አለ። ከህመም የዳነን ሰው እንኳን እግዚአብሔር ማረህ ትሉታላችሁ የሞተንስ?

በአለም ስለሚሆነው እንዳስታውሳቸው ትፈልጋላችሁ በእየቀኑ እየጸለዩና እየተፀለየላቸው ስንቶቹ ይሞታሉ፤ ስንቶቹስ በተፈጥሮ አደጋ ከፀሎት ቤታቸው ሳይመለሱ ቀርተዋል። በአለም የሚደርሱትን አስቀያሚ ታሪካዊ ክስተቶች በማየት ማንም የሚጠብቀን፣ ማንም ሊያድነን የሚችል ሀይል እንደሌለ እንረዳለን። ይህን እውነት ማወቃችን የወንዞችን ሙላት፣ የአየር ለውጥን፣ የአደጋዎች የመከሰት እድልን እየተከታተልን እንድነሸሽ ያደርገናል። ሳይንስ ፈጹም ነው ባይባልም የተፈጥሮ አደጋዎች መቸና የት እንደሚፈፀም ተቀራራቢ ትንቢት በመስጠት ዜጎችን ከሞት እየጠበቀ ይገኛል። ለጉዳዩ ትኩረት ያልሰጡና ኢኮኖሚያቸው የማይፈቅድ ሀገራት ግን ዛሬም ዜጎቻቸውን ውሃ እየበላቸው ይገኛል። ምን አልባት ከተፈጥሮው አደጋ የተረፈው በእየ ቤተ እምነታቸው እሄዱ የስብከቱን ናዳ፣ የአዳኛቸውን ፍቅር ይሰብካሉ። በእውነት ያሳፈራል 1000 ሰው ሙቶ እኔ በጌታ ጠባቂነት ተረፍኩ ማለት ለሟች ቤተሰቦች የሚያስከፋ ምስክርነት ነው። እነዚህ መስካሪዎች ጠበቆኛል አድኖኛል ከሚሉ እድላቸውን ቢያመሰግኑ መልካም ነበር። በግሌ እንነዚህ አይነት ሰዎች እጅግ ያናድዱኛል። በሰዎች ሞት የሚቀልድ ያላናደደ ምን ያናድዳል። ጉዳዩን በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን አድምጣችሁ ፈረዱኝ።

ለበርካታ አማኞች ሃይማኖት ስለ ተፈጥሮ መልስ ከመስጠት የበለጠ ትርጉም አለው። መልካም ነገርን ሁሉ ያደርጋል። በሥነ ምግባር የተሞላ ሕይወት እንድንኖር አድርጓል ይላሉ። እንዲሁም የማህበራዊ የኑሮ ስርዓት ዘርግቷል። በአንዳንድ ቦታዎች ባህልና ኃይማኖት በጣም የተጣበቁ ስለሆኑ እርስ በርሳቸው አይነጣጠሉም እናም የሃይማኖትን መሠረተ ትምህርቶች አለመቀበል የመገለል ስሜትን ሊያስከትል ይችላል።እውነት ለመናገር አብያተ ክርስቲያናት፣ መስጊዶች፣ ቤተመቅደሶች እና ሌሎች የሃይማኖት አደረጃጀቶች በርካታ ጥቅሞች አሏቸው። ማህበራዊ ህይወትን ያሻሽላሉ፤ ጓደኝነት ይፈጥራሉ፤ መንፈሳዊ እና የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣሉ፤ የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ ወ.ዘ.ተ። አንዳንድ የኃይማኖት ቡድኖች በማኅበረሰቦቻቸው ላይ

Created in Master PDF Editor

ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ። ለዚህ ነው ብዙ የታወቁ የበጎ አድራጎት ማህበራት ሃይማኖታዊ የሆኑት።

ይሁን እንጂ የኃይማኖት ማህበረሰቦች ጥቅሞች የሚያመልኩትን አምላክ መኖር አያረጋግጥም። የሰዎቹ መልካም ነገር የሚያሳየን ሰዎች እርስ በእርሳቸው ቢተባበሩ ሊፈጠሩት የሚችሉትን ታላቅ ነገር ነው። ይህን በጎ ምግባር ደግሞ በማያምኑት ማህበረሰብ በኩል ማግኘት ይቻላል። ብዙ አምላክ የለሽ ቡድኖች እና ድርጅቶች ለሚኖሩበት ማህበረሰብ ድጋፍ ይሰጣሉ። ይልቁንም የአንድ ሃይማኖታዊ ማኅበረሰብ አባል መሆን የሚያስገኛቸው ጥቅሞች እንደተጠበቁሆኖ ጎጂ ከሆኑ የሃይማኖት ተፅእኖዎች ውጭ መሆኑ የላቀ ያደርገዋለል።

እግዚአብሔር ሰዎችን የሚረዳ መሆኑን የሚያሳዩ ምንም ማስረጃዎች የሉም። ይሁን እንጂ ሰዎች እርስ በርሳቸው ሲረዳዱ ማየት የተለመደ ነው። ለምን ቢባል ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ስለሆነ።

በአንድ የተወሰነ ሃይማኖታዊ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ አንድ አንድ ሰዎች ከተፈጥሮ አደጋ ቢተረፉ፣ ከማይድን በሽታ ቢፈወሱ እና ሌሎች ተዐምራዊ ክስተቶችን ቢመለከቱ እነዚህ ልዩ ተዐምራት ስለ እግዚአብሔር መኖር ማረጋገጫ አይሆኑም። አምላክ የለሾች እና ሌሎች አማልክትን የሚያመልኩምልዩ ክስተት ሊያጋጥማቸው ይችላል። እኛ አምላክ የለሾች የፈውስ ቤተመቅደሶች አሉን።እነሱም ሆስፒታሎች እና የጤና አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ናቸው። ሳይንስበእሱ ቢያምፁም በማያምፁም ሙሉ አቅሙን እና ችሎታውን ተጠቅም በተሻለ መንገድ ይፈውሳል።እንዳንዶቹ ፈውሶች እጅግ የረቀቁ እና ልዩ ተዕምራት ናቸው።

ለነገሩ በቤተ እምነቶች የተጠለሉ ሰዎች የሚያገጥማቸው መልካም መልካሙ ነው ያለው ማነው? The Compatibility of the Problem of Evil and The Existence of God በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና ት/ክፍል የሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ ጽሁፍ ያቀረበው ዮናስ ዘውዴ እንዲህ ሲል ይጠይቃል። “If God exists, why does he allow little children to die of starvation? Why does he permit the earth quake? Why does he permit the rape? Why does he let babies to be born addicted to drugs? Why does God allow millions to die at the hands of wicked dictators? Why so many suffer from arthritis, cancer, or birth defects while others are healthy? Why does God permit any suffering at all?”(ዮናስ ዘውዴ፣ 2015፣ Abstract) ተመራማሪው መጥፎ ነገር መኖሩ የእግዚአብሔርን አለመኖር አያስረዳም (God and evil are compatible) የሚል ትንታኔ ቢያቀርብም ጥያቄዎቹ ግን ዛሬም <<ግን ለምን>> ያስብላሉ። አጥኚው ዮናስ ዘውዴ በመግቢያው ገጽ 1 ላይ እንደጠቀሰው “If

Created in Master PDF Editor

God really exists, if he is so good, then why does He allow evil? If he is all powerful, why does He not eliminate or prevent all evil? If He is all knowing, why does He not find a way to avoid evil in the world?" ስንል ዛሬም እንጠይቃለን።

አማኞች እራሳቸውን እስከማጥፋት በሚደርስ ጭንቅ ውስጥ ያልፋሉ። እንደማንኛውም ሰው አደጋ ይደርስባቸዋል። የማንም መኖርያ ቤት በመብርቅ እንደሚመታ ቤተ እምነቶችም በመብረቅ ይቃጠላሉ። የሚገርመኝ ቤት ክርስቲያን በመብረቅ ሲመታ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ነው ይባላል። እኔ እምለው ሲበሳጩ እራሳቸውን የሚያጠፉ እና ቤታቸውን የሚያቃጥሉ ሰዎች ልምዱን የወረሱት ከእግዚአብሔር ልበል።

ሁሉንም ተውትና እግዚአብሔር ወይም ሐይማኖት መልካም ነገሮች ስላመጣልን የሚመሰግን ከሆን በእየ ቀኑ ለሚፈጠሩት እልቂቶች ማን ተጠያቂ ይሁን እግዚአብሄር ወይስ መከረኛው ሰይጣን ብቻ አናንተ እዳትሉኝ።እንዲያውም በተቋም እና በግልም ሃይማኖት ለበርካታ ጥፋቶች ተጠያቂ ነው። የመስቀል ጦረነትን እና ጁሀድን መጥቀስ በቂ ነው። በሰው ህይወት ውስጥ ለሚገኙ መልካም ነገሮች ምክንያት እግዚአብሔር ከሆነ መጥፎ ነገሮችን ያደረሰብን እግዚአብሔር ነው ብላችሁ እንዳትቀበሉ ያደረጋችሁ ምክንያቱ ምንድን ነው? የሆነ ሁኖ መልካም እና መጥፎ ክስተቶች የተፈጥሮን ህግ እንጅ የፈጣሪን መኖር አያስረዱም አራት ነጥብ።!

16. **እግዚአብሔር ፍቅር ነው**

ቅዱስ፣ ፍቅር፣ ጽድቅ፣ ጥበብ፣ ሁሉን ቻይ፣ ሁሉን አዋቂ፣ ኃያል፣ የሰራዊት ጌታ፣ ምሉዕና ዘለዓለማዊ የሚሉት እግዚአብሔር ለሚለው ቃል ሞክሸ ናቸው። በመጽሃፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በእንነዚህ የተግባር ስሞች ተጠርቷል። ለጊዜ አንዱ ላይ ማተኮር ፈለኩ ግን እግዚአብሔር ፍቅር ነው?

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" (ዮሐንስ 3፡16) እንደጋናም እንዲህ ይላል፦ "ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና። ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና፤ ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል። ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።" (ሮሜ 5፡7-8) መነባንቡ ደስ ይላል እውነቱ ሲመረመር ግን ወግ ብቻ ነው? እንዲያው ለነገሩ የእግዚአብሔር ፍቅር አንድያ ልጁን እስከመስጠት መውደድ ምንድን ነው?

Created in Master PDF Editor

ክርስቲያኖች እግዚአብሔር አለምን ከፈጠረበት ያደነበት ጥበቡ ይደንቃል ይላሉ፡፡ አለምን ያዳነበት ጥበብ የሚደነቀው ደግሞ የሰራዊት ጌታ ከዙፋኑ ወርዶ፣ የሰውን ስጋ ለብሶ፣ በበረት በተወለዶ፣ በዩርዳኖስ ተጠምቆ፣ አርባ ቀን አርባ ሌሊት ፁሞ፣ ብዙ ሽህ ግርፋቶችን ተገርፎ፣ ፍቅርን በቃልና በተግባር አስተምሮ፣ በደቀ መዝሙሩ በይሁዳ ተክዶ፣ በመስቀል ተሰቅሎ ማደኑ ነው፡፡ በሰሞነ ህማማት የጌታን ቁስል ለማሰብና የመከራው ተካፋይ ለመሆን እማኞቹ ይፆማሉ፣ ይሰግዳሉ፣ ያዝናሉ፣ አንዳንዶቹ እራሳቸውን ይገርፋሉ ይህንና ሌሎች ስርዓቶችን ይፈፅማሉ፡፡ የኢየሱስን ፊልሞች እያዩ ይደነቃሉ፣ ያለቅሳሉ፣ ያለጫማ ይሄዳሉ፣ የበገና መዝሙሮችና የምህላ ስብከቶች ከእየ ደብሩ ይሰማሉ፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነው ረቂቅ የተባለው የጌታን ፍቅር ለማሰብ ነው፡፡ ግን እውነት ጌታ እራሱን እስከሞት የመስጠት ፍቅር እውነተኛ ነውን? አይደለም ለምን?

አንደኛ በሚስጠረ ስላሴ ህገ መሰረት ወልድ ወደ መሬት የመጣው ከአብ ሳይለይ ነው ለዚህም ነው ሰባኪዎች ከላይ ሳይንስ ከታች ሳይጨምር የሚሉት፡፡ ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ከዙፋኑ እንዳለ ሆኖ ወደ መሬት መጣ፣ በመሬት ላይ 33 ዓመት ሲያሳልፍ በሰማይም ነበር በዙፋኑ ላይ፡፡ ስለዚህ የሚሆነውን ነገር ከላይ ሆኖ ይመለከታል ማለት ነው አይ አይደለም ከሰማያዊ ዙፋኑ ወርዶ (ለቆ) ነው የመጣው የሚባል ከሆነ ሚስጢር ስላሴ ተናጋ ማለት ነው፡፡ ያም ይሁን ይህ ክርስቶስ የተቀበለው መከራ እውነት እንኳ ቢሆን ትርጉም የለውም በአለም ሁሉ የሚገኝን ጌታ መግረፍ አይቻልምና፡፡ ኧረ በስጋ ተወስኖ ነው ቁስላችንን በቁስሉ የፈወሰን ከሆነ መልካም ሲጀመር ከየትኛው ቁስል ከአባታችን ከአደም በዘር ከመጣው ነው እንዳትሉ ይህ ሌላ ጣጣ ያመጣል፡፡ እግዚአብሔር ሀጢአትን በዘር ማስተላለፍ ብቻ ፍቅር የማይገባው ፍትህ የሌለበት ያደርገዋል፡፡ ማንንም በዚህ ምድር ያለ ያችን ፍሬ የበላ የለም፡፡ ታዲያ ለምን ባልሰራነው ሀጢአት እንወቀሳለን? መስዋትነትስ ለምን አስፈለገ ሀጢአትን በዘር ማስተላለፉ ቆጭቶት ነውን? ቢቆጨውስ ቢሆን አንድ ነብይ ልኮ ይቅር ብያለሁ የምትጠየቁት በሰራችሁት ሀጢዓት ነው ማለት ይችላል ነበር ያለ አግባብ በከንቱ ደከመ፡፡

ሌላው የክርስቲያን ፍቅር የሚነካው አዋቂነቱ ነው፡፡ እናንተ ልጅ አላችሁ እነበል ልጃችሁን ሀገር እንዲጠብቅ የከታማይቱ ዘብ እንዲሆን አዘዛችሁት ልጃችሁም ተልዕኮውን በፀጋ ተቀብሎ ወደ ስራው ሄደ፡፡ ሌቦች እንደሚያስቃዩትና እንደሚገድሉት ታውቃላችሁ ግን ምንም አይሆንም በሞተ በ3ኛው ቀን ይነሳል፡፡ ወደ ቤቱና ወደ ስራውም ይመለሳል ይህን ታውቃላችሁ፡፡ በክርስቶስ የሆነው ይህ ነው አብም ወልድም መቸ እንደሚሞት መቸ እንደሚነሳ ያውቃሉ ታዲያ ለሚታወቅ ነገር የሚከፈል ዋጋ መስዋትነት (sacrification)ነውን? በጭራሽ ህይወትን መስጠት ሲባል እንዲህ አይደለም የክርስቶስ ሞትመስዋዕትነት የለውም፡፡

Created in Master PDF Editor

ክርስቶስ ሲመጣም ምክንያታዊ በሆነ መንገድ አልነበረም ሙቶ የተነሳው አንዳች የሚደንቅ ፍቅር የለውም። ይልቅስ ደም የሚለግሱትን ወገኖቻችንን አድንቁ። የሰጡትን መልሰው አያገኙትምና። ክርስቶስ በመሰቀሉ በመገረፍና በመሞቱ ምን ጎደለበት እኔ እማደንቀው ክርስቶስ ለአለም የሰጠውን ፍቅር ሳይሆን አለም ለክርስቶስ የሰጠውን ፍቅር ነው። ለእግዚአብሔር እኮ ፆመ፣ ሰገደ፣ ተመታ፣ ተሰቀለና ሞተ የሚበሉ ነገሮች አይመጥኑትም። ለሰው የሆነ እንደሆን እስከ 11:00 ሰዓት የፆመ ቁርስና ምሳዋን መስዋእት አድርጓል ማለት ነው ይህም ጌታ ከጾመው አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ይበልጣል። አንድ ምዕመን 40 ጊዜ ሲሰግድ ከክርስቶስ ከተገረፈው እልፍ ግርፋት የበለጠ ነው አካሉ ይቆስላልና። ቅዱሳን በክርስቶስ ስም በአላውያን ነገስታት በተለይ በመጀመሪያዎቹ የክርስትና ክፍል ዘመናት መከራው የፀና ነበር። በወቅቱ ብዙዎቹ እውነተኛ መስዋዕትነት ከፍለዋል። ክርስቶስ ከሰጠን ስጋና ደም ይልቅ ቅዱሳን በክርስቶስ ስም የሰጡት ስጋና ደም ይደንቃል፣ ይበልጣልም በእውነተኛ ሲቃሙተዋልና።

ከሁሉም ነገር የሚሳዝነው ግን ክርስቶስ የከፈለው ዋጋ ለኒሳኛው ትውልድ ያመጣነው አዲስ ነገር ምንድን ነው ከአሪት መታደስ በስተቀር። አሁንም ሲኦል አለ። አሁንም ገሃነም አልተዘጋም። ሁሉም ነገር በነበረበት ነው የቀጠለው። ይህን እና ሌሎች ለክርስቶስ የተጋነነ ስዕል፣ በተለይ ብቸኛ መንገድና ህይወት ማድረጋቸውን ሳስብ ክርስቲያኖች ያሳዝኑኛል። ክርስቶስ የፈወስን የቱን ቁስል ነው? መሰቀሉ እንደሰው ቢያሳዝነንም የተረፈን ምንድን ነው ማለት ግን ተገቢ ነው?

እውነት እንነጋገር የክርስቶስ ፍቅር ምንድን ነው? ለሰዎች ያበረከተውስ ምንድን ነው? በመጽሀፍት እንደተባለው በእውነት የዋለልን ወለታ እንኳን ቢኖር ክርስቶስ ፍቅርን በተግባር ስብኳልን? በቅዱሳን መጽሃፍት ስለ ክርስቶስ ፍቅር የተሰበከው እውነት አለውን? ኦሾ The Golden Future በሚለው ንግግሩ ይመልሳል፦ "---scriptures talk about, great virtues of truth, of love, of silence, of peace, of brotherhood. But they are only to be talked about; you are not supposed to practice them. These beautiful words are just decorative. Yes, in the name of love you can kill as many people as you want. Millions of people have been killed in the name of Christian love; millions of others have been killed in the name of peace, by the Mohammedans." ሀቁ ይህ ሁኖ እያለ አማኞች ግን ስለ እግዚአብሔር እንዲህ የሰብካሉ፦

> እግዚአብሔር ለሕዝቡ ኃይል ነው፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ መጠጊያ ነው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ረዳት ነው። የማሸነፊያ መሠረቱ ኃይል ነው። ኃይል አንቀሳቃሽ፣ ኃይል ድል መንሻ፣ ኃይል የተፈሪነት ምሥጢር፣ ኃይል ዓለም የቆመችበት እጅ ነው። ወጥተን የምንገባው፣ ተኝተን የምንነቃው፣ በተኩላዎች መካከል በሰላም የምናልፈው፣ ሞት ታውጆብን በሕይወት ያለነው፣ የምናቀደው

Created in Master PDF Editor

> የምንሮጠው እግዚአብሔር አንቀሳቃሽ ኃይል ስለሆነልን ነው። ኃይል ድል መንሻ ነው። የኃይል መመጣጠን ከሌለ ድል አይታሰብም። ከሚዋጋን ዓለም፣ ከሚዋጋን ሰይጣን የሚዋጋልን እግዚአብሔር ኃይሉ ፍጹም ነው። መገመት፣ መመዘን፣ መለካት፣ መወሰን፣ መቆጠብ፣ ማነስ የለበትም። እኛን የሚችሉ ጠላቶቻችን አምላካችንን አይችሉትም። ኃይል የተፈሪነት ምሥጢር ነው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ የግርማ አጥራቸው የመወደድ ሞገሳቸው ነው። እግዚአብሔር የከበባቸው አይደፈሩም፣ እግዚአብሔር የተከራከረላቸው አይረቱም፣ እግዚአብሔር የተዋጋላቸው አይሸነፉም። ይህችን ዓለም የሚያራምዳት፣ አጽንቶ የያዛት፣ በባሕር ላይ የመሠረታት፣ ያለ ምሰሶ ያጠናት ኃይል እግዚአብሔር ነው።እግዚአብሔር የሕዝቡ መጠጊያ ነው። መሠረታዊ ከሆኑ የሕይወት ፍላጎቶች አንዱ መጠጊያ ነው። ማንኛውም ፍጡር ጥግ ይፈልጋል። ወይ ያማረ ቤት ወይ አጥር ጥግ፣ ወይ ዛፍ ሥር፣ ብቻ ፍጡር መጠጊያ ይፈልጋል። መጠጊያ ማረፊያ ነው። መጠጊያ መሸሻ ነው። መጠጊያ ነጻ ግዛት ነው። መጠጊያ ሰው የእኔ የሚለው ሀብት ነው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያስፈልጋል። እግዚአብሔር መጠጊያ ነውና ያለ እርሱ መኖር አይቻልም። እግዚአብሔር ያሳርፋል፣ መሸሻ ይሆናል፣ ነጻ ግዛታችን ነው፣ የእኔ የምንለው ነው። እግዚአብሔር ለሚያምኑት ረዳት ነው። ረዳት የሚከላከልልን፣ የሚሟገትልን፣ የሚዋጋልን፣ የሚያሸንፍልን ነው። ረዳት ያለው አይጠቃም፣ ረዳት ያለው ተሸንፎ አይገባም። እግዚአብሔር ረዳት የሆነላቸውም አይጠቁም። ተሸንፈውም አይገቡም። ተስፋ ቆርጠውም ራእያቸውን አይተውም። (http://betelhemm.blogspot.com/)

ስለክርስቶስ ፍቅር ሲሰብኩም፦ “ሔዋን በደልን በአምስት (5) ወገን አምጥታለች። ይኸውም በዓይኗ የተተከለውን ዛፍ ተመልክታለች፤ በጆሮዋ የእባብን ምክር ሰማች፤ በእግሯ ሔደች፤ በእጇዋ ቆረጠች፤ በአፍዋ በላች። ክብር ይግባውና ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህን ሁሉ ክሶልናል። በጆሮው የአይሁድን ዝብዘባ ሰምቷል፤ በዐይኑ ግርማ የአይሁድን አሳፋሪነት አይቷል፤ እጆቹ እና እግሮቹ ተቸንክረዋል፤ በአፉ መራራ ሐሞትን ቀምሷል፤ በዚህ ሁሉ ክሶልናል።” (ፍኖተ ብርሃን፣ 10ኛ ዕትም፣ 2009 ዓ.ም)

ብዙዎቻችን ‘የፍቅሩን ፍጻሜ’ ገለጸው በመስቀል የሚለውን ስንኝ በእንባ ጭምር ዘምረነዋል። ብዙዎች ግን እየሱስ ተሰቅሎ እንኳ ቢሆን እንዲህ መግነኑ አይዋጥላቸውም። Lemuel K. Washburn በ1911 ባሳተመው Is the Bible Worth Reading and Other Essays በሚለው ድንቅ መጽሃፉ የክርስቶስን የጥቂት ሰዓታት መስዋዕትነት ከወላጅ አሳዳጊ እናት ጋር ያነጻጽረዋል። ሀያሉ ጌታ እየሱስ በመስቀሉ ያሳለፈውን መከራና እናቶቻችን የከፈሉትን በሰፊው ካወዳደረ በኋላ የክርስቶስ ውለታ እንደ ኢምንት እንደሆነበት ይናገራል። “The sacrifice of Jesus,

Created in Master PDF Editor

so much boasted by the Christian church, is nothing compared to the sacrifice of a mother for her family. It is not to be spoken of in the same light. A mother's sacrifice is constant: momentary, hourly, daily, life-long. It never ceases. It is a veritable providence; a watchful care; a real giving of one life for another, or for several others; a gift of love so pure and holy, so single and complete, that it is an offering in spirit and in substance." (Lemuel K. Washburn, page 7) እየሱስ በእለተ አርብ ያሳለፈው መከራ እውነት ከሆነ እጅግ አሳዛኝ መሆኑን ለመመስከር አማኝ መሆን አይጠይቅም ቢሆንም Lemuel K. Washburn እንዳለው ከሚገባው በላይ ሽፋን ተሰቶታል፣ ለምን ቢባል ክርስቶስ ለእኛ ሲል መከራ የተቀበለው አንድ ቀን ብቻ ነው:: ብዙ ወገኖቻችን በተለይ ወላጆቻችን ግን በቀን ብቻ ሳይሆን ለብዙ አመታት መስዋዕት ሁነዋል:: እስኪ ለእናንተ ከወላጆቻችሁ መስዋዕትነትና ከክርስቶስ የመስቀል ውለታ የትኛው ልብ ይሰብራል?

ይልቅስ ወደ መራራው እውነት ስንሄድ ነገረ እግዚአብሔር በቅዱሳን መጽሃፍት እንደተሰበከው ፍቅር ሳይሆን ጥላቻ ነው፣ መስጠት ሳይሆን መቀበል ነው፣ ይቅርታ ሳይሆን ቅጣት ነው፣ መታገስ ሳይሆን መፍረድ ነው፣ መቻል ሳይሆን መቆጣት ነው፣ ማክበር ሳይሆን መናቅ ነው፣ መውደድ ሳይሆን መጥላት ነው፣ መሳብ ሳይሆን መግፋት ነው፣ እኩል ሳይሆን ማዳላት ነው:: እግዚአብሔር ፍርተን ካልሆንን በስተቀር የፍቅር አምላክ ወይም እራሱ ፍቅር ነው ልንለው አንችልም::ከብዙ በጥቂቱ ከቅዱሳን መጽሃፍት ያለማብራርያና ያለምንም ማጣመም ምሳሌዎችን ላሳያችሁ:: ፍረዱኝ ፍቅር ምን ማለት ነው? ? ? ? ?

- ስለ ሴቶች

<<እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው:: ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው:: ሴት ብታረግዝ ወንድ ልጅም ብትወልድ፥ ሰባት ቀን ያህል የረከሰች ናት፤ እንደ ሕመምዋ መርገም ወራት ትረክሳለች:: በስምንተኛውም ቀን ልጁ ከሥጋው ሸለፈት ይገረዝ:: ከደምዋም እስክትነጻ ሠላሳ ሦስት ቀን ትቀመጥ፤ የመንጻትዋ ቀንም እስኪፈጸም ድረስ የተቀደሰን ነገር አትንካ፥ ወደ መቅደስም አትግባ:: ሴት ልጅም ብትወልድ እንደ መርገምዋ ወራት ሁለት ሳምንት ያህል የረከሰች ናት፤ ከደምዋም እስክትነጻ ድረስ ስድሳ ስድስት ቀን ትቀመጥ::>>(ዘሌዋውያን 12: 1-5)

<<አየሁም፥ እነሆም፥ በጉ በጽዮን ተራራ ቆሞ ነበር፥ ከእርሱም ጋር ስሙና የአባቱ ስም በግምባራቸው የተጻፈላቸው መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ::እንደ ብዙ ውኃም ድምፅና እንደ ታላቅ ነጐድጓድ ድምፅ ያለ ከሰማይ ድምፅን ሰማሁ፥ ደርዳሪዎችም በገና እንደሚደረድሩ ያለ ድምፅ ሰማሁ:: በዙፋኑም ፊት በአራቱም እንስሶችና በሽማግሌዎቹ ፊት አዲስ ቅኔ ዘመሩ፤ ከምድርም ከተዋጁት ከመቶ አርባ አራት ሺህ በቀር ያን ቅኔ ሊማር ለማንም አልተቻለውም::

Created in Master PDF Editor

ከሴቶች ጋር ያልረከሱ እነዚህ ናቸው፥ ድንግሎች ናቸውና። በጉ ወደሚሄድበት የሚከተሉት እነዚህ ናቸው። ለእግዚአብሔርና ለበጉ በኵራት እንዲሆኑ ከሰዎች የተዋጁ እነዚህ ናቸው።>> (ራእይ 14: 1-4)

<<እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው። ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው። ማናቸውም ሰው ሰውን ለእግዚአብሔር ሊሰጥ ቢሳል አንተ እንደምትገምተው መጠን ስለ ሰው ዋጋውን ይስጥ። ለወንድ ከሃያ ዓመት ጀምሮ እስከ ስድሳ ዓመት ድረስ እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን ግምቱ አምሳ የብር ሰቅል ይሁን። ሴትም ብትሆን ግምትዋ ሠላሳ ሰቅል ይሁን። ከአምስት ዓመትም ጀምሮ እስከ ሀያ ዓመት ድረስ ግምቱ ለወንድ ሀያ ሰቅል፥ ለሴትም አሥር ሰቅል ይሁን። ከአንድ ወርም እስከ አምስት ዓመት ድረስ ለወንድ ግምቱ አምስት የብር ሰቅል፥ ለሴትም ግምትዋ ሦስት የብር ሰቅል ይሁን። ከስድሳ ዓመትም ጀምሮ ከዚያም በላይ ወንድ ቢሆን ግምቱ አሥራ አምስት ሰቅል፥ ለሴትም አሥር ሰቅል ይሁን።>> (ዘሌዋውያን 27: 1-7)

<<ንጉሡም ሰሎሞን ከፈርዖን ልጅ ሌላ፥ በሞዓባውያንና በአሞናውያን በኤዶማውያን በሲዶናውያንና በኬጢያውያን ሴቶች፥ በብዙ እንግዶች ሴቶች ፍቅር ተነደፈ። እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች። አምላኮቻቸውን ትከተሉ ዘንድ ልባችሁን በእውነት ያዘነብላሉና ወደ እነርሱ አትግቡ፥ እነርሱም ወደ እናንተ አይግቡ ካላቸው ከአሕዛብ፥ ከእነዚህ ጋር ሰሎሞን በፍቅር ተጣበቀ። ለእርሱም ወይዛዝር የሆኑ ሰባት መቶ ሚስቶች ሦስት መቶም ቁባቶች ነበሩት፤ ሚስቶቹም ልቡን አዘነበሉት።>> (1ኛ. ነገሥት 11፡ 1-3)

<<ሚስቶች ሆይ፥ በጌታ እንደሚገባ ለባሎቻችሁ ተገዙ። (ቆላስይስ 3:18)ሴት በነገር ሁሉ እየተገዛች በዝግታ ትማር፤ ሴት ግን በዝግታ ትኑር እንጂ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሰለጥን አልፈቅድም። አዳም ቀድሞ ተፈጥሮአልና፥ በኋላም ሔዋን ተፈጠረች። የተታለለም አዳም አይደለም፥ ሴቲቱ ግን ተታልላ በመተላለፍ ወደቀች፤ ነገር ግን በእምነትና በፍቅር በቅድስናም ራሳቸውን እየገዙ ቢኖሩ በመውለድ ትድናለች።>> (1ኛ ጢሞ. 2: 11-15)

<<ከወር አበባም ይጠይቁሃል። እርሱ አስጠያፊ ነው። ሴቶችንም በወር አበባ ጊዜ ራቋቸው። ንጹሕ እስከሚኾኑም ድረስ አትቅረቡዋቸው። ንጹሕ በኾኑም ጊዜ አላህ ካዘዛችሁ ስፍራ ተገናኙዋቸው።>> (ቁዕራን 2፡222)

<<ሴቶቻችሁ ለናንተ እርሻ ናቸው። እርሻችሁንም በፈለጋችሁት ኹነታ ድረሱ።>> (ቁዕራን 2፡223)

<<ሴቶች በማህበር ዝም ይበሉ ህግ ደግሞ እንደሚል እንዲገዙ እንጂ እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውምና።ለሴት በማህበር መካከል መናገር ነውር ነውና ምንም ሊማሩ ቢዱወዱ በቤታቸው ባሎቻቸውን ይጠይቁ። (1ኛ ቆሮ. 14፡34)፣ሴት ግን በዝግታ ትኑር እንጂ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሰለጥን አልፈቅድም። (1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2፡12)፣ ሚስትም ከባልዋ አትለያይ፥ ብትለያይ ግን ሳታገባ ትኑር ወይም ከባልዋ ትታረቅ፥።(1ኛ ቆሮ. 7፡10-11)፣ ሴት ግን በዝግታ ትኑር እንጂ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሰለጥን አልፈቅድም። አዳም ቀድሞ ተፈጥሮአልና፥ በኋላም ሔዋን ተፈጠረች። (1ኛ ጢሞ. 11፡12)

Created in Master PDF Editor

<<ነገር ግን የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ፥ የሴትም ራስ ወንድ፥ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ልታውቁ እወዳለሁ። ራሱን ተከናንቦ የሚጸልይ ወይም ትንቢት የሚናገር ወንድ ሁሉ ራሱን ያዋርዳል። ራስዋን ሳትሸፍን ግን የምትጸልይ ወይም ትንቢት የምትናገር ሴት ሁሉ ራስዋን ታዋርዳለች፤ እንደ ተላጨች ያህል አንድ ነውና። ሴትም ራስዋን ባትሸፍን ጠጉርዋን ደግሞ ትቆረጥ፤ ለሴት ግን ጠጉርዋን መቆረጥ ወይም መላጨት የሚያሳፍር ከሆነ ራስዋን ትሸፍን። ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና ክብር ስለ ሆነ ራሱን መከናነብ አይገባውም፤ ሴት ግን የወንድ ክብር ናት። ሴት ከወንድ ናት እንጂ ወንድ ከሴት አይደለምና። ሴት ስለ ወንድ ተፈጠረች እንጂ ወንድ ስለ ሴት አልተፈጠረምና።(1ኛ ቆሮ. 11፡3-10)

<<ማናቸውም ሰው ሚስት ቢያገባ፥ ከደረሰባትም በኋላ ቢጠላት፥ የነውር ነገር አውርቶ። እኔ ይህችን ሴት ሚስት አድርጌ አገባኋት፥ በደርስሁባትም ጊዜ ድንግልናዋን አላገኘሁባትም ብሎ በክፉ ስም ቢያሳጣት፥የብላቴናይቱ አባትና እናት የድንግልናዋን ምልክት ወስደው በበሩ በአደባባይ ወደ ተቀመጡ ወደ ከተማ ሽማግሌዎች ያምጡት፤ የብላቴናይቱም አባት ሽምግሌዎቹን። እኔ ለዚህ ሰው ልጄን ዳርሁለት እርሱም ጠላት፤ እነሆም በልጅህ ድንግልና አላገኘሁባትም ብሎ የነውር ነገር አወራባት፤ የልጄም ምልክት ይኸው ይላቸዋል። በከተማም ሽማግሌዎች ፊት ልብሱን ይዘረጋሉ። የዚያችም ከተማ ሽማግሌዎች ያንን ሰው ወስደው ይግረፉት፤ በእስራኤል ድንግል ላይ ክፉ ስም አምጥቶአልና መቶ የብር ሰቅል ያስከፍሉት፥ ለብላቴናይቱም አባት ይስጡት፤ እርስዋም ሚስት ትሁነው፥ በዕድሜውም ዘመን ሁሉ ሊፈታት አይገባውም። ነገሩ ግን እውነት ቢሆን፥ በብላቴናይቱም ድንግልናዋ ባይገኝ፥ ብላቴናይቱን ወደ አባትዋ ቤት ደጅ ያውጡአት፥ በእስራኤልም ዘንድ የማይገባውን ነገር አድርጋለችና፥ በአባትዋም ቤት አመንዝራለችና የከተማዋ ሰዎች እስክትሞት ድረስ በድንጋይ ይውገሩአት፤ እንዲሁም ክፉውን ነገር ከመካከልህ ታስወግዳለህ።>> (ዘዳግም 22፡ 13-21)እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም። (ማቴዎስ 5፡17)

<<ማናቸውም ሰው ከሌላ ሰው ሚስት ጋር ተኝቶ ቢገኝ፥ አመንዝራውና አመንዝራይቱ ሁለታቸው ይሙቱ፤ እንዲሁም ክፉውን ነገር ከእስራኤል ታስወግዳለህ። ማናቸውም ሰው ድንግልና ያላትን ልጃገረድ ቢያጭ፥ ሌላ ሰውም በከተማ ውስጥ አግኝቶ ከእርስዋ ጋር ቢተኛ፥ ሁለቱን ወደዚያች ከተማ በር አውጡአቸው፤ ብላቴናይቱ በከተማ ውስጥ ሳለች አልጮኸችምና፥ ሰውዮውም የባልንጀራውን ሚስት አስነውሮአልና እስኪሞቱ ድረስ በድንጋይ ውገሩአቸው፤ እንዲሁም ክፉውን ነገር ከመካከልህ ታስወግዳለህ። ነገር ግን ሰው የታጨችውን ልጃገረድ በሜዳ ቢያገኛት፥ በግድ አሸንፎም ቢደርስባት፥ ያ የደረሰባት ሰው ብቻውን ይገደል። በብላቴናይቱ ላይ ግን ምንም አታድርጉ በብላቴናይቱ ላይ ለሞት የሚያበቃ ኃጢአት የለባትም፤ ሰው በባልንጀራው ላይ ተነሥቶ እንደሚገድለው ይህ፤ ነገር ደግሞ እንደዚሁ ነውና፤በሜዳ ባገኛት ጊዜ የታጨችው ልጃገረድ ጮኻለችና፥ የሚታደጋትም አልነበረምና።ማናቸውም ሰው ድንግልና ያላትን ያልታጨች ልጃገረድ ቢያገኝ፥ ወስዶም ቢደርስባት፥ ቢያገኙትም፥ ያ የደረሰባት ሰው አምሳ የብር ሰቅል ለብላቴናይቱ አባት ይስጥ፤ አስነውሮአታልና ሚስት ትሁነው፤ በዕድሜውም ዘመን ሁሉ ሊፈታት አይገባውም።>> (ዘዳግም 22፡ 28-29)

<<ሰውነታቸውንም ደስ ባሰኙ ጊዜ ወስላቶች የሆኑ የከተማው ሰዎች ቤቱን ከበቡ በሩንም ይደበድቡ ነበር፤ ባለቤቱንም ሽማግሌውን። ወደ ቤትህ የገባውን ሰው እንድንደርስበት

Created in Master PDF Editor

አውጣልን አሉት። ባለቤቱም ሽማግሌው ወደ እነርሱ ወጥቶ። ወንድሞቼ ሆይ፥ ይህን ክፉ ነገር፥ እባካችሁ፥ አታድርጉ፤ ይህ ሰው ወደ ቤቴ ገብቶአልና እንደዚህ ያለ ኃጢአት አትሥሩ። ድንግል ልጄና የእርሱም ቁባት፥ እነሆ፥ አሉ፥ አሁንም አወጣቸዋለሁ፤ አዋርዱአቸው እንደ ወደዳችሁም አድርጉባቸው፤ ነገር ግን በዚህ ሰው ላይ እንደዚህ ያለ ኃጢአት አታድርጉ አላቸው። ሰዎቹ ግን ነገሩን አልሰሙም፤ ሰውዮውም ቁባቱን ይዞ አወጣላቸው፤ ደረሱባትም፥ ሌሊቱንም ሁሉ እስኪነጋ ድረስ አመነዘሩባት፤ ጎህ በቀደደም ጊዜ ለቀቁአት። ሴቲቱም ማለዳ መጣች፥ ጌታዋም ባለበት በሰውዮው ቤት ደጅ ወድቃ እስኪነጋ ድረስ በዚያ ቀረች። ጌታዋም ማለዳ ተነሣ የቤቱንም ደጅ ከፈተ፥ መንገዱንም ለመሄድ ወጣ፤ እነሆም ቁባቲቱ ሴት በቤቱ ደጃፍ ወድቃ፥ እጅዋም በመድረክ ላይ ነበረ። እርሱም። ተነሺ፥ እንሂድ አላት፤ እርስዋ ግን ሞታ ነበርና አልመለሰችም፤ በዚያን ጊዜ በአህያው ላይ ጫናት፥ ተነሥቶም ወደ ስፍራው ሄደ።>> (ዘፍጥረት 9: 4-8)

<<ሴት ልጅ ለአባቷ የተሠወረ ቁርጥማት ናት አሷን ማሰብ እንቅልፍ ያሳጣዋል። (መጽሐፈ ሲራክ 42.9) “ከልብስ ብል ይገኛል፤ ኃጢያትም ሁሉ ከሴቶች ይገኛል” (መጽሐፈ ሲራክ 42:13-14)“በሦስት ነገር ምድር ትናወጣለች፥ አራተኛውንም ትሸከም ዘንድ አይቻላትም። ባሪያ በነገሠ ጊዜ፣ ሰነፍም እንጀራ በጠገበ ጊዜ፥ የተጠላች ሴት ባል ባገኘች ጊዜ፥ ሴት ባሪያም እመቤቷን በወረሰች ጊዜ።”>> (ምሳሌ 30፡21-23)

<<ሴት ፈሳሽ ነገር ቢኖርባት በሥጋዋም ያለው ፈሳሽ ነገር ደም ቢሆን፥ በመርገምዋ ሰባት ቀን ትቀመጣለች የሚነካትም ሁሉ እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው።መርገምም ስትሆን የምትተኛበት ነገር ሁሉ ርኩስ ነው የምትቀመጥበትም ነገር ሁሉ ርኩስ ነው። መኝታዋንም የሚነካ ሁሉ ልብሱን ያጥባል፥ በውኃም ይታጠባል፥ እስከ ማታም ድረስ ርኩስ ነው። የምትቀመጥበትንም ነገር ሁሉ የሚነካ ሁሉ ልብሱን ያጥባል፥ በውኃም ይታጠባል፥ እስከ ማታም ርኩስ ነው።>> (ኦሪት ዘሌዋውያን 15፡19-22)

<<ወንድማማቾች በአንድነት ቢቀመጡ፥ አንዱም ልጅ ሳይኖረው ቢሞት፥ የሞተው ሰው ሚስት ሌላ ሰው ታገባ ዘንድ ወደ ውጭ አትሂድ፤ ነገር ግን የባልዋ ወንድም ወደ እርስዋ ገብቶ እርስዋን ያግባ፥ ከእርስዋም ጋር ይኑር። የምዋቹ ስም ከእስራኤል ዘንድ እንዳይጠፋ ከእርስዋ የሚወለደው በኵር ልጅ በሞተው በወንድሙ ስም ይጠራ።>> (ዘዳግም 25፡5-7)

በክርስትና ታሪክ ማንም ቅድስት ለዋና ሐዋርያነት አልተመረጠችም፣ ማንም ቅድስት ከቅዱሳን መፅሐፍት አንዱን አልፃፈችም፣ አንድም ቅድስት እንደ አብርሃም፣ ያዕቆብ፣ ይስሀቅ፣ ሙሴ፣ ዳዊት፣ ሰለሞን..... ጳውሎስ፣ ጴጥሮስ፣ .... ቅርብ ግንኙነት ወይም ቃል ኪዳን አልተገባለትም። ሁሌም ሴቶች የማገዝና ብዙ ጊዜ ደግሞ የማጥፋት ተልዕኮ ተሰቷቸው ይገኛል። በጣት የሚቆጠሩ ሴቶች ብቻ በመፅሐፍ ቅዱስ መልካም ዝና ተጎናፅፈዋል። እነሱም በከፊል ለመጥቀስ ያህል የአብርሃሟ ሳራ፣ አስቴርና የአዲስ ኪዳኖቹ ማርያሞች ናቸው። ሌላው ግን በወንድ የበላይነት የተሞላ ነው። የሚያሳዝነው አለመከበራቸውና እኩል አለመሆናቸው ብቻ ሳይሆን እንደ ሙሉ ሰው አለመቆጠራቸው ነው።

Created in Master PDF Editor

ይህ የፍቅር አምላክ ሴቶችን እንዲህ ነው የሳላቸው፣ እንዲህ ነው ያከበራቸው፣ እንዲህ ነው ፍቅር ያሳያቸው።ታድያ ጤነኛ አዕምሮ ያላት ሴት ለምን ብላ ለምን አትጠይቅም? ብዙዎች ጠይቀውዋል ነጻነትም ወተዋል። በዙዎቹ ግን የቅዱሱን መፅሃፍ የተቃወሙብትና ወንዳዊ አማልዕክትን የተበቀሉብት ስልት አስፈሪ ነው። በተለይ የሴቶች መገለጫ የሆነውን ውበት በመጠቀም ምድርን በወሲብ እየናጧት ነው። ወሲብ ተገቢና መብት ቢሆንም ወንዶችን ታላቅ ማግኔቲክ ሃይል ያለውን ስስ ገላቸውን በማሳየት የወንዶችን ህሊና መግዛትና ለልቅ ወሲባዊ ግንኙነት ማነሳሳት ጥቃት ማድረስ ነው። ይህ አስገድዶ የመድፈር ሙከራ ነው። ይህን የተረዳው ሊዮ ቶልስቶይእንዲህ ይላል፦ “ሴቶችን በሴተኛ አዳሪዎች አለባበስ ሳያቸው እሸበራለሁ፤ በዚህ ወቅት የሆነ አደጋ እንደተጋረጠብኝ ይሰማኛል፤ እናም ይሄ አደጋ ከኔ ይርቅ ዘንድ ውስጤ ፖሊስ ጥራ ፖሊስ ጥራ ይለኛል፤ ሆኖም ግን ይሄንን አደጋ ህግ አያውቀውም። ከመቆመርና በአደባባይ ወሲብ ቀስቃሽ ልብሶችን ከመልበስ ይበልጥ አደገኛው የቱ ነው ይበልጥ አደገኛ የሆነው የሴቶች ወሲብ ቀስቃሽ አለባበስ ሆኖ ሳለ ህግ ግን የሚከለክለው መቆመርን ነው።” (ፍልስፍና 1፣ 9ኛ ዕትም፣ 143) ማንም መካድ የማችለው ሴት ውበቷን ለጥፋት ከተጠቀመችበት ወንድን ባርያ ማድረግ ትችላለች። ይልቁንም ወንዶች ወንዳዊ አማልዕክትን ትተው ሴቶችን እንዲያመልኩ ማድረግ ይችላሉ። ውበት ሀይል ነው፣ ታላቅ የስበት ሀይል።ሴቶች የውበት አማልዕክት ናቸው። ጥበብም የሴቶች ውበት ታመልካለች።

> ክርስትና፣ ሴቶች ዋጋው እጅግ በከበረ ልብስ እንዲታዩ አልፈቅድም ቢልምና እስልምናም ሴቶች የውስጥ ጌጦቻቸውን በአደባባይ አይገልጡ ቢልም፤ ዘመናዊ ሴቶች ግን በበዛ ቁሳዊ ተጠቃሚነትና በወሲብ ቀሳቃሽ አለባበስ አማካኝነት ሲቸቁናቸው የነበረውን ወንዳዊና ሃይማኖታዊ ስርዓት እየተበቀሉ ነው። ሃይማኖታዊውና ወንዳዊው ስልጣኔ በተለየም ሴቶች ላይ ያሳደረው ጫና የበረታ ስለነበር ሴቶች ይሄንን መነኩሴያዊ ስልጣኔ ለመበቀል በቁሳዊው ዓለም በማመለል የመጀሪያዎቹ ናቸው። ቅዱስ ጳውሎስ፣ "ሴቶች በሹሩባና በወርቅ ወይም በዕንቁ ወይም ዋጋው እጅግ በከበረ ልብስ እንዲታዩ አልፈቅድም" (1ጢሞ 2፣10) ቢልም፤ በእስልምናም (ሴቶች) አይኖቻቸውን ይከለክሉ፣ ብልቶቻቸውንም ይጠብቁ፣ ጌጣቸውንም ከእርሷ ግልፅ ከሆነው በስተቀር አይገልጡ፤ ጉፍታዎቻቸውንም በአንገትጌዎቻቸው ላይ ያጠፉ፣ የውስጥ ጌጦቻቸውንም ለባሎቻቸው ወይም ለቅርብ ዘመዶቻቸው ካልሆነ በስተቀር አይግለጡ። (አል-ኑር 31) ቢባልም ሴቶች ግን ውድና ዘመናዊ በሆኑ አልባሳት፣ በመዋቢያ ቅባቶችና ቁሳቁሶች እንዲሁም በተለያዩ ፋሽኖች፣ የፀጉር ስታይሎች በመግለልና በብዛትም በመጠቀም ለዘመናት ሲጨቁኗቸው የነበሩትን አስተምህሮዎች እየተቀበሉ ነው። (ፍልስፍና 2፣ 3ኛ ዕትም፣ 177-182)

Created in Master PDF Editor

ሴት መሆን በራሱ ውበት ነው! እንደያው እንደምሳሌ እንኳ ብናነሳው ባለቅኔዎች ስለወንድ ልጅ ፍቅር ይጽፉ ይሆናል እንጂ ስለውበቱ ስንኝ አያባክኑም፡፡ ስለሴት ልጅ ውበት ያልገጠመ ባለቅኔ ግን ባለቅኔ የሆነም አይመስለው፡፡ በውቀቱ ስዩም በኗሪ አልባ ጎጆዎች ውስጥ ‹‹ብታውቂ›› ብሎ የጻፋትን እናስታውስ፡-

ስትሥቂ!

ጠፈርን እንደምታደምቂ

መንፈስን ካዚም እስራት

እንደምታላቅቂ

ብታውቂ!

ስትስሚ!

አጥንት እንደምታለመልሚ

ታማሚ ልብ እንደምታክሚ

ብታውቂ!

ስታወሪ!

ዱዳ እንደምታናግሪ

መነኩሴውን ከሱባኤ፣

ፈላስፋውን ከጉባኤ

እንደምትጠሪ

ብታውቂ! ...

❖ **ስለ ባርነት**

<<ዕብራዊ ባሪያ የገዛህ እንደሆነ ስድስት ዓመት ያገልግልህ፥ በሰባተኛውም በከንቱ አርነት ይውጣ፡፡ ብቻውን መጥቶ እንደሆነ ብቻውን ይውጣ፤ ከሚስቱ ጋር መጥቶ እንደሆነ ሚስቱ ከእርሱ ጋር ትውጣ፡፡ ጌታው ሚስት አጋብቶት እንደ ሆነ ወንዶች ወይም ሴቶች ልጆች ብትወልድለት፥ ሚስቱና ልጆችዋ ለጌታው ይሁኑ፥ እርሱም ብቻውን ይውጣ፡፡ ባሪያውም፡፡ ጌታዬን ሚስቴን ልጆቼንም እወድዳለሁ፥ አርነት አልወጣም ብሎ ቢናገር፥ ጌታው ወደ ፈራጆች ይውሰደው፥ ወደ ደጁም ወደ መቃኑ አቅርቦ ጆሮውን በወስፌ ይብሳው፤ ለዘላለምም ባሪያው ይሁን፡፡>> (ዘጸአት 21: 2-6)

<<ሰውም ሴት ልጁን ለባርነት ቢሸጥ ባሪያዎች እንደሚወጡ እርስዋ አትውጣ፡፡ጌታዋን ደስ ባታሰኘው በምጃ ይስደዳት፤ ስለ ናቃት ለሌላ ወገን ሰዎች ይሸጣት ዘንድ አይገባውም፡፡ ለልጁም

Created in Master PDF Editor

ብድራት፥ ለሴት ልጆች የሚገባውን ያድርግላት። ከእርስዋ ሌላም ቢያጋባው፥ መኖዋን ልብስዋንም ለምንጣፍዋም ተገቢውን አያጕድልባት።ይህንም ሦስት ነገር ባያደርግላት ያለ ገንዘብ በከንቱ ትውጣ።>> (ዘጸአት 21: 7-11)

<<ሰውም ወንድ ባሪያውን ወይም ሴት ባሪያውን በበትር ቢመታ፥ ቢሞትበትም፥ ፈጽሞ ይቀጣ፣ የተመታው ግን አንድ ወይም ሁለት ቀን ቢቈይ ገንዘቡ ነውና አይቀጣ። (ዘጸአት 21: 20-21) ሰውም የባሪያውን ወይም የባሪይይቱን ዓይን ቢመታ ቢያጠፋውም፥ ስለ ዓይኑ አርነት ያውጣው። የባሪያውን ወይም የባሪያይቱን ጥርስ ቢሰብር፥ ስለ ጥርሱ አርነት ያውጣው።>> (ዘጸአት 21: 26-27)

<<ባሪያዎች ሆይ፥ ለክርስቶስ እንደምትታዘዙ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ በልባችሁ ቅንነት በሥጋ ጌቶቻችሁ ለሆኑ ታዘዙ፤የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያደርጉ እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች እንጂ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ አትሁኑ።ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምትገዙ በትጋትና በበጎ ፈቃድ ተገዙ፤ ባሪያ ቢሆን ወይም ጨዋ ሰው፥ እያንዳንዱ የሚያደርገውን መልካም ነገር ሁሉ ከጌታ በብድራት እንዲቀበለው ታውቃላችሁና። እናንተም ጌቶች ሆይ፥ ዛቻውን ትታችሁ እንዲሁ አድርጉላቸው፥ በእነርሱና በእናንተ ላይ የሚገዛው ጌታ በሰማይ እንዳለ ለሰው ፊትም እንዳያደላ ታውቃላችሁና። (ኤፌሶን 6: 5-9)ባሪያዎች ሆይ፥ በቅን ልብ ጌታን እየፈራችሁ እንጂ፥ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ ሳትሆኑ፥ በሥጋ ጌቶቻችሁ ለሆኑ በሁሉ ታዘዙ።>>(ቆላስይስ 3:22)

<<የእስራኤልም ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን ነገር አደረጉ፥ አምላካቸውንም እግዚአብሔርን ረስተው በኣሊምንና አስታሮትን አመለኩ።ስለዚህ የእግዚአብሔር ቍጣ በእስራኤል ላይ ነደደ፥ በመስጴጦምያ ንጉሥ በኵሰርሰቴም እጅ አሳልፎ ሰጣቸው፤ የእስራኤልም ልጆች ለኵሰርሰቴም ስምንት ዓመት ተገዙለት።(መሳፍንት 3: 7-8) "የእስራኤልም ልጆች በእግዚአብሔር ፊት እንደ ገና ክፉ ሥራ ሠሩ፤ በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ ስለ ሠሩ እግዚአብሔር የሞዓብን ንጉሥ ዔግሎምን በእስራኤል ላይ አበረታባቸው። የአሞንን ልጆችና አማሌቅን ወደ እርሱ ሰበሰበ፤ ሄዶም እስራኤልን መታ፥ ዘንባባም ያለባትን ከተማ ያዙአት። የእስራኤልም ልጆች ለሞዓብ ንጉሥ ለዔግሎም አሥራ ስምንት ዓመት ተገዙለት።" (መሳፍንት 3: 12-14) "የእግዚአብሔርም ቍጣ በእስራኤል ላይ ነደደ፥ በፍልስጥኤማውያንና በአሞን ልጆች እጅ አሳልፎ ሰጣቸው። በዚያም ዓመት የእስራኤልን ልጆች ሥቃይ አበዙባቸው፤ በዮርዳኖስ ማዶ በአሞራውያን አገር በገለዓድ ውስጥ ያሉትን የእስራኤልን ልጆች ሁሉ አሥራ ስምንት ዓመት ተጋፉአቸው።">> (መሳፍንት 10: 7-8)

ባርነት በእግዚአብሔር የተፈቀደ ቅዱስ ተግባር እንደሆነ ሲሰብኩ የኖሩት ሰባኪዎች ዛሬ ዛሬ ርዕስ ቀይረዋል፣ መጽሃፉ ግን ዛሬም ያው ነው። የባርያ ንግድን ሲያጦፉት የነበሩት የካቶሊክ ቤ/ን ቡርጃዎች ምን ይሉ ይሆን? የባርያ ንግድን ለማስቆም በተደረገው ትግል ውስጥ ትልቁ ፈተና መጽሃፍ ቅዱስ እንደነበር ታሪክ ያስታውሳል። ባርነትን የሚፍቅድ አምላክ ፍቅር ከተባለ የማይፈቅዱት ምን ሊባሉ ይሆን?

Created in Master PDF Editor

❖ ዘረኝነት

<<እግዚአብሔርም አብራምን አለው። ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ። ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን፤ የሚባርኩህንም እባርካለሁ፥ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤>> (ዘፍ 12: 1-3)

<<ቍላው የተቀጠቀጠ ብልቱም የተቈረጠ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ።ዲቃላ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ፤ እስከ አሥር ትውልድ ድረስ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ።>> (ዘዳግም 23፡1-2)

<<አምላካችንም እግዚአብሔር እርሱን አሳልፎ ሰጠን፤ እርሱንም ልጆቹንም ሕዝቡንም ሁሉ መታን። በዚያን ጊዜም ከተሞቹን ሁሉ ወሰድን የተቀመጡባቸውንም ሰዎች ሁሉ ሴቶችንም ሕፃናቶችንም አጠፋን፤ አንዳችም አላስቀረንም፣ ከብቶቻቸውንና ከከተሞቻቸው ያገኘነውን ብዝበዛ ለራሳችን ወሰድን እንጂ።>> (ዘዳ 2: 33-35)

<<አምላክህም እግዚአብሔር በእጅህ አሳልፎ የሚጥላቸውን አሕዛብን ሁሉ ታጠፋቸዋለህ፤ ዓይንህም አታዝንላቸውም፤ ያም ወጥመድ ይሆንብሃልና አማልክቶቻቸውን አታምልካቸው። በልብህም እነዚህ አሕዛብ ከእኔ ይልቅ ይበዛሉና አወጣቸው ዘንድ እንዴት እችላለሁ? ብትል፥ አትፍራቸው፤ ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር በፈርዖንና በግብፅ ሁሉ ያደረገውን፥ አምላክህ እግዚአብሔር፥ ዓይንህ እያየች፥ ታላቅን መቅሠፍት ምልክትንም ተአምራትንም የጸናችውን እጅ የተዘረጋውንም ክንድ አድርጎ እንዳወጣህ፥ አስብ፤ እንዲሁ አምላክህ እግዚአብሔር አንተ በምትፈራቸው በአሕዛብ ሁሉ ላይ ያደርጋል። ደግሞም አምላክህ እግዚአብሔር የቀሩት ከፊትህም የተሸሸጉት እስኪጠፉ ድረስ ተርብ ይሰድድባቸዋል። አምላክህ እግዚአብሔር፥ ታላቅና የሚያስፈራ አምላክ፥ በመካከልህ ነውና ከእነርሱ የተነሣ አትደንግጥ።>>(ዘዳ 7: 16-21)

<<አምላክህ እግዚአብሔር ትወርሳቸው ዘንድ የምትሄድባቸውን አሕዛብን በፊትህ ባጠፋ ጊዜ፥ አንተም በወረስሃቸው ጊዜ፣ በምድራቸውም በተቀመጥህ ጊዜ፥ ከፊትህ ከጠፉ በኋላ እነርሱን ለመከተል እንዳትጠመድ።>> (ዘዳ 12: 29-30)

<<ለመዋጋት ወደ አንዲት ከተማ በደረስህ ጊዜ አስቀድመህ በዕርቅ ቃል ጥራቸው። የዕርቅ ቃልም ቢመልሱልህ ደጅም ቢከፍቱልህ፥ በከተማ ውስጥ ያለው ሕዝብ ሁሉ ይገብሩልህ ያገልግሉህም። የዕርቅ ቃልም ባይመልሱልህ ከአንተም ጋር መዋጋት ቢወድዱ፥ አንተ ከተማይቱን ትከብባለህ ታስጨንቃትማለህ፤አምላክህም እግዚአብሔር በእጅህ አሳልፎ በሰጣት ጊዜ፥ በእርስዋ ያሉትን ወንዶች ሁሉ በሰይፍ ስለት ትገድላቸዋለህ፤ ነገር ግን ሴቶቹንና ሕፃናትን እንስሶቹንም በከተማይቱም ያለውን ምርኮ ሁሉ በዝብዘህ ለአንተ ትወስዳለህ፤ አምላክህም እግዚአብሔር የሚሰጥህን የጠላቶችህን ምርኮ ትበላለህ።>> (ዘዳ 20: 10-14)

<<የአምላክህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ብትጠብቅ፥ በመንገዱም ብትሄድ፥ እግዚአብሔር እንደ ማለልህ ለእርሱ የተቀደሰ ሕዝብ አድርጎ ያቆምሃል። የምድር አሕዛብም ሁሉ የእግዚአብሔር ስም በአንተ ላይ እንደ ተጠራ አይተው ይፈሩሃል።>> (ዘዳ 28: 9-10)

Created in Master PDF Editor

<<ሕዝቡም ጮኸ፥ ካህናቱም ቀንደ መለከቱን ነፉ፤ ሕዝቡም የቀንደ መለከቱን ድምፅ በሰሙ ጊዜ ታላቅ ጩኸት ጮኸ፥ ቅጥሩም ወደቀ፤ ሕዝቡም ሁሉ እያንዳንዱ አቅንቶ ወደ ፊቱ ወደ ከተማይቱ ወጣ፥ ከተማይቱንም ወሰዱ:: በከተማይቱም የነበሩትን ሁሉ፥ ወንዱንና ሴቱን፥ ሕፃኑንና ሽማግሌውን፥ በሬውንም በጉንም አህያውንም፥ በሰይፍ ስለት ፈጽመው አጠፉ::>>(ኢያሱ 6: 20-21)

<<እንዲህም ሆነ፤ እስራኤልን ሊያሳድዱ ሄደው የነበሩትን የጋይን ሰዎች ሁሉ በሜዳና በምድረ በዳ ከገደሉአቸው በኋላ፥ እነርሱም በሰይፍ ስለት እስኪያልቁ ድረስ ከወደቁ በኋላ፥ እስራኤል ሁሉ ወደ ጋይ ተመለሱ፥ በሰይፍም ስለት መቱአት:: በዚያም ቀን የወደቁት ሁሉ ወንድም ሴትም የጋይ ሰዎች ሁሉ አሥራ ሁለት ሺህ ነፍስ ነበሩ::ኢያሱም በጋይ የሚኖሩትን ሁሉ ፈጽሞ እስኪያጠፋ ድረስ ጦር የዘረጋባትን እጁን አላጠፈም:: ነገር ግን እግዚአብሔር ኢያሱን እንዳዘዘው ቃል የዚያችን ከተማ ከብትና ምርኮ እስራኤል ለራሳቸው ዘረፉ::ኢያሱም ጋይን አቃጠላት፥ እስከ ዛሬም ድረስ ድብድባና በረሃ ለዘላለም አደረጋት:: የጋይንም ንጉሥ እስከ ማታ ድረስ በዛፍ ላይ ሰቀለው፤ ፀሐይም በገባች ጊዜ ኢያሱ አዘዘ፥ ሬሳውንም ከዛፍ አወረዱት፥ በከተማይቱም በር አደባባይ ጣሉት፥ በላዩም እስከ ዛሬ ድረስ ያለውን ታላቅ የድንጋይ ክምር ከመሩበት::የዚያን ጊዜም ኢያሱ በጌባል ተራራ ላይ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር መሠዊያን ሠራ::>>(ኢያሱ 8: 24-30)

<<እግዚአብሔርም ኢያሱን:: በእጅህ አሳልፌ ሰጥቼአቸዋለሁና አትፍራቸው፤ ከእነርሱም አንድ ሰው የሚቋቋምህ የለም አለው:: ---- እግዚአብሔርም በእስራኤል ልጆች እጅ አሞራውያንን አሳልፎ በሰጠ ቀን ኢያሱ እግዚአብሔርን ተናገረ፤ በእስራኤልም ፊት እንዲህ አለ:: በገባዖን ላይ ፀሐይ ትቁም፥ በኤሎንም ሸለቆ ጨረቃ፤ ሕዝቡም ጠላቶቻቸውን እስኪበቀሉ ድረስ ፀሐይ ቆመ፥ ጨረቃም ዘገየ:: ይህስ በያሻር መጽሐፍ የተጻፈ አይደለምን? ፀሐይም በሰማይ መካከል ዘገየ፥ አንድ ቀንም ሙሉ ያህል ለመግባት አልቸኰለም:: (ኢያሱ 10: 8-13) እግዚአብሔርም ኢያሱን:: ነገ በዚህ ጊዜ ሁሉን እንደ ሞቱ አድርጌ በእስራኤል እጅ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁና አትፍራቸው፤ የፈረሶቻቸውንም ቋንጃ ትቈርጣለህ፥ ሰረገሎቻቸውንም በእሳት ታቃጥላለህ አለው::>>(ኢያሱ 11: 6)

<<የእስራኤል ሕዝብ ካህናቱም ሌዋውያኑም እንደ ከነዓናውያን እንደ ኬጢያውያን እንደ ፌርዛውያን እንደ ኢያቡሳውያን እንደ አሞናውያን እንደ ሞዓባውያን እንደ ግብጻውያንና እንደ አሞራውያን ርኵሰት ያደርጋሉ እንጂ ከምድር አሕዛብ አልተለዩም፤ለራሳቸውና ለልጆቻቸውም ሴቶች ልጆቻቸውን ወስደዋል፥ የተቀደሰውንም ዘር ከምድር አሕዛብ ጋር ደባልቀዋል፤ አስቀድሞም አለቆቹና ሹማምቶቹ በዚህ መተላለፍ መጀመሪያ ሆነዋል አሉኝ::ይህንም ነገር በሰማሁ ጊዜ ልብሴንና መጐናጸፊያዬን ቀደድሁ፥ የራሴንና የጢሜንም ጠጉር ነጨሁ፥ ደንግጬም ተቀመጥሁ::>>(ዕዝራ9: 1-3)

አለምን ለጥፋት ሲያጣድፏት ከኖሩትና ካሉት ውስጥ ዋናው ዘረኝነት ነው:: ለዚህ የናዚውን አለቃ ሂትለርን ማስታወስ በቂ ነው:: ምርጥ ዘር ነበር ሞፈክሩ:: እኔ እምለው ከሂትለርና ከእግዚአብሔር ማን ነው ዘረኛ? ይህን ሁሉ የተረዳው ደረጀ ፀጋዬ እንዲህ ነበር በአዲስ አድማስ ላይ የጻፈው “የናዚ ጀርመንን የተቀነባበረ የዘር

Created in Master PDF Editor

ማጥፋት ዘመቻና የሩዋንዳን ጅምላ ፍጅት የሰማ ጤነኛ ህሊና ያለው ሰው፤ ድርጊቱን እንደሚያወግዝ ጥርጥር የለውም፡፡ በመሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህንን የመሰሉ ብዙ ድርጊቶች ሞገስ ተላብሰው ተከትበዋል፡፡ ሌሎችም ብዙ ብዙ አሉ፡፡” (ደረጀ ፀጋዬ፣ የኢ-አማኒው ኑዛዜ) ይህን መረን የለቀቀ ስርዓት ለማውገዝ አይኑን ቀና የሚያደርግ ሙህር፣ ፖለቲከኛና አክቲቪስት ግን በሻማ ቢፈለግ ቢፈልግ ይገኝ ይሆን? መጽሃፍ ቅዱስንና ዘረኛ አምላክን ማውገዝ ቀይ መስመር ያደረገው ማን ነው?

❖ ስለ በቀል

<<እግዚአብሔርም በከተማይቱ በኢየሩሳሌም መካከል እለፍ፥ በመካከልዋም ስለ ተሠራው ርኵሰት ሁሉ በሚያለቅሱና በሚተክዙ ሰዎች ግምባር ላይ ምልክት ጻፍ አለው፡፡ እኔም እየሰማሁ ለሌሎቹ እርሱን ተከትላችሁ በከተማይቱ መካከል እለፉ ግደሉም፤ ዓይናችሁ አይራራ አትዘኑም፤ ሽማግሌውንና ጕበዙን ቈንጆይቱንም ሕፃናቶቹንና ሴቶቹን ፈጽማችሁ ግደሉ፤ ነገር ግን ምልክቱ ወዳለበት ሰው ሁሉ አትቅረቡ፤ በመቅደሴም ጀምሩ አላቸው፡፡ በቤቱም አንጻር ባሉ ሽማግሌዎች ጀመሩ፡፡ እርሱም ቤቱን አርክሱ፥ በተገደሉትም ሰዎች አደባባዮችን ሙሉ፤ ውጡ አላቸው፡፡ እነርሱም ወጥተው በከተማይቱ ገደሉ፡፡>> (ሕዝቅኤል 9: 4-7) በቃኝ! ስለበቀል ለመናገር እኮ ሲኦልን ማስታወስ በቂ ነው፡፡

በመጽሃፍት እንትአተረከው እግዚአብሔር ፍቅር ነው ለማለት የሚያስችል አስደሳች ዘገባ የለም፡፡ የፍቅር መጨረሻ እንደሆነ የሚነገርለት ክርስቶስ እንኳ ታሪኩ የሚጀምረው በኢ-ፍትሀዊ የህጻናት ሞት ነው፡፡ ከጌታ ልደት ጋር መርሳት የሌለበት የህፃናት እልቂት ታሪክ ነው፡፡ ሄሮድስ ጌታን ለማግኘት የብዙ ህፃነት ደም በማያውቁት ታሪክ ከእናታቸው ጡት እየተነቀሉ በሰይፍ ታርደዋል፡፡ ሰዎች ይህን ታሪክ እንዴት በልደት ሰሞን እንደማያስቡት ግራ ይገበኛል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሰማዕታት ተብለው ታቦት ተቀርፆላቸው፣ ድርሳን ተፅፎላቸው ሊከበሩ የሚገባቸው ነበሩ፡፡ የ “God is imaginary” ድህረ ገጽ መስራች ማርሻል ብሬን ግን ነገሩን በፀፀት መሆን አልነበረበትም ሲል አማራጭ መፍትሔዎችን ይጠቁማል፡፡

1. እግዚአብሔር ለሄሮድስ ተገልጦ ህፃናቱን እንዳይገድል መናገር
2. ሄሮድስ የማየሰማ ልበ ደንዳና እንኳ ቢሆን እራሱን መግደል (በኋላ እንደሆነው)
3. እግዚአብሔር ሰባ ሰገሎችን ወደ ሄሮድስ እንዳይሄዱ ማዘዝ
4. እግዚአብሔር ህፃናትን በታማራት ከሞት መታደግ
5. እግዚአብሔር ህፃናቱን ለገደሉት ወታደሮች እጆቻቸውን በህፃነቱ ላይ እንዳያነሱና የንጉሱን ትዕዛዝ እንዳይፈፅሙ ማድረግ
6. እግዚአብሔር ለህፃነቱ ወላጆች ተገልፆ እስከ ወላጆቻቸው ወደ ግብፅ እንዲሸሹ ማድረግ
7. ጌታ በተወለደበት ዘመን ወንድ ልጆች እንዳይወለዱ ማድረግ

Created in Master PDF Editor

8. ደንዳናው የስልጣን ጥም ያለበት ሄሮድስ ሲጀመር እንዳይነገስ ማድረግ ወይም ልበ ሙሉ ማድረግ ወዘተ... ግን ይህ ሁሉ ሃሳብ ለባለቤቱ አልመጣለትም::

17. **ሳይንስና ፍልስፍና አምላክ መኖሩን ያረጋግጣሉ**

<<የፍልስፍና እውቀት እየሰፋ ሲመጣ በሃይመኖትና በፖለቲካው እምነቶች ውስጥ የተደበቁ የስህተት አስተሳሰቦችና ውሸቶችን እየመረመረ ማጋለጥ ጀመረ:: በዚህ ጊዜ ውሸት ለረጅም ዘመናት ከእንቀላፋበት ደንብሮ ነቃ፤ የህልውናው መጨረሻ መሆኑን ሲረዳ እውነት የሚያስመስለውን የርዕዩተ ዓለም ካባ በማጥለቅ እመኑኝ እውነት ነኝ እያለ በእየ አደባባዮቹ መስበክ ጀመረ:: በጠንካራ የፍልስፍና አስተሳሰባቸው የተሟገቱትን ክርክራቸውን መቋቋም ሲሳነው ጉልበቱን የእውነቱ ማሳያ አድርጎ በመጠቀም ብዙዎችን በአሰቃቂ ሁኔታ እየገደለ የእፎይታ ጊዜ ማግኘት ቻለ:: በዚህ ሁኔታ ነው ጉልበታቸው እውነት የሆነላቸው ሁሉ የጉልበታቸውን ኃይል በፈላስፋዎች ላይ ማሳረፍ የጀመሩት፤ የግሪክ ፈላስፋዎችም ቀዳሚዎቹ ገፈት ቀማሾች ሆኑ::>>(ዋለልኝ እምሩ በፍልስፍና መደመም)

ሳይንስ የእግዚአብሔርን መኖር ያረጋግጣል ለሚሉ ሰዎች John Loftus <Why I Became an Atheist: A Former Preacher Rejects Christianity> በሚለው ድንቅ መጽሃፉ እውነቱ በተቃራኒው መሆኑንን ለማስረዳት የሚከተሉትን ምሳሌዎች ይጠቅሳል::

- ✓ *Astronomy tells us the universe is 13-15 billion years old and arose out of a cosmic singularity. No account of the development of this universe can be harmonized with the creation accounts in Genesis except that these accounts were pure mythic folklore.*
- ✓ *Archaeology shows us there isn't any evidence for Israelites being slaves in Egypt for four hundred years, or that they wandered in the wilderness for forty years, or that they conquered the land of Canaan.*
- ✓ *Geology confirms the slow evolutionary development of life in the sedimentary rock layers on a planet nearly five billion years old, just as astronomy confirms the slow evolutionary development of galaxy, star, and planet formation. Geology also disconfirms that there was a universal flood that covered the earth.*
- ✓ *Neurology confirms that strokes, seizures, and other illnesses stem from a brain malfunction and hence disconfirms that there is something called a mind or soul.*
- ✓ *Modern medicine has achieved astounding results that such superstitious practices like exorcisms, bloodletting, and supernatural healings are delusional.*

Created in Master PDF Editor

- ✓ *Psychology confirms that who we are and how we behave are determined to an overwhelming degree before we reach the age of accountability.*
- ✓ *The order of creation depicted in Genesis chapter 1 is totally out of sync with what cosmology teaches. InGenesis the earth existed first, then the universe of stars; there was plant life before the sun; afully formed man existed before there was a female, and so on*
- ✓ *The Copernican theory of the heliocentric universe defended by Galileo. Man was no longer the center of our particular solar system. The discovery that our solar system is not central to the Milky Way galaxy, but located on the periphery, out on a spiral arm. Man was not even central in his own galaxy. The discovery that our galaxy is only one of billions of galaxies. Man isn't even central to the universe as a whole. <u>We are insignificant</u>. The possibility that there are an infinite number of universes, called a multi- verse. God is no longer needed.*

ብዙ ሰዎች የሚያምኑትን የሚደግፈላቸው ጥናት ተገኘ ሲባል ጮቤ ይረግጣሉ። በሀይማኖቶችና በቅዱሳን መፅሀፍት የተካሄዱት ቁፋሮዎችና ምርምሮች ግን ውጤታማ አይደሉም፣ የተገኑት አንዳንድ ማስረጃዎችም ከሚታመነው በተለየ መልኩ ነው። የተሻለ አርጋጋጭ መፃህፍትን ሲፈለጉ ከአሁኖቹ ጋር የሚጠረሱና የተወገዙ ሁነው ይገኛሉ። የአራቱን ወንጌላውያን ቀደምት ፅሁፎች ሲፈለግ ሌላ ወንጌል እየተገኘ ችግር ሆኗል። ጥረቱ እንደቀጠለ ቢሆንም እምነትን በአርኬዎሎጅ ማፅናት ግን የማያዋጣ መንገድ ከሆነ ሰንብቷል። ይሁን እንጅ ሰባኪዎች የኖህ መርከብ ተገኘች፣ እግዚአብሔር ያጠፋቸው ከተሞች በቁፋሮ ተገኙ …. ወዘተ እያሉ ወሬ በመንዛት ላይ ናቸው። እውነት ለመናገር እንደ እርኬወሎጅ እምነትን የተገዳደረ የለም። ኦሪት ዘፍጥረትን ትረት ያደረገው እኮ አርኬወሎጅ ነው። በአርኬወሎጅ የተደረጉ የቁፋሮ ውጤቶች የሚያሳዩት ሰዎች ከብዙ ሽህ አመታት ጀምሮ ያመልኩ እንደነበር እንጅ የሚያመልኩት እውነት መሆኑን የሚያስረዳ ፍንጭ አላገኙም።

በነገራችን ላይ ብዙ መመራመርና መፈላሰፍ ክሃዲ አያደርግም። አንዳንድ ሳይንቲስቶችና ፈላስፎች እንደሚሉት ብዙ በተመራመሩና በተፈላሰፉ ቁጥር በፋጣሪ መኖር ያላቸው እምነት ይጨምራል። ሰባኪዎችም ለማመን የሚገፋፋትን ወይም አለማመንን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡትን አልያም ሳይንስ ያልፈታቸውን እንቆቅልሾች እንደ ምሳሌ በመጥቀስ ይሰብካሉ።በተለይ ሁለተኛውን የቴርሞዳይናሚክስ ህግ ዝግመተ ለውጥን ለማጣጣል ይጠሙበታል። በዝግመተ ለውጥ ቦታም ታስቦ የተመቻቸ (Fine-tuned) መላምልትን ይሰብካሉ።

ሁለንታ ለህይወት ሆን ተብሎ የመተቻቸና ሚስጥሩን ማንም ሊደርስበት በማይችል ጥበብ የተሰራ ውስብስብነቱን ሳይንስ ሊፈታው የማይችል ስለመሆኑ እና በተለይም

Created in Master PDF Editor

ውስብስብነት በአጋጣሚ ሊሆን እንደማይችል ለማስረዳት ጥያቄዎች ይቀርባሉ። እነሱም፦

1) አራቱ ሀይሎች(የግራቪቲ ሀይል፣ ኤሌክትሮ ማግኒቲክ ሀይል፣ ደካማውና ጠንካራው የኒውክለር ሀይሎች እንዴት ተመጥነው ተገኙ?
2) የመጨረሻው ትንሹ አካል አተም (Atom) የተገነባባቸው ሶስቱ ኤሌክትሮን፣ ፕሮቶን እና ኒውትሮን እንዴት ተመጥነውና ተቻችለው ሊገኙ ቻሉ?
3) አቶሞች ተሰባስበው እንዴት ንጥረ ነገሮችን ሊፈጥሩ ቻሉ?
4) ንጥረ ነገሮች በምን አጋጣሚ ተዋህደው እና ተዋደው ወይም ተጋጭተው ውህዶችን ሊፈጥሩ ቻሉ?
5) ውህዶች በምን አይነት መጣመር ህይወት ያለው ህዋስ(Cell) ሊሆኑ ቻሉ?
6) ህዋሶችስ በምን አይነት ቅንጅት ህብረህዋስ (Tissue) ሊሆኑ ቻሉ?
7) ህብረ ህዋሶችን ወደ ስርዓተ አከለት፣ ስርዓተ አካላትም ወደ መሉ አካልነት እንዴት አድርጉ?
8) ፍጥረትን ለምን እንዲህ ብዙ እና ልዩ ልዩ ሆነ?
9) መሬት ተመጣጣኝ ሙቀት እንዴት ሊኖራት ቻለ?
10) ውሃ እንዴት በሁሉም የመሬት ክፍል ሊገኝ ቻለ?
11) በከባቢ አየር ውስጥ የኮርቦን፣ የኦክስጅን፣ የሀይድሮችን እና የሌሎች ንጥረ ነገሮች በጣም ሳይበዛና በጣም ሳያንስ በልኬት ያስቀመጠው ማን ነው?
12) የህይወት መስረት የሆነው ፕሮቲን እንዴት ተቀመመ?
13) ታላቁ ቤተ መፅሀፍትና የመረጃ ማዕከል የሆነው DNA እንዴት ተገነባ? የመረጃውን ፍሰትስ ማን ፕሮግራም አደረገው?
14) የመሬት መጠን ሳይሰፍን ሳያንስ በልኬት ማን ስራው?
15) መሬት ከፀሐይ በትክክለኛው ርቀት እና በትክክለኛው የዙሪትና የእሽክርክሪት መስመር ላይ ትገኛለች። ይህ በአጋጣሚ ይሆናልን?
16) መሬት ከጨረቃ ጋር እና ከሌሎች ፕላኔቶች ጋር ያላት ርቀትና በትክክለኛው መንገድ የሃሳብ መስመር ላይ እንድትሆን አድርጓል እንዴት በአጋጣሚ ሊሆን ይችላል?
17) መሬት የምትዞረውና የምትሽከረከረው በትክክለኛው ፍጥነት እንዲሆን ማን አደረገ?
18) መሬትን ከህዋ ከሚወረውሩ አለቶች በታላቁ ጁፒተር እንድትጠበቅ ያደረገው ማን ነው?
19) የከባቢው አየር በአስፈለጊው መጠን እና ይዘት እንዲዋቀር ማን አደረገ?
20) የአየር እፍግታ ሳይበዛና ሳያንስ በተቀመረ ስሌት እንዴት ሊሆን ቻለ?
21) ድንቅ የሆነው ብርሃን አስተፃምሮ እንዴት ሊጀመር ቻለ?
22) ስርዓተ - ፀሀዮችና ጋላክሲዎች እንዴት ተመሰረቱ?
23) አንድ ነገር እንዴት ያለምንም አጋዥ ወደ ሌላ ነገር ይቀየራል?
24) ሁሉም ነገር እንዴት ስምምነት እና ስርዓተ (Order) ሊኖረው ቻለ?
25) ሳይንስ ያልደረሰበት ብዙ እውቀት ቢኖርም ደርሽበታለሁ በሚለው እንኳ ሚሰጠው መረጃ የመጨረሻ አይደለም። ታድያ ሳይንስን መተማመን ይገባልን?

Created in Master PDF Editor

26) በተፈጥሮ እና በሰው ህይወት ለመግለፅ የሚከብዱ ታምራት ይሰራሉ። የሁሉ ታምራትና ስራቶች ምንጫቸው ምንድን ነው?
27) በእውነት ሰው እንደ እንሰሳ ነውን? በውስጡስ ነፍስ የለውምን? ንቃተ ህሊናው የምን መገለጫ ነው?
28) የእምነቶች መሰረት የሆኑትን ታላላቅ ቅዱሳን መፅሐፍት የሰው ልጅ ሊፅፍላቸው ይችላልን?
29) ስነ ፍጥረት በተለይም ሰው ያለፈጣሪ እርዳታና መግቦት መኖር ይችላልን?
30) የስነ ዲዛይን፣ የስነ ኑባሬ፣ የስነ ፍጥረት፣ የስነ ባህሪ፣ የአስተርዮና የምቹነት ፍልስፍናዎችስ አምላክ መኖሩን አያስረዱምን?

ከላይ ከ1 -29 የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች 30ኛው ጥያቄ ይጠቀልላቸዋል።

የስነ-ዲዛይን ማስረጃ (Argument from design or teleological argument.)

1. አንድ ተግባር ያለው ነገር ካለ ያን እንዲተገበር አስቦ የሰራው አካል አለ ማለት ነው።
2. የፍጥረታትን ስሬት እና ሱደት ካየነ ለሆነ አላማ እንደተሰሩ ይመሰክራሉ። ለምሳሌ:- አይን ለማየት፣ ጆሮ ለመስማት፣ ወዘተ
3. ስለዚህ እያንዳንዱ ነገር ሲፈጠር በፈጣሪው ህልውና ውስጥ ታሳቢ የተደረገ ከሆነ ያን ያሰበው ፈጣሪ አለ ማለት ነው።
4. በተጨማሪም ፍጥረታት እጅግ ውስብስብ በመሆኑ ዲዛይኑን ያዘጋጀው ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ያስረዳል።
5. ስለዚህ ይህን ውስብስብና የሰው ልጅ ሊሰራው ቀርቶ ሊረዳው የማይችል ዲዛይን ያዘጋጀው ሁሉን ቻይ ፈጣሪ አለ ማለት ነው።

በእርግጥ ሁለንታ እና በውስጡ ያለው ነገር ስናስብ ዲዛይነሩ ከጀርባ እንዳለ ይገባናል። ነገር ግን አሁን ዘመኑ በደረሰበት የሳይንስ መረጃ መሰረት ይህን የሚገርም ድንቅ ነገር ዲዛይን ያደረገው ሳይንቲስቶቹ እውሩ ዲዛይነር (Blind watchmaker) የሚሉት ነው ማለትም ዝግመተ ለውጥ።

ስነ-ዲዛይንን ለማስረዳት በአንድ ኮምፒውተር አከፋፋይና በገዥው መካከል ሊደረግ የሚችል የግብይት ድርድርን ምሳሌ ላድርግ። አንድ የኮምፒውተር ሸማች ወደ አንድ የኮምፒውተር አከፋፋይ ጎራ ይልና ኮምፒውተር መግዛት እንደሚፈልግ፣ ምርጥ የሚባል ከሁሉም የኮምፒውተር ሞዴሎች የተሻለ ፍጥነት፣ ጥራት፣ ፋሽን፣ ምቹነት እና ዲዛይን ያለው ኮምፒውተር እንዲያቀርብለት ይጠይቀዋል። ሻጩም የደንበኛውን ፍላጎት ለማርካት እጅግ ልዩ ስለሆነ የኮምፒውተር ሞዴል ማውራት ጀመረ። ይህ ኮምፒውተር ሞዴል ብሎ ጀመረ። ይህ የኮምፒውተር ሞዴል ለአያያዝ ቀለላል ነው፣ ፍጥነቱን ልነግረህ አልችልም፤ ያልተገደበ ውስጣዊ ሚሞሪ አለው፤ ወ.ዘ.ተ ይህን

Created in Master PDF Editor

ኮምፒውተር ገዛህ ማለት ኑሮህን አቀለልክ፣ ሸክምህን አራገፍክ ማለት ነው። ዲዛያኑ የሚገርም የሚደንቅ ተአምር ነው። እጅግ ድንቅ በሆነ ጥንቃቄ የተመረተ ነው። የሚገርምህ ይህን ምርት ለማምረት እስከ 9 ወር ድረስ ይፈጃል። ከዚህ ተነስተህ ምን ያህል ጥንቃቄ እንደሚደረግበት መገንዘብ ትችላለህ። ስለምርቱ አንተ ራስህ ምስክር ትሆናለህ። ሻጩ እየማለ እየተገዘተ ገዡን ለማሳመን ይጥራል።

ይህን ሁሉ ሲሰማ የቆየው ሸማች እንዲህ ሲል ጠየቀ "ምን አልባት አንዳንድ ችግሮች፣ ተጋላጭነቶች፣ አስቸጋሪ ባህሪያትና ድግመቶች ይኖሩበት ይሆን?" ሻጩ የንግግር ፍጥነቱን ቀንሶ፣ አይኑን ወደ አንዴ ወደ መሬት አንዴ ወደ ሰማይ አንዴ ወደ ምርቶቹ እየተመለከተ ሀቁን መናገር ጀመረ።

በእርግጥ ምርቱ አሉ ከሚባሉት ሞዴሎች አንደኛ ደረጃ ነው ቢሆንም ጥቂት ችግሮች እንዳሉበት ግን አይካድም። ለምሳሌ ሁሌ ቻርጅ መሆን አለበት ያለባትሪ አይሰራምና፣ አንዳንዴ ቢዚ (ታማሚ) ሊሆን ይችላል፤ አንዳንዴ መረጃዎችን ሊደብቅ፣ ሊያጠፋ ወይም በስርዓት ላይከፍት ይችላል። አንዳንዴ የመቃጠል ወይም የመበላሸት አደጋ ሊደርስበት ይችላል። አንዳንዴ መደበኛ የሆነ መቼ ስርዓት ካልተፈጠረለት ተግባሩን ሊያስተጓጉል ይችላል። በተለይ ግን ለበርካታ ቫይረሶች እና ተያያዥ በሽታዎች ተጠቂ ነው አለና በረዥሙ ተንፍሶ ንግግሩን አበቃ።

ከግብይት ድርድሩ እንደምንረዳው ኮምፒውተሩ የተሰራው ፍጹም በሆነ ዲዛይነር አይደለም። ፍጹም በሆነ ዲዛይነር ቢሰራ ኑሮ ባትሪ አያስፈልገውም ነበር፣ ብልሽትም አይደርስበትም ነበር፣ በአግባቡ ለመስራት ቅደመ ሁኔታዎችን አያስቀምጥም ነበር በተለይም ለበሽታ የማይጠቃ ይሆን ነበር። የሰው ልጅና የጠቅላላው የስነ ፍጥረት ታሪክም የሚያስረዳን ይህን ነው። በኢንተለጀንት ዲዛይነር ሳይሆን በአን-ኢንተለጀንት ዲዛይነር ዲዛይን መደረጉን።

ማነው ፈፅሞ ዲዛይን? ማንም። አንኢነተለጀንት ዲዛይነር (ዝግመተ ለውጥ) ስህተቶቹን ያለማቋረጥ እያሻሻለ የሚሄድ ቢሆንም ከስተቶቹ ብዛት አንጻር ፍጹም ሊሆን አይችልም። የዝግመተ ለውጥ ዲዛይን ውብ ቢሆንም እልቆ ቢስ ግድፈቶችና ድክመቶች አሉበት። በእያንዳንዱ ድንቅ ስነ ፍጥረት ውስጥ መሆን የነበረበት ብዙ ነገር ጎሏል። በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ ፍትህአዊ አይደለም። ለምሳሌ፡- አንዱን መልከ መልካም፣ አንዱን መልከ ጥፉ፣ አንዱን ጤነኛ ሌላውን በሽተኛ፣ አንዱን በተለመደው አበባል ባለሙሉ አካል ሌላው በሙሉ ወይም የሆኑ አካላት የጎደሉት አድርጎ ይሰራል። በስነ ፍጥረት የበዛ የፍትሐዊነት ችግር አለ። አንዱ በሰማይ እየበረረ አንዱ በምድር ይኳትናል። አንዱ 60 ኪ.ሜ በሰዓት ሲፈረጥጥ አንዱ በሰዓት 60 ሜትር ለመጓዝ ያደግተዋል። አንዱ ከተማ መስርቶ ሰልጥኖ ሲኖር ሌላው በዛፍ በገደሉ በጥሻ በጉድጓዱ ሳይበራለት ይኖራል። ኸረ ስንት ኢ-ፍትሐዊነት አለ።

Created in Master PDF Editor

ኢን-ኢንተለጀንት ዲዛይነር ምንም ቢያጠፋ ሊከሰስ ሊገረሰስ አይችልም። ምክንያቱም ምን እየሰራ እንደሆነ እራሱም አያውቅምና። አንኢነተለጀንት ዲዛይነር እብድ ነው እብድን ማን ይከሳል። ተፈጥሮን አሰቡት፣ ሁለንታን አሰቡት፣ ህይወትን አስቡት የእብት ውጤት ነው። እብድ ግድ የለውም፣ እብድ ይሉኝታ የለውም፣ እብድ ፅድቅና ኩነኔ አይገባውም፣ እብድ መልካምና ክፉ ለይቶ አያውቅም፣ እብድ እብድ ነው። ዝግመተ ለውጥ እብድ ነው። ይሉኝታ የለውም፣ ፍቅር አይገባውም፣ የነበረው ያለውና የሚመጣውም ምንም ነው። ለዝግመተ ለውጥ ህያወት ትርጉም የለውም።

ተፈጥሮ ያለምንም ርህራሄ ፍጥረታትን በቅፅበት ዶግ አመድ ታደርጋለች። በወረርሽኝ ምክንያት ሚሊዮኖች ቢሞቱ ለተፈጥሮ ዴንታ አይሰጣትም። እንኳን ሚሊዮኖች ጠቅላላ ስነ-ፍጥረት እንደ ኢምንት ነው። በዚህ ሁሉ ግፍ መሀል አንድ ተስፋ ሰጭ ጉዳይ አለ። ዝግመተ ለውጥ ስነ-ፍጥረትን ከተፈጥሮ ጋር ለማስታረቅ ሁሌ ይጥራል። በተለይ የአካል ለውጦችን፣ የአካባቢ መለመድና መመሳሰል ልምምዶችን፣ የዝርያ መሻሻሎችን፣ ልዩ ክህሎቶችን እና ጥበቦችን የማዳበር ስርዓቶች መኖራቸው መልካም የሚያስብል ነው።

ስነ-ኑባሬ ማስረጃ (Ontological Argument)

1. ህልውና የሌለው ነገር ልናስብ አንችልም።
2. ስለዚህ ስለ እግዚአብሔር ካሰብና ይኖራል ማለት ነው።
3. እግዚአብሔር የለም ብለን እንኳ ብናስብ መኖርን በከፊል እየመሰከርን ነው።
4. እግዚአብሔር የለም ብሎ ማሰብ የለም ማለት አይደለም።
5. እናም እግዚአብሔር አለ።

ይህ የስነ-ኑባሬ ማስረጃ በፈለሰፋው ኢማኑኤል ካንት ውድቅ ከተደረገ ቢቆየም ዛሬም እንደ ማስረጃ መጠቀሱ አልቀረም። እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ ሀሳቦች (Premise) እንዳሉት ሆኖ ማስረጃው ከመሰረቱ ህልውና የሌለው ነገር ልናሰብ አንችል ብሎ መጀመሩ ብቻ ውድቅ እንዲሆን ያደርገዋል። የሰው ልጅ ቅንጭላት በእየቀኑ ህልውና የሌላቸው ነገሮችን(ፈጣሪን ጭምር) ያስባል። ደራሲዎች የፈጠሯቸው ገፀ ባህሪያት እውን ናቸውን? የፍቅር እስከ መቃብሮቹ፣ የዶርቶጋዳዎቹ፣ እንዲሁም በሌሎች ተወዳጅ ድርሰቶች የምናውቃቸው ገጸ-ባህርያት እውን ናቸውን?

የስነ- ፍጥረት ማስረጃ (Consmological-The first causeargument)

1. ሁሉም ነገር መነሻ(መንስኤ) አለው።
2. ሁለንታ በሙሉ መንስኤ አለው።
3. ምንም ነገር ለራሱ መንስኤ ሊሆን አይችልም
4. ሁለንታም እራሱን አያስገኝም።

Created in Master PDF Editor

5. ስለዚህ ሁለንታን ያስገኘ ከሁለንታ ውጭ የሆነ አካል አለ፡፡
6. ከሁለንታ ወጭ ሊኖር የሚችል ደግሞ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡
7. ስለዚህ ሁለንታን ያስገኘው(የፈጠረው) እግዚአብሔር ነው፡፡
8. ስለዚህ እግዚአብሔር አለ፡፡

በዚህ የኮስሞሎጂካል ማስረጃ ላይ ጉድለቶች አሉበት፡፡ አንደኛ ነገር ቁጥር 1 ሁሉም ነገር መንስኤ ያስፈልገዋል እና ቁጥር 3 ማንም እራሱን አያስገኝም ይላሉ፡፡ እናማ ሁሉም ነገር አስገኝ ካስፈለገው እግዚአብሔርን ማን አስገነው፣ እራሱን አስገኘ እንዳንል ማንም እራሱን አያስገኝም ብለናልና፡፡ አይ እግዚአብሔር አስገኝ አያስፈልገውም ካልን ሁለንታም አስገኝ ላያስፈልገው ይችላል፡፡ ሳይንቲስቱ እስቴፈን ሀውኪንግ ምን ነበር ያለው፦ “When people ask me if a God created the universe, I tell them that the question itself makes no sense. Time didn’t exist before the Big Bang so there is no time for God to make the universe in.” (Brief answer to big questions)

ሁለተኛ ነገር በቁጥር 5 ላይ ሁለንታን ያስገኘው ከሁለንታ ውጭ የሆነ አካል ነው የሚል ድምዳሜ አለው፡፡ ከሁለንታ ውጭ የሚኖር ማለት ምን ማለት ነው? ይህን ማለት የተፈለገበት ምክንያት ከጊዜና ከቦታ ውጭ ነው ለማለት ነው፡፡ ግን ምንም ይሁን ምንም ከጊዜና ከቦታ ውጭ የሚሆን ነገር የለም፡፡ የሆነ ነገር ካለ ቢያንስ ያ ነገር የኖረበት ጊዜ አለ ማለት ነው፡፡ ያ አካል ሁሌ የኖረ ከሆነ ጊዜም ሁሌም ነበር ማለት ነው ስለዚህ የመጀመሪያ የሚባል ነገር ላይኖር ነው፡፡

ሆን ተብሎ ለህይወት መኖር ማመቻቸት (The argument from the fine-tuning)

1. በሁለንታ ውስጥ ለህይወት መኖር የሚመች ስርዓት በአጋጣሚ ሊኖር አይችልም፡፡
2. ህይወት ያለው አካል ማስገኘት የሚችል ተፈጥሮአዊ እድል የለም፡፡
3. ስለዚህ ህይወት የኖረው ለህይወት መኖር አመቻች (Fine Tuner) ስለኖረ ነው፡፡
4. ያም አመቻች እግዚአብሔር ነው፡፡

በእርግጥ ህይወት በመሬት ላይ እንዴት ሊገኝ ቻለ የሚለው ጥያቄ በአስተማማኝ መልኩ አልተመለሰም ግን ባለማወቅ ፈንታ ሌላ አለማወቅ መተካት አግባብ አይደለም፡፡ ሁለንታ ለህይወት የተመቸች አይደለችም፡፡ በሁለንታ ውስጥ 74% Dark energy ሲሆን 22%ቱ ደግሞ Dark matter በድምር 96% ይሆናል፡፡ ይህ ማት የሁለንታ 96% ለህይወት በፍጹም አይመችም፡፡ 4% መደበኛ አተም (Atom, or total visible matter) ነው፡፡ ሳይንስ ጥናት የሚያደርገውና ማወቅም የሚገባን ይህን አካል

Created in Master PDF Editor

ነው። ከዚህ 4% ውስጥ ለህይወት ምቹ የሆነችው ነጥብ መሬት ብቻ ናት። (እስካሁን ባለን መረጃ)። የመሬትን ይዘት ከ4%ቱ ሁለንታ ጋር ሳይሆን ከስርዓተ ፀሐይ ወይም ከሚልክወይ ጋላክሲ አንፃር እንኳ ምንም (ኢምንት) እንደ ማለት ነው። እናም ሁለንታ ለህይወት የተፈጠረች ሳይሆን ህይወት ለሁለንታ የተፈጠረ፣ ከሁለንታ የተፈጠረና በሁለንታ የተፈጠረ ነው። ፕ/ር እስቴፈን ሀውኪንግ ሁለንታ ለህይወት ምቹ እንድትሆን ታስቦ የተፈጠረች አለመሆኗን አስረድቷል፣ ይልቅም ምን ያህን ያልተመቸች እንደሆነች ከ66 ሚሊዮን አመታት በፊት እንደሆነው ክፉ ቀን ሊያጋጥም እንደሚችልም አስጠንቅቋል።

<<The universe is a violent place. Stars engulf planets, supernovae fire lethal rays across space, black holes bump into each other and asteroids hurtle around at hundreds of miles a second. These phenomena do not make space sound very inviting, but these are the very reasons why we should venture into space instead of staying put. An asteroid collision would be something against which we have no defence. The last big such collision with us was about sixty-six million years ago and that is thought to have killed the dinosaurs, and it will happen again. This is not science fiction; it is guaranteed by the laws of physics and probability.>>(Brief answer to big questions)

አስተርዮ - (Evidence from revelation)

ሰባኪዎች እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ለፈጥረቱ እንደሚገለጥ ይሰብካሉ። ብዙ ሰዎችም በግል እግዚአብሔር እንደተገለጠላቸው ይመሰክራሉ። የዚህ ማስረጃ መሰረታዊ ችግሩ መገለጥ የሚባለው ነገር ትክክለኝነቱ እስከምን ድረስ የሚለውን ለማወቅ መክበዱ ነው። መገለጦች ምን አልባት የተሳሳተ አረዳድ (erroneous perception)፣ የተሳሳተ እምነት (illusion) እና መሰረት የሌላቸውን ነገሮች በሃሳብ የመስማትና የማየት ሁኔታ (halucination) ሊሆኑ ይችላሉ። እናም በዚህ ሁኔታ አስተርዮን እንደ ማስረጃ ለመውሰድ ይከብዳል።

ስነ መግባር- (Argument from Moral Giver)

እኔ እስከሚገባኝ ድረስ በተፈጥሮ ውስጥ ስነ መግባር ወይም እዝነት የሚባለው ነገር ያለው በጥቂቱ ብቻ ነው። አንዳንዴ የአለምን የጦርነት እና የመጠፋፋት ታሪክ ሳስብ እንኳን ተፈጥሮ እራሷ በተፈጥሮ ውስጥ ማሰብ የሚችለው የሰው ልጅ እንኳ ምን ያህል መጥፎ እንዲሆን ይቀረፅብኛል። በሌላ በኩል ደግሞ እንስሳት ሰውን ጨምሮ ወላጆቻቸውን ሲወዱ፣ እርስ በእርሳቸው ሲረዳዱና ሲፋቀሩ ሳይ ተስፋየ ይለመልማል።

Created in Master PDF Editor

ወደ ተፈጥሮ ከመጣን ግን እጅግ ዘግናኝ ግፍ ይፈፅማል። መሬት እንዴ ሙቀቷ ከመደበኛው በታች ሆኖ በበረዶ ትሸፈናለች፣ እንዴ በጎርፍ ትጥለቀለቃለች፣ እንዴ በሀሩር ትቃጠላለች፣ እንዴ የስብርባሪ ከዋከብት መፈንጫ ትሆናለች፣ እንዴ ወደ ላይ ትፈላለች፣ እንዴ ወደ ውስጥ ትሰጥማለች። ይህ ሁሉ ተፈጥሮአዊ አደጋ እንኳ ቢቀንስ ፍጥረታት እራሳቸውን ለማቆየት የሚያደርጉት ጦርነት ማቆሚያ የለውም።

የስነ ዲዛይን፣ የስነ ኑባሬ፣ የስነ ፍጥረት፣ የስነ ባህሪ፣ የአስተርዮና የምቹነት ፍልስፍናዎችስ አምላክ መኖሩን አያስረዱምን ለሚለው ጥያቄ መልሱ አያስረዱም። ምን አልባት አለመኖሩን ሊያስረዱ ይችላሉ።

> Peter Tatchell **ምን ነበር ያለው?** *So began a period of intellectual wrestling with my faith. Echoing the eighteenth-century Franco-German philosopher Baron D'Holbach, I reasoned:*

1) *If God made the world and the natural laws of physics, chemistry and so on, according to his will and design, why does he intervene to adjust his own natural laws by allegedly performing miracles that defy the natural laws that he devised?*
2) *If God is love and infinitely good, why do religionists speak of God's wrath and fear him, and why does God condemn sinners to hell, which is supposedly a place of immensely cruel, barbaric torment and suffering?*
3) *If God is perfect, wise, infallible, and master of the universe, why do his creations include the "imperfections" of people born with terrible deformities and genetic disorders; and why does his earthly firmament include the flaws and terrors of devastating tsunamis, earthquakes, and tornados?*
4) *If God watches over us and protects us, why do sincere believers nevertheless have fear, including fear of death, and why do they have tragic accidents and die in wars and natural disasters? If God made man in his own image, why are there thieves, murderers, torturers, and rapists?*
5) *If the righteous are destined for heaven, why do they worry about whether or not they die and why do the followers of God mourn (sorrow) their passing?*
6) *If God knows everything, why do the faithful have to inform him of their needs and bother him with their prayers?*
7) *If God is just, why does he allow the good and godly to suffer?*
8) *If God is fair, why does he punish people who are born with genetic traits, and into dysfunctional families headed by bad parents, which predispose them to doing wrong?*
9) *If God made nature, why did he make it so harsh and cruel, based as it is on the survival of the fittest where the weak and vulnerable suffer and die, and where*

Created in Master PDF Editor

horrific natural diseases like Ebola and HIV kill decent, honorable people, including people of faith?

10) *If God is all-powerful, how is it possible to break his laws, resist his will, and cause him offense?*

11) *If God is so great, why does he need to be worshipped and idolized, and why does he need to be protected by laws against blasphemy and apostasy?*

(source, 50 voices of disbelief, page 304-305)

18. በአምላክ ማመን ለህይወት ትርጉም ያስገኛል ካለሱ ሕይወት ትርጉም የለሽ ይሆናል

ኃይማኖት በተለይም የተደራጀ ሃይማኖት ለብዙ ሰዎችን ለህይወት ትርጉም ይሰጣል:: ሃይማኖታዊ ማህበረሰቦች ብዙ ጥቅሞች ይኖራቸዋል እናም ብዙውን ጊዜ የባህል ማዕከላት ተደርገው ይቆጠራሉ:: በእያንዳንዱ ማዕከል ውስጥ ብዙ የበጎ አድራጎት ስራዎች ይሰራሉ:: ይህ የሰዎች መልካም ስራ የራሳቸውን ስብእና እንጅ የፈጣሪን መኖር አያስረዳም:: በምትኩ ግለሰቦች በሚኖራቸው እንቅስቃሴ ለሕይወታቸው ትርጉም መስጠት አለባቸው ሲጀምር የህይወት ትርጉም የምንሰጠው እንጅ የምንቀበለው አይደለም::

አንድ ሰው "እግዚአብሔር ባይኖር ሕይወት ትርጉም የለውም" ብሎ ተናገረ ማለት "ሕይወትን ትርጉም እንዳለው አምናለሁ፣ እናም ያለ አምላክ እንደዚያ ማሰብ አልችልም፣ ስለዚህ እግዚአብሔር እውን እንደሆነ ማመን አለብኝ::" ማለቱ ነው:: ይህ ሀሳብ ምኞት ነው፣ አሳማኝ እና አስፈላጊ አይደለም::

የሃይማኖቶች ትምህርትመጀመርያ ሰዎች ባዶ ማንነት እንዲኖራቸው ያደርጉና ይህን ባዶነት የሚሞላ እግዚአብሔር፣ አላህ ወይም ሌላ አካል ይፈጥራሉ::ይህ ለሶፍት ዌር ጠበብቶች ከሚንሳው ቫይረሱን ፈጥረው አንቲ ቫይረስ ይሸጡልናል ከሚለው ትችት ጋር ተመሳሳይ ነው:: ስብከቶችን አስቡ መነሻቸው በዝምታ እና በልብ ስብራት የተሞላ ሆኖ መጨረሻ ላይ በእልልታ እና በጭብጨባ ይደመደማል::

የክርስትና መሰረት የሆነው ክርስቶስ ለምን ወደ ምድር መጣ ብላችሁ ብትጠይቁ ዋናው መልስ አዳም አጠፋ ይህም ጥፋት ለትውልድ ሁሉ ሆነ:: ይህን ሀጢአት ለመደምሰስ ፈጣሪ ከሰማያት ወረደ ከድንግል ተወለደ ትባላላችሁ::እሰቡት ኢየሱስን እንደ አዳኝ (አንቲ-ቫይረስ) ለመቀበል መጀመርያ መታመም ነበረብን ለዚህም ሲባል አዳም ለሰው ልጆች ሁሉ የሚደርስ ሀጢአት እንደሰራ ተደርጎ ተማርን::እኛ ሰው ሲወለድ ነጻ ነው ለምንለው ግን የራሳችንን ትርጉም ለመፍጠር ነጻ ነን ንስሀ የምንገባበት በዘር የተላለፈ ሀጢአት የለብንም መሲህ እስኪ መጣም እየጠበቅን አይደለም:: ስለማንሆነው፣ ስለማይሆነውና ስለማንመስለው አንጨነቅም ፌድሮቭ

Created in Master PDF Editor

እንዲህ ይላል፦ “እኔ ለምሳሌ አንድ ሰው ነኝ፤ ማመን የምችለውም አንድ ነገር ነው፤ መሆንም የምችለው አንድ ነገር ነው፣ ገነት የሚገቡት ደግሞ የተመረጡት ናቸው፤ ካልተመረጥኩ የዘላለም እሳት ይጠብቀኛል:: ትልቁ ጥያቄ ደግሞ ለመመረጥ የሚያበቃው መመዘኛ (Criteria) እንደ ሀይማኖቱ የተለያየ ከመሆኑ ላይ ነው:: **የአንዱ የገነት መግቢያ ለሌላው የገሀነም ደጅ ነው::** ለአንዱ እግዚአብሔርን መምሰያ ለሌላው የሰይጣን ወንድምነት ይሆናል:: እንግዲህ አስቀድሞ ሲፈጥራችሁ እሱን አስመስሎ ካልሰራችሁ እሱን መምሰል ለምን ፈለጋችሁ?” (ጥበብ ቅጽ አንድ፣ 2009፣ 96-97) አማራጮች በብዙ ቅጥር ለመምረጥ እንቸገራለን፣ ሀይማኖቶች ስለ ህይወት ትርጉም፣ ስለ ነገረ ድህነትና ስለተፈጥሮአዊ ሂደቶች ያለ የለለ እየጻፉ ይሰብኩናል:: ጻህፊዎቹ የማያወሩት መላዕክ የማያናዝዙት መንፈስ የለም:: እንኳን የህይወት ትርጉም እያንዳንዱ እንቅስቃሴና ድርጊት ከሰይጣንን ወይም ከፈጣሪን የመጣ ነው:: ተክለ ኪዳን ሰይጣንን እንዴት እንዳናዘዘው ስሙ “--- ልንገልጽላችሁ የምንፈልገው ለማፍሸኩ፣ ለማዛጋቱ፣ ለማሰነጠሱ፣ ለማግሳቱ፣ ለመፍሳቱ፣ ለማከኩ፣ ለመንጠራራቱ እንደ ሌሎች ስያሜ እንዳታወጡልንና እንዳትሰይሙን አደራ እንላለን:: ይኸውም ቫይረስ፣ ባክቴሪያ ጀርም፣ ካንሰር፣ ኤድስ ብርድ፣ አላርጂክ፣ ዱካክ፣ ድብርት ጭንቀት፣...ወዘተ እይላችሁ እንዳትሰዩሙንና በተሰጣችሁ **የመከላከያ ጸጋ ጸሎት፣ ጾም፣ ስግደት፣ ቅን ሐሳብ፣ መልካም ተግባር፣ እውነተኛ አምላኮ፣ የክርስቶስን ስጋና ደም ተጠቅማችሁ ፍዳችንን እንዳታሳዩን ነው::** ከዚህ ውጭ በግልጽ ሰይጣን፣ ዛር፣ ውቃቢ፣ ጠንቋይ፣ ቦረንትቻ፣ መተት፣ አሰማት... ወዘተ እያላችሁ ስያሜ ብትሰጡን ሰማችን ስለሆነ ቅር አይለንም:: የምንመካበት ስም ስለሆነ አናፍርበትም::” (የጨለማው ገዥ ተግባርና ንግግር፣ 2009 ዓ.ም፣28) በዚህ አስተሳሰብ የህይወት ትርጉም የሰይጣንን እና የፈጣሪን ድምፅ መለየት ነው፣ ሌላው ይጨመራል:: ግን ተክለ ኪዳንን ያናገረው ሰይጣን ምንድን ነው? ብሩህ አለምነህ ስለሰይጣን ማንነት መልስ ሲሰጥ እንዲህ ነበር ይላል፦ “ሰይጣን የሚባል ራሱን የቻለ ህልውና ባህሪ፣ መልክና አካል ያለው ነገር በጭራሽ የለም:: እግዚአብሔርም ሰይጣንንም ሁለቱም በእኛ ሕይወት ውስጥ ያሉና በአእምሯችን ውስጥ የሚፈጠሩ የቅራኔ ሃሳቦችና ስሜቶች ናቸው::” (ፍልስፍና 2፣ 3ኛ ዕትም፣ 111)

ለእኔበሕይወት የመኖር ውበት እና የተፈጥሮን ድንቅ ስራ ማየት ለህይወት የሰጠሁት ትርጉም ነው ሁሉም ሰው የራሱ የሆነ የህይወት ፍልስፍና ቢኖረው ይመረጣል:: ለህይወታችን ከውጫዊ አካል ትርጉም ስንርቅ መልካም ስሜት እና ነፃነት ይኖረናል:: በውጭ ኃይል ካልተጠመድን ለመመርመር ነጻ ነን፣ ለህይወታችን ትርጉም የመስጠት ችሎታም አለን::

ታላቁ ጸሀፊ Robert Green Ingersoll እንዲህ ነበር ያለው <<*When I became convinced that the universe was natural, that all the ghosts and gods were myths, there*

Created in Master PDF Editor

entered into my brain, into my soul, into every drop of my blood, the sense, the feeling, the joy of freedom. The walls of my prison crumbled and fell. The dungeon was flooded with light and all the bolts and bars and manacles turned to dust. I was no longer a servant, a serf, or a slave. There was for me no master in all the wide world, not even in infinite space.

I was free to think. Free to express my thoughts, free to live in my own ideal. Free to live for myself and those I loved. Free to use all my faculties, all my senses. Free to spread imagination's wings, free to investigate, to guess, and dream and hope. Free to judge and determine for myself. Free to reject all ignorant and cruel creeds, all the inspired books that savages have produced, and the barbarous legends of the past. Free from sanctified mistakes and "holy" lies. Free from the fear of eternal pain, free from the winged monsters of the night. Free from devils, ghosts and gods. For the first time I was free.

There were no prohibited places in all of the realm of thought. No error, no space where fancy could not spread her painted wings. No chains for my limbs. No lashes for my back. No flames for my flesh. No Master's frown or threat, no following in another's steps. No need to bow or cringe or crawl, or utter lying words. I was free; I stood erect and fearlessly, joyously faced all worlds.

My heart was filled with gratitude, with thankfulness, and went out in love to all the heroes, the thinkers who gave their lives for liberty of hand and brain, for the freedom of labor and thought to those who fell on the fierce fields of war. To those who died in dungeons, bound in chains, to those by fire consumed, to all the wise, the good, the brave of every land whose thoughts and deeds have given freedom to the sons of men. And then, I vowed to grasp the torch that they held, and hold it high, That light might conquer darkness still.>> -Robert Green Ingersoll (1833-1899) ምንጭ (https://whynogod.wordpress.com/)

ቁመታችሁን ተላኩ ከ2 ሜትር ላይበልጥ ይችላል። ክብደታችሁን ተለኩ ከ100 ኪሎ ግራም ላይበልጥ ይችላል፣ እድሜአችሁን አስቡት ቢበዛ 100 ዓመት ነው። ይህን ማንነት ከምንኖርበት መሬት ስፋት፤ ክብደትና እድሜ ጋር አወዳድሩት። የመሬትን ዲያሜትር፣ ስፋትና ክብደት ከሰው ልጅ ቁመት፣ ስፋትና ክብደት ጋር ማወዳደር እብደት ነው። መሬት 6 X 10 ^{24} ኪ.ግ ትመዝናለች ተብሎ ይገመታል። በዚህ ክብደት ውስጥ 100 ኪሎ ግራም ምንድን ነው? መሬት 4.6 ቢሊዮን አመታት ኑራለች ሰው እድሜ ግን መቶ እንኳን አይሞላም። ምን ማለት ነው? መሬት ከእኛ አንፃር ግዙፍና እድሜ ጠገብ ብትሆንም ከሰርዓተ-ፅሀይ አንፃር ካየናት እንደ ነጥብ

Created in Master PDF Editor

ናት። ስርዓተ ፀሐይም በሚልክወይ ጋላክሲ ውስጥ እንደ ጠብታ ነው። ሚልክውይ ጋላክሲም በሁለንታ ውስጥ በአጉሊ መነጸር እንደሚታይ ቅንጣት ነው። ምን አልባት ይህ ሁለንታም በአማዞን ደንውስጥ እንዳለች እንዲት ዛፍ ይሆናል። ይህ ትረካ የሰው ልጅ ምን ያህ ኢምንት እንደሆነ ያስረዳል፣ ያ ማለት ግን ትርጉም የለውም ማለት አይደለም። ህይወት ትልቅ ትርጉም አለው መኖር የሚባል ነገር። ሌላው ሁሉ የድብረት ፈጠራ ነው። የፍርሃት መጠጊያ፣ ራስን ያለቦታው የማንገስ ልምምድ፣ በተፈጥሮ ላይ የማመፅ ዘመቻና ሀይማኖቶች በእምነት ብቻ የሚሰጡት ትርጉም ነው። ሰዎች አምላክ ከሌላ እኛ ምንም (ባዶ) ነን የሚሉት ስለዚህ ነው። ቢያሳዝንም ምንምነትን በጸጋ መቀበል አለብን።ነገር ግን በተፈጥሮ ምንም ብንሆንም ለህይወታችን ግን ነባራዊ የሆነ ትርጉም መስጠት አለብን።

ሀይማኖቶች በተለይም የምስራቁ ሀይማኖቶች ከተፈጥሮ ጋር ስለመዋሀድ በትኩረት ይሰብካሉ። በምዕራቡ ሀያላን ሀይማኖቶቹም በተለይ በገዳማት እራሳቸውን በመመሰጥና በምስጋና ከተፈጥሮ ጋር ሊዋሀዱ ይችላሉ። ይህ ደስ የሚል ውህደት ከተፈጥሮም ጋር ይሁን ከእግዚአብሔር ጋር በኤቲስቶችም አለ። የሌሎችን ምስክርነት ልተወው እኔ የተፈጥሮ ጉዳዮች ሳይ፤ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሀይማኖታዊ ክርክሮች ሲደርጉ ሳይ፤ የታሪክ፣ የፈላስፋና፣ የሳይንስና የሀይማኖት መፅሀፍትን ሳነብ፤ የሰማይ ከዋከብትን፣ የተፈጥሮን ስሪት፣ የሳይንስና ቴክኖሎጅ ውጤቶችን ስመለከት ወደ ህዋው እሰምጣለሁ። ፍፁም ውህደ እዋሃዳለሁ በዚህ እያለው ሁሉ ደስ ይለኛል፣ ጉደለቱም ያመኛል።

የምስራቁ ሀይማኖቶች ይህን መንቃት ይሉታል። እውነትም መንቃት ነው ከተፈጥሮ ጋር እንደመዋሀድ የሚያስደስት የለም። በእየ ሙዝየሙ፣ በእየ ቤተ-ሙከራው እና በእየምርምር ጣቢያው እየተገኘሁ የማየት እድሉ ባይኖረኝም ቦታው ላይ ያለሁ በሚመስል ተመስጦ ውህደትን እለማመዳለሁ። የአማዞን ጥቅጥቅ ደንን በህይወት ዘመኔ ላልረግጠው እችላለሁ ግን አይቸዋለሁ። የአረቢያን ስነ-ምድር ላልረማመድበት እችላለሁ ግን አይቸዋለሁ። በአለም አስገራሚ ቅሬት አካሎችንና ቅርሶችን የያዙ ሙዝየሞችን በአይኔ በብረቱ እያየሁ፣ እየዳሰስኩ ላልገረም እችላለሁ ግን በጥቂቱ አይቸዋለሁ ምስጋና ለዩቱብ (Youtube) ይሁንና። በእርግጥ ከእነ ሶቅራጠስ፣ ፕልቶ፣ አርስትትል፣ አንስታየን፣ ዳርዋን፣ ኮፐርኒካስ፣ ጋሊሊዩ እና ከሌሎች ባለምጡቅ አዕምሮ ባለቤቶች ስር ቁጭ ብየ ላልማር እችላለሁ ግን በመፅሀፎቻቸው በጥቂቱም ቢሆን አውቃቸዋለሁ፣ አስተምረውኛል። ታድያ ይህ ልምምድ የህይወት ትርጉም ተድርጎ ቢሰድስ? የህይወት ትርጉም የግድ ገነትን ማለም ብቻ መሆን አለበት እንዴ?

Created in Master PDF Editor

19. **በጣም ብዙ ቅዱሳን ሰዎች ለእግዚአብሔር እና ለሀይመኖታቸው ሞተዋል**

“. . . የግብፅን ከተሞች በደም ገንብተናል

በመግደል ጽድቅ የለም ሞተን ግን ኖረናል

ማህተብሽን ፍቺው በጥሺው ቢሉኝ

እኔስ ከነአንገቴ ውሰዱት አልኩኝ።

ጴጥሮስ ተሰቀለ ጳውሎስ ተሰየፈ

ተዋህዶ እያለ እረ ስንቱ አለፈ

ሌሎችም በእሣት በስቃይ አልፈዋል

ዘመን የማይሽረው ታሪክን ጽፈዋል።” (ምንጭ፦ተዋህዶ ሃይማኖቴ ከተሰየ መዝሙር)

የዓለም ሃይማኖቶች ታሪክ በደም የተሞላ ታሪክ ነው። በርካታ ቅዱስ ጦርነቶች ተካሄዷል። በተለያዩ አማኞች መካከል በተደረገ የበላይነት ጥያቄ ሰዎች ራሳቸውን ለሰማዕታት በግድም በፈቃደኝነትም አሳልፈው ሰጥተዋል። ቁጡ አማልክት ለማስደሰት የሰዎች ህይወት መስዋት ተደረጓል።በሃይማኖት ስም ማህበረሰቦች ተጨፍጭፈዋል እንዲሁም አፈንጋጭ ፈላስፎች እና ሳይንቲስቶች ተገድለዋል።

ይህ ታሪክ ስለ ሰብአዊ ተፈጥሯዊ የጥቃት ገጽታዎች የበለጠ ይናገራል እንጂ ስለ እግዚአብሔር መኖር መረጃ አይሰጥም። አንድ እጅግ የሚያሳዝን ታሪክ ላስታውሳችሁ በመስቀል ጦርነት ወቅት በተደጋጋሚ ክርስቲያኖች ተሸነፉ። የክርስትና ሊቃውንት የተዋጉት ህጻናት ቢሆኑ ኖሮ እግዚአብሔር ይረዳን ነበር ብለው አሰቡ። ከዚያም በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ህጻናት ከአውሮፓ ተሰበሰቡ እና ቅድስት ኢየሩሳለምን ነጻ ለማውጣት ጉዞ ተጀመረ። አንድም ህጻን ቅድስት ኢየሩሳለም አልደረሰም። ብዙዎቹ በርሃብ እና በበሽታ ሞቱ፣ የተረፉት ለባርነት ተሸጡ። ይህን ጥቁር ታሪክ ማስታወስ የሚፈልግ የለም።

በቅርቡ ስለጠንን በሚሉት ምእራባዊያን አማኞች የራስን ሕይወት የማጥፋት ዘመቻ መስማት ብርቅ አይደለም። ሰዎች በጅምላ ራስን እስክመግደል ድረስ ያምናሉ። ለምሳሌ በ 1997 እ.ኤ.አ. በገነት በር ማህበረሰብ (Heaven’s Gate community) ውስጥ 39 ሰዎች ራሳቸውን ገለዋል። እ.ኤ.አ በ 1970ዎቹ 900 በላይ ሰዎችን ራሱን መሲህ ላደረገው ጆም ጆንስ ራሳቸውን ገለዋል።በእነዚህ ሃይማኖቶች ተሳትፎ ብዙ ሰዎች ሞቱ እንጅየእነሱ መሥራቾች እውነታነት እና የሞቱለትን ሀይማኖት ትክክለኛነት አያሳይም።

Created in Master PDF Editor

እስከአሁን ድረስ ክርስቶስ ይመጣል ከተባለ ሁለት ሽ ዘመን አለፈ፡፡ ዛሬ ይመጣል ነገ ይመጣል የሚሉት ገን በእየጎዳናው እና በእየ ሚድያው ይሰብካሉ፡፡ ለእኔ እነዚህ ሰዎች አሸባሪዎች ናቸው፡፡ ሞኞች በኋቸው እየሱስ ዳግም መምጠት ከነበረበት በአረገ ቢበዛ በመቶ አመት ውስጥ ነበር፡፡ እንዴት ብትሉ ጌታ ይላል፦“እንዲሁ ደግሞ እናንተ ይህን ሁሉ መሆኑን ስታዩ ቀርቦ በደጅ እንደ ሆነ እወቁ፡፡ እውነት እላችኋለሁ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም፡፡ ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም፡፡”ማርቆስ 13: 29-31፡፡

የተለያዩ አማኞች ለተለያየ ሃይማኖታዊ ለእምነታቸው ሲሉ ሞተዋል፡፡ ሰማዕታት በክርስትና፣ በእስልምና፣ ሂንዱዝም እና በሌሎች ሃይማኖቶችአለበተጨማሪም ለሳይንስ ማበብ እና ልፍልስፍና የበላይነት ሲሉ ብዙ ሊህቃን ሰማዕት ሁነዋል፡፡ሁሉም ለትክክለኛው ምክንያት እንደሚሞቱ ያምናሉ፡፡ቢሆንም ሁሉም ትክክል ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ቢያንስ **አንዳንዶቹ ሰማዕታት በከንቱ ሙተዋል**፡፡ ከሞት በኋላ ሕይወት አለ በሚለው እምነት ወይንም በተለየ መልኩ ለሚሰጥ የሰማዕታት ሽልማት ሰዎች ውድ ሕይወታቸውን ያባክናሉ፡፡ ያለምንም አሳማኝ ምክንያት እና እንዲሁም የጥንት አፈ ታሪኮች መሰረት በማድረግ ራስን ለሞት አሳልፎ መስጠት ፍጹም አሳዛኝ ነገር ነው፡፡ ሰዎች አንድ አሳዛኝ ታሪክ ከመፅሀፍ ቅዱስ ልጥቀስ ሳነበው እያለቀስኩ ነበር ግን ታሪኩ ተፈፅሞ ባይሆን ብየ ተመኝሁ እስኪ አንቡት፦

> “ዮፍታሔም (አለ) በእውነት የአሞንን ልጆች በእጄ አሳልፈህ ብትሰጠኝ ከአሞን ልጆች ዘንድ በደኅና በተመለስሁ ጊዜ ሊገናኘኝ ከቤቴ ደጅ የሚወጣው ማንኛውም ለእግዚአብሔር ይሆናል፡፡ለሚቃጠልም መሥዋዕት አቀርበዋለሁ ብሎ ለእግዚአብሔር ስእለት ተሳለ፡፡ ዮፍታሔም ሊዋጋቸው ወደ አሞን ልጆች አለፈ፡፡ እግዚአብሔርም በእጁ አሳልፎ ሰጣቸው፡፡ ከአሮዔርም እስከ ሚኒትና እስከ አቤልክራሚም ድረስ ሀያ ከተሞችን በታላቅ አገዳደል መታቸው፡፡ የአሞንም ልጆች በእስራኤል ልጆች ፊት ተዋረዱ፡፡ ዮፍታሄም ወደ ቤቱ ወደ ምጽጳ መጣ፡፡እነሆም ልጁ ከበሮ ይዛ እየዘፈነች ልትገናኘው ወጣች፡፡ ለእርሱም አንዲት ብቻ ነበረች፤ ከእርስዋም በቀር ወንድ ወይም ሴት ሌላ ልጅ አልነበረውም፡፡ እርስዋንም ባየ ጊዜ ልብሱን ቀድዶ አወይ ልጄ ሆይ! ወደ እግዚአብሔር አፌን ከፍቻለሁና ከዚያውም እመለስ ዘንድ አልችልምና በጣም አዋረድሽኝ አስጨነቅሽኝም አላት፡፡ እርስዋም አባቴ ሆይ አፍህን ለእግዚአብሔር ከከፈትህ (ከተሳልክ) እግዚአብሔር በጠላቶችህ በአሞን ልጆች ላይ ተበቅሎልሃልና በአፍህ እንደ ተናገርህ አድርግብኝ አለችው፡፡ አባትዋንም ከዚህ ሄጄ በተራሮች ላይ እንድወጣና እንድወርድ፥ ከባልንጀሮቼም ጋር ለድንግልናዬ እንዳለቅስ ሁለት ወር አሰናብተኝ አለችው፡፡ እርሱም ሂጂ አለ፡፡ ሁለት ወርም አሰናበታት፤ ከባልንጀሮችዋም ጋር ሄደች፥ በተራሮችም ላይ ለድንግልናዋ አለቀሰች፡፡ ሁለትም

Created in Master PDF Editor

ወር ከተፈጸመ በኋላ ወደ አባትዋ ተመለሰች፥ እንደ ተሳለውም ስእለት አደረገባት፤ እርስዋም ወንድ አላወቀችም ነበር:: መሳፍንት 11:30-39

ምስኪን በአጭሩ ተቀጨች። ምን አልባት ታሪኩ እውነት ከሆነ እግዚአብሔር የሰው ልጅ መስዋዕት ከሚቀርብላቸው ደም መጣጭ ጣኦቶች አንዱ ይሆናልማለት ነው:: በነገራችን ላይ የአብርሃምን ልጅ ይሳቅን ባዳነበት ጥበቡ ማዳን ይችል ነበር ደም ስለጠማው እንጅ:: ዛሬም ሰዎች ለእምነታቸው ሰው ሲገሉ ወይም እራሳቸውን ሲያጠፉ ብትሰሙ ከመፅሃፍ የተወሰደ ልምድ ስለሆነ አዲስ አይምሰላችሁ::

20. እምነት የለሽነት ከሃይማኖት በላይ ብዙ ሰዎችን አስገድሏል፣ መጥፎና ሰይጣን አምላኪነት ነው

አንዳንድ አማኞች ኤቲስትዎች የጭካኔ ጦርነቶችን እንዳስነሱለማስረዳት ይጓጓሉ:: እንደ እውነቱ ከሆነ አንዳንዶች በቅርቡ የከሸፉት አምላክ የለሽ ኮሚኒስት መንግስታት አሰቃቂ እልቂት አድርሰዋል:: በዚህ ዝርዝር ውስጥየጆሴፍ ስታይሊን፣ የሞሶሎኒ፣ የማኦዘዶንግ እና የመንግስቱ ኃ/ማርያም አገዛዝ ይገኛሉ:: እነዚህ ሰዎች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ንጹሐን ዜጎችን (አማኞችን እና ኢ-አማኞችን) ደም አፍሰዋል:: የጥፋት ምክንያታቸው ፖለቲካዊ እንጅ ጸረ-ሐይማኖታዊ አልነበረም:: በእርግጥ ሰወቹ ሐይማኖትን የእድገት እንቅፋት እንደሆነ በማሰባቸው የሃይማኖት መሪዎችን ያሳድዱ ነበር:: ቢሆንም ቀይ ሽብር ፖለቲካዊ እንጅ ሐይማኖትን የማጥፋት ዘማቻ እንዳልነበር ይታወቃል::ኤቲዝም በአማልክት አለማምን ነው:: ኤቲዝም መሰረታዊ መርሆዎች፣ የመተዳደሪያ መጽሐፍ እና የማይገሰሱ አይዶሎጅዎች ያሉት አይደለም:: ኢ-አማኝነት መሠረተ-እምነት የለውም:: ይወገር፣ ይገደል፣ ይሰቀል፣ ይረሽን የሚል ህግ የለውም:: ኤቲስቶች በማህበረሰባዊ፣ ሀገራዊ እና አለም አቀፋዊ ህጎች የሚመሩ እንጅ ከሰማይ በወረደ ዶግማ የሚነዱ አይደለም::

ይልቁንም እንደ ዴንማርክ እና ስዊድን ያሉ ኤቲስቶች የበዙባቸው ሀገራት በጣም ሰላማዊና የበለጸጉ ሀገሮች ናቸው:: ሽብርተኝነት እና አጥፍቶ ማጥፋት አይፈጽምባቸውም ከሆነም ድርጊቱን የሚፈጽሙት ከአማኝ ሀገራት የመጡ ስደተኞች ሆነው ይገኛሉ::እንደ እምነታችን ፅናት ቢሆን ኖሮ ዛሬ ኢትዮጵያ የት ነበረች:: አኗኗራችን፣ ህይወታችን እና ምግባራችን ከሃዲ ከምንላቸው ቢያንስ እንጅ አይበልጥም:: <ከማመን መጠራጠር ይሻላል> ችግራችን አላማምን ሳይሆን ማመን (ሀይማኖት) መሆኑን እስክመፍትሄው በአብራራበት ጹህፉ እንዲህ ይመክረናል፦

የሰዉ ልጅ ከጥንት ጀምሮ በተናጠልም ይሁን በግሩፕ እየሆነ እርስ በርሱ ሲገዳደል ኑሯል:: ወደ ፊትም ይገዳደላል:: ይህ የሚያሳየዉ የሰዉ ልጅ የመጨረሻ ስግብግብ፣ ሁሌም የበላይ መሆንን የሚፈልግ፣ ባለዉ ነገር

Created in Master PDF Editor

> የማይረካ፣ ባተሌ መሆኑን ነዉ። እነኝህ ባህሪወቹን ካላስወገደ የሰዉ ልጅ በሰላም፣ በመቻቻልና፣ በመከባበር አይኖርም። የሰዉ ልጅ ከጥንት ጀምሮ ህግጋቶችን እየመሰረተ በህግ ለመተዳደር ቢሞክርም ፍላጎቱ ከህግ በላይ ስለሆነ ከወንጀል የፀዳ ህይወትን መኖር አልቻለም። የተለያዩ ሐይማኖታዊና ዲሞክራሲያዊ (መንግስታዊ) ህግጋቶች የሰዉ ልጅን ከጦርነትና ከተመሰቃቀለ ህይወት አልታደጉትም። ሊታደጉትም አይችሉም።

ይህን ትንታኔ የፖለቲካ እና የማህበረሰብ ጥናት ሊህቀን ይስማሙበታል። የሰው ልጅ ሁሌም በግጭት የጸዳ አይሆንም። በተለይ የተለያዩ የሀብትና የሀይል የበላይነት ለወቀዳጀት የሚደርገው ፍትጊያ ማቆሚያ ያለው አይመስልም። ኢኮኖሚስቶች እንደሚሉት ፍላጎት ገደብ የለውም። ሀብት (Resourse) ግን ገደብ አለው። ይህ አለመመጣጠን ግጭት (Conflict of interest) ይፈጥራል። የአለም ታሪክም የሚያስረዳን የተካሄደበት ጀምላ ጨረሽ ጦርነቶች ሀብትን ለመቀራመት ወይም የፖለቲካና የሃይማኖት የበላይነት ለማግኘት የተደረጉ ናቸው። በእኔ አመለካከት ይላል <ከማመን መጠራጠር ይሻላል> መፍትሄውን ሲጠቁም፦

> በኔ አመለካከት የሰዉ ልጅ እርስ በርሱ ተከባብሮና ተቻችሎ በፍቅር ሊኖር የሚችለዉ ፓለቲከኞችና ሐይማኖተኞች ከምድረ ገፅ ሲጠፉና የሰዉ ልጅ ንቃተ ህሊና ከፍ ሲል ብቻ ነዉ። የሰዉን ልጅ ሊዳኘዉ የሚገባዉ የራሱ ህሊና ነዉ። የሰዉን ልጅ ፍቅር እንጅ ህግ አይገዛዉም። በአለማችን ፍቅር እንድሰፍን ከተፈለገ ለፓለቲካና ለሐይማኖት የሚበተኑ ዶላሮች የሰወች ጭንቅላት ላይ ኢንቨስት መደረግ አለባቸዉ። የጦር መሳሪያ ለማምረት የተከፈቱ ካምፓኒወች ወደ ቤተ-መፅሐፍት መቀየር አለባቸዉ። የጦር መሳሪያ የሚያመርቱ እጆች መፅሐፍትን መፃፍ አለባቸዉ። ሶቅራጥስን በአለማችን የሚታየዉ ክፋትና ተንኮል ምንጩ ምንድነዉ ብለዉ ቢጠይቁት መሀይምነት (Ignorance) ብሎ መለሰላቸዉ። አለማችንን ሲኦል ያደረጋት አለማወቃችን ነዉ። የሰወች የማሰብ ደረጃ ከፍ ሲል የሚሰራዉ የወንጀል ቁጥር ዝቅ ማለቱ አይቀርም። ብሄር፣ ሐይማኖት፣ ሀገር፣ የለኝም እኔ የአለም ዜጋ ነኝ የሚል ትዉልድ ካልተፈጠረ አለም ሰላም አትሆንም።

እናም መሰረታዊ አመክንዮ ባይሆንም የመስቀል ጦርነትን ያወጁት ጳጳሳት፣ ጅሀድን ያጧጧፉት ካሊፎችና መሬትን የባሩድ በርሚል ያደረጉት አማኝ ገዥዎች እያሉ ጥቂት ጨካኝ አረመኔና ልበ ደንዳና ኤቲስት መሪዎችን መዘርዘር መልሱ የካፋ ነው። አንዳንዶች ደግሞ ጥፋቶችን ለማጋራት ኤቲዝም እራሱ ሀይማኖት ነው ሲሉ ይደመጣሉ። አማኞች አለማመን እራሱ እምነት ስለሚያስፈልገው ኢ-አማኝነት እራሱ ሀይማኖት ነው ሲሉ ይደመጣሉ። አንዳንዴም ለማመን ከሚያስፈልገው በላይ

Created in Master PDF Editor

ለአለማመን እምነት ያስፈልጋል ይላሉ። እንደማስረጃው ኤቲሳቶች በሳይንስና በሳይንቲስቶች ያምናሉ፣ ያመልካሉም ሲሉ ይደመጣሉ። መጋነኑ ነው እንጅ ነገሩ እውነት አለው። ኤቲስቶች በሳይንስና በተፈጥሮቸዊ ፍልስፍና ይመራሉ። ምንም አይነት ዶግመና ቀኖና፣ ስርዓተ አምልዕኮ፣ ቅዱስን መፅሐፍትና ሰዎች የሚባል የምንመራበት ግን የለም። አማኞች የማይገባቸው የሀይማኖት ተቃራኒ አለማመን ሳይሆን ሌላ ሀይማኖት ነው። ኤቲስቶች ከአማኞችን የሚቀበሉትና የሚያከብሩት አስተሳሰብ ይኖራል። ኢ-አማኞች በሳይንስና በፍልስፍና ስለላቸው አክብሮትና መመካት ለሚያደርስባቸው አጭር መከላከያው ኑ እና እዩ ነው። ሳይንቲስቶችበእየዘርፎቹ የሚያደርጉት ምርምር የሚያስመልክ ባይሆንም ያስመካል ለዚህ ነው In God we trust በሚለው ቦታ In Reason and Science we trust የምንለው። ኤቲስቶች ታላላቅ ሳይንቲስቶች እና ፈላስፎችን ያመልካሉ ለሚባለው የት አያችሁ ማለቱ ተገቢ ቢሆንም ማንም ጤናማ ኤቲስት የቻርለስ ዳርዊንን፣ የካርል ስጋንን፣ የሪቻርድ ዳውኪንስን፣ የእስቴፈን ሀውኪንግን፣ የአንስታየንን፣ የኦሽን፣ ወይም የሌላ የማንኛውንም ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰውን ሀውልት ሰርቶ በቤተ መቅደስ አስቀምጦ አይሰግድም።በስሙ አያፀልዩም በፃፈው ጽሁፍ አይባረክም፣ አይታመንም። እነዚህ ሰዎች እንደኛው ሰው በመሆናቸው ለእኛ ሊተርፍ የማይገባ ስብእና ሊኖራቸው ይችላል። አንዳንዶቹ ጠጭች፣ አጫሾችና አደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ። እኛ በግላችን ውሳኔ ካልሆነ እነዚህን ነገሮች አናደርግም ብናከብራቸውም እነሱን ለመምሰል አንጥርም። እኔን ምሰሉ ያለንም የለም። ሁሉም እራሳችሁን ሁኑ ነው ያሉን።

ምን አልባት በተቃራኒው ለታላላቅ ኤቲስቶች ምስል ሰርቶና ቤተ-መቅደስ ገንብቶ የሚያመልክ ወይም በግሉ የማያሳሳቱ ፈፁማን ናቸው ብሉ የሚያስብ ካለ ያ ሰው በእርግጥ ሀይማኖተኛ ነው።

የሚገርመው እኛ ኤቲስቶች እግዚአብሔር የለም ብለን አናምንም። ይልቅ የምንመሰክረው ያየነውን ስለሆነ በምናውቀው ተፈጥሮዊ ነገር እንመካለን ስለፈጣሪ ሲጠይቁን ግን ከ100,000 አማልዕክት ውስጥ ትክክለኛውን አምላክ ለማወቅ አንችልም የላኳቸው ሰዎችና ያፃፏቸውቅ መፅሀፍት ከምናየውና ከምንኖረው ጋር የሚጋጩና ከፍፁም አምላክ የማይጠበቅ ስህተቶች የታጨቁባቸው ናቸው እንላለን። ልባችንን ክፍት አድርገን ከሁሉም የተሻለውን እየመረጥን ህይወታችንን እንመራለን እንላለን። ይህ ደግሞ ከአማኞች የተሻለ የአኗኗርና ስነ-ምግባር ልኬታ እንዲኖረን አድርጓል። በማህበራዊ ስምምነት ህግ እንጅ በአምላካዊ ትዕዛዝ አንመራም። እንደ ቡደን ካየነው ኤቲስቶች በተሲስቶች በተስፋ፣ በፍቅር፣ በመተሳሰብ፣ በመለገስ፣ በትዕግስት ወይም በአማንኛውም የስነ መግባር መመዘኛ የተሻሉ ናቸው። ይህ ብዙ አማኞችን እንደሚያናድዳቸው አውቃለሁ። ሚስጠሩ በመፅሀፍት ከሚመራ በህገ ልቦና የሚመራ

Created in Master PDF Editor

የተሻለ ነው፡፡ ሰዎች ላለፉት ሚሊዮን አመታት ያደበሩት ነገር በልቦና ህግ መመራትን ይጨምራል፡፡ ከቅዱሳን መፅሀፍት ይልቅ የሰው ልጅ ልቦና የስነ-ምግባር ምንጭ ነው፡፡ በዘርፉ ጥልቅ ምርምር ባለደርግም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ አባሯቸው የሚል በሁላችን ማንነት ላይ የተቀረፀ ህግ የለም በቅዱሳን መፅሀፍት ግን አለ፡፡ በጥቅሉ ከህገ መፅሀፍት ህግ ልቦና ይበልጣል ይጠቅማልም፡፡ ምናልባት ግለሰቦች በህገ ልቦናቸው መጥፎ ከሆኑ ማህበራዊ ልቦና ይገዛቸዋል፣ ይቀጣቸዋል፣ ያስተምራቸዋል፡፡ የማህበረሰብና የግለሰቦች ህግ ልቦና ደግሞ በማያቋርጥ መሻሻልና መታደስ ላይ ነው ያለው፡፡ ይህ የመታደስ ሂደት የተሻለ ስብአዊነት እንድናጎናፅፍ ያስችለናል፡፡ ያልተፃፈ ህጉ መንግስት የሚባለው ይህ ይሆን?

በአጭሩis a theisn a religion? ብለው ለሚጠይቁ No, it is not ነው መልሱ፡፡ ለምን ብትሉ Atheism is the absence of belief in gods ነውና፡፡ ምን አልባት ኤቲዝምን እንደ ሃይማኖት ያስቆጠረው በአደጉት ሀገራት የተቋቋሙት ኤቲስት ማህበራትና ድርጅቶች ከሆኑ ማህበር ሁሉ ሃይማኖት አይደለም፡፡ ማህበር ቅዱሳን በሆነ አጀንዳ የተቋቋመ እንጅ በራሱ ሃይማኖት አይደለም፤ በእየሰፈራችን የተቋቋሙት የአድርና የሰንበቴ ማህበራት ሃይማኖታዊ የሆኑ እንደሆነ እንጅ ሃይማኖት አይደሉም፡፡

በኤቲስት አለምም ከፌስቡክ ግሩፕ እስከ አለም አቀፋዊ ድርጅቶች ድረስ መቋቋማቸው ለማህበራዊ ግንኙነት እንጅ ለአምልዕኮ አይደለም፡፡ ምን አልባት የኤቲስቶችን መዳረጃት የሚናቅፉትና ሀይማኖታዊ ትርጓሜ የሚሰጡት ሰባኪዎች ግለሰቦችን ማጥቃት ድርጅቶችን ከማጥቃት ስለሚቀል ነው፡፡ እኔ የየትኛውም ማህበር አባል ባልሆንም የማህበራቱ መኖር ግን ለአስተሳሰቡ ጉልበት ይሰጣል ብየ አምናለሁ፡፡ ማንም እየተነሳ እንደ እባብ የሚቀጠቅጠን አውሬዎች አይደለንም፡፡ ለአለም ሰላምና ብልፅግና ህይወታችን እስከ መስጠት የምንዘምርና የምንሰራ የሰው ልጆች ነን፡፡ ያለንን እንከፍላለን፣ ያወቅነውን እንናገራለን፣ ያየነውን እንመሰክራለን፣ ለእውነትና ለፍትህ ሁሉም እንተጋለን፡፡ በቅዱሳን መፅሀፍ ከተፃፉት የተሻለ እጅግ የተሻለ ደንቦችንና ማህበራዊ ህጎችን እናከብራለን፡፡ ሰብአዊ እንድንሆንም ያደርገናል፡፡ ይህን የምለው እንደ ቡድን እንጅ በግላቸው ማፊያና ጭራቅ ሰው በላ ኤቲስቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ አውቃለሁ፡፡

አማኞች ኢ-ኢማኞችን እንደሚፈሯቸውና እንደማያምኗቸው ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡ የሚገርመው ሪፖርቶቹ ሲወጡ አማኞች በበዙባቸው እንደ USA ባሉት ሀገራት Least trusted በሚል ሰያሜ ነው፡፡ አማኞች ኢቲስቶችን የማያምኑት እንዳነሱ በመፅሀፍት ትዕዛዝ ስለማይመሩ ነው፡፡ በኤቲስት አለም 10ቱ ትዕዛዝ ወዘተ የሚባል የለም፡፡ ሁሉን ስለተፈቀደ ሁሉን የምናደርግ ይመስላቸዋል፡፡ በቅዱስ መፅሁፍ አትግደል፣ አታመንዝርና አትዋሽ ቢባልም ባይባልም ህሊና ላለው ማንኛውም ሰው

መግደል፣ ማመንዘርና መዋሸት ወንጀል ነው። አማኞች ስለ ኤቲስቶች ያላቸው የወረደ ግምት እየተስተካከለ ቢሆንም እንዲህ መታማቱ ግን ይገርማል። ኤቲስት ማለት ሰው የሚበላ ሰው የሚመስላቸውም አሉ። ይቅር ይበላቸው እኛስ ፍቅር የሚገዛን፣ ሰብዓዊነት የተሞላን፣ የሰላም ሰዎችና የምድር ወራሾች ነን። በድጋሚ ይህን ስል ሁሉም ኤቲስት መልካም ነው እያልኩ አይደለም። ከቡድን አንፃር ነው ያየሁት።

አማኞች የማያምኑትን ሀይማኖት የለሾች የሰይጣን አማኞች ናቸው ብለው ይከሳሉ። በጭራሽ ስህተት ነው በሰይጣን የሚያምኑ አማኞች ናቸው። ሰይጣን የእግዚአብሔር ሌላኛው ገጽ እንጅ ሌላ አካል አይደለም። ሰይጣን እና እግዚአብሔር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፆች ናቸው። የማናምነው እግዚአብሔርን ትተን የሰይጣንን የምናምንበት ምንም ምክንያት የለም። በሰይጣን የሚያምኑ ሰዎች በእርግጥ አሉ። እነዚህ ሰዎች እንደ አንድ የሃይማኖት ቡድን ይቆጠራሉ እንጅ ኤቲስቶች አይደሉም። በሰይጣን ለማናምነው ኤቲስቶች ግን ሰይጣን ከትረት የዘለለ ትርጉም የለውም። ለአማኞች ግን የሰይጣን መኖር ለእግዚአብሔር መኖር ዋስትና እና የእምነት መሰረት ነው። ያለ ሰይጣን የእግዚአብሔር ህልውና ጥያቄ ውስጥ ይወድቃል። ብሩህ አለምነህ በፍልስፍና ቁጥር 2 መጽሃፉ እንዲህ ይላል፦

> ካህሊም ጅብራንም "satan" በሚለው አጭር መጣጥፉ ውስጥ እንዲህ ብሎ ነበር፤ <የሰይጣን መኖር ሃይማኖትንና ቤተክርስቲያንን ከማቋቋሙም ባሻገር ቤተክርስቲያን እንጀራቸውን የምትሰጣቸው ቀሳውስት፤ ዲያቆናት፣ ዘማሪያን፣ ሰባኪያንና ለማኞችም እንዲኖሩ አድርጓል። አማኖችን ፈጥሯል፤ አማኞችም ከኪሳቸው ብርና ወርቅ እያወጡ እንዲለግሱ አድርጓቸዋል። የሰይጣን መኖር አማኞች ከእግዚአብሔር ጋር እንዲጣበቁ ቄሶችም በህብረተሰቡ ውስጥ ተሰሚ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።> ሰይጣን ከሌለ እግዚአብሔርም አስፈላጊነቱንና ምንነቱን ያጣል። እናም ቅድስት ክርስቶስ ሳምራ በየዋህነት ሰይጣንን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ ባደረገችው ሙከራ ውስጥ እግዚአብሔር በሰዎች ውስጥ የነበረውን አስፈላጊነት ልታሳጣው ነበር። (ፍልስፍና 2፣ 3ኛ ዕትም፣ 101)

ሰይጣን ለአማኞች የእምነታቸው ምሰሶ፣ የተቃርኖዎች መነሻ መደረሻ፣ የታሪካቸው ተጋሪ ነው። ለእኔ ግን ሰይጣን ከድንቅ ልብወለዳተዋናይ የዘለለ ትርጉም የለውም። ይህን ፅሁፍ ሳዘጋጅ ሰይጣን አላማከረኝም አማክሮኝም አያውቅም በአጭር ቋንቋ ሰይጣን የለም። ሙቷል። አልሰማችሁም? እውነት ለመናገር ከልጅነቴ ጀምሮ የሰይጣን ፎቢያ አለብኝ። ሰዎች ከመናፍስት ጋር እንደሚያወሩና የተለያዩ እርዳታዎች እንደማያደርጉና ሲቆጡና ያለ ሰዓት ሲያገኙ

Created in Master PDF Editor

ለበሽታ አሳልፈው እንደሚሰጡ ስሰማ እሸበር ነበር፡፡ እንዲያው በበረሃ ብቻየን የማደር ወይም የማምሸት አጋጣሚ ሲያጋጥመኝ፣ ቀን ወይም ሌሊት 6 ሰዓት ብቻየን ሰይጣን ይኖርባቸዋል በተባሉ ቦታዎች ስሆን እፈራ ነበር፡፡ ከእባብም፣ ከማንኛውም አውሬ ሰይጣናትን እፈራቸው ነበር፡፡ ምን አልባት ነክተውኝ ሊሆን ይችላል በሚል ስጋት ጸበል ጀምሬም ነበር፡፡ ነገር ግን ፍርሃቴ ሰዎች ከሚፈራት ያነሳ ሁኖ መሰለኝ አልያዘኝም፡፡ ስለ ሰይጣንና መናፍስት ህልውና ያየሁት እስከለለ ድረስ የለም ማለቱ ምክንያታዊ ነው፡፡ ካሉ ደግሞ አሉ ብየ እመሰክራለሁ፡፡ እስከዚያው ግን የለለ ነገር የማምለክና የመፍራት ሱስ ስለሌለብኝ እንደ ማንኛውም ኤቲስት ሰይጣንን እክደለሁ፣ እክዳለሁ፣ እክዳለሁ አሜን !

21. የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ

ታዋቂው የክርስትና ሰባኪና ተከራካሪ William Lane Craig የእግዚአብሔርን መኖር ላማስረዳት የክርስቶስን መመጣት እንደማስረጃ ይጠቀምበታል፡፡ God? a debate between a Christian and an atheist (William Lane Craig, and Walter SinnottArmstrong) በተባለ ድንቅ የሞቀ የክርክር መጽሃፍ William Lane Craig የእግዚአብሔርን መኖር ለማስረዳት የሚከተለውን ትንታኔ አስቀምጧል፡፡

1. There are four established facts concerning the fate of Jesusof Nazareth: (his honorable burial by Joseph of Arimathea, thediscovery of his empty tomb, his post-mortem appearances, and the origin of his disciples' belief in his resurrection.)
2. The hypothesis "God raised Jesus from the dead" is the bestexplanation of these facts.
3. The hypothesis "God raised Jesus from the dead" entails thatGod exists.
4. Therefore, God exists.

ይህ የWilliam Lane Craig አመክንዮ ችግሮች አሉበት፡፡ ቲወሎጅያኖችና የዘርፉ ሙህራን ኢየሱስ ክርስቶስን በተመለከተ 3 አቋሞችን ያራምዳሉ፡፡ አንደኛ ክርስቶስ ዛሬ በሚሰበከው ወንጌላውያን በተረኩት አኳኋን የነበረ ነው ይላሉ፡፡ ሁለተኛዎቹ በተቃራኒው ኢየሱስ ክርስቶስ የሚባል ጭራሽኑ አልነበረም እንደማንኛውም አማልዕክት በሰዎች የተደረሰ ነው ይላሉ፡፡ ሦስተኛዎቹ ማዕከላዊ ናቸው፣ አስተሳሰባቸው ኢየሱስ የሚባል ታላቅ መምህር ነበር ግን በወንጌል እንደተረከው አይደለም፡፡ በአዲስ ኪዳን መጽሀፍት የተተረከው ኢየሱስ የተጋነነ ነው ብለው የሚምኑ ናቸው፡፡

Created in Master PDF Editor

እኔ በጉዳዩ ጥናት እያደረኩ ቢሆንም ለጊዜው ግን የWilliam Lane Craigን መከራከሪያ ከChrist Myth Theory ጋር ማለትም እፈልጋለሁ፡፡ William Lane Craig ከመነሻው የክርስቶስ እውነተኝነት የተረጋገጠ ስለሆነ የእግዚአብሔርን መኖር ይመሰክራል የሚል ነው፡፡ በእርግጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ታሪክ ነው ወይስ ተረት? ታሪኩ ይቆይና ትረት ነው የሚሉት ሰዎች ከሚያቀርቡት ማስረጃ እንቃኝ፡፡

1ኛ. የአዲስ ኪዳን ወንጌል ከመጽሀፍ በፊት ከነበሩ ባህሎች የተኮረዠ ነው፡፡

2ኛ. በሁሉም ጥንታዊ ስልጣኔዎች ለየት ያሉ ሰዎችን መድረስ (መፍጠር) የተለመደ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ፅንሰቱ ከመልዕክ የተናገረ መሆን፣ ያለ ወንድ ዘር መጸነስ፣ የተለየ የልደት ስርዓት መኖር፣ ህፃኑ የተለየ ባህሪ እንዲኖረው ማድረግ፣ ታላቅ አስተማሪ ግን በሰዎች እና በሰይጣን የሚፈተን መሆን፣ ያለ አግባብ (በተጓደለ ፍርድ) መገደል፣ ከሙታን ተለይቶ መነሳትና ወደ ሰማይ ማረግ ወ.ዘ.ተ አይነት ታሪኮች በበርካታ ባህሎች ለተለያዩ አማልዕክት መገለጫዎች ናቸው፡፡

3ኛ. በመጽሀፍቱ ላይ የተንዣበበው ጥርጣሬ፡፡ የአዲስ ኪዳን መጽሀፍት የቆዩ እና ከክርስቶስ ማዕረግ በኋላ እስከ 100 ዓመት ድረስ ባለው ጊዜ የተጻፉ ቢሆንም በጽሀፊዎቹ ማንነት እና እርስ በእርሳቸው ባለው የምስክርነት ብቃት ላይ ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ ማንም በቀላሉ እንደሚረዳው በአራቱ ወንጌላውያን መጽሀፍት በርካታ ልዩነቶች አሉ፡፡ በአንድ ጉዳይ (ለምሳሌ ስሙነ ስቅለትን) በተመለከተ የተለያየ ምስክርነት ይሰጣሉ፡፡ ይህ የሁሉንም መጽሀፍት ተቀባይነት ያሳድፈዋል፡፡

4ኛ. ከወንጌል ውጭ ስለ ክርስቶስ እውነተኛነት የሚመሰክሩ በቂ በወቅቱ የተዘጋጁ መረጃዎች የሉም፡፡ ክርስቶስ በእርግጥ በወንጌል በተተረከው መልክ ኑሮ ቢሆን ኑሮ ከወንጌል የማይተናነሱ የሶስተኛ ወገን ማስረጃዎች ይኖሩን ነበር፡፡ ቢያንስ እንኳ ክርስቶስ መልካም ነገር ያደረገላቸው ሰዎች ታሪካቸው ይኖረን ነበር፡፡በተለይ ደግሞ በሰቅለቱ ሰሞን የተከሰቱት ታላላቅ ተዓምራት (የሙታን መነሳት ጨምሮ) በታሪክ ተመዝግቦ እናገኘው ነበር፡፡

5ኛ. የተገባው ቃል ኪዳን አለመፈፀሙ፡፡ ክርስቶስ ሲያስተምር አማኞች ሁሉን ነገር ማድረግ እንደሚችሉና ሁሌም እንደማይቻላቸው ነበር፡፡ ነባራዊ እውነታውን ካየን ግን ክርስቶስ ከማን ጋር እንዳለ የትኛው ቤተ ክርስቲያን ትክክለኛ እንደሆነ ለማወቅ አማኞች ሳይቀር ተቸግረዋል፡፡ ከ30,000 በላይ የሚሆኑ የተለያዩ ቤተ ክርስቲያናት የተለያየ ኢየሱስን ይሰብካሉ፡፡ ይህ መሰረታዊ ችግር ነው፡፡ ሰዎች ከዚህም ከዚያም እውነተኛው ክርስቶስ ተገለጠልኝ በማለት በየጊዜው አዳዲስ ሀይማኖቶችን ይፈበርካሉ፡፡ ግራ የተገቡት አማኞችም ለሰው የተገለጠ እውነትን ለራሳቸው በማድረግ የመገለጡ አጃቢ ይሆናሉ፡፡ ይህ ዝብርቅርቅ ያለ ሁኔታ ባለበት እና የተገቡት ቃል

Created in Master PDF Editor

ኪዳኖች ቃል ብቻ ሁነው በቀረቡት ሁኔታ ክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል በሚተርከው ልክ ነበር ለማለት ይከብዳል።

በአጠቃላይ ከላይ በተዘረዘሩት እና በሌሎች "Christ Myth Theory" አራማጆች የሚነሷቸው ነጥቦች ምክንያት ክርስቶስ እውነት William Lane Craig በሚለውና በሚሰብከው አግባብ ነበር ለማለት ይከብዳል። ስለዚህ የ William Lane Craig መነሻ ትክክል አይደለም። መነሻው ትክክል ካልሆነ መድረሻውም እንዲሁ ነው። ምን አልባት ክርስቶስ በተገለጠው አግባብ እንኳ ባይሆን እግዚአብሔር ግን አለ የሚል አስተሳሰብ ስላለ በሌሎች መከራከሪያዎች መልስ ተሰጥቶበታል።

ማርሻል ብሬን Why Won't God Heal Amputees በሚል ድህረ ገጹ ላይ እንዲህ ይላል፦ *How do we know, for sure, that Jesus was a normal human being? We can ask this simple question: If a man were to proclaim himself to be the son of God today, what would we do? We would ask to see unquestionable proof. Jesus does not get a pass because he lived 2,000 years ago. We note the fact that none of Jesus' miracles left any lasting evidence. For example, even though Jesus proclaimed that anyone can move a mountain, we note that no one -- not even Jesus -- has moved a mountain. All of Jesus' miracles are either faith healings or magic tricks, and we all know that faith healers and magicians are frauds. We also note that there is no evidence that Jesus is resurrected. Jesus could easily appear to each of us in the flesh to prove that he is resurrected, just as he did with Paul. And he promises that he will. Yet Jesus never appears. It is obvious that Jesus was a man like any other and that the Bible's description of Jesus is standard mythology. Jesus, in other words, is like Zeus."*

22. የእግዚአብሔር እርዳታ በሚፈልጉበት ጊዜ አማኝ ትሆናላችሁ

ከዚህ በስተጀርባ ያለው ሀሳብ ህይወት ጥሩ እየሆነ ሲሄድ ኤቲስት መሆን ቀላል ነው፣ ነገር ግን አስቸጋሪ ጊዜ ሲያጋጥማችሁ በአግዚአብሔር ታምናላችሁ ወይም ቢያንስ እርሱ እውን መሆኑን ተስፋ ታደርጋላችሁ የሚል ነው። ይህ አስተሳሰብ ለአንዳንድ ሰዎች ሊሆን ቢችልም እንጅ ዓለም አቀፋዊ ሀቅ አይደለም። እግዚአብሔር አለመኖሩ ጎዳን እንጅ ቢኖርስ በማንኛው ጊዜ ያስፈልገን ነበር። ለምን ቢባል <ከማመን መጠራጠር ይሻላል> እንዲህ ይላል፦

> ህይወታችን በሩጫ የተሞላች ነች። አሁን የምፈልገዉ ሁሉ ተሟልቶልኛል። ዉጣ ዉረዱን፣ መሰናክሉን ሁሉ አልፌ የድካሜን ሁላ ዋጋ አግኝቻለሁ! ከዚህ በኋላ እንደ እሰከ ዛሬዉ ሁሉ የምሮጥለት ጉዳይ የለኝም። ሩጫየን ጨርሻለሁ የሚል ማነዉ? ካንዱ ክፍል ወደ ሌላዉ ክፍል፣ ካንዱ ትምህርት ቤት ወደ ሌላዉ ትምህርት ቤት፣ከዩኒቨርሲቲወደ ስራእንደገናምወደ ዩኒቨርስቲ፥ አንዱ ጉዞ

> ሲያልቅ ሌላኛው ሽክርክሪት ይጀምራል፡፡ በስራዉም እድገት ለማግኘት ወይም ሌላ የተሻለ ስራ ለመስራት ሲል ብዙ አክሮባት ይሰራል፡፡ እንደገና ማግባትና ልጅ ወልዶ ቤተሰብ መመስረት፣ ወልዶ ልጅን ኮትኩቶ ማሳደግ ሌላ ፕላን ሌላ የወደፊት ዕቅድ ከብዙ እሩጫወች ጋር... በእጃችን ከያዝነዉ ነገር ይልቅ ገና ወደፊት ፍላጎት ያሳደርንበት፣ እቅድ ያወጣንለት ነገራችን ይበዛል...<ከማመን መጠራጠር ይሻላል>

በዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ የሰው ልጅ አለ ከሚባለው አምላክ ድጋፍ ይፈልጋል፡፡ ቢሆንም በራስ መተማመናችን ከፍ እያለ ሲሄድ አይን ያላየውን ጆሮ ያልሰማውን የአምላክ እርዳታ ተስፋ ማድረግ ትተን ተፈጥሮ በሰጠን አቅም እንበረታለን፡፡ ምን አልባትም አንዳንዶቹ ህይወት አልሳካላቸው ሲል ወይም በጣም ሲቸግራቸው ተመልሰው መማፀን ሊጀምሩ ይችላሉ፡፡ተማፅነውም ካልተሳካ ጠቢቡ ሰለሞን እንዳለዉ አለም የከንቱ ከንቱ ናት ብለው ሁሉን ትተው ገዳም ይገባሉ፡፡ በዚያም አለማዊ ፍላጎታቸው ተከትሎ ከባእታቸው ያስወጣቸዋል ወደ ናቋት አለም ይመለሳሉ፡፡ ሞት እስኪያቆማት ድረስ ህይወት እስከፈተናዋ ትቀጥላለች፡፡

ሞትን ማንም ሊፈራ (እየሱስ ጭምር) ይችላል፣ አማኞች ሁለት አይነት ሞት አለ ይሉናል፡፡ የስጋና የነፍስ ሞት፡፡ የነፍስ ሞትም እንደገና ከሁለት ይከፈላል፣ ሞት ለድልና ሞት ለሽልማት፡፡ "የቅዱስ ጴጥሮስ ሞትና የአስቆሮቱ ይሁዳ ሞት አንድ አይደለም፡፡ የአትናቴዎስ ሞትና የንስጥሮስ ሞት አንድ አይደለም፡፡ የፊያታዊ ዘፀጋም (የግራው ወንበዴ) እና የክርስቶስ ሞት ያው ሞት ነው፤ የሞቱበት ምክንያት ግን የክርስቶስን ሞት ቅዱስ፣የነፃነት፣ የቤዛነት ሞት ሲያሰኘው የወንበዴውን ግን የሀጢያት፣ የውድቀት፣ የሽንፈት ሞት ያደርገዋል፡፡" (ፍኖተ ብርሃን፣ 10ኛ ዕትም 2009 ዓ.ም) ሁላችንም ሞት በሃያም ይከፈል በሰላሳ የማይቀርልን መሆኑን ተረድተናል፡፡ የሞታችን መባቻ አካባቢ ሊፈጠሩ የሚችሉ ወደ እምነት የማጋደል ነገር የሚፈጠረው በከፍተኛ ፍርሃትና ድብርት ምክንያት ነው፡፡

ከመከራው ብዛት፣ በሌሎች ሰዎች ተጽእኖ አሊያም በአኗኗሩ ከተረዳው ተነስቶ ሰው ሃሳቡን ሊቀይር ይችላል፡፡ አንድ ኤቲስት በመጨረሻዋ የኑዛዜ ስአት በኢየሱስ አመነ ቢባል ሁለት አማራጮች አሉ አንደኛው ውሸት (ፌክ) ሊሆን ይችላል፡፡ በጣም የሚያሳዝነው የሟች ቤተሰብን እስከመደለል የሚደርሱ የእምነት ጋዜጦች አሉ፡፡ የካርል ሳጋንን ባለቤት ባለቤቷ በጣም ዝነኛና ታዋቂ ኤቲስት ስለነበረ በሞተበት ጊዜ ሀሳቡን ቀይሮ ከሆነ በሚል አማኞች በተደጋጋሚ ይጠይቋት ነበር፡፡ የዝግመተ ለውጥ ባዮሎጂስት እና ኤቲስት አክቲቪስት አራማጅ የሆነው ሪቻርድ ዶኪንስ ከቢል ማሄር (Bill Maher) ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ "ስሞት ቴፕ ሪከርደሬ ኦን እንዲሆን እፈልጋለሁ እንደ እኔ ያሉ ሰዎች የውሸት ታሪኮች ሰለባ ናቸው፡፡" ሲሉ ሊመጣ

Created in Master PDF Editor

የሚችለውን ፊክሽን ዜና አክሽፎታል፡፡ የኔ ኑዛዜ ደግሞ ከመቃብሬ <ሀዋርያው ቅዱስ አርዮስ በተወለደ 15 ቢሊዮን አመቱ አፈር ነውና ከመሬት ጋር ተዋሃደ> እንዲባል ነው፡፡

ሁለተኛው አማራጭ በሞት ስአት በትክክል ሀሳባቸውን ቢቀይሩም ማሰብ በማይችሉበት ወይም ከፍርሃት በመጣ ጭንቀት ስለሆነ የፈጣሪን መኖር አያስረዳም፡፡ ሲጀምር ሁሉም ሰው በፈጣሪ የማመን ፍላጎት አለው፡፡ ይህ ሀሳብ በከፊል ኮንሽስነስ ማይንድ (Sub consciousness mind) ውስጥ ያለ ሃሳብ ለሞት በቀረብን ጊዜ መንጸባረቁ ድንቅ ሚስጥር አይደለም፡፡Professor Michael Shermer እንዳለው “The brain is a belief engine. Once beliefs are formed, the brain begins to look for and find confirming evidence in support of those beliefs, which adds an emotional boost of further confidence in the beliefs and thereby accelerates the process of reinforcing them; round and round the process goes in a positive feedback loop of converting beliefs into truths.” (Skepticism 101, page, 3)በሞት መባቻ ብዙ ልንዘባርቅ እንችላለን እንደ ሶቅራጠስ ልበ ሙሉ ካልሆንን፡፡ ይህ ሞት ማለት እኮ ክርስቶስንም አምላክነቱን የሚያስተቹ ንግግሮችን እንዲናገር አድርጎታል፡፡ ለምን ተውከኝ ነበር ያለው?

ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሞት ሲያስብ በሞቱ ዋዜማ በጌተሰማኒ የአትክልት ስፍራ ቆሞ፡ ሲተክዝም ነበር መጽሐፍ ቅዱስ እንደነገረን፣ ለደቀመዛሙርትም በዚያ ምሽት ሲናገር፡- ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፤ በዚህ ቆዩ ትጉም አላቸው ይለናል ማርቆስ 14፡34፡፡ ኢየሱስ እንደገናም እንዲ አለ፡- ‹‹አባ አባት ሆይ፤ ሁሉ ይቻልሀል፤ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን አንተ የምትወደው እንጅ እኔ የምወደው አይሁን›› እዚህ ላይ በአብና በወልድ የሃሳብ ልዩነት ተፈጥሮል ወልድ ኢየሱስ የሚፈልገው መኖሩን ነበር፣ አባቱ ግን የልጁን ሞት ወዷልና ለሞት አሳልፎ ሰጠው፡፡ ፈላስፎቹ ይህን በሞቱ ዋዜማ ሁኖ የተናገረውን የኢየሱስን ሀሳብ መሰረት አድርገው ክርስቶስ በምድር ላይ በኖረበት ዘመን የአባቱን ፍቃድ ሙሉ በሙሉ ለመፈፀሙ አጠራጣሪ የሚያደርገው በሞቱ የመጨረሻ ሰዓት የያዘው የአቋም ልዩነት ነው ቢሉ የሚገርም አይደለም፡፡ በጣረ ሞት ስዓት ብዙ እውነቶችና ኑዛዜዎች ሊወጡ ይቻላሉና፡፡ እንዲህ ክርስቶስን ሳይቀር ያስደነገጠው ሞት ምን የሚያስፈራ ነገር አለው? ሀይለ ጊዮርጊስ ማሞ እናዳለው “ብዙዎቻችን ሞትን የምንፈራው የት እንደምንሄድ ስለማናውቅ ብቻ ነው፡፡ ገነት ለመግባታችን እርግጠኛ ብንሆን ሞትን አንፈራም ነበር፡፡ ቢያንስ መድረሻችን አሁን ካለንበት ሕይወት የተሻለ ነውና፡፡ ሞት ደግሞ ገነትንም ሆነ ገሃምን እስከዛሬ ሊያረጋግጥልን አልቻለም፡፡ ለጊዜው ሞትን የመጨረሻ አድርገን ብንወስደውስ?” (ጥበብ ቅጽ አንድ፣ 2009፣ 137) ይልቅም እኔን ምረጡ እኔን ምረጡ የሚሉትን አማልዕክት ትተን ያለችንን ህይወት አሟጠን

Created in Master PDF Editor

ብንጠቀማትስ? የጥንቲቱ ፋርስ ፈላስፋ፣ ሳይንቲስትና የሂሳብ ሊቅ የነበረው ኦመር ካያም የጻፋትን ስንኝ በዕውቀቱ ስዩም እንዲህ ተረጎማት፡፡

ጎህ እንደቀደደ፤ በሚጣፍጥ ዜማ

መላክ ከሰማይ ላይ፤ እንዲህ ሲል ተሰማ

ቶሎ ቶሎ ውደድ

የድሜህ ጀንበር ሳይጠልቅ፤ ሳይውጥህ ጨለማ

በህይወት መስከር ነው፤በፍቅር መመርቀን

የፊት የፊቱን ኑር፤ ምንድነው ሰቀቀን

ህያው ፍጥረት ሁሉ

ያከትማል አንድ ቀን፡፡

23. ብዙ ታዋቂ ሳይንቲስቶች፣ አክተሮች፣ እስፖርተኞ፣ ዶክተሮች ወ.ዘ.ተ በእግዚአብሔር ያምናሉ

አንዳንድ አማኞች ስለ እምነታቸው ሲጠየቁ ‘አቶ X በጣም ሊቅ ነው ደግሞም በአምላክ መኖር ያምናል ስለዚህ እኔ ማን ነኝ እሱ ያላወቀውን የማውቅ?’ በዚ ዘመን ሰዎች በተለይ ወጣቶች ሰለብሪቲ(Celebrity) አምላኪ እየሆኑ ነው፡፡ ሳይንቲስቶች፣ አክተሮች፣ እስፖርተኞ፣ ዶክተሮች፣ ጋዜጠኞች እና ሌሎች ተወዳጅ ግለሰቦች የሚያደርጉት ንግግር እንደወረደ የመቀበል አዝማሚያ ይታያል፡፡ መታወቅ ያለበት ብልህ እና ሙህራን ሰዎች ስህተት ሊሠሩ ይችላሉ፡፡ እኔ ከሀይማኖት የራኩት ከልቤ እንጅ በማንም ምክር እይደለም በእርግጥ የሀይማኖት፣ የሳይንስ እና የፍልስፍና መጽሐፍትን አነብ ነበር፡፡ ዛሬ የጨለማው ዘመን ብርሃን የምላቸው ሁሉም ክርስትናን ቢቀበሉ እንኳ ለራሴ እስካልመሰልኝ ድረስ ምንም አይምስለኝም፡፡ ስላልመሩኝ አልከተላቸውም፡፡

ብዙ አማኞች አንስታየንን እንደምሳሌ እያነሱ ስለ እምነት በጎነት የተናገራቸውን ንግግሮ እንደምሳሌ በመውሰድ አማኝ እንደነበር ሊያስረዱ ይሞክራሉ፡፡ ነገር ግን አስፈላጊ እንኳ ቢሆን አንስታየን በግሉ አማኝም ኢ-አማኝም አልነበረም፡፡ እንደ ማሰረጃ ሃይለ ጊዮርጊስ ማሞ (ጲላጦስ) ካዘጋጀው <ጥበብ ቅጽ አንድ> ገጽ 230-232 የተወሰኑ ሃሳቦችን ልዋስ፡፡

እግዚአብሔር እንግሊዞችን በመቅጣቱ ደስ ሲልህ ይገባል ላለው ሜየር ለሚባል ጋደኛው መልስ ሲሰጥ፦ “እኔ ከእግዚአብሔርም ሆነ ከእንግሊዞች ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌለኝ በሚገባ ታውቃለህ፡፡ የሰውን ዘር በምድር ላይ እየቀጣ ያለው

Created in Master PDF Editor

እግዚአብሔር ከሆነ ኃላፊነቱን ሊወስድ ይገባ ነበር፤ እግዚአብሔር የሚባል ነገር አለመኖሩ ግን በራሱ ይቅር አስብሎታል" በማለት መልሶለታል።

ራስህን ከእግዚአብሔር በላይ አድርገህ ታየዋለህ ብለው ለጠየቁት ተማሪዎች ሲመልስ፡- "አዎን! ከኢየሱስ በላይ ማድረግ ከቻልኩ እንዴት ከእግዚአብሔር ላንስ እችላለሁ። እኔ ከማደርገው በላይ ታደርጋላችሁ አላለም እንዴ?" በማለት መልሷል።

የቅርብ ጓደኛው አይሁዳዊ ሄይል ፍሬድማን የአይሁድ ዘር ሆነህ በእግዚአብሔር አለማመንህ ምንአልባት መጽሐፍ ቅዱስ ያለማንበብህ ውጤት ይሆናል በማለት ለፃፈለት ደብዳቤ ደግሞ መልስ ሲልክ፡- "ያነበብኩት መጽሐፍ ቅዱስ ኮፒውን ነው። በሙሴ የተፃፈው ኦሪጅናሉ ካለህ እባክህ ላክልኝ... በእግዚአብሔር መኖር የማላምን ኃይማኖተኛ መሆኔን ግን አሁንም የረሳኸው አይመስለኝም" ብሎታል።

በነገራችን ላይ አንስታየንን እንደምሳሌ ወሰድኩ እንጅ ብዙ ድንቅ ሳይንቲስቶችና ፈላስፎች ከተወዳጅነታቸው አንጻር አማኝ ለማስመሰል ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል። ብዙዎችም የዚህ ጥቃት ሰለባ ሁነዋል፣ ለምሳሌ ዳርዊን። በእርግጥ ብዙ አማኝ የሳይንስና የፍልስፍና መኖራቸውን አልክድም በተለይ ኒውተን። ግን ለምን?

In fact, ይላልMichael Shermer "in fact, many smart people believe weird things, and they do so because they are skilled at defending beliefs they arrived at for non-smart reasons." (Skepticism 101, page, 6)በኬምስትሪ ሙህር የሆነ በፊዚክስ ሙህር ላይሆን ይችላል። የሚደንቅ የእስፖርት ሪከርድ የሚሰብር የስነ-መለኮት እውቀት ላይኖረው ይችላል። ከሀገር አቀፍ እስከ አለም አቀፍ የሽልማት ብዛት የሚንጎዳጎድለት አክተር የስነ-ህይወት እውቀት ላይኖረው ይችላል። ሰውን ከሞት አፋፍ የሚያተርፍ ዶክተር ስለ ዝግመተ ለውጥ ዕውቅና ላይኖረው ይችላል። ሲናገር የማይሰለች ተናጋሪ ስለ ሀይማኖቶች ታሪክ ላያውቁ ይችላሉ። የከበደውን አቅሎ፣ ሚስጡሩን ገልጦ የታሰረውን ፈትቶና የጨለመውን አብርቶ የሚሰብክ ቄስ ስለ ተፈጥሮ ሳይንስ እውቅና ላይኖረው ይችላል። አንድ ሰው በአንድ ዘርፍ የተሳካለት ሊሆን ይችላል። በዚያ በተሳካለት ዘርፍ የሚተነትነው እውነት ሊኖረው ይችላል። ነገር ግን ስለ ሌሎች ጉዳዮች የሚመስለውን ይናገራል እንጅ ጥልቅ እውቀት አይኖረውም።

አንድ የማራቶን አሸናፊ ፀሀይ አምላኪ ያሸነፈበት ሚስጥር ፀሀይን በማምለኩ እንደሆነ ጋዜጣዊ መግለጫ ቢሰጥ ስኬተማ ለመሆን ፀሀይን መለማመን ያለብን አይመስለኝም። ስኬታማ የመሆን ሚስጢር ፀሀይን በማምለክ በሆን ኑሮ ስኬት የሚፈልጉ ሁሉ ፀሀይን ባመለኩ ነበር። ግን ፀሀይን፣ ጨረቃን፣ ከዋክብትን

Created in Master PDF Editor

ተራሮችን፣ ወንዞችን እና ዛፎችን የሚያመልኩ ስኬታማ ሊሆኑ ወይም ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ምርጫውና እድሉ ያለው ከመዳፋችን ይመስለኛል ማለቴ ከእጃችን፡፡

24. ሀገር የምትመሰረተው፣ የምትጠበቀው በፈጣሪ ነው ኢትዮጵያ እንደማሳያ

እምነት እና አስተዳደር ተነጣጥለው በሚቆሙበት ማኅበረሰብ ውስጥ የቄሳርን ለቄሳር፣ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ነጥሎ መተንተን ይቻል ይኾናል፡፡ የእኔ እና የአንተ ማኅበረሰብ ግን የቄሳር እና የእግዚአብሔር ጥምር መንግሥት ውጤት ነው፡፡ አንዱን ካንዱ ነጥሎ መመልከት ብዙ አይሳካም፡፡ የኢትዮጵያ የረጅም ዘመን ታሪክ እና ባሕል ባንድ ገጹ ስናየው ሃይማኖታዊ ነው፡፡ የእኛ ከሃይማኖታዊነትም የባሰ ነው፡፡ ምናልባት ተክለሃይማኖታዊ ነው የሚለው የተሻለ ይገልጸዋል፡፡ (በእውቀቱ ስዩም፣ እግር ዐልባው ባለ ክንፍ)

ሳይንስ የኢትዮጵያ ባህል ክፍል እንዲሆን ገና ብዙ ይቀረናል፡፡ እንዲሆንም ደግሞ ብዙ ጥረት፣ ብዙ ለጉዳዩ ታታሪ የሆኑ የሳይንስ ምሁሮች ተግባር ያስፈልጋል፡፡ በአምልኮና በተለያዩ ዕመነቶች የተተበተበው ባህላችን ያደራበት ጨለማ ገለል የሚለው ሳይንስ የባህላችን ክፍል ሲሆን ነው፡፡ (ሽብሩ ተድላ፣ የህያው ፈለግ፣ 2010 ዓ.ም)

ሀገራችንን በተመለከተ ትልቁ ቁጭታችን እንዴት ማሽኖችንና መኪኖችን፣ ድልድዮችንና ህንፃዎችን መስራት አቃተን የሚለው ሳይሆን፣ እነዚህን ነገሮች እንዳንሰራ ምንድነው ያፈዘዘን ምንድነው የስራና የፈጠራ ክህሎታችንን የሰለበብን? የሚለው ነው፡፡ ምንድነው ለመለወጥና ለመሻሻል፣ ለዕድገትና ለብልፅግና ያለንን ተነሳሽነት የገደለብን? ምንድነው ለዕውቀትና ለአዲስ ነገር ያለንን ፍላጎት ያኮላሸብን? ምንድን ነው እንዳንለወጥና እንዳንሻሻል ሰቅዞ የያዘን? የሚለው ነው ዋናው ቁጭት፡፡ . . . እንዴት ፈጣሪዎችን፣ ለዕውቀት የሚተጉ ሰዎች፣ ለለውጥና ለአዲስ ነገር ጉጉ የሆኑ ሰዎችን ባህላችን መፍጠር ተሳነው? ከመቼ ጀምሮ ነው ባህላችን እንደዚህ መሐን የሆነው ለሚለው ቁጭታችን መልሱ አንድና አንድ ነው እሱም ከ6ኛው ክ/ዘ መጨረሻ ጀምሮ 'በክርስቲያናዊ ደሴትነት' ከዓለማቀፍ ንግድና ባህል ተነጥለን እንደ ማህበረሰብ የብሕትውና (የብቸኝነት) ህይወትን መምረጣችን ነው፡፡" (የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ 4ኛ ዕትም፣ 200-204)

ርግጥ ነው ይላል ዳንኤል ክብረትም

ርግጥ ነው በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የተፈጠሩ የመስተጋብር ችግሮች ሁሉ በኛም አገር ተፈጥረዋል፡፡ በኛ አገር የተፈጠሩትም በሌሎች ይገኛሉ፡፡ በዓለም ሕዝቦች ታሪክ ውስጥ የኩራትም የውርደትም፣ የፍቅርም የጠብም፣ የሰላምም የጦርነትም፣ የእኩልነትም የጭቆናም፣ የመረዳዳትም የመጠፋፋትም፣ የሥልጣኔም የሥይጣኔም ታሪኮች አሉ፡፡ እንኳን በአንድ አገር የሚኖሩ የተለያየ ዘውግ፣ ቋንቋ፣ እምነትና

Created in Master PDF Editor

የኑሮ ደረጃ ያላቸው ቀርተው በተመሳሳይ ቋንቋ፣ ባሕልና የኑሮ ደረጃ የሚገኝ የአንዲት አገር አንድ ወጥ ሕዝብ እንኳን በውስጡ ጽጌረዳም እሾህም አለው:: የሚገርመው ነገር ኢትዮጵያን ከዓለም የተለየች የሚያደርጋት ምን እንደሆነ አለመታወቁ ነው:: ኢትዮጵያኮ ሲኦልም አልነበረችም፤ መንግሥተ ሰማያትም አልነበረችም:: አገር ነበረች፤ አሁንም አገር ነች:: (ዳንኤል ክብረት፣ የቀለም ቀንድ ቅፅ 3 ቁጥር 11)

የኢትዮጵያን ሁኔታ የሚገልጽ ግጥም ኢንተርኔት ላይ አግኝቸ ደጋግሜ አነበብኩት:: ግጥሙ "ምን ያደርጋል ሀገር.....?" የሚል ርዕስ ተሰቶታል:: ማን እንደጻፈው ባላውቅም ሶረኔ - መስከረም - 2011 የሚል ማስታወሻ ግን ተጽፎበታል::

ምን ያደርጋል ሀገር፣ .... ምን ሊበጅ ዜግነት፣

ወልደው ካልሳሙበት፣.... ዘርተው ካልቃሙበት፣

ህጻናት በመስኩ፣.... አዛውንት በሸንጎ፣.... ደምቀው ካልታዩበት፣

እምቦሳን በጓሮ፣.... ጥገትቱን ከጨፌው፣... ታስረው ካልዋሉበት፣

ጋማ ከብቱ በመስክ፣... አውሬም በውርማ፣... ሞልተው ካልታዩበት፣

ፏፏቴው በዳገት፣... ጅረት በሸለቆ፣... ሲፎክር ካልሰሙት፣

ተራራውም በደን፣... ክምሩ ባውድማ፣.... ገኖ ካልታየበት::

ምን ያደርጋል ሀገር......?

ከሰው ተወዳጅተው፣... ከሰው ተዋውለው፣.... ህይወት ካልመሩበት፣

ቅጠሉን በጥሰው፣... አፈሩንም ልሰው፣.... ቆመው ካልሄዱበት፣

አርሰው፣ አሳርሰው፣.... ነግደው፣ አትርፈው... ሐብት ካልደረጀበት፣

ከእውቀትም ጨልፈው፣... በሳይንስ ተራቀው፣... ለድገት ካልሰሩበት፣

እናቶች፣ ህጻናት፣... መበለት፣ አዛውንት፣... ካልተከበሩበት፣

ታመው ካልዳኑበት፣... አርጅተው አፍጅተው፣... ካልተቀበሩበት::

ወጥተው ካልገቡበት፣.... ሰርተው ካልኖሩበት፣

ከሸንጎው ዳኝነት፣.... ከወንበሩ ፍትህ፣.... ነጥፈው ከጠፉበት፣

መብት ሚዛን አጥቶ፣.... ስርዓት ባገር ጠፍቶ፣... እብሪት ከገዛበት፣

ዜግነት ከሀገር፣.... ማንነት ከአንድነት፣.... ሰላም ከመቻቻል፣... ከተለያዩበት፣

Created in Master PDF Editor

ባሳብ ተደራጅተው፣... ደግፈው ተቃውመው፣... ውለው ካልገቡበት፣

በልዩነት ደምቀው፣... በባህል፣ በእምነት፣... ካልተከበሩበት።

ምን ያደርጋል ሀገር......?

መውጣትና መግባት፣.... መኖርና መስራት፣... ከሚያስጨንቁበት፣

ያገር መውደድ ፍቅር፣.... ነጻነት፣ አርነት፣... ወንጀል ከሆነበት፣

ቃዬል በመንበሩ፣... ይሁዳ ከልፍኙ፣... ከሰለጠኑበት.

ዜጋው ጠላት ሆኖ፣... ዘራፊና ባእድ፣.... ተከብረው ካሉበት፣

ስደትና ረሀብ፣.... እስራትና ሞት፣.... ዳረጎት ከሆኑት፣

በስልጣን መባለግ፣.... በሀብት መንደላቀቅ፣... ገነው ከታዩበት።

የሰው ነፍስ ረክሶ፣... በየጉራንጉሩ፣.... ጭዳ ከሆነበት፣

ውንብድና ባገር፣... ሸንጎ ተቀምጦ፣... ህግ ካረቀቀበት፣

ከሐዲ በዙፋን፣... ገንጣይ ባማካሪ፣... ነግሰው ከኖሩበት፣

ጦቢያ ማለት ቀርቶ፣.... ቋንቋ፣ የዘር ሐረግ፣... ሀገር ከመሩበት.

የእብሪት ማራገፊያ፣... ያአምባገነን ቅርሻት፣... መትፊያ ከሆኑበት.

ምንስ ሀገር አለን......!

በስሟ እምንጠራት፣....ምን ወዳጅ ተገኝቶ፣... ወገኔ የሚሉት።

ሲታመም ካላዩት፣... ሲወድቅ ካላነሱት፣... ሲሞት ካልቀበሩት፣

ሲቸገር ካልረዱት፣.... ሲራብ ካልጎበኙት፣.... ሲዳር ካላኮሩት፣

ሲበደል ሲጨቆን፣ ድምጽ ካልሆኑለት፣ እጅ ካልዘረጉለት

በሸንጎ ተሟግተው፣... መብቱን አስመልሰው፣.. ካላስከበሩለት፣

ዘምተው ግዳይ ጥለው፣... ወድቀው ተሰውተው፣...ታሪክ ካልሰሩለት፣

ውርደቱን በክብር፣..... ጥቃቱንም በድል፣... ታግለው ካልቀየሩት፣

ቢፎክር፣ ቢቅራሩ፣... ሀገር! ሀገር! ቢሉት፣... ዲስኩር ቢያበዙለት፣

ህንፃው ቢደረደር፣...አስፋልቱ ቢነጠፍ፣... ግድብ ቢሰሩለት፣

ምን ያደርጋል ታዲያ፣... ምን ያደርጋል ሃገር፣.... ያለሰው ቢወዱት።

ይህ ታልቅ የቁጭት ግጥም ሀይል አለው። ከሩቅ የሚጣራ ሀይል ወደ ፊት የሚገሰግስ ሀይል፣ እንቅፋቶቹን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሃይል። ከገጠሙ አይቀር እንዲህ ነበር መግጠም። ለኢትዮጵያ እና ለልጆቿም መልካም ምልዕክት ይዟል።

Created in Master PDF Editor

ኢትዮጵያ ሶስት አይነት ልጆች አሏት፡፡ በጣም የሚወዷት፣ በጣም የሚጠሏት እና በመውደድ በመጥላት መካከል ያሉ፡፡ በጣም የሚወዷት ከፍቅራቸው የተነሳ ሀገራቸው በምንም አይነት መንገድ በክፉ እንድትነሳ አይፈልጉም፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ የሁሉም ሀገር መጀመሪያ ናት ብለው ያምናሉ፡፡ ለምሳሌ፡- የስልጣኔ ሁሉ መጀመሪያ ናት፡፡ የሰው ልጅ መጀመሪያ ናት፡፡ የሀይማኖት መጀመሪያ ናት፡፡ የሰላም፣ የፍቅር እና የነፃነት ሀገር ናት ይላሉ፡፡

በአለም ውስጥ ያለው መልካም ነገር ሁሉ ምንጩ ኢትዮጵያ ናት ብለው እራሳቸውን ያሳምናሉ፡፡ በዚህ ዘመን የምናያቸው እጅግ የተራቀቁ ፈጠራዎች በጥንት ጊዜ አባቶቻችን የሞከሯቸው እና ሲጠቀሙባቸው የነበሩ ናቸው ይላሉ፡፡ በዝግመት ለውጥ የማያምኑት ሳይቀሩ የመጀመሪያ የሚለውን ክብር ላለማጣት ኢትዮጵያን የሰው ዘር መገኛ ይሏታል፡፡ ይህ ማለት ሰው ሁሉ የተበተነው ከኢትዮጵያ ተነስቶ ነው ለማለት ነው፡፡ እንዲያውም በመጽሀፍ ቅዱስ የተጠቀሱ ቅዱሳን በሚደንቅ ሁኔታ ክርስቶስን ጨምሮ ኢትዮጵያዊን እንዳሆኑ ያምናሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ አዳም እና ሄዋን እራሳቸው የተፈጠሩት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ያላሉ፡፡ እግዚአብሔርም ኢትዮጵያ ከማንም ሀገር አስበልጦ ይወዳታል ይላሉ፡፡ ካስፈላገቸውም ከመጽሀፍ ቅዱስ እናንተ የእስራኤል ልጆች ለእኔ እንደ ኢትዮጵያዊያን አይደላችሁምን የሚለውን እና ሌሎችንም ይጠቅሳሉ፡፡ የእነዚህ ሰዎች ፍላጎት ኢትዮጵያ የመልካምነት፣ የሰብአዊነት፣ የነፃነት፣ የጀግንነት እና የስልጣኔ መሰረት መሆኗን ማመን እና ማሳመን ነው፡፡

ችግራቸው ስለ ኢትዮጵያ አንዳች ክፉ ነገር የሚያወራ፣ የሚፅፍና የሚያስተምር ካዩ አይናቸው ይቀላል፣ ጥርስቸው ይንቀጫቀጫል፣ እራሳቸው ይዞራል እናም ሙሉ ሰውነታቸው ይደነዝዛል፡፡ ስለ ኢትዮጵያ አንዳች ክፉ ዜና መስማት አይፈልጉም፡፡ እነዚህ ሰዎች በእየሚዲያው፣ በእየመፅሀፎቻቸው፣ እና በእየሰብሰባው ስለ ኢትዮጵያ የአለም ቁንጮነት አውርተው አይጠግቡም፡፡ ከፍቅራቸው የተነሳ ብዙ ይዋሹላታል፡፡

ፍቅር እውር ነው የሚባለው ለእነዚህ ሰዎች በትክክል ይሰራል፡፡ በኢትዮጵያ ጉዳይ ሜዳውን ተራራ ነው ካሉ አበቃ፡፡ እነዚህን ሰዎች ስለ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊን ክፉ አጋጣሚዎች እና በርካታ የመክሸፍ ታሪኮች ብትነግሯቸው አይሰሙም፣ ቢሰሙም አይገባቸውም፣ ቢገባቸውም አያምኑም፣ ምን አልባት ቢያምኑም እንኳ ያስተባብላሉ እንጅ እውነቱን መጥፎ ታሪክ እንዳወረደ አይቀበሉም፡፡ እነዚህ ሰዎች በሆነ ጊዜ እንደነበሩ አባቶቻቸው ኢትዮጵያ ከአለም ምንም አትፈልግም እንዲያውም ለአለም የሚበቃ በረከት አላት ይላሉ፡፡ ይህ አስተሳሰባቸው ከኢትዮጵያ ውጭ ያለው አለም የሰይጣን እንደሆነ እና ላለመገናኘት ደግሞ የዝግ ፖሊሲ መተግበር አለበት ይላሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ውጮች ባህላችንን እና ስልጣኔያችንን ዘርፈውናል እያሉ

Created in Master PDF Editor

ሁሌም ይከሳሉ። ከዚህም አልፈው ውጮች የዘረፉን ሀብት ባይበቃ አሻሽለው እና አሰይጥነው ያመጡትን የአኗኗር ዘይቤ በልጆቻችን ላይ ጥለውብናል ብለው ያማርራሉ። ከእነዚህ ሰዎች ስለኢትዮጵያ ክፉ ነገር ስለ ነጮች መልካም ነገር መስማት ብርቅ ድንቅ ነው።

ከእነዚህ ሰዎች ጋር ስለ ኢትዮጵያ፣ ስለ ኢትዮጵያዊነት፣ ስለፍልስፍና፣ ስለ ሳይንስ፣ ስለ ታሪክ እና ባህል ማውራት ትርፍ ጥላቻ ነው። ከእነሱ በተቃራኒ ያለ ሰው የኢትዮጵያ ጠላት ከሀዲ ተደርጎ ይቆጠራል። ለውይይት ያህል ኢትዮጵያ ኋላቀር ሀገር ናት ብትሉ ምን ይመልሳሉ? መጀመሪያ ሀሳቡ በመነሳቱ ይናደዱ እና መልስ ፍለጋ ፊታቸውን ያኮማትራሉ። ከዚያም እናንተ የአክሱም፣ የላሊበላ፣ የጎንደር፣ የጣና እና የሌሎችም ብርቅ እና ድንቅ ቅርሶች ባለቤት እንዴት ኋላቀር ትላላችሁ። አይገባችሁም እንጅ የአለም ስልጣኔ የተኮረጀው ከኢትዮጵያ ነው። በራሳቸው መልስ መርካት ሲጀምሩ ፊታቸው ይፈታል። ማሳመናቸው ይቀጥላል። ኢትዮጵያ እኮ ምርጥ ባህል፣ ልዩ ስልጣኔ፣ ድንቅ አኗኗር፣ ተመርምሮ የማያልቅ ዕውቀት፣ ቀና የሆነች ያለተበረዘች ሀይማኖት ያላት ሀገር ናት። ቅድስት ኢትዮጵያየ እያሉ ይቀጥላሉ።

ዘፈናቸው እና ሙዚቃቸው ኢትዮጵያ ሀገሬ ይመርልሽ ሰብሉ እና የመሳሰሉት ሲዘምሩም እኛ አልተሳሳትም መሰል ናቸው።በአጭሩ እነዚህ ሰዎች ኢትዮጵያን ከመቶ አንድ ሽህ ፐርሰንት የሚወዱ ከሷ ውጭ ያለው ከንቱ የሚመስላቸው ከዚህ የእብድ ፍቅር መውጣት በየብስ ለመኖር እንደሚቸገር አሳ ናቸው። ሙሉ ሃሳባቸው የሚያጠነጥነው በኩሬው ውስጥ ብቻ ነው።

ሁለተኞቹ ኢትዮጵያን አምረው የሚጠሉ እነዚህ ኢትዮጵያን በመጥላት የሚደሰቱ ናቸው። ሲጀምሮ ኢትዮጵያ ማለት እኮ ምድራዊ ሲኦል ናት። ኢትዮጵያ ማለት እኮ በመከራ የተቃጠሉ ሰዎች የሚኖሩበት ሀገር ናት። ኢትዮጵያ ማለት እኮ እደሜ ዘመኗን የሞት፣ የድርቅ፣ የጦርነት፣ የቸነፈር፣ የባርነት፣ የበሽታ፣ የዕልቂት፣ የፍጅት፣ የወረርሽኝ በአጠቃላይ የክፉ ነገር ሁሉ ምሳሌ ናት ይላሉ።

ኢትዮጵያ እኮ ለአለም መድረክ ታፍራ እና ተከብራ ሳይሆን አፍራ እና ተዋርዳ ነው የኖረችው በ3000 ዘመን 3000 ጊዜ የከሸፈች ሀገር ማለት ኢትዮጵያ ናት። ፈጣሪ አለምን ሲፈጥር በወር ሰባት ቀን ሳይሆን በወር ሰላሳ ቀን ደም ይፈሰስሽ ብሎ የረገማት የምትመስል ልጆቿ ከተወረሩ ከውጭ ወራሪ ጋር፣ ወራሪ ካልመጣ እርስ በእርሳቸው የሚጋደሉበት የደም ገንቦ ብትሆንም የባሩዱ በርሚልም ናት ይህን ማንም ይመሰክራል ይላሉ። ስልጣኔ ፊቱን ያዞረባትና መክሸፍ የሰለጠነባት ሀገር መሆኗን ይመሰክራሉ። ለነገሩ በፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም “በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እስከዘመናችን ድረስ ያልከሸፈው አንድ ነገር ብቻ ነው እሱም የሀገራችን ነፃነት ነው፤ የነፃነትንና ክብርን ከአባቶቹ የወረሰው ትውልድ ግን ለሚቀጥለው ትውልድ ምን

Created in Master PDF Editor

አወረሰ? ምን አዲስ ነገርን ፈጠረ? ማህበረሰቡን በምን የኑሮ ደረጃ ላይ አደረሰ? ጥሬ በወፍጮ በሰው ጉልበት መፍጨት፣ጌሾ ቆሞ በሰው ሀይል በጉልበት መውቀጥ ስንት ምዕተ ዓመታት ፈጁ? ጎጆ ውስጥ በመኖር ስንት ትውልዶች አለፉ? አህያ ስንነዳ ስንት ትውልድ ተፈራረቀ? ከበቅሎና ከፈረስ ፍጥነት ሳንወጣ ስንት ዘመናት አስቆጠርን?” ይልላቸዋል:: (መክሽፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ፣ ገጽ 9-10)

እነዚህ ሰዎች የሚመረጡት ዘፈን ‘አረ አይነጋም ወይ’ን ከቴዲ አፍሮ፣ ‘ዋይ ዋይ’ን ከጥላሁን ገሰሰ እና ይህን መስል ብሶት የሚያንፀባርቁትን ነው:: ከዘመሩም ተውከን፣ ራከን፣ ወዘተ ነው:: ሲያነቡም መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ፣ በአባቶቻችን አፈርን መስል የቁጭት መጽሃፍት ላይ ያተኩራሉ::

እነዚህ ሰዎች ባለፉት ሶስት ሽህ ወይም ሁለት ሽህ አመታት በኢትዮጵያ ምድር ስለተከሰቱት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሀይማኖታዊ ችግሮች መደስኮር ሱሳቸው ነው:: ክንፍ ቢኖራቸው ኑሮ ኢትዮጵያ የምትባልን ሀገር ትተው በበረሩ ነበር:: ብዙ ጊዜ ኢትዮጵያ የሲኦል ምሳሌ እንደሆነች አድርገው ይስሏታል:: ለደረሰው ጥፋት እና ለአጋጠሟት መከራዎች አባቶቻቸውን በተለይም እድሏን ተጠያቂ ያደርጋሉ:: ከዚህ ሀገር መወለድ አለመታደል እንደሆነ ያምናሉ:: ስራቸው ሁልጊዜ ማማረር ነው:: ተመስገን ሲሉ አትሰሟቸውም ሁሌም ያለቃቅሳሉ:: የፈለገውን ያህል ቢሳካላቸው በባርነት ቀንበር ውስጥ እንዳሉ ይሰማቸዋል:: ኢትዮጵያ ውስጥ የተሰሩት ጥንታዊ ስልጣኔዎች የውጭ ሀገራት ጥበብ ነው ብለው ያምናሉ:: የአክሱም ስልጣኔ ከመካከለኛው ምስራቅ፣ የላሊበላ እና ምንኩስና የፈጠረውን ስልጣኔ ከግብፅ እና የጎንደር ስነ ህንፃ ካፖርቹጋል የተኮረጀ አሊም እራሳቸው የውጭ ዜጎች የሰሩት ነው ይላሉ:: ኢትዮጵያ በኋላቀርነት ኑሬ ምሀይምነትን እና ዘረኝነት ተጎናፅፋ የምትኖር በምስራቅ አፍሪካ ቀንድ የምትገኝ ሁሉ የሚወጋት ሁሉን የምትወጋ የበሬ ቀንድ ናት:: ህዝቦቿ ሰነፍ ስራ ጠል፣ ወንዞቿ ቢሊዮን ዶላር ከልወጣባቸው የማይጠለፉ፣ ቋሚ የወቅቶች መፈራረቅ የሌላት፣ አፈሯ አሲዳማ፣ መንግስቶቿ ቀማኛ፣ ሙህራኗቿ ጉረኛ፣ አገልጋዮቿም ተገልጋዮቿም ሙሰኛ፣ ሚድያዎቿ ጎጠኛ፣ አረ ስንቱን ችግር እንጥራው ይላሉ:: በጥቅሉ እነዚህ ሰዎች ስለ ኢትዮጵያ የሚያስታውሱት ደንቃራ ታሪኳን እና የደንቀራ ልጆቿን ተግባር ነው::

ሶስተኛ ወደው የሚጠሏት፣ ጠልተው የሚወዷት እነዚህ ሰዎች ጥረት ያለ አቋም የላቸውም:: ዛሬ ስለ ኢትዮጵያ መድረክ ላይ ሲሰብኩ ብታገኟቸው ነጋ ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያን አምርረው ሲጠሉ ታገኟቸዋላችሁ:: ኢትዮጵያ እንዳይወዷት እሬት እንዳይጠሏት ማር የምትሆንባቸው ተለዋዋጭ መንፈስ ናት:: ስኬቷን ሲያስቡ በደስታ ይቦርቃሉ መክሸፍን ሲያስቡ በሀፈረት ይኮመሸሻሉ:: ኢትዮጵያ ከሚጠላ ጋር ይጠላሉ ከሚወድ ጋር ይወዳሉ:: ቢሆንም ለመጥላታቸው እና ለመውደዳቸው ለዘብተኛ

Created in Master PDF Editor

ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል ያሉ ዜጎች ፍፁም ጥላቻም ፍፁም ፍቅርም የላቸውም ሁሉም ነገር ወቅታዊ እና አንፃራዊ ነው፡፡ ለእነዚህ ሰዎች የውጭ የውስጥ የሚባል ባህል፣ ስልጣኔ ፍልስፍና፣ ሳይንስ፣ ሀይማኖት የለም፡፡ ባህል ባህል ነው፡፡ ስልጣኔ ስልጣኔ ነው፡፡ ሳይንስ፣ ፍልስፍና እና ሀይማኖት ያው የዕውቀት ምንጮች ናቸው፡፡ የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው አይነት ናቸው፡፡ አንድ ልብስ ኢትዮጵያ ይስራ፣ ቻይና ይስራ፣ አሜሪካ ይስራ አይመለከታቸውም የሚፈልጉት ልብስነቱን ብቻ ነው፡፡ የእነዚህ ሰዎች ጥሩ ባህሪ ለደንበር የላሸ አስተሳሰብ ቅርብ መሆናቸው ነው፡፡ ለውጥን አይፈሩም፡፡ የሬድዮ እና የስልክ ሞገድ የሰይጣን ስራዎች ናቸው ብለው አያምኑም፡፡ መሰልጠን መሰይጠን ነው ብለው አያምኑም፡፡

መልካም የመሰላቸውን ነገር ከማህበረሰቡ ብዙም ሳያፈንግጡ ያደርጉታል፡፡ በማህበረሰቡ መሳሳም ክልክል ቢሆን በራቸውን ዘግተው ይሞጫሞጫሉ፡፡ በማህበረሰቡ ጭፈራ ቤት መሄድ ክልክል ቢሆን የጭፈራ ቤት ክንውኖችን ከቤታቸው ያደርጋሉ፡፡ ከኢትዮጵያዊ የቆየ ልምድ በይፋ ሳይሆን በድብቅ ያፈገፍጋሉ፡፡ እንዲያውም ኢትዮጵያዊነትን እና ውጫዊነትን ቀይጠው መልካም መዓዛ ያለው እስፕሪስ ባህል፣ ዕውቀት እና ሀይማኖት ይፈጥራሉ፡፡ እጅግ በጣም ልክ ናቸው አንድ ቅጠል ብቻውን መድሀኒት አይሆንም፡፡ አንድ ምግብ ሁሌ መብላት ይሰለቻል፡፡ አንድ መፅሀፍ ሁሌ መድገም ድካም ነው፡፡ ሁሌም አዲስ ባህል፣ አዲስ ፍልስፍና፣ አዲስ ሳይንስ፣ አዲስ ሀይማኖት፣ አዲስ ዝማሬና እና ፀሎት፣ አዲስ ታሪክ፣ አዲስ አኗኗር ብዙ አዲስ ነገር ያስፈልገናል፡፡ ቢሆንም ጠቢቡ ሰለሞን እንዳለው ከፀሐይ በታች አዲስ ነገር የለም፡፡ ምን ማለት ነው? አዲስ ነገር ማለት ያለን ነገር በመገጣጠም የሚፈጠር ልዩ ክስተት ነው፡፡ ነገቲቭ ቻርጅ እና ፖዘቲቭ ቻርጅ ሲገናኙ ሀይል ይፈጠራል፡፡ ሴት እና ወንድ ሲገናኙ ሌላ ሰው ይፈጠራል፡፡ እግዚአብሔር እና ሰይጣን ሲገናኙ ዕውቀት ይፈጠራል፡፡ አዲስ ነገር በነገሮች ስምምነት ከሚሆን በፍትጊያ ቢሆን ይመረጣል፡፡ በነገሮች ፍተጊያ ውስጥ ነው ሀይል የሚወለደው፡፡ ያን ሀይል ነው አዲስ ነገር የምንለው፡፡ ወገኖች ማንም በፍፁም አትወደዱ ምንንም በፍፁም አትጥሉ፡፡

እግዚአብሔር እሱን በፍፁም እንድትወዱት እና ሰይጣንን በፍፁም እንድትጠሉት ነግሯችሁ ነበር፡፡ እኔ ግን እላችኋለሁ ሁለቱንም ወደ ቤታችሁ እንዲመጡ ፈቀዱላቸው፡፡ ሁለቱም በእኩል ግን በተቃራኒ አቅጣጫ ወደ ህሊናችሁ ይግቡ፡፡ በግጭቱ የሚፈጠረውን አላውቅም ነብይ አይደለሁምና ነገር ግን አዲስ ሰው እንደምትሆኑ አልጠራጠርም፡፡ በአባቶቻችን ኩራን የሚል መጽሀፍ የሚያነብ ሰው 'በአባቶቻችን አፈርን' የሚል መጽሀፍ ሲያይ መበሳጨት የለበትም፣ ቢችልስ ያንብና ይቃወም፡፡ በእርግጥ መጽሃፉ ተጽፏል፣ ፍልጋችሁ አንቡት፡፡

Created in Master PDF Editor

ለመሆኑ ኢትዮጵያ እግዚአብሔር ሀገርን እንደሚመሰረት ማሳያ ናትን?

እንዳለጌታ ከበደ ሸገር ብሎግ ላይ እንዲህ ጽፎ ነበር “ኢትዮጵያ በአማልክት አንደበት ስትገለፅ ደሴቶቿ የተቀደሱ፣ ወንዞቿዋ ያማሩ፣ ውሃዎችዋ የጠሩ፣ ዛፎችዋና ተራራዎችዋ የተዋቡ መሆናቸውን አንብበናል። ኢትዮጵያ፣ ከግሪክ አማልክቶች ሁሉ የበላይ በሆነው በዜውስ ልቦና ስትመዘን ነቀፌታ የማይገኝባቸው ህዝቦች መናኸሪ የመሆኗን በሆሜር ሥራዎች ውስጥ አንብበናል። ኢትዮጵያ፣ ታማኝ የአምላክ ባለሙዋሎች የሚያብቡባት ማለፊያ የአትክልት ቦታ መሆኗን በሙስሊም ድርሳናት አንብበናል።”

መርጌታ ፅጌ ኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ መንግስታት ባልና ሚስት ናቸው ይላሉ። ደፋሩ መርጌታ ፅጌ ትክክል ብለዋል። የባል የሆነ የሚስት ነው፣ የሚስት የሆነም የባል ነው። ስለዚህ የቤተ-ክርስቲያን የሆነ የመንግስት ነው፣ የመንግስት የሆነ የቤተ-ክርስቲያን ነው። ታሪክ አጥኝዎች እንደሚመሰክሩት የኢትዮጵያን የመንግስት ታሪክ ከኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን ታሪክ ለይቶ ማየት አይቻልም። አንዳንዴም ነገስታት የሆኑ ጳጳሳት፤ ጳጳሳት የሆኑ ነገስታት ነበሩ። ምንኩስናን ክህነትን እና ብታውህናን ከንጉስነት ጋር ደርበው እንደገዙ ይታወቃል። በኢትዮጵያ ታሪክ ቤተ-ክርስቲያን ሲሶ መንግስት ነበረች እየተባለ ሲወራ የሚያጉረመርሙ የቤተ-ክርስቲያን ሰዎች አሉ። እውነቱ ግን ሲሶ ብቻ ሳይሆን ግማሽ እንዲያው ከዚህ ይልቃል። ኢትዮጵያን ከመንግስታት ታሪክ ለይተን የማናየው ከሆነ በተጨማሪም ቤተ-ክርስቲያንን የመሰረታት እግዚአብሔር ከሆነ የኢትዮጵያን እና የኢትዮጵያን ነገስታት የመሰረታቸው እግዚአብሔር ነው ማለት ነው።

ኢትዮጵያን የመሰረታት ብቻ ሳይሆን ዳር ደንበሯን አስከብሮ መሀሏን ማርና ወተት የምታዘንብ የሰማያዊት እየሩሳሌም ምሳሌ አድርጎ የፈጠራት ሀገር ናት ማለት ነው። ኢትዮጵያ እግዚአብሔር የመሰረታት፤ ያፀናት እና የሚያስተዳድራት መሆኑን ሰባኪዎች ይሰብካሉ፤ ፖለቲከኞች ይፖለትካሉ፣ ጋዜጠኞች ያነባሉ፣ ሙህራን ይደሰኩራሉ፤ ትንቢተኞች ይተነብያሉ፤ ፅሀፊዎች በተለይም ተክለ ኪዳን እና ንቡረ ዕድ ኤርሚያስ ከበደ ይፅፈሉ።

ግርም የሚደርገኝ ኢትዮጵያን የመሰረታት እግዚአብሔር ከሆነ ቀሪዎቹን 200 ሀገራት የመሰረተቸው ሰይጣን ነው እንዴ? ጥያቄውን ተክለ ኪዳን እና ንቡረ ዕድ ኤርሚያስ ከበደ ይመልሱት። ነገሩ ግን አይደለም ሀገር የሚመሰረተው በህዝብ ነው፤ የሚተዳደረውም አማረሞ ከፋም ከህዝብ ሆድ በተወለዱ ሰዎች ነው። ሁሉን ነገር ለእግዚአብሔር መስጠት ልማዳችን ስለሆነ ነው እንጅ እግዚአብሔር ይሄን አይፈልግም። እሱ የሰራዊት ጌታ እንጅ ብርጋዴር ጀነራል አይደለም፤ እሱ የሁለንታ ዋና ፅሀፊ እንጅ ከብሔር እንተን የተወለደ ሀገረ ግዥ አይደለም። እግዚአብሔር

Created in Master PDF Editor

ሀገራትን ይባርክ ይሆናል፤ መሪዎችንም ጥበብ ይገልፅላቸው ይሆናል፤ ወታደሩንም አሸናፊ መንፈስ ያድለው ይሆናል፣ አንዳንድ ህልመኞች እንደሚሉት ግን ሀገር አይገዛም። የሀገር ጠ/ሚኒስትር ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ሊቀ መንበር ወይም የቤተ-ክርስቲያን ጳጳስ ወይም የጉባኤያት ስራ አስኪያጅ አይደለም።

የምንወደው፣ የምንመኘው እንዲሆን ማሰብ እንችላለን ካልሆነ ግን መራራውን እውነት መቻል መቀበል አለብን። የተለያዩ መራራ መጠጦችን እንደምንጠጣው ሁሉ መራራ እውነቶችንም መጎንጨት አለብን። እውነት ሁሌ መራራ ባትሆንም ጣፋጭ እንድትሆንም አይጠበቅም። ሀገራት ህዝቦች የመሰረቷቸውና የሚያሳተዳድሯቸው መሆናቸውን መቀበል የሚከብዳቸውና የሚመራቸው ቢኖርም ሀቅ እስከሆነ ድረስ ልባቸውን ክፍት ማድረጉ ተገቢ ነው።

የቆየ ባህላችን ያየን እንደሆነ እግዚአብሔር በትውልድ እስራኤላዊ ሲሆን በዜግነት ኢትዮጵያዊ ነው። ዜግነት የተሰጠው በሚገርም ሁኔታ ነው። የተወለደባቸው እስራኤልአዊያን ብዙ ዘመናትን በስደት ስለኖሩ እሱም ሲሰደድ ኑሯል። በኋላ ግን አለምን አዳርሶ እንደ ኢትዮጵያ የሚወደው ስላጣ ከዘጠኙ ቅዱሳን ጋር ዜግነት ተሰቶት ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖራል። ኢትዮጵያ ለእግዚአብሔር የሰጠችው ዜግነት ብቻ አይደለም ንግስና ክህነት እና ፈጣሪነት ጭምር እንጅ። ስለዚህ እግዚአብሔር ለኛ ለኢትዮጵያዊያን የማይሻር የማይገሰስ ንጉስ፣ የማያረጅ ካህን እና የእያንዳንዱ ሰከንድ ክስተቶች ባለቤት ነው።

የ1966 አብዮት ዙፋኑን አላዛነፈውም። ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር ኢትዮጵያ ውስጥ ከነገሰ ጀምሮ የኖረው በሠላም ነው ማለት አይደለም በአንዳንድ ጊዜያት በግለሰብም በቡድንም ሰዎች አምፀውበታል። ስልጣኑንም ሸራርፈው የወሰዱበት ነበሩ። ከዚህም ውስጥ አፄ ቴዎድሮስ፣ ፕሬዚዳንት መንግስቱ እና ጠ/ሚኒስተር መለስ ይገኙበታል። እነዚህ በመንግስተ ደረጃ ሲሆኑ በግለሰብ ደረጃ ደግሞ ፈለስፈው ዘረዓ ያዕቆብ እና እኔ የምንጠቀስ ይመስለኛል። በቅርቡ ቢሮው ድረስ ሂጄ ለዋራው ብዙ ጥረት አድርጌ ነበር በየስርጉ፣ በእየ ሀዘኑ፣ በእየ ንግዱ፣ በእየ ግጭቱ፣ በእየ ሽምግልናው፣ በእየ ግላዊ፣ ቤተሰባዊ እና ሀገራዊ ጉዳዮች ጥሪ ስለሚደረግለት ተገናኝተን ማውራት አልቻልነም። እግዚአብሔርን ካገኛችሁት የምትነግሩልኝ ቢኖር ምክትል አስተዳደሪ እንዲሹም ነው። ስራ እየተበደለ ነው።

በተጨማሪም ከመከላከያ ሠራዊቱ እስከ ሲቪል ሰርቪስ ድረስ ጥልቅ ተሀድሶ እንደሚያስፈልገው ንገሩት። ከሰማችሁ በአፅንኦት ንገሩት የ4ኛው ክ/ዘመን ወታደር ተይዞ በ10ኛው ምዕተ አመት አስተዳደራዊ ስርዓት እንኳን ህዝብ ቤተሰብ አይመራም በሉት። በግዛቱ መልካም አስተዳደር ከፈለገ ከካብኔው እስከ መዝገብ ቤት ያሉ ሠራተኞቹ በእሙያቸው ዘመናዊ ትምህርት መማር አለባቸው። ይልቅም ልቦናቸው

Created in Master PDF Editor

ስፊ መሆን አለበት። ኢትዮጵያ የሁላችንም ናትና እኛም የማናምነው ስንናገር ይስሙን።

ማንም ሀገሩን እንደሚወድ ሀገሬን እወዳለሁ። ከሌሎች ትበልጣለች ግን አልልም። ታሪኳ ሁለት መልክ አለው በአንድ በኩል ውብ ባህል፣ የሚደንቅ ፍቅር እና የሚያኮራ ጥበብ አለን በሌላ በኩል ጦርነት፣ ርሀብ እና በሽታ ወደባቸው ኢትዮጰያ ነው። ያለ ጦርነት፣ ርሀብና ወረርሽኝ የኖርንበት ዘመን የለም። ኢትዮጵያውያን እኮ ለገዳይ የሚዘፍኑ፣ በድህነታቸው የሚመፃደቁ እና ከሞት ጋር የተላመዱ ሰዎች ናቸው ብሉን መን እንመልሳለን።

ብዙዎቻችን የምናውቀው አስደናቂ ህንፃዎችን፣ ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያንን እና መስጊዶችን እና ድንቅ ስብጥራችንን ነው። ከዚህ ሁሉ ጀርባ ያለው ታሪክ ግን በጆሮአችን መስማት በአፋችን መናገር አንፈልግም። በእርግጥ ምንም አይጠቅምም ይሆናል ግን መርሳት የለብንም ታሪካችንና የረሳን ጊዜ እንዋሻለን። ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ለእመቤታችን የተሰጠች የተባረከች እና የተቀደሰች ሀገር ናት እስከ ማለት እንድርሳለን። ደንበሯ በመበዕክት የሚጠበቅ መንግስታቶቿ ከእግዚአብሔር የሚሻሙ እያለን ብዙ እናወራለን። እውነት ይሆን?

እኔ እንደገባኝ በኢትዮጵያ እንደማንኛውም ሀገር ሰዎች የመሰረቷት በደስታ፣ በአንድነት፣ በጦርነት፣ በርሀብና በእልቂት የኖሩባት እና የምንኖርባት ናት። እግዚአብሔር ማንንም ሀገር እንዳልመሰረተ ኢትዮጵያንም አልመሰረተም። አትዮጵያ አመልዕክትን ትፈጥራለች እንጅ አመልዕክት አልፈጠሯትም። እጇን ወደ እግዚአብሔር ብትዘረጋም ባትዘረጋም ያው ነው። እውነት እንናገር ካለን ለ2ሽህ አመታት እጃችን ዘረጋን አንዳንዴ ፍቅር እና ሰላም ሲዘንብልን ብዙ ጊዜ ግን ጦርነት፣ ርሀብና በሽታ ዘነበልን። ስለምትወዷት ኢትዮጵያ ብላችሁ እጁን ለዘረጋ ለማኝ እሳት ፍም ትሰጡታላችሁን? በአንጻሩ እጃቸውን ከመዘርጋት ይልቅ ጠንክረው የሰሩት በብዙ እርቀት አልፈውን ሂደዋል። ወደ ሰማይ አንጋጠን ሰናይ መናው ሳይዘንብ ቀረ። የተረፈንተስፋ ነው። በእርግጥ ተስፋ መልካም ነገር ነው ማንጋጠጥ ማለት ግን አይመስለኝም። በእውነት ለሽህ ዘመናት እጃችንን መዘረጋታችን ጠቅሞን ከሆነ ተቃውሞ የለኝም። ግን አይመስለኝም።

በነገራችን ላይ ሰነፎች ነን ብየ አላምንም። ኢትዮጵያዊያን ትጉህ ሰራተኞች ነበርን ሀይማኖት ግን አለሰራን አለ። በ1 ልደታ፣ በ3 በዓታ፣ በ5 አቦ፣ 7 ስላሴ፣ 12 ቅ/ሚካኤል፣ በ16 ኪዳነምህረት፣ በ19 ቅዱስ ገብርኤል፣ በ21 ማርየም፣ በ23 ቅ/ጊዮርጊስ፣ በ24 ተክልየ፣ በ27 መድሀኒአለም እና በ29 ባለእግዚአብሔር ዋና ዋና ስራ የማይሰራባቸው ቀኖች ናቸው። በእነዚህ ቀናት የሚሰራ ተወገዘ ነው በተጨማሪም ቅዳሜ እና እሁድ አለ። አረ ሌላም አለ በተለይ በእርሻና በአረም ሰዓት

Created in Master PDF Editor

ታአምር ተብሎ ለ2 ሳምንት ያህል መስራት አይችልም። በፈጣሪ እባካችሁ አስቡት በአመት ስንት ቀን እንሰራለን። ጠብ ያለ ነገር የለም እንጅ ወደን በፈቃዳችን ሳንወድ በሲኖዶስ አዋጅ ለሽህ ዘመናት ፀልየናል። ወንደሞች እና እህቶች እሁድ ጥዋት ተምረ ማርያም ከመነበቡ በፊት የተወገዘ ይሁና የሚለውን ምንበብ አስተውላችሁታል? እንደገና ስሙት እኔ አርዮስ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ሰው ተወግዟል። እነዚያ አባ ሚካኤል እና አባ ገብርኤል የሚባሉ አውጓዦች ግን እነማን ናቸው? እናንተ ያላችሁትን በሉ እኔ ግን አባ ገብርኤል እና አባ ሚካኤል የተወገዙ ይሁኑ ብያለሁ። ጊዜው እረስ በእርሳቸን የምንዋደድበትና የምንተባበርበት እንጅ አማልዕክትን የምንማጸንበት ጊዜ አይደለም። የረሱንን አማልዕክት ብንረሳቸው መልካም ነው።

እንዳለጌታ ከበደ አማልክት ሆይ ይላል፦

> አማልክት ሆይ የዛሬይቷን ኢትዮጵያ የምታዩበት መነፅር እንዴት ያለ ነው? ረስታችሁት ነው ወይስ ረስተናችሁ ነው? የዛሬይቷን ኢትዮጵያ እንዴት ባለ ሚዛን ነው የሰፈራችኂት? በእናንተ ሚዛን ስንሰፈር ከብደን ለመገኘት ከኛ ምን ትጠብቃላችሁ? ድህነትን እንደ ቆሻሻ ጥራጊ አርቀን እንወረውረው ዘንድ ስለምንድነው የመነቃቃት አቅማችንን የማታበረታቱት?ተቅበዝብዘን ስንጠፋ ዝም የማለታችሁ ምስጢር ምንድነው? በእናንተ አይን ድሮ እንዲያ ታይተናል። ዘንድሮስ እኛ ለናንተ ምንድን ነን?እንግዲያውስ ምንድነው የእኛ እጣ ፈንታ? ድህነትን አንበርክከን ለመግዛት፣ ድንቁርናን አስደንግጠን ለማባረር ለማን ምን መሳል ምን መሆን፣ ምን መስዋዕት ይጠበቅብናል?የመርገምት ልጆች የሆነን ይመስል በውርደት ውስጥ የመኖራችን ምስጢር ምንድነው ብለው ለሚጠይቁን የአገር ተወላጆች ምላሻችን ምን ይሁን? (እንዳለጌታ ከበደ፣ ሽገር ብሎግ)

Created in Master PDF Editor

ክፍል ሦስት

ሐዋርያው ቅዱስ አርዮስ ማን ነው?

እኔ ሐዋርያው ቅዱስ አርዮስ የተወለድኩት በገጠሪቱ የኢትዮጵያ ክፍል ነው። እንደ አብዛኛዎቹ የገጠር ህፃናት እናቴ ካስመቸችኝ አዝላ መፍጨት፣ ማረም፣ ማጨድ፣ መኮትኮት እና መጋገር ነው። በደመነብስ ቢሆን ከእናቴ ብዙ ሙያዎች ተምሬያለሁ። ታዝሎ ማልቀስ ክልክል ነው ካለቀስኩ ቅጣቱ ከባድ ነው። እንደ እንስሳት በአራት እግር መሄድ መውደቅ መጋጋጥ አይቀሬ ነው። የሚሻለው ነገር የሳቱን ጢስ እና ሙቀት መታገስ፣ የሚሻለው ነገር መቻል ነው ርሀቡንም ጭምር። ይህን ስል እናቴ አሰቃይታኛለች ለማለት ሳይሆን የአኗኗር ዘይቤው ስለነበር መገመት አያዳግተኝም ለማለት ነው። ከባለ አራት እግር ወደ ሁለት እግር ስለውጥ እረኝነት ጀመረ። በተደራቢም የእርሻ ስራን የማገዝ ሸክም በተክሻየ ተጫነ። ከ7 እስከ 17 አመቴ የሆነውን በብዛት አስታውሳለሁ አሁን ላለሁበት እና ለቀጣይም መሰረት ነው። ያም ይሁን ይህ ቀለሜ ተማሪ መሆኔ አወጣኝ እንጅ ነገሮች ከባድ ነበሩ።

አስተዳደጌ በኒለኛው ዘመኔ ተጽዕኖ እንዳደረሰብኝ ይሰማኛል። ቤተሰቦቸ አስተዳደጌን በቅራኔ የተሞላ እንዲሆን አድርገውታል። የመወያየት ዕድሉ ስላልነበረኝ እጅግ እጨነቅ ነበር። ወላጆቸ እንግዳና የጎረቤት ልጅ አክባሪ ናቸው፣ ልጅን ስለማክበር ግን ብዙ ይቀራቸዋል። (በእርግጥ አሁን አሁን አሻሽለዋል)። በእኔ እመነት ከእንግዳ ይልቅ ልጅ ክብር አለው። እነሱ ያደጉትም እኔንም ያሳደጉኝ እንግዳ ትክብሮ ልጅ ተማሮ ነው። አንድ ታሪክ አስታወስኩ ልጅ እያለሁ ምሳ የቋጠርኩበት አሮጌ የመዳበሪያ ሻንጣ ጠፋብኝ። ቤቴ ስገባ ስድብ እንደሚጠብቀኝ እርግጠኛ ነበርኩ። የተጠበቀኝ ግን ምክር አዘል ስድብ አልነበረም። አሉ የሚባሉ የእርግማን አይነቶች ናቸው። እስከ ዛሬ ድረስ ያን ወቅት ማስታወስ አልፈልግም። በወቅቱ ራሴን እስከ ማጥፋት በሚደርስ ጭንቀት ውስጥ ነበርኩ። እንደልጅነቴ አጥፍቸ ተገርፌ አውቃለሁ ግርፋቶቹን በውል አላስተውሳቸውም በሻንጣው መጥፋት የደረሰብኝን ስብራት ግን ላስታውሰው ባልፈልግም መረሳት እንደማልችል ገብቶኛል።

ወላጆቸ ልጆቻቸውን እንዴት ማሳደግ እንዳለባቸው ካላወቁ መዘዙ ከባድ ነው። ደስ የሚለው ነገር ያን ክፉ ቀን አይኔ ደም እስኪለብስ አልቅሸ አለፍኩት። የሞት ሽረት ትግሉ ተጀመረ ለራሴ ቃል ገባሁ ነፃ ለመውጣት የነበረኝ ብቸኛ አማራጭ ተግቶ መማር ነበር። (ጠፍቸም ነበር ከቤተሰብ መጥፋቱ ግን ያተረፈልኝ የጎዳና ህይወትን ነበር፣ ስላልቻልኩት በአባቴ ቤት ባርያ ብሆን ይሻለኛል ብየ ተመለስኩ)። ትኩረት ለትምህርት! ከክፍል ክፍል መዛወርና 1ኛ ደረጃ መውጣት ለኔ ትርጉም አልነበራቸውም ምኞቴ መራቅ ነበር ማለት ወደ ከተማ መኮብለል። ቀኑ ደርሰና የ5ኛ

Created in Master PDF Editor

ክፍል መሸኛየን ይዤ ወደ ከተማ፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር የእግር ጉዞ ተጀመረ። በእየ መንገዱ ውሾች ይጮሁሉ ግመሉ ግን ወደ ኋላ ይመለስ ዘንድ አልወደደም።

ከ5ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የተወሰነውን አመት አባቴ ካስተዋወቀኝ ዘመዶች ጋር ቀሪውን ደግሞ ተከራይቸ ጨረስኩት። ምሃሉ አይነገርም። ኑሮ ከባድ ቢሆንብኝም ትምህርት ወዳጅ በመሆኔ ግን ሁሉም እኮራ ነበር።

እረኝነቱም፣ አራሽነቱም በተለይ እንደ እብድ መቆጠሩ ቀርቶ ዩኒቨርስቲ ተገባ። ዝግመታዊ ለውጥ ማለት ይህ ነው። ለእኔ ዩኒቨርስቲ መጋባት መንግስተ ሰማያት የመግባት ያህል ነበር። ዩኒቨርስቲ ውስጥ ወጥ መሰራት፣ እንጀራ መጋገር፣ እንጨትና ክሰል መግዛት ወዘተረፋ የሚባሉ ነገሮች የሉም። መማር ብቻ ስራ የሆነበት አለም ማለት ዩኒቨርስቲ ነው።

ወሎየ እንዲህ ነበር። ከጥዋቱ 12:30 እነሳለሁ። 1:00 ቁርስ እባላለሁ። 1:30 መማሪያ ክፍል እገኛለሁ። 2:00 ትምህርት ይጀመራል። በትምህርት ሰዓት ያለምንም መሰልቸት በሙሉ አፅንኦት እከታተላለሁ። እጠይቃለሁ፣ እመልሳለሁ። በአንዳንዱ ክፍለ ጊዜዎች መምህሩ ከሚያወራው ጊዜ በልተናነሰ እሳተፋለሁ። አንዳንዴ ጥያቄዎቼ መምህራንን የሚያስቸገሩ ይመስለኝ ስለነበር እጨነቃለሁ። አንዴ የmaths for finance መምህራችን ከዛሬ ጀምሮ ፊት ወንበር እንዳትቀመጥ፣ ጥያቄም እንዳትጠይቅ ብሎኝ ነበር፣ ያውም ክፍል ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች እየሰሙ ጥያቄየ ጊዜ የገደለበት ይመስለኛል። ብዙዎች ክፍሉ ጭር ሲል የማይወዱ መምህራን በጣም ይወዱኝ ነበር።

5:30 ምሳ እበላለሁ፣ 6:00 ቤተ መጽሀፍት እገባለሁ፣ 8:00 ክፍል እሄዳለሁ (ካለ) 11:00 እራት እባላለሁ። 12:00 ቤተ መጽሀፍት እገባለሁ። በአማካኝ 5:00 ወደ ዶርሜ እሄደላሁ፣ 6:00 እተኛለሁ። በቀን ውስጥ አብዛኛው ጊዜየን የማስልፈው ቤተ መጽሀፍት ነበር፣ በተለይ ከቤተ መጽሀፍቱ ኮምፒውተር ክፍል። ኮምፒውተር አጠቃቀሜን ሳስታውስ ግርም ይለኛል። ቀጥታ ከፍየል ጠበቂነት ወደ ፈጣን ጎግል ተጠቃሚነት። የማልጠይቀው ጥያቄ የጥያቄ አይነት የለም።

የክፍል ጓደኞቸ ቤተ መጽሀፍት ውስጥ መምህራን የሚሰጡንት የ10 ብር ሃንዳውት (Instructor Note) የማነብ ይመስለቸዋል። እኔ ግን ውሎ አደሬ ከጎግል ጋር ነበር። ይህን ሚስጢር የኮምፒውተር ክፍል አሰነባቢ በክፊል ታውቅ ነበር። በተለይ አንዴ የትምህርት ነክ ነው የማናበው ብለት ስላላመነችኝ ሂስትሪውን ከፍታ አየችው። አብዛኞዎቹ ከሀይማኖት ጋር የተያያዘ መሆኑን አይታ አስጠነቀቀችኝ። ማሰጠንቀቂያውን ብዙም ባለከብረውም ነፃነት እንዲሰማኝ እያልኩ ከቤተ መጽሀፍት

Created in Master PDF Editor

ውጭ ባሉ ኮምፒውተር ክለሶችና እንዲሁም ከሌላኛው ኮምፓስ ቤተ መጽሀፍት ኮምፒውተር ክፍል እየተዘዋወርኩ የጥያቄየን ጥማት በጎግል እወጣ ነበር።

ጎግል እጅግ ባለሙለታየ ነው። መረጃ ለኔ ምግብ ነው። እርቦኛ ትንሽም ቢሆን ልታገስ እችላለሁ። የመረጃ እጥረት ግን ያንገበግበኛል። ዛሬ በብዙ ህይወቴ ደስተኛ ነኝ። ትልቁ ችግሬ ኢንተርኔት (Internet) ነው። ዛሬም ረሃብ አለብኝ። ፈጣን Wifi ካለበት ሆቴል ገብቼ የ20 ብር ለስላሳ ተጠቅሜ የ200 ብር ጽሁፍ አውራጃ እመስላለሁ። በስልኬ ኢንተርኔት የምጠቀም ቢሆን ኑሮ ደሞዜን ለኢትዮ-ቴሌኮም በቅድሚያ መክፈል ይኖርብኛል። ይህ ሃሳብ ፌስ ቡክና ቴሌግራም የሚጠቅሙት አይገባቸውም። መጽሀፍትና ዶክመንታሪ የሚያውርዱ ግን ይረዱታል። ፈጣን ኢንተርኔት ማለት በመንገድ ስታልፉ እንደምትመለከቱት ውደ ኬክ ማለት ነው። መጎምጀት ከተገኘም ባመት። ለኔ አንድ ሰው ጎግል ላይ ነው ማለት በአለም ውስጥ ካለው ብቸኛ ሁሉን አቀፍ የመረጃ ማዕከል ውስጥ እንዳለ ይሰማኛል። መርጃ ሃብት ብቻ ሳይሆን መሰረታዊ ፍላጎት ጨምርም ነው።

በግሌ አፓርታማ ባላቸውና ውድ መኪኖችን በሚነዱ ሰዎች አልቀናም ጎግልን እንደፈለጉ በሚጠቀሙበት ሰዎች ግን እቀናለሁ። በቅርቡ ሳይንቲስት ስቴፈን ሀውኪንግ ከአለም ጋር በ Internet connected ነኝ በማለቱ የተገጠመለትን Wifi ምን ያህል ፈጣን ይሆን ብየ አስቤ ነበር።

ከሌሎች ቦታዎች በተሻለ መጠን ዩኒቨርስቲ ውስጥ ኢንተርኔት አለ። በተለይ ተማሪ በነበርኩበት ወቀት ሰፊ ጊዜም ስለነበረኝ ጎግልን በሚገባ ተጠቅሜበታለሁ። 1ኛ አመት እያለሁ የማህበረ ቅዱሳንን እና ሌሎች የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ገጾችን አዘወትር ነበር፣ 2ኛ አመት ላይ የሌሎች ሃይማኖቶችን ገጾች መገኘት ጀመርኩ። 3ኛ አመት ስሆን አቅጣጫየን ወደ ኤቲዝም አዞርኩ። ስለነገ አላውቅም፣ ያኔም በእምነቴ እርግጠኛ ነበርኩ።

ዩኒቨርስቲ ያስለወጠኝ ነገር ዋናው እምነቴን ነው። ዩኒቨርስቲ ለእኔ ዩኒቨርስ ነው። ከልጅነት ጀምሮ ሲከተለኝ ከነበረው መጠረጠር ጋር አጋፈጠኝ። ጥያቄየ አንድ አይደለም በጣም ብዙ ነው። አንዱን ሳስታግሰው ሌላው ይከሰታል መቋቋም አቃተኝ። በአየለቱ ጥዋት እና ማታ ቤተ-ክርስቲያን እሄድ ነበር። በጣም ብዙ ፀሎት በጣም ብዙ ስለት አደርግ ነበር። ዋናው ጸሎቴ ውጤቴ እንዲሻሻል አልነበረም በዚህስ የምታማ አልነበርኩም። (በእርግጥ ስለውጤቴ መሻሻል የጸለይኩበት ጊዜም ነበር።)

ይልቅስ የፀሎቴ ትኩረት እግዚአብሔር እሱን ከመጠራጠር እንዲያድነኝ ነበር። በኋላ ጭረሽ ሙሉ በሙሉ ከማበዴ በፊት መጠራጠሬን አምኘ ተቀበልኩ። ቢሆንም ቦታ የሰጠሁት መጠራጠር ወደ ክህደት አደገ። እግዚአብሔር የለም አልኩ። በሰንበት ቀን

ከህዝብ ፊት የተሸለምኩትን ማተብ በጠስኩ:: ማምለክ፣ መፀለይ፣ መሳል፣ መመላለስ እና ማልቀስ በአንዴ አቆሙ:: ፊቴን በዋናነት ወደ ትምህርቴ እና በተጨማሪም ወደ ሳይንስ እና ፍልስፍና ጥናት አታኮርኩ:: በተለይም የኤቲሳቶችን መጣጥፎችን እና መጽሀፍትን ማንበብ ተያያዝኩት:: ክህደቴ በማይነቃነቅ መሰረት ላይ ተጣለ:: ኢ-አማኝ በሆንኩ በአመቴ የዩንቨርስቲ ሌክቸር ሁኘ ተቀጠርኩ:: ስለ እምነት፣ ፍልስፍና፣ ሳይንስ እና ፖለቲካ ያለኝን የመመራመር ፍላጎት ገድየ ወደ ስራየ እና ወደ 2ኛ ደግሪ ትምህርቴ አተኮርኩ:: 2ኛ ዲግሪው እንዳለቀ በይደር የተውኩት የምርምር ፍላጎት ሊያፈነዳኝ ተነሳ:: በስራ ደርርቦሽ ወቅትም ቢሆን ስለእምነት፣ ስለፍልስፍና እና ስለሳይንስ የማሰብ ዝንባሌየ ጨመረ::

በመሀል ፍቅር ያዘኝ እና ለራሴ ከማህበረሰቡ የወጡ ሀሳቦችን ላላነብ እና ላላስብ ቃል ገብቼ ክርስቲያን መስየ መኖር ጀመርኩ:: (ከፈላስፋው ዘርዓ ያዕቆብ የተማርኩት ይሆን?):: ቢሆንም የተጀመረው ፍቅር ሊሳካ ስላልቻለ ተመልሸ በፍልስፍና መደመም ጀመርኩ:: በምንም አይነት ቃል ኪዳን እራሴን አላሸንፍም:: በዚህ መሀል የመማርያ መጽሀፍ (Text Book) የመፃፍ ፍላጎቴ ተነሳሳ:: መጽሐፍን ለመፃፍ ያሰብኩት ሌሊት እየተነሳው ነበር:: ቢሆንም አጋዥ የምላቸውን መጽሀፍት አደራጅቼ መፃፍ ሲጀምር ከእኔ ቀደመው የሚነሱት ቂሶች አላጽፈኝ አሉ:: እኔን ሳይሆን እነሱን ማዳመጥ ተያያዝኩት:: ሂዶ ከሚሳለመው በላይ እሰማቸው ነበር:: በተለይም ስለ ኢ-ኢማኝነት ያላቸው ግንዛቤ እና ጥላቻ ሃሳቤን ቀይሬ በእምነት ላይ እንድዘምት ገፋፉኝ:: እናም ማንም ተነስቶ ነብይ ነኝ በሚልበት ሀገር ራሴን ቅዱስ ሀዋርያ አድርጌ ሾምኩ:: መልዕክቴ ከማንም ባይበልጥም ከማንም አያንስም:: መልዕክቴ ሰዋዊ ነው ሰማያዊ አይደለም ከማንም አልተላኩም ከ666ም ቢሆን::

እኔ የፍልስፍና፣ የሀይማኖት እና የሳይንስ ተማሪ ነኝ:: ሲባል እንደሰማሁት እኔም እንደማምነው እውቀት ሙሉ ሰው ያደርጋል:: ፍልስፍና ብቻ ባጣና በሀይማኖታዊ ተመስጦ እና በጥልቅ ሳይንሳዊ ምርምር የሚመለሱ ጥያቄዎች አልመልስም:: ሀይማኖትን ብቻ ባጣና አንድ በኩል ብቻ የተሣልኩ ለአማራጮች እድል የማልስጥ ደረቅ እሆናለሁ:: ሳይንስን ብቻ ባጣና በፍልስፍና እና በመንፈሳዊ ተመስጦ የሚመለሱ ሳይንሳዊ እንቆቅልሾችን መፍታት አልችልም:: ከዚህ የተነሳ ጊዜየን፣ ገንዘቤንና ጉልበቴን ለፍልስፍና፣ ለሀይማኖት እና ለሳይንስ ጥናት ልሰጥ ቆረጥኩ::

ተማሪ እንደመሆኔ ብዙ ሩጫና ፈተና ይጠብቀኛል:: ምርጫየም ሰፊ በመሆኑ ገና ጀማሪ ነኝ ልጨርስም አልችልም:: ሁሌም በእግዚብሔር ዘንድ የተከለከለችውን የእውቀት ዛፍ ፍሬ እበላለሁ:: ሁሉንም በጥርጣሬ ለመመልከት አይኔ ተገልጧል:: ያየሁትን ተፈጥሮ አጅግ ወደድኩት፣ እንጅ አልተሸማቀኩም:: ደርቻው ስለማይታወቀው ሁለንታ እና በአይን የማይታዩ ጥቃቅን ፍጥረታት ሳስብ መቼ፣

የት፣ እንዴት፣ ለምን እና ከማን የሚሉ ጥያቄዎች ወደ አጥንቴ ሰርገው ይገባሉ፡፡ ሰውነቴ ይርዳል፣ የደም ዝውውሬ ይፈጥናል፣ ልቤ በፍጥነት ይመታል፣ የደም ስሮቼ ይረገበገባሉ፡፡ በዚህ ሁከት መሀል አእምሮየ ትዕዛዝ ያስተላልፋል፡፡ በየአላችሁበት እርጉ በቅርብ ለሁሉም ጥያቄ መልስ አመጣለሁ ብሎ ያዛል፡፡ በቅፅበት ሁሉም ወደ ስራው ይመለሳል፡፡ እስከ አሁን የማረጋጊያ መልስ ከመጽሀፍት እና ከምርምሬ አገኘሁት ያለውን መልስ ሰጥቷል፡፡ ገናም ብዙ ማንበብ ብዙ መመራመር ይፈልጋል ግዴታው ነው፡፡

ማወቅ የምፈልገው የግልና የቡድን አስተሳሰቦች የሚፈልቁበትን ምንጭ ነው፡፡ እስከ አሁን ያወኳቸው ምንጮች በከፊል አድፈዋል፡፡ ከእነዚሁ ምንጮች ውሃ የሚጠጣ በአብዛኛው በውሃ ወለድ በሽታ ተይዟል፡፡ አንዳንዱን ደግሞ ከጊዜ በኋላ ያመዋል፡፡ ከነዚህ ምንጮች መጠጣትን እደግፋለሁ፡፡ ቢሆንም ከመጠጣታችን በፊት ውሀው በማሽን እንዲወጣና ማጣሪያ ቢደረግበት ካልሆነም ውሃ አጋርን እንጠቀም ስል እመክራለሁ፡፡ ቢያንስ እንኳ አፍልተን አጥርተን እንጠጣ፡፡ ካልሆነ ግን ታመን ሌሎችንም በሽታችንን አስተላልፈን እንኖራለን፡፡ የውሃ ወለድ በሽታዎች ደግሞ በቀላሉ ከሰው ወደ ሰው የመተላለፍ እድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ጽንፍ ወለድ አስተሳሰቦችም ከወሃ ወለድ ይከፋሉ፡፡ አኗኗራችንን እንዳስተዋልኩት ብዙ ሰዎች በዚህ የሞራል ዝቅጠት በሽታ ታመዋል፡፡ የሚገርመው መታመማቸውን እንደ ጤንነት ስለሚቆጥሩት ቢነገሩ አይሰሙም፡፡ የኔ ሃይማኖት፣ ብሔርና ዘር የተለየ ብቸኛ እውነት ነው የሚሉ ሰዎችን ማግኘት ብርቅ አይደለም፡፡ <እሱ ይሁነን> እንጅ እየኖርን ያለነው ከትናንሽ ሂትለሮች ጋር ነው፡፡ ሰው ሃይማኖቱን፣ ብሔሩን እና ዘሩን ቢወድ የተመሰገነ ነው፣ ችግሩ <እናንተ አታስፈልጉም> ያለ ጊዜ ነው፡፡ በፍጹምነት የሚያምን እራሱን ለመፈተሽና የኋላ ታሪኩን በጥንቃቄ ለማጥናት አይፈልግም፡፡ ይህ በፍጹምነት የማመን አባዜ ደግሞ ለመቻቻል እንቅፋት ነው፡፡ ስንት ምርጥ ዘር አለ? ስንት ምርጥ ሀይማኖት አለ? ስንት ምርጥ ሀገር አለ? ስንት ምርጥ አህጉር አለ? ስንት ምርጥ አባቶችና እናቶች አሉ? እንደመላሹ የአዕምሮ እድገት ሁኔታ መልሱ ሁሉም ወይም የእኔው መንገድ ነው፡፡

እርግጥ ነው አባቴ ከእኔ በእድሜ ይበልጣል፡፡ ደግሞም እወደዋለሁ ፍጹም እውነት የሚገኘው ከእኔ አባት ብቻ ነው ግን አልልም፡፡ የጥበብ መጀመሪያ ከእኔ ያለው ከሁሉም ይበልጣል የሚለውን አስተሳሰብ መተው ነው፡፡ በእያንዳንዳችን ህይወት ውስጥ ያለው ጥበብ ካማንም አያንስም፣ ከማንም አይበልጥም፡፡ ለእኔ ሰው ሁሉ ሳይንቲስት፣ ፈላስፋ እና ተመራማሪ ነው፡፡ ቢሆንም ማንም ቢሆን የምርጥ ዘር አስተሰሰብን እስካራምደ ድረስ መሃየም ነው፡፡ ምርጥ ዘር የሂትለረዝም አስተሳሰብ ነው፡፡ ሂትለርን እያወገዙ የሂትለርን አስተሳሰብ ማራመድ መሀይምነት ካልተባለ ምን ይባል ይሆን? በ21ኛው ክ/ዘመን አንዱ የልቡን እየተናገረ አንዱ አፉን መታሰሩ ምን

Created in Master PDF Editor

ሊባል ይችላል? እነሱ ይናገሩ እናንተ ዝም በሉ ማለትስ ምን አይነት ዲሞክራሲ ነው? ሰው ከተፈጥሮ ባገኘው ማንነቱ ምክንያት ለምን ተሸማቆ ይኖራል? የዜጎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩት በቡድን እስከተደራጁ ብቻ የሚሆነውስ እስከመቼ ነው?

በእኔ እምነት መብት ከገብረ ኪዳን ቀምተው ለባልቻ የሚሰጡት አይደለም፡፡ ቄስ አያሌውን ነጥቀው ለሸህ አብዱሂ የሚሰጡት አይደለም፡፡ አርዮስን ነፍገው ለፀረ-አርዮሳዊያን የሚያድሉትም አይደለም፡፡ መብት ለገብረ ኪዳንም፣ ለባልቻም፣ ለሸህ አብዱላሂም፣ ለአርዮስም፣ ለዶ/ር አስጨናቂም፣ ለጋዜጠኛ ምናላቸውም ለሁሉም እኩል የሚሰጥ ነው፡፡ መብት ልጅና እንጀራ ልጅ የሚባል የለውም፡፡ መብትን ከፍሎ ወይም አዳልቶ ከመስጠት አለመስጠት እጅግ ይሻላል፡፡

ከሁሉ የከፋው ደግሞ የአንዱ መብት ለሌላው ወንጀል በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡ <ሌባ ብሎ የሚሳደብ> ሌባ ብለው የሚናገሩ ወንጀለኞች ናቸው አለ ማለት ምን ማለት ነው? ሰዎች እንዳንናገር ከተፈለገ ምላሳችንን መቆረጥ ነበረበትን? እንዳንጽፍስ እጃችን መቆረጥ ነበረበት ወይ? ሁሌስ የወቅቱ መንግስታትን እና ጊዜ የሰጣቸው ባለጊዜዎችን ፈርተን እነሱን መስለን መኖር አለብን? አንዳንዴ መራራ እውነቶችን በትዕግስት ብንሰማቸውና ብናነባቸው የሚቀርብን ምንድን ነው? እኛ እንደተናገርን እና እንደጻፍን ሁሉ ሌሎች እንዲናገሩና እንዲጽፉ ብምፈቅድስ?

የእኔ ሀሳብ መንግስት የንግግር እና የጹሁፍ ነጻነትን በመስጠት ዜጎች ለ5 አመት የሚመራቸውን የፖለቲካ ሲስተም ብቻ ሳይሆን ለረጅም ጊዜ የሚምሩበትን መንፍሳዊ ህይወት የመምረጥ መብት ሊታድላቸው ይገባል ነው፡፡ የተረጋጋ ማህበረሰብ የሚፈጠረው ሰላማዊ ድርድሮች እና ክርክሮች በማድረገ እንጅ አንዱ ስለሌላኛው እንዳያወራ በመከልከል አይደለም፡፡ የውይይት ምህዳሩ ሰፊ እና ሁሉን አቅፍ መሆን አለበት፡፡ ዜጎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እኩል መታየት አለባቸው፡፡ ቢያንስ ከርቀት በሚሰማ ማይክራፎን አርዮስን የሚያውግዝ ሰባኪ እና ለፈለጉት ብቻ የሚጽፍ አርዮስ እኩል መታይት አለባቸው፡፡ ለሰባኪው የሀይማኖት አባት በሚል ስም የውሎ አበል እየከፈለ አርዮሳውያንን የሚያሳድድ መንግስት ሳይሆን የአሸቃባጮች ስብስብ ነው፡፡ ይህን ያልኩት መንግስታቶቻችን ሀይማኖቶችን እንጅ ዜጎችን ጠባቂ ስላልነበሩ ነው፡፡ መንግስታዊ ሀይማኖት እና ሀይማኖታዊ መንግስት ባሉበት የዜጎች ነጻነት ይጠበቃል ማለት ዘበት ነው፡፡ ምስክር አያስፈልግም ታሪክን ማስታወስ በቂ ነው፡፡

አንዳንዶች የፖለቲካ ወይም የዘር ወይም የሐይማኖትን ጥግ ይዘው የፈለጉትን በማን አለብኝነት ይደሰኩራሉ፡፡ የሚያሳዝነው መደስኮራቸው አይደለም ሰው ሃሳቡን የመግለፅ መብት አለው ይባላልና ችግሩ ሌላ ዲስኩር የሚደስኩሩ በምድር ገጽ እንዲኖር አይፈልጉም፡፡ የአለም ብቸኛው መንገድ የባለጊዜዎች ዲስኩር መሆኑ

Created in Master PDF Editor

ያሳዝናል። ይህ ሁሌም የሚከነክነኝ ጉዳይ ነው። <I Have a Dream> ከማለት በተጨማሪ የራሴን ሰላማዊ ትግል ማድረግ እንዳለብኝ ግን ይሰማኛል። ለዚህም እስከለተ ሞቴ ደረስ ዝግጁ ነኝ።

ራሴን እንድገልጥ መጽሀፍትን እንድጽፍ የገፋፋኝ የሰውን ሀሳብ ለመዝለፍ ሳይሆን ከትልቁ መጽሀፍ ቅዱስ ጀምሮ እስከ ጠጅ ቤት ሠባኪዎች ስለ ኢ-አማኝነት ያለቸውን ፍፁም የተሳሳተ አስተምህሮ መልስ ለመስጠት ነው። ኢ-አማኝነት አማኞች ከሚደነቁባቸው ሚስጢራተ ቤተክርስቲያን እኩል ድንቅ ነው። ስለዚህ አባቶቻችን እና እናቶቻችን መሰረት ያስቀመጡልን፣ እኛም ሁሌም ለእውነት፣ ለፍትህ እና ለፍቅር ልዕልና የምንተጋ እንዲሁም ራሱን መመርመሮ ለማወቅ የተሻለ አማራጭ አስተሳሰብ ያለን መሆኑን ላረጋግጥላቸው ስለምወድ ነው።

ሁሉም ሰው ሲወለድ ኢ-አማኝ ነው። ሀይማኖት ከአሳዳጊዎቻችን የተማርነው ነው። ሃይማኖት ሰው ስራሽ ነው። ሀይማኖት በሰማያዊ ሀይል የተመሰረተ ሳይሆን የሰዎችን መሰባሰብ ተክትሎ የተመሰረተ ማህበራዊ ቡድን ነው። አለም አቀፋዊ የሆነ አንድም ሀይማኖታዊ እውነት የለም። ምን አልበት ሀይማኖቶችን አንድ የሚያደርጋቸው በአምላክ መኖር ማመናቸው ቢሆን በስሙ፣ በተግባሩ እና በብዛቱ እና በሌሎች ምክትያቶች አንድ አቋም የላቸው። ሃይማኖቶች እንደ ማንኛው ማህበራዊ ቡድኖች በጊዜ፣ በቦታና በሁኔታ የተገደቡ ናቸው።

አለማመን ግን ከዚህ ወጣ ይላል። ማንም ሰው ደርሶ ሀሰት ሊያደርገው አይችልም። ለምን ቢባል የተመሰረተው በማመን ሳይሆን በመጠራጠር ነው። ማመንን በመረጃ አስደግፈን ውድቅ ማድረግ ይቻላል። አለማመን ግን አይቻልም።

የማያምን ሰው መሰረቱ ጥርጥር ነው። አብን ይጠራጠራል፣ ወልድን ይጠራጠራል፣ መንፈስ ቅዱስን ይጠራጠራል፣ በድንግልና መወለድን፣ ቅዱሳን ይጠራጠራል፣ በባህር ላይ መራመድን ይጠራጠራል፣ በአየር ላይ መንሳፈፍን ይጠራጠራል፣ ከሞት መነሳትን ይጠራጠራል። የጳጳሳትን ፈጣሪ ወኪልነት ይጠራጠራል፣ ፈላስፎችን ይጠራጠራል፣ ሳይንስን ይጠራጠራል፣ እራሱን ይጠራጠራል። ታዲያ እንዲህ ብሎ የሚያስብን ሰው ሃሳብህ ትክክል አይደለም ልንለው እንችላለን? ምን አልባት እንችላለን። መንፈስን ከተሰወረበት ገልጦ በማሳየት በባህር እየተራመዱ በአየር እየተንሳፈፈ በማሳየት፣ ሙታንን አስነስቶ በማሳየት፣ ቡድሀን፣ ኢየሱስን እና ሙሀመድን ከስማያት ጠርቶ አቤት በማስባል፣ ወደ ግዙፍ የምርምር ተቋም ወስዶ ግዝፍን በቴሌስኮፕ ደቃቁን በማይክሮስኮፕ በማሳየት ማሳመን ይቻላል። አምልዕኮን ግን ችግሩ በቴሌስኮፕና በማይክሮስኮፕ አንመረምረውም ወይም በጹሁፍ እንጅ በተግባር መሳየት አንችልም። ማመንን ፉርሽ ለማድረግ ግን አንድ ጥቅስ በቂ ነው።

Created in Master PDF Editor

አለማመን ማለት ግን ሁሉን መካድ ማለት አይደለም። ማመን ያለብንን ለማመን ዝግጁ ነው። ዋናው መረጃና ማስረጃ ማቅረቡ ነው። አማኞች ኢ-አማኞችን ለማሳመን የሚያቀርቡት መረጃ በቅብብሎሽ የወጣውን ትውፊታዊ አስተሳሰብ ነው። ፈጣሪ ለሙሴና ለሐዋርያት ተገለጠ ማለት በቂ ነው ማለት አይቻልም። የተመረጠ፣ ለተመረጡ ብቻ የሚባል መገለጥ የለም። መገለጥ መገለጥ ነው። ምንም ዙሪያ ጥምጥም አያስፈልገውም። አማኞች ኢ-አማኝነትን ትክክል እንዳልሆነ ማስረዳት የማይችሉ ከሆነና ይልቅም ራሳቸውን መከላከል የማይችሉ ከሆነ እኛ ኢ-አማኞች ራሳችንን "The Brights, Freethinkers, Godless, Nonbelivers, Materialists, naturalists, Rationalists, Skeptics, Secularists, Humanists and Atheists" ብለን በኩራት እንዲሁም አማኞች ባወጡልን "Heathens, Heretics, Infidels and Pagans" ተብለን ብንጠራ ክብር ይሰማናል። እነዚህ ስያሜዎች "7th day Adventist, The only Jusus, mormon, ….. etc" እንደማለት አይደለም። የአንድ ሰው የተለያዩ ስሞች ናቸው። ኢ-አማኞች የወረደ ወይም የተፃፈ ቅዱስ መፅሀፍ የለንም። የትም ይፃፍ ትክክል ከሆነ እንቀበላለን። ክርስቲያኖች፣ ሙስሊሞች፣ አይሁዶች፣ ቡዲስቶች ወ.ዘ.ተ በጻፏቸው መፅሀፍት ውስጥ እውነት ካገኘን እንቀበላለን። ኢ-አማኞችን ነፃ ህዝብ የሚያስብላቸው ሰብአዊነታቸው የሚገዛቸው ስለሆነ እና ከወዮላችሁ ነፃ ስለሆኑ ጭምር ነው። የመጠየቅ፣ የመመለስ እና ጥልቁን የመመርመር ነጻነት ያለው ከማያምኑት ዘንድ እንደሆነ አስባለሁ።

እስኪ ልጠይቃችሁ እውነትን ትፈልጉታላችሁ ብታገኟት እና ከእናንተ እምነት ውጭ ብትሆንስ ልትቀበሏት ዝግጁ ናችሁን? ብዙ ሰዎች እውነትን መስማት አይፈልጉም ውሸታቸውን ለመተደግ ሲሉ። እርግጥ ነው ከዋከብትን እንደሾላ ፍሬ ለሚያስብ ሰው ስለ ከዋከብት ግዙፍነት እንዲነገረው አይፈልግም።

ካልሆነማ በታላቁ ፋላሲ ውስጥ ይወድቃል። ከመሬት ብዙ እጥፍ የሚገዝፉ ከዋከብት ኢያሳያስ፣ ማቴዎስ እና ባለራዕዩ ዮሐንስ እንዳሉት ወደ መሬት ረገፉ ማለት ዝሆኖች በአንዴት ዝንብ ላይ ረገፉባት እንደማለት ነው። ይህን ፋላሲ (Fallacy) መሸከምም መቀበልም የማይፈልግ አዕምሮ ከእውነት መሻሹ አይደንቅም።

ይልቁንም ከዋከብትን እንደ ጠጠር ወይም እንደሾላፍሬ የሚቆጥሩት መጽሀፍት ምን ያህል ስህተት እንደሰሩ ማወቅ ባንፈልግም አንድ የኮከብ ስባሪ መሬት ላይ ቢወድቅ የመሬት ቅርጽ ፍጹም ይቀየራል። ይህ ክፉ ኮከብ መሬት ላይ የወደቀ ቀን ማንም መቋቋም አይችልም ዳይኖሰርም ቢሆን። የአለም ፍፃሜ መድረሱን ለማወቅ የኮዋከብት ሰብርባሪዎች መሬት ላይ የሚደርሱበትን ማሰብ ነው። መጽሀፍቱ ከዋከብት የሚሏቸው የዛሬ 2000 ዓመት ረገፈው ከሆነ ቅሬታቸውን ማግኘት ያቻልይሆን ለምነው? ተመልሰው አረጉ አንበል። ከረገፉት ከዋከብት ደግሞ ግርም የሚያደርገው

ሰባ ሰገልን የመራቸው ኮከብ ነው። ግዝፍቱ ባይጠቅስም የአነስተኛ አውሮፕላን ግዙፍነት ያለው ይመስለኛል። ሰዎቹ በምድር እየሄዱ ኮከቡ በሰመይ እየመራቸው በሰዎቹ ፍጥነት እየተራመደ ጌታ በተወለደበት ስፍራ የሚቆም አይነት ምስል ተስሏል።

ስለከዋከብት ግዝፉነት ጋሊዮን እና የዘመኑን ጠበብቶች መጠይቅ አይከፋም። ኢትዮጵዊው ፈላስፋ ዘርዓያዕቆብ እንኳ በመራቃቸው ምክንያት ትንሽ የሚመስሉትን ከዋከብት ግዙፍነታቸውን የሚያውቅ አለን ሲል እራሱን ጠይቆ ነበር።

እንደታዘዝኩት በፈለሰፋው ጥያቄ ላይ ሌላ ጥያቄዎች ልጨምር ለመሆኑ ፀሀይ ደም መሰለች፣ ፀሀይ ቆመች፣ ጨረቃ ብርሀኗን ከለከለች ማለት ምን ማለት ነው??? በመፅሀፍት እባብ፣ አህያ እና ሌሎች እንስሳት እንደሚነጋገሩ ተደርጎ መሰሉ ብዙ አይደንቅም ሀሰት መሆኑን ማሳመን አልችልም። ሊያሳምነኝ የሚችል አንድም ሰው አለብየ አላምንም። ካለ እባብ ሲናገር፣ ድንጋዮች ሰዘምሩ፣ እንጀራ ከሰማይ ሲወርድ፣ ከዋከብት ሲረግፉ (አንድም ቢሆን)፣ ፀሀይ ስትቆም ሰዎች በክንፋቸው ሲበሩ፣ የተራብ እንበሳ የሰውን ስጋ አልበላም ሲል፣ ሰዎች በእሳት እና በብሃር ሲመላለሱ ማየት እፈልጋለሁ። ይህን መጠየቅ ምንም ሀጢአት አይደለም። እውነትን መሻት እንጅ። ማንም አጥማቂ ነኝ፣ ነብያ ነኝ ወ.ዘ.ተ የሚል የእኔን እንቆቅልሽ ሊፈታ አይችልም። ማስመሰል እና ትናንሽ ቅዥቶችን ማንም ሊያደርጋቸው ይችላል። ይህም እንደታምር ሳይሆን እንደ ድንቃድንቅ ዜና ቢወስድ መልካም ነው።

በዚህ አለም የምንኖረው ለጥቂት አስርት አመታት ብቻ ነው። ብዙዎች እንደተወለዱ ለአቅመ መጠይቅ ሳይደርሱ አልፈዋል። ከዚህ የሚለቁት ሳይወለዱ ሙተዋል። በጣም ከዚህ የሚበዙት ደግሞ ጭራሽ አልተፀነሱም። ለአቅመ መጠይቅ መድረስ መባረክ ነው። መጠየቅ ማንን ይጎዳል። መጠይቅ የማንን መብት ይገፋል። በዚህች አጭር እና ውስብስብ ህይወት ራሱን የማይጠይቅ እና ምክንያታዊነትን እንደ መከራከሪያ የማይጠይቅም ሰው ለእርድ እደሚደልብ በሬ ቢቆጠር ይበዛበታል እንጅ አያንስበትም።

እንደበሬ በደንደሱ እና በቀንዱ የሚመካ ሰው ከብት ካልተባለ ምን ሊባል ይችላል? እንስሳ እንደመሆናችን ከከብቶች የተጋባብን ግን ልንተወው የሚገባን ባህሪ በደንደሳችን እና በቀንዳችን ማሰባችንን ነው። በሀይሌ ካላሸነፍኩ ገድየ ወይም ሙቸ እገኛለሁ ማለት የደመ ነብሱ እንጅ የመንፈስ ሀሳብ አይደለም። ከብቶች ደም ሲሸታቸው እርስ በራሳቸው እየጮሁ ይጋጠማሉ፣ በአንድ መንጋ ውስጥ ያሉ ሳይቀሩ ያለ አቅማቸው ተራራን ይገፋሉ፣ ያቅራራሉ፣ ይፎክራሉ። ቋንቋቸው ባይገባኝም ከደመነብስነት ውጭ ግን አይመስለኝም።

Created in Master PDF Editor

እኛ ሰዎች ግን መሻል ነበረብን ግን ከብትነታችን ሰብአዊነታችን ተጭኖታል፡፡ ከቀበሌ ገበሬ ማህበር እስከ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ድረስ የሚመሩን የደለቡ በሬዎች ናቸው፡፡ የበሬ ስራ መንጋውን ለመጠበቅ ቀንዱን ያሾላል፡፡ መንገስታቶቻችንም እንደዚያው ኒውክለር ይሰራሉ፡፡ ያለ የሌላ ሀብታቸውን አባክነው ደንደሳቸውን ያወፍራሉ፡፡ ደንደሳቸው መወፈሩን ሲያረጋግጡ ይጮሀሉ ተጋጣሚ ፈለጋ፡፡ መጀመሪያ ባለ ትናንንሽ ደንደሶችን ይገፌትራሉ ከዚም ከሚመጥናቸው ጋር ይፋለማሉ፡፡ ፍልሚያው ያለቅጥ በመጮህ ሲሆን ይችላል፡፡ አንዳንዶቹ በሬዎች እረኞቻቸውን ሲገለግሏቸው ይብስባቸዋል፡፡

ተዳፍረው ቢገጥሙ እንኳ ማምለጫቸውን እያሰቡ ነው፡፡ ከነዚህ በሬዎች ግጥሚያ ይልቅ ለግጥሚያው በሚደርጉት ዝግጅት ብዙ አፈር ይበተናል፡፡ ብዙ እጭድ ይረገጣል፡፡ መንጋቸውን ይረብሻሉ፡፡ ሀያልን መንግስታትም ከነዚህ የበሬዎቹ ሀሳብ የተለየ ሃሳብ የላቸውም፡፡ በአለም ታሪክ ዋነኛው የመንግስት ተልኮ እንደበሬ መዋጋት መሆኑ እጅግ የሚያስቀይም ሲሆን እንዲያው መንግስት የሚባል ነገር ባይሆኖር የሚያስብል ሁኔታ ነው፡፡

ወገኖች የሰው ሞቱ እስትፋሱ ሲያቆም አይደለም፡፡ እንደ እንስሳ እያሰቡ መኖር ሲጀምር ነው፡፡ እንደበሬ ተጠምዶ መታረስ፣ እንደ አህያ ተጭኖ መነዳት፣ እንደ በግ ተነድቶ መሸጥ፣ እንድ ደሮ በጥሬ ተታሎ መታገድ፣ እንደ ላም እየታከኩ መታለቡ፣ እንደፋየል <እረ ነይ> ሲሉት ግር ብሎ መምጣት፣ እንደ ድመት ሚው ሲሉት ሚው ማለት፣ እንደ ውሻ ፀጉር ለውጥ እንግዳ ሲያዩ መጮህ፣ እንደ ፈረስ ሁሌ ጋሪ መጉተት ሞት አይደለም ትላላችሁ፡፡ ለኔስ ሞት ብቻ አይደለም የሞት ሞት ነው እንጅ፡፡ የእኔ መልዕክትም ይሄ ነው ሰው ነጻ መውጣት አለበት፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ተተኪው ትውልድ የእራሱን እድል በእራሱ የሚወስን መሆን አለበት፡፡

ምን አገባህ ብትሉኝም ባትሉኝም የተተኪው ትውልድ የአስተዳደግ ሁኔታ ይመለከተኛል፡፡ ህፃናት በግድ ወላጆቻቸውን መስለው እንዲያደጉ የሚደርግበት ሁኔታ ያበሳጫል፡፡ ማንም ሰው ወደ አለም ሲመጣ ንፁህ እና ነፃ ነው፡፡ ዜግነት፣ ሀይማኖት፣ ጎሳ፣ ብሔር እና ሌሎች ቅራቅንቦዎች የሉትም፡፡ ህፃናት ራሳቸውን ፈልገው ከማግኘታቸው በፊት በግድ እነዚህንዶግማዎች እንደ ክትባት ይሰጣቸዋል፡፡ በግድ ይወጡታል፡፡ ብዙ ወላጆች የማፈልጉት ልጆቻቸው የራሳቸውን ዕድል ራሳቸው እንዲወሰኑ ሳይሆን እነሱ የሄዱበትን መንገድ ብቻ እንደሄዱበት ነው፡፡ ለዚህም አሳሪ ወላጆች በልጆቻቸው የደም ዝውውር ውስጥ ሀሳባቸውን ይዘሩታል፡፡

ህፃናቱም ካቶሊክ ህፃን፣ ኦርቶዶክስ ህጻን፣ ኤቲስት ህፃን፣ ዲሞክራት ህፃን፣ ሊበራል ህፃን፣ ግንቦት 7 ህፃን፣ ወያኔ ህፃን፣ ተብለው ያድጋሉ፡፡ በእውነት የካቶሊክ ወላጆች ህፃን እንጅ ካቶሊክ ህፃን የለም፡፡ የሙስሊም ወላጆች ህፃን እንጅ ሙስሊም ህፃን

Created in Master PDF Editor

የለም፡፡ የኤቲስት ወላጆች ህፃን እንጅ ኤቲስት ህፃን የለም፡፡ የግንቦት 7 ደጋፊ ወላጆች ልጅ እንጅ ግንቦት 7 ህፃን የለም፡፡ ለኦነግም እንዲሁ፡፡

አንደኔ አስተሳሰብ ህፃናት ሁለንተናዊ ሁነው የማደግ መብት አላቸው፡፡ ወላጆች እንዲያስቡ የመምራት እንጅ የመገደብ ስልጣን የላቸውም፡፡ ቢችሉስ ወላጆች ለልጆቻቸው ተቃርኖወችን ማስተማር አለባቸው፡፡ ካቶሊኮች እንደዚህ ይላሉ፤ ፕሮቴስታቶች እንደዚህ ይላሉ፤ ኦርቶዶክሶች እንዲህ እንላለን፤ ሙስሊሞች እንደዚህ ይላሉ፤ ህንዲዝሞች፣ ቡድሂስቶች፣ ታኦስቶች እንደዚህ ያምናሉ ብንላቸው ተገቢ ነው፡፡ ደሞክራቶች፣ ፌደራሊስቶች፣ ኮንሰርቫቲስቶች፣ አብዮታዊ እና ወታደራዊ መንግስታት መግለጫቸው እነዚህ ባህሪያት ናቸው ብንላቸው ክፋት የለውም፡፡

በተፈጥሮ እና በህይወት ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ተቃርኖዎችን እያስተማርናቸው ቢያድጉ ታላቅ የፈጠራ ሰዎች መሆናቸው አያጠራጥርም፡፡ ብዙዎች ወላጆች እንኳን ለልጆቻቸው ጥያቄ እና መልስ ሊፈጥሩ ቀርቶ ህፃናቱ በራሳቸው ተነሳሽነት ለሚጠይቁት እንኳ መልሳቸው <<እንደሱ አይባልም>> ነው፡፡ ታላቁ እስራት ይህ ነው እንደሱ ማሰብ እና መጠየቅ አይችልም፡፡ ይህ የአይችልም ጠባሳ መቸም ነፃ አይወጡበትም መልሱን እንኳ ባናውቀው ወይም ለአእምሮአቸው የማይመጥን ትንታኔ የሚያስፈልገው ጥያቄ ከሆነ በይደር ስታድጉ ታውቁታላችሁ ብሎ ማጓጓቱ የተሻለ ይመስለኛል፡፡

የአናኗራችን ሚዛን መስተካከል አለበት፣ ያም ጊዜው አሁን ነው፡፡ ሽክማችንን የምናቀልበት ጊዜው አሁን ነው፡፡ ከእስራታችን የምንፈታበት ጊዜው አሁን ነው፡፡ ከባርንት ነፃ የምንወጣበት ጊዜው አሁን ነው፡፡ ከህዝብነት እና ከአህዝብነት ክፍፍል የምንወጣበት ጊዜው አሁን ነው፡፡ ካለፉት ስህተቶቻችን የምንማርበት ጊዜው አሁን ነው፡፡ የምንዋደድበት እና የምንዋሀድበት ጊዜው አሁን ነው፡፡ ኑ እንዋቀስ ወደ ጥልቁ የምንሰርግበት ወደ ምጥቁ የምንከንፍበት ጊዜው አሁን ነው፡፡ ወደ ኋላ ታሪክን የምናስታውስበት ዛሬን የምንኖርበት እና ነገን የምንተነብይበት ጊዜው አሁን ነው፡፡ ስለጥንቱ ተነግሮናል እንጅ አላየነም ስለነገ የምናውቀው አንዳች ነገር የለም ብዙ ያልተጠበቁ ክስተቶች አሉና፡፡ ትላንት ሁኑ ስለተባሉና ነገሮች መጠራጠር መብታችን ነው፡፡ ልክ እንደ ሀዋርያው ቶማስ ካለየን አናምን ማለት እንችላለን፡፡ ቶማስ እንደሞተ ያወቀውን ክርስቶስን ሲነሳ ከተጠራጠረ እኛስ ክርስቶስ ሞቶ ከተነሳ 2000 አመት በኋላ ብንጠራጠር ጥፋቱ ምንድን ነው?

ኢየሱስ አላረገም ይሆናል፡፡ አልተነሳም ይሆናል፡፡ አልተሰቀለም ይሆናል፡፡ በድንግል ማህፀን አልተወለደም ይሆናል፡፡ በቅዱሳን መፅሀፍት የተፃፉት ሁሉ እውነት ላይሆኑ ይችላሉ ማለቱ ደግ ምንፍቅና ነው፡፡ ዛሬ የምናየው እባብ ሲነደፍ እንጅ በሰው ቋንቋ ሲያወራ አይደለም፡፡ አህያ በሰው ቋንቋ ስታወራ አልሰማነም፡፡ ወንዝ ሲገደብ እንጅ

Created in Master PDF Editor

በታምር ሲቆም አላየነም። እመጣለሁ አለን እንጅ አልመጣም፣ ከየትስ ወደ ሄት ይመጣል። ሰላሜን እሰጣለሁ አለን እንጅ ሰላምን አላከም። ለምኑ ይሰጠችኋል አለን እንጅ አልሰጠንም። ጠይቁ ይመለስላችኋል አለን እንጅ አልመሰለንም። እንኳኩ ይከፈትላችኋል አለን እንጅ አልተከፈተልንም። ወደ ፈተና አታግባን በሉኝ ቢለንም ወደ ፈተና እኛም እንገባለን እሱም ተው አይለንም። ፈልጎን እንደመጣ ቢነገረንም ስንፈልገው ግንጠፈ። ከ7ሽህ አመት አመት በፊት ፈጠርኳችሁ ቢለንም አፅማአችን ግን የ7 ሚሊዮን ሆኖ ተገኘ። ከሰው ቁጥር እጅግ የሚልቁ መናፍስት አሉኝ ቢለንም አንዱንም አላየነም። እኔ የአለም ብርሀን ነኝ ቢለንም በጨለማ ውስጥ ትቶናል። እኔ የእውነት መንገድ ነኝ ቢለንም ከብዙ የእውነት መንገድ ተብየዋ የሚለየውን መግለጫ አላሳየንም። በእኔ ያመነ አይራብም ቢለንም ከጠኔ የራቀ ታሪክ ግን የለንም።

በሀዘናችሁ ጊዜ ጥሩኝ ቢለንም ስንጠራው አልመጣም። እንባችንን በማህረባችን ጠረግነው እንጅ የሞተው ወንድማችን አልአዛር ከመቃብር አልተነሳም። ብዙ ታሪክ፣ ብዙ ምሳሌ እና ብዙ ተስፋ ሰጠን አንዱም በግልፅ ሲተገበር አይታይም። ግን ለምን ጌታ ይዋሽናል? ለምንስ ንጉሰዊ ዘፈኑን እጅግ አራቀው።

አኛንስ ለምን በማወቅ እና ባለማወቅ ማዕከል አድርጎ ፈጣሪን? ለምንስ በእሱ ስራ ይበሳጫል? ለምን አንድንሰገደለት እና አንድናሽረግድለት ይጠይቀናል? ከእኛ ምን ይጨምርለታል? ለሰዎች ለምን መልዕክት ይልካል? መልዕክተኛስ ለምን አስፈለገ? ፈጣሪ ከሰው ልጅ የሚፈልገው ምንድን ነው? የሰውን ልጅ ከመፍጠሩ በፊት ለአንፍኒቲ ጊዜ ምን ሲሰራ ኖረ? ብዙ ጥያቄ ነበረኝ ስለማይመለስ ተውኩት እንጅ።

እኔ አርዮስ ብሔሬ ሰው መሆን ነው፣ ሀይማኖቴ መታደስ፣ ሀገሬ መሬት ናት፣ ዜግነቴ መሬታዊ ነው፣ ወንጌሌ ውይይት ነው፣ ማንነቴ ሁለንተናዊ ነው። ይህን ይፋ ባደርግ በተለወለድኩበት ቀየ፣ በአደኩበት ሰፈር፣ በኖርኩበት ከተማ እንደግዞተኛ እቆጠራለሁ ብየ ስለምሰጋ በስልታዊ የማፈግፈግ ትግል እንድኖር ተገድጃለሁ። ሰው እንደገደለ፣ ሙስና እንደሰራ፣ ቃሉን እንዳጠፈ በማንነቴ ተሸማቅቄ መጠቋቆሚያ ከምሆን ነገሮች እስኪስተካከሉ ድረስ ፈላስፋው ዘርዓ ያዕቆብ እንዳስተማረኝ መስየ እኖራለሁ። እውነቱን ብናገር ከማ ጋር እኖራለሁ። የትስ እሰራለሁ። ማንስ ያቀረበኛል ጥቂቶች ካልሆኑ ብዙ ይጠለኛል። ይህን ሀቅ አውቃለሁ። ስለዚህ አሣ እንዳልሆንኩ እያመኩ ኩሬ ውስጥ እኖራለሁ። የሚመጣውን ሁሉ ፊት ለፊት የሚጋፈጥ ደፋር ልቦና የለኝም። (ግን እኮ ምንም ላይፈጠር ይችላል)። ያም ይህመጽሃፉ በፍርሀት ከተከበበች ድፍረት አፈትልኮየወጣ ነው። የውይይት ባህላችን እየዳበረ ሲሄድ ደግሞ በግልጽ ነጻ አስተሳሰቦችን በነጻነት ብዕር እጽፋለሁ።

ፕሮፌሽናል ጋዜጠኛ አይደለሁም፣ ራሴን የስነ ፅሁፍ ባለሙያም አደርጌም አላስብም። በፍልስፍና፣ በስነ መለኮትና በሳይንስ ፕሮፌሰር አይደለሁም ይልቅስ ተማሪ ነኝ።

Created in Master PDF Editor

የምፅፈው ለእንጀራ አይደለም የምርምር ማዕከል የለኝም፣ የቀጠርኳቸው ኢዲተሮች እና ገምጋሚዎችም የሉኝም፣ ይህን መጽሃፍ ለማሳተም እንኳ 3 አመት <ጥሬ ቆርጥሜ> ነው፡፡ ኑሮየን በዩኒቨርስቲ መምህርነት የምመራ ለፍልስፍና፣ ለሃይማኖት እና ለሳይንስ ልዩ ትኩረት የምሰጥ ወንድማችሁ ነኝ፡፡

ቸር ይግጠመን !!!

Created in Master PDF Editor

የመውጫ መልዕክት

ይህን መፅሐፍ በመገምገም የመጀመሪያ እኔ ነኝ። በተለይ ከስነ-ፅሁፋዊ ይዘቱ አንፃር ብዙ የሚተች ነው። በአማረኛ ስነ-ፅሁፍ እንዲህ አይነት ስነ-ፅሁፋዊ ህጎችን የሚጥስ መፅሐፍ አላጋጠመኝም። ምክንያቱም፦

- ✓ በምዕራፎች መካከል አለመመጣጠን አለ። አንዱ እጅግ ሲበዛ ሌለኛው እግጅ ያንሳል።
- ✓ በስነ ፅሁፍ ሀያሲያን የሚዘወተረው ቀጠይነት ወይም ኮንቲንቲ የሚባለው ነገር ተጥሷል።
- ✓ ለምን እንደሆነ ያለቦታቸው የገቡ ጽሁፎች አሉ። ያልተቋጩ ሃሳቦችም ቁጥር ሰፈር የላቸውም።
- ✓ የግድፈቶች ብዛት አማርኛ የአፉ መፍቻና የስራ ቋንቋው ከሆነ ጎልማሣ የማይጠበቅ ይመስላል።
- ✓ በእየቦታው የተሰነቀሩት የእንግሊዝኛ ቃላትና ትንተናዎች መጽሀፍ የተፃፈበትን ቋንቋ ለማወቅ አስቸጋሪ አድርጎታል።
- ✓ የመጽሃፉ አብዛኛው ሃሳቦች ከቤተ መጽሀፍትና ከጎግል የተወሰዱ ናቸው።
- ✓ መጽሀፍ የግል ምስክርነት፣ የሳይንሳዊ ምርምር ነው፣ የዳሰሳ ጥናት ወይስ የመጽሀፍት ቅኝት ለመለየት ይከብዳል።

ግን ለምን? መልሱን እንደሚከተለው ይቀርባል።

መፅሀፉን የፃፍኩት የስነ ጽሁፍ ሽልማት ላይ ለመታጨት አይደለም። በአንድ ነገር አምናለሁ ግጥም ቤት ቢመታም ባይመታም የሚፈልገው መልዕክቱ ነው። በእርግጥ ቤት መትቶ ግቡንም ቢመታ መልካም ነበር። ነገር ግን የቤት መምታት ጉዳይ ገጣሚያንን በማያስጨንቅበት ወቅት እኔ ስለ ፊደል መጣመም ስጨነቅ አልኖርም። ቋንቋ መግባቢያ ነው ለሚፈላስብበት ግን የፊደሎች ቅርፅ ሳይቀር ጥበብ ነው፣ ሳይንስ ነው። ለእኔና ለብዙዎች ግን ስነ-ጽሁፍ መልዕክት ማስተላለፊያ ቱቦ ወይም መስመር ነው። መጨነቅ ያለብን በመስመሩ ስለሚተላለፈው የመልዕክት ይዘት እንጅ ስለማስተላለፊያው ብዙ መጨነቅ ጊዜ ማባከን ነው። ቢሆንም ለሰራሁት ስነ-ጽሁፋዊ ስህተት ታዳሚዎችን ይቅርታ እየጠኩ ለቀጣይ ማሻሻል ላይ ባተኩር መልካም ይመስለኛል።በተረፈ ግን የፃፍኩትን ፃፍኩ ነበር ያለው ጲላጦስ።

Created in Master PDF Editor

ምንጮች

አማርኛ ዋቢ መፅሕፍት

1. መጽሐፍ ቅዱስ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር (አሳታሚ) 1980፤ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፥ መጀመሪያ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ፥
2. ቅዱስ ቁርዓን (አሳታሚው እና አመቱ አልተጠቀሰም)
3. ሃ/ጊዮርጊስ ማሞ (ጲላጦስ)፣ጥበብ ቅጽ አንድ፣ 2009፣
4. ሊቀ ካህናት ኃይለሥላሴ ዓለማየሁ፣ https://addisababa.eotc.org.et/am/
5. መ. ኃ. መስቀል (ዶ/ር)፣ ከምድራዊነታችን ባሻገር፣ ሦስተኛ መጽሐፍ 'ሳይንስ፥ እምነት፥ ሥልጣኔ - ማስታወሻና ማስተዋያ'
6. ሽብሩ ተድላ፣ የህያው ፈለግ፣ 2010 ዓ.ም፣ ኢትዮጵያ አካዳሚ ፕሬስ
7. መስከረም አበራ፣ የቀለምቀንድቅዕ 3 ቁጥር 11 መስከረም 22 2008
8. ማኅበረቅዱሳን፣ ሐመረ ኖኅ፣ ፳ኛ ዓመት ቁ.ጥር ፪
9. ማህበረ ቅዱሳን፣የገሃነብደጆች፣ 2011 3ኛዕትም
10. ምስጢሬን ላካፍላችሁ፣ስምዐጽድቅ፣ (2011) ቁጥር 1,2 እና 3 ኢ.ኦ.ተ. ቤ/ን ማህበረ ቅዱሳን
11. በኢትዮጵያ ባሃኢዎች ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባኤ የትርጉም ኮሚቴ፣ ባሃኦላህ እና አዲሱ ዘመን (ትርጉም)፣ 2008
12. በኢየሱስ እናምናለን፣ ትምህርትአምስት/JES5፣ ንጉሥ
13. በዕውቀቱ ስዩም፣ http://www.shegerblogs.com/author/Bewketu
14. በፍልስፍ ናመደመም፣ 2009 ዓ.ም፣
15. ብሩህ አለምህ፣ 2009፣ ፍልስፍና 2፣ 3ኛዕትም፣
16. ብሩህ አለምህ፣ 2010፣የኢትዮጵያፍልስፍና፣ 4ኛዕትም፣
17. ብሩህ አለምህ፣ 2010፣ፍልስፍና 1፣ 9ኛዕትም፣ግራፊክአታሚዎች
18. ተክለኪዳን፣የመጨረሻው ፍርድ አፈጻጸም ውሳኔ፣ 2ኛዕትም፣ 2009 ዓ.ም
19. ተክለኪዳን፣የጨለማው ገዥ ተግባርና ንግግር፣ 2009 ዓ.ም፣
20. ታላቅ ምክር ለአዲሱ ትውልድ (ጸሃፊው አልተረለጸም)
21. ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ፣ፍልስምና፣ቁጥር 2፣ 2004 ዓ.ም፣ HY Printing.
22. ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ፣ፍልስምና፣ቁጥር 3፣ 2005 ዓ.ም፣ HY Printing.
23. ትንሳኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት (አሳታሚ)፥ 1990፤ ፍትሐነገሥት ንባቡናትርጓሜው፥ ትንሳኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ።
24. ንቡረእድ ኤርሚያስ ከበደ፣ኢትዮጵያ የአለሙ መፍረጃ፣ 2011 ዓ.ም፣
25. አሌክስ አብርሃም፣ http://www.shegerblogs.com/author/alex/
26. አባጎርጎርዮስ፥ 1978፤የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፥ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ
27. አብርሃም ጎዝጊዜ፣የጽሃይም ልክቶች (ትርጉም)፣ 2009
28. አገኘሁአሰግድ፣ http://www.shegerblogs.com/author/agegnehu/
29. ዓሥራ ገብረማርያም፣ትምህርተ መለኮት፣ 3ተኛ ዕትም
30. እንዳለጌታ ከበደ፣ http://www.shegerblogs.com/author/endalegeta/
31. ዕዝራስነ-ጽሁፍ፣ (ዘላለም መንግሥቱ፣ እስላም እናክርስትና ንጽጽራዊ አቀራረብ ለዶ/ር ሙሀመድ ዓሊ የተሰጠ ምላሽ)

Created in Master PDF Editor

32. ካሳሁንደምሴ፣ 'የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ዐበይት ፈተናዎች ከቅድመ ንጉስ ኢዛና እስከ ዘመነ ኢህአዴግ' 2009
33. ወንጌል በድረ-ገፅአገልግሎት፣እውን እግዚአብሔር አለ?
34. ዋለል ኙእምሩ፣የህይወት ትርጉም፣ 2002 ዓ.ም፣ብራና ማተሚያ ድርጅት
35. ዘበነ ለማ (ዶ/ር)፣ ምንትኑ ውእቱ ሰብእ፣ 6ኛእትም፣ 2011 ዓ.ም
36. ሐሰን ሐትሁት፣ ሙስሊሙ ምን ያስባል? (ተርጓሚ ዘከሪያ መሐመድ)፣ 2011 ዓ.ል.
37. አህመዲን ጀበል፣ ክርስቶስ ማን ነው? 303 ወሳኝ ጥያቄዎች፣ 2001
38. የበፍቄዓለም፣https://befeqe.wordpress.com/
39. የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ን ቅዱስሲ ኖዶስ (2006 ዓ.ም) 'ሕገ ቤተክርስቲያን'
40. የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ን እምነትና ሥርዓተ አምልኮ
41. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን እምንት፣ ሥረዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት (ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1996)
42. የካንሳስ ደብረ ብርሃን ኪዳነ ምህረት፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤት መዝሙር ደብተር (2004 ዓ.ም)
43. ያህያ ኢብኑ ኑህ፣ ከ100 በላይ የመጽሀፍ ቅዱስ ግጭቶች ከመጠነኛ ማብራሪያ ጋር፣ ታህሳስ 2008
44. ደረጀ ፀጋዬ፣ የኢ-አማኒውኑዛዜ፣ addisadmassnews.com
45. ዳንኤል ክብረት፣ የቀለም ቀንድ ቅፅ 3 ቁጥር 11 መስከረም 22 2008
46. ጆንፓይፐር፣ ስለ ኢየሱስ የሚጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው፣ 2002ዓ.ም
47. ጎልጉል የድረ ገጽ ጋዜጣን፣ http://www.goolgule.com/
48. ፍኖተ ብርሃን፣ 10ኛዕትም 2009 ዓ.ም
49. <ከማመን መጠራጠር ይሻላል> የፌስ ቡክ ገጽ
50. ፕ/ር መስፍን ወልደማርያም፣ http://www.shegerblogs.com/author/mesfin/

Created in Master PDF Editor

Bibliography and Recommended Reading

1. Ali Sina, Debunking the Myth of Science in the Quran
2. Armin Navabi, Why There Is No God, Atheist Republic
3. Barker, Dan, Losing Faith in Faith: From Preacher to Atheist, Freedom from Religion Foundation, (1992)
4. Barker, Dan. Godless: How An Evangelical Preacher Became One of America's Leading Atheists. Ulysses Press, (2008).
5. Barker, Dan. Life driven purpose: how an atheist finds meaning ; foreword by Daniel C. Dennett. Pitchstone Publishing, (2015)
6. Bill Bryson, A Short History of Nearly Everything
7. Blackford, Russell and Udo Schüklenk, (Editors), 50 voices of disbelief: why we are atheists. Blackwell Publishing Ltd. (2009).
8. Bobby Henderson, The Gospel of Flying Spaghetti Monster
9. Carrier, Richard. On the Historicity of Jesus: Why We Might Have Reason for Doubt. (2014).
10. Carrier, Richard. Proving History: Bayes's Theorem and the Quest for the Historical Jesus. (2012)
11. Carrier, Richard. Sense & Goodness Without God: A Defense of Metaphysical Naturalism. Authorhouse, 2005.
12. Carrier, Richard. Sense and Goodness Without God: A Defense of Metaphysical Naturalism . (2005).
13. Carroll, S. M. 2016. The big picture: On the origins of life, meaning, and the universe itself. New York: Dutton.
14. Chaline, Eric. The Book of Gods and Goddesses: A Visual Directory of Ancient and Modern Deities.New York: Harper Entertainment, 2004.
15. Clifton D. Bryant, & Dennis L. Peck. (coeditors in chief), 21st century sociology: A reference handbook, (2007) by Sage Publications, Inc.
16. Collins, Francis, 2006, The Language of God: A Scientist Presents Evidence for Belief
17. Covell, Tim. Born Atheist.
18. Coyne, Jerry A. Why Evolution Is True: Oxford University Press. (2009)
19. Craig, William Lane. God? a debate between a Christian and an atheist / William Lane Craig, Walter Sinnott-Armstrong. (2014)
20. David Buss, Evolutionary Psychology, 4th ed. Pearson Education Limited, (2014)
21. Dawkins, Richard. The Blind Watchmaker: Why the Evidence of Evolution Reveals a Universe Without Design. W. W. Norton, 1986.
22. Dawkins, Richard. The God Delusion, (2006).
23. Dawkins, Richard. The Magic of Reality
24. Dennett, Daniel C. Breaking the Spell: Religion as a Natural Phenomenon. (2006).

Created in Master PDF Editor

25. Dennett, Daniel C. Darwin’s Dangerous Idea: Evolution and the Meanings of Life. (1995).
26. Drake, Alexander. The Invention of Religion: 2012 Smashwords Edition
27. Ellerbe, Helen. The Dark Side of Christian History. (1995).
28. Evald, Pierre. OSHO Source BOOK, A bio-bibliography 1931-1974 (2014)
29. Ferrell, Vance. The Evolution Cruncher
30. Grayling, A. C. Against All Gods: Six Polemics on Religion and an Essay on Kindness. (2007).
31. Guy P. Harrison, 50 Reasons People Give for Believing in a God.
32. Harris, Sam, Letter to a Christian Nation, (2007)
33. Harris, Sam. The End of Faith: Religion, Terror, and the Future of Reason. (2005).
34. Harun Yahya (Adnan Oktar), A Chain of Miracles
35. Haught, James. 2000 Years of Disbelief: Famous People with the Courage to Doubt.
36. Hawking, Stephen and Leonard Mlodinow. The Grand Design, (2010).
37. Hawking, Stephen Brief. Brief Answers to the Big Questions, 2018
38. Hitchens, Christopher. God Is Not Great: How Religion Poisons Everything. (2007).
39. Ibn Warraq, Why I Am Not a Muslim
40. Jerry A. Coyne, Faith versus fact: why science and religion are incompatible.
41. Konner, Joan. The Atheist's Bible: An Illustrious Collection of Irreverent Thoughts. (2007)
42. Krauss, Lawrence. A Universe From Nothing: Why Is There Something Rather Than Nothing (2012),
43. Lemuel K. Washburn (1911) Is the Bible Worth Reading and Other Essays. The Project Gutenberg EBook.
44. Loftus, John W. & Rauser, Randal (2013): God or Godless? One Atheist. One Christian. Twenty Controversial Questions.
45. Loftus, John W. (Ed.). The Christian Delusion: Why Faith Fails. (2010)
46. Loftus, John W. Why I Became an Atheist: A Former Preacher Rejects Christianity. Prometheus Books, (2012).
47. Love Letters from Grampa – about Life, Liberty, and the Zen of Zero, http://zenofzero.net/
48. Marshall Brain, How “God” Works: A Logical Inquiry on Faith By
49. Maurice Bucaille. The Bible, The Qur’an, and Science: The Holy Scriptures Examined in the Light of Modern Knowledge;
50. McAfee, David G. Disproving Christianity: Refuting the World's Most Followed Religion. (2010)
51. Michael Shermer, Skepticism 101: How to Think like a Scientist, The Teaching Company, 2013.

Created in Master PDF Editor

52. Mills, David. The Atheist Universe: The Thinking Person’s Answer to Christian Fundamentalism. Ulysses Press, 2006.
53. Myers, P. Z. The Happy Atheist. Pantheon, 2013.
54. National Academy of Sciences, Science, Evolution, and Creationism. http://www.nap.edu/catalog/11876.html
55. Noor, Abbas Abdul (2015), My Ordeal with the Qurʾān and Allah in the Qurʾān, Translated by Hassan Radwan
56. Onfray, Michel. In Defense of Atheism: The Case Against Christianity, Judaism and Islam. Penguin Canada, 2007.
57. Osho, God is Dead, Now Zen is the Only Living Truth,
58. Osho, I Celebrate Myself: God Is No Where, Life Is Now Here, English Discourse
59. Osho, The Golden Future, English Discourse series
60. Osho, The Great Pilgrimage: From Here to Here, English Discourse series
61. Osho, The Last Testament, Vol 1, English Discourse series
62. Osho, The Rebel, English Discourse series
63. Osho, Zarathustra: A God That Can Dance, Commentaries on Friedrich Nietzsche’s Thus Spoke Zarathustra, English Discourse series.
64. Paine, Thomas, The Age of Reason, New York: Dover Publications, 2004
65. Parnovsky, Serge & Aleksei Parnowski, How the Universe works an Introduction to modern Cosmology (2014)
66. Price, Robert M. The Christ-Myth Theory and Its Problems. (2011).
67. Rennie, John, 15 Answers to Creationist Nonsense.
68. Riaan Booysen, Barbelo -The Story of Jesus Christ
69. Robert Wright, The Evolution of God
70. Russell, Bertrand. Why I Am Not a Christian and Other Essays on Religion and Related Subjects (George Allen and Unwin, 1957; reprint, 2004).
71. Sagan, Carl, The Demon-Haunted World: Science as a Candle in the Dark, 1995
72. Shanks, Niall. God, the Devil, and Darwin: A Critique of Intelligent Design Theory. (2007)
73. Shermer, Michael. Why people believe weird things: pseudoscience, superstition, and other confusions of our time.
74. Smith, George E., Atheism: The Case Against God, Prometheus, 1979
75. Stenger, Victor, God: The Failed Hypothesis, (2007)
76. Steve Wells, The Skeptic’s Annotated Bible
77. Theobald, Douglas L. "29 Evidences Macroevolution: The Scientific Case for Common Descent." The Talk.Origins Archive.
78. Usama Hasan and Athar Osama (Editors): Muslim Responses to Science’s Big Questions Report of the İhsanoğlu Task Force on Islam & Science,
79. We Believe in Jesus By 3rd Millennium Ministries (በኢየሱስእናምናለንተከታታይመጽሃፍት፣ተርጓሚእሸቴበለጠ)

Created in Master PDF Editor

80. Worku Fekade, (2015) Religion and Its Impact upon the Realization of Human Actual and Potential Capacities, A Thesis Submitted to the School of Graduate Studies of Addis Ababa University in Partial Fulfillment of the Requirement For the Degree of Master of Arts in Philosophy.
81. Wright, Robert. ‘The Evolution of God’ (2009)
82. Yonas Zewde, (2015), The Compatibility of the Problem of Evil and The Existence of God, A Thesis Submitted to the School of Graduate Studies of Addis Ababa University in Partial Fulfillment of the Requirement For the Degree of Master of Arts in Philosophy.
83. Zakir Naik, Answer to Non-Muslims’ Common Questions About Islam
84. Zuckerman, Phil. "Atheism: Contemporary Rates and Patterns." The Cambridge Companion to Atheism, ed. Michael Martin፣ Cambridge: Cambridge University Press, (2005)

Created in Master PDF Editor

INTERNET REFERENCES

1. http://abenezerteklu.blogspot.com/
2. http://andadirgen.blogspot.com/
3. http://betelhemm.blogspot.com/
4. http://dekikenabute.blogspot.com/
5. http://eotcmk.org/a/
6. http://ethiopiathekingdomofgod.org/
7. http://semayawithought.com/theology.html
8. http://tesfalem7.blogspot.com/
9. http://www.atheistscholar.org/
10. http://www.chorra.net/
11. http://www.cyberethiopia.com/warka/
12. http://www.danielkibret.com/
13. http://www.ewnetlehulu.org/am/home/
14. http://www.goolgule.com/
15. http://www.islamicbulletin.org/Amharic/
16. http://www.saintmaryvancouver.org/index.htm
17. http://www.shegerblogs.com/
18. https://befeqe.wordpress.com/
19. https://d1.islamhouse.com/data/am/ih_articles/single/am_Eid_alfeter.pdf
20. https://ethioleul.wordpress.com/
21. https://ethiopiansite.com/
22. https://islamictrueth.wordpress.com/
23. https://jontambek.wordpress.com/
24. https://ru.tgchannels.org/
25. https://www.amharicbooksforunity.org/
26. https://teteyeq.wordpress.com/
27. https://wol.jw.org/am/wol/h/r93/lp-am
28. https://www.addisadmassnews.com/
29. https://www.gotquestions.org/Amharic
30. https://www.habeshastudent.com/
31. https://www.answering-islam.org/amargna.html
32. http://youth-mission.blogspot.com/
33. https://www.scientificamerican.com/article/15-answers-to-creationist/

Created in Master PDF Editor